# ታላቅ ርስት

## የኤፌሶን መልዕክት ማብራሪያ

ያሬድ ጥላሁን

For more books www.amharicchristianbooks.com

ታላቅ ርስት
የኤፌሶን መልዕክት ማብራሪያ
ያሬድ ጥላሁን © 2004 ዓ.ም

*ያለ ደራሲው ፈቃድ ይህን መጽሐፍ ወይም ማንኛውንም የመጽሐፉን ክፍል ለማባዛት፣ ለመገልበጥ፣ ለመቅረጽ፣ ወይም በሌላ መጽሐፍ በስፋት ለመጥቀስ አይቻልም፡፡ ሆኖም ግን ለጥናት፣ ለማስተማሪያነትና ለመሳሳሉት ዓላማዎች ማንኛውም ግለሰብ፣ ቡድን ወይም ድርጅት ከዚህ መጽሐፍ ለመጥቀስ ቢፈልግ የመጽሐፉን ስም፣ የደራሲውን ስምና መጽሐፉ የተጻፈበትን ዓ.ም. በመጥቀስ ለትርፍ ባልሆነ መልኩ ግልጋሎት ላይ ማዋል ይቻላል፡፡*

*በተለየ ሁኔታ ካልተጠቀሰ በቀር የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች የተወሰዱት በ1954 ዓ.ም. በኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ከታተመው የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ወይም በ1993 ዓ.ም. በኢንተርናሽናል መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ከታተመው አዲሱ መደበኛ ትርጉም ነው፡፡*

የሽፋን ዲዛይን፡ በረከት ታደሰ

አሳታሚ

*Golden Oil Ministries*
*Life Publishing*
*P.O.Box 18007*
*Addis Ababa, ETHIOPIA*

ኢ-ሜይል፡ talakerest@goldenoil.org

ድረ ገጽ፡ www.goldenoil.org



For more books www.amharicchristianbooks.com

**ለእናቴ ለወ/ሮ ጽጌ ወልደየስ**



For more books www.amharicchristianbooks.com

# □□□□ "□□□ □□□"

*ሐዋርያው ጳውሎስ በመንፈስ ቅዱስ ረድኤት በኤፌሶን መልዕክት ውስጥ በብዕሩ የሳለልንን "የታላቅ ርስት" ምሥጢር ወንድማችን ወንጌላዊ ያሬድ ጥላሁን በሚያስደንቅ ሁኔታ በመተንተን እነሆ! ለንባብ አብቅቶልናል። ያሬድ፣ እጅግ ግሩም በሆነ የሥነ-ጽሁፍ ውበትና ለዛ፣ ለጳውሎስና ለመልዕክቱ ታማኝ በመሆን፣ ከእግዚአብሔር የተቀበልነውን ታላቅ ርስት እንድናውቅ፣ በርስታችን ላይ እንድንመላለስ፣ እንዲሁም ርስታችንን ከመንፈሳዊ ጠላቶቻችን እንድንጠብቅ ከቡር ጥሪ አስተላልፎልናል። ይህን በዓይነቱ እጅግ ልዩ የሆነና በአማርኛ ቋንቋ እንደ ፋና ወጊ ተደርጎ ሊወሰድ የሚችለውን "ታላቅ ርስት" የተሰኘ የኤፌሶን መልዕክት ማብራሪያ፣ ለግልና ለቡድን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት፣ እንዲሁም በሥነ-መለኮት ትምህርት ቤቶች ውስጥ እንደ ዋና መማሪያ መጽሐፍ አድርገን እንድንገለገልበት በደስታ እጋብዛለሁ።*

***ፍሬው ታምራት***
***የኢቫንጀሊካል ቲዎሎጂካል ኮሌጅ፡ - ፕሪንሲፓል***

*ለወዳጄ ያሬድ፣ የተሰጠው ትጋት እጅግ ያስደንቀኛል። አሁንም ሌላ አዲስ መጽሐፍ እነሆ ይለናል!! ይህ የኤፌሶን መጽሐፍ ማብራሪያ የጥልቅ ጥናትና አገልግሎት ውጤት ብቻ ሳይሆን በላቀ ጥንቃቄ የተጻፈ ሆኖ አግኝቼዋለሁ። መልዕክቱ እጅግ ወቅታዊ ነው። ከምድር ጋር ብቻ የተጣበቀ "ወንጌል" በሚናፈስበት በዚህ ዘመን ታላቁን ሰማያዊ ርስት እንድናይ ቀና የሚያደርግ መለኮታዊ መልዕክት ይዟል። የሃሳብ ፍሰቱና ወጥነቱ ተነባቢ አድርጎታል። የኤፌሶንን መጽሐፍ ትርጉም ብቻ ሳይሆን ለአሁን ዘመን ያለውን ጠቀሜታም ያሳያል። ሁሉ ሰው እንዲያነበው እያበረታታሁ፤ ለእንደኔ ዓይነት የቃሉ መምህራን ግን አጋር መሣሪያ እናድርጋት እላለሁ። መልካም ንባብ!*

***ማሙሻ ፈንታ***
***በኮርኔል ዩኒቨርስቲ፤ ቦስተን የዶክቶራል ተማሪ***

*ያሬድ ጥሩ ሐታቴ ነው። ገላጭ፣ ተንታኝ፣ አብራሪ፤ ራሱን ምንባቡን ርስበርሱ አነጋግሮ፣ አወያይቶና አከራክሮ ውስጡ ያለውን እውነት ሊገባ በሚችል መንገድና ጣፋጭ ቃላት፣ መልዕክቱን በሚመጥን ቋንቋ፣ ፍንትው አድርጎ በመግለጥ የሚያሳይ አስተማሪ። የኤፌሶን መልዕክት ማብራሪያ የሆነውን ይህን መጽሐፍ ሳነብ፣ ከአንድ ደረጃውን የጠበቀ የመጽሐፍ ቅዱስ ማብራሪያ የምጠብቀውን ሁለት ዋና ዋና ነገሮች ባጥጋቢ ሁኔታ አግኝቻለሁ። አንደኛ፣ መልዕክቱ የተጻፈበትን አውድና ታሪካዊ ዳራ አስሶ፣ ኦርጅናል መልዕክቱን አብራርቶ ማሳየት ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ተግባራዊ ተዛምዶ ነው። ቃሉ በተወሰነ ዘመን በቦታ ለተከለሉ ተደራሲያን በቀጥታ የተጻፈ ቢሆንም መልዕክቱ ግን ዘመን ተሻጋሪ፣ ለአሁኑም ትውልድ ያኔ እንዳደረገው ሁሉ አንባቢውን ሊያስተምር፣ ሊመክር፣ ሊወቅስ፣ ሊያበረታና ለበጎ ሥራ ሊያነሳሳ መቻሉን አሳይቶናል። ያሬድ ይህንን ክፍል ከሃተታው ጋር አዋህዶ፣ ድርና ማጉን ፈትሎ፣ ማራኪ በሆነ መንገድ አስቀምጦታል። በሌላ በኩል ደግሞ የመጽሐፉን ወጥነትና ትስስራዊነት እጅግ አድንቂያለሁ። "ታላቅ ርስት"ን ሰው ሁሉ*



For more books www.amharicchristianbooks.com

*ያንብበው፤ የርስት ነገር ነውና! ለዚያውም የዘላለማዊ ርስት ጉዳይ! ያነበበው ሁሉ ደግሞ ብርሃን ይሁንለት! የቃሉ ፍቺ ያበራልና፡፡ (መዝ. 119፡130)*

***እንዳልካቸው ሣህሌ (መጋቢ)***
***የኢትዮጵያ ወንጌላዊያን ቤተ-ክርስቲያን፡ - ፊላደልፊያ***

*መንፈሳዊ ሃብት የታመቀባትን የኤፌሶንን መልዕክት ይዘት ፍንትው አድርጎ የሚያሳይ ግሩም ኮሜንታሪ!! የገባንበትን የሕይወት ርስት ክብር አጥርተን እንድናይ የሚያደርግ ድንቅ ሥራ!! "ታላቅ ርስት" ስለ ተስፋ፣ ስለ ዘላለማዊ ሕይወትና ስለ በረከት የሚያምታቱንን ከቃሉ ያፈነገጡ ሐሳቦች በብርቱ የሚበረብርና መጣል ያለብንን እንድንጥል፣ መያዝ ያለብንን በአግባቡ እንድንይዝ የሚያደርግ መጽሐፍ ነው፡፡ ከቅዱሳን ሁሉ፣ ይልቁንም ከአገልጋዮች እጅ እንዳትለይ እመክራለሁ፡፡*

***መጋቢ አብይ ኢሳያስ***
***የጸጋው ቃል አማኞች ቤተ-ክርስቲያን ፤ ኑረምበርግ፣ ጀርመን***

*አንዳንዶች ከሐዋርያው ጳውሎስ መልእክቶች ሁሉ "እጅግ የላቀው" ይሉታል፤ የኤፌሶንን መልእክት፡፡ መልእክቶች ሁሉ የተጻፉበት የየራሳቸው ዓላማ ስላላቸው, አንዱን ከሌላው ማነጻጸር አስፈላጊ ላይሆን ይችላል፣ ይሁን እንጂ እያንዳንዱ አማኝ በክርስቶስ ያለውን ማንነት እና ከዚያም ማንነቱ የተነሣ የሚቋደሳቸውን መንፈሳዊ በረከቶች በዝርዝር በማሳየት ረገድ በእውነትም የኤፌሶንን መጽሐፍ የሚያክል የለም፡፡ ወንጌላዊ ያሬድ በዚህች መጽሐፉ ይህንን የከበረ መልዕክት የበለጠ እንድገነዘበው ረድቶኛል፡፡*

***በቀለ ወልደ ኪዳን (መጋቢ)***
***ኢትዮጵያ ሙሉ ወንጌል ቤተ-ክርስቲያን፤ አዲስ አበባ***

*ያሬድ፣ የሚጽፍ አስተማሪና የሚያስተምር ጸሐፊ ነው። ይህ ደግሞ በአገልግሎት ቆይታው እየጎለበተ ሲመጣ አይቼዋለሁ። ለዚህም ይህ የኤፌሶን መልእክት ማብራሪያ ቅርጽና ይዘት ምስክር ይሆናል። የተረዱትን ከደጀ ሰላሙ ምስባክ ባሻገር በወረቀት ላይ ማኸይወት ረጅም ጉዞ ነው፤ ያሬድ ይህን ጉዞ ደጋግሞ ተጓዘ።  በሥላሴ ተመሥርታ እንደ ርስት የተለየችው የክርስቶስ አካል - አብ ያቀዳት፣ በልጁ ደም የተገዛችና በመንፈስ ቅዱስ የታተመች ስለ ሆነች የጠራትን የክብር አባት፣ የተጠራችበትን ተስፋና ኃይል፣ ከነውጤቱ ልታውቅ ይገባታል (ኤፌ1፡1 – 23) የሚለውን ሐዋርያዊ አዋጅ ያሬድ በዚህ መጽሐፍ ዳግም መለፈፍ አለበት እያለን ነው። ይህ ማብራሪያ ወሳኝ በሆኑ ቁልፍ ቃላት ላይ በማተኮርም ሐዋሪያው ጳውሎስ በኤፌሶን ይኖሩ ለነበሩት የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት የጻፈውን መልእክት የኛ ያደርግዋል፣ ይሄኔ ነው አሜን ማለት!*

***ሰሎሞን ጥላሁን***
***በሬጀንት ዩኒቨርስቲ፣ ዌስት ቨርጂኒያ የዶክቶራል ተማሪ***



For more books www.amharicchristianbooks.com

# ምሥጋና

ከሁሉ አስቀድሜ አምልኮአዊ ምሥጋናዬን በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ቅዱስ መንፈሱን ለሰጠኝ ለአብ አቀርባለሁ፡፡ በማይጠቅሙት መጠቀም ልማዱ የሆነው ጌታ በእኔ ትንሽ አዕምሮና ብዕር ቅዱስ ቃሉን ለማብራራት ስለወደደ ልቤ ደስታዬን ለመደበቅ አቅም ያንሳታል፡፡ ይህን ያደረገው እርሱው ራሱ በእኔ ሠርቶ ሲያበቃ መልሶ እኔኑ ሊያከብረኝ ሰበብ ፈልጎ እንጂ አንዳች የሚጠቅም ነገር ኖሮኝ እንዳይደለ ልቤ ያውቀዋል፡፡ ታዲያ ለእርሱ ምን ይከፈላል? በሕይወቴ ዘመን ሁሉ አምልኮአዊ ምሥጋናዬ ይድረሰው፡፡

በመቀጠል አክብሮታዊ ምሥጋናዬን በሕይወቴና በአገለግሎቴ አሁን የደረስኩበት ለመድረስ በተለያየ መንገድ አስተዋፅኦ ላደረጉ ወገኖቼ አቀርባለሁ፡፡ ዳሩ ግን ገና ለመጻፍ ብዕሬን ሳሾል ወፈ-ሰማይ ስሞች በላዬ ያንዣብባሉ፡፡ በ25 አመታት የእምነት ጉዞዬ፣ በ22 አመታት የአገለግሎት ሩጫዬ በልባቸው ፍቅር፣ በአንደበታቸው ምክር፣ በፊታቸው ገፅታ፣ በእጃቸው ሥጦታ የባረኩኝ ሰዎች ሰብዕና እንደ ወንዝ በአይነ ሕሊናዬ ይፈሳል፡፡ እናም  የእያንዳንዱን ሥም በዚህች ትንሽ መደብ ማስፈር ባልችልም እንኳ፣ አንኳር አንኳሩን ዘግኜ ላቅርብ፡፡

ወልደው ያሳደጉኝ ወላጆቼ፣ አብሬያቸው ለማደግ የታደልኩት እህቶቼና ወንድሞቼ፣ በተለይም ባለፈው ዓመት 70ኛ ዓመት የልደት በዓሏን ላከበረችው ለእናቴ ለወ/ሮ ጽጌ ወልደየስ (አባይዬ) ምሥጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

እግዚአብሔር ባለቤቴን ምኞቴን የሰጠኝ ሌጣዋን አልነበረም፣ ከእርሷ ጋር የማይጠገብ ቤተሰብ ይልቁኑም ዘወትር ለሕይወቴና ለአገልግሎቴ ደጀን የሆኑትን ኮ/ል ክፍሌ ሥዩም (አባቢ)፣ ወ/ሮ ዘለቃ በቀለ (ቃቂ)ን ሰጥቶኛል፡፡ ስለ እነርሱ በጎነት ለመዘከር ሌላ  መጽሐፍ መጻፍ ይኖርብኝ ይሆን?

ያለፈው አመት በጌታ እጅግ የምወዳትን እህቴን በአፀደ-ሥጋ ያጣሁበት ዓመት ነበር፡፡ የሽቱትጋርቷ ልቅም ወርቅ መክብብ  ከተዋወቅንበት ከ 1999 ዓ.ም (እ.ኤ.አ) አንስቶ ለእኔ፣ ለቤተሰቤና ለአገልግሎቴ ድንቅ እናት ነበረች፡፡ ልቅም በጌታ ቀን ላይሽ እናፍቃለሁ፡፡

ጎልደን አይል ሚኒስትሪን በአሜሪካ ከመመሥረት አንስቶ በበርካታ ጉዳዮች በጊዜውም አለጊዜውም ከጎኔ የቆሙት የአከላሆማዎቹ ዶ/ር ቢንያም ባይሳ እና  ጤናዬ ኃይሉ ከመላው ቤተሰባችሁ ጋር ስላሳያችሁኝ ፍቅር ምሥጋናዬ የላቀ ነው፡፡

ላለፉት ሦስት ዓመታት ዘወትር እሁድ  ከሰአት በኋላ አያት የመኖሪያ መንደር



For more books www.amharicchristianbooks.com

በሚገኘው ቤታችን እየተሰበሰብን የጌታን ቃል ስናጠናና ስናመልክ አብረውን የክርስቶስን ሕይወት ለተካፈሉት ወንድሞችና እህቶች በተለይም ካገኘሁት ቀን አንስቶ ባሳለፍናቸው ጊዜያት ሁሉ ከአፉ የፀጋ ቃል አጥቼ የማላውቀው ወንድሜ በረከት ዮሴፍ ምሥጋናዬ ይድረሳችሁ፡፡

የዚህን መጽሐፍ የመጀመሪያ ቅጂ በማንበብ ጠቃሚ ምክራቸውን የለገሱኝን መጋቢ በቀለ ወልደ ኪዳን፣ የፊላደልፊያው መጋቢ እንዳልካቸው ሳህሌ፣ የኢቫንጀሊካል ቲዎሎጂካል ኮሌጅ ፕሪንሲፓል ወንድም ፍሬው ታምራት፣ የፖፒሌሽን ሚዲያው ዶ/ር ንጉሴ ተፈራ፣ ገጣሚው ወንድሜ ደረጄ በላይነህ፣ በአሜሪካ ዶክትሬቱን የሚሠራው ሰለሞን ጥላሁን፣ የጥንት ወዳጄ የሲያትሉ ሲሳይ ደሳለኝ፣ ወንድም ማሙሻ ፈንታ፤ የኑረምበርጉ መጋቢ አብይ ኢሳያስ፣ ወንድም ንጉሴ ቡልቻ፣ እንዲሁም ሆሄያቱን የለቀሙት መቶ አለቃ ኃይሉ አበበ፣ ኢያሱ ደምሴ፣ ሀዲስ አለማየሁ፣ ዳዊት ካሣ እግዚአብሔር በዚህ መጽሐፍ በተጻፈው በረከት ሁሉ ይባርካችሁ ማለት እወዳለሁ፡፡

የመውለጃ ወሯ ገብቶ "ልጄና ይህች መጽሐፍ አብረው ይወለዳሉ!" በሚል እልህ በድርስ አቅሟ የመጀመሪያውን የእጅ ጽሁፌን በኮምፒውተር የተየበችው ውድ እህቴ ሩት መንድም አገኝ ጌታ አንቺንም ልጅሽንም ይባርክ ከማለት ውጪ ምን እላለሁ? በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አቅጣጫ ልቤን ያሳረፈውና የዚህንም መጽሐፍ የገጽ ሽፋን ያዘጋጀው ወንድሜ በረከት ታደሰ የጌታ በረከት ይብዛለት፡፡ መጽሐፍ በጻፍኩ ቁጥር አንብቦ አስተያየት መስጠትና ቅርፁን በኮምፒውተር መልክ፣ መልክ ማስያዝ የማይታክተው ወንድሜ ተወልደ መኮንን እግዚአብሔር አብዝቶ ይባርከው፡፡

ለእግዚአብሔር ቃል ባላቸው ጥማትና አክብሮት ሁሌም የሚያስደምሙኝ የኢትዮጲያ አየር መንገድ የክርስቲያን የበረራ ሠራተኞች ሕብረት እህቶቼ ስለ ድንቅ መሰጠታችሁ ሳላመሰግናችሁ ማለፍ አልችልም፡፡

ስማችሁን እዚህ መዘርዘር የማልችል፣ ለዚህ መጽሐፍ መታተምና አንባቢያን እጅ መድረስ የተለያየ አስተዋጽኦ ያደረጋችሁ የጎልደን አይል አገልግሎት ተባባሪዎች ሁሉ የከበረ ምሥጋና ይድረሳችሁ፡፡

በመጨረሻ ነገር ግን ከሁሉ በላቀ መልኩ አክብሮታዊ ምሥጋናዬን የማቀርበው ለውድ ባለቤቴ ለምኞቴ ክፍሌ ነው፡፡ ያላንቺ ድጋፍ አገልግሎቴ ፍሬ ሊኖረው አይችልም ነበር፡፡ ማሬ፣ ከልቤ እወድሻለሁ!



For more books www.amharicchristianbooks.com

# ማውጫ


**መቅድም ........................................................................................ XI**

**መግቢያ ........................................................................................ 1**

መወድሰ መልዕክተ ኤፌሶን ........................................................ 1
የመልዕክቱ ጸሐፊ ........................................................................ 2
የመልዕክቱ የመጀመሪያ ተደራሲያን ........................................... 3
የኤፌሶንና የቆላስያስ መልዕክቶች ትስስር .................................... 7
የእሥር ቤት ደብዳቤ .................................................................... 9
የመልዕክቱ ትኩረት ....................................................................12
ሰላምታ ለተደራሲያን .................................................................16

**ክፍል አንድ፡ ርስትን ማወቅ .......................................................19**

መግቢያ .......................................................................................19

**ምዕራፍ ፩ ምስጋና .....................................................................22**

ዶሎጊያ .......................................................................................23
በረከት..........................................................................................25
በረከትና የተስፋ ቃል....................................................................27
የርስት በረከት ..............................................................................30
ለርስት መመረጥ ..........................................................................37
ወራሽ ልጆች.................................................................................40
ለርስት መዋጀት............................................................................43
ለርስቱ የሆነ መገለጥ ...................................................................44
ርስትን መቀበል ...........................................................................48
እኛና እናንተ ..............................................................................48
ርስታችን .....................................................................................51
የመውረስ ሂደት...........................................................................54
ለክብሩ ምስጋና ...........................................................................56

**ምዕራፍ ፪ ልመና .......................................................................59**

የመዳን ማረጋገጫ ........................................................................62
የጥበብና የመገለጥ መንፈስ............................................................63
ታውቋ ዘንድ.................................................................................68
የኃይል ታላቅነት .........................................................................73

**ምዕራፍ ፫ ያኔና አሁን ...............................................................79**




For more books www.amharicchristianbooks.com

ያኔ...81
አሁን...84
የሁለት ዓለም ንጽጽር ...87

**ምዕራፍ ፬ አብሮ መግባት...89**

ሰላማችን ኢየሱስ ...94

**ምዕራፍ ፭ የተገለጠ ምሥጢር...105**

የምስጢሩ ምንነት ...107
የመገለጥ ሠንሰለት...109
ምልጃ...112
ቡራኬ ...120

**ክፍል ሁለት በርስት ላይ መመላለስ...123**

መግቢያ ...123

**ምዕራፍ ፮ የመንፈስ አንድነትን መጠበቅ...128**

የመንፈስን አንድነት መጠበቂያ ባሕሪያት ...130
"ፍፁም አንድነት" ፡ - ሰባቱ የአንድነት ምሰሶዎች ...133
በልዩነት አንድነት ...141
የአገልግሎት ሥጦታዎች...145
የእውነተኛ አገልግሎት ፍሬ ...147

**ምዕራፍ ፯ በአዲስነት መመላለስ...150**

ከውሸት ወደ እውነት...153
ከቁጣ ወደ ይቅርታ ...154
ከሥርቆት ወደ ማካፈል...156
ከክፉ ቃል ወደ በጎ ቃል...156
መንፈስ ቅዱስን አታሳዝኑ ...157
ከመራርነት ወደ ርህሩህነት...159
በፍቅር መመላለስ ...161

**ምዕራፍ ፰ በቅድስናና በብርሃን መመላለስ ...163**

**ምዕራፍ ፱ በጥበብ መመላለስ...173**

**ምዕራፍ ፲ ክርስቲያናዊ የቤተሰብ ግንኙነት...180**

ባልና ሚስት ...187
ወላጆችና ልጆች...192
ጌቶችና ባሮች (አሠሪና ሠራተኛ) ...197

**ምዕራፍ ፲፩ መልካሙን የእምነት ገድል መጋደል...202**



For more books www.amharicchristianbooks.com

# መቅድም

በአገራችን "መጽሐፍ በጉንጭ" ነው! ታሪክ በአፍ ይተረካል፤ ዕውቀትም በቃል ይነገራል እንጂ በጽሑፍ ለትውልድ ማስተላለፍ እምብዛም አይደለም ። ታዲያ ይህ ዓይነቱ ልማድ በተቆራኘው ሕብረተሰብ ውስጥ ተወልዶ ላደገ ሰው ከመጻፍ ይልቅ በማናገር ብቻ ዘመንን ለመፈፀም እያጣደፈ፣ እየጠበበና ፍጥነቱን እየጨመረ የሚሄደው የአዙሪት ስበት አይጣል ነው! ሆኖም በሌላ ወገን ማዕበሉን ተቃርኖ ለመዋኘት የሚያግዙ መሰዕቦች አይጠፉም። በቅርቡ ጆሮዬ የገባው አንድ እውነታ በምሳሌነት ለመጠቀስ የሚበቃ ነው። በውጭው ዓለም በአዲስ ኪዳን መጽሐፍቶች ላይ፣ ለዚያውም በጳውሎስ መልዕክቶች ላይ ብቻ የተጻፉ መጽሐፍት ሌላ ሳይጨመርባቸው አንድ ግዙፍ ቤተ-መጻሕፍት እንደሚሞሉ ስሰማና በዚያው ቅፅበት ወደ አገራችን ክርስቲያናዊ ሥነ-ጽሁፍ ዘወር ስል የታየኝ ልዩነት የብዕር ያለ!! ያሰኛል።

ይህን መጽሐፍ ካጠናቀቅሁ በኋላ ሁለት ተቃራኒ ስሜቶች ተሟግተውኛል። አንደኛው፣ የኤፌሶንን መልዕክት ዳግም ባነበብኩ ቁጥር ፊቴ ድቅን የሚልብኝ "ይህን ታላቅ መዕክት ማብራራትህን መጨረስ ይቅርና፣ መች በቅጡ ጀመርከው?" የሚል ወደ ዕትመት እንዳልሄድ የሚያቅበኝ ስሜት ሲሆን፤ ሁለተኛው "እንዲህ እንዳለ፣ አንባቢያን ዘንድ ቢደርስ እንኳ ለአሁኑም፣ ለወደፊቱም ትውልድ ይጠቅማል!" በሚል ወደ ፊት የሚያንደረድረኝ ስሜት ናቸው። ሆኖም ሁለተኛው ስሜቴ ስላየለ፣ አንደኛውን አባብዬ እነሆ "ታላቅ ርስት" እርስዎ እጅ ልትደርስ ችላለች።

ባሳለፍኳቸው 22 የአገልግሎት ዘመናት የኤፌሶንን መልዕክት አንዳንዴ በወፍ በረር፣ አንዳንዴም በጥልቀት የማስተማሩን ዕድል አግኝቻለሁ። ከእነዚህም ውስጥ በ 1989 ዓ.ም በቀጠና ሁለት ሙሉ ወንጌል፣ በ 1994 ዓ.ም በተለምዶ "ቺካጎ ኮንፈረንስ" ተብሎ በሚጠራው የሰሜን አሜሪካ ወንጌላዊያን ክርስቲያኖች ማሕበር እ.ኤ.አ በ 2002 በዴንቨር - ኮሎራዶ ባዘጋጀው ስብሰባ ላይ፣ ከ 8 ዓመታት ቆይታ በኋላ በኢትዮጵያ አቆጣጠር በ 2002 ዓ.ም በወንጌል ብርሐን ቤተ-ክርስቲያን፣ እንዲሁም እየጻፍኩት በነበረበት በ 2004 ዓ.ም መግቢያ በቀጠና ሁለት ሙሉ ወንጌል የወጣቶች ስብሰባ ላይ ያስተማርኩትን አልረሳውም። ባስተማርኩት ቁጥር ተምሬዋለሁና! በዚህ አጋጣሚ ይህን መጽሐፍ በመድረካቸው ለማስተማር ዕድል የሰጡኝን አብያተ-ክርስቲያናትና በጥሞና የተከታተሉኝን ምዕመናን ጌታ ይባርካችሁ ማለት እወዳለሁ።

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ብዕረ-መንገዴን ትምህርተ-ሥላሴን፣ ክርስቲያናዊ ተስፋን፣ የዘላለም ሕይወትን የመሳሰሉ በክርስትና እምነት ውስጥ መሰረታዊያን የሆኑ ዐብይ



For more books www.amharicchristianbooks.com

ርዕሰ ጉዳዮችን አንስቻለሁ፡፡ እነዚህ አንኳር ርዕሶች በራሳቸው፣ ለየብቻቸው በጥልቀት ሊታዩ እንዲገባ ባውቅም ከመልዕክቱ ይዘት አኳያ በመጠኑም ቢሆን ሳላነሳቸው ማለፍ አልቻልኩም፡፡ በአንፃሩም በጥልቀት እንዳልሄድባቸው በመልዕክቱ አውድ ተወስኛለሁ፡፡ አንባብያን ይህንን ውሱንነት እንዲረዱልኝና እነዚህን ርዕሰ ጉዳዮች በተመለከተ እንደኔ በአውዱ ተወስነው እንዲያይዋቸው እማፀናለሁ፡፡

ይህ መጽሐፍ በሁለት ዓይነት አንባቢያን፣ በተለያየ መልኩ ሊነበብ ይችላል፡፡ አንደኛው፤ እንደ ጥሞና መጽሐፍ በጥቅሶችና በግርጌ የማብራሪያ ሐተታዎች ሳይደናቀፉ ማንበብ ለሚሹ የሚመች ሲሆን፤ ሁለተኛው እያንዳንዱን ተዛማጅ ጥቅሶች በማየት፣ ከሌሎችም ዋቤ መጽሐፍት ጋር በማመሳከር በጥልቀት ማጥናት ለሚፈልጉ የቃሉ ተማሪዎች የሚያገለግል ነው፡፡

ሌላው በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ከጠቀስኳቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች መካከል በአንዳንዶቹ ላይ ያዘሉት ሐሳብ ከክፍሉ ጋር ያለውን ተዛማጅነት አጉልቼ ለማሳየት ስል፤ ከሥራቸው የማስመር፣ የማድመቅና ቅርፃቸውን የመለወጥ (underline, bold, italics) ድርጊት ፈፅሜያለሁ፡፡ ሆኖም እነዚህ አጽንኦቶች የእኔ እንጂ መጽሐፍ ቅዱስ ላይ የሌሉ መሆናቸውን አንባብያን እንዲረዱልኝ እፈልጋለሁ፡፡

በአጸደ-ሥጋ እያለሁ የክርስቶስ ሙሽራ ለሆነችው ክብርት ቤተ-ክርስቲያን በጽሑፍ ላበረክታቸው ከምመኛቸው ገፀ-በረከቶች መካከል አንዱ የሆነውን የኤፌሶንን መልዕክት ማብራሪያ እነሆ፡ - ብያለሁ፡፡ ሆኖም ይህን መጽሐፍ ወደ አንባቢያን ዘንድ የምልከው ሌጣውን አይደለም፤ የዘላለም ርስቱ ያደረገን፣ እርሱም ራሱ ርስታችን የሆነልን ቅዱስ እግዚአብሔር፣ ለሚያነቡት ሁሉ የርስቱን ክብር ባለጠግነት ያውቁ ዘንድ የልቦና ዓይናቸውን የሚያበራ የጥበብና የመገለጥ መንፈስ እንዲሰጥ ከመማለድና ከልብ ቃተቶ ጋር ነው፡፡

ያሬድ ጥላሁን<br>ወርኃ ሰኔ 2004 ዓ.ም<br>አዲስ አበባ



For more books www.amharicchristianbooks.com

# መግቢያ

## መወድሰ መልዕክተ ኤፌሶን

የኤፌሶን መልዕክት ባለፉት 2000 ዓመታት የክርስትና ታሪክ ውስጥ የነበረውን ጉልህ ድርሻ አንድ ባንድ ለመዘርዘር፣ በፊደል ለመቅረፅና በቃላት ለመግለፅ መሞከር አባይን በጭልፋ ይሆናል፡፡ በዘመናት ውስጥ ይህን መልዕክት በማንበብ ብዙዎች ወደ ጌታ መጥተዋል፣ ብዙዎች ተለውጠዋል፣ ብዙዎች ለአገልግሎት ተለይተዋል፡፡ መልዕክቱ አስቀድሞ በእጃቸው ከገባው ከአንደኛው ክፍለ ዘመን አንባቢዎች አንስቶ እስካለንበት ሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን ድረስ በተለያየ ደረጃ ያሉ የተለያዩ ሰዎች ስለ መልዕክቱ ብዙ ብለዋል፡፡ ሁሉን በፊደል ለማስፈር የማይቻል ቢሆንም እንኳ ጥቂቶቹን ለአብነት እናንሳ፡፡ ታዋቂው ዊሊያም ባርክሌይ የሳሙኤል ቴይለርን ጽሁፍ ዋቢ በማድረግ የኤፌሶንን መልዕክት "የመልዕክቶች ሁሉ ንግስት" በማለት ጽፏል፡፡[1] ታዋቂው የአዲስ ኪዳን ምሁር ኤፍ. ኤፍ ብሩስ ደግሞ "የጳውሎሳዊነት መገለጫ አካል"[2] ብሎታል፡፡ አርሚቴጅ ሮቢንሰን እና ሲ ኤች ዶድ በተመሳሳይ መልኩ "የጳውሎስ መልዕክቶች ሁሉ አክሊል"[3] ሲሉ፣ ዊሊያም ሄንድሪክሰን በበኩሉ "በሰው እጅ የተፃፈ መለኮታዊ ውቅር" "የጠለለና የጠራ የክርስትና እምነት ገጽታ" "ፍጹም ባለሥልጣን የሆነና የተሟላ የክርስትና እምነት የዕውቀት ምጥን" "መንፈስ ቀስቃሽ ሃሳቦች እስከ አንገቱ ድረስ ጢም ያሉበት ሕያው መልዕክት" በማለት ስለ ኤፌሶን መጽሐፍ ያለውን አድናቆት ለመግለፅ ስንኝ ቋጥሯል፡፡[4] እነዚህን የአድናቆት መግለጫዎች ብቻ እንኳን ብንወስድ ስማቸው ከላይ የሰፈረው ታላላቅ የእግዚአብሔር ሰዎች በረዥም የሕይወትና የአገልግሎት ዘመናቸው ከመልዕክቱ በሚፈልቀው የሕይወት ብርሃን ምን ያህል እንደተነኩ መረዳት እንችላለን፡፡

እውነትም የኤፌሶን መልዕክት በቃላት የተዋቀረ ሥነ ጽሁፋዊ እንቁ ነው፣ ተዝቀው የማያልቁ የወርቅ ቡችሎች (golden naggets) የሞሉበት መንፈሳዊ የማዕድን ስፍራ ነው፡፡ ይህንን መልዕክት እያነበቡ በእግዚአብሔር ሐሳብ አለመደነቅ፤

[1] Sttot, John R W Ephesians P. 15

[2] As cited by F. F. Bruce in The Epistles To The Colossians, To Philemon, and To the Ephesians (Grand Rapids, William B. Eerdmans Publishing Company, 1984), p. 229

3 Ibid (ዝኒ ከማሁ)

[4] William Hendriksen, Exposition of Ephesians (Grand Rapids: Baker Book House, 1967), p. 32



For more books www.amharicchristianbooks.com

በፍቅሩ አለመመሰጥ፤ ለታላቅነቱ አለመስገድ አይቻልም፡፡ መልዕክቱ ከተጻፈ ሁለት ሺ አመት የተጠጋው ቢሆንም ለየትውልዱ፣ ይልቁንም ለምንኖርበት ለዛሬው ዘመን ይህ ነው የማይባል ፋይዳ አዝሏል፡፡ ልዩነት በበዛበት አንድነትን፣ ጠብ ባየለበት ሰላምን፣ ጥላቻ በነገሰበት ፍቅርን፣ ግራ መጋባት በሰፈነበት የዘላለምን ራዕይ እያበራ ደምቆ ይኖራል፡፡

እንግዲህ ይህንን ታላቅ መልዕክት በጽሞናዊ ማብራሪያ ዘልቀን ማየት ከመጀመራችን በፊት የመልዕክቱን ጸሐፊ፣ የመጀመሪያዎቹን ተደራሲያን፣ የተጻፈበትን ዓላማና መሰል ጉዳዮችን በቅድሚያ መዳሰስ ይኖርብናልና ወደዚያው እናቅና፡፡

## የመልዕክቱ ጸሐፊ

ምንም እንኳ ስለ ኤፌሶን መልዕክት ይህንን ያህል ብንልም ወደ ጸሐፊውና ወደ ተደራሲያኑ ማንነት ስንመጣ ከሌሎቹ የአዲስ ኪዳን መልዕክቶች በተለየ መልኩ ለልዩ ልዩ መላምቶችና ክርክሮች የተጋለጠ መሆኑን ሳናነሳ ማለፍ አንችልም፡፡ የመልዕክቱ ጸሐፊ ሐዋርያው ጳውሎስ ስለመሆኑ ኤፍ ሲ ባወር የተሰኘ የሥነ መለኮትና የቋንቋ ሊቅ ጥያቄ እስካስነሳበት 1847 ድረስ ለአሥራ ስምንት ምዕተ ዓመታት ያለአንዳች ጥያቄ ቅቡል ሆኖ ኖሯል፣ ፡፡ ይህ ሰው ያነሳቸው የቋንቋ፣ የአፃፃፍ ስልት፣ የሥነ መለኮትና የግንኙነት ጥያቄዎች ከእርሱ በኋላ የሚሰለፉ ደጋፊዎች አላሳጣውም፡፡ ከእነዚህም መካከል አንዱና ዋነኛው አሜሪካዊው ምሁር ኢ ጄ ጉድ ስፒድ ነው፡፡ እነዚህ ምሁራን ከሚሟገቱባቸው የራሳቸው ምክንያቶች የተነሳ መልዕክቱ በጳውሎስ እጅ አለመጻፉን ሽንጣቸውን ገትረው ይከራከራሉ፡፡ እነዚህ የሥነ ጽሁፍ ሃያሲያን ለህትመት ባበቋቸው መጻህፍት ውስጥ "ጸሐፊው" እንጂ አምልጧቸው እንኳ "ጳውሎስ" አይሉም፡፡[5] እነዚህ ዘመናዊ የሥነ መለኮት ሊቃውንት "በጳውሎስ ዘመን የነበረ ከእርሱ ሥር የተማረ አንድ ደቀ መዝሙሩ በጳውሎስ ስም ጽፎት ይሆናል ወይም ጳውሎስ ካለፈ በኋላ የቆላስያስን መልዕክት በማንበብ የተመሰጡ ተከታዮቹ ጽፈውት ይሆናል" በማለት መላ ይመታሉ፡፡ አንዳንዴም "አናሲሞስ" ሊሆን ይችላል ወይም የኤፌሶን ቤተክርስቲያን ቢሾፕ የነበረው ፖሊካርፕ ሊሆን ይችላል በማለት መላምታቸውን ሥጋ ሊያለብሱት ይሞክራሉ፡፡

እነዚህ ሊቃውንት የሚያነሷቸው ነጥቦች በንቀት ሊታለፉ የማይችሉ አንዳንዴም

[5] World Bible Commentary, Ephesians.



For more books www.amharicchristianbooks.com

ሚዛን የሚደፉ ይመስላሉ፡፡ ሆኖም የእነርሱን አመክንዮና የክርክር ሃሳብ ስናወጣ ስናወርድ ፍሬ ነገሩን እንዳንጥል ይህን መሰል ጉዳይ መጽሐፉን ከዚህ በተሻለ ጥልቀት ለሚያጠኑ መርማሪዎች ትተን፤ ወደ ፍሬ ነገሩ ለመዝለቅ ግድ ይለናል፡፡ የምንዘልቀውም የኤፌሶንን መልዕክት ሐዋርያው ጳውሎስ ጽፎታል የሚለውን ጽኑ ሃሳብ አንግበን ነው፡፡ ይህንንም ለማለት ድፍረት የሚሰጡን በርካታ ምስክሮች አሉን፤ አንድም ጥንታዊ፣ አንድም ዘመናዊ፡፡ ጥንታዊያኑ በሁለተኛው ክፍለ ዘመን የኖሩ ምስክርነታቸውንም በጽሑፍ ጭምር ያኖሩ እንደ ሮማው ክሌመንት፣ ኢግናቲየስ፣ ሄርማስና ፓሊካርፕ የመሳሰሉ የጥንቷ ቤተክርስቲያን የእምነት አባቶች ሲሆኑ ዘመናውያኑ ደግሞ በእኛው ትውልድ የኖሩ እንደ ማርከስ ባርዝ፣ ኤፍ ኤፍ ብሩስ፣ ፒተር ቲ ኦብራይን ያሉ አንጋፋና ስመ-ጥር የሥ-መለኮት ምሁራን ናቸው፡፡ ከእነዚህም ባሻገር መልዕክቱን ያኔና እዚያ ማንም ቢጽፈው እዚህና አሁን ላለን ለእኛ መለኮታዊ ምሪት ይሆነን ዘንድ በመንፈስ ቅዱስ ባለቤትነት እንደተፃፈ ስለምናውቅ መንፈስ ቅዱስ መሳሪያ አድርጎ የተጠቀመበትን ሰው ማንነት ማወቅ አለማወቃችን መልዕክቱን ለመመርመርና በውስጡ የተሰወሩትን እንቁዎች ለመግለጥ የሚከለክለን አይመስለኝም፡፡ ዳሩ ጸሐፊዎቻቸውን የማናውቅ ብቻ ሳይሆን ለመገመት የምንቸገርባቸው ሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አሉ አይደል?[6] ሆኖም ጸሐፊዎቻቸውን አለማወቃችን ከማንበብም ሆነ ከመታነፅ አልከለከለንም፡፡

## የመልዕክቱ የመጀመሪያ ተደራሲያን

የኤፌሶን መልዕክት ለማን ነው የተፃፈው? የሚለው ጥያቄ ለዘመናት የመጽሐፍ ቅዱስ መርማሪዎችን ሲያከራክር የኖረና እስከ አሁንም ድረስ አንድ እልባት ያልተገኘለት ጉዳይ ነው፡፡ ምናልባት መልዕክቱን በግልብ የሚያነብ ሰው "በመግቢያው ላይ በትላልቅ ፊደላት *"የሐዋሪያው የጳውሎስ መልዕክት ወደ አፌሶን ሰዎች"* የሚል ተጽፎ የለም ወይ? ደግሞስ ምዕራፍ አንድ፣ ቁጥር አንድ ላይ ሲጀምር *"በእግዚአብሔር ፈቃድ የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋሪያ የሆነ ጳውሎስ በኤፌሶን ላሉ ቅዱሳን . . . ፡፡"* ይል የለም ወይ? በማለት ሊጠይቅ ይችላል፡፡ ሌላው ብዙ ምርምር የማይሻ፣ ለነፍሱ የዕለት እንጀራ የሚፈልግ አንባቢ ደግሞ "በዚያን ዘመን ለማንም ተፃፈ ለማን ዛሬ፣ ከሁለት ሺህ ዓመታት ባሻገር ላለን ለእኛ የሚናገር የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን ካወቅን ሌላ ምን ያስፈልገናል?" ይል ይሆናል፡፡ እነዚህ ሁለት ጥያቄዎች እንዳሉ ሆነው ከመልዕክቱ ጋር በተዛመደ

[6] ለምሣሌ ያህል የዕብራውያንን መልዕክት መጥቀስ ይቻላል፡፡



For more books www.amharicchristianbooks.com

መልኩ የመጀመሪያዎቹን ተደራሲያን እነማን እንደሆኑ ለማወቅ ጥረት አደርጋለሁ፡፡ ይህንንም የማደርገው የመልዕክቱን ፍሬ ሃሳብ ወደ ጎን በመተው ለጸሐፊውና ለተደራሲያኑ መቼት  ዋና ሥፍራ በመስጠት አይደለም፡፡ ይልቅ ፍለጋው እግረ- መንገድ አንባቢያን መልዕክቱንና ዙሪያ ገባውን ለመቃኘት እንዲችሉ ያግዛል ብዬ ስለማምን ነው፡፡ ሆኖም ግስጋሴው ለብቻ የሚያዋጣ አይደለምና አንባቢዎቼም አብራችሁ በታሪክ ሰረገላ ላይ ትሳፈሩ ዘንድ እየጋበዝኩ ፍለጋዬን ልቀጥል፡፡

በቅድሚያ በመልዕክቱ መግቢያ ላይ “በኤፌሶን ላሉት” የሚለው ሐረግ እያለ ለምን ጥያቄ ሊፈጠር ቻለ? የሚለውን ልመልስ፡፡ አብዛኞቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች እንደሚስማሙበትና አንዳንዶቹም በግርጌ ማስታወሻዎቻቸው ላይ በግልጽ እንዳሰፈሩት "በኤፌሶን ላሉት" የሚለው ቃል በመልዕክቱ የጥንት ቅጂዎች ላይ አይገኝም፡፡[7]

ለዚህም እንደ ኦሪገን ያሉ በሦስተኛው ምዕተ-ዓመት የነበሩ የቤተክርስቲያን አባቶች በጽሑፎቻቸው ውስጥ መልዕክቱ ለኤፌሶን ቤተክርስቲያን መጻፉን አለማውሳታቸው ይጠቀሳል፡፡ ታዲያ ለነማን ተፃፈ? ይህን ጥያቄ ለመመለስ ከበርካታ አመለካከቶች መሃል አንዱን ላንሳ፡፡

አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት ይህ መልዕክት እንደሌሎቹ የሐዋሪያው ደብዳቤዎች ለአንድ አጥቢያ ቤተክርስቲያን የተፃፈ ሳይሆን፣ በትንሿ እስያ በሚገኙ በርካታ አብያተክርስቲያናት በመዘዋወር እንዲነበብ ታስቦ የተላከ ዘዋሪ (circular) ደብዳቤ  ነው ይላሉ፡፡ ስለዚህም በመግቢያው ላይ የቤተክርስቲያኒቱ ስም የሚሰፍርበት ቦታ ክፍት የተተወና ቅጂው የሚደርሳቸው ቤተክርስቲያናት ያሉበትን ስፍራ ስም የሚጽፉበት እንደሆነ ያትታሉ፡፡ ታዲያ ይህ መልዕክት ከተላከላቸው በትንሿ እስያ ከሚገኙ ከተሞች መሃል ታላቋ ከተማ ኤፌሶን ስለነበረችና በዚያም የምትገኘው የክርስቶስ ማኅበር ጠንካራና ግዙፍ ስለሆነች መልዕክቱ የኤፌሶንን ስም ያዘ ይላሉ፡፡ በእርግጥ ኤፌሶን በዚያን ዘመን በሦስት አቅጣጫ ዝነኛ ነበረች፡፡ ከፖለቲካው አንፃር፣ የሮም መንግስት ለእስያ ግዛቱ ዋና ከተማ አድርጎ መርጧታል፡፡ ወደ ኢኮኖሚው ስንዘልቅ ደግሞ በዘመኑ ድንቅ የተባለ ወደብ የነበረው የባሕር በር ነበራት፡፡ ስለዚህ የበርካታ መርከቦች ማረፊያ፣ የብዙ ሸቀጦች ማራገፊያ የወደብ ከተማ ነበረች፡፡ ከኃይማኖት አንፃርም የረጅም ዓመታት ታሪክ ያላት ግሪኮቹ አርጤምስስ፣ ሮማውያኑ ደግሞ ዳያና እያሉ

[7] አዲሱ መደበኛ ትርጉም ኤፌ. ፲፡፲ የእግርጌ ማስታወሻ ይመልከቱ



For more books www.amharicchristianbooks.com

የሚጠሩአት ጣኦትና ቤተጣኦቷ በዚያ ይገኙ ነበር፡፡

ስለዚህ ኤፌሶን በዘመኑ ዓለም ከነበራት ሥፍራ የተነሳ ለአካባቢዋ የተፃፈው ተዘዋዋሪ መልዕክት የእርሷን ስም ቢይዝ አያስደንቅም፡፡ በሌላም በኩል የመልዕክቱ ይዘት እንደሌሎቹ የሐዋሪያው መልዕክቶች በአንድ አጥቢያ ውስጣዊ ጉዳዮች ላይ ያተኮረ አካባቢያዊ ከመሆን ይልቅ፣ በአሕዛብ ጉዳይ ላይ ያነጣጠረ ወገናዊ መሆኑ ተዘዋዋሪነቱን የበለጠ አሳማኝ ያደርገዋል፡፡

ሌላም እሳቤ አለ፡፡ ሐዋሪያው ጳውሎስ ለሦስት ዓመታት የእስያ ዋና ከተማ በሆነችው በኤፌሶን ተቀምጦ ወንጌልን ሲያገለግል በአካባቢው ከሚገኙ ከተሞች ወደየትኛውም አልተጓዘም፤ ነገር ግን በኤፌሶን ቆይታው በእስያ የሚኖሩት አይሁድና አሕዛብ በሙሉ የክርስቶስን ወንጌል ሰሙ፡፡[8] ይህ እንዴት ሊሆን ቻለ? ሐዋርያው ከዚህ ቀደም ወንጌልን ለማሰማት ይጠቀምበት የነበረው ስልት ወደ አካባቢዎቹ እየሄደ ወንጌልን መስበክና ቤተክርስቲያንን መትከል ነበር፡፡ ወደ ኤፌሶን ሲመጣ ግን መንፈስ ቅዱስ ይህንን ስልት አስለወጠው፡፡[9]

አዲሱም ስልት ወደ ተለያዩ የእስያ ከተሞች በግንባር ከመሄድ ይልቅ በኤፌሶን ከተማ ጢራኖስ የሚባል ት/ቤት ውስጥ ከደቀመዛሙርት ጋር ዕለት ተዕለት መነጋገር ያዘ፡፡ በዚህ ስፍራ ከእግሩ ስር ተሰይመው የተማሩትና ለወንጌል ሥራ የተዘጋጁት ሠራተኞች ወደየአካቢዎቻቸው በመሄድ ወንጌል ሰበኩ፣ አብያተክርስቲያናት ተመሰረቱ፡፡ ከእነዚህም ሠራተኞች መሃል አንዱ ኤጳፍራ ሲሆን፣ ቤተክርስቲያናት ከተመሠረቱባቸው አካባቢዎች መሃል ከኤፌሶን ከሰማኒያ እስከ መቶ ማይልስ ርቀት ላይ የሚገኙት ቄላስይስ፣ ሎዶቂያና ኢያራ የሚባሉ ከተሞች ይገኛሉ፡፡ ሐዋርያው በእነዚህ ከተሞች የሚገኙትን አማኞች አብሮት ከሚሠራው ከኤጳፍራ ከሰማው በቀር በስጋ ፊት ለፊት አይቶአቸው አያውቅም፡፡ በእርግጥ በሥጋ ባይሆንም በመንፈስ እንዳያቸው እርሱ ራሱ መስክሯል፡፡[10] ሐዋርያው የኤፌሶን ቆይታውን ፈጽሞ ወደ ኢየሩሳሌም ካቀናና በኢየሩሳሌም አይሁድ ባስነሱት ሁከት ታስሮ ለቄሳር ይግባኝ በማለቱ ምክንያት በመርከብ ወደ ሮም በመጓዝ በግዞት ቤት ከተቀመጠ በኋላ በእነዚህ አካባቢዎች አንዳንድ የትምህርት ጥያቄዎች ይነሳሉ፡፡ እነዚህንም ሾልከው በገቡ ሃሰተኞች የተነሳውን የትምህርት ችግር ለመፍታት በጳውሎስ እጅ የሰለጠኑት የአካባቢው ሠራተኞች

[8] ሐዋ. ሥራ 19፡10
[9] ጳውሎስ በዚህ ሥልት በአካይያና በመቄዶንያ ወንጌልን ያሠራጨ ቢሆንም በዚህ መልኩ ወደ እስያ (ኤፌሶን የምትገኝበት) እንዳይገባ መንፈስ ቅዱስ ከልክሎት ነበር፡፡ ሐዋ. ሥራ 16፡ 6 - 8
[10] ቆላ. 1፡7፣8; 2፡5



For more books www.amharicchristianbooks.com

አቅም ስላልበቃ መፍትሔ ለመሻት ኤጳፍራ ጳውሎስ ወዳለበት ወደ ሮም ይላካል፡፡

ኤጳፍራ በሮም ግዞት ቤት ከጳውሎስ ጋር እንደታሰረ ሆኖ አብሮት በመቀመጥ ያለውን ሁኔታ ያጫውተዋል፡፡ ጳውሎስም መፍትሔ ለመሻት መልዕክቶችን ጽፎ ወደነዚህ አካባቢዎች በሚጓዘው በቲቂቆስ እጅ ይልካቸዋል፡፡[11] እነዚህም ደብደቤዎች ለቆላሲያስና ለሎዶቂያ አብያተክርስቲያናት የተፃፉ ሲሆኑ የኤፌሶን መልዕክት ብለን የምንጠራው ደብዳቤ ለሎዶቂያ ሳይጻፍ እንዳልቀረ ይታመናል፡፡ ይህንን አመለካከት ለመጀመሪያ ጊዜ ያስተጋባው በሁለተኛው ክፍለ ዘመን የኖረው ማርሲዮን[12] ሲሆን፣ እንደ ቴዎዶር ቤዛ እና ጆን ላይትፉት ያሉ ሌሎች መምህራንም በብርቱ ይስማሙበታል፡፡[13] ምክንያቶቹን በጥሞና ስንመረምር እንዲህ ለማለት የሚያስደፍሩ አንዳንድ ተጨባጭ ማስረጃዎችን እናገኛለን፡፡

ሐዋርያው ጳውሎስ ጥቂት ጊዜ እንኳን ወደቆየባቸው ቤተክርስቲያናት መልዕክቶችን ሲጽፍ ቢያንስ ለሚቀርቡት ወገኖች ስም ጠቅሶ ሰላምታ የመስጠት ልማድ አለው፡፡ ወደ ኤፌሶን ሁለት ጊዜ ከመጓዙ ባሻገር በአንድ ጊዜ ሦስት ዓመታት እንደቆየ፣ በቆይታውም ሌሊትና ቀን፣ በእንባ እያንዳንዳቸውን ያለማቋረጥ እየገሰፀ በጉባዔም በየቤታቸውም እንዳስተማረ ታሪክ ፀሐፊው ሉቃስ በሐዋርያት ሥራ 20 ላይ ዘግቦልናል፡፡ ታዲያ ይህ መልዕክት ለኤፌሶን ሰዎች ተጽፎ ቢሆን ኖሮ ምንኛ የቅርበት ሰላምታ ባቀረበ ነበር! አንድ ጊዜ እንኳ ፊት ለፊት ላላያቸው ለሮሜ ሰዎች ሲጽፍ አይሁድ ከኢየሩሳሌም በተባረሩ ጊዜ በአካይያና በእስያ አውራጃዎች ላገኛቸው በኋላም ወደ ሮም ለተመለሱ ወገኖች ስማቸውን እየጠራ አንድ ምዕራፍ ሙሉ ሰላምታ እንዳቀረበ እናውቃለን፡፡[14] ይህን መልዕክት (ኤፌሶንን) ስንመለከት ግን በጽሑፍ የገለፀው እንዳላያቸውና እንዳላዩት፣ ይልቅ ስለ እነርሱ እንደሰማና ስለእርሱ እንደሰሙ ብቻ ነው፡፡ እርሱ ስለ እነርሱ ያለውን ዕውቀት፡-

> *"ስለዚህ እኔ ደግሞ በእናንተ ዘንድ ስለሚሆን በጌታ በኢየሱስ ስለ ማመንና ለቅዱሳን ሁሉ ስለሚሆን መውደድ ሰምቼ ስለ እናንተ እየመሰገንሁ ስፀልይ ስለእናንተ ማሳሰብን አልተውም . . . ፡፡" ኤፌ.1፡15*

---

[11] ኤፌ. 6፡ 21-22; ቆላ. 4፡ 7-9

[12] ማርሲዮን ትምህርቱ ሕፀፅ የነበረበት የብሉይ ኪዳንን መጻሕፍት እንደ ቅዱሳን መጻሕፍት የማይቀበልና የጳውሎስን መልዕክቶች በተዛባ መልኩ ይተረጉም የነበረ መምህር መሆኑን የጥንት የቤተ ክርስቲያን አባቶች ይመሰክራሉ፡፡

[13] Theodore Beza, Novum Testamentum, cum versione Latina veteri, et nova Theodori Bezæ;

[14] ሮሜ 15፡ 22-24; 16፡ 1-16



For more books www.amharicchristianbooks.com

እነርሱ ስለርሱ ያላቸውን ዕውቀት ፡-

> *"ለእናንተ ስለተሰጠኝ ስለ እግዚአብሔር ፀጋ መጋቢነት በእርግጥ ሰምታችኋል። አስቀድሜ ባጭሩ እንደጻፍሁ ይህን ምስጢር በመግለጥ አስታወቀኝ፣ ይህንንም ስታነቡ የክርስቶስን ምሥጢር እንዴት እንደማስተውል ልትመለከቱ ትችላላችሁ።" ኤፌ. 3፡2-4*

በማለት ፍንትው አድርጎ ገልጧል፡፡

ታዲያ እነዚህ በሥጋ ያላያቸው፣ ነገር ግን ስለእነርሱ የሰማ፣ እነርሱም ስለ እርሱ የሰሙ እነማን ናቸው? ስንል የምናገኘው መልስ ከቈላስይስ ሰዎች ጋር መልዕክት የተላከላቸው የሎዶቅያ ሰዎች እንጂ፣ ሦስት ዓመታት በቅርበት አብሮአቸው የኖረ፣ ሲለያቸው በታላቅ ለቅሶ አንገቱን አቅፈው እየሳሙ እስከ መርከብ ድረስ የሸኙት የኤፌሶን ሰዎች አለመሆናቸውን መገመት አያስቸግርም፡፡[15] ስለ ሎዶቂያውያን ግን፡

> *"ስለ እናንተና በሎዶቂያ ስላሉት ፊቴንም በሥጋ ስላላዩት ሁሉ እንዴት ያለ ትልቅ መጋደል እንዳለኝ ልታውቁ እወዳለሁና . . . ።" ቆላ. 2፡1 ብሏል።*

ለቈላስይስና ለሎዶቅያ በአንድ ጊዜ ከእስር ቤት ሁለት መልዕክቶች መፃፋቸውንና በአንድ ሰው እጅ መላካቸውን፣ ከቆላስይስ መልዕክት መረዳት እንችላለን፡፡ እነዚህ በመልዕክታቸው ይዘትና በሥነ ጽሑፋዊ ቅርፃቸው ከፍተኛ ተመሳሳይነት ያላቸው ሁለት መልዕክቶች፣ በአንድ ሰው በቲኪቆስ እጅ መላካቸው ብቻ ሳይሆን የቆላስይሱን መልዕክት ሎዶቅያዎች፣ የሎዶቅያውን ደግሞ ቈላስይሶች እንዲያነቡ መታዘዛቸው የበለጠ ነገሩን ግልጽ ያደርገዋል፡፡

> *"ይህችም መልዕክት በእናንተ ዘንድ ከተነበበች በኋላ በሎዶቅያ ሰዎች ማኅበር ደግሞ እንድትነበብ አድርጉ። ከሎዶቅያ የምትገኘውን መልዕክት እናንተ ደግሞ አንብቡ።" ቆላ. 4፡16*

ይህን ሃሳብ ስንጨምቀው መልዕክቱ በሎዶቅያ ላሉ አማኞች እንደተጻፈ የሚያሳይ ፍንጭ አለው፡፡ ሆኖም በአንባቢያን ዘንድ መግባባትን ለመፍጠር እንዲያመች በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የመልዕክቱን የመጀመሪያ ተደራሲያን "የኤፌሶን ሰዎች" በማለት እንቀጥላለን፡፡

## የኤፌሶንና የቆላስያስ መልዕክቶች ትስስር

የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በተለያዩ ሰዎች ብዕር፣ በተለያየ ዘመን የተጻፉ ቢሆኑም

[15] ሐዋ. ሥራ 20፡ 36-38



For more books www.amharicchristianbooks.com

የአንዱ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ በመሆናቸው የመልዕክት አንድነት እንዳላቸው አሌ የማይባል ጉዳይ ነው፡፡ ነገር ግን የኤፌሶንና የቆላስያስ መልዕክቶች ዝምድና ከሌሎቹ በተለያ መንገድ ይጠብቃል፡፡

በርካታ ተመሳሳይነታቸውን ከመዘርዘሬ በፊት ጥቂት ልዩነት መሰል ነገሮችን ልጥቀስ፡፡ ቆላስያስ የቤተክርስቲያን ራስ በሆነው ክርስቶስ ላይ ሲያተኩር፣ ኤፌሶን የክርስቶስ አካል በሆነችው በቤተክርስቲያን ላይ በማተኮሩ ጥቂት ልዩነት ያላቸው ይመስላል ሆኖም የሁለቱ ድምር አንድ አዲስ ሰው ስለሚያሳየን ዝምድናቸውን ያጠናክረዋል እንጂ አይለያየውም፡፡ በእርግጥ አንድ ደማቅ መሠረታዊ ልዩነት አለ፤ ይኸውም ከተጻፉበት ዓላማ ጋር ይያያዛል፡፡ የቆላስያስ መልዕክት በቤተክርስቲያኒቱና በአካባቢዋ የተነሳውን የስህተት ትምህርት ለመመከት የተሠራ የዕቅበተ-እምነት ሥራ ጎልቶ ይታይበታል፡፡ የኤፌሶን መልዕክት ግን ያለውን በማጠናከር ላይ እንጂ የስህተት ትምህርትን ለመመከት የተደረገ ጥረት አይስተዋልበትም፡፡

ወደ ተመሳሳይነታቸው ስንመጣ ሁሉን መዘርዘር ባይቻል እንኳ ጥቂቱን ለመመልከት እንሞክር፡፡ ሁለቱም መልዕክቶች ጳውሎስ ለሚጽፍላቸው አማኞች በሚፀልያቸው ረዥም ፀሎቶች የሚጀምሩ ናቸው፡፡[16] በእነዚህ ክፍሎች ውስጥ ጳውሎስ ስለ እምነትና ስለ ፍቅር ተመሳሳይ ነገር ጠቅሷል፡፡[17] ሁለቱም መልዕክቶች በራስና በአካል መካከል ባለው ሕይወታዊ ግንኙነት ላይ ያተኩራሉ፡፡[18] ስለ ቤተክርስቲያን ማንነት ሲዘግቡ ከእግዚአብሔር ምሥጢር ጋር ያገናኙዋታል፡፡[19] ሁለቱም አሮጌውን ሰው ስለማስወገድና አዲሱን ሰው ስለ መልበስ ይናገራሉ፡፡[20] የሙሴ ሕግ በክርስቶስ የመስቀል ሥራ መሻሩን የሚያበስሩት ክፍሎች በእጅጉ ያመሳስሏቸዋል፡፡[21] ሁለቱም መልዕክቶች ስለ ክርስቲያናዊ ቤተሰብ በዝርዝር ይዘግባሉ፡፡[22] በመጨረሻም ሁለቱም መልዕክቶች ከሮም እሥር ቤት በቲኪቆስ እጅ

---

[16] ኤፌ. 1፡ 16-19ን ከ ቆላ. 1፡9-11 ጋር ያወዳድሩ፡፡

[17] ኤፌ. 1፡15 እና ቆላ. 1፡ 4; 8 ያስተያዩ (በእርግጥ በቆላስያስ ላይ ከእምነትና ከፍቅር ባሻገር ስለ "ተስፋ" ጠቅሷል፡፡ በኤፌሶን ላይ ስለ ተስፋ የሚያነሳው 1፡18; 2፡12; 4፡4 ላይ ነው፡፡

[18] ኤፌ. 1፡22ን ከ ቆላ. 1፡18 ጋር ያነፃፅሩ፡፡

[19] ኤፌ. 3፡3; 4; 9ን ከ ቆላ. 1፡26; 27; 2፡2; 4፡3 ያንብቡ

[20] ኤፌ. 4፡22-24ን ከ ቆላ. 3፡ 10 ጋር ያመሳክሩ፡፡

[21] ኤፌ. 2፡14-15; ቆላ. 2፡14-16 ይመልከቱ

[22] ኤፌ. 5፡21-6፡9 እና ቆላ. 3፡18-4፡1



For more books www.amharicchristianbooks.com

የተላኩ የእሥር ቤት ደብዳቤዎች መሆናቸው ተመሳሳይነታቸውን ያጎላዋል፡፡[23]

## የእሥር ቤት ደብዳቤ

ፀሐፊው በሮም እሥር ቤት ውስጥ በግዞት ላይ ነው፡፡ ይህ እስር የእስያ አገልግሎቱን ፈፅሞ፣ በኢየሩሳሌም ላሉት ቅዱሳን የሰበሰበውን የፍቅር ስጦታ አድርሶ፣ በዚያ ላሉት ለሕግ ቀናእያን ለሆኑት አይሁድ ሕሊና ሲል በቤተ መቅደስ የመንፃት ስርዓት ሲፈፅም በተፈጠረው ሁከት ከተያዘ በኋላ የገጠመው የመጀመሪያው እስር ነበር፡፡ ይህ እስር ባብዛኛው በጉዞና በግዞት የተሞላ የጳውሎስ ረዥሙ የእስራት ጊዜ እንደነበር ይገመታል፡፡ በዚህ የመከራ ወቅት ጳውሎስ ከኢየሩሳሌም እስከ ሮም ያሉ በርካታ ዘብጥያዎችን ጎብኝቷል፡፡ አንዳንዱ ጓደኞቹን በነፃነት ተቀብሎ ማስተናገድ የቻለበትና አንፃራዊ እፎይታ የነበረበት ቢሆንም፣ አብዛኛው ግን ዛሬ ላይ ቆሞ ለማሰብ እንኳ የሚሰቀጥጥ የመከራ ማሣ ነበር፡፡ ምንም እንኳ መልዕክቶቹ የእስሩን ሁኔታ ምን እንደሚመስል ግልፅ ያለ መረጃ ባይሰጡንም የአንደኛው ክፍለ ዘመን ታሪክ ጸሐፊዎች ዘገባ በሚሰጠን ስዕል ታግዘን ሁኔታውን በምናባችን መሳል አይቸግረንም፡፡

መልዕክተኛው ሙሉ የጦር ዕቃቸውን በታጠቁ የሮማ ወታደሮች እየተጠበቀ፣ አንዳች በሚያህሉ የተጠረቡ ድንጋዮች ከፍ ብሎ የተገነባ አጥር ባለው፣ ውስጥ ውስጡን ብዙ ክፍሎች በታመቁበትና እያንዳንዳቸው በብረት ዘንግ በተከለሉበት፤ ለአየርና ለብርሃን ማስገቢያ ካልሆነ በቀር ውጭውን ለማየት የማያስችሉ መስኮቶች ባሉት ጠባብ ክፍል ውስጥ ተዘግቷል፡፡ ምንም እንኳ የእስር ቤቱ ግድግዳና አጥር የውጭውን ዓለም እንዳያይ ቢጋርደውም እርሱ ግን የልብ ዓይኑ በርቶለት፣ ከፍጥረት መጋረጃ ባሻገር ወደ እግዚአብሔር መንበር ዘልቆ፣ ዓለም ሳይፈጠር የነበረውን፣ በዘመን መጨረሻ የሚሆነውን ከዚህ ቀደም ኖረው ባለፉት የሰው ልጆች ታውቆ የማያውቀውን አስደናቂ ምስጢር እያየ በአምልኮ ይንበረከካል፡፡ ይህ ሰው የታሰረው በእስር ቤቱ ውስጥ እንደታጎሩት እንደሌሎቹ በሌብነት ወይም በነፍስ ገዳይነት አልነበረም፡፡ ሁሉ በራሳቸው ምክንያት የራሳቸውን መከራ ለመቀበል ታስረዋል፡፡ እርሱ ግን ወንጌልን ከመስበኩ በቀር ሌላ በደል አልነበረበትም፡፡ ስለሰው ልጆች ኃጢአት በመስቀል ላይ የሞትን መከራ የተቀበለውን ጌታውን ለመምሰል ስለ ሌሎች መዳን በእስር ቤት ተጥሏል፡፡

[23] ኤፌ. 3፡1; 4፡1; 6፡20; እና ቆላ. 4፡3 የሁለቱም መልዕክቶች ጸሐፊ በእሥር ላይ መሆኑን የሚገልፁ ሲሆን ኤፌ.6፡ 21-22 እንዲሁም ቆላ.4፡7 ሁለቱም መልዕክቶች በቲኪቆስ እጅ መላካቸውን ያሳያል፡፡



For more books www.amharicchristianbooks.com

ወንጀሉም አሕዛብ ከአይሁድ ጋር አንድ አካል ሆነው በክርስቶስ ኢየሱስ የሆነውን የርስት ተስፋ እንዲካፈሉ የተገለጠለትን እውነት መግለጡ ነው፡፡

ጳውሎስ እስር ቤት ሆኖ የጻፋቸውና «የእስር ቤት ደብዳቤዎች» በመባል የሚታወቁ አምስት የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት አሉ፤ (ፊሊጵስዩስ፣ ኤፌሶን፣ ቈላስይስ፣ ፊሊሞናና ሁለተኛ ጢሞቴዎስ) ሆኖም ከዚህ እስር ቤት እንደወጡ የሚታመነው ሦስቱ መጻህፍት ማለትም ቈላስይስ፣ ፊሊሞናና[24] አሁን የምንመለከተው የኤፌሶን መልዕክቶች ናቸው፡፡

ሐዋርያው የታሰረው ስለ እግዚአብሔር ቃል ነውና የታሰረለትን ተግባር ለማከናወን እንደ ልማዱ ብዕሩን ከብራናው ማዛመዱን ቀጥሏል፡፡ በስለት የሾለውን ብዕሩን ከቁርበት በተሠራው ብራና ላይ ደቅኖ በልቡ የፈለቀውን የዘላለም እውነት በቀለም ማፍሰስ ተያያዘው፡፡ እርሱ ራሱ ለአጋሩ ለጢሞቴዎስ በፃፈው ደብዳቤ፡-

> *"በወንጌል እንደምሰብከው ከሙታን የተነሳውን ከዳዊት ዘርም የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስን አስብ፡፡ ይህንም በመስበክ እንደ ክፉ አድራጊ እስከታሰር ድረስ መከራ እቀበላለሁ የእግዚአብሔር ቃል ግን አይታሰርም፡፡ ስለዚህ እነርሱ ደግሞ በክርስቶስ ያለውን መዳን ከዘላለም ክብር ጋር እንዲያገኙ ስለተመረጡት በነገር ሁሉ እፀናለሁ፡፡" 2ጢሞ. 2፡8-10*

እንዳለ እርሱ ታስሮ ሳለ የታሰረለት የእግዚአብሔር ቃል በብዙዎች ጆሮና ልብ ይፈታ ዘንድ ይፅፋል፡፡ ይህ በሥጋው የሚቀበለው የክርስቶስ መከራ የክርስቶስ አካል (ቤተክርስቲያን) የሚጎድላትን እንደሚሞላ አጥርቶ ያውቀዋል፡፡ ስለዚህ፡-

> *"አሕዛብ ስለሆናችሁ ስለ እናንተ የክርስቶስ ኢየሱስ እስር የሆንሁ እኔ ጳውሎስ ለእግዚአብሔር እንበረከካለሁ፡፡" ኤፌ. 3፡1*

ደግሞም፡-

> *"እንግዲህ በጌታ እስር የሆንሁ እኔ በተጠራችሁበት መጠራታችሁ እንደሚገባ ትመላለሱ ዘንድ እለምናችኋለሁ፡፡ ኤፌ. 4፡1*

ይላቸዋል፡፡ ይልቅ የሚያሳስበው ስለ እነርሱ በሚቀበለው በእርሱ እስርና መከራ የሚታከቱት አሕዛብ አማኞች ጉዳይ ነው፡፡ በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን በሜዴትራንያን ዙሪያ ባሉ አገሮች ባሕል፣ እስርና ውርደት የማይነጣጠሉ የአንድ ሣንቲም ሁለት ገጽታዎች ተደርገው ይወሰዱ ነበር፡፡ በማንኛውም ምክንያት ለእስር

[24] ፊሊሞና በቈላስይስ ከተማ የሚኖር፣ በቤቱ ብዙ ባሮችን የሚያስተዳድር፣ የቤተክርስቲያን አገልጋይ ነበር፡፡



For more books www.amharicchristianbooks.com

የተዳረገ ሰው ቆይቶ ከእስር ቢፈታ እንኳ የነውር ጠባሳው እስከማይለቀው ድረስ በማኅበረሰብ ዘንድ ትልቅ ተጽእኖ የሚያመጣ ጉዳይ ነበር፡፡[25] አንድ ሰው ሲታሰር ከእርሱ ጋር አብሮ መቆጠር እንደነውር ይታይ ስለነበር የቅርብ ዘመዶችና ጓደኞች እንኳን ሳይቀር እንደማያውቁት ለመምሰል የሚደርስባቸው ፈተና ቀላል አልነበረም፡፡[26]

የዚህ መልዕክት ተቀባይ የሆኑት የጳውሎስ ተደራሲያንም ከዚህ ፈተና አላመለጡም፤ በሐዋርያቸው እስራት ያፈሩ ብቻ ሳይሆን የታከቱም ይመስለል፡፡ እርሱ ግን እስራቱ በሥጋ አሕዛብ ስለሆኑት ስለእነርሱ (3፡1) ስለ ጌታ (4፡1) ስለወንጌል (6፡20) መሆኑን በማሳየት የማይነጣጠሉ ሦስት የእስራቱን ምክንያቶች ያቀርባል፡፡

ይህንንም በአጭር ቃል ሲመልስላቸው እንዲህ ይላል፡- “ስለዚህ ስለ እናንተ ስላለ መከራዬ እንዳትታክቱ እለምናችኋለሁ፡፡ ክብራችሁ ነውና፡፡” (3፡13)

በእስር ቤት ያለ ሰው (ለዚያውም በዚያ ጥንታዊ የሮም እስር ቤት) ከሚቀበለው መከራ የተነሳ ቢያዝን ፈጽሞ አያስደንቅም፡፡ ይህ ሰው ግን ዛሬ ላይ ቆመን ልናስበውና ልንገምተው በማንችል ውርደትና ሥቃይ ውስጥ ሆኖ፣ ክብር በሞላበት ሐሴት ይፈነድቃል፡፡ ልቡ ከላይ የሚወርድባትን የደስታ ብዛት መሸከም ተስኗት፣ በደስታ ሲቃ ልትፈነዳ የደረሰች እስክትመስል ድረስ ከብዕሩ የደስታ ቃል ይዘንባል፡፡[27]

ይህ ሰው የመንግሥት መልዕክተኛ ነው፤ የእግዚአብሔር መንግሥት ባለ ሙሉ ስልጣን አምባሳደር፡፡ በዚያን ዘመን ዓለምን የሚገዛው የሮም መንግሥት ወደ ተለያዩ ግዛቶች የሚላኩ አምባሳደሮች ነበሩት፡፡ እነዚህ አምባሳደሮች የንጉሡን የምሥራች ወይም ፍርድ ይዘው በብዙ አጀብ ወደ ተላኩበት ግዛት ይጓዛሉ፡፡ ጳውሎስ የሰላምን ወንጌል እንዲያውጅ ወደ አሕዛብ የተላከ የክርስቶስ አምባሳደር ነው፡፡ ሆኖም በእስር ቤት ተጥሏል፡፡ የዚያን ዘመን አምባሳደሮች ለጌጥና የላካቸውን መንግሥት ባለጠግነት ለማሳየት ሲባል በሕዝብ ፊት ሲቀርቡ

---

[25] Dictionary of New Testament backgraound: a compendium of contemporary biblical scholarshiop Pp. 829

[26] 2ጢሞ. 1፡ 15-18; 4፡16;

[27] የፊሊጲስዮስ መልዕክትም እንደ ኤፌሶን መልዕክት የእስር ቤት ደብዳቤዎች በመባል ከሚታወቁት ከአምስቱ መልዕክቶች አንዱ ነው፡፡ በዚህ አጭር ደብዳቤ ውስጥ ጳውሎስ ደስታ የሚለውን ቃል 18 ጊዜ መጠቀሙ በዚያ ውርደትና መከራ ውስጥ ምን ያህል የደስታ መንፈስ እንደፈሰሰበት ያሳያል፡፡



For more books www.amharicchristianbooks.com

በአንገታቸውና በእጃቸው ላይ በከበሩ ድንጋዮች ያሸበረቁ የወርቅ ሰንሰለቶች ማድረግ የተለመደ ተግባር ነበር፤ ይህ መልዕክተኛ ግን ለጌጥ የሚሆን የወርቅ ሰንሰለት ሳይሆን ለሮማ እስረኞች እንደሚገባ የብረት ሰንሰለት ለብሷል፡፡[28] ለዚህም ነው በመልዕክቱ መደምደሚያ ላይ፡-

> *". . . ስለ ወንጌልም በሰንሰለት መልዕክተኛ (አምባሳደር) የሆንሁ መናገር እንደሚገባኝ ስለ እርሱ በግልጥ እናገር ዘንድ ለምኑ፡፡" ኤፌ.6፡20*

በማለት ለሚጽፍላቸው ቅዱሳን የፀሎት ጥያቄ የሚያቀርበው፡፡ (ማብራሪያ ከራሴ) ባጭር ቃል ይህ የእስር ቤት መልዕክት በታሰረ ሰው በኩል የተፈቱ የሕይወት ቃሎች መድበል ነው፡፡

## የመልዕክቱ ትኩረት

በተለያዩ ዘመናት እጅግ በርካታ ፀሐፍት በኤፌሶን መልዕክት ላይ ተመስርተው የተለየዩ መጻሕፍትን ጽፈዋል፡፡ ከእነዚህም ውስጥ የመልዕክቱን ዋና ሃሳብ ሳያፋልሱ ለኖሩበት ትውልድ በሚጠቅም መልኩ የጻፉ በርካታ ናቸው፡፡ ሆኖም ጸሐፍቱ እንደ ዓቢይ ጉዳይ የወሰዷቸውና ሊያስተላልፉ የፈለጉትን ሃሳብ ለማጉላት ያጠነጠኑባቸው ርዕሶች ይለያያሉ፡፡

በእርግጥ የኤፌሶን መልዕክት የማይፋለስ ወጥና ቋሚ መልዕክት አለው፡፡ ከዳር እስከዳር የሚተርከው ስለክርስቶስና ስለ ቤተ ክርስቲያን ነው፡፡ በተለይ በቤተ ክርስቲያን ላይ በማተኮር ለአብ ልጆች፣ ለክርስቶስ ኢየሱስ አካልና ሙሽራ፣ ለመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንዲሆኑ ከአይሁድና ከአሕዛብ ተመርጠው አዲስ ሰው ሆነው ወደ ፍፁም ሙላት ለመድረስ የሚገሰግሱ አማኞች ስብስብ መሆኗን በስፋት ይተርካል፡፡ በመቀጠልም እግዚአብሔር አብ ሁሉን በክርስቶስ ኢየሱስ ሥራ በመንፈሱ በአንድ ለመጠቅለል ያለውን ምሥጢራዊ ሃሳብ በጥበብ ይገልጣል፡፡ በማያያዝም የሰው ልጆች በገሃዱ ዓለም ላይ የምንኖረው ኑሮ እዚሁ ተቦክቶ እዚሁ የሚጋገር ሳይሆን ፣ከቅዱሱም ይሁን ከዕርኩሱ መንፈሳዊ ዓለም የሚመነጭ ተፅዕኖ መኖሩን ለማሳየት ከሥጋ የስሜት ህዋሳቶቻችን ባሻገር በሰማያዊ ሥፍራ የሚከወን ረቂቅ እንቅስቃሴ መኖሩን ያሳያል፡፡ በመቀጠልም የመልዕክቱ አንኳር ሃሳብ በሆነው በርስት ጉዳይ ላይ ሰፊ ትንተና ይሰጣል፡፡ ይህም የርስት ሃሳብ በክርስቶስ ያመኑ ሰዎች እግዚአብሔር በመንፈሱ አማካይነት

[28] Stott, John, R.W The message of Ephesians God's new society 2nd ed. (BST) PP. 287. ሐዋ. ሥራ 26፡ 29 አማርኛው እስራት የሚለውን የግሪኩ ሠንሰለት ይለዋል፡፡



For more books www.amharicchristianbooks.com

በውስጣቸው ከማደሩ የተነሳ ዘላለማዊ ርስቱ መሆናቸውንና፣ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነትም በውስጣቸው በማደሩ፣ ዘላለማዊ ርስታቸው ሊሆን መፍቀዱን የሚገልፀው ሃሳብ ነው፡፡[29] ይህ በአዲስ ኪዳን መጻህፍት ውስጥ በጉልህ የሚታይ ከርስት ጋር የተዛመደ ሃሳብ ውስጥ ውስጡን እንደ መሠረት የተዘረጋ የመልእክቱ ንጣፍ ዓለት ነው ለማለት ያስደፍራል፡፡

እኔም በኤፌሶን መልዕክት ላይ ተመስርቼ ይህን መጽሐፍ ለመፃፍ ስነሳ የመልዕክቱን አሳብ ከዳር እስከዳር ይገልጽኛል ብዬ የመረጥኩት መሠረታዊ አሳብ "ርስት" ነው፡፡ ስለ ርስት ሲወሳ በርስቱ ላይ ስለሚኖር ሕዝብ መነሳቱ የማይቀር ነው፡፡ ስለዚህ ርስቱ፤ በርስቱ ላይ ይኖር ዘንድ የተጠራው ሕዝብና ሕዝቡም በርስቱ ላይ ሲመላለስ ሊጠብቀው የሚገባው ሕግና ሥርዓት ፈጽሞ የማይነጣጠሉ አንድም ሦስትም ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡

የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ከብሉይ ኪዳን የቀጠሉ እንጂ የተነጠሉ አይደሉም፡፡ በእርግጥ በብሉይ ኪዳን ቅዱሳት መጻሕፍት ተስፋ ብቻ የነበሩት ነገሮች በአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ የምሥራች ሆነው ተገልጠዋል፡፡ የአዲስ ኪዳን ጸሐፍትም ያደረጉት ነገር ቢኖር በቀደሙት ዘመናት የተነገሩትን የተስፋ ቃሎች በመጥቀስ መፈፀሙን ማብሰር ነው፡፡ ለዚህ ነው የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ገፆች በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ ተስፋ ሆነው በተነገሩና በክርስቶስ ኢየሱስ ፍፃሜ ባገኙ ክፍሎች የተሞሉት፡፡

የመልዕክቱ ፀሐፊ ሐዋርያው ጳውሎስ ምንም እንኳን መልዕክቱን የሚጽፈው ለአሕዛብ፤ የሚጠቀምበትም ቋንቋ የግሪክ ቢሆንም፣ እርሱ ራሱ ግን በእሥራኤል ሕግና ሥርዓት ያደገ አይሁዳዊ እንደመሆኑ መጠን በመልዕክቱ ላይ የማንነቱ ነፀብራቅ መኖሩን መካድ አንችልም፡፡ ደግሞም የሚሰብከው ወንጌል ምንም እንኳ በአንደኛው ክፍለ ዘመን የናኘ አዲስ ሃይማኖት ቢመስልም፣ ከጥንት ዘመን አንስቶ በእሥራኤል አማካኝነት ለዓለም የመጣው፣ የተስፋው ቃል ኪዳን ፍፃሜ እንደመሆኑ መጠን የእሥራኤልን እሴቶች መንፈሳዊ ገጽታ በሙላት እንደሚዳስስ መረዳት አያስቸግርም፡፡

---

[29] ይህ ሃሳብ ራሱን ችሎ ሊተነተንና ብዙ ሊጻፍበት የሚገባ መሆኑን ጸሐፊው ይረዳል፡፡ ነገር ግን በጥቂቱም ቢሆን የተሻለ ለመረዳት ይህን ክፍል በጥሞና መመልከቱ ይጠቅማል፡፡ "መንፈሱን ስለ ሰጠን፣ እኛ በእርሱ እንደ እንደምንኖር እርሱም በእኛ እንደሚኖር እናውቃለን፡፡ . . . ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ አምኖ በሚመሰክር ሁሉ፣ እግዚአብሔር በእርሱ ይኖራል፣ እርሱም በእግዚአብሔር ይኖራል፡፡ . . . እግዚአብሔር ፍቅር ነው፣ በፍቅር የሚኖር በእግዚአብሔር ይኖራል፣ እግዚአብሔርም በእርሱ ይኖራል፡፡ በዚህ ዓለም እርሱን እንመስላለንና፡፡" ፩ዮሐ. 4፡ 13 - 17



For more books www.amharicchristianbooks.com

የእሥራኤላዊነትን ምንነት ስንመለከት በሦስት የማይነጣጠሉ ነገሮች የተገመደ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ እሱም በዕብራይስጥ ቋንቋ "ኤሬጽ-እሥራኤል" "አም-እሥራኤል" እና "ቶራት" ናቸው፡፡ ሲተረጎም "የእሥራኤል ምድር" "የእሥራኤል-ሕዝብ" እና የሕዝቡ የኑሮ መሠረት የሆነው "የሙሴ ሕግ" ናቸው፡፡

በእርግጥ ጳውሎስ በክርስቶስ ኢየሱስ ስለተባረክነው መንፈሳዊ በረከትና ስለዚህም በረከት ምንነት በገለፀበት የመጀመሪያ ክፍል፣ በመቀጠልም ይህን መንፈሳዊ በረከት ለመውረስ የተጠራን አማኞች እንዴት ልንመላለስ እንደሚገባን በመከረበት ሁለተኛ ክፍል፣ በመጨረሻም ከዚህ መንፈሳዊ በረከት ሊያጎድሉንና ሊያፈናቅሉን የሚመጡትን፣ መንፈሳዊ ኃይላት እንዴት ልንቃወም እንደሚገባን ባስተማረበት ሦስተኛ ክፍል፣ ስለ ርስት ላይ ላዩን ብቻ ሳይሆን ውስጥ ውስጡንም በስፋት ጽፎአል፡፡ ውስጥ ውስጡን የሆነበትም በቂ ምክንያት አለ፡፡ መሠረት ከወለል በታች ያለ የማይታይ የሕንፃው አካል ቢሆንም የሚታየው ሁሉ የቆመበት ወሳኝ ክፍል ነው፡፡ ይህም ርዕሰ ጉዳይ የመልዕክቱ ክፍሎች ሁሉ የተዋቀሩበት ዋና ጉዳይ መሆኑን እንደምሰሶ ወጥተው በሚታዩት አዕማድ አሳቦች መመልከት ይቻላል፡፡ (ይህ እውነት መልዕክቱን ዘልቀን ስናነብበ በስፋት የምናየው ይሆናል) ሆኖም እስከዚያው ለንባብ የሚረዳ መሠረት ጥሎ ለማለፍ በእያንዳንዱ ክፍል ውስጥ ስለርስትና ከርስት ጋር ስለተዛመዱ ጉዳዮች የሚያወሱ አንዳንድ ክፍሎችን ልጥቀስ፡፡

ሐዋርያው በክርስቶስ በሰማያዊ ስፍራ ስለተባረክነው መንፈሳዊ በረከት ከፃፈ በኋላ የበረከቱን ምንነት ሲዘረዝር፡-

> *"እንደ ፈቃዱ ምክር ሁሉን የሚሠራ እንደእርሱ አሳብ አስቀድመን የተወሰንን በክርስቶስ ደግሞ ርስትን ተቀበልን፡፡ እናንተም ደግሞ የእውነትን ቃል ይኸውም የመዳናችሁን ወንጌል ሰምታችሁ ደግሞም በክርስቶስ አምናችሁ በተሰፋው መንፈስ በመንፈስ ቅዱስ ታተማችሁ እርሱም የርስታችን መያዣ ነው . . . ፡፡" ኤፌ. 1፡ 11-13*

በማለት አስቀድሞ ለአይሁድ ከዚያም ደግሞ ለግሪክ (ለአሕዛብ) ለሚያምኑ ሁሉ በረከቱ ርስት መሆኑን ይገልፃል፡፡ በመቀጠልም አምነን ልንቀበለው ብቻ ሳይሆን ጠልቀን ልናውቀው የሚገባን ዋና ነገር የርስቱ ጉዳይ መሆኑን ለማሳየት እንዲህ በማለት ይማልዳል፡-

> *"የክብር አባት የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ እርሱን በማወቅ የጥበብንና የመገለጥን መንፈስ እንዲሰጣችሁ እለምናለሁ፣ ይህም የልባችሁ*



For more books www.amharicchristianbooks.com

*ዓይኖች ሲበሩ . . . በቅድሳኑም ዘንድ ያለውን የርስት ክብር ባለጠግነት ምን እንዲሆን . . . ታውቁ ዘንድ ነው።" ኤፌ. 1፡ 17-19*

በማለት ይቀጥላል፡፡ ለዘመናት ተሰውሮ የነበረው ምሥጢር በእርሱ በኩል ለአሕዛብ መገለጡን ባበሰረበት ክፍል የምስጢሩን ምንነት ሲያብራራ፡፡

*"ይህን ስታነቡ የክርስቶስን ምሥጢር እንዴት እንደማስተውል ልትመለከቱ ትችላላችሁ፣ ይህም አሕዛብ አብረው እንዲወርሱ በአንድ አካልም አብረው እንዲሆኑ በወንጌልም መስበክ በክርስቶስ ኢየሱስ በሆነ የተስፋ ቃል አብረው እንዲካፈሉ ለቅዱሳን ሐዋርያትና ለነቢያት በመንፈስ አሁን እንደተገለጠ በሌሎች ትውልዶች ዘንድ ለሰው ልጆች አልታወቀም።" ኤፌ. 3፡4-6*

በማለት ይጽፋል፡፡ አማኞች በርስቱ ላይ እንዴት መመላለስ እንዳለባቸው ተግባራዊ መመሪያ በሰጠበት ክፍል ውስጥ የቅዱሳንን ኑሮ ከርስት ጋር አያይዞ ሲጽፍ፡-

*"ይህን እወቁ አመንዝራም ቢሆን ወይም ርኩስ ወይም የሚመኝ እርሱም ጣኦትን የሚያመልክ በክርስቶስ በእግዚአብሔር መንግስት ርስት የለውም።" ኤፌ. 5፡5*

ይላል፡፡ ስለ ክርስቲያናዊ የቤተሰብ ሕይወት መመሪያ በሰጠበት ክፍል ልጆች ለወላጆቻቸው በጌታ እንዲታዘዙ ሲመክር ከዘፀዓት 20፡12 በመውሰድ

*"አባትህንና እናትህን አክብር፣ እግዚአብሔር አምላክ በሚሰጥህ ምድር እድሜህ እንዲረዝም።" ይላል። ኤፌ. 6፡2*

ይህም ቃል እሥራኤላውያን በሚወርሷት ምድር ላይ እንዴት ሊኖሩ እንደሚገባ ግብረ ገባዊ ሕግጋት ከተሰጡበት ከአስርቱ ትዕዛዛት የተወሰደና በግልጥነት ስለ ርስት የሚናገር ቃል ነው፡፡

ከላይ እንደተመለከትናቸው ክፍሎች ፊት ለፊት ርስት የሚለውን ቃል በመጠቀም ባይሆንም በምዕራፍ 2፡12 እና 19 ላይ በቀደሙት ዘመናት አሕዛብ አማኞች ከእሥራኤል መንግሥት ርቀው የኖሩትን ኑሮ ለማሳየት የተጠቀመባቸው ቃላት ከርስት ጋር ጽኑ ተዛምዶ እንዳላቸው ማየት ይችላል፡፡

*". . . በዚያን ዘመን ከእሥራኤል መንግስት ርቃችሁ ለተስፋውም ቃል ኪዳን እንግዶች ሆናችሁ በዚህም ዓለም ተስፋን አጥታችሁ ከእግዚአብሔርም ተለይታችሁ ያለ ክርስቶስ ነበራችሁ። . . . ከእንግዲህ ወዲህ ከቅዱሳን ጋር ባለአገሮችና የእግዚአብሔር ቤተሰቦች ናችሁ እንጂ እንግዶችና መጻተኞች አይደላችሁም።" ኤፌ. 2፡12፣ 19*



For more books www.amharicchristianbooks.com

በሌላም በኩል በተደጋጋሚ የተጠቀመባቸው መግባት (2፡18፣ 3፡12) መመላለስ (4፡1፣ 17፡ 5፡2፣ 10፣ 15) የተሰኙት ቃላት ርስትን መውረስንና በርስት ላይ መኖርን የሚያሳዩ ቃላት መሆናቸውን ከሌሎች የጳውሎስ መልዕክቶችና የአዲስ ኪዳን ጽሑፎች መረዳት እንችላለን፡፡

እንግዲህ ከዚህ በመነሳት ነው በኤፌሶን መልዕክት ላይ ተመስርቼ የጻፍኩትን ይህን ጽሑፍ "ታላቅ ርስት" በሚል ርዕስ የሰየምኩት፡፡ በውስጡም ያሉት ክፍሎች ይህንኑ ሃሳብ በመተንተን "ርስትን ማወቅ" "በርስት ላይ መመላለስ" እና "ርስትን መጠበቅ" በሚል ተሰይመዋል፡፡

## ሰላምታ ለተደራሲያን

በስፋትና በጥልቀት ልናየው ስላለን መልዕክት መቼት አንዳንድ መነሻዎችን ይዤ ታሪካዊ ዳራውን ለመቃኘት ይህን ያህል ከተጓዝኩ  ስለ መልዕክቱ ዋና ክፍል የበለጠ ልጽፍ የሚገባኝ ይመስለኛል፡፡

መልዕክቱ በቀጥታ የተላከበትን ቦታ እርግጠኛ መሆን ባንችል እንኳ፣ ስለተፃፈላቸው ሰዎች ማንነት ግን እርግጠኛ በመሆን ልንናገራቸው የምንችላቸው እውነቶች አሉ፡፡ እነዚህንም በምዕራፍ 1 ቁጥር 1 እና 2 ላይ በፀሐፊው ሰላምታ ውስጥ እናገኘዋለን፡፡

የዚህ መልዕክት ተቀባዮች ቅዱሳን ናቸው፡፡ ምንም እንኳ «ቅዱስ» የሚለው መጠሪያ በአሃዳዊ አጠራር ለእግዚአብሔር ብቻ ጥቅም ላይ የዋለ ቢሆንም በአንዳንድ ስፍራ በብዙ ቁጥር ለእስራኤላውያን መጠሪያ ሆኖ እንዳገለገለ እናያለን፡፡ አሁን ግን ይህ ልዩ የማዕረግ ስም በወንጌል ላመኑ ሁሉ መሰጠቱን እናያለን፡፡ የተሰጠውም ላመኑ አይሁዳዊያን ብቻ ሳይሆን ለአሕዛብ ጭምር መሆኑ፣ በቤተክርስቲያን ውስጥ ላሉ ለተወሰኑ ምጡቅ መንፈሳውያን ሳይሆን በክርስቶስ ኢየሱስ አምነው ዳግም ለተወለዱ አማኞች ሁሉ መሆኑ የሚያስደምም ነው፡፡

እግዚአብሔር ከምድር ለራሱ የሚሆንን ወገን ለመለየት አብርሃምን እንደ ግለሰብ በመጥራት የጀመረውን የማዳን ሥራ ከግለሰብ ወደ ቤተሰብ፣ ከቤተሰብ ወደ ኅብረተሰብ፣ ከኅብረተሰብ  ወደ ሕዝብ፣ ከሕዝብ ወደ መንግስት በማሳደግ ቀጥሎ በፍፃሜው ላይ በክርስቶስ ኢየሱስ ሰዎችን ከነገድ፣ ከቋንቋ፣ ከወገን በመዋጀት ዓለም አቀፋዊ ይዘት እንደሰጠው እናያለን፡፡

በመቀጠል የምናገኘው የዚህ መልዕክት ተቀባዮች መለያ "የታመኑ" የሚል ነው፡፡



For more books www.amharicchristianbooks.com

በርግጥ ቃሉ በሁለት ትርጉሞች መሃል አሻሚ ነው፡፡ አንደኛው ያመኑ፣ የተማመኑ የሚል ትርጉም ሲይዝ ሌላኛው ታማኝ የሆኑና እምነት የሚጣልባቸው የሚል ስሜት ይይዛል፡፡ ምንም እንኳ ማመናችን እያደር ወደ መታመን ሊያመጣን የሚገባ ቢሆንም ፀሐፊው ግን ያነጣጠረው በመጀመሪያ ትርጉም ላይ መሆኑ ብዙም አያጠያይቅም፡፡

ጸሐፊው የተደራስያኑን ማንነት በተመለከተ ቅዱሳንና የታመኑ (ምዕመናን) መሆናቸውን ከጠቆመ በኋላ በመቀጠል አድራሻቸውን ይጠቅሳል፡፡ የሚያስገርመው ጉዳይ የዚህ መልዕክት ተቀባዮች ሁለት አድራሻ ያላቸው መሆኑ ነው፡፡ አንደኛው በኤፌሶን! ሁለተኛው በክርስቶስ ኢየሱስ!

*"በኤፌሶን ለሚገኙ በክርስቶስ ላሉ . . ." ኤፌ. 1፡1*

ይላልና፡፡ *"በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉ"* የሚለው ቃል በመጀመሪያ በተፃፈበት በግሪኩም ሆነ በሌሎች ቋንቋዎች "በክርስቶስ ኢየሱስ ውስጥ" የሚል ትርጉም ስላለው ክርስቶስ ኢየሱስ መታመኛ ብቻ ሳይሆን መኖሪያ አድራሻ ጭምር እንደሆነ ያሳያል፡፡ እነዚህ አማኞች በኤፌሶን እንዳሉ ሁሉ በክርስቶስም አሉ፡፡ ኤፌሶን አካላዊ አድራሻቸው ሲሆን ክርስቶስ ሕይወታዊና መንፈሳዊ አድራሻቸው ነው፡፡

ይህ ሀሳብ እዚህ መግቢያ ላይ በጥቂት ቃላት ይስፈር እንጂ ወደ መልዕክቱ ስንዘልቅ የመልዕክቱ ዋና ሀሳብ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ በምዕራፍ አንድ ውስጥ ብቻ "በክርስቶስ (ውስጥ)" (in Christ) የሚለው ቃል አሥራ ሁለት ጊዜ ተደጋግሞ መፃፉ በቂ ማስረጃ ነው፡፡ እኔም የመጽሐፉ አብይ ትኩረት አድርጌ የመረጥኩት የርስት ጉዳይ በዚህ ቃል ውስጥ እውን ይሆናል፡፡ በምድር ጊዜያዊ መኖሪያ እንዳለን ሁሉ በክርስቶስ ዘላለማዊ መኖሪያ አግኝተናልና፡፡ ክርስቶስ መኖሪያ ቦታ ሳይሆን መኖሪያ ሕይወት ነው፡፡ ሕይወት በቦታ ውስጥ እንድንኖር ያደርገናል እንጂ ቦታ በሕይወት እንድንኖር አያደርገንም፡፡ በምድር ሆንን በሰማይ ከክርስቶስ የተነሳ በሕይወት እንኖራለን፡፡

በመቀጠልም ሐዋርያው በሌሎች መልዕክቶች እንደተለመደው "ከእግዚአብሔር ከአባታችን፣ ከጌታም ከኢየሱስ ክርስቶስ ፀጋና ሰላም ለእናንተ ይሁን፡፡" በማለት የመግቢያ ሰላምታውን ይደመድማል፡፡

ፀጋና ሰላም በዘመኑ የደብዳቤ አፃፃፍ ስልት የተለመዱ የመግቢያ ቃላት ሲሆኑ፣ ፀጋ በግሪኮች፣ ሰላም ደግሞ በአይሁዳውያን ዘንድ በብዛት ጥቅም ላይ የሚውሉና የሚዘወተሩ ናቸው፡፡ በዚህ መልዕክት ውስጥ ግን ከዚህ የላቀ ፋይዳ እንዳዘሉ መገመት አያስቸግርም፡፡ በክርስቶስ ኢየሱስ *ሥራ* ኃጢአተኞች የነበሩ ሰዎች



For more books www.amharicchristianbooks.com

ከእግዚአብሔር ጋር ታርቀው የመንፈስ ቅዱስን ሥጦታ ማግኘታቸው፣ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል አስተማማኝ ሰላም መገኘቱን ያበስረናልና፡፡ ይህም ሰላም ሕግን በመፈፀም ወይም በራስ ጥረት ላይ የተመሠረተ ሳይሆን በፀጋ የተገኘ ነው፡፡ ፀጋ ነፃ ብቻ ሳይሆን ለማይገባው የሚሰጥ፣ ተቀባዩ የማይመጥነው፣ ሰጪውን የሚያህል ስጦታ ነው፡፡ በፀጋ ካልሆነ በስተቀር ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም ሊኖረው አይችልም፡፡ ይህም ዘላቂ ሰላም በፀጋ በመጽደቅ የሚገኝ ቢሆንም፣ በፀደቅንበት በዚያው ፀጋ ታግዘን በጽድቅ በመኖር የሚገለፅ ነው፡፡

እንግዲህ በመግቢያዬ ላይ ይህንን ያህል ካልኩ እያንዳንዱን ክፍልና አንቀፅ እየተነተንን ወደምናይበት የማብራሪያው ዋና ክፍል በአንድነት እንድንዘልቅ እጋብዛለሁ፡፡



For more books www.amharicchristianbooks.com

# ክፍል አንድ፡ ርስትን ማወቅ

## *መግቢያ*

የመልዕክቱ የመጀመሪያ ክፍል የሆነውን ከ1፡3 እስከ 3፡21 የሚገኘውን ክፍል የኤፌሶን መልዕክት ስለ ዘላለማዊ ርስት፣ በርስቱም ላይ ለመኖር ስለተጠራ ሕዝብና ሕዝቡ በርስቱ ላይ ሊመላለስበት ስለሚገባ የሕይወት ሥርዓት በተለየ ሁኔታ የሚተርክ ስለመሆኑ በመግቢያዬ ላይ ጠቅሻለሁ፡፡ ይህንንም እውነት ወደ መልዕክቱ ዘልቀን ስንገባና እያንዳንዱን ክፍል ለመፍታት ስንሞክር በግልጽ የምናየው ይሆናል፡፡

ይህም ሆኖ "ርስትን ማወቅ" የሚል ስያሜ የሰጠሁት የመጀመሪያው ክፍል በርስቱ ላይ እንዴት መኖር እንዳለብን፣ ከርስታችን ሊያፈናቅሉን የሚመጡ ጠላቶቻችንን እንዴት መቃወም እንደምንችል ከመመልከታችን በፊት የርስቱን ምንነት፣ እኛም ከማንነታችን የተነሳ የርስቱ ተካፋዮች ለመሆን ምን ያህል ብቁዎች እንዳልነበርን፣ ወራሾች እንሆን ዘንድ ያበቃን ሥራ ምን እንደሆነ፣ እንዴትና በማን እንደተሠራ፣ ይህን ታላቅ ርስት በተመለከተ ለዘላለም ተሰውሮ የነበረው ምስጢር እንዴት እንደተገለጠና የዚህን ምስጢር ምንነት ማወቅ በአዲሱ የሕይወት ሥርዓት ለመመላለስም ሆነ በጽናት ለመቆም እንዴት ሊያበረታን እንደሚችል የምንማርበት ክፍል ነው፡፡

ክርስትናን ከሌሎች ኃይማኖቶች ልዩ የሚያደርገው ዋና ነገር ቢኖር ከመታዘዝ የሚጀምር ሳይሆን ከማወቅና ከማመን የሚነሳ መሆኑ ነው፡፡[30] ለዚህ ነው ሐዋርያው መልዕክቱን ሲጽፍ ከምዕራፍ 1 እስከ 3 ልናውቀውና ልናምነው የሚገባንን እንጂ ልንታዘዘውና ልናደርገው የሚገባንን አንዳች ነገር ያልጠቀሰው፡፡ በክርስትና መሰረታዊ አስተምህሮ ላይ ያተኮሩትን ሦስቱን ምዕራፎች ደጋግመን ብናነብ የማናገኘው ነገር ቢኖር፣ መሥራትና መፈፀም ያለብንን የሚነግረንን ክፍል ነው፡፡ በአንፃሩ ከምዕራፍ 4፡1 አንስቶ እስከ ምዕራፍ 6፡20 የሚዘልቀውን ሁለተኛና ሦስተኛ ክፍል ስንመለከት እያንዳንዱ ቁጥር በትዕዛዛትና በመመሪያዎች የተሞላ፣ ልንኖርበት የሚገባውን የላቀ ደረጃ ከፍ አድርጎ የሚያሳይ እንደሆነ እንገነዘባለን፡፡ ከዚህም የአፃፃፍ ስልት የምንረዳው የተሠራለትንና እንዲያው በፀጋ የተሰጠውን ያላወቀ አማኝ ሊኖርበት በሚገባው ደረጃ ሊኖር እንደማይችልና ማወቅ የመኖር መሠረት መሆኑን ነው፡፡

---

[30] ሮሜ 1፡5



For more books www.amharicchristianbooks.com

ይህም እውቀት በአእምሮ ምጥቀትና በምርምር ጥልቀት የሚገኝ የሰው ጥረት ውጤት ሳይሆን እግዚአብሔር ራሱ ዘላለማዊ ምስጢሩን በቅዱስ መንፈሱ አማካይነት በሐዋሪያቱና በነቢያቱ በኩል ለቤተክርስቲያን በመግለጡ ምክንያት የተገኘ ነው፡፡ ይህ መገለጥ በርካታ ምስጢራትን የመመርመርና የተሰወሩ ነገሮችን ፈልፍሎ የማውጣት ጉዳይ አይደለም፡፡ ሚስጥሩ አንድ ነው፣ እርሱም እግዚአብሔር በክርስቶስ አይሁድንና አሕዛብን፣ በሰማይና በምድር ያሉትን ሁሉ ለመጠቅለል ማሰቡና ከአይሁድና ከአህዛብ ለተዋጁት ቅዱሳን አስቀድሞ በተስፋ የተሰጠውን፣ የዘላለም ርስት የሆነውን መንፈስ ቅዱስን እንዲካፈሉ መወሰኑና ይንንም በኢየሱስ ክርስቶስ ትንሳኤ አማካይነት መፈጸም መጀመሩ ነው፡፡

ከምዕራፍ 1 እስከ 3 ያለው ክፍል ይህንን ግዙፍ ሃሳብ በማስተዋወቅ ይጀምርና (1፡3) ይህንን ሕይወት የተሞላ ምሥጢር የገለጠልንን እግዚአብሔርን በማክበር ይፈፅማል (3፡21)፡፡ እግዚአብሔር ከዘላለም ዘመናት በፊት የወሰነውን፣ ከሁለት ሺህ ዓመታት በፊት በክርስቶስ ኢየሱስ የፈጸመውን ድንቅ ሥራና የሰጠንን ታላቅ ፀጋ እርሱ ራሱ ባይገልጥልን ኖሮ ውሱን በሆነው ሰዋዊ የአእምሮ አቅም እንዴት ሊታወቅ ይችል ነበር?

በመቀጠልም እግዚአብሔር ዓለም ሳይፈጠር አስቀድሞ እኛን በመምረጥ የጀመረውን ሥራ፣ በዘመን ፍፃሜ በሰማይና በምድር ያለውን ሁሉ በክርስቶስ በመጠቅለል እንዴት ወደ ሙላት እንደሚያደርሰው ይነግረንና፣ በዚህ ሥራ ውስጥ እኛ ተመልካች ብቻ ሳንሆን ተሳታፊ መሆናችንን በማንሳት እግዚአብሔር የፈቃዱን ምስጢር ሊያሳውቀን መውደዱን *"በክርስቶስ ለማድረግ እንደወደደ እንደ አሳቡ የፈቃዱን ምስጢር አስታውቆናልና፡፡"* 1፡9 በማለት ይነግረናል፡፡

ይህን መልዕክት ከሌሎቹ የጳውሎስ መልዕክቶች ሁሉ ልዩ ከሚያደርጉት ባሕሪያት አንዱ በፀሎት የተሞላ፣ በእንብርክክ የተፃፈ መሆኑ ነው፡፡ ሐዋርያው ለሚጽፍላቸው ከአሕዛብ ወገን ለሆኑ አማኞች ወደ እግዚአብሔር ያለውን ልመናና ምልጃ በጽሑፍ ይገልፃል፡፡ አነዚህም ምልጃዎች በዋነኛነት በመጀመሪያው ክፍል የሚገኙ ሲሆን በዋናነት ከመንፈሳዊ እውቀት ጋር የተያያዙ ናቸው ፡፡

> *"የክብር አባት የጌታችን የኢየሱስ ክርስትስ አምላክ እርሱን <u>በማወቅ</u> የጥበብንና የመገለጥን መንፈስ እንዲሰጣችሁ እለምናለሁ፡፡ 1:17*

የጥበብና የመገለጥ መንፈስ በአማኞች ውስጥ አድሮ የልቦና (የአእምሮ) ዓይኖችን በማብራት የሚያስገኘውን ውጤት ሲያመለክት በአንድ ቃል ". . . ታውቁ ዘንድ ነው፡፡" 1፡19 በማለት ይገልፀዋል፡፡



For more books www.amharicchristianbooks.com

እርሱ ራሱ ይህን በዓለም ዙሪያ ላሉ ሕዝቦች የሚገልጠውን ምስጢር እንዴት ሊያውቀው እንደቻለ ሲያስረዳ፡-

*“. . . ይህን ምስጢር በመግለጥ አስታወቀኝ” 3፡3*

በማለት ይጽፍና፡፡ የምስጢሩን ታላቅነትና አሁናዊነት ለማሳየት፡-

*“. . . ለቅዱሳን ሐዋርያትና ለነቢያት በመንፈስ አሁን እንደተገለጠ በሌሎች ትውልዶች ዘንድ ለሰው ልጆች አልታወቀም፡፡” 3፡5*

ይላል፡፡

አገልግሎቱንም በተመለከተ ለምን ሐዋርያ ሆኖ እንደተሾመ፣ ለምን ጌታ በኃይል በእርሱ እንደሚሠራ፣ ለምን ፀጋ ስጦታ እንደተሰጠው፣ ለምን የወንጌል አገልጋይ እንደሆነ በአንድ ቃል ሲያስረዳ፡-

*“ፍለጋ የሌለውን የክርስቶስን ባለጠግነት ለአሕዛብ እሰብክ ዘንድ፣ ሁሉንም በፈጠረው በእግዚአብሔር ከዘላለም የተሰወረው የምስጢር ሥርዓት ምን እንደሆነ ለሁሉ እገልጥ ዘንድ ...” (3፡8፣ 9)*

በማለት ይጽፋል፡፡ ይህንንም አባባል በአንድነት ስንጨምቅ የምናገኘው አሳብ “ማወቅ” እና “ማሳወቅ” ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

ለአሕዛብ የወንጌል ምስጢር ይገለጥላቸው ዘንድ የክርስቶስ እስር የሆነው ጳውሎስ አሁንም በዚያ የግዞት ቤት በሰማይና በምድር ያለ አባትነት ሁሉ በሚሰየምበት ዙፋን ፊት ተንበርክኮ ስለ ቅዱሳን ሲቃትት የሚለምነው

*“... የእናንተ ሥርና መሠረት በፍቅር ይፀና ዘንድ ከቅዱሳን ሁሉ ጋር ስፋቱና ርዝመቱ፣ ከፍታውም፣ ጥልቀቱም ምን ያህል መሆኑን ለማስተዋል ከመታወቅም የሚያልፈውን የክርስቶስን ፍቅር ለማወቅ ትበረቱ ዘንድ ...፡፡” (3፡18፣ 19) በማለት ነው፡፡*

በዚህ ልመና ውስጥ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ጉዳይ የተገለጠው እውነት ከመታወቅ እንደሚያልፍ፣ ይህንንም ለማወቅ ኃይል (ብርታት) እንደሚያስፈልግ፣ ማወቁም ኃይል እንደሚያስገኝ፣ ያም ኃይል የሚሠራ ኃይል እንደሆነ ለማሳየት ሐዋርያው ያደረገው ጥረት ነው፡፡

እንግዲህ የመጀመሪያውን ክፍል በተመለከተ “ማወቅ” ላይ ተንተርሶ የተጻፈ መሆኑን ለማሳየት ሞክሬአለሁ፡፡ ከዚህ የዘለቀውን የምናየው በሚቀጥሉት ክፍሎች ነውና ወደዚያው እናቅና፡፡



For more books www.amharicchristianbooks.com

# ምዕራፍ ፩
# ምስጋና

ኤፌ. ፲፡ 3 – 14[31]

ስለዚህ ክፍል በተለያዩ ዘመናት የኖሩ የተለያዩ ፀሐፍት ብዙ ብለዋል፡፡ አንዳንዶቹም የክፍሉን ውበት፣ የአፃፃፍ ረቂቅነትና መንፈሳዊ ኃይል ለመግለጽ በርካታ ስዕላዊ መግለጫዎችን ተጠቅመዋል፡፡ ከብዙዎቹ መሃል በጣም የመሰጠኝን አንዱን ብቻ ልጥቀስ፡፡ ፀሐፊው ዊልያም ሄንድሪክሰን ይባላል፡፡ ስለዚህ ክፍል የፃፈው አስተያየት እንዲህ ይነበባል፡፡ "ይህ ክፍል በበረዶ ከተሸፈነ ተራራ ላይ እየተንከባለለ የሚወርድ፣ በተንከባለለ ቁጥር መጠኑንና የመንደርደር ኃይሉን እየጨመረ እንደሚሄድ የበረዶ ኳስ ይመስላል" በማለት ጽፏል፡፡[32]

ይህን ክፍል በአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ስናነበው፤ "አራት ነጥብ የተሰኘው የዓረፍተ ነገር መቋጫ ሥርዓተ ነጥብ፣ አሥር ጊዜ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ በተጻፈበት የግሪክ ቋንቋ ግን ከዚህ የተለየ ገፅታ አለው፡፡ ከሌሎች የአዲስ ኪዳን ክፍሎች ባሻገር በግሪክ ቋንቋ ከተፃፉ በርካታ ጽሑፎች ልዩ የሚያደርገው በአንድ አራት ነጥብ የተፃፈ ረዥም ዓረፍተ ነገር መሆኑ ነው፡፡ ምንም እንኳ የኤፌሶን መልዕክት በውስጡ ስምንት ረዣዥም አረፍተ ነገሮች ቢያዝልም ፲፡ 3-14 የሰፈረው ዓረፍተ ነገር ለርዝመቱ አቻ አይገኝለትም፡፡[33] ይህ አንድ ወጥ ዐረፍተ ነገር በግሪኩ ቋንቋ "ዩሎጊያ" ወይም "ዮሎጌቶስ" ተብሎ ይጠራል፡፡ ቃሉ እያደር በእንግሊዘኛም ተወርሶ "ዮሎጂያ" በሚል መጠሪያ በዓለማችን የመግባቢያ ቃል ሆኖአል፡፡

ከጥንታዊ ግሪክ በቀጥታ የተወሰደ ይህ ቃል አንድን ሰው ስለሠራው ሥራ፣ ስለዋለው ውለታ፣ ስለፈፀመው ጀብድ በሕዝብ ፊት የሚወደስበት የምስጋና ቃል ነው፡፡ ጳውሎስም ኤፌሶን ከ፲፡3 አንስቶ ለእኛ ስለሰራው ታላቅና አስደናቂ ሥራ እግዚአብሔርን በሚያመሰግንበት ክፍል "ይባረክ" የሚለውን አሳብ ለመግለጽ የተጠቀመው ይህንኑ በግሪክ "ዮሎጊያ" የተሰኘውን ቃል ነው፡፡ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ያደረገውን ታላቅ ሥራና የሰጠውን ድንቅ በረከት በመንፈስ እየተረዳና በታደሰ አእምሮ እያስተዋለ፣ ብዕሩን ከብራናው ሳይነቅል በአንድ የብዕር

---

[31] ንባብዎን ከመቀጠልዎ በፊት ኤፌ. ፲፡ 3-14 ያለውን ቢያነቡ ይመረጣል፡፡

[32] Hendriksen, P. 72

[33] John F. Walvoord, Roy B. Zuck; The Bible Knowledge Commentary; SP Publications, Inc. 1983; Page 616



For more books www.amharicchristianbooks.com

ትንፋሽ ያለማቋረጥ እግዚአብሔርን ሲባርክ እናያለን፡፡

ምንም እንኳ ጳውሎስ ለተደራሲያኑ ሲል ይህን ክፍል በግሪክ ቋንቋ ቢጽፈውም ተግባራዊ የድርጊቱ ልማድ ግን በአይሁዳውያን ዘንድ ጥንት ጀምሮ የነበረና የኖረ ነው፡፡ እሥራኤላውያኑ በየሰንበቱና በየበዓሉ እግዚአብሔርን ሊያመልኩ ሲሰበሰቡ በሊቀ ካህኑ ወይም በአንድ በተመረጠ ሰው፣ ከፍ ባለ ድምጽ የሚቀርብ በዕብራይስጥ “ባራኾት” በመባል የሚታወቅ ውዳሴ ነው፡፡ አብርሃምን ከከለዳውያን ዑር ከማውጣቱና የከነዓንን ምድር ለዘሩ እንደሚሰጥ ተስፋ ከመግባቱ አንስቶ በዘመናት ሁሉ ለእስራኤል ያደረገውን በጎነት በመጥቀስ እግዚአብሔርን ይባርካሉ፡፡ ሆኖም አዲስ ኪዳን በተጻፈበት ዘመን በአለም ላይ በገነነው የግሪክ ቋንቋ "ዮሎጊያ" ተብሎ ተጠርቷል፡፡ ለመሆኑ "ዮሎጊያ" ምን ማለት ነው?

## ዩሎጊያ

በተወሰነ መጠን የአጠራሩ ድምፅና የትርጉሙ ቃና ቢለወጥም የግሪኩ "ዩሎጊያ" በእንግሊዘኛ ቋንቋ ተወርሷል፡፡ እንግሊዘኛ ተናጋሪዎቹ "ዩሎጂ" ይሉታል፡፡ ሰው ሲሞት በመቃብሩ ላይ ወይም ለመታሰቢያው በሚዘጋጅ መርሃ ግብር ላይ የሚነበብ ገድል ነክ መነባንብ ነው፡፡ ርዝመቱና ድምቀቱ እንደ ሟች ማንነት ይወሰናል፡፡ ይህን የእንግሊዘኛ ቃል ለመጀመሪያ ጊዜ የሰማሁት በዚህ አጋጣሚ ነበር፡፡

ወቅቱ በሰሜናዊው ንፍቀ ክበብ ለሚገኙ አገሮች የበጋ ወራት ነው፡፡ ገና ከማለዳው አየሩ እንደ እሳት ይጋረፋል፡፡ ከረዥም ወራት በረዶና ዝናብ በኋላ በደመቀችው ፀሐይ የተደሰተው ነዋሪ፣ ደራርቦት የነበረውን ካፖርት፣ የአንገት ልብስና የእጅ ጓንት ጣጥሎ በላዩ ላይ ስስ ጨርቅ ጣል አድርጎ ወዲህ ወዲያ ይጣደፋል፡፡ ይህችን ከሁለትና ከሦስት ወራት የማታልፍ ፀሐይ ለመሻማት የቸኮለ በሚመስል ስሜት፡፡

ለጥቂት ደቂቃዎች ባረፍኩበት ሆቴል መስኮት ውጭውን ስቃኝ ከቆየሁ በኋላ፣ በክፍሌ ውስጥ የነበረውን ቴሌቪዥን አበራሁ፡፡ በዚያን ዕለት በአሜሪካ ውስጥ የዜና ማሠራጫዎችን ቀልብ የሳበ ትልቅ ትዕይንት ነበር የገጠመኝ፡፡ አልጋዬ ላይ አረፍ አልኩና በትኩረት መከታተሌን ተያያዝሁ፡፡

የአሜሪካንን ሕዝብ ለአርባ ሰባት ዓመታት ሙሉ በታማኝነት ያገለገሉት፣ እሳቸው ብቻ ሳይሆኑ በቀኝ አክራሪዎች የተገደሉት፣ ሁለት ታላላቅ ወንድሞቻቸውን



For more books www.amharicchristianbooks.com

ጨምሮ መላ ቤተሰባቸው በአሜሪካ የሚታወቁትና የሚከበሩት፣ የቀድሞው የአሜሪካ ኘሬዘደንት የጆን ኤፍ ኬኔዲ ታናሽ ወንድም አድዋርድ (ቴድ) ኬኔዲ፣ ባደረባቸው ሕመም ከሰሞኑ አርፈዋል፤ የቀብር ሥነ-ሥርዓታቸው የሚፈፀምበት ቀን ነው፡፡

በሰው እጅ በመገደላቸው ምክንያት እንደ እሳቸው ዕድሜ ጠግበውና በሚወዷቸው ተከበው እስከ ወዲያኛው ለማሸለብ ያልታደሉትን የሁለቱን ታላላቅ ወንድሞቻቸውን ቁጭት ለመወጣት ይመስል አሜሪካውያን የቴድ ኬኔዲን የቀብር ሥነ-ሥርዓት ሞቅ ደመቅ አድርገውት ነበር፡፡ አስከሬኑን የያዘው መኪና 100 ኪሎ ሜትር ርቀት ሲጓዝ ቴሌቪዥኑ እየተከታተለ ያሳያል፡፡ በመሀሉም ጋዜጠኞቹ ስለ አንድ ነገር መላ ይመታሉ፣ ይከራከራሉ፡፡ የክርክራቸውም ነጥብ በሥነ-ሥርዓቱ ላይ የሴኔተር ቴድ ኬኔዲን «ዩሎጂያ» የሚያነብ ማነው? የሚል ነበር፡፡ አንዱ «የወንድሙ ልጅ እገሊት ናት ይላል» ሌላው ደግሞ «አይ የቅርብ ጓደኛው እገሌ ሊሆን ይችላል» እያሉ መላ ይመታሉ፡፡ ይህ ቃል ለእኔ ለመጀመሪያ ጊዜ የሰማሁት እንግዳ ቃል ነበርና ትኩረቴን ሳበው፡፡ የማይደርስ የለምና ከረዥም ጉዞ በኋላ በአርሊንግተን በሚገኘው የመቃብር ሥፍራ ደረሱ፡፡ የቀድሞ የአሜሪካን ፕሬዝዳንቶች፣ ምክትል ፕሬዝዳንቶች፣ በዓለም ዙሪያ ያሉ ታዋቂና ዝነኛ ሰዎች በተሰበሰቡበት ትልቅ አዳራሽ የቴድ ኪኔዲን "ዩሎጂያ" የሚያቀርበው ማን ይሆን? ተብሎ በጉጉት ይጠበቃል፡፡ ከጥቂት ቆይታ በኋላ በቅርቡ ለአሜሪካ ፕሬዘዳንትነት ቃለ መሃላ የፈፀሙት ባራክ አባማ ድንገት ተነሱ፡፡ ፕሬዘዳንቱ ወደ መድረኩ አቀኑና በተዋቡ ቃላት፣ ልብን በሚመስጥ ቃና፣ የቴድ ኬኔዲን ገድል፣ ለአሜሪካ ሕዝብ የዋሉትን ውለታ፣ አሜሪካ ዛሬ ያላትን ገጽታ እንድትይዝ በሴኔትና በኮንግረስ ውስጥ ያበረከቱትን አስተዋጽኦ፣ የሰሩትን ትሩፋት በማወደስ ምስጋናቸውን ያዘንቡት ጀመር፡፡

የእንግሊዘኛው"ዩሎጂ"በተወሰነ መጠን የፈለቀበትን የግሪክ ትርጉም ለመያዝ ቢጥርም በአንድ ምክንያት ለዛውን አጥቷል፡፡ ምክንያቱም የሚያወሳው ስለ ሕያው ሳይሆን ስለ ሙት ነው፡፡ "ዩሎጊያ" ግን ለዘላለም ሕያው ሆኖ ስለሚኖር ስለ እግዚአብሔር ማንነትና ሥራ፣ በእርሱ ሕያዋን ለሆኑ ፍጥረታቱ የሚታወጅ የበረከትና የምስጋና ቃል ነው፡፡

ምንም እንኳ መልዕክቱ የተጻፈው በግሪክ ቋንቋ ቢሆንም፣ የመልዕክቱ ሃሳብ ግን የመነጨው አይሁዳዊ ከሆነው ከጳውሎስ አዕምሮ በመሆኑ በእስራኤል የአምልኮ ሥርዓት ውስጥ ሥርክ ከሚቀርበው የመሥዋዕት ጢስ ጋር ወደ ሰማይ የሚያርገውን፣ የበረከት ቃል እንደሚያመለክት ጥርጥር የለውም፡፡ ከዚህም የተነሳ



For more books www.amharicchristianbooks.com

"ዩሎጊያ" እንዲያው በፀጋ የሰጠን ክብር ይመሰገን ዘንድ ለእኛ በሰራው ታላቅ ሥራ ምክንያት ለእግዚአብሔር የሚቀርብ የበረከት ቃል ነው ለማለት እንደፍራለን፡፡

## በረከት

ይህ አሥራ አራት ቁጥሮች በሸፈነ አንድ ወጥ ዐረፍተ ነገር ምሥጋናን የሚያውጅ ክፍል የሚያተኩረው በበረከት ላይ ነው፡፡ የባረከን ይባረክ ይላልና፡፡ ሆኖም የዚህን በረከት ምንነት ለማወቅና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትርጉሙን ለመረዳት ዘልቀን መመልከት ይኖርብናል፡፡ በረከት በተለያየ የሕብረተሰብ ክፍል የተለያየ ትርጉም እንዳለው እሙን ነው፡፡ ሆኖም በዘመናችን የወንጌል አማኞች ዘንድ ባብዛኛው “በረከት” ሲባል ወደ አእምሮአችን የሚመጡት ነገሮች ተመሳሳይ ናቸው ለማለት ያስደፍራል፡፡ አንድ አማኝ ኑሮው ከተቃናለት፣ ከተማረ፣ ሃብት ካገኘ፣ ትልቅ ቤት ከሠራ፣ ምቹ መኪና ከነዳ፣ ካገባ፣ ልጆች ከወለደ፣ ወደ ውጭ አገር የመሄድ እድል ካገኘ፣ ይልቁንም በዚያ ከኖረ፣ አገልግሎቱ ከሰፋለት፣ ብዙ ተከታይ ካፈራ፣ በየስፍራው እየተጋበዘ አገር ለአገር ከዞረ፣ ምን ያስፈልጋል ባጭር ቃል ተባርኳል፣ ማለት ነው፡፡ እነዚህ ነገሮች በራሳቸው አንዳች ክፋት የሌላቸው መልካም ነገሮች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን የምናጠናውን የኤፌሶንን መልዕክት በጥሞና ስንመረምር ዓይናችን ላይ የተደቀነውን መመልከቻ መነጽራችንን እንድንፈትሽ ግድ ከሚሉን እውነቶች ጋር መፋጠጣችን አይቀሬ ነው፡፡

በኤፌ. 1፡3 ላይ ጳውሎስ በረከትን ለመግለጽ የተጠቀመበት የግሪክ ቃል አስቀድመን እንዳየነው “ዮሎጊያ” የተሰኘውን ቃል ነው፡፡ ዮሎጊያ ማለት ደግሞ በቀጥታ ሲተረጎም ቃል ወይም ንግግር ማለት ነው፡፡ አንዱ ስለሌላው የሚናገረው የመልካምነት፣ የበጎነት፣ የምስጋና ቃል ነው፡፡

ይህ ክፍል እግዚአብሔር እንደባረከን እኛም እንደምንባርከው ይናገራል፡፡ “... የባረከን ... ይባረክ፡፡” ስለሚል፡፡ እንዲህ ከሆነ፣ እግዚአብሔር ባርኮቱን በተግባር ከመግለፁ በፊት ከዘላለም ዘመናት አንስቶ የባረከን በቃል ነው፡፡ እኛም መልሰን የምንባርከው በቃል ነው፡፡ ስለዚህ በረከት በቃል የሚመጣ፣ በቃል የሚተላለፍ መሆኑን ለመረዳት ብዙ ምርምር አይጠይቅም፡፡ ከዘፍጥረት 1 ጀምሮ እግዚአብሔር ሰውን፣ ሰውም ሌላውን ሰው የባረከባቸውን ክፍሎች ሁሉ በተናጠል እያወጣን ብንመለከት የምናገኘው በረከት በቃል ሲነገር ነው፡፡ ይህንንም የበረከት መጽሐፍ እንደሆነ በሚታወቀው በዘፍጥረት ውስጥ ለማየት እንሞክር፡፡

እግዚአብሔር አዳምና ሔዋንን ሲባርክ፡-



For more books www.amharicchristianbooks.com

*“እግዚአብሔርም ባረካቸው እንዲህም አላቸው . . . ፡፡” ዘፍ. 1፡28*

እግዚአብሔር ኖኅና ልጆቹን ሲባርክ፡-

*“እግዚአብሔርም ኖኅንና ልጆቹን ባረካቸው እንዲህም አላቸው . . . ” ዘፍ. 9፡1*

መልከ ጼዴቅ አብርሃምን ሲባርክ፡-

*“ባረከውም፡- . . . አለውም፡፡” ዘፍ. 14፡19፣20*

ላባና ባቱኤል ርብቃን ሲባርኩ፡-

*“ርብቃንም መረቁአት . . . አሉአት፡፡” ዘፍ. 24፡60*

ይስሐቅ ያዕቆብን ሲባርክ፡-

*“አባቱ ይስሐቅም ልጄ ሆይ ወደ እኔ ቅረብ ሳመኝም አለው፡፡ ወደ እርሱም ቀረበ ሳመውም የልብሱንም ሽታ አሸተተ፣ ባረከውም እንዲህም አለ፡- . . . ፡፡” ዘፍ. 27፡26-29*

እግዚአብሔር ያዕቆብን ሲባርክ፡-

*“እግዚአብሔርም ለያዕቆብ ከሁለት ወንዞች መካከል ከሶሪያ ከተመለሰ በኋላ እንደገና ተገለጠለት ባረከውም፡፡ . . . አለ፡፡” ዘፍ. 35፡9፣10*

ያዕቆብ ዮሴፍንና የዮሴፍን ልጆች ሲባርክ፡-

*“ያዕቆብም ዮሴፍን ባረከ እንዲህም አለ፡- . . . ፡፡” በዚያን ቀን እንዲህ ብሎ ባረካቸው ...፡፡” ዘፍ. 48፡15-20*

ያዕቆብ ልጆቹን ሲባርክ፡-

*“ያዕቆብም ልጆቹን ጠርቶ እንዲህ አለ፡- ... እነዚህም ሁሉ አስራ ሁለቱ የእስራኤል ነገዶች ናቸው፡፡ አባታቸው የነገራቸው ይህ ነው፣ ባረካቸውም እያንዳንዳቸውን እንደበረከታቸው ባረካቸው፡፡” ዘፍ. 49፡1፣ 28*

ወደ አዲስ ኪዳን ስንመጣም ምንም እንኳ ያው በረከት የሚለው ቃል በአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ በአንዳንድ ስፍራ “ምርቃት” ተብሎ ቢተረጎምም የሚያስተላልፈው እውነት ግን ተመሳሳይ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

*“እኔ ግን እላችኋለሁ በሰማያት ላለ አባታችሁ ልጆች ትሆኑ ዘንድ . . . የሚረግሙአችሁን መርቁ፡፡” ማቴ. 5፡44*

*“. . . ሲሰድቡን እንመርቃለን. . . ፡፡” 1ቆሮ. 4፡12*



For more books www.amharicchristianbooks.com

*"በእርሱ ጌታንና አብን እንባርካለን በእርሱም እንደ እግዚአብሔር ምሳሌ የተፈጠሩትን ሰዎች እንረግማለን፣ ከአንድ አፍ በረከትና መርገም ይወጣሉ፡፡" ያዕ. 3፡9*

*". . . ክፉን በክፉ ፈንታ ወይም ስድብን በስድብ ፈንታ አትመልሱ በዚህ ፈንታ ባርኩ እንጂ በረከትን ልትወርሱ ለዚህ ተጠርታችኋልና፡፡" 1ጴጥ. 3፡9*

## <u>በረከትና የተስፋ ቃል</u>

እግዚአብሔርም ዓለም ሳይፈጠር በፊት አንድ ጊዜ "በቃል" እንደባረከን ይህ መልዕክት ብቻ ሳይሆን በሐዋርያው ጳውሎስ እጅ የተፃፉ ሌሎች መልዕክቶች በአንድ ድምጽ ይመሰክሩልናል፡፡ ይህም ቃል እንኳን ሰው፣ ሰው የተበጀበት የምድር አፈር ሳይፈጠር የተነገረ ቃል ስለሆነ ሰው ተፈጥሮ ጊዜው ደርሶ እስኪፈፀም ድረስ "የተስፋ ቃል" በመባል ሲጠራ ኖሯል፡፡ ይህም ቃል፣ ቃል በቃል የተፃፈ ባይሆንም የተለያዩ ክፍሎችን በአንድነት ስንመለከት በተለያዩ መልዕክቶች ውስጥ ደምቆ እናገኘዋለን፡፡ ከነዚህም መካከል ጳውሎስ በወንጌል አብረውት ለሚሠሩት ለጢሞቴዎስና ለቲቶ በፃፋቸው ሁለት መልዕክቶች ውስጥ ብቻ ያሉትን እንኳ ብንመለከት ግልጽ ምስል ልናገኝ እንችላለን፡፡

*"በክርስቶስ ኢየሱስ እንደሚሆን የሕይወት ተስፋ በእግዚአብሔር ፈቃድ የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያ የሆነ ጳውሎስ ለተወደደ ልጁ ለጢሞቴዎስ፡፡" 2ጢሞ. 1፡1*

*"ይህም ፀጋ ከዘላለም ዘመናት በፊት በክርስቶስ ኢየሱስ ተሰጠን፣ አሁን ግን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ ታይቷል፡፡ እርሱ ሞትን ሽሮአልና እኔ ሰባኪና ሐዋርያ አሕዛብንም አስተማሪ እንድሆን በተሾምኩበት በወንጌል ሕይወትንና አለመጥፋትን ወደ ብርሃን አውጥቷል፡፡" 2ጢሞ. 1፡10፣ 11*

*"የእግዚአብሔር ባርያና የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያ የሆነ ጳውሎስ በእግዚአብሔር ለተመረጡት እምነት እንዲሆንላቸው በዘላለም ሕይወት ተስፋ እንደ አምልኮት ያለውን እውነት እንዲያውቁ የተላከ፡፡ ስለዚህም ሕይወት የማይዋሽ እግዚአብሔር ከዘላለም ዘመናት በፊት ተስፋ ሰጠ፡፡ በዘመኑም ጊዜ መድኃኒታችን እግዚአብሔር እንዳዘዘ ለእኔ አደራ በተሰጠኝ ስብከት ቃሉን ገለጠ፡፡" ቲቶ 1፡1-3*

ከእነዚህ ክፍሎች እንደምንረዳው በረከት ቃል የሚተላለፍ ነው፤ ቃሉም የተስፋ



For more books www.amharicchristianbooks.com

ቃል ነው፤ ተስፋውም የሕይወት ተስፋ ነው፤ የተሰጠውም ከዘላለም ዘመናት በፊት ሲሆን፣ የደረሰንም በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል ነው፡፡

ይህ ከዘላለም ዘመናት በፊት በአብ ተነግሮ፣ በክርስቶስ ኢየሱስ ተሰውሮ የኖረ ዓለማት ካለመኖር ወደ መኖር የመጡበት ሰበበ ፍጥረት፣ ለወራሾቹ የሰው ልጆች የታየው ሥጋ ሲሆን ነው፡፡[34] ለዚህም ነው ኢየሱስ ክርስቶስን የእግዚአብሔር ቃል ብለን የምንጠራው፡፡ ለእኛ የተገባ የሕይወት ቃል መገለጥ ነውና፡፡ ስለ እርሱ የተባለውም ምን እንደሆነ ዮሐንስ በአንደኛ መልዕክቱ እንዲህ በማለት ፍንትው ያደርግልናል፡፡

> *“. . . ሕይወት ተገለጠ አይተንማል እንመሰክርማለን ከአብ ዘንድ የነበረውንም ለእኛም የተገለጠውን የዘላለም ሕይወት እናወራላችኋለን፡፡” 1ዮሐ. 1፡2*

ከአብ ዘንድ በኢየሱስ ክርስቶስ ለሰው ልጆች የተገለጠው ሕይወት መንፈስ ቅዱስ ነው፡፡ ዮሐንስ ተገለጠልን የሚለው በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል እንጂ ኢየሱስ ራሱን ብቻ ማለቱ አለመሆኑን የሚያረጋግጥልን ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ ሲመጣ የሚታይና የሚዳሰስ ሆኖ መጥቷልና ልዩ መገለጥ እንደማያስፈልገው በቀላሉ መረዳት መቻላችን ነው፡፡ ምንም እንኳ ከአንድነታቸው የተነሳ ወልድን ከመንፈስ ቅዱስ ለይቶ መናገር አስቸጋሪ ቢሆንም፣ በዚህ ክፍል ውስጥ በሚታይ፣ በሚሰማ፣ በሚዳሰስ የወልድ አካልና ኑሮ ውስጥ የተገለጠው ሕይወት በአብ ዘንድ የነበረው፣ ከአብ የወጣው፣ በኢየሱስ ክርስቶስ ያደረው መንፈስ ቅዱስ መሆኑን ማየት እንችላለን፡፡

እንግዲህ የሕይወት ቃል አስቀድሞ በአብ የተነገረ፣ ለዘመናት ተስፋ ሆኖ የኖረ፣ በክርስቶስ ሞትና ትንሳኤ ወደ ብርሃን የወጣ፣ በመንፈስ ቅዱስ የሆነ የዘላለም ሕይወት መሆኑን ማየት እንችላለን፡፡ አብና ወልድ በሥላሴ ውስጥ የሚጫወቱት ልዩ የሆነ ድርሻ እንዳለ ሁሉ፣ አንዱም በሌላኛው ድርሻ ተደጋፊ እንደሆነ ሁሉ፣ መንፈስ ቅዱስም በስላሴ ውስጥ በዋነኝነት የሚጫወተው ልዩ ድርሻ ሕይወትነት ነው፡፡ ኢትዮጵያዊው የሥነ-መለኮት ሊቅ መሠረት ስብሐት ለአብ «ሥላሴ በተዋህዶ» በተሰኘው መጽሐፋቸው ከጥንታዊ የአበው መጽሐፍት የተገኘውን ትምህርት ተንተርሰው ሲጽፉ እንዲህ ብለዋል ፡-

> *"አብ በራሱና ለራሱ ልቡናና አዕምሮ ነው፡፡ ለወልድና ለመንፈስ ቅዱስም ልቡናቸው ነው፡፡ ያለ እርሱም ሌላ ልቦና የላቸውም፡፡*

---

[34] ዮሐ. 1፡1 እና 14 - 16



For more books www.amharicchristianbooks.com

*ወልድም በራሱና ለራሱ ቃል ነው፡፡ለአብና ለመንፈስ ቅዱስም ቃላቸው ነው፡፡ያለ እርሱም ለእነርሱ ሌላ ቃል የላቸውም፡፡ መንፈስ ቅዱስም በራሱና ለራሱ ሕይወት ነው፡፡ለአብና ለወልድም ሕይወታቸው ነው፡፡ ያለ እርሱም ለእነርሱ ሌላ ሕይወት የላቸውም፡፡" 35*

ከዚህ ምስጢረ ሥላሴን አብርቶ ከሚያሳይ ጽሑፍ የምንረዳውና ላነሳነው ርዕሰ ጉዳይ የሚጠቅመን ሃሳብ፣ አብ በወልድ በኩል ሊባርከን የገባው የተስፋ ቃል፣ አብና ወልድ ለማይቆጠር የዘላለም ዘመናት ሲካፈሉት የኖሩት ዘላለማዊ ሕይወት፣ እርሱም መንፈስ ቅዱስ መሆኑና ይህም የሕይወት መንፈስ በወንጌል ላመኑ ሰዎች ሁሉ እንዲያው በፀጋ መሰጠቱ ነው፡፡ እኛም ከዘላለም ዘመናት አንስቶ በተስፋ የተባረከንበት ቃል በክርስቶስ ሞትና ትንሳኤ የተፈፀመ፣ እየተፈፀመ ያለና ገናም የሚፈፀም የተስፋ ቃል ነው፡፡ እርሱም፡- ሰው የእግዚአብሔር ሕይወት የሆነውን፣ ከአብና ከወልድ የሚወጣውን መንፈስ ቅዱስን እንዲካፈልና በመንፈስ ቅዱስ ሕይወትነት አስቀድሞ መንፈሱ፣ ከዚያም በሂደት ነፍሱ፣ መጨረሻም በሙታን ትንሳኤ ሥጋው (አካሉ) ሕያው ሆነው በእግዚአብሔር ውስጥ ከእግዚአብሔር ጋር ለዘላለም እንዲኖር የተነገረው የእግዚአብሔር የተስፋ ቃል ነው፡፡

እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በ1898 ተወልዶ በ1963 ያንቀላፋው የአይሪሽ ተወላጁ ሲ ኤስ ሉዊስ "ሜር ክርስቲያኒቲ" በተሰኘ መጽሐፉ ይህንን ሃሳብ ለመግለጥ ሲጥር እንዲህ ብሏል፡ - "ከአብና ከወልድ የሕይወት ሕብረት ውስጥ የአንድነታቸው መሠረት ሆኖ የሚገለጥ ሕያው አካል አለ፤ ይህም አካል እርሱ ራሱ ከአብና ከወልድ ጋር አንድ የሆነና የሥላሴ ሶስተኛ አካል የሆነ መንፈስ ቅዱስ ነው፡፡ . . . እንግዲህ ይህ የአንድነትና የሕይወት ሕብረት ንድፍ ነው ለእኛም የተሰጠን፡፡ ይህም ሕይወታዊ እንቅስቃሴ ወይም ተውኔት ወይም ሥርዓት በእያንዳንዳችን ውስጥ ይቀጥላል፡፡"[36]

በዚህ ቃል ዓለማት ተፈጠሩ፣ ዘመኑ ሲደርስም ቃል ሥጋ ሆነና ወደ ዓለም መጣ፡፡ እርሱም በሞቱ ኃጢአትን ካስተሰረየና በትንሳኤው የአዲሱን ፍጥረት ጅማሬ ካበሰረ በኋላ የምሥራቹ ቃል በዓለም ናኘ፣ እኛም ቃሉን ባመንንም ጊዜ አብ መንፈስ ቅዱስን በመስጠት ባረከን፡፡ እውነተኛ በረከት ይሏል ይህ ነው!

እግዚአብሔር በክርስቶስ ኢየሱስ በሰማያዊ ስፍራ የባረከን ብዙዎቻችን እንደምናስበው “በመንፈሳዊ በረከቶች” አይደለም፡፡ “በመንፈሳዊ በረከት” እንጂ፡፡

---

[35] መሠረተ ስብሃት ለአብ፣ ሥላሴ በተዋህዶ፣ መካነ የሱስ ሴሚናሪ 1996

[36] Lewis, C. S. 1952 New York. Mere Christianity, Page 152 - 153



For more books www.amharicchristianbooks.com

ይህን ያልኩት ያለምክንያት አይደለም፡፡ ለብዙዎች "በመንፈሳዊ በረከት ተባረክን" ሲባል ፈጥኖ ወደ እዕምሮቸው የሚመጣው ልዩ ልዩ ፀጋዎች፣ ስጦታዎች፣ በረከቶች ወ.ዘ.ተ. ማግኘት ነው፡፡ ይህ ክፍል የሚነግረን ግን ሥጦታው አንድ እንደሆነና እርሱም ከአብና ከወልድ ጋር ሕላዌነት ያለው የሥላሴ አካል መንፈስ ቅዱስ መሆኑን ነው፡፡ ባጭር ቃል ሥጦታው "ነገሮች" ሳይሆኑ መንፈስ ቅዱስ ነው፡፡ እርሱም የዘላለም ሕይወት ነው፡፡ አብ በልጁ ስናምን የዘላለም ሕይወት የሆነውን መንፈስ ቅዱስን ሰጠን፡፡ ወንጌል ስለ እግዚአብሔር የሚናገር ብቻ ሳይሆን ራሱ እግዚአብሔር ነው፡፡ የወንጌል ሃሳብ በአጭሩ ሲቀመጥ "አብ ወደ አለም በላከው በልጁ ስናምን የዘላለም ሕይወት የሆነውን መንፈስ ቅዱስን ሰጠን" በሚለው ቃል ይጠቀለላል፡፡[37]

ሆኖም በሕይወት ስለተባረከን "ነገሮችን" አጣን ማለት አይደለም፡፡ መልካም ነገሮች ሁሉ በሕይወት ውስጥ አሉ እንጂ በመልካም ነገሮች ውስጥ ሕይወት አይኖርም፡፡ አንድ ሰው በምድር ላይ የሚገኙ ነገሮችን ማግኘት የሚችለው በሕይወት ሲኖር ነው፡፡ በሕይወት ከሌለ ግን እሱም ለእነዚያ ነገሮች፣ እነዚያም ነገሮች ለእርሱ ሞተዋልና ሊገናኙ አይችሉም፡፡ ልክ እንዲሁ በጊዜም ሆነ በዘላለም ውስጥ ያሉትን መልካም ነገሮች ለማግኘት የሚቻለው በሕይወት ውስጥ ሲኮን ብቻ ነው፡፡ ይህም ሕይወት መንፈስ ቅዱስ ነው፡፡

እግዚአብሔር የሕይወትን ተስፋ ቃል በመናገርና፣ በጊዜውም የሕይወትን መንፈስ በመስጠት አንድ ጊዜ ባረከን፡፡ ይህ እውነት የተገለጠልን እኛ ደግሞ እግዚአብሔርን ዘወትር ያለማቋረጥ እንባርከዋለን፡፡ የምንባርከውም የከንፈሮቻችን ፍሬ የሆነውን የምስጋናን ቃል በማቅረብ ነው፡፡ [38]

## የርስት በረከት

በረከት በአዲስ ኪዳናዊ ቋንቋ ምን እንደሆነ ለማየት ሞክረናል፡፡ ሆኖም ይህ በረከት እንዲሁ በአዲስ ኪዳን ዘመን ከሰማይ ዱብ ያለ ድንገተኛ ነገር አይደለም፡፡ አስቀድሜ እንዳልሁ ከዘላለም ዘመናት በፊት ተስፋ ተሰጥቷል፡፡ ይህም ተስፋ በዘመናት ውስጥ ለተለያዩ ሰዎች ተነግሯል፣ ታምኗል፣ ተጠብቆአልም፡፡ ከእነዚህም ውስጥ የመጀመሪያና አውራ የሆነው የእምነት አባት የተባለው አብርሃም ነው፡፡

[37] ዮሐ. 3፡16፤ ሮሜ 6፡21

[38] ዕብ. 13፡ 15



For more books www.amharicchristianbooks.com

እግዚአብሔር አብርሃምን ከአገሩ፣ ከዘመዶቹና ከአባቱ ቤት ለይቶ የጠራው ሊባርከውና በረከት ሊያደርገው እንደሆነ እሙን ነው፡፡ የባረከውም ተስፋን በመስጠት ሲሆን፣ ተስፋውም የዘርና የርስት ተስፋ ነበር፡፡ ይህ ተስፋ የሁለትዮሽ ፍቺ ያዘለ ነው፡፡ አንደኛው የምሳሌና የጥላ፣ ሌላኛው የእውነተኛ አካል፡፡ በቅርብ የነበረውንና በነዚያው ዘመናት የተፈፀመውን ጥላና ምሳሌ ስንመለከት ዘሩ ይስሐቅ፣ ርስቱም ከነዓን ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ይህም ተስፋ በመቶ ዓመቱ ይስሐቅን ከሣራ በመውለዱና ከአራት መቶ ሃምሳ ዓመታት[39] በኋላ የተስፋው ዘር ልጆች የሆኑት እስራኤላውያን በኢያሱ መሪነት የከነዓንን ምድር በመውረሳቸው ተፈጽሟል፡፡

ነገር ግን ተስፋው ከምሳሌና ከጥላ ባሻገር እውነተኛ አካል ያለው በመሆኑ እውነተኛው የተስፋው አካል ብዙ ዘመናትን ቆጥሮ ተፈጽሟል፤ በመፈፀምም ላይ ነው፡፡ በዚህ የተስፋው እውነተኛ አካል ውስጥ ዘሩ ክርስቶስ ሲሆን፣ ርስቱም የዘላለም ሕይወት የሆነው "መንፈስ ቅዱስ" ነው፡፡

ተስፋው በይስሐቅ መወለድና በእስራኤላውያን ከነዓንን መውረስ ተፈጽሞ የተጠናቀቀ ቢሆን ኖሮ የዕብራውያን መልእክት ፀሐፊ የእምነት አባቶችን ገድል በዘከረበት ምዕራፍ መደምደሚያ ላይ፡ -

> *"እነዚህ ሁሉ አምነው ሞቱ፣ የተሰጠውን የተስፋ ቃል አላገኙምና ዳሩ ግን ከሩቅ ሆነው አዩትና ተሳለሙት . . . እነዚህ ሁሉ በእምነታቸው ተመስክሮላቸው ሳለ የተሰጠውን የተስፋ ቃል አላገኙም . . . ፡፡" (ዕብ. 11፡13፣ 39)*

ባላለን ነበር፡፡ ስለ ርስቱም፡-

> *"ኢያሱ አሳርፎአቸው ኖሮ ቢሆንስ ከዚያ በኋላ ስለሌላ ቀን ባልተናገረ ነበር፡፡" (ዕብ. 4፡8)*

ባላለንም፡፡ ለአብርሃም በተሰጠው የበረከት ተስፋ ውስጥ የተስፋው ቃል ወራሽ፣ ቀዳሚ ተምሳሌት ሆኖ የምናገኘው "ይስሐቅ" ወይም ከእርሱ ዘር የተወለዱት የእስራኤል ልጆች ሳይሆኑ ክርስቶስ መሆኑን ሐዋርያው ጳውሎስ ሲያስረዳ፡-

> *"ለአብርሃምና ለዘሩም የተስፋው ቃል ተነገረ፡፡ ስለብዙዎች እንደሚነገር፡- ለዘሮቹም አይልም፣ ስለ አንድ እንደሚነገር ግን፡-*

[39] ይህ የእሥራኤል ልጆች በግብፅ በባርነት የቆዩበት የዘመን ቁጥር በተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱ ክፍሎች በተለያየ ቁጥር የተቀመጠ ሲሆን እንደየ ምንባቡ አመቺነት ተጠቅሜበታለሁ፡፡ ዘፍ. 15፡13 አራት መቶ ዓመታት ተብሎ የተጻፈ ሲሆን፣ በዘፀ. 12፡40 እና ገላ. 3፡ 17 ላይ አራት መቶ ሰላሳ ተብሎአል፡፡



For more books www.amharicchristianbooks.com

*ለዘርህም ይላል እርሱም ክርስቶስ።” ገላትያ 3፡16*

በማለት ግልጽ ያደርገዋል፡፡ የርስቱም ተስፋ ግዑዝ ምድር ሳይሆን የዘላለም ሕይወት የሆነው መንፈስ ቅዱስ መሆኑን፡-

> *“የመንፈስን ተስፋ በእምነት እንድንቀበል የአብርሃም በረከት ወደ አሕዛብ በኢየሱስ ክርስቶስ ይደርስላቸው ዘንድ።” (ገላ. 3፡14)*

በማለት ያስረዳል፡፡ በኤፌሶን 1 ላይ እንደምናየው ተስፋው የርስት ቢሆንም ርስቱ ግን በመካከለኛው ምሥራቅ የሚገኘው የፍልስጤም ምድር ሳይሆን ለዘላለም መኖሪያ የሆነው መንፈስ ቅዱስ መሆኑን፡-

> *“. . . በተስፋው መንፈስ በመንፈስ ቅዱስ ታተማችሁ እርሱም የርስታችን መያዣ ነው . . . ።” ኤፌ.1፡13*

ይለናል፡፡ መንፈስ ቅዱስ የርስታችን መያዣ ነው፡፡ ነገር ግን መያዣው አንድ፣ ርስቱ ሌላ እንደሆነ ልናስብ አይገባም፡፡ በአገራችን እንደ ተለመደው መያዣ ስንሰጥ ቀኑ ሲደርስ የምንሰጠውን ሙሉ ክፍል ውስኑን እንሰጣለን እንጂ ቀብዱ አንድ፣ መያዣው ሌላ አይሆንም፡፡ ስለዚህ የርስታችን መያዣ ሆኖ የተሰጠን መንፈስ ቅዱስ ራሱ ርስታችን ሲሆን አሁን ያገኘነው ግን እንደ መያዣ በከፊል ነው፡፡ ይህም የሆነበት ብቸኛ ምክንያት አሁን ድነትን በማግኘት መንፈስ ቅዱስን የተካፈለው መንፈሳችን ስለሆነና ሥጋችን መንፈስ ቅዱስን ለዘላለም በሕይወት የሚያኖር ርስት አድርጎ የሚካፈለው በቤዛ ቀን ስለሆነ ነው፡፡

ጳውሎስ በመቀጠል ርስቱ መንፈሳዊ መሆኑን ለማስረዳት፡-

> *“ይህም የልባችሁ አይኖች ሲበሩ የመጥራቱ ተስፋ ምን እንዲሆን በቅዱሳንም ዘንድ ያለው የርስት ክብር ባለጠግነት ምን እንዲሆን . . . ታውቁ ዘንድ ነው።” ኤፌ. 1፡18*

በማለት ያረጋግጥልናል፡፡ ርስቱ ምድር የሚገኝ ቢሆን ኖሮ ለማየት የሥጋ ዓይን እንጂ የልብ ዓይን አያስፈልገውም ነበር፡፡ አሁን ግን ከክርስቶስ ዘር ዳግመኛ በመወለድ የዘላለሙ ርስት የመንፈስ ቅዱስ ተካፋዮች ሆነናል፡፡ ምንም እንኳ ይህን ክቡር ተስፋ በሥጋ የምንወርሰው በመጨረሻው ቀን በአካለ-ትንሳኤ ቢሆንም አሁን በመንፈስ ወርሰነዋል፣ በእርሱም እንኖራለን፣ እርሱም በእኛ ይኖራል፡፡ ዮሐንስ በመልዕክቱ፡-

> *"ከመንፈሱ ስለሰጠን፣ በእርሱ እንድንኖር፣ እርሱም በእኛ እንዲኖር በዚህ እናውቃለን።" 1ዮሐ. 4፡13*

እንዳለው፡፡ ዘወትር “ስሞት ወደ ጌታ እሄዳለሁ፣ ከእርሱም ጋር ለዘላለም



For more books www.amharicchristianbooks.com

እኖራለሁ፡፡" እንላለን፡፡ እንዲህ በማለታችን እግዚአብሔርን እንደ "ኗሪ" ብቻ እያሰብን መሆኑን ንግግራችን ይገልጣል፡፡ አዎን እግዚአብሔር ኗሪ ነው፣ ለዘላለም ኗሪ፡፡ ነገር ግን ኗሪ ብቻ ሳይሆን መኖሪያም ነው፡፡ ይህን የምለው እግዚአብሔር ኗሪ እንጂ መኖሪያ መሆኑ በብዙ አማኞች አንደበት ስለማይደመጥ ነው፡፡ ሆኖም እግዚአብሔርን በማወቅ ጉዞአችን ውስጥ መኖሪያነቱን መገንዘባችን ብዙ እመርታ እንደሚያመጣልን ምንም ጥያቄ የለውም፡፡

ሐዋርያው ጳውሎስ ለአቴና ሰዎች የእግዚአብሔርን መኖሪያነት ሲተርክ፡-

> *"ከእናንተ ከባለ ቅኔዎች አንዳንዶች እኛ ደግሞ ዘመዶቹ ነንና ብለው እንደተናገሩ፡- በእርሱ ሕያዋን ነንና በእርሱ እንኖራለን እንንቀሳቀስማለን፡፡" ሐዋ. 17፡28*

> ብሎአል፡፡ ጌታም "በእኔ ኑሩ . . . ፡፡" (ዮሐ. 14) በማለት ጥሪ ሲያቀርብ መኖሪያነቱን እየገለፀ ነው፡፡ በብሉይ ኪዳን ዘመን ርስት በመባል የሚታወቀው ምድሩ ቢሆንም፣ ዳዊት ግን "እግዚአብሔር የርስቴ እድል ፈንታና ጽዋዬ ነው፡፡" (መዝ.16፡5) በማለት የእግዚአብሔርን ርስትነትና መኖሪያነት ያውጃል፡፡ ይህም ርስት፣ አብ በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስናምን ለዘላለም በውስጡ እንኖር ዘንድ፣ በውስጣችንም ይኖር ዘንድ የሰጠን መንፈስ ቅዱስ ነው፡፡ በመንፈስ ቅዱስ ውስጥ ከኖርን፣ በአብና በወልድ ውስጥ እንኖራለን። አብና ወልድም በእኛ ውስጥ ይኖራሉ፡፡

> *"ከመንፈሱ ስለ ሰጠን በእርሱ እንድንኖር እርሱም በእኛ እንዲኖር በዚህ እናውቃለን፡፡" 1ዮሐ. 4፡13*

ተብሎ እንደተፃፈ ነው፡፡

ስለዚህ በረከታችን ሃብት ንብረት፣ ክብር ፣ሹመት ብቻ ሳይሆን ዘላለም በውስጡ እንድንኖር፣ እርሱም በእኛ እንዲኖር የተሰጠን መንፈስ ቅዱስ ነው፡፡ ለዚህ አይደል ሐዋርያው ጳውሎስ ያንተ ነን፣ የአጵሎስ ነን፣ እያሉ ለሚከራከሩት የቆሮንቶስ አማኞች፡-

> *"ስለዚህ ማንም በሰው አይመካ፡፡ ነገር ሁሉ የእናንተ ነውና ጳውሎስ ቢሆን፣ አጵሎስም ቢሆን፣ ኬፋም ቢሆን፣ ዓለምም ቢሆን፣ ሕይወትም ቢሆን፣ ሞትም ቢሆን፣ ያለውም ቢሆን፣ የሚመጣውም ቢሆን፣ ሁሉ የእናንተ ነው፣ እናንተም የክርስቶስ ናችሁ ክርስቶስም የእግዚአብሔር ነው፡፡" 1ቆሮ. 3፡21-23*

ያለው። እግዚአብሔር በክርስቶስ ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ ባርኮናል፡፡ ሲባርከንም ያስቀረው አንዳች ነገር የለም፡፡ መንፈስ ቅዱስን ሲሰጠን በመንፈስ ቅዱስ ውስጥ



For more books www.amharicchristianbooks.com

ያለው መንፈሳዊ በረከት ሁሉ በአንድነት ተሰጥቶናል፡፡

ርስት በምድር ተምሳሌትነት እንደምናየው በሕይወት ለመኖር የሚያስፈልግ ሁሉ ያለበት መኖሪያ ነው፡፡ ስጋችን የተበጀው ከምድር አፈር ነው፣ የምንበላው ከምድር የበቀለውን ነው፣ የምንለብሰውም እንዲሁ ከምድር የሚገኝ ነው፡፡ የምንጠለልበት ቤት የተንጣለለ ቪላ ይሁን፣ ደሳሳ ጎጆ፣ የተሠራው ያው ከምድር በተገኙ ነገሮች ነው፡፡ የምንቀባው ቅባት፣ የምናጌጥባቸው ጌጦች፣ የምንጠቀምባቸው ቁሳቁሶች ሁሉ ከመሬት ናቸው፡፡ ከመሬት ያልሆነ ምን አለ? እኛም ስናረጅና ስጋችን ነፍሳችንን ማሳደር ሲሳነው ተመልሰን የምንገባው ወደተገኘንበት ምድር ነው፡፡ ታሪካችን ተጀምሮ እስኪጨረስ ድረስ ርስትና መኖሪያ ተደርጎ ከተሰጠን ከምድር ጋር በጽኑ የተቆራኘ ነው፡፡ ታዲያ ይህ ርስት ጉልበት እስካለን ድረስ፣ ራሱን የሚመግበን፣ የመኖር አቅም ሲያንሰን ደግሞ እኛኑ የሚመገበን የርስት ዓይነት ነው፡፡ ለዚህ አይደል የተስፋይቱን ምድር ከሰለሉት መካከል አስሩ *"እኛ ዞረን የሰለልናት ምድር የሚኖሩባትን ሰዎች የምትበላ ምድር ናት . . . ፡፡" (ዘኍ. 13፡32)* ያሉት፡፡

ይህ የዘላለም መኖሪያ የሆነ በክርስቶስ ኢየሱስ ከአብ ዘንድ የተሰጠን መንፈስ ቅዱስ ግን ሁለንተናችንን ለዘላለም በክብር የሚያኖር የሕይወት ኃይል ነው፡፡ ለዘላለም ራሱን ይመግበናል እንጂ መቼም አይመገበንም፡፡

«ታዲያ በረከቱ የመንፈስ ሕይወት ሆኖ ሳለ፣ በረከትን ከቁሳቁስ ጋር ማዛመዱ ከወዴት መጣ? መባረክ ማለት በምድራዊ ሃብት መበልፀግ ብቻ እንደሆነ አድርገው በየመድረኩ የሚያስተጋቡት አያሌ ሰባኪዎችስ የሚያኾነኩት ጥቅስ ከወዴት አመጡት?» የሚል ጥያቄ ቢነሳ አግባብነት ያለው ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱሳችን በዋነኝነት ሁለት ኪዳኖችን ያዘለ ነው፡፡ ብሉይና አዲስ፡፡ ሆኖም መዘንጋት የሌለብን አንድ ቁምነገር፣ አዲስ ኪዳን ከውስጡ የወጣበት ብሉይ ኪዳን በውስጡ የተሰወረ ኪዳን መኖሩን ነው፡፡ ያም ኪዳን ከዘላለም ዘመናት የጀመረ ሆኖ ለአብርሃምና ከእርሱም በኋላ ለተነሱ ነቢያት የተነገረው የተስፋው ኪዳን ነው፡፡ ሌላኛው ደግሞ ይህ የተስፋ ኪዳን ከተገባ ከአራት መቶ ሰላሳ ዓመታት በኋላ የመጣ እግዚአብሔር በሥጋ ከሆነው ከእሥራኤል ጋር በሙሴ መካከለኛነት፣ በመላዕክት ሥርዓት የገባው የሕግ ኪዳን ነው፡፡

የሕጉ ኪዳን ዋነኛ ዓላማ የእስራኤል ልጆች ተስፋ ተደርጎ ወደተሰጣቸውና የሰማያዊው ምሳሌ ወደ ሆነው ግዑዝ ርስት ሲገቡ እንዲኖሩበት የተሰጠ የሥጋ ሥርዓት ነው፡፡ ታዲያ እስራኤላዊያኑ በዚህ ግዑዝ ርስት ላይ እንደ ሕጉ ከሄዱ



For more books www.amharicchristianbooks.com

እንደሚያገኙት የተነገረላቸው በረከት አለ፡፡ ይህም በረከት እንደ ርስቱ ሁሉ ግዑዝ ነው፡፡ ይህንንም በረከት በዘዳግም 28 ላይ ተንጣሎ እናገኘዋለን፡፡ በረከቱም፣ በማኅበረሰብ ዘንድ ተቀባይነትና የበላይነት ፣ በጦር ሜዳ ድልን የማግኘት፣ በልጆች፣ በእርሻ፣ በከብት፣ በቦሃቃ፣ በጎተራ ፍሬን የማግኘት በረከቶች መሆናቸውን መመልከት እንችላለን፡፡ ሆኖም እነዚህ በረከቶች በሁኔታ ላይ የተመሠረቱ፣ ሕጉን በመጠበቅ ብቻ የሚገኙ በረከቶች ሲሆኑ በተቃራኒው የሚያመጡት ርግማን ለመጥራት እንኳ የሚዘገንን የትዬ ለሌ ነው፡፡ መጠኑን ስንቃኝ በረከቱ በ14 ቁጥሮች የተቋጨ ሲሆን፣ ርግማኑ ግን ከቁጥር 15 አንስቶ እስከ 68 የሚዘልቅ በ54 ቁጥሮች የታጀበ ነው፡፡ ሌላው ችግር ሕጉ በራሱ ቅዱስ ቢሆንም እንኳ እንዲፈጽመው የተሰጠው እስራኤል ሕጉን ሊፈጽም የሚታገለው ለኃጢአት በተሸጠ ሥጋ ስለሆነ ሕጉ በብቃት የማይፈፀም፣ በረከቱም በሙላት የማይበላ አድርጎታል፡፡

እንግዲህ የኪዳኑን መለወጥ፣ የሕጉን መቀየር፣ የበረከቱንም ከጥላ ወደ አካል፣ ከምሳሌ ወደ እውነት መሻገር የማያስተውሉ ሰዎች አዲስ ኪዳን የብሉይ ኪዳን ቅጥያ እንደሆነ በማሰብ ለአዲስ ኪዳን አማኞች እስራኤላውያኑ እንኳ በቅጡ ሊበሉት ያልቻሉትን የብሉይ በረከት ሊግቱ ይወዳሉ፡፡ ምንም እንኳ እነዚያ የምድር በረከቶች ዛሬም እንደሚያስፈልጉን እሙን ቢሆንም፣ በሥራና በትጋት የምናገኛቸው የምድር ነዋሪዎች ሁሉ የጋራ ሃብት እንጂ፣ በክርስቶስ የምንወርሳቸው የመንፈስ ትሩፋት አይደሉም፡፡ ስለዚህ በክርስቶስ ኢየሱስ ሞትና ትንሳኤ የተመረቀው አዲስ ኪዳን የተስፋው ኪዳን ፍፃሜና የአሮጌው ኪዳን ሽረት እንጂ የብሉይ ኪዳን ቅጥያ አለመሆኑን መገንዘብ አስፈላጊ ነገር ነው፡፡

በምንኖርበት የአዲስ ኪዳን ዘመን ለእውነተኛ የእግዚአብሔር ልጆች የበረከት መለኪያ ምድራዊ ሳይሆን ሰማያዊ፣ ሥጋዊ ሳይሆን መንፈሳዊ ነው፡፡ በምድር ያሉ ነገሮች አያስፈልጉንም ማለት አንችልም፡፡ አዎን በምድር ያሉ መልካም ነገሮች ሁሉ ያስፈልጉናል፡፡ የተፈጠሩትም እንጠቀምባቸው ዘንድ ለእኛ ነው፡፡ ነገር ግን በእግዚአብሔር ፊት የበረከት መለኪያ አይደሉም፡፡[40]

ከጥንት ጀምሮ እንደምናየው መንፈሳዊው ዓለም ግዑዙን ይገዛል፡፡ መንፈሳዊው ግዑዙን ይገዛል እንጂ፣ ግዑዙ መንፈሳዊውን ገዝቶ አያውቅም፡፡ እኛም የተባረክነው በመንፈሳዊው ነው፡፡ ስለዚህ በበላይነት ገዥ የሆነው ወገን እንጂ በበታችነት ተገዢ የሆነው ወገን አይደለንም፡፡ ገዥነት ባለን ሀብት መጠን የሚለካ

[40] ሉቃስ 12፡15



For more books www.amharicchristianbooks.com

አይደለም፡፡ አንድ ሰው ብዙ ገንዘብ ስላለው ገንዘብን እየገዛ ነው ማለት አይደለም፡፡ ምናልባት በገንዘብ እየተገዛ ሊሆን ይችላል፡፡ ገንዘብ በዓለም ላይ ስንት ባሪያዎች እንዳሉት ቆጥሮ መዝለቅ አይሞከርምና፡፡ በረከት መግዛት እንጂ መገዛት አይደለም፡፡ መግዛትም በመሰብሰብና በማከማቸት የሚገለጥ ሳይሆን አመጽን እምቢ በማለት፣ ገንዘብን መሳሪያው አድርጎ ዓለምን የሚያሽከረክረውን የዚህን ዓለም ገዢ መቃወምና በገንዘባችን የማይጠፋ ዘላለማዊ ሥራ መሥራት መቻል ነው፡፡ ይህ ዓይነቱ ኑሮ ደግሞ በመንፈስ ሕይወት እንጂ በሥጋ ሕይወት አይታሰብም፡፡

እንግዲህ በክርስቶስ ኢየሱስ በሰማያዊ ስፍራ የተባረክነው የዘላለም ሕይወትና የዘላለም ርስት የሆነው የመንፈስ ቅዱስ በረከት፣ ከቁሳቁስ በላይ፣ ከዚህም ፍጥረት በላይ እጅግ የላቀ የሕይወት በረከት እንደሆነ ልንገነዘብ ይገባል፡፡

ሌላው ይህ ክፍል የሚያስተምረን ወሳኝ ጉዳይ ይህ በረከት ገና ወደ ፊት የሚሰጥ ተስፋ ሳይሆን ለሚያምኑ ሁሉ የተሰጠ መሆኑን ነው፡፡ ሐዋርያው በኤፌሶን ያሉ አማኞች እንዲባረኩ እየለመነ አይደለም፡፡ ይልቁንም በመግቢያችን ላይ እንዳነበብነው ስለ በረከቱ እግዚአብሔርን እያመሰገነ ነው፡፡ ይህን የተረዳ ሰው እግዚአብሔርን ያለማቋረጥ ያመሰግናል እንጂ "ባርከኝ" ብሎ አይጠይቅም፡፡ የቃሉን የጊዜ ግሥ ብንመለከት ያለፈ ጊዜ እንጂ የአሁን ወይም የወደፊት ሆኖ አናገኘውም፡፡ በቃ! እግዚአብሔር አንድ ጊዜ ባርኮናል፡፡ እግዚአብሔር ይህን በረከት እንዲገልጥልንና እንዲገለጥብን እንለምናለን እንጂ እንዲባርከን አንጠይቅም፣ ልንጠይቀውም አይገባም፡፡ ይህን በረከት ያላገኙ ኢ-አማንያን ቢሆኑም እንኳ በረከቱን የሚያገኙት በልመና ሳይሆን፣ በረከቱን ለመካፈል ብቁ ይሆኑ ዘንድ የሞተላቸውንና ከሙታንም የተነሳውን ኢየሱስ ክርስቶስን የሕይወታቸው ጌታ አድርገው በመቀበል ነው፡፡ ያኔ በረከቱ በቅጽበት የእነርሱም ይሆናል፡፡

በርግጥ ዛሬ በሚያሳዝን መልኩ በየመድረኮቻችን የምንሰማቸው፣ ለዚያውም በአማኞች ጆሮ የሚያስተጋቡት ድምፆች በመንፈሳዊ በረከት እንደተባረክን የሚገልፁ ሳይሆኑ ገና እንደምንባረክ ተስፋ የሚሰጡ መሆናቸው የሚያሳዝን ብቻ ሳይሆን ልብ የሚሰብር ነው፡፡ ምድራዊውም እንኳ ቢሆን በሥራ የሚገኝ እንጂ በተስፋና በእምነት የሚጠበቅ አለመሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ በስፋት ያስተምረናል፡፡ ብዙ አማኞች ምድራዊ ሃብትን በተስፋ ሲጠብቁ፣ ተስፋ ምን እንደሆነ የማያውቁ ሌሎች በትጋት እየሠሩ እየወረሱት እንደሆነ ማየት ለምን እንደተሳነን ቆም ብለን ልንጠይቅ ይገባል፡፡ ደግሞስ ምድራዊውን በረከት ምንም ያህል ብናግበሰብሰው



For more books www.amharicchristianbooks.com

ለሌሎች በማካፈል የምንደሰትበት ካልሆነ በቀር ስንቱን እንበላዋለን? ስንቱንስ እንለብሰዋለን? የሚያስፈልገን እንደሆነ ጥቂት ነው፡፡ ብዙ ስላለን ከልክ በላይ ልንበላ፣ ከልክ በላይ ልንተኛ፣ ከልክ በላይ ልንኖር አንችልም፡፡ በእርግጥ ለሥጋ ምኞታችን የምንኖር ከሆነ፣ እንኳን ጥቂቱ በዓለም ያለው ሁሉ ተሰብስቦ የምኞት ጉድጓዳችንን ሊሞላ አይችል ይሆናል፡፡ ዓይኑ ለሚሰስት ሥጋዊ ሰው ዓለም ራሷ ግጦሽ ሆና ብትሰጠው መች ይጠግብና!!

ሕይወት በሆነው በመንፈስ ቅዱስ እንደተባረከ የገባው ሰው ግን ስለምድሩ "ኑሮዬ ይበቃኛል" ይላል፣ ስለ ሰማያዊው ደግሞ በመንፈስ ድሃ ሆኖ የትናንቱን እየረሳ በፊቱ ያለውን ለመያዝ ይዘረጋል፡፡

ኤፌሶን 1፡3 ላይ የሚገኘው አሳብ በተቀሩት የመልዕክቱ ክፍሎች ውስጥ በየሐረጎችና አንቀጾቹ ተሰናስሎ የምናገኘው መሪ ሀሳብ በመሆኑ ሰፊ ሽፋን ሰጥተን ተመልክተነዋል፡፡ ሆኖም ቀደም ብዬ እንደገለፅኩጽ 1፡3-14 በአንድ የብዕር ትንፋሽ የተፃፈ ትልቅ ዓረፍተ ነገር ነውና ነጣጥለን ልናየው ስለማይገባ እንደፍጥረቱ በአንድነት እንመለከተዋለን፡፡

በኤፌሶን 1፡4-14 ተዘርዝረው የምናገኛቸው አሳቦች ከ1፡3 የተለዩ ወይም ቀጣይ የሆኑ በረከቶች አይደሉም፡፡ ፀሐፊው በ1፡3 ላይ ያወጀውን በረከት እየተነተነልን ነው፡፡ አስቀድመን በረከቱ ከአብ ዘንድ በክርስቶስ አማካይነት የተሰጠን መንፈስ ቅዱስ ነው ብለናል፡፡ ሆኖም ይህ በረከት በቅጽበት የደረስንበት፣ በድንገት ዘው ብለን የገባንበት ሳይሆን ዘላለምንና ዘመናትን አቋርጦ የመጣ፣ በእግዚአብሔር በኩል ትልቅ መስዋዕትነት የጠየቀ፣ ግዙፍ የግልጠትና የማሳወቅ ሥራ የተሠራበት መሆኑን ሐዋርያው ከቁ. 4 እስከ 14 ሂደቱን በአስገራሚ ጥበብ ይተነትንልናል፡፡

## ለርስት መመረጥ

> *"ዓለም ሳይፈጠር በፊቱ ቅዱሳንና ነውር የሌለን በፍቅር እንሆን ዘንድ በክርስቶስ መረጠን፡፡" ኤፌ. 1፡4*

ለዘላለም እንኖርበት ዘንድ ልንወርሰው ለጀመርነው ርስት የተመረጥነው ዓለም ሳይፈጠር አስቀድሞ እንደሆነ ይህ ክፍል ይነግረናል፡፡ ይህም ምርጫው ከራሱ ከመራጩ እንጂ ከእኛ ሥራና ማንነት የመነጨ አለመሆኑን ያስገነዝበናል፡፡ እግዚአብሔር ከራሱ፣ በራሱ፣ ለራሱ መረጠን እንጂ እንደ ዲሞክራሲያዊ ምርጫ በአስመራጭ ኮሚቴ አልመረጠንም፡፡ በእርግጥ በርካታ የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት በዚህ ክፍል ላይ ተመስርተውና በሁለት ጎራ ተከፍለው ሲከራከሩ



For more books www.amharicchristianbooks.com

ኖረዋል፡፡[41] አንዱ ጎራ «አስቀድመን ተወስነናል» ሌላው ጎራ ደግሞ «አይደለም የዳንነው እኛ ስላመንን እንጂ አስቀድሞ የተወሰነ የለም» በማለት የአስተሳሰቦቹ ፊታውራሪ የሆኑትን ካልቪንንና አርመንን ተተግነው ሲከራከሩ ዘመናት ተቆጠረዋል፣ እስካሁንም የተገኘ እልባት ስለመኖሩም መረጃ የለኝም፡፡ ቢኖረኝም በዚህ ጽሑፌ ይህንን ዘመን ጠገብ፣ ጉንጭ ብቻ ሳይሆን ብዕር አልፋ ክርክር ልነካካው አልሞክርም፡፡ ምክንያቱም ርዕሰ-ክርክሩ በኋላ የመጣ እንጂ የፀሐፊውም ሆነ የተደራሲያኑ ዋና ትኩረት እንደነበር አላስብም፡፡ ይልቅ በክፍሉ ውስጥ የሚታየውን የሕይወትን ረሃብ የሚያስታግሰውን ምግብ ሙዳ ሙዳውን እየቆረጥሁ ባካፍል ይቀናኛል፡፡

እግዚአብሔር ዓለምን ሳይፈጥር አስቀድሞ መርጦናል ወይስ አልመረጠንም? ለሚለው ጥያቄ መልሱ እነሆ ፊታችን ተደቅኗል፡፡ ክፍሉ በደማቁ "ዓለም ሳይፈጠር . . . መረጠን" ይላላ! እግዚአብሔር እንዴት ይመርጣል? እንዴትስ አንዱን ከአንዱ ይለያል? ብሎ ለሚጠይቅ ሰው፣ የያዝነው መጽሐፍ ቅዱስ፣ እግዚአብሔር ከምድር ሰዎች መካከል አንድ አብርሃምን፣ ከምድር ሕዝቦች መካከል አንድ እስራኤልን መምረጡን በግልጽ እንደሚተርክ ማየቱ በቂ ነው፡፡ ሆኖም እግዚአብሔር አብርሃምንም ሆነ እስራኤልን መምረጡ የእነርሱን ልዩ ብቃት ፈጽሞ አያሳየንም፡፡ ምንም እንኳ እስራኤላውያኑ ከዚህ የተለየ ነገር ባያስቡም እውነቱ ግን ይህ ነው፡፡ እስራኤልን በመምረጡ ጎልቶ የሚታየው የእግዚአብሔር ምህረትና ፍቅር ብቻ ነው፡፡ የማይመረጠውን መርጧላ! የማይወደደውን ወድዷላ! ዳሩ እርሱም ስለምርጫው አይፀፀት፡፡[42] ማንም ተነስቶ ለምን መረጥከ ብሎ ሊጠይቀው አይችልም፡፡[43]

መመረጥ መብትን ብቻ ሳይሆን ግዴታንም የሚያሳይ ነው፡፡ እስራኤል ከምድር ሕዝቦች መካከል ተለይታ ስትመረጥና በእግዚአብሔር ክንድ ከግብፅ ምድር ከባርነት ቤት ስትወጣ እንዴት መኖር እንዳለባትና ምን መሥራት እንዳለባት የሚገልጽ መመሪያ በሲና ተሰጥቷታል፡፡ እኛም ልናይ የሚገባን በመመረጣችን ያገኘነውን መብት ብቻ ሳይሆን ግዴታችንን ጭምር ነው፡፡ በዚህ ክፍል ግዴታችንም ተገልጧል "በፊቱ ቅዱሳንና ነውር የሌለን" መሆን፡፡ ቅድስና በራሳችን ልንፈፅመው የማንችል በክርስቶስ ኢየሱስ በሆነ እምነት ከእግዚአብሔር ዘንድ

[41] Nosotro, Rit; Calvinisim and Arminism, Comparative Essay; www.hyperhistory.net; August, 2011.

[42] ሮሜ 11፡29

[43] ሮሜ 9፡20-21



For more books www.amharicchristianbooks.com

በጸጋ የተሰጠን ቢሆንም፤ የተሰጠንን ጸጋ በአግባቡ በመጠቀምና ፍሬ በማፍራት በፊቱ ቅዱሳንና ነውር የሌለን ሆነን መኖር የተመረጥን ሰዎች ድርሻ ነው፡፡ መመረጣችንንም የምናፀናው በዚህ ነው፡፡

በእግዚአብሔር ዘንድ የአንዱ መመረጥ በዚያ በአንዱ በኩል የሚደረሱትን ሁሉ የሚጠቀልል እንጂ የተናጠል ጉዳይ አይደለም፡፡ አብርሃም ከከለዳውያን ዑር ሲጠራ የተነገረለት ቃል "የምድር ነገዶች ሁሉ በአንተ ይባረካሉ" (ዘፍ. 12፡3) የሚል ነው፡፡ ይህም እግዚአብሔር አብርሃምን የመረጠበት ዋነኛ ምክንያት ከእርሱ ባሻገር መላውን ዓለም የሚመለከት መሆኑን መረዳት እንችላለን፡፡

በሌላ በኩል ቀደም ሲል ያየነው፣ አሁንም በዝርዝር እያየን ያለነው በረከት ከዚህ ፍጥረት የሆነ ቁሳዊ ጉዳይ አለመሆኑን ይህ ክፍል ያስረዳናል፡፡ ምክንያቱም ለዚህ በረከት የተመረጥነው ይህ ግዑዝ ዓለም ሳይፈጠርና የትኛውም ቁሳቁስ ወደ መኖር ሳይመጣ በፊት ነውና፡፡ ይልቅ ምርጫውና ውሳኔው ከእኛ ውጭ ስለሆኑ ሌሎች ጉዳዮች ከማውሳት ይልቅ በእኛ ማንነት ላይ የሚያጠነጥን ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ *“ቅዱሳንና ነውር የሌለብን እንሆን ዘንድ”* ይላልና፡፡ ይህም በረከት ዙሪያችንን የከበበን ጥሪት ሳይሆን በውስጣችን ያለ ማንነት መሆኑን በቅጡ የሚመልስ ነው፡፡ በቁሳዊ ነገሮች የተሞላው ግዑዙ ዓለም ያስፈልገናል፡፡ ለአሁን ብቻ ሳይሆን ለዘላለምም የሚያስፈልገን ይመስለኛል፡፡ ለእኛ ብቻ ሳይሆን ለእግዚአብሔርም ለክብሩ ያስፈልገዋል፡፡ ለዚህም እግዚአብሔር በዘመን ፍፃሜ በክርስቶስ ሊጠቀልለው መውደዱ በቂ ምሥክር ነው፡፡[44] የሚጠቀልለውም ሰማይን ብቻ ሳይሆን በምድርም ያለውን ሁሉ ነው፡፡ ነገር ግን ይህ የሚሆነው ግዑዙ ዓለም በዲያቢሎስ የአመጽ መዋቅር እንደተተበተበ፣ አምሮና ተብለጭልጮ በአማኞች ልብ ውስጥ ያለውን የአባት ፍቅር እየመጠጠ፣[45] በዓለም የሚኖሩትን ሁሉ በወጥመዱ ይዞ እያሰገደ[46] ሳይሆን፣ አመጽ በኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ ከተሻረና በአፉ እስትንፋስ ከምድር ላይ ከተገፈፈ በኋላ ነው፡፡[47] ያን ጊዜ እንዳሁኑ በአመጽ የተያዘች ሳትሆን ጽድቅ የሚያድርባት አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር ትኖረናለች፡፡[48]

[44] ኤፌ. 1፡10
[45] 1ዮሐ. 2፡15-17፤ ያዕ. 4፡4-5
[46] 1ዮሐ. 5፡19
[47] 2ተሰሎ. 2፡8
[48] 2ጴጥ. 3፡13



For more books www.amharicchristianbooks.com

## ወራሽ ልጆች

> *"በበጎ ፈቃዱ እንደወደደ በኢየሱስ ክርስቶስ ሥራ ለእርሱ ልጆች ልንሆን አስቀድሞ ወሰነን። በውድ ልጁም እንዲያው የሰጠን የጸጋው ክብር ይመሰገን ዘንድ ይህን አደረገ።" ኤፌ.1፡5፣6*

እግዚአብሔር ለአባቶቻቸው የማለላቸውን የርስት ተስፋ ለማውረስ እስራኤልን ከግብፅ ምድር ሲጠራ በሙሴ አማካይነት ለፈርዖን ያስተላለፈው መልዕክት *"እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡- እስራኤል የበኩር ልጄ ነው፤ ይገዛልኝ ዘንድ ልጄን ልቀቅ አልሁህ፣ አንተም ትለቀው ዘንድ እንቢ አልህ፣ እነሆ እኔ የበኩር ልጅህን እገድላለሁ"* (ዘፀ. 4፡23) የሚል ነበር። በኋላም በነቢያት መጽሐፍት "እስራኤል ሕፃን በነበረ ጊዜ ወደድሁት፤ ልጄንም ከግብፅ ጠራሁት።" (ሆሴ. 11፡1) ብሎአል። ወራሽ ለመሆን ልጅ መሆን የግድ ነውና።

ሆኖም በዚህ ሥፍራ የተጠቀሰውን የልጅነት ዓይነት በቅርበት ስንመለከት ከአንድ እውነት ጋር ፊት ለፊት ለመፋጠጥ እንገደዳለን። ይህን "ልጅነት" ለመግለፅ፣ ሥራ ላይ የዋለው የግሪክ ቃል (huiothesia)[49] የሚል ሲሆን ሁሉም የእንግሊዘኛ ትርጉሞች ከሃሳቡ ጋር በመስማማት "አዶፕሽን" ብለው ተርጉመውታል። ይህ ቃል የሚያመለክተው በቀጥታ መወለድን ሳይሆን በኦሮምኛ "ጉዲፈቻ" በአማርኛ ደግሞ "ማደጎ" ብለን የምንጠራውን የልጅነት ዓይነት ነው።[50] ምንም እንኳን በሌሎች የአዲስ ኪዳን ክፍሎች ከእግዚአብሔር ዘር በመንፈስ የተወለድን መሆናችን ቢጠቅስም፣ ይህ ክፍልና ሌሎች መሰሎቹ ግን ሆን ብለው ልጅነትን ከ"አዶፕሽን" ጋር ያያይዙታል።[51] ሰው ልጁን ወይ ይወልዳል፣ ወይ በማደጎ ያሳድጋል እንጂ ሁለቱንም በአንዴ ማድረግ አይችልም። እግዚአብሔር ግን የሰው ልጆችን፣ ለዛውም "የቁጣ ልጆች" (ኤፌ. 2፡3) የነበርነውን በአዶፕሽን ከወሰደን በኋላ የአንድያ ልጁን አባ አባት ብሎ የሚጮህ መንፈስ በውስጣችን በመላክ ልጆቹ አድርጎ ወለደን (ገላ. 4፡ 6; ሮሜ 8፡ 15)። ስለዚህ ለእግዚአብሔር ጉዲፈቻም፣ ውልድም ልጆች ነን። ጉዲፈቻ የሰውን ልጅ፣ ልጅ አድርጎ የመውሰድ ተግባር ሲሆን በልጁና በአዲሱ ወላጁ ነፃ ፈቃድ የሚከናወን ነው። ልጁ የአዲሶቹ ወላጆቹ

---

[49] Gerald F. Hawthorne; Raalph P. Martin; Daniel G. Reid; Dictionary of Paul and His letter 1993; Pp. 15

[50] ጥናታዊ ማረጋገጫ ባይኖረኝም ማደጎ በአገራችን በጥሩ ዓይን የማይታየው፣ ማደግን እንጂ ሙሉ የልጅነትን ሥልጣን ተጎናጽፎ መውረስን ስለማያካትት ነው። የኦሮሞን ባህል የሚያንፀባርቀው ጉዲፈቻ ግን መውረስንም ያካትታል።

[51] 1ጴጥ.1፡23፤ ያዕ.1፡18 መወለድን ሲያሳዩ ዮሐ. 1፡12 ሮሜ 8፡15 እና 23፤ ገላ. 4፡5 ጉዲፈቻን ወይም ልጅ ተደርጎ መወሰድን ያመለክታሉ።



For more books www.amharicchristianbooks.com

ልጅ ለመሆን መስማማቱን ሲገልፅ የቀድሞ ወላጆቹን በሕግ በመተው፣ የአዲሱ ወላጆቹ ሕጋዊ ልጅ ይሆናል፡፡ አዶፕሽን ይህ መልዕክት በተጻፈበት ዘመን በሮማውያን ዘንድ የታወቀና በሥፋት በሥራ ላይ የሚውል ልምምድ እንደነበር ታሪክ ይዘክራል፡፡ አንድ በጉዲፈቻ የተወሰደ ልጅ ከሌሎች የተወለዱ ልጆች እኩል የአዲሱ ወላጆቹ ወራሽ እንዲሆን በወቅቱ ዓለምን የሚገዛው የሮም መንግሥት ሕግ ይደነግጋል፡፡[52]

ጉዲፈቻ ወይም ማደጎ የሚለው ቃል በተለይ በእኛ ባህል እምብዛም ተወዳጅ አይደለም፡፡ ለአንድ አማርኛ ለሚናገር አማኝ "እኔ የእግዚአብሔር ልጅ የሆንኩት በአዶፕሽን ነው" ብሎ ማሰብ የሚከብድ ይመስላል፡፡ ነገር ግን ይህ እንዲሆን የተፈለገበትን ምክንያት ስንረዳ ነገሩን ከመቀበል ባሻገር ስለ ድንቅ ጥበቡ እግዚአብሔርን የምናመሰግንበት ይሆናል፡፡

የእግዚአብሔር ልጆች እንድንሆን የተወሰነው አስቀድሞ ነው፡፡ "አስቀድሞ" የሚለው ቃል ደግሞ "ዓለም ሳይፈጠር" ወይም "ከዘላለም ዘመናት በፊት" ከሚሉት ቃላት ጋር አቻ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ልጆቹ እንድንሆን የተወሰነው አለም ሳይፈጠር ከሆነ፣ ሰው ሆነን ከመፈጠራችን በፊት የእግዚአብሔር ልጆች እንድንሆን መመረጣችን እንደሚቀድም እንመለከታለን፡፡ ታዲያ የሰው ልጆች ከመሆናችን በፊት ልጆቹ እንሆን ዘንድ የወሰነን እግዚአብሔር ስለምን የእርሱ ልጆች ከመሆናችን በፊት የሰው ልጆች እንድንሆን ፈለገ? ጥያቄውን የጫረብን ሃሳብ ኤፌ. 1፡5 ላይ ያለ ሲሆን፤ መልሱ ብዙም ሳይርቅ ቁጥር 6 ላይ በጉልህ ሰፍሯል፡፡ ይህም እያየን ያለነው ዐውድ ገዢ ሃሳብ የሆነው "የፀጋው ክብር ይመሰገን ዘንድ!" በሚለው ሃረግ ውስጥ የተጠቃለለ ነው፡፡ ይህንን ሃሳብ ለማጠናከር አንድ የቅርብ ገጠመኝ ላንሳ፡፡

አንድ ቀን በመኖሪያ ቤቴ በእግዚአብሔር ቃል ዙሪያ ከወገኖች ጋር ሕብረት እያደረግሁ ሳለ ይህንን ክፍል አነሳንና መወያየት ቀጠልን፡፡ በዚህ ስፍራ የተጠቀሰው ልጅነት ጉዲፈቻ (አዶፕሽን) መሆኑን ስናገር አንዲት እህት እጅግ ከፋት፡፡ "እንዴት እንዲህ ትላለህ? እኔ ለእግዚአብሔር የማደጎ ልጅ አይደለሁም" አለች የቅሬታ ስሜት በተቀላቀለበት ሁኔታ፡፡ ጉዳዩን ለማስረዳት ስሞክር በመካከላችን የነበሩ ባልና ሚስት የሰሞኑን ገጠመኛቸውን በመተረክ በምሳሌ አገዙኝ፡፡ "ክረምቱ ከማለቁ በፊት ልጆቻችንን ለማስደሰት ያለንን ገንዘብ ሰብስበን ለእረፍት ከከተማ ወጣን፡፡ ሐዋሳ ከደረስን በኋላ እንዳቅማችን ሆቴል ተከራይተን

[52] ዝኒ ከማሁ (Ibid) note # 49



For more books www.amharicchristianbooks.com

ለጥቂት ቀን ተቀመጥን፡፡ አንድ ቀን ልጆቻችንን ለማጫወት ወደ ሌዊ ሆቴል ይዘናቸው ሄድን፡፡ የዘጠኝ አመት ወንድ ልጃችን ሌሎች ልጆች የመዋኛ ገንዳ ውስጥ ሲዋኙ አይቶ ካልገባሁ አለን፡፡ "አይ አንተ ከዚህ ቀደም ዋና ስላልተለማመድክ፣ የመዋኛም ትጥቅ ስላልያዝክ መግባት አትችልም አልነው፡፡ እሱም በሃዘን ስሜት "እኔ እኮ እንዲህ የተበደልኩት የእናንተ ልጅ በመሆኔ ነው፤ የሌላ ሰው ልጅ ብሆን ኖሮ እንደ ሌሎቹ እሆን ነበር" አለን፡፡ ይሄኔ በጣም ካነሰ የኑሮ ሁኔታ በአዶፕሽን የወሰድነው ልጃችን ቢሆን ኖሮ አሁን ያለውን የተሻለ ኑሮ እያሰበ ያመሰግነናል እንጂ "ድሮስ ማን ውለዱኝ አላችሁ?" በሚል ስሜት አይማረርብንም ነበር፤ ብለው አጫወቱን፡፡

በእርግጥ የወለድናቸው ልጆቻችን ምንም ብናደርግላቸው መብታቸው እንደሆነ ያስባሉ እንጂ "አባቴና እናቴ እንኳን ወለዳችሁኝ" ብለው አያመሰግኑንም፡፡ እግዚአብሔር ግን ምንም እንኳ በክርስቶስ *ሥራ* ልጆቹ እንድንሆን የወሰነን አለም ሳይፈጠር አስቀድሞ ቢሆንም ገና ከመጀመሪያው ልጆቹ ሆነን እንድንወለድ አላደረገም፡፡ ይልቅ *መጀመሪያ* የሰው ልጆች ሆነን እንድንፈጠር ካደረገ በኋላ በክርስቶስ እየሱስ ስናምን ልጆቹ አደረገን፡፡ አዶፕሽን የሰውን ልጅ የራስ ልጅ አድርጎ መውሰድ እንደመሆኑ መጠን እግዚአብሔርም የሰው ልጅ የሆንነውን ልጆቹ አድርጎ ወሰደን፡፡ ለምን? የሚለውን ጥያቄ የሚመልስልን የሚቀጥለው ቁጥር ነው፡፡ *"በውድ ልጁም እንዲያው የሰጠን የጸጋው ክብር ይመሰገን ዘንድ ይሆን ዘንድ አደረገ" ቁ. 5* እግዚአብሔር ምስጋናን ይፈልጋል፡፡ ከፍ ብዬ እንደጠቀስኩት የወዳጆቼ ገጠመኝ ገና የሰው ልጅ ሳንሆን በፊት የእርሱ ልጆች ሆነን ተወልደን ቢሆን ኖሮ ስለ ልጅነታችን እንደ መብት እንወስደዋለን እንጂ ተመስጠን አናመሰግንም ነበር፡፡ አሁን ግን ከየት እንደመጣን፣ ከምን፣ በምን እንደተዋጀን ስለምናውቅ የተሰጠንን ልጅነት እያሰብን ዘወትር እናመሰግናለን፡፡

እግዚአብሔር ልጆቹ ያደረገን *"በበጎ ፈቃዱ፣ ወዶ"* ነው እንጂ ያለ ሃሳብ ባጋጣሚ ወይም በግድ አይደለም፡፡ ነገር ግን ከዘላለም ልጁ በሆነው በሚወደው በኢየሱስ ክርስቶስ *ሥራ* የመጨረሻ ታላቅ የሆነውን ክብር ሰጠን፡፡ *"በውድ ልጁም እንዲያው የሰጠን የጸጋው ክብር ይመሰገን ዘንድ ይሆን አደረገ"* ልጅ በመደረጋችን የውድ ልጁ የኢየሱስ ክርስቶስ ዘላለማዊ ክብር በጸጋ ተሰጥቶናል፡፡[53] ይህም ክብር ከአብ ጋር ሕይወት የሆነውን መንፈስ ቅዱስን በመካፈል እርሱ በእኛ እኛም በእርሱ የመሆናችን ምሥጢር ነው፡፡ በሰማይም ሆነ በምድር ከዚህ የሚበልጥ

[53] ዮሐ. 17፡ 22-23



For more books www.amharicchristianbooks.com

ክብር የለም፡፡[54] በኃጢያት ከጎሰቆለ የሰው ልጅነት አሁን በሥጋ አዕምሮ ልንረዳውና በሰው ቋንቋ ልንገልፀው ወደማንችል የእግዚአብሔር ልጅነት መሸጋገር እንዴት ያለ ታላቅ ሥጦታ ነው! ይህ መረዳት ይህን ክብር በጸጋ የሰጠንን እግዚአብሔርን በጊዜውም ያለጊዜውም በደስታ እያመሰገንን በፊቱ እንድንኖር ግድ ይለናል፡፡

## ለርስት መዋጀት

*"በውድ ልጁም እንደ ፀጋው ባለጠግነት መጠን በደሙ የተደረገ ቤዛነታችንን አገኘን እርሱም የበደላችን ስርየት፡፡" ኤፌ. 1፡7*

ዓለም ሳይፈጠር የተመረጥንና የተወሰንን ከሆነ ከጊዜ በኋላ ለምን በደም መዋጀት አስፈለገን? ስርየቱስ ምንድነው? ይህ ክፍል ያረገዘው ብርሃን ከፊደላቱ ማኅፀን ሠርፆ እንዲታየንና እንዲያሳየን ከፈለግን የእሥራኤልን ልጆች ታሪክ መመልከት ግድ ይለናል፡፡ ይህም እሳቤ ጳውሎስ ይህን መልእክት ሲጽፍ በውስጡ እንደነበረ መገመት ይቻላል፡፡ መልዕክቱ ምንም እንኳ በግሪክ ቋንቋ ለግሪካውያን አንባቢዎች ቢጻፍም የእግዚአብሔርንና የእስራኤልን ታሪክ ጠንቅቆ በሚያውቅ አእምሮና ብዕር ማለፉን ልንዘነጋ አይገባም፡፡

በግብጽ በባርነት ቤት የነበሩት እስራኤላውያን የተመረጡት ከረዥም ዘመናት በፊት በአብርሃም በኩል ነው፡፡ አብርሃም ብቻውን ሳለ እነዚህ ሁሉ በወገቡ እንደነበሩ በመጠራቱ እንደተጠሩ፣ በመመረጡ እንደተመረጡ መጽሐፍ ያረጋግጥልናል፡፡[55] እኛም እንዲሁ ዓለም ሳይፈጠር በክርስቶስ ተመረጥን፡፡ ታዲያ ምንም እንኳ ዓለም ሳይፈጠር በፊቱ ቅዱሳንና ነውር የሌለን እንሆን ዘንድ በክርስቶስ ብንመረጥም፣ በአዳም ከተፈጠርን በኋላ በኃጢአት ወድቀናል፡፡ እንደ አመራረጣችን ሁሉ አወዳደቃችንም እንዲሁ ነው፡፡ እኛ በተናጠል፣ በነፍስ ወከፍ አልወደቅንም በወገቡ የነበርነው የአዳም ውድቀት ውድቀታችን፣ ሞቱም ሞታችን ሆነ፡፡[56]

በአዳም መተላለፍ ምክንያት ከተሰጠን የርስት ተስፋ ርቀን፣ የኃጢአት ባርነት ውስጥ ስለተዘፈቅን ተመልሰን ወደዚያ ተስፋ እንድንመጣ መዋጀት ያስፈልገን ነበር፡፡ ምሳሌያችን በሆኑት በእስራኤላውያንም የሆነው ልክ እንዲሁ ነው፡፡ ባርነት

[54] ዕብ. 1፡5
[55] ዕብ. 7፡10
[56] ሮሜ 5፡ 15-19



For more books www.amharicchristianbooks.com

ምን እንደሆነ በማያውቁት አባቶች ዘመን የተመረጡት እስራኤላውያን ይመጣ ዘንድ ላለው መዳን ምሳሌ ለመሆን ወደ ግብጽ መውረድ በዚያም በባርነት መገዛት ነበረባቸው፡፡ ይህም በእግዚአብሔር ቅድመ እውቀት የተከናወነ መሆኑን ለመግለጽ እግዚአብሔር ለአብርሃም አስቀድሞ አሳይቶታል፡፡[57] በአብርሃም የሆነው ሥጋዊው የተስፋ ዘር ወደ ግብጽ ባርነት መውረድና በበጉ ደም ከባርነት ቤት መዋጀት እንዳስፈለገው ሁሉ፣ በኃጢአት ባርነት ውስጥ የገባው በክርስቶስ የሆነው ሰማያዊው የተስፋ ዘር ነውርና እድፍ እንደሌለው እንደ በግ ደም በክቡር የክርስቶስ ደም መዋጀቱ የግድ ነበር፡፡

እስራኤላውያኑ በፈሰሰው የበግ ደም ከመቅሰፍት ድነው በተስፋ የተሰጣቸውን ርስት ሊወርሱ የፈርኦን ግዛት ከሆነችው ከግብጽ ምድር እንደወጡ፣ እኛም በክርስቶስ ዓለም ሳይፈጠር የተወሰነልንን የዘላለም መኖሪያ ርስት ለማግኘት በደሙ ተዋጅተንና የኃጢአታችንን ሥርየት አግኝተን የጨለማው ስልጣን ከሚገዛው ክፉ ከሆነው ከአሁኑ ዓለም ወጣን፡፡ ስለዚህ ዓለም ሳይፈጠር የተመረጥነውና የተወሰንነው ለርስት እንደሆነ ሁሉ ከሁለት ሺህ ዓመታት በፊት በመስቀሉ ደም የተዋጀነው ለርስቱ የምንገባ ሆነን እንቆጠር ዘንድ ነው፡፡

መዋጀት ወይም መቤዠት አስቀድሞ የራስ የነበረን፣ ነገር ግን በተለያየ ምክንያት ከባለቤቱ እጅ ወጥቶ በሌላው እጅ የሆነን ንብረት ዋጋ ከፍሎ መግዛት እንደመሆኑ መጠን፣ እግዚአብሔርም በምርጫው አስቀድመን የእርሱ የነበርነውን በኋላም በክፉው ግዛት በኃጢያት እጅ የወደቅነውን እንደፀጋው ባለጠግነት መጠን በዋጋ የማይተመን የልጁን ደም አፍስሶ ገዛን፡፡

## ለርስቱ የሆነ መገለጥ

> ***"ጸጋውንም በጥበብና በአእምሮ ሁሉ አበዛልን፡፡ በክርስቶስ ለማድረግ እንደወደደ እንደ አሳቡ የፈቃዱን ምስጢር አስታውቆናልና፡፡ በዘመን ፍጻሜ ይደረግ ዘንድ ያለው አሳቡም በሰማይና በምድር ያለውን ሁሉ በክርስቶስ ለመጠቅለል ነው፡፡" ኤፌ. 1፡8-10***

ሕዝቡን ለመታደግ በተዘረጋች ክንድና በፀናች እጅ በግብጽ ላይ የተገለጠው እግዚአብሔር ልባቸውን ያደነደኑበትን ፈርኦንንና የግብፅን ሕዝብ የተመኩባቸውንም አማልክቱን የመታው በጽኑ እጅ ነበር፡፡ "እግዚአብሔር ማነው? አላውቅም፣ ባሪያዎቼንም አልለቅም!" እያለ ሲመፃደቅ የነበረውን ፈርዖን

[57] ዘፍ. 15፡ 13-16



For more books www.amharicchristianbooks.com

«ውጡልኝ» ብሎ እስኪማፀን ያደረሰው የበትሩ ክረት እንደሆነ አያጠያይቅም፡፡ ነገር ግን እስራኤላውያን ከወጡ ከጥቂት ቀናት በኋላ ለፈርኦን *"በምድር ይቅበዘበዛሉ ምድረ በዳም ዘጋቻቸው፡፡"* (ዘፀ. 14፡3) የሚል የሚያስገርም ወሬ ደረሰው፡፡ እርሱም ከተመረጠው ሠራዊቱ ከፈረሶቹና ከሰረገሎቻቸው ጋር በባሕር እንደሚሰምጥ ሳያውቅ *"እንዳይገዛልን እስራኤልን የለቀቅነው ምን አድርገናል?"* በማለት ሊመልሳቸውና ዳግም በባርነት ሊገዛቸው ተመመ፡፡ ከዚህ ደካማ መረጃ የተነሳ ውጡልኝ ብሎ፣ ብርና ወርቅ ሰጥቶ የሰደደውን እስራኤልን ከመንገድ ሊመልስ መውጣቱ "ወዳሰቡበት ወደ ከነዓን ለመሄድ መንገዱ በፍልስጤም አገር ሆኖ ሳለ፣ አምላካቸው መንገድ በሌለበት ምድረ በዳ መርቶ በባህር ዳር ያሰፈራቸው፣ መቅሰፍ እንጂ መምራት ስለማይችል ይሆናል" ብሎ ያሰበ ይመስላል፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔር በባህር ሊያሰምጠው፣ ክብሩንም ሊገልጥ አደረገው እንጂ ሕዝቡን ለምን እንደሚመራ፣ እንዴት እንደሚመራ፣ በየት እንደሚወስድና በፍፃሜውም የት እንደሚያደርስ እርሱ ቀርቶ አያቶቹና ቅድመ-አያቶቹ ፈርዖኖች ሳይወለዱ ከአራት መቶ ሃምሳ ዓመታት በፊት ለአብርሃም ነግሮታል፡፡[58]

ይህን ያነሳሁት እግዚአብሔር ያዳነውን ሕዝብ ወዴት እንደሚመራ፣ ታሪክን ወዴት እንደሚዘውር፣ ጊዜና ዘመናትን እንዴት እንደሚያስኬድ የሚያውቅ፣ የሚያውቅ ብቻ ሳይሆን ለተከተሉት ሁሉ የሚያሳውቅ አምላክ መሆኑን ለመጠቆም ነው፡፡ በዚህ ክፍል ላይ እንደምንመለከተው እግዚአብሔር ክፉ ከሆነው ከአሁን ዓለም አድኖ ወዴት እየመራን እንዳለ፣ እኛንም ብቻ ሳይሆን ታሪክን፣ ዘመናትን፣ ባጠቃላይ ፍጥረተ-ዓለሙን ወዴት እየወሰደ እንዳለ እንድናውቅ መፈለጉን በግልጽነት ይነግረናል፡፡ ይህን በቅድመ ዓለም (ቁጥር 4) ጀምሮ እስከ ድህረ ዓለም (ቁ. 10) የሚዘልቅ ግዙፍ ጥበብ፣ እኔ ነኝ ያለ ሰው በትክሻው መሃል በተሰካና በአንገቱ ተደግፎ በቆመ ትንሽ ጭንቅላቱ ሊመረምረውም ሆነ ሊረዳው አይችልም፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔር በልጁ ደም የዋጀን እኛ የፍቃዱንም ምሥጢር፣ ምክሩን፣ አሳቡንና እቅዱን ሁሉ እንድንረዳ በመውደዱ ፀጋውን በጥበብና በአእምሮ ሁሉ አበዛልን፡፡ ይህንን ነው ሐዋርያው የምሥራች የሚለን፡፡ ፀጋ ለዚያውም የበዛ ፀጋ ለአእምሮአችን ባይሰጥ ኖሮ እንኳን የዘላለሙን የመለኮት ሃሳብ የዛሬውን ውሎ አዳራችንን ምን እናውቅ ነበር? የእግዚአብሔርን ዘላለማዊ ምክር፣ ፈቃድ፣ ዓላማና ዕቅድ የቱንም ያህል ብናውቅ፣ ባሳወቀን በእግዚአብሐር እንጂ በማወቃችን ልንመካ አንችልም፡፡ ምክንያቱም "አስታውቆናል" እንጂ

[58] ዘፍ. 15፡ 13-16



For more books www.amharicchristianbooks.com

በራሳችን አላወቅንማ! የተቀበለ ደግሞ ያመሰግናል እንጂ አይመካም፡፡ ቢመካም አያምርበትም፡፡

ይህን መልዕክት ከሌሎች የጳውሎስ መልዕክቶች ሁሉ ልዩ ከሚያደርጉት ገጽታዎች አንዱ ሐዋርያው "ምስጢር" በማለት ስድስት ጊዜ ደጋግሞ የፃፈው ቃል ነው፡፡ ምንም እንኳ ስድስት ጊዜ ቢደጋግመው በእግዚአብሔር ዘንድ አንድ እንጂ ስድስት ምስጢር እንደሌለ ቃሉ የገባባቸው አውዶች በግልፅ ያሳያሉ፡፡ "ምስጢር" የሚለው የግሪክ ቃል፣ ነገሩ አሁንም በምስጢርነት ያለ የተሰወረና ሊታወቅ የማይችል ሳይሆን፣ ተሰውሮ የኖረ፣ ግን አሁን በክርስቶስ የተገለጠ፣ በመገለጡም ምክንያት ምስጢርነቱ ያበቃ መሆኑን ያሳያል፡፡ አንዳንድ ሰዎች ክርስትና ተቆጥረው በማይዘልቁ ምስጢሮች የተሞላ፣ ምስጢራዊ ኃይማኖት እንደሆነ አድርገው ለማሳየት ይሞክራሉ፡፡ ሌሎችም ምስጢሩ ተገልጦም ከሆነ የሚገለጠው ለተወሰኑ ቅቡዓን ብቻ እንደሆነና ተርታው ሕዝብ እነዚህን ቅቡዓን "እግዚኦ" እያለ ከመከተልና ከማድነቅ በስተቀር ወደ ምስጢሩ ሊደርስ እንደማይችል ይናገራሉ፡፡ ነገር ግን ይህ አስተሳሰብ ፈጽሞ ስህተት እንደሆነ የምንረዳው የኤፌሶንን መልዕክት በማንበብ ስንዘልቅና ወደ ምዕራፍ ሦስት ስንደርስ ነው፡፡

አብዛኞቹ "ምስጢር" የሚሉት ቃላት የሚገኙበት ይህ ክፍል ምስጢሩ አንድ እንደሆነ እርሱም "አሕዛብ (ከአይሁድ ጋር) አብረው እንዲወርሱ በአንድ አካልም አብረው እንዲሆኑ በወንጌልም መስበክ በክርስቶስ ኢየሱስ በሆነ የተስፋ ቃል አብረው እንዲካፈሉ ..." መገለጡ ነው፣ ይለናል፡፡ (3፡5፣6) ይህ በመንፈስ ቅዱስ የሆነ አንድነት በአይሁድና በአሕዛብ የተከናወነ (3፡5፣6) በክርስቶስና በቤተ-ክርስቲያን በመከናወን ላይ ያለ (5፡32) ወደፊትም በሰማይና በምድር ባሉት ሁሉ ዘንድ የሚካሄድ (1፡9-10) ሁሉንም በፈጠረው በእግዚአብሔር ከዘላለም የተሰወረ (3፡9) አሁን ግን በወንጌል ቃል የተገለጠ (6፡19) የሕይወት ትስስር ምሥጢር ነው፡፡ ሆኖም ይህ ሁሉን በአንድ ሕይወት፤ በአንድ ጌትነትና በአንድ አባትነት ሥር የመጠቅለል ሥራ በየትኛውም መልኩ ክፋዎችን እንደማይጨምር መጽሐፍ ቅዱስ በግልጥ ያስተምራል፡፡ (5፡5) ይህን ክፍል ምዕራፍ 3 ላይ ስንደርስ በስፋት የምናየው ስለሚሆን ላሁኑ በዚህ እንግታውና እያየን ወዳለነው ክፍል እንመለስ፡፡

ምስጢርን ማሳወቅ የቅርበትና የወዳጅነት ምልክት ነው፡፡ ለዚህ ነው ጌታ ራሱ በመጨረሻው ሰዓት ለቀደመዛሙርቱ "ከእንግዲህ ወዲህ ባሮች አልላችሁም፣ ባሪያ ጌታው የሚያደርገውን አያውቅምና ወዳጆች ግን ብያችኋለሁ ከአባቴ የሰማሁትን ሁሉ ለእናንተ አስታውቄያችኋለሁና" ያለው፡፡ (ዮሐ. 15፡15) እግዚአብሔር ከመረጠን፣ ከወሰነንና ከኃጢአት ባርነት ከዋጀን በኋላ በቀጥታ ያመራው የፈቃዱን



For more books www.amharicchristianbooks.com

ምስጢር ወደ ማሳወቅ ነው፡፡ ፍቃዱም በዘመን ፍፃሜ በሰማይና በምድር ያለውን ሁሉ በክርስቶስ መጠቅለል ነው፡፡ የኤፌሶንን መልዕክት ስንመለከት ከክፉውና የክፉው ከሆኑት በስተቀር በክርስቶስ የማይጠቀለል የማይዋሃድና አንድ የማይሆን እንደሌለ እናያለን፡፡ በክርስቶስ ጠቅላይነት አንድ አድራጊነትና አዋሃጅነት ሰማይና ምድር በአንድ ራስ ሲዋሃዱ (1፡10) ክርስቶስና ቤተክርስቲያን በአንድ አካል ሲዋሃዱ (1፡22፤23)፣ አይሁድና አሕዛብ በአንድ መንፈስ ሲዋሃዱ (2፡14-18) መልዕክቱ የአንድነት፣ የጥምረት፣ የውህደት መልዕክት ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ የዚህም ምስጢር ዋናው ቁልፍ ከአብና ከወልድ የሚሰርጽ በጸጋ በአማኞች ሁሉ የሚያድር፣ በአማኞችም በኩል በወዲያኛው ትንሳኤ ፍጥረትን ሁሉ የሚሞላ፣ አንድ ሆኖ አንድ የሚያደርግ የሥላሴ አካል፣ መንፈስ ቅዱስ ነው፡፡

ምሳሌያችን የሆኑት የእስራኤላውያን ጉዞ ዛሬ ለእኛ ያለውን አብነት ስንመለከት፣ በአብርሃም አስቀድመው እንደተመረጡና እንደተወሰኑ ፤(ከኤፌ.1፡4 ጋር ያነፃፅሩ) ወደ ግብጽ ከገቡና በባርነት ከተገዙም በኋላ በበጉ ደም እንደተዋጁ (ኤፌ. 1፡7) ከዚያም ርስት አድርገው ሊቀበሉት ወዳለው ምድር ጉዞ እንደጀመሩ እናውቃለን፡፡ ነገር ግን ታሪካቸው በዚህ አላበቃም በምድረ በዳ በሲና ተራራ እግዚአብሔር እንደ ተገለጠላቸውና እንደተናገራቸው፣ ለምን ከግብጽ ምድር እንዳወጣቸውና በእነርሱ ሊያደርግ ያለውን ፈቃዱን እንዳሳወቃቸው እናነባለን፡፡ (ኤፌ. 1፡ 8፤9) እንደ ሕዝብና እንደ መንግሥት በሺህ ለሚቆጠሩ አመታት የኖሩት የእስራኤላውያን የአምልኮ ቢሆን፣ የሥራ፣ የግብረገብ ቢሆን፣ የመንፃት፣ የቤተ ክህነት ቢሆን፣ የቤተመንግስት፣ መመሪያ ዕውቀት የፈለቀው በሲና ከተሰጣቸው ሕግ እንደሆነ ለአፍታም ልንጠራጠር አልችልም፡፡

ይህን ታላቅ የዕውቀት ምንጭ ወደ ርስታቸው ሳይገቡ ለምን በምድረ በዳ ገለጠላቸው? ብለን ብንጠይቅ መልሱ “ትወርሷት ዘንድ የምትገቡባት ምድር አባቶቻችሁ ጥንት እንደኖሩበት (ኡር) ወይም እናንተ አሁን እንደወጣችሁባት (ግብጽ) ዓይነት ምድር አይደለችም፡፡ ልዩ ምድር ናት፡፡ በግብጽ ዕውቀታችሁ በተስፋይቱ ምድር ልትመላለሱ አትችሉም፡፡ ስለዚህ በርስቴ ላይ እንዴት እንደምትኖሩ ወደርስቴ ሳትገቡ እነግራችኋለሁ፡፡” ማለቱ ይመስላል፡፡ እግዚአብሔር የእስራኤልን ልጆች ከግብጽ ያወጣው በከነዓን የሚኖሩትን፣ በኃጢአታቸው የረከሱትን፣ ለአመፃቸው ቁጣና ፍርድ እንጂ ንስሐና ስርየት የሌላቸውን ከነዓናውያን አጥፍቶ ምድሪቱን በመረጠውና በተቤዠው ሕዝብ ለመጠቅለል እንደነበር ሁሉ፣ አሁንም በሰማይና በምድር ያለውን ሁሉ የአካሉ የቤተክርስቲያን ራስ በሆነው በክርስቶስ ለመጠቅለል ወዷል፡፡ (ኤፌ. 1፡10) ይህም



For more books www.amharicchristianbooks.com

በምሳሌውና በእውነተኛው፣ በጥላውና በአካሉ መካከል ያለውን ዝምድና በጉልህ በማሳየት የፈቃዱን ምሥጢር የመረዳት አቅማችንን ከፍ ያደርገዋል፡፡

## ርስትን መቀበል

> *"እንደፈቃዱ ምክር ሁሉን የሚሠራ እንደ እርሱ አሳብ አስቀድመን የተወሰንን በክርስቶስ ደግሞ ርስትን ተቀበልን። ይኸውም በክርስቶስ አስቀድመን ተስፋ ያደረግን እኛ ለክብሩ ምስጋና እንሆን ዘንድ ነው። እናንተም ደግሞ የእውነትን ቃል ይኸውም የመዳናችሁን ወንጌል ሰምታችሁ ደግሞም በክርስቶስ አምናችሁ በተስፋው መንፈስ በመንፈስ ቅዱስ ታተማችሁ። እርሱም የርስታችን መያዣ ነው። ለእግዚአብሔር ያለውን ሁሉ እስኪዋጅ ድረስ ይህም ለክብሩ ምስጋና ይሆናል።" ኤፌ. 1፡11-14*

ሐዋርያው በርስት ስለባረከን፣ ለርስት ስለመረጠንና ስለወሰነን፣ ለርስት ስለተቤዠንና ይቅር ስላለን፣ የርስቱን ፈቃድ ስለገለጠልንና ምስጢሩን እናውቅ ዘንድ ፀጋን ስላበዛልን፣ ከሁሉም በላይ የርስቱን መያዣ ስለሰጠንና ወደ ፊትም ርስቱን በሙላት እንወርስ ዘንድ ታላቅ ተስፋ ስላሰነቀን፣ እግዚአብሔርን በአንድ ትንፋሽ፣ በሚያስተጋባ ብዕር ያመሰገነበትን አንቀጽ በአራት ነጥብ ሊቋጭ ተቃርቧል፡፡ አሁን ልናያቸው ባሉት በተቀሩት 4 ቁጥሮች ውስጥ እኛም አብረነው በምስጋና እንሞላ ዘንድ የተደረገልንን እንዲህ በማለት ይተርክልናል፡፡

## እኛና እናንተ

ሐዋርያው ለአሕዛብ በሚጽፍበት ብዕር በአይሁድና በአሕዛብ መካከል ያለውን መሠረታዊ ልዩነት (ምንም እንኳ ዛሬ ለእኛ እምብዛም ባይታየን) ማሳየት የሚጀመረው እዚህ ጋ ነው፡፡ ምንም እንኳ የዚህን ልዩነት ስፋትና ጥልቀት፣ ልዩነቱንም አስወግዶ ከሁለታቸው አንድ አዲስ ሰው ለመፍጠር የተደረገውን ትግል በሚቀጥለው ምዕራፍ (2፡11-22፤ 2፡1-3፤ 3፡1-6 ) በጥልቀት የሚያወሳው ቢሆንም ብልጭታውን በዚህ ክፍል (1፡11-14) ፈንጠቅ አድርጎት ያልፋል፡፡ ልዩነቱንም የምናስተውለው "እኛ" እና "እናንተ" እያለ በሚጠራቸው ተውላጠ ስሞች ነው፡፡

> *"ይኸውም በክርስቶስ አስቀድመን ተስፋ ያደረግን "እኛ" ለክብሩ ምስጋና እንሆን ዘንድ ነው። "እናንተም" ደግሞ የእውነትን ቃል ይኸውም የመዳናችሁን ወንጌል ሰምታችሁ ደግሞም በክርስቶስ አምናችሁ በተስፋው መንፈስ፣ በመንፈስ ቅዱስ ታተማችሁ።" 1፡12-13*



For more books www.amharicchristianbooks.com

አንድነቱን ከማወጇ በፊት የልዩነቱን ስፋት ማሳየቱ ልዩነቱን አስወግዶ አንድነቱን ለማምጣት የተሠራውን ሥራ እንድናደንቅ ይረዳናልና በኋላ በሙላት እስክንመጣበት ድረስ አሁን በጥቂቱ እንየው፡፡

ጳውሎስ በአይሁዳውያንና በአሕዛብ አማኞች ልዩነት ለተናወጠችው የሮም ቤተክርስቲያን በፃፈው መልዕክት ውስጥ፡- *"እንግዲህ የአይሁዳዊ ብልጫው ምንድነው?"* (ሮሜ 3፡1) ብሎ መጠየቁን እናስታውሳለን፡፡ የራሱን ጥያቄ ራሱ ሲመልስም *"በሁሉ ነገር ብዙ ነው፡፡"* ይላል፡፡ ምክንያቱንም ሲያስረዳ *"አስቀድሞ የእግዚአብሔር ቃላት አደራ ተሰጡአቸው፡፡"* (ሮሜ 3፡2) *በማለት ይዘጋዋል፡፡ ክርክሩ በጦዘበት በዘጠነኛው ምዕራፍ ላይ የእስራኤላዊነትን ልዩ መብት በስምንት ከፍሎ ሲዘረዝር ከሚያነሳቸው ነጥቦች መካከል አንዱ ". . . የተስፋውም ቃላት ለእነርሱ ናቸውና . . . ፡፡"* (ሮሜ 9፡4፣5) በማለት ይዘረዝራል፡፡ እስራኤላውያንን በእግዚአብሔር ፊት ልዩ ከሚያደርጋቸው ነገሮች አንዱና ዋነኛው ከሁሉ አስቀድመው የተስፋውን ቃል መቀበላቸው ነው፡፡ ነገር ግን ያ ተስፋ ከግብጽ ወጥተው በኢያሱ መሪነት የወረሱት የከነዓን ምድር አልነበረም፡፡ ቢሆን ኖሮ በተስፋው ምድር ላይ ቆመው ሌላ ተስፋ ባልጠበቁም ነበር፡፡ በዘመናቸው ሁሉ ተስፋ ሲጠብቁ እንደኖሩ ሉቃስ በሐዋርያት ሥራ ላይ ጳውሎስ በንጉስ አግሪጳ ፊት የተናገረውን በመጥቀስ እንዲህ ይጽፍልናል፡፡

> *"አሁንም ከእግዚአብሔር ዘንድ ለአባቶቻችን ስለተሰጠው ስለ ተስፋ ቃል አለኝታ ልፋረድ ቆሜያለሁ። ወደዚህም ወደ ተስፋ ቃል አሥራ ሁለቱ ወገኖቻችን ሌሊትና ቀን በትጋት እያመለኩ ይደርሱ ዘንድ አለኝታ አላቸው።" ሐዋ. 26፡6-7*

ይህም አሁን በመካከለኛው ምሥራቅ የሚገኘው የእስራኤል ምድር የሌላ ሕያው ርስት ምሳሌና ጥላ እንጂ እውነተኛ አካል እንዳልሆነ ያረጋግጥልናል፡፡ ለዘመናት ለእግዚአብሔር የሚሰገድበት ስፍራ እየሩሳሌም እንደሆነ ይታመን ነበር፡፡ ጌታ ኢየሱስ ግን ለሳምራዊቱ ሴት "አንቺ ሴት እመኚኝ በዚህ ተራራ ወይም በኢየሩሳሌም ለአብ የማትሰግዱበት ጊዜ ይመጣል፡፡ . . . ነገር ግን በእውነት የሚሰግዱ ለአብ በመንፈስና በእውነት የሚሰግዱበት ጊዜ ይመጣል አሁንም ሆኗል፣ . . ." (ዮሐ. 4፡21-24) በማለት ጉዳዩ የመንፈስ እንጂ የቦታ አለመሆኑን፣ በምሳሌነት ሲያገለግል የኖረው እውነተኛ አካሉ በመምጣቱ ምክንያት ስፍራ መልቀቁን ቁልጭ አድርጎ አሳይቷል፡፡ ጳውሎስም በገላትያ መልዕክቱ " ይህም ነገር ምሳሌ ነው፣ እነዚህ ሴቶች እንደ ሁለቱ ኪዳኖች ናቸውና፡፡ ከደብረ ሲና የሆነችው አንዲቱ ለባርነት ልጆችን ትወልዳለች፣ እርሷም አጋር ናት፡፡ ይህችም አጋር በዓረብ



For more books www.amharicchristianbooks.com

ምድር ያለችው ደብረ ሲና ናት፡፡ አሁንም ያለችውን ኢየሩሳሌምን ትመስላለች፣ ከልጆቿ ጋር በባርነት ናትና፡፡ ላይኛይቱ ኢየሩሳሌም ግን በነፃነት የምትኖር ናት እርሷም እናታችን ናት፡፡" (ገላ. 4፡24-26) በማለት፡፡ ጴጥሮስም፣ አይሁዳውያንም ሆኑ አሕዛብ በክርስቶስ ያመኑ ሁሉ በዳግም መወለድ የሚገቡበት፣ ወደፊትም በሥጋ ትንሳኤ በሙላት የሚወርሱት ሰማያዊ ርስት መኖሩን ሲገልጽ፡- *"ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን በመነሳቱ ለሕያው ተስፋና ለማይጠፋ፣ እድፈትም ለሌለበት፣ ለማያልፍም ርስት እንደምህረቱ ብዛት ዳግመኛ የወለደን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ፡፡"* (1ጴጥ. 1፡3-4) በማለት ጽፏል፡፡ ከላይ የተዘረዘሩት ባህሪያት ያሉት ርስት ከራሱ ከእግዚአብሔር በቀር ከቶ ማን ሊሆን ይችላል!?

ሆኖም ይህን በመሃላ የፀና ቅዱስ ተስፋ[59] በማግኘት አይሁዳውያኑ አሕዛብን ይቀድማሉ፡፡ ይህም ፈጽሞ የማይናቅ ትልቅ ክብር ነው፡፡ ተስፋው የምሥራች ሆኖ ለአሕዛብ ሳይበሰር በፊት የሰው ዘር ሁሉ በጨለማ በነበረበት ወቅት እስራኤላውያን የተስፋውን ቃል ተቀብለው በናፍቆት ይጠብቁ ነበር፡፡ ይህንንም ጸሐፊው እንዲህ በማለት ይገልፀዋል፡-

> *". . . በዚያን ዘመን ከእስራኤል መንግሥት ርቃችሁ ለተስፋውም ቃል ኪዳን እንግዶች ሆናችሁ በዚህም ዓለም ተስፋን አጥታችሁ፣ ከእግዚአብሔር ተለይታችሁ ያለ ክርስቶስ ነበራችሁ፡፡" ኤፌ. 2፡12*

ይላል፡፡ አይሁዳውያኑ ምን ተስፋ አደረጉ? ብንል የምናገኘው መልስ "ክርስቶስን" የሚል ይሆናል፡፡ "በክርስቶስ አስቀድመን ተስፋ ያደረግን እኛ" ስለሚል፡፡ ነገር ግን ክርስቶስን ተስፋ ያደረጉት መምጣቱን ብቻ ሳይሆን በመምጣቱ የሚያገኙትን ሁሉ ነው፡፡ አይሁዳውያኑ አስቀድመው ተወሰኑ፣ አስቀድመውም ተስፋ አደረጉ፡፡ እኛ በሥጋ አሕዛብ የሆንን ደግሞ ቀጥለን ወንጌልን ሰማን፡፡ ለዚህ ነው ጳውሎስ ምንም እንኳ ለአሕዛብ ሐዋርያ ሆኖ ቢላክም፣ በደረሰበት ከተማ ሁሉ ወንጌልን የሰበከበት ቅደም ተከተል "... አስቀድሞ ለአይሁዳዊ ደግሞም ለግሪክ ሰው ...፡፡" (ሮሜ 1፡16) የሆነው፡፡ አስቀድሞ የተስፋው ቃል ለነበረው የምሥራቹ ሲመጣ ቀድሞ ሊሰማ ይገባል፣ ሲነገረውም ካልለገመ በቀር ይገባዋል፡፡ እርሱን ለማስረዳት ብዙ ሀተታ አያስፈልግም፤ "መሲህን አግኝተናል" (ዮሐ. 1፡42) ወይም "ሙሴ በሕግ ነቢያትም ስለ እርሱ የጻፉትን የዮሴፍን ልጅ የናዝሬቱ ኢየሱስን አግኝተነዋል፡፡" (ዮሐ.1፡46) ማለት ይበቃል፡፡ እነርሱ (የአይሁዳውያን) አስቀድመው የሰሙት "የተስፋ ቃል" ነው፣ እኛ (አሕዛብ) ግን በኋላ የሰማነው "የእውነት ቃል" ነው፡፡ (ቁ.13)

[59] ሉቃ. 1፡73፣ ሐዋ. ሥራ 13፡34



For more books www.amharicchristianbooks.com

## ርስታችን

እነርሱ ሳይፈፀም በፊት አስቀድመው ተስፋውን ሰሙ፣ እኛም ከተፈፀመ በኋላ እውነቱን ሰማን፤ ውጤቱ ግን ፍፁም አንድ ነው፡፡ የአይሁድ መዳንና የአሕዛብ መዳን የሚባል ነገር የለምና፡፡ *"በአይሁድና በግሪክ ሰው መካከል ልዩነት የለምና፣ አንዱ ጌታ የሁሉ ጌታ ነውና፣ ለሚጠሩትም ሁሉ ባለጠጋ ነው፣ የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናልና፡፡"* (ሮሜ 10፡12-13) ተብሎ እንደተፃፈው ነው፡፡ በክርስቶስ ያመንነውን ሁላችንንም አንድ የሚያደርገን አንዱ መንፈስ፣ አንዱ ርስት ነው፡፡ ይህንንም ተስፋውን በመስማትና ባለመስማት ልዩነት እንደነበረን የተረከው ጳውሎስ በመቀጠል የምሥራቹን ሲያበስረን "በተስፋው መንፈስ በመንፈስ ቅዱስ ታተማችሁ" ካለ በኋላ "እርሱም የርስታችን ማያዣ ነው፡፡" (ቁ.14) በማለት ርስቱ አንድ እንደሆነና እኛንም አንድ እንዳደረገን ይነግረናል፡፡ አይሁዳውያኑም ሆኑ አሕዛብ ርስትን የተቀበሉት በክርስቶስ በማመን ብቻ እንደሆነ ለመግለጽ፡፡ *"እኛ. . . በክርስቶስ ርስትን ተቀበልን"* (ቁ.11) *"እናንተም . . . በክርስቶስ አምናችሁ በተስፋው መንፈስ በመንፈስ ቅዱስ ታተማችሁ እርሱም የርስታችን መያዣ ነው፡፡" (ቁ. 13)* ይላል፡፡ እንዲህ የሚለው የወንጌል እውነት እንዳይጣመም በመጠንቀቅ ነው፡፡ ይህ ለዘመናት ጎልቶ የኖረ ልዩነት የተጋጠመው በክርስቶስ ባገኘነው የሕይወት ርስት ነው፡፡ ለዚህ ነው ሐዋርያው ልዩነቱን በአንድነት እንደተዋጠ ሲያሳይ የአንድነቱን ምሥጢር "ርስታችን" በማለት የጠራው፡፡

ለመሆኑ ርስታችን ማነው? ይህ ጥያቄ የመልዕክቱ ምሰሶ ይመስለኛል፡፡ ይህን ጥያቄ በአግባቡ መመለስ ከቻልን የመልዕክቱን ጭብጥ አግኝተነዋል ማለት ይቻላል፡፡ ከዚህ ጽሑፍ ዋና ርዕስ (ታላቅ ርስት) አንስቶ ውስጡ እስከተከፋፈለባቸው ንዑስ ርዕሶች (ርስትን ማወቅ፣ በርስት ላይ መመላለስ፣ ርስትን መጠበቅ) የሚያጠነጥኑት በዚህ አሳብ ዙሪያ ስለሆነና አሳቡ ሰርክ የሚወሳ ባለመሆኑ ወደ ሌሎች ክፍሎች ከማለፋችን በፊት ትኩረት ሰጥተን ልናየው ይገባል፡፡

ለዚህ ደግሞ አይነተኛ ምሳሌ ሊሆነን የሚችል ከሙሴና ከከነዓን የተሻለ ምሳሌ አናገኝም፡፡ ሙሴ ተወልዶ ያደገው በግብጽ ምድር ነው፡፡ በግብጽ መወለድ ብቻ ሳይሆን ከጨቅላነቱ አንስቶ በፈርኦን ቤተመንግስት ውስጥ የዘመኑን ጥበብና ዕውቀት ለመማር፣ ሀብትና ንብረት ለማከማቸት፣ ሥልጣንንና ስልጣኔን ለመጎናፀፍ የታደለ ሰው ነበረ፡፡ የከነዓንን ምድር በተመለከተ እግዚአብሔርም ለአባቶች ስለሰጠው ተስፋ ገና በጨቅላነቱ ተከፍሏት ከምታጠባው እናቱ ሳይሰማ እንደማይቀር መገመት እንችላለን፡፡ እግዚአብሔር ተገልጦለት ወደ ፈርኦን ከላከውና የእስራኤልን ሕዝብ እየመራ የኤርትራን ባሕር ከተሻገረም በኋላ ቢሆን



For more books www.amharicchristianbooks.com

በቃል ከሰማው፣ ምንልባትም በጽሑፍ ካነበበው በቀር ስለምድሪቱ ግልጽ መረጃ የለውም፡፡ ነገር ግን በተለያዩ ጊዜያት ስለምድሪቱ ከእግዚአብሔር አፍ አስገራሚ ነገሮችን ሰምቷል፡፡ "መልካሚቱ ምድር፣ ከአፈሯ ወርቅና መዳብ የሚማስ ምድር፣ እግዚአብሔር ዓመቱን ሙሉ የሚጎበኛት ምድር፣ ተራሮችና ሸለቆዎች የሞሉባት ምድር፣ የምድር ሁሉ ጌጥ . . . ወዘተ"

ታዲያ ምንም እንኳ በአይኑ ባያያት ስለምድሪቱ ከእግዚአብሐር አፍ ከሰማው የተነሳ ምን ያህል ጉጉት፣ ምን ያህል ናፍቆት ሊኖረው እንደሚችል መገመት አይቀርም፡፡ ምን እንደምትመስል ወዳላያት ምድር ስድስት መቶ ሺህ አባ ወራ አስከትሎ ቀንና ሌሊት ሲገሰግስ ዓመታት ተቆጥረዋል፡፡ በፍፃሜው ግን በመሪባ ውሃ ዘንድ ስለተቆጣው ቁጣ ወደ ተስፋይቱ ምድር እንደማይገባ ቁርጥ ውሳኔ ተነገረው፡፡ እንደዚያ በምናቡ እየሳለ ለ40 ዓመታት በናፍቆት የጓጓለትን ምድር ለመርገጥ ሲከለከል ምን ያህል በውሳኔው ልቡ እንደሚሰበር ለመገመት ፈጽሞ አያስቸግርም፡፡ ነገር ግን አንድ እድል ተሰጠው፤ ወደ ሞአብ ተራራ ጫፍ እንዲወጣና እግዚአብሔር ለዘርህ እሰጣታለሁ ብሎ ለአብርሐምና ለይስሐቅ ለያዕቆብም የማለላቸውን ምድር እንዲያይ ተፈቀደለት፡፡ ምንም እንኳ ዕድሜው መቶ ሃያ ዓመት ቢሆን ዓይኑ ያልፈዘዘው፣ ጉልበቱም ያልደነገዘው ሙሴ ምድሪቱን ሊያይ ወደ ተራራ ወጣ፡፡ አንድ ርምጃ ወደ ላይ በተራመደ ቁጥር ከጥቂት ቅጽበቶች በኋላ ስለሚያያት፣ ነገር ግን ከብላቴንነቱ አንስቶ ሕልሙና ናፍቆቱ ስለነበረች ምድር "ምን ትመስል ይሆን? . . . ዓይኔ ምን ያይ ይሆን?" በማለት የልቡ ምት እንደሚጨምር መገመት አያስቸግርም፡፡ የማይደርስ የለምና ወደ ጫፍ ወጣ ደግሞም አያት፡፡ በሰሜን፣ በደቡብ፣ በምሥራቅ፣ በምዕራብ፣ እያንዳንዱ ነገድ የሚወርሰውን ስፍራ ዓይኑ በሚፈቅድለት ልክ አየ፡፡ ከዚያም ወረደና ከመሞቱ በፊት አንድ መዝሙር ፃፈ፡፡ በዘዳግም 33 ከሚገኘው ከዚህ የበረከት መዝሙር ውስጥ መጨረሻ ላይ የሰፈረው አሳብ እንዲህ ይነበባል፡፡

> *"ይሹሩን ሆይ በሰማያት ላይ ለረድኤትህ፣ በደመናትም ላይ በታላቅነት እንደሚሄድ እንደ እግዚአብሔር ያለ ማንም የለም፡፡ መኖሪያህ የዘላለም አምላክ ነው፣ የዘላለም ክንዶች ከአንተ በታች ናቸው . . . ፡፡" ዘዳ. 33፡27*

ከዚያ ሁሉ ጉጉት በኋላ የተስፋይቱን ምድር ተመልክቶ ከላይ የተጠቀሰውን አስተያየት መስጠቱ የሚያስተላልፈው ትልቅ ዘላለማዊ መልዕክት አለ፡፡

> *"አዎን ጠላቶቻችሁን ታሳድዳላችሁ፣ ወደ ምድሪቱም ትገባላችሁ፣ ትወርሷትማላችሁ፣ ፍሬዋንም ትበላላችሁ፣ ስለዚህ ለእናንተ*



For more books www.amharicchristianbooks.com

*የሚታያችሁ መኖርያ ይህ ምድር ነው፡፡ እኔ ግን ከዚህ ተስፋ ባሻገር ሌላ ተስፋ፣ ከዚህም መኖሪያ ባሻገር ሌላ መኖሪያ ይታየኛል፡፡ ያም መኖሪያ የዘላለም አምላክ ነው፡፡ ያም ማረፊያ የዘላለም ክንዶች ናቸው፡፡ እስራኤል ሆይ መኖሪያህ የዘላለም አምላክ ነው፡፡"*

የሚል፡፡ ወደ ኤፌሶን ስንመለስ ጳውሎስ ተስፋው ምድር ሳይሆን መንፈስ እንደሆነ ይህም መንፈስ ርስት እንደሆነ፣ ይጽፍልናል፡፡ ርስት መኖሪያ ነው፡፡ ለመኖር የሚያስፈልግ ሁሉ ያለበት መኖሪያ፡፡ መንፈስ ቅዱስም የሕይወት መንፈስ ነው፤ ለዘላለም የሚያኖር ሕይወት፡፡ አብና ወልድም ይህን ሕይወት ይካፈላሉ፡፡ አብም በዚህ ሕይወት ለዘላለም እንድንኖር በልጁ በኩል ጠርቶናል፡፡ የዘላለም ሕይወት የሆነውንም መንፈስ ቅዱስ ሰጥቶናል፡፡

አንድ ሰው ከሌላ ሰው ጋር ሲዋዋል የጠየቀው ነገር ሙሉ በሙሉ ተጠናቅቆ እስኪቀርብለት ድረስ መያዣ የሚሆን ቀብድ ይከፍላል፡፡ ቀብድ አድርጎ የሚሰጠውም ሥራው ሲጠናቀቅ የሚሰጠውን ሙሉ ክፍያ የተወሰነ ክፍል ነው፡፡ በዚህ ስርዓት ውስጥ ቀብድ ሌላ፣ ሙሉ ክፍያ ሌላ ሊሆኑ አይችሉም፡፡ በቅድሚያ እሰጣለሁ ያለውን አነስተኛ ክፍል መጀመሪያ ከሰጠ በኋላ የዚያኑ ክፍያ የተቀረውን ድርሻ በፍፃሜ ለማስረከብ ቃል ይገባል፡፡ እግዚአብሔርም ያደረገው ይህንኑ ነው፡፡ የዘላለም መኖሪያ ይሆነን ዘንድ መንፈሱን ሊሰጠን አስቀድሞ ተስፋ ሰጠ፡፡[60] ባመንን ጊዜም የመንፈሱን መያዣ ሰጠን፡፡ ይህንንም ያደረገው በዘመን ፍፃሜ ያንኑ መንፈስ ሙሉ በሙሉ በመስጠት ሰውነታችንን ከሙታን እንደሚያስነሳና እንደሚያከብረን ተስፋ አሰንቆን ነው፡፡ ስለዚህ የርስታችን መያዣ መንፈስ ቅዱስ ከሆነ፣ በዘመን መጨረሻ ከሰማይ የሚገለጠው ርስታችን ከእርሱ ሌላ ሲሆን አይችልም፡፡ ይህም በተስፋ ሲጠበቅ የነበረው መንፈስ፣ ከተሰጠም በኋላ ተስፋነቱ እንደቀጠለ ያሳየናል፡፡

ዘወትር በሰማይ ርስት እንዳለን ሲነገር ፈጥኖ ወደ አዕምሮአችን የሚመጣው ሥፍራ እንደሆነ እሙን ነው፡፡ ይህም ወደን ያመጣነው ሳይሆን በፍጥረታዊ ሕይወት የተያዘችው ሥጋዊ አእምሮአችን ከዚህ ፍጥረት ውጭ ልታስብ አለመቻሏ ነው፡፡ በሥጋ አዕምሮ የፈለገውን ያህል ብናስብ ከቦታ ያለፈ ልናስብ አንችልም፡፡ በርግጥ ሥፍራውን ንፁህ፣ ውብ፣ የሚያበራ፣ የሚያብለጨልጭ ልናደርገው እንሞክር ይሆናል እንጂ ከዚያ አናልፍም፡፡ እግዚአብሔር ግን የመኖሪያ ሕይወት

---

[60] ሐዋ. ሥራ 1፡ 4-5; 2፡ 38-39; ገላ. 3፡ 14; ቲቶ 1፡2;



For more books www.amharicchristianbooks.com

ተስፋ እንጂ የመኖሪያ ስፍራ ተስፋ አልሰጠንም፡፡ [61]

እንዲህ ሲባል መኖሪያ ሥፍራ የለም ማለት አይደለም፡፡ በምድርም ይሁን በሰማይ መኖሪያ ሥፍራ አለ፤ ነገር ግን መኖሪያ ስፍራንና መኖሪያ ሕይወትን ለይቶ ማየት ያስፈልገናል፡፡ በሥፍራ ላይ መኖር የምንችለው ሕይወት ሲኖረን ብቻ ነው፡፡ እግዚአብሔር መኖሪያ ሕይወት እንጂ መኖሪያ ሥፍራ አይደለም፡፡ የምንኖረው በምድር ይሁን በሰማይ፣ ያለ እርሱ ሕይወትነት ከእርሱ ጋር መኖር አንችልም፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ የሰፈረው ተስፋ ስለ ሥፍራ ብቻ የሚናገር ቢሆን ኖሮ፣ ለእኛ በሥፍራ ውስጥ ለምንኖር ሰዎች፣ አዲስ ነገር ሊሆንብን ስለማይችል *“ዓይን ያላየው፣ ጆሮም ያልሰማው፣ በሰውም ልብ ያልታሰበው . . .”* (1ቆሮ. 2፡9) ተብሎ ባልተጻፈልንም ነበር፡፡ ይህም ክፍል፣ ተስፋው በሥፍራ ውስጥ የሚገለጥ የሕይወት መንፈስ እንጂ ግዑዝ ሥፍራ እንዳይደለ ያሳየናል፡፡ አዎን ይህ ሕይወት በሥጋ ይገለጣል እንጂ ሥጋ አይደለም፣ ሥፍራን ይቆጣጠራል እንጂ ሥፍራ አይደለም፡፡

## የመውረስ ሂደት

> *“. . . ለእግዚአብሔር ያለውን ሁሉ እስኪዋጅ ድረስ ይህም ለክብሩ ምሥጋና ይሆናል” ቁ.14*

ሐዋርያው ይህን አሳብ ለመግለጽ የተጠቀመበት ቋንቋ በዕለት ተዕለት የኑሮ ልምምድ ሊተረጎም የሚችል ነው፡፡ አንዳንዴ ከገበያ ዕቃ ስንገዛ ሙሉ በሙሉ ክፍያውን ፈጽመን ደረሰኝ ከተቀበልን በኋላ የተወሰነውን የዕቃውን ክፍል ተረክበን የተቀረውን ግን ወደፊት ለመረከብ በቀነ ቀጠሮ እንለያያለን፡፡ በዚህ ሁኔታ የተቀረውን ዕቃ ገና አንረከበው እንጂ ከፍለንበታል፣ በእጃችን አይግባ እንጂ የኛ ነው፡፡ "ተከፍሏል!" የሚል ማህተም የተመታበት ደረሰኝ በእጃችን ይገኛል፡፡ ልክ እንዲሁ እግዚአብሔር በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ለሁለንተናችን የቤዛነት ዋጋ ከፍሏል፡፡ ነገር ግን ሁለንተናችን ገና ተዋጅቶ አልተፈፀመም፡፡ ክፍሉ “ለእግዚአብሔር ያለውን “ሁሉ" እስኪዋጅ ድረስ” ይላል፡፡ ይህም ሁለት መሰረታዊ ነገሮችን ያስገነዝበናል፣ አንደኛው “ሁሉ” ስለሚል የተዋጀ ማንነት ቢኖረንም፣ ገና ሁሉንተናችን[62] ተዋጅቶ እንዳላበቃ፣ በቀጣይነትም "ድረስ" ስለሚል የተጀመረና

[61] መንፈስ ቅዱስ የተስፋው መንፈስና ርስታችን ነው፤ ስንል ለዘመናት ሲጠበቁ የኖሩት ለወደፊትም የሚጠበቁት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ተስፋዎች ማለትም ጽድቅ፣ ልጅነት፣ ክብር . . . በክርስቶስ አምነን መንፈስ ቅዱስን ስንቀበል በእርሱ ስላገኘናቸውና ስለምናገኛቸው ነው፡፡

[62] 1ተሰ. 5፡23



For more books www.amharicchristianbooks.com

በሂደት ላይ ያለ ሥራ መኖሩን ያሳየናል፡፡ ለዚህም ነው በኤፌ. 4፡30 ላይ "ለቤዛ ቀን የታተማችሁበትን ቅዱሱን የእግዚአብሔርን መንፈስ አታሳዝኑ" በማለት ከፊታችን የሥጋችንን ቤዛነት የሆነ ትንሳኤ እንደሚጠብቀን የሚጠቁመው፡፡ እዚህ ጋ አንድ ጥገኛ የሆነ ከመለመዱና ቤተኛ ከመሆኑ የተነሳ እንደ እውነት የሚቆጠር ስህተት አለ፡፡ "እግዚአብሔር በዋነኝነት ሊያድን የሚፈልገው ነፍሳችንን ነው፡፡" "ነፍሴ ከዳነች ምን እፈልጋለሁ?" "ክርስቶስ ኢየሱስ የሞተው ነፍሴን ለማዳን ነው፡፡" ወ.ዘ.ተ የሚል፡፡ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የሞተው ለመንፈሳችን፣ ለነፍሳችን፣ ለስጋችንም ባጠቃላይ ለሁለንተናችን ድነት እንጂ ለነፍሳችን ብቻ አይደለም፡፡ "ነፍሴ ከዳነች ምን እፈልጋለሁ?" የሚለው አባባል የፈለገውን ያህል መንፈሳዊ ይምሰል የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስን የማዳን ሥራ የሚያሳንስ፣ የእግዚአብሔርንም ክብር ምስጋና የሚያጎድል እንጂ የማዳን ዕቅዱን በትክክል የሚያሳይ አይደለም፡፡

መዳን ምንድነው? መዳን ቤዛነትን ማግኘት ነው፡፡ ቤዛነት ደግሞ አስቀድመን እንዳልነው ከትክክለኛ ባለቤቱ እጅ ወጥቶ ባለቤት ባልሆነ ባላንጣ እጅ የገባውን፣ ባለቤቱ ዋጋ ከፍሎ ሲገዛውና መልሶ በእጁ ሲያስገባው ማለት ነው፡፡

ታዲያ ቁጥር 7 ላይ "… እንደ ፀጋው ባለጠግነት መጠን በደሙ የተደረገ ቤዛነታችንን አገኘን …፡፡" ብሎን ሲያበቃ በመቀጠል ቁጥር 14 ላይ ". . . ለእግዚአብሔር ያለውን ሁሉ እስኪዋጅ ድረስ . . . ፡፡"[63] ለምን ይላል? እነዚህ ሁለት ክፍሎች፣ አንደኛው ስለ አላፊ ጊዜ ሌለኛው ደግሞ ገና ሊሆን ስላለው የወደፊት ጊዜ የሚናገሩ ናቸው፡፡ በመስቀል ላይ ከተሠራው ሥራ የተነሳ በደሙ የኃጢያትን ሥርየት አግኝተን ዳግመኛ ተወልደናል፡፡ የተወለደውም መንፈሳችን ነው፡፡[64] ነገር ግን ዳግም በተወለድን ጊዜ ይህን ርስት ያገኘው ስሉስ ከሆነው ሁለንተናችን መሃል አንዱ፣ መንፈሳችን ብቻ ነው፡፡ ለምሳሌ ሥጋችን ገና ሁለተኛ አልተወለደም፣ ገና አልተዋጀም፣ ገና በሕይወት አልተዋጠም፣ ገና አልወረሰም፣ አልተወረሰም፡፡

> *"ክርስቶስ በእናንተ ውስጥ ቢሆን ሰውነታችሁ በኃጢአት ምክንያት የሞተ ነው፣ መንፈሳችሁ ግን በጽድቅ ምክንያት ሕያው ነው፡፡" ሮሜ 8፡10*

እንደሚል□□ ነገር ግን ስጋችን ሙት እንደሆነ አይቀርም፡፡ አንቀላፍተንም ይሁን ነቅተን ክርስቶስ ሲመጣ ቤዛነትን ያገኛል፡፡ ሐዋርያው በመቀጠል፡-

[63] መዋጀትና መቤዠት የሚሉት አማርኛ ቃላት በግሪክ ተመሳሳይ ቃል ናቸው፡፡

[64] ዮሐ. 3፡5



For more books www.amharicchristianbooks.com

> *"ነገር ግን ኢየሱስን ከሙታን ያስነሳው የእርሱ መንፈስ በእናንተ ዘንድ ቢኖር ክርስቶስ ኢየሱስን ከሙታን ያስነሳው እርሱ በእናንተ በሚኖረው በመንፈሱ ለሚሞተው ሰውነታችሁ ደግሞ ሕይወትን ይሰጠዋል፡፡" ሮሜ 8፡11*

ይላልና፡፡ በኤፌሶን 1፡14 ላይ "እስኪዋጅ ድረስ" የሚለው አሳብ በዘመን ፍፃሜ ይደረግ ዘንድ ያለውን መጠቅለል የሁለንተናን መዳን የሚያሳይ ነው፡፡ ሐዋርያው በዚሁ መልዕክት ውስጥ ይህን አሳብ በሙሉ መልኩ ይደግመዋልና፡፡

> *"ለቤዛም ቀን የታተማችሁበትን ቅዱሱን የእግዚአብሔር መንፈስ አታሳዝኑ፡፡" ኤፌ. 4፡30*

በማለት፡፡ ይህ ገና ወደፊት ይፈፀም ዘንድ ያለ የሰውነት ቤዛነት ቀድሞ ያገኘነውን የመንፈስ ቤዛነት ተከትሎ የሚመጣ በዘመን ፍፃሜ የሚከናወነውን ሁለንተናዊ ድነት የሚያመላክት ነው፡፡ እነዚህ ሁለቱ ያለፉና ገና የሚመጣ፣ ባመንንበት ቅጽበት የተፈፀመና ጌታ ዳግም በሚመጣበት ቅጽበት የሚከናወን የመንፈስና የስጋን ቤዛነት ያመለክታሉ፡፡ የነፍሳችን መዳን ግን ዘመናችንን በዋጀን [65] መጠን በጊዜ ሂደት ውስጥ የሚፈፀም የአዕምሮአችን መታደስ ውጤት ነው፡፡ [66]

ከዚህ በመነሳት መዳን ወይም ቤዛነት መውረስና መወረስ መሆኑን ማየት እንችላለን፡፡ መንፈሳችን ከተያዘበት ከጨለማው ስልጣን፣ ከኃጢአትና ከሞት እጅ ተላቆ በእግዚአብሔር መንፈስ ውስጥ ሲገባ፣ መንፈስ ቅዱስም ወደ መንፈሳችን ሲገባ እግዚአብሔርን ወርሰን (ርስትን ተቀበልን) በእግዚአብሔርም ተወረስን (የባለቤትነት ማህተም ታተሙብን) ማለት ነው፡፡ መውረስና መወረስ የማይነጣጠሉ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ናቸውና፡፡ የተጠራነውም እግዚአብሔርን ልንወርስ፣ በእግዚአብሔርም ልንወረስ ነው፡፡ መጽሐፍስ "የእግዚአብሔር ዕድል ፈንታ ሕዝቡ ነው፡፡ ያዕቆብም የርስቱ ገመድ ነው፡፡" ዘዳ. 32፡9 ይል የለ!

## <u>ለክብሩ ምስጋና</u>

ይህ ክፍል አሃዱ ያለው በምስጋና፣ የሚቀጥለውና የሚደመድመውም በምስጋና ነው፡፡ በቅድሚያ *"በውድ ልጁም እንዲያው የሰጠን የፀጋው ክብር ይመሰገን ዘንድ ይህን አደረገ፡፡"* ቁ.6 በማለት የገዛ የራሱን ክብር በገዛ ራሱ ፈቃድ በክርስቶስ

---

[65] ኤፌ. 5፡16

[66] ኤፌ. 4፡23



For more books www.amharicchristianbooks.com

ኢየሱስ ከሰጠን በኋላ ፈጽሞ የእኛ ያልሆነ የእርሱ ክብር እኛ ላይ ተገልጦ እርሱ ይመስገን ዘንድ ለቅድስናና ለነውር አልባ ሕይወት እኛን መምረጡንና ለልጅነት መወሰኑን ነገረን፡፡ በመቀጠልም አስቀድመው የተወሰኑትና አስቀድመው ተስፋ ያደረጉት እስራኤላውያን በክርስቶስ አምነው ዳግም በመወለድ የዘላለም ርስት የሆነውን መንፈስ ሲቀበሉ በእነርሱ ላይ የተገለጠው ክብሩ እንዲመሰገን፡- *". . . ለክብሩ ምስጋና እንሆን ዘንድ ነው፡፡"* ቁ.12 በማለት የምስጋናውን ምክንያት ነገረን፡፡ በመጨረሻም በወንጌል ያመኑ አይሁድና አሕዛብ የጋራ ርስታቸው በሆነው በመንፈስ ቅዱስ በአንድ ተጣምረው በልጅነት ክብር ሲገለጡ፣[67] ፍጥረት ሁሉ ሲታደስና በእግዚአብሔር ክብር ሲዋጥ፣ ውሃ ባሕርን እንደሚከድን፣ ምድር እግዚአብሔርን በማወቅ ስትሞላ፣[68] ከጥንት ጀምሮ በቅዱሳን ነቢያቱ አፍ የተናገረው፣ ነገር ሁሉ የሚታደስበት ዘመን ሲመጣ፣[69] ለእግዚአብሔር የሚቀርበውን ምስጋና በማስመልከት *"ይህም ለክብሩ ምስጋና ይሆናል" ቁ.14* በማለት በአራት ነጥብ ትንፋሹን ይሰበስባል፡፡

ይህንንም የሚያደርገው ሥርዓቱን በጠበቀ መልኩ እንደ መዝሙር አዝማችና ቁጥር ከተወሰኑ ቁጥሮች በኋላ በየመሃሉ ሃሳቡን እየገታ ምስጋና በማቅረብ ነው፡፡ አፃፃፉም የሥላሴን እውነት አጉልቶ የሚያሳይ ነው፡፡ ሥላሴ የሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በቀጥታ፣ ቃል በቃል እንዳልተፃፈ ብናውቅም፣ እውነቱ ግን በሸማ ላይ እንደሚጠለፍ ድርና ማግ ግልጽ በሆነ መንገድ እንደተሸመነ ማየት አያዳግትም፡፡ ታዲያ ምንም እንኳ በየአንዳው አብንም፣ ወልድንም፣ መንፈስ ቅዱስንም በሦስት አካልነት ቢጠቅስም ምስጋናው ግን የብዙ አለመሆኑ ልብ ሊባል የሚገባው ጉዳይ ነው፡፡ *"የፀጋው ክብር ይመሰገን ዘንድ . . . ለክብሩ ምስጋና እንሆን ዘንድ . . . ለክብሩ ምስጋና ይሆናል፡፡"* በማለት ለአንድ የሚሆን ምስጋና ያቀርባልና፡፡ ይህም የእግዚአብሔርን ሦስት አካልነትና አንድ አምላክነት በገሃድ ያሳየናል፡፡

እኔ ግን ይህን ምዕራፍ ከማገባደዴ በፊት ጥቂት የሙግት ጥያቄዎችን ላነሳ እፈልጋለሁ፡፡ ቅዱስ ቃሉ ምንም በማያሻማ መልኩ፣ በጥቁርና በነጭ በደማቁ "በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ ባረከን" በማለት መባረካችን የተፈፀመና የተከናወነ መሆኑን፣ እንከፍጣፊ ያልቀረበት ሙሉ መሆኑን ካበሰረን በኋላ፣ ለአማኞች ባርከን ብሎ መፀለዩ፣ ይባርከናል ብሎ ተስፋ መጣሉ፣ በረከት ፍለጋ ከስፍራ ስፍራ

[67] ሮሜ 8፡ 18-21
[68] ኢሳ. 11፡9
[69] ሐዋ.ሥራ 3፡21



For more books www.amharicchristianbooks.com

መዋለሉ ከየት መጣ? እንደተሰጠው የተነገረው ሰው ያመሰግናል እንጂ ዳግም አይለምንም! ታዲያ ሕይወታችንን ስንፈትሽ፣ የፀሎት ጓዳችንን ስንመረምር፣ የተሞላው በልመና ነው ወይስ በምስጋና? የምናመሰግንም ከሆነ የምስጋናችን እፍታው፣ አውራውና አንኳሩ የሚተመው ስለበላን ስለጠጣን፣ ስለለበስን ስላጌጥን፣ ስለተማርን ስለተመረቅን፣ ስለሠራን ስለተከናወንን፤ ስለ ነገድን ስላተረፍን፣ ስላገባን፣ ስለወለድን፣ ስለተሾምን፣ ስለከበርን ነው? ወይስ በአብ ተጠርተንና በወልድ ተዋጅተን የዘላለም ርስት የሆነውን መንፈስ ቅዱስን ስለተቀበልን ነው? ይህን ስል ከላይ ስለዘረዘርኳቸው ነገሮች ልናመሰግን አይገባም ማለቴ አይደለም፡፡ ፈጽሞ!! ነገር ግን እነዚያን ብናገኛቸውም ባናገኛቸውም የማይነጥፍ የምስጋና ዥረት ከልባችን ሊፈልቅ የሚገባው ስለዚህኛው ነው ማለቴ እንጂ፡፡ በዚህ ክፍል የተሠራልንን ሥራና የተሰጠን ስጦታ ምንነት ብንረዳ በከፍታም ይሁን በዝቅታ፣ በሐዘንም ይሁን በደስታ፣ በማግኘትም ይሁን በማጣት የማይጎድል የምስጋና በጀት በእቅፋችን አለ ማለት ነው፡፡ ለፀጋው ክብር ምስጋና ይሁን፡፡ አሜን፡፡



For more books www.amharicchristianbooks.com

# ምዕራፍ ፪
# ልመና

ኤፌ. 1፡15 – 23

ይህን መጽሐፍ ማዘጋጀት በጀመርኩበት ሰሞን የጥንቷን ኤፌሶንን ጨምሮ በርካታ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ታሪካዊ ቦታዎች ወደሚገኙባት ዘመናዊቷ ቱርክ ተጉዤ ነበር፡፡ የሄድኩትም የቱርክ የቱሪዝምና የንግድ ማዕከል ወደ ሆነችው የቤዛንታይኗ "ኮንስታንቲኖፕል" በኋላም የኦቶማኖቹ ኢስታንቡል ከተማ ነበር፡፡ ዓላማዬ ጉብኝት ነበርና የነበረኝን አራት ቀናት በአግባቡ ለመጠቀም እቅዴን ዘረጋሁና እንቅስቃሴዬን ጀመርኩ፡፡ የሦስተኛው ቀን መርሃ ግብር በሞተር ጀልባ የሙሉ ቀን ጉብኝት ማድረግ ነበርና በሰዓቱ በባህሩ ዳርቻ ደርሼ በጀልባዋ ተሳፈርኩና እንደ እኔ ኢስታንቡልን ለመጎብኘት ከተለያየ ዓለም ከመጡ ጎብኚዎች ጋር ጉዞ ተጀመረ፡፡ ጉዞአችን በስተደቡብ የማርማራ ባሕርንና በስተ ሰሜን ጥቁር ባሕርን በሚያገናኘው፣ የአውሮፓዋን ኢስታንቡልና የኤዥያዋን ኢስታንቡል መሐል ለመሃል በሚከፍለው "ቦስፈርስ" በተሰኘ የባሕር ሰርጥ ላይ ነበር፡፡ ይህ የሁለት ግዙፍ አህጉሮች መለያ የሆነ ሰርጥ በሁለት ግዙፍና ረዣዥም ድልድዮች የተጋጠመ ነው፡፡ ባጭር ቃል የከተማዋ ውበት የራሱ መሳጭ ገጽታ ነበረው፡፡ በጀልባው ጫፍ ላይ ወጥቼ በአድናቆት እየተመለከትኩ ሳለ ቁመናው ሰብሰብ፣ እንቅስቃሴው ቀልጠፍ፣ ንግግሩ ፈጠን ያለው ቱርካዊ አስጎብኛችን ወዳለሁበት መጣ፡፡ አድናቆቴን እንዲጋራኝ የልቤን ጥቂት ተነፈስኩለት፡፡ እሱም ወንበር ሳብ አድርጎ ከተቀመጠ በኋላ ከተማይቱን ለአንድ ሺህ ዓመታት የነገሱባት ቤዛንታይን እንዴት ከሮም ወደዚህ ሊመጡ እንደቻሉ አንድ አፈ-ታሪክ መሰል ወግ ያጫውተኝ ጀመረ፡፡

በጥንት ዘመን በሮም የሚኖሩ ሰዎች ቦታ ጠበባቸውና የሚሄዱበት ተቸገሩ፡፡ ከብዙ ምክር በኋላ ጓዛቸውን ጠቅለው መኖሪያ ሥፍራ ፍለጋ መጓዝ እንዳለባቸው ተስማሙና ለጉዞ ተሰናዱ፡፡ ከመሃከላቸው በእድሜ የገፉ አንድ ሽማግሌ "ጉዞ ከመጀመራችን በፊት በአቅራቢያችን አንዲት ከአፏ የወጣ ቃል መሬት የማይወድቅ አዋቂ (oracler) ሴት አለችና እሷን ጠይቀን እንንቀሳቀስ" ብለው አሳብ አቀረቡ፡፡ ሁሉም ተስማሙና ወደ አዋቂዋ ሄደው "ለእርሻም ሆነ ለከብቶቻችን የሚሆን ሥፍራ ስለጠበበን መኖሪያ ቦታ ፍለጋ መሄዳችን ነው፡፡ ነገር ግን ወዴት እንደምንሄድ አናውቅምና በመንገድ ምን የሚገጥመን ይመስልሻል?" ብለው



For more books www.amharicchristianbooks.com

ይጠይቋታል፡፡ ሴቲቱም በጥሞና ከሰማቻቸው በኋላ “ርቃችሁ ሂዱ፣ በየብስም በባሕርም ተጓዙ፣ ከረዥም ጉዞ በኋላ አንድ ብዙ ዓይነስውሮች የሚኖሩባት፣ የዓይነ ስውሮች ከተማ ታገኛላችሁ፣ ያ መኖሪያችሁ ነውና በዚያ ተቀመጡ፡፡” በማለት ትመክራቸዋለች፡፡ ሰዎቹም እንደተነገራቸው ጉዞ ይጀምሩና ብዙ ከተሞችን አልፈው በባህርም በየብስም ይነጉዳሉ፡፡ በየደረሱበትም ዓይነስውሮች የሚበዙበትን ከተማ ይፈልጋሉ፣ ሲያጡ ጉዟቸውን ይቀጥላሉ፡፡ ከብዙ ጉዞ በኋላ እዚህ ስፍራ (የቀድሞዋ ኮንስታንቲኖፕል የአሁኗ ኢስታንቡል) ይደርሱና እንደ ልማዳቸው በከተማይቱ ዓይነስውራን ይበዙ እንደሆነና እንዳልሆነ እየተዘዋወሩ ያጣራሉ፡፡ ሆኖም ሌላ ነገር ዓይናቸውን ይስበዋል፡፡ የሥፍራው ውበት፣ የተፈጥሮ ፀጋ ድንቅ የመልከዓ ምድራዊ አቀማመጥ ይማርካቸውና እርስ በርሳቸው ይነጋገራሉ፡፡

በኋላም የከተማይቱ ሰዎች አድናቆታቸውን ያጋሯቸው ዘንድ ስለ ስፍራው ውበት ሲያወሯቸው መልስ የሚሰጣቸው ያጣሉ፡፡ ካጋጠሟቸው የከተማይቱ ሰዎች መሃል ስለ ስፍራው የሚደነቅ፣ የሚደሰትና መልካም ነገር የሚያወራ አንድም ሰው አላገኙም፡፡ እነርሱም ተሰበሰቡና እንዲህ ተባባሉ፡፡ “ያች አዋቂ የነገረችን ዓይነ ስውሮች የሚበዙባት ከተማ ከዚህ ሌላ ልትሆን አትችልም፡፡ ተመልከቱ የዚህች ከተማ ሰዎች እንዲህ ያለ ውብ ስፍራ ላይ ተቀምጠው ውበቱን ማየትና ማድነቅ አልቻሉም፡፡ ስለዚህ ስፍራችን እዚህ ነው፡፡” ብለው ሰፈሩባት፡፡ ለአንድ ሺህ ዓመታትም ኖሩባት፡፡ መቀመጫቸውንም እዚህ አድርገው የያኔውን ዓለም ገዙ፣ በማለት አጫወተኝ፡፡ አብዱላሂ በተሰባበረ እንግሊዝኛው እየተረከልኝ ሳለ እኔ ግን በሌላ አሳብ ተውጫለሁ፡፡ አሳቤም ኤፌሶን 1፡15 – 2፡10 ላይ ነበር፡፡

በቀደመው ምዕራፍ ጸሐፊው የመረጠንን፣ የዋጀንን፣ በጥቅሉ በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ የባረከንን እግዚአብሔርን መልሶ በመባረክ በአንድ የብዕር ትንፋሽ ያቀረበውን አስደናቂ ምስጋና ተመልክተናል፡፡ በዚህ ሁለተኛ ክፍል ደግሞ ድምፁን ቃና በመለወጥ ከምሥጋና ወደ ልመና ሲዞር እንመለከታለን *". . . ስለ እናንተ እያመሰገንሁ ስጸልይ ስለ እናንተ ማሳሰብን አልተውም . . . እለምናለሁ፡፡"* (1፡16) በማለት፡፡ ልመናው የመልዕክቱ ተደራሲያን ለሆኑት አሕዛብ አማኞች ስለ መሆኑ ምንም ጥርጥር የለውም፡፡ የሚለምነው ግን ዳግም እንዲባረኩ ሳይሆን የተባረኩትን በረከት እንዲያውቁ ነው፡፡

*ይህንንም “. . . የልቦናችሁ ዓይኖች ሲበሩ የመጥራቱ ተስፋ ምን እንዲሆን፣ በቅዱሳኑም ዘንድ ያለው የርስት ክብር ባለጠግነት ምን እንዲሆን፣ ለምናምንም ከሁሉ የሚበልጥ የኃይሉ ታላቅነት ምን እንዲሆን ታውቁ ዘንድ ነው . . .”*



For more books www.amharicchristianbooks.com

(1፡18፥19) በማለት ይገልጸዋል፡፡

መቼም ዓይኑ እንዲበራለት የሚያስፈልገው ማየት የተሳነው ስለመሆኑ ሳይታለም የተፈታ ነው፡፡ ስለዚህ ሐዋርያው በሌላ አገላለጽ፡- "ታላቅ ርስት ተሰጥቷችኋል፣ ነገር ግን እናንተ ዓይነ ስውር ናችሁ፣ የርስቱን የተስፋ ሕያውነት፣ የክብር ባለጠግነት፣ የኃይል ታላቅነት ታዩና ታደንቁ፣ ለርስቱም እንደሚገባ ትመላለሱ፣ ከዚህም ርስት ሊያፈናቅሏችሁ የሚመጡትን ጠላቶቻችሁን በጽናት ትቃወሙ ዘንድ ርስቱን ማወቅ ያስፈልጋችኋል፡፡ ስለዚህ እኔም ርስቱን የሰጣችሁንና እርሱ ራሱ ርስታችሁ የሆነውን እግዚአብሔርን ታውቁ ዘንድ ዓይኖቻችሁ እንዲበሩ እለምናለሁ" የሚል ይመስላል፡፡ ምንም እንኳ የሥጋ ዓይናቸው በግንባራቸው ተሰክቶ አጥርቶ እያየ ከቦታ ቦታ ቢያመላልሳቸውም ልቦናቸው አስተውሎ የሚኖሩበትን ሥፍራ ሊያደንቁ ያልቻሉትን የጥንት የኢስታንቡል ሰዎች ከሮም የፈለሱት ቤዛንትያን "ማየት የተሳናቸው" እንዳሏቸው ሁሉ እኛም በክርስቶስ የተሰጠንን የሕይወት ርስት ካላወቅንና ካላደነቅን ከእነርሱ በምንም አንለይም፡፡

ይህን እውነት ለመረዳት አንድ ጋሻ መሬት በስጦታ የተሰጠው ማየት የተሳነው ሰው በምናባችን እንሳል፡፡ የተሰጠውን መሬት ለማየት ቢወርድ የመሬቱን አቀማመጥ፣ የእርሻውን ለምነት፣ በውስጡ ያሉትን የተክሎችና የአዝርት ዓይነት ባጠቃላይ ስፋቱንና ልኩን በምን አይቶ ሊያመሰግን ይችላል? ፍለጋ የሌለውን የክርስቶስን ባለጠግነት ለአሕዛብ ይገልጥ ዘንድ አስቀድሞ ከአይኑ ቅርፊት የወደቀለት የተርሴሱ ጳውሎስ ስላየው ርስት ተደንቆ እግዚአብሔርን ባረከ፣ ርስቱ እኩል ለእኛም ተሰጥቷልና እኛም እንድናይ ይለምንልን ጀመር፡፡ በዙሪያው በከበቡት የሦርያ ጭፍሮች ጠላቶቹን ብቻ እያየ “ወየው ጠፋን” ለሚለው ሎሌው “አቤቱ እባክህ ያይ ዘንድ ዓይኖቹን ክፈት” ብሎ እንደለመነው ነቢይ ሐዋርያውም ያየውን እንድናይ ይማልድልናል፡፡[70]

ሙሴ ከየነገዱ አለቆች 12 መርጦ የተስፋይቱን ምድር እንዲሰልሉ በላካቸው ጊዜ የልብ ዓይናቸው ታውሮ በሥጋ ዓይናቸው ብቻ የተመለከቱት አሥሩ ስለምድሪቱ ክፋት እያወሩ የሕዝቡን ልብ ሲያርዱ ልዩ የጥበብና የመገለጥ መንፈስ[71] የሞላባቸው ኢያሱና ካሌብ መላውን የእስራኤል ማህበር ፀጥ አሰኝተው የርስቱን ታላቅነት እንዳወጁ፤ ዛሬም ርስቱን ለማወቅና፣ በርስቱ ላይ ለመኖር፣ የርስቱንም ባለጠግነት ለመካፈል፣ በጥበብና በመገለጥ መንፈሳዊ የልብ ዓይናችን ሊበራልን

[70] 2ነገሥት 6፡ 14-17

[71] ዘኁ. 32፡11-12; 14፡24; ዘዳ. 34፡9



For more books www.amharicchristianbooks.com

ያስፈልጋል፡፡ ይህ እውነት የገባቸው አማኞች ሌላ በረከት እንዲባረኩ ሳይሆን፣ የተባረኩበት በረከት እንዲገለጥላቸውና እንዲገለጥባቸው ይለምናሉ፡፡ እነርሱም ካዩ በኋላ ላላዩት ያዩ ዘንድ ይማልዳሉ፣ ይጋደላሉም፡፡ የተሰጠንን ርስት የክብር ባለጠግነትና፣ የኃይል ታላቅነት እናውቅ ዘንድ እግዚአብሔር የልብ ዓይኖቻችንን ያብራ! አሜን!!

## <u>የመዳን ማረጋገጫ</u>

> *"ስለዚህ እኔ ደግሞ በእናንተ ዘንድ ስለሚሆን በጌታ በኢየሱስ ስለማመንና ለቅዱሳን ሁሉ ስለሚሆን መውደድ ሰምቼ ስለ እናንተ እያመሰገንሁ ስፀልይ ስለ እናንተ ማሳሰብን አልተውም . . ." ኤፌ.1፡15*

ሐዋርያው ለሚጽፍላቸው አማኞች ይፀልያል፡፡ ይህም የዘወትር ልማዱ ነው፡፡[72] በዋነኝነት የሚፀልየውም የተሰጣቸውን እንዲያውቁ ነው፡፡ ሆኖም እንዲሁ በመላምት አይፀልይም ስለ እነርሱ በክብር አባት ፊት የሚቀርብላቸውን "አማኞች" ማንነት አስቀድሞ ማወቅ ይሻል፡፡ በዚህ ጽሁፍ መግቢያ ላይ በጥልቀት እንደተመለከትነው፣ ይህም ክፍል እንደሚነግረን ጳውሎስ መልዕክቱን የሚጽፍላቸውን አማኞች በአካል አያውቃቸውም፡፡ "ሰምቼ" ይላልና፡፡ ታዲያ በአፀደ-ሥጋ ስላላያቸው ነገር ግን ወንጌልን እንደ ተቀበሉ መረጃ ስለ ደረሰው አማኞች ከመፀለዩ በፊት የእምነታቸውን እውነተኝነት የሚመዝንበት አንድ የማያወላዳ ሚዛን እንዳለው መረዳት እንችላለን፡፡[73]

በእርግጥ ዛሬ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስ ከያዙ፣ የጌታን ስም ከጠሩ፣ ወደሚታወቅ ቤተክርስቲያን ከሄዱ፣ መዝሙር ከዘመሩና የተለመዱ ክርስቲያናዊ ቃላት ከተጠቀሙ አማኞች ብለን ለመጥራት አንቸገርም፡፡ በተለይ በልሳን ከተናገሩ፣ ትንቢት ካመጡ፣ ከሰበኩና ለበሽተኞች ከፀለዩማ እነርሱን መመርመር መንፈስ ቅዱስን እንደመጠርጠር ይቆጠራል፡፡ እነዚህ የእውነተኛ የአማኝና የአገልጋይ መለያ ማህተም ተደርገው ተወስደዋልና፡፡

ሐዋርያው ግን ስለነርሱ የሰማውን መንፈሳዊ ማንነት ለመረዳት የጠየቃቸው ጥያቄዎች ሁለት ብቻ ናቸው፡፡ እነዚህ ጥያቄዎች በየትኛውም ዘመን፣ በየትኛውም ስፍራ የአማኞችን ማንነት መለያ "አሲድ ቴስት" ወይም "የሊትመስ ወረቀቶች"

---

[72] 2ቆሮ. 13፡9; ፊሊ. 1፡3-5; ቆላ. 1፡3-5; 1ተሰሎ. 1፡2-3; 3፡9-10

[73] ይህንኑ ሀሳብ በቆላ. 1፡ 3-8፤ በ1ኛ ተሰሎ. 1፡ 2-3፤ በ2ኛ ተሰሎ. 1፡ 3-4 ላይ እናገኛለን፡፡



For more books www.amharicchristianbooks.com

ናቸው ማለት ይቻላል፡፡[74] የሐዋርያው መመዘኛዎች "እምነት" ና "ፍቅር" መሆናቸውን እናያለን፡፡ የአዲስ ኪዳንን ገፆች ከዳር እስከ ዳር ብንዘልቅ ከዚህ ሌላ የሕይወት ማንጠሪያ እሳት፣ መለኪያ ሚዛን አናገኝም፡፡

እምነትና ፍቅር አንድ ሆነው ሳሉ ሁለት አቅጣጫ አላቸው:- "እምነት" በጌታ በኢየሱስ፣ "ፍቅር" ለቅዱሳን ሁሉ፡፡ አንዱ ወደ ላይ ሌላው ወደ ጎን፡፡ የሚያያዙትም እንዲህ ነው፡፡ አንድ ሰው ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ሲያምን ከእግዚአብሔር ይወለዳል፣ መንፈስ ቅዱስ በውስጡ ያድራል፡፡ ይህ በውስጡ ያደረ እግዚአብሔር ደግሞ ፍቅር ነው፡፡ "በፍቅር የሚኖር በእግዚአብሔር ይኖራል፣ እግዚአብሔርም በእርሱ ይኖራል" ተብሎ እንደተፃፈ[75] ሁሉን የሚያቅፍ የእግዚአብሔር ፍቅር አይሁድ አሕዛብ ሳይል፣ ባርያ ጌታ ሳይለይ፣ ምሁር መሃይም ሳይመርጥ በክርስቶስ ኢየሱስ አምነው ለዳኑ ቅዱሳን ሁሉ ይገለጣል፡፡ ይህም ሰው ከእግዚአብሔር የተወለዱትን ሁሉ ይወዳል፡፡ ቅዱሳንን ሁሉ መውደድ ማለት፣ ባሕሪያቸውን ሁሉ፣ አመለካከታቸውን ሁሉ፣ ሥራቸውን ሁሉ መውደድ ማለት አይደለም፡፡ ነገር ግን ከእነዚህ ነገሮች ሁሉ ባሻገር የትንሳኤውን ጌታ በውስጣቸው እያየን በእርሱ እናውቃቸዋለን፣ እንቀበላቸዋለን፣ እንራራላቸዋለን፣ መልካምም እናደርግላቸዋለን ማለት ነው፡፡ ይህ ደግሞ ከእግዚአብሔር የመወለዳችን፣ የተስፋውን መንፈስ የመቀበላችን ዋና ማረጋገጫ ነው፡፡ ሐዋርያውም ይህን ስላረጋገጠ ነው ስለእምነታቸውና ስለፍቅራቸው እያመሰገነ የልብ አይኖቻቸው እንዲበሩ የሚለምነው፡፡ እነዚህ ከሐዋርያት ዘንድ ፈጽመው የማይጠፉ መመዘኛዎች ዛሬም ከእኛ ሊሰወሩ አይገባቸውም፡፡

## የጥበብና የመገለጥ መንፈስ

በዚህ ሥፍራ ሐዋርያው የተለያዩ የፀሎት ዓይነቶችን ሥራ ላይ አውሎአል፡፡ የሚጽፍላቸው አማኞች ኢየሱስ ክርስቶስን በማመን ከላይ የጠቀሰውን በረከት (1፡3-14) ስለ ተካፈሉ እያመሰገነ ይፀልያል፣ አዘውትሮም ያሳስባል፣ እግዚአብሔርን ያውቁ ዘንድ የጥበብና የመገለጥ መንፈስ እንዲሰጣቸው አብዝቶ ይለምናል፡፡ ልመናውም ያነጣጠረው በመጽሐፉ ሁሉ ውስጥ በድንቅ ተሰናስሎ እንደምናየው የክብር አባት ብሎ ወደሚጠራው የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ ነው፡፡ የ

[74] እነዚህ ነገሮች በላብራቶሪ ውስጥ የአንድ ንጥረ ነገር የአሲድ መጠንና የአልካላይን መጠን የሚታወቅባቸው ቀላል መሳሪያዎች ናቸው፡፡

[75] 1ዮሐ. 4፡17-16



For more books www.amharicchristianbooks.com

“ክብር አባት” ማለቱ መንፈሱን በመካፈል ክብሩን ይወርሱ ዘንድ ላላቸው ሁሉ አባት መሆኑን ለማሳየት ሲሆን "የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ” ማለቱ ደግሞ ወልድ ሰው ሆኖ በምድር ላይ በስጋ በተመላለሰበት ጊዜ ሁሉ እንዳመለከውና ፍፁም በሆነ መንገድ እንደተገዛለት ለማሳየት ነው፡፡ ጌታ ኢየሱስ ፍፁም አምላክ ቢሆንም እንኳ በሥጋ ልደት ፍፁም ሰው በመሆኑ አብ አባቱ ብቻ ሳይሆን አምላኩ ተብሎ መጠራቱ አግባብ እንደሆነ እናስተውላለን፡፡[76]

የሐዋርያው ልመና፣ አማኞች የክብርን አባት በሕይወት ልምምድ <u>እንዲያውቁ</u> ማድረግ የሚችለውን የጥበብና የመገለጥ መንፈስ እንዲያገኙ ነው፡፡ የጥበብና የመገለጥ መንፈስ በእነርሱ ዘንድ የሚሰራው ሥራ የልባቸውን ዓይኖች በማብራት የተጠሩበትን ተስፋ፣ በመካከላቸው ያለውን የእግዚአብሔርን ርስት ክብር ባለጠግነትና በውስጣቸው የሚሠራውን ከሁሉ የሚበልጠውን የኃይሉን ታላቅነት <u>እንዲያውቁ</u> ማድረግ ነው፡፡ እነዚህ የተሰመረባቸው ሁለት ማወቆች የሚያመለክቱት እግዚአብሔርን በማወቅና ርስቱን በማወቅ መካከል ልዩነት አለመኖሩን፣ እግዚአብሔርን አወቅን ማለት ርስቱን አወቅን፣ ርስቱን አወቅን ማለት ደግሞ እግዚአብሔርን አወቅን ማለት መሆኑን ነው፡፡ ስለዚህ ሐዋርያው በብርቱ የፈለገው ተደራሲያኑ አዲስና ያልነበራቸውን ለማወቅ እንዲጥሩ ሳይሆን የተሰጣቸውን በማወቅ እንዲያድጉ ነው፡፡ የተሰጣቸውን እንዲያውቁ ደግሞ የጥበብና የመገለጥ መንፈስ አስፈልጓቸዋል፡፡ ለዚህ ነው ከምንም አስቀድሞ የጥበብና የመገለጥ መንፈስ እንዲሰጣቸው የሚለምነው፡፡

ለመሆኑ የጥበብና የመገለጥ መንፈስ ማን ነው? ፈጥነን መንፈስ ቅዱስ ነዋ! እንደምንል እገምታለሁ፡፡ እንዲያ ከሆነማ ቀደም ሲል “በተስፋው መንፈስ በመንፈስ ቅዱስ ታተማችሁ” በማለት ባመንን ጊዜ መንፈስ ቅዱስ እንደ ተሰጠን ተናግሮ የለምን? ታዲያ አንዴ ከተሰጠን እንደ ገና እንዲሰጠን ልመናው ለምን አስፈለገ?

በቁጥር 13 ላይ በተጠቀሰው “መንፈስ ቅዱስ” እና በቁጥር 18 ላይ በተጠቀሰው “የጥበብና የመገለጥ መንፈስ” መካከል ልዩነት የለም፡፡ ነገር ግን በትኩረት ስንመለከተው የመጀመሪያው በግሪኩ መስተአምር (Article) ያለው ሲሆን ሁለተኛው ግን ይህ መስተአምር የለውም፡፡[77]

መንፈስ ቅዱስ አንድ ነው ሁለት ወይም ሦስት መንፈስ የለም፤ ነገር ግን አንዱ

---

[76] ማቴ. 27፥46

[77] ኤፌ. 1፥17 ን በሪቫይዝድ ስታንዳርድ ቨርዥን ያንብቡ



For more books www.amharicchristianbooks.com

መንፈስ ቅዱስ በርካታ የሚገለጥባቸው ሥራዎችና ባሕሪያት አሉት፡፡ የቅዱሳት መጻሕፍት ፀሐፊዎች መንፈስ ቅዱስንና ከእርሱ የሚሠርፁ ተግባራቱን ከእርሱ ጋር አያይዘው መፃፋቸው የተለመደ ነው፡፡ ለምሳሌ፡- “እግዚአብሔር የናዝሬቱን ኢየሱስን በመንፈስ ቅዱስ ፣በኃይልም ቀባው . . . ፡፡” (ሐዋ. 10፡38) ይላል፡፡ ጌታ ኢየሱስ የተቀባው በመንፈስ ቅዱስ ነው፣ ታዲያ "በኃይል" የሚለውን መጥቀስ ለምን አስፈለገ? እንል ይሆናል፡፡ ለማሳየት የተፈለገው መንፈስ ቅዱስ በናዝሬቱ ኢየሱስ ላይ በዮርዳኖስ ወንዝ የመጣው ከፊት ባሉት ሦስት ዓመት ተኩል በኃይል የሚገለጠውን የጌታ ኢየሱስን አገልግሎት ለማመልከት ነው፡፡

በሌላም ስፍራ በተመሳሳይ ሁኔታ ጳውሎስ “. . . ቃሌም ስብከቴም መንፈስንና ኃይልን በመግለጥ ነበር፡፡” 1ቆሮ. 2፡4 ይላል፡፡ በአንድ ስፍራ ደግሞ መንፈስ ቅዱስ በአማኞች ላይ የሚመጣው የማጥራትን ሥራ ለመስራት መሆኑን ማሳየት ሲፈልግ “. . . እርሱ በመንፈስ ቅዱስና በእሳት ያጠምቃችኋል፡፡” ሉቃ. 3፡16 ብሏል፡፡ ሐዋርያው ጴጥሮስ በታላቅ መከራ ውስጥ ለነበሩት አማኞች ሲጽፍ፣ ከሚያልፉበት ውርደት የተነሳ በወቅቱ የሚያስፈልጋቸው የመንፈስ ቅዱስ ሥራ በእግዚአብሔር ዘንድ ያላቸውን ክብር መግለጥ መሆኑን ለማመልከት “ስለ ክርስቶስ ስም ብትነቀፉ የክብር መንፈስ የእግዚአብሔርም መንፈስ በእናንተ ላይ ያርፋልና፡፡” (1ጴጥ. 4፡14) በማለት ሲጽፍላቸው እናነባለን፡፡ በእነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በቅፅልነት አብረው የተጠቀሱ ኃይል፣ እሳት፣ ክብር የሚሉ ስያሜዎች ሌላ መንፈስን የሚያመለክቱ ሳይሆኑ ከአንዱ ከመንፈስ ቅዱስ የሚወጡ የእርሱ ባህሪና ሥራ መገለጫዎች መሆናቸውን በቀላሉ መረዳት እንችላለን፡፡

ጳውሎስ የጥበብና የመገለጥን መንፈስ ሲጠቅስ፣ ኢሳይያስ ስለመሲሁ ትንቢት በተናገረበት ክፍል ከእሴይ ግንድ በትር እንደሚወጣ ከስሩም ቁጥቋጥ እንደሚያፈራ የጻፈበት ክፍል በውስጡ አልነበረም ማለት ያስቸግራል፡፡ ኢሳያስ “የእግዚአብሔር መንፈስ፣ የጥበብና የማስተዋል መንፈስ፣ የምክርና የኃይል መንፈስ፣ የዕውቀትና እግዚአብሔርን የመፍራት መንፈስ ያርፍበታል፡፡” (ኢሳ. 11፡12) በማለት በግልጽ አስቀምጦታልና፡፡ ሆኖም እንዲህ ሲል ሰባት የተለያዩ መንፈሶች መኖራቸውን ለማሳየት ሳይሆን አንዱ የእግዚአብሔር መንፈስ በመሲሁ፣ በኋላም በእርሱ በማመን የእግዚአብሔርን መንፈስ በሚቀበሉ ሁሉ (ቤተ-ክርስቲያን) ሕይወትና አገልግሎት ውስጥ በሰባት ወይም በተለያዩ አቅጣጫዎች እንደሚገለጥ ለማሳየት የተጻፈ ይመስላል፡፡ ለዚህም ማስረጃ የሚሆነን ነቢዩ ዘካሪያስ በመቅረዙ ላይ ስለነበሩት ሰባት ቧንቧዎች፣ በእነሱም ላይ ስለሚበሩ በምድር ሁሉ የሚዘዋወሩ የእግዚአብሔር ዓይኖች እያለ ስለሚጠራቸው



For more books www.amharicchristianbooks.com

ሰባት መብራቶች ሲጽፍ ሁሉም ከአንድ የወርቅ መቅረዝ የሚወጡ መሆናቸውን ማሳየቱ፣ በሰባት[78] አቅጣጫ በሙላት የሚገለጠውን የመንፈስ ቅዱስን ባሕሪና ሥራ እንደሚያመለክት መረዳት እንችላለን፡፡[79] በኤፌሶን 1፡18 ላይ የምናየው ይህ የጥበብና የመገለጥ መንፈስ ከመንፈስ ቅዱስ ሥራዎች መካከል አንዱ ሲሆን በአማኞች መንፈስ ውስጥ አድሮ አዕምሮአቸውን በማብራት የክብርን አባት እንዲያውቁና የተጠሩለትን ተስፋ፣ ክብርና ኃይል እንዲገነዘቡ ለማድረግ የሚሰራውን ሥራ ያመለክታል፡፡

የሰማያዊው ምሳሌ በሆነው ፊተኛው የማደሪያ ድንኳን፣ ካህናት ዕለት ተዕለት እየገቡ አገልግሎታቸውን የሚፈጽሙባት ቅድስት የተባለች ክፍል ውስጥ፣ ከጠለለ የወይራ ዘይት ተዘጋጅቶ ያለማቋረጥ የሚበራ ሰባት አንጓ ያለው አንድ መቅረዝ ነበረ፡፡[80] ካህናቱ በድንኳን ውስጥ ያላቸው አገልግሎት የሚሰምረው በብርሃኑ እየታገዙ ስለሚንቀሳቀሱ ነበር፡፡ ልክ እንዲሁ መንፈስ ቅዱስ በአዲስ ኪዳን የእግዚአብሐር ማደሪያ በሆኑት አማኞች መንፈስ ውስጥ የመንፈሱንና የቃሉን ብርሃን በማብራት በተለያዩ ፀጋዎች ይገልጣል፡፡ ታዲያ እያንዳንዱን መገለጥ "መንፈስ" ብለን ብንጠራውም[81] የተለያየ መንፈስ መኖሩን ሳይሆን አንዱ መንፈስ በሰዎች ውስጥ በተለያየ መንገድ መገለጡን እያጎላን ነው፡፡ ጳውሎስም የልባችሁ ዓይኖች "ሲበሩ" ለማለት የተጠቀመበት ቃል በጨለማ ሥፍራ የተለኮሰን መብራት የሚያመለክት መሆኑን የግሪኩ ቃል ይጠቁማል፡፡ በመቅረዙ ሰባት አንጓዎች ላይ የሚበሩትን መብራቶች ነቢዩ ዘካርያስ በራእዩ ላይ "በምድር ሁሉ የሚዘዋወሩ የእግዚአብሔር ዓይኖች"[82] ይላቸዋል፡፡ በእነዚህ በሁለቱ ክፍሎች መካከል ያለውን ግንኙነትና የዘካርያስን ራእይ ትንታኔ በበቂ ሁኔታ በድፍረት መናገር ባይቻልም አንዱ ዘይት በመቅረዝ ውስጥ ገብቶ በሰባት አንጓዎች ላይ ሲበራ እነዚያ እያንዳንዱ ነበልባል የእግዚአብሔር ዓይኖች ተብለው መጠራታቸው የሚፈነጥቀው ብርሃን ያለ ይመስለኛል፡፡ ምክንያቱም ከዘካርያስ ራእይ ጋር ተመሳሳይ የሥነ-ጽሑፍ ዘውግ (Genre) ያለው የዮሐንስ ራእይ የጌታ ዓይኖች የእሳት ነበልባል እንደሆኑና ሰባት አንጓ ያለውም መቅረዝ አብያተክርስቲያናት መሆናቸውን በግልጽ ጽፏል፡፡[83]

ጠቢቡ ሰሎሞንም የሰው መንፈስ የእግዚአብሔር መብራት እንደሆነና መንፈስና

[78] ሰባት ቁጥር በመጽሐርፍ ቅዱስ ውስጥ ፍፁምነትን የሚያመለክት ቁጥር እንደሆነ ይታመናል

[79] ዘካ. 4፡2 እና 10

[80] ዕብ. 9፡2

[81] 1ቆሮ. 12፡4-11

[82] ትን. ዘካ. ምዕራፍ አራትን በሙሉ ያንብቡ

[83] ዮሐ. ራዕይ 1፡ 14 እና 20



For more books www.amharicchristianbooks.com

ሕይወት በሆነው በእግዚአብሔር ቃል ሲለኮስ እንደሚበራና ሰው በተፈጥሮው ሊያየው የማይችለውን ጥልቅ ነገር ውስጣዊ ማንነቱ ድረስ በመዝለቅ እንደሚመረምር ይናገራል፡፡[84] በተጨማሪም ጳውሎስ በ1ቆሮ. 2፡10-12 እግዚአብሔር አስቀድሞ ከዘመናት በፊት ለክብራችን የወሰነውን ተሰውሮም የነበረውን የእግዚአብሔርን ጥበብ በምሥጢር ስለመናገር ሲጽፍ *“መንፈስም የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገር ስንኳ ሳይቀር ሁሉን ይመረምራልና ለእኛ እግዚአብሔር በመንፈሱ በኩል ገለጠው፡፡ በእርሱ ውስጥ ካለው ከሰው መንፈስ በቀር ለሰው ያለውን የሚያውቅ ሰው ማን ነው? እንዲሁም ደግሞ ከእግዚአብሔር መንፈስ በቀር ለእግዚአብሔር ያለውን ማንም አያውቅም፡፡ እኛ ግን ከእግዚአብሔር እንዲያው የተሰጠንን እናውቅ ዘንድ ከእግዚአብሔር የሆነውን መንፈስ እንጂ የአለምን መንፈስ አልተቀበልንም፡፡”* በማለት ግልጽ ያደርገዋል፡፡

በክርስቶስ አምነን በተስፋው መንፈስ በመንፈስ ቅዱስ ከተጠመቅን በኋላ እንደገና የጥበብና የመገለጥ መንፈስ እንዲሰጠን ልመና ለምን አስፈለገ? ወደሚለው ወደ ሁለተኛው ጥያቄ ስንመለስ፣ ስለ መንፈስ ቅዱስ ሙላት ትልቅ ትኩረት ልንሰጠው ከሚገባን ትምህርት ጋር ፊት ለፊት እንፋጠጣለን፡፡ በዚህ መልዕክት ውስጥ በመንፈስ ቅዱስ መሞላት ያለበት መንፈሳችን ብቻ ሳይሆን የማወቂያ ክፍላችን የሆነው አእምሮአችን ጭምር መሆኑን እንመለከታለን፡፡ አማርኛው “የልባችሁ ዓይኖች” የሚለውን የእንግሊዘኛው መጽሐፍ ቅዱስ የማስተዋላችሁ ወይም የመረዳታችሁ ዓይኖች ይለዋል፡፡ ይህም ትርጉም ከአዕምሮ ጋር እጅግ ተዛማጅ ነው፡፡ ይህም ባመንን ጊዜ መንፈሳችን በእግዚአብሔር መንፈስ እንደተሞላ ሁሉ በሂደት የልቦናችን ዓይን የተባለው አእምሮአችን በጥበብና በመገለጥ መንፈስ ሊሞላ እንደሚገባው ያስገነዝበናል፡፡ ጸሐፊው በክርስቶስ በማመን እንደተሞላን ከነገረን በኋላ እንደገና እንድንሞላ የሚያዘን ከሆነ ሙላቱ የተጀመረ እንጂ ያልተፈፀመ መሆኑን፣ አንዱ በማመን በቅፅበት፣ ሌላው በማወቅ በሂደት የሚከናወን መሆኑን መረዳት እንችላለን፡፡[85] ከሙላት ወደ ሙላት ይሏል ይህ ነው፡፡

ሁለት ሰዎች በአንድ ላይ ጌታን ተቀብለው ሳለ ከጥቂት ዓመታት በኋላ አንደኛው በሕይወቱ አድጎ ፍሬ ሲያፈራ ሌላኛው ጠውልጎ ካየን፣ ልዩነቱን ያመጣው አዳዳናቸው ሳይሆን ከዳኑ በኋላ የአዕምሮአቸው መታደስ ጉዳይ ነው፡፡ አዕምሮን የሚያድሰውና በእግዚአብሔር እውቀት የሚሞላው ደግሞ የጥበብና የመገለጥ

---

[84] ምሳ. 20፡27(አ.መ.ት)

[85] ቆላ. 2፡9-10ን ከኤፌ. 3፡19; 4፡12-13; 5፡18 ጋር ያነፃጽሩ



For more books www.amharicchristianbooks.com

መንፈስ በአማኞች ውስጥ ያለመከልከል ሲሰራ ነው፡፡ ያኔ የመረዳትና የማስተዋል ዓይኖቻችን ይበራሉ፣ እኛም እግዚአብሔር እንደሚያይ እናያለን፡፡ ይህም መንፈስ በጸሎትና በልመና ሊገኝ እንደሚችል ከክፍሉ መረዳት እንችላለን፡፡ ሆኖም ኃላፊነቱን በመንፈስ ቅዱስ ላይ ብቻ ጥለን ልንተኛ አይገባንም፤ የልባችንን ዓይኖች ማብራት የርሱ መለኮታዊ ድርሻ ቢሆንም ቃሉን ማንበብ፣ ማጥናት፣ ማሰብና ማሰላሰል እንዲሁም አዕምሮአችንን ማሰራት የእኛ ሰዋዊ ድርሻ መሆኑን ልንዘነጋ አይገባንም፡፡

## ታውቁ ዘንድ

እያየን ያለነው ንዑስ ርዕስ “ርስትን ማወቅ” የሚል ነው፡፡ ቀደም ብለን ማወቅ የመኖር መሠረት ነው ብለናል፡፡ ነገር ግን እውቀትን ሁሉ ማለታችን ሳይሆን ምንጩ እግዚአብሔር የሆነ፣ በዓይናችን ልናየው በጆሮአችን ልንሰማው፣ በልባችንም ልናስበው የማንችለውን እግዚአብሔር ያዘጋጀልንን መንፈሳዊ በረከት የሚገልጥልን ዕውቀት ማለት እንደሆነ ግለጽ ነው፡፡ በዚህ ስፍራ ጳውሎስ የጥበብንና የመገለጥን መንፈስ እንዲሰጣቸው እግዚአብሔርን የሚለምንበት ምክንያት የመንፈስ ፍሬ እርሱም “እምነት” እና “ፍቅር” የታየባቸው አማኞች ከዚህም የበለጠ ያፈሩ ዘንድ ክርስቶስን እንዲያውቁና እንዲያሳውቁ በማሰብ ነው፡፡ ሊታወቁ የሚገባቸውን ነገሮች ሲዘረዝር በሦስት ከፍሎ ያስቀምጣቸዋል፡፡ እነርሱም "የመጥራቱ ተስፋ" "በቅዱሳኑ ዘንድ ያለው የርስቱ ክብር ባለጠግነት" እና "ለምናምን ከሁሉ የሚበልጥ የኃይሉ ታላቅነት ናቸው፡፡

የመጥራቱን ተስፋ አለማወቅ ምን እንደሚያስከትል ምሳሌዎቻችን ከሆኑት ከእሥራኤል ልጆች የምድረ በዳ ጉዞ መማር እንችላለን፡፡[86] እግዚአብሔር ለአባቶቻቸው በሰጠው ተስፋ መሠረት መልካም ርስት አዘጋጅቶ፣ ከባርነት ቤት በማውጣት በድንቅና በተዓምራት ቢመራቸውም አብዛኞቹ ከግብጽ ምድር የወጡለትን የርስት ተስፋ አላስተዋሉም ነበር፡፡ ምንም እንኳ የምሥራቹ ቃል ቢሰበክላቸው የሰሙት ቃል ከሰሚዎቹ ጋር በእምነት ስላልተዋሃደ ሊጠቅማቸው አልቻለም፡፡ ይህንንም በየመንገዱ ከሚያነሱት ጥያቄና፣ ተግዳሮት በገጠማቸው ቁጥር ከሚናገሩት መራር ቃል መረዳት አያዳግትም፡፡

> *“ሕዝቡም በእግዚአብሔርና በሙሴ ላይ፡- በምድረ በዳ እንሞት ዘንድ ከግብጽ ለምን አወጣችሁን? እንጀራ የለም፣ ውሃ የለም*

[86] 1ቆሮ. 10፡6፣11



For more books www.amharicchristianbooks.com

*ሰውነታችንም ይህንን ቀላል እንጀራ ተፀየፈ ብለው ተናገሩ።" ዘኁ. 21፡5*

ከግብጽ የወጣው ትውልድ በእግዚአብሔር ላይ ሲያጉረመርምና ሲያጉተመትም የኖረው፣ በራሱ ላይ እንደተናገረውም ሬሳው በምድረ በዳ ወድቆ የቀረው፣ ሌላ ከምንም ምክንያት ሳይሆን የመጥራቱን ተስፋ ካለማወቅ የተነሳ ነው፡፡ የመጥራቱን ተስፋ ምን እንዲሆን የሚያውቁበት ልዩ መንፈስ [87] የነበራቸው ካሌብና ኢያሱ ግን አዲሱን ትውልድ እየመሩ የተስፋውን ምድር ወረሱ፡፡ ዛሬም የመጥራቱን ተስፋ ያላወቁ አማኞች በዙሪያቸው ካለው ችግርና ፈተና ባሻገር የሚጠብቃቸውን ክብር ማየት ስለሚሳናቸው ከማጉረምረምና ግራ ከመጋባት ውጭ የድል ኑሮ ሊመሩ አይችሉም፡፡

በጳውሎስ ስነ-መለኮት ውስጥ "ተስፋ" እንደ ዛሬው የምድራዊ ቁሳቁስ ጉዳይ አይደለም፡፡ እንበልና ዛሬ ጳውሎስ በሥጋ መጥቶ በ "ይሆንልሃል" በ "ይሳካልሃል" በ "ትወጣለህ" "ትጥሳለህ" "ትወርሳለህ" የተሞላውን የ "ክርስትና እምነታችንን" ቢያይ "ከእነዚህ ሰዎች ጋር በኃይማኖት አንድ ነን! ብሎ የሚያስብ ይመስሎታል? እንኳን ለጳውሎስ፣ የእርሱን መልዕክቶች በሚገባ ላነበቡና ለተረዱ ሰዎች እንኳ፣ በዘመናችን ስለ ተስፋ ያለው አመለካከትና ልምምድ ፈጽሞ ባዕድ ነው፡፡

ተስፋ የሚለው ቃል በኤፌሶን መልዕክት ውስጥ 7 ጊዜ፣ ባጠቃላይ በጳውሎስ መልእክቶች ውስጥ ደግሞ ከ65 ጊዜያት ተጠቅሷል፡፡ ከእነዚህ ሁሉ ውስጥ አንድም እንኳን የ "ይሆንልሃል" "ይሳካልሃል" ምድራዊ ተስፋ አናገኝም፡፡ ይልቅ ተስፋው፡- የመንፈስ ቅዱስ ተካፋይ የመሆን፣ የእግዚአብሔር ልጅነት፣ የጽድቅ፣ በክርስቶስ ኢየሱስ እግዚአብሔርን የመምሰል፣ የኢየሱስ ክርስቶስ ክብር መገለጥ፣ የአካል ትንሳኤ፣ የሚመጣውን ዓለም መግዛትና ባጠቃላይ እግዚአብሔርን በሙላት የመውረስና በእግዚአብሔር ሙሉ ለሙሉ የመወረስ ተስፋ መሆኑን ከቅዱስ ቃሉ እናነብባለን፡፡ ይህም ተስፋ አንድም ነው፣ ብዙም ነው፡፡ ብዙ ያደረገው በአንዱ ተስፋ ውስጥ እጅግ ብዙ በረከቶች በመኖራቸው ነው፡፡ [88]

ይህንን የክብር ተስፋ በእምነት ተቀብለነዋል፣ በእምነትም እንጠብቀዋለን እንጂ አሁን በዓይናችን ልናየው አንችልም፡፡ ቃሉም እንደሚል ማንም የሚያየውን ተስፋ አያደርግም፡፡[89] ነገር ግን በቃሉ ብርሃን፣ በእምነት አስረጅነት ከሩቅ እያየን በትዕግስት እንጠብቀዋለን፡፡ ይህም ተስፋ "ላም አለኝ በሰማይ . . . " ዓይነት ቀቢፀ

---

[87] ዘኁ. 14፡24፤ዘዳ. 34፡9

[88] ኤፌ. 4፡4

[89] ሮሜ 8፡24፤25



For more books www.amharicchristianbooks.com

ተስፋ ሳይሆን በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት በልባችን ከፈሰሰው የእግዚአብሔር ፍቅር የተነሳ የማያሳፍር ይልቁንም በመከራ ውስጥ እንኳ የሚያስመካ የክብር ተስፋ ነው፡፡[90]

ደግሞም ይህን ሰማያዊ ተስፋ እያሰብን የምድሩን ኑሯችንን እንረሳለን ማለት አይደለም፡፡ ተስፋው ወደላይ አንጋጦ የሚያሳይ፣ በር አስዘግቶ የሚያስቆዝም ወይም ከተማን አስጥሎ የሚያስመንን ሳይሆን ትምህርታችንን በትጋት እየተማርን፣ የተሰማራንበት የሥራ መስክ የቱም ይሁን በንጽሕና እየሰራን፣ ቤተሰባችንን በአግባቡ እየመራን የምንጠብቀው ተስፋ ነው፡፡ ለዚህም የጠራን እግዚአብሔር የታመነ ነው፡፡ እርሱም ያደርገዋል፡፡

"ምስጋና" በሚል ርዕስ የቀደመውን ምዕራፍ ስናይ ርስት በሆነው በተስፋው መንፈስ፣ በመንፈስ ቅዱስ እንደታተምን ተመልክተናል፡፡ አሁን ደግሞ "ልመና" በሚል ርዕስ ርስቱን ለማወቅ የጥበብና የመገለጥ መንፈስ እንዲሰጠን በምንማፀንበት ክፍል የርስቱ አሳብ ዳግመኛ ሲነሳ እናያለን፡፡ ሆኖም አሁን የተነሳበት አነሳስ ከቀደመው ጋር አንድም የሚመሳሰልበት አንድም የሚለያይበት ሁኔታ አለ፡፡

የቀደመው (ኤፌሶን 1፡14) "ርስታችን" በማለት ርስቱ የእኛ እንደሆነ ሲገልጽ፣ ይህኛው ግን (ኤፌሶን 1፡18) የ "ርስቱ" [91] በማለት ርስቱ የእግዚአብሔር እንደሆነ ያሳያል፡፡ እነዚህ ሁለት ተቃራኒ የሚመስሉ ቃሎች አንድ ድንቅ ፍቺ አላቸው፡፡ በዚህ መልዕክትም ሆነ በሌሎች የአዲስ ኪዳን ክፍሎች ምስጢር የተባለው ሁሉ በዚህ ይጠቀለላል፡፡ የዚህን ምስጢር ፍቺ ያገኘ ሰው ሌሎቹን ሁሉ የሚከፍትበት ዋና ቁልፍ አለው ቢባል ማጋነን አይሆንም፡፡ ነገሩ እንዲህ ነው፡- ርስቱ በዋነኝነት የእግዚአብሔር እንጂ የእኛ አይደለም፡፡ የዕብራውያን መልዕክት ፀሐፊ እንደሚለው ርስቱ "የዘላለም ርስት"[92] ነው፡፡ ዘላለም ደግሞ ወደፊት መጨረሻ የሌለው ብቻ ሳይሆን ወደኋላም መጀመሪያ የሌለው እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡

ስለዚህ ይህ የዘላለም ርስት ከዘላለም አምላክ ውጭ የማንም ሊሆን አይችልም፡፡ ቀደም ብለንም ርስቱ "ሕይወት" እንጂ ቦታ አይደለም ብለናል፡፡ ይህም ሕይወት የስላሴ አንዱ አካል የሆነው መንፈስ ቅዱስ ነው፡፡ አብም ወልድም ለማይቆጠሩ የዘላለም ዘመናት ሲካፈሉ የኖሩበት ሕይወት እሱ ነው፡፡ ጌታ ኢየሱስ በዮሐንስ

[90] ሮሜ 5፡5

[91] ከ1962 ኢ.ኤ.አ የአማርኛ ትርጉም በስተቀር ሌሎች ትርጉሞች በግልጽ "ርስቱን" ይላሉ፡፡

[92] ዕብ. 9፡15



For more books www.amharicchristianbooks.com

ወንጌል *"አብ በራሱ ሕይወት እንዳለው እንዲሁ ደግሞ ለወልድ በራሱ ሕይወት እንዲኖረው ሰጥቶታል" (ዮሐ. 5፡26)* ብሎአል፡፡ ይህንንም ዮሐንስ በራእይ መጽሐፉ መጨረሻ ላይ "በአደባባይዋም መካከል ከእግዚአብሔርና ከበጉ ዙፋን የሚወጣውን እንደ ብርሌ የሚያንፀባርቀውን የሕይወትን ውሃ ወንዝ አሳየኝ፡፡" (ራእይ 22፡1) ይላል፡፡ ይህም የሕይወት ውሃ ወንዝ ኢየሱስ በዳስ በዓል በመጨረሻው ቀን "በእኔ የሚያምን መጽሐፍ እንዳለ የሕይወት ውሃ ወንዝ ከሆዱ ይፈልቃል፡፡"[93] ብሎ የጮኸለት በእርሱ የሚያምኑ የተቀበሉት መንፈስ ቅዱስ ነው፡፡

ይህን አብና ወልድ ለማይቆጠር የዘላለም ዘመናት የኖሩበትን የዘላለም መኖሪያ የሆነ የሕይወት ርስት፣ እኛም እንኖርበት ዘንድ ስፍራ አገኘን፡፡ ይህም በአብ የዘላለም ውሳኔና በክርስቶስ *ሥራ* የሆነ የጸጋ *ሥጦታ* ነው፡፡ *ታዲያ* እኛ በዚህ ሕይወት ስንጠቀለል ወራሽ ብቻ አንሆንም፡፡ በአብና በወልድ ውስጥ ያለው አንድ መንፈስ በእኛ ውስጥ ሲሆን፣ እግዚአብሔር የእኛ ርስት እንደሆነ ሁሉ እኛም የርሱ ርስት እንሆናለን ማለት ነው፡፡ እነዚህ ሁለቱ በተናጠል ሳይሆን በአንድነት የሚፈፀሙ ተወራራሽ እውነታዎች ናቸው፡፡ ይወርሰናል፣ እንወርሰዋለን፡፡ በወረሰን መጠን እንወርሰዋለን፣ በወረስነው መጠን ይወርሰናል፡፡

ይህን ካነሳን ዘንድ በዚህ ብርሃን እንድንፈትሸው የሚገባን የተለመደ አስተሳሰብ አለ፡፡ ጳውሎስ በሮሜ 8፡17 ላይ

> *"ልጆች ከሆንን ወራሾች ደግሞ ነን፣ ማለት <u>የእግዚአብሔር ወራሾች ነን</u>፡፡ አብረንም ደግሞ እንድንከብር አብረን መከራ ብንቀበል ከክርስቶስ ጋር አብረን ወራሾች ነን፡፡"*

ይላል፡፡ ቁጥራቸው ቀላል የማይባል አማኞች በሚመጣው ዓለም እግዚአብሔርን ስለ መውረስ ሲያስቡ የምድሩ አልበቃ ብሎአቸው ከወርቅ በተሰራ መንገድ ላይ እንደሚሄዱ፣ በአልማዝ በተሽቆጠቆጠ ቤት እንደሚኖሩ ያስባሉ፡፡ ይህም ሊወርሱ የሚያስቡት የእግዚአብሔርን ንብረት እንጂ ራሱን እግዚአብሔርን እንዳልሆነ ያሳብቃል፡፡ እነዚህ የዘረዘርናቸው ነገሮች የእግዚአብሔር ሃብት እንጂ ራሳቸው እግዚአብሔር አይደሉም፡፡ ከፍ ብለን ያየነው ክፍል የሚነግረን ግን እግዚአብሔርን ራሱን እንደምንወርስ ነው፡፡ ሐዋርያው "ወራሾች ነን" ካለ በኋላ "ማለትም" ብሎ "የእግዚአብሔር ወራሾች ነን" ያለው የአንባቢዎቹን አስተሳሰብና አተረጓጎም

[93] ዮሐ. 7፡37-39



For more books www.amharicchristianbooks.com

ለመቃኘት ይመስለኛል፡፡

ታዲያ እግዚአብሔርን የምንወርስ ከሆነና “ነገሮችን” የምንወርሰው እግዚአብሔርን በመውረሳችን ምክንያት ከሆነ ይህን “የነገሮችን” ወራሽነት አጉልቶ ማየት ከየት አመጣነው? በአንድ በኩል እንዲህ የሚያስቡትን ሰዎች ልንፈርድባቸው አንችልም፡፡ ምክንያቱም በዕለት ተለት ሰዋዊ ሥርዓት ልጆች አባቶቻቸውን ሲወርሱ ያያሉ፡፡ ሆኖም የሚያዩት ልጆች ወላጆቻቸውን ራሳቸውን ሲወርሱ ሳይሆን ከሞቱ በኋላ ያከማቹትን ጥሪት ሲወርሱ ነው፡፡ ሰዎቹ ሟች ስለሆኑ ሊወረሱ አይችሉም፣ ንብረታቸው ግን ቋሚ ስለሆነ ከቀብር መልስ ይወረሳል፡፡ ታዲያ ንብረታቸውንም ለመውረስ ሰዎቹ እስኪሞቱ መጠበቅ ግድ ይላል፡፡ አለዚያ ተወራሾቹ ወላጆች ራሳቸው “በቁሜ ልትወርሱኝ ነው እንዴ?” ይላሉ፡፡ ይህ የሰው ሥርዓት ነው፡፡ ሰማያዊው አባታችን ግን አይሞትም፡፡ ስለዚህ እንደ ለመድነው ቀብረን ንብረት ልንወርስ አንችልም፡፡ ይልቅ እርሱ ራሱ ርስት ነው! እርሱ ለሙታን ሕይወትን የሚሰጥ መንፈስ፣ የሚወረስ ሕይወት ነው! እርሱ ወራሽም፣ አውራሽም ተወራሽም ነው! እርሱን ከወረስን ሁሉን ወረስን ማለት ነው፡፡[94]

ስለዚህ የሕይወት ርስት በሆነው መንፈስ ቅዱስ አማካይነት እግዚአብሔር ርስታችን፣ እኛም ርስቱ ነን፡፡ እግዚአብሔር መኖሪያችን እኛም መኖሪያው ነን፡፡ ይህም ርስት አሁን በቅዱሳኑ ዘንድ ያለ[95] ቀና ብለን በሰማይ የምናየው ብቻ ሳይሆን ዞር ብለን ባጠገባችን ባሉ ቅዱሳን ውስጥ በእምነት የምናየው፣ በፍቅር የምንከባከበው፣ በደስታ የምንካፈለው ርስት ነው፡፡ ሆኖም ይህን እናደርግ ዘንድ የልብ ዓይኖቻችን ሊበሩ ያስፈልጋል፡፡ ያ የጥንቱ የከነዓን ነብይ፡-

> *“… ዓይኖቹ የተከፈቱለት ሰው እንዲህ ይላል፡- የእግዚአብሔርን ቃል የሚሰማ፣ የልዑልንም እውቀት የሚያውቅ፣ ሁሉን የሚችል የአምላክን ራእይ የሚያይ፣ የወደቀው ዓይኖቹም የተከፈቱለት እንዲህ ይላል፡- …፡፡” ዘኍ. 24፡15፣16*

እንዳለ፣ ዓይኖቹ የበሩለት ሰው በክርስቶስ አካል በቤተክርስቲያን ውስጥ ሕይወትን ያያል፡፡ በዙሪያው ያሉትን አማኞች በሥጋ ማንነታቸው ሳይሆን እግዚአብሔር እንደሚያውቃቸው በክርስቶስ ለማወቅ ይተጋል፡፡

94 1ቆሮ. 3፡ 21

95 ኤፌ. 1፡ 18; ቆላ. 1፡27



For more books www.amharicchristianbooks.com

ይህ በቅዱሳኑ ዘንድ ያለው የእግዚአብሔር ርስት በመጨረሻው ቀን በሙላት ሊገለጥ የተዘጋጀ የክብር ባለጠግነት የሞላበት ነው፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ በዚህ መልዕክቱ ከሌሎች ስፍራዎች በበለጠ "ባለጠግነት" የሚለውን ቃል ተጠቅሟል፡፡ ይህም ባለጠግነት የሚያልፍ ባለጠግነት ሳይሆን የጸጋ ባለጠግነት (1፡7፣ 2፡7) የክብር ባለጠግነት (1፡18፣ 3፡16) ፍለጋ የሌለው የክርስቶስ ባለጠግነት (3፡8) ነው፡፡

ይህ ዛሬ በዓይናችን የማናየው፣ ነገር ግን በዚያን ቀን በመንፈሳችን ብቻ ሳይሆን በስጋችን ላይ የሚገለጠው፣ ፍጥረት ሁሉ በመካፈል ነፃ ሊወጣበት በመቃተት የሚጠብቀው ክብር ፣ከክብር አባት ብቻ የሚገኝ፣ በምላሹም ለክብር አባት ብዙ ምስጋናን የሚያመጣ ዘላለማዊ ክብር ነው፡፡ እኛም በፀጋ ስለ ተሰጠን ስለዚህ ክብር ምስጋናን እንሰጣለን፡፡ በዚህ ክብር ነፃ የሚወጣውም ፍጥረት አብሮን ያመሰግናል፡፡

## <u>የኃይል ታላቅነት</u>

ኃይል በሥራ የሚገለጥ ጉልበት ነው፡፡ ይነስም ይብዛም ኃይል የማያስፈልገው ሥራ የለም፡፡ የእኛን የዕለት ተለት ኑሮ፣ የምንኖርባትን የምድር እንቅስቃሴ፣ ከአዕምሮአችን በላይ የሆነውን የሕዋ ሥርዓት ስናስብ በአንድ ሰከንድ ውስጥ የሚወጣው ኃይል ምን ያህል እንደሆነ መለካትም ሆነ መገመት አይቻልም፡፡ ታዲያ እነዚህን ሁሉ ካለመኖር ወደ መኖር ያመጣው እግዚአብሔር ምንኛ ኃይል ይኖረው ይሆን? አንድ የእግዚአብሔር ሰው "እግዚአብሔር ፍቅሩን ሰዎችን ሊምርበት፣ ኃይሉን ግን ለማዳኛ ተጠቅሞበታል" እንዳለ ፍቅሩ ባይምረን፣ ኃይሉ ባያድነን ይልቅ ጽድቁ ቢፈርድብን፣ ኃይሉ ቢወድቅብን ኖሮ ወዴት እንታይ ነበር? የእግዚአብሔር ኃይል እጅግ ታላቅ ነው፡፡

ሐዋርያው የርስቱን የክብር ባለጠግነት ከፃፈ በኋላ "ታውቁ ዘንድ" በሚለው ማዕቀፍ ውስጥ የሚዘልቀው የርስቱን የኃይል ታላቅነት ወደ መተረክ ነው፡፡ ይህ የኃይል ታላቅነት ወደፊት የሚታይ ብቻ ሳይሆን በሥራ ላይ ውሎ የታየ፣ አሁንም ለእኛ ለምናምን የሚሠራ ኃይል ነው፡፡ ጳውሎስ የዚህን ኃይል ታላቅነት ለመግለጽ የግሪክ ቋንቋ የሚያበረክታቸውን አሉ የተባሉ ኃይልን በተለያየ መልክ የሚገልፁ ዱናሚስ፣ ኢስቹስ፣ ክራቶስ፣ ኤክሶዚያ የተሰኙትን ቃላት በዚህ ሥፍራ



For more books www.amharicchristianbooks.com

ተጠቅሟል፡፡[96]

ከዚህ ክፍል አገላለጽ አኳያ እግዚአብሔር ሰማይን ለመዘርጋትና ምድርን ለመመስረት ከተጠቀመበት ኃይል ይልቅ፣ ክርስቶስን ከሙታን በማስነሳት የገለጠው ኃይል እንደሚበልጥ ማየት ይቻላል፡፡ የክርስቶስ ትንሳኤ የአንድ ሰው ትንሳኤ ሳይሆን የአዲስ ፍጥረት መጀመሪያ ነውና፡፡ በመጨረሻም በክርስቶስ ያንቀላፉትን ሁሉ በሚያስነሳበት ጊዜ የኃይሉ ታላቅነት ለፍጥረት ሁሉ ይገለጣል፡፡ ሐዋርያው በዚህ ክፍል የእግዚአብሔር ኃይል በአንድ ወቅት በተያያዥነት በተፈፀሙ ድርጊቶች እንደ ተገለጠ ድርጊቶቹን በአራት በመከፈል ያሳየናል፡፡

### *1. "ክርስቶስንም ከሙታን ሲያስነሳው . . . "*

የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሳኤ በዘመን ፍፃሜ የሚጠናቀቀው የአዲስ ፍጥረት ጅማሬ ነው፡፡ ይህም ኃይል አንድ ጊዜ ሥራ ላይ ውሎ የሚጠፋ ተፈጥሮአዊ ኃይል ሳይሆን ለዘላለም የሚኖርና የሚያኖር መለኮታዊ ኃይል ነው፡፡ ላለፉት ሁለት ሺህ ዓመታት ወደፊትም ጌታ እስኪመጣ ድረስ የሚድኑ ሰዎች ዳግም የሚወለዱበትና አዲስ ፍጥረት የሚሆኑበት ኃይል ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን በተነሳ ጊዜ አንዴ፣ ለሁሉም ሰው፣ ለሁሉም ዘመን፣ እንዲሠራ ሆኖ የተገለጠ የትንሳኤ ኃይል ነው፡፡ ለዚህ ነው ጥቂት ዝቅ ብሎ "ከርሱ ጋር አስነሳን" የሚለው፡፡ ሞቶ የነበረውን የኢየሱስን አካል ያስነሳው ይኸው ኃይል አንድ ቀን በአፈር ውስጥ ያሉትን ስጋዎች ሁሉ የማስነሳት ብቃት አለው፡፡ ይህም እግዚአብሔር ለዘላለም ሲወደስበት የሚኖር በእርሱ ዘንድ ብቻ የሚገኝ ታላቅ ኃይል ነው፡፡ ይህም ኃይል ለእኛ ርስታችን ነው፡፡ በትንሳኤም ቀን እንለብሰዋለን፡፡

ይህ ኃይል ርስታችን ብቻ ሳይሆን ለርስታችን የሚጠብቀን ኃይል መሆኑን ጴጥሮስ "ይህም ርስት በመጨረሻ ዘመን ይገለጥ ዘንድ ለተዘጋጀ መዳን በእምነት በእግዚአብሔር ኃይል ለተጠበቃችሁ ለእናንተ በሰማይ ቀርቶላችኋል፡፡" (1ጴጥ. 1፡5) በማለት ይመሰክርልናል፡፡ ጳውሎስም በዚህ መልእክቱ ተከታይ ክፍሎች ይህ ኃይል ወንጌልን በመስበክ ሥራው እንደሚገለጥ (3፡7፣20) አማኞችን በውስጥ ሰውነታቸው እንደሚያጠነክር (3፡16) እንዲሁም ከመንፈሳዊ ኃይላትና ሥልጣናት ጋር ለሚኖራቸው ፍልሚያ ብቸኛ የብርታት ምክንያት እንደሆነ (6፡10) በጥልቀት ጽፏል፡፡

[96] greattreasure.org/gnt/main.do August, 2011



For more books www.amharicchristianbooks.com

2. *"ከአለቅነትና ከሰልጣንም ከኃይልም ከጌትነትም ሁሉ በላይና በዚህ ዓለም ብቻ ሳይሆን ነገር ግን ሊመጣ ባለው ዓለም ደግም ከሚጠራው ስም ሁሉ በላይ በሰማያዊ ሰፍራ በቀኙ ሊያስቀምጠው . . . "*

ይህ ለእኛ ላመንን የዘላለም ርስታችን የሆነ ከሁሉ የሚበልጥ ታላቅ ኃይል፣ ብርታትና ጉልበቱ የተገለጠው፣ ኢየሱስ ክርስቶስን በአካል ከሙታን በማስነሳት ብቻ ሳይሆን የአዲሱ ፍጥረትና የአዲሱ የሰው ዘር ራስ ሆኖ የተነሳውን ኢየሱስ ክርስቶስን ከሁሉ በላይ ያለ ልክ ከፍ በማድረግ ነው፡፡

የኤፌሶን መልዕክት ጳውሎስ እንደጻፋቸው ከሚታመኑ ከሌሎች መልዕክቶች የሚለይበት አንዱ ባህሪ የመንፈሳዊውን ዓለም የአለቅነት፣ የስልጣን፣ የኃይልና የጌትነት ተዋረድና አሰላለፍ ደጋግሞ ማንሳቱ ነው፡፡ በሰማይና በምድር ወይም በሌላ አጠራር በሚታዩትና በማይታዩት ዓለማት ያሉት ዙፋናት፣ ጌትነት፣ አለቅነት፣ ሥልጣናት በክርስቶስ፣ ለክርስቶስ እንደተፈጠሩ ከዚህ መልዕክት ጎን ለጎን በጻፈው በቆላስያስ መልዕክት ላይ ጠቅሷል፡፡[97] ከዚህ በመነሳት እነዚህ የአገዛዝ ተዋረዶች በግዑዙ ብቻ ሳይሆን በመንፈሳዊውም ዓለም እንደሚገኙ መረዳት እንችላለን፡፡ በዓለም ላይ ሰዎች በጋራ በሚኖሩበት ሥፍራ ሁሉ ሰዎች ሰዎችን ይገዛሉ፣ ያስተዳድራሉ፡፡ እነዚህም ሰዎች የራሳቸው አለቅነት፣ ሥልጣን፣ ኃይል ያላቸው ሲሆን እንደ አስፈላጊነቱ በስራቸው የተለያዩ ሹመቶችን ይሰጣሉ፡፡ ሆኖም እነዚህ ሰዋዊ ሥልጣናት ከመንፈሳዊ ተፅዕኖ የፀዱ አለመሆናቸውን መጽሐፍ ቅዱስ ይልቁንም የብሉይ ኪዳን የትንቢት መጻሕፍት ግልጽ ያደርጉልናል፡፡ በመንፈሳዊው ዓለም ያሉት አለቆችና ስልጣናት ፈቃዳቸውን በምድር ላይ የሚፈጽሙት በሚታዩትና ስጋ ባለበሱት አለቆችና ስልጣናት ውስጥ እንደሆነ ከእነዚህ ክፍሎች መረዳት እንችላለን፡፡[98] ነገር ግን ከዚህ በመነሳት በኤፌሶን 1፡19-21 ሆነ በ 3፡10 ላይ የተጠቀሱትን አለቆችና ስልጣናት ሁሉ የክፋት ኃይላት ናቸው ብለን መደምደም አንችልም፡፡ ምክንያቱም የወደቁ መላዕክት እንዳሉ ሁሉ የአግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያደርጉ ቅዱሳን መላዕክት እንዳሉ፣ በእነርሱም ዘንድ የአለቅነትና የስልጣን ተዋረድ መኖሩን መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናልና፡፡[99]

ዋናው ነገር ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን ተነስቶ ሥልጣን ከተባለ፣ አለቅነት ከተባለ፣

---

[97] ቆላ. 1፡15
[98] ኢሳ. 14፡4 እና 12፣ ሕዝ. 28፡1 እና 11
[99] ዳን. 9፡21



For more books www.amharicchristianbooks.com

ኃይል ከተባለ፣ ጌትነት ከተባለ ሁሉ በላይ ከፍ ብሎአል፡፡ ፀሐፊው "በዚህ ዓለም ብቻ ሳይሆን ነገር ግን ሊመጣ ባለው ዓለም ደግሞ ከሚጠራው ስም ሁሉ በላይ" ሲል "ዓለም" የሚለው ይህን ግዑዝ ፍጥረት የሚገልፀውን በግሪኩ "ኮስሞስ" የሚለውን ቃል ሳይሆን፣ የአሁንና እና የሚመጣውን የዓለም "ዘመን" የሚገልፀውን "ኤዮን" የሚለውን ቃል ነው፡፡ ይህም በአሁኑና በሚመጣው ዓለም መካከል ያለው ዋነኛ ልዩነት አካላዊ ሳይሆን ሥርዓትና አገዛዝን የሚያሳይ ሕይወታዊ ለውጥ መሆኑን በጥቂቱ ይፈነጥቅልናል፡፡ ዓላማውም ከአዳም ጀምሮ ባለው በአሁኑ አለም የተጠሩ ብዙ ስሞች እንደነበሩ፣ ይህ ዘመን እስከሚፈፀም ድረስ ወደፊትም እንደሚኖሩ ሁሉ፣ በሚመጣውም ዓለም የሚጠሩ ስሞች መኖራቸውን፣ ነገር ግን እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስን ከሙታን አስነስቶ ከእነዚህ ስሞች ሁሉ በላይ በሰማያዊ ስፍራ በቀኙ ማስቀመጡን ማሳየት ነው፡፡ ይህ "ቀኝ" ምንድነው? ስለዚህ ስፍራ ምንነት ብዙ ደፍረን መናገር ባንችልም፣ ከክፍሉ እንደምንረዳው በዚህ የክብር ባለጠግነትና፣ የኃይል ታላቅነት ማዕከል ላይ በመቀመጥ ሁሉን ለመግዛትና ለማስገዛት የሚቻልበትን ስልጣን መረከብን የሚያመለክት ይመስላል፡፡ በዚህ ክፍል ውስጥ የምናየው ትልቁ የምሥራች ፍፁም ሰው የሆነው የእግዚአብሔር ልጅ ከሁሉ በላይ በመከበሩ፣ በእርሱ የሆነው አዲሱ የሰው ዘር ይህን ዓለም ሲገዙ ከኖሩት መላዕክት በላይ ሆኖ፣ ሊመጣ ያለውን ዓለም ለመግዛት በዝግጅት ላይ መሆኑ ነው፡፡[100]

### 3. "ሁሉን ከእግሩ በታች አስገዛለት"

ይህ ቋንቋ በዘመኑ የግሪክ አለም ወታደራዊ ቋንቋ ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስም ሆነ የታሪክ መጽሐፍት እንደሚተርኩልን ያ የጥንቱ ዓለም በጦርነት የታመሰ ነበር፡፡ በየጊዜው የሚነሱትም ኃያላን መንግስታት ምኞታቸው ድንበራቸውን አስከብረው መኖር ብቻ ሳይሆን በዙሪያቸው ያለውን ሕዝብና መንግሥት በማስገበር ዓለምን ጠቅልሎ መግዛት ነበር፡፡ ለዚህም የባቢሎንን፣ የሜዶንና ፋርስን፣ የግሪክን እና የሮምን መንግሥታት ዋቢ አድርገን መጥቀስ እንችላለን፡፡ እነዚህ መንግስታት በለስ ቀንቷቸው በያኔው ዓለም የሚታወቁትን አገሮች፣ ወገኖች፣ ቋንቋዎች፣ ሕዝቦችና ነገዶች ከእግራቸው በታች አስገዝተው ነበር፡፡ እግዚአብሔርም ለክርስቶስ፣ ከእርሱም ጋር የእርሱ ለሆኑት ሁሉ ያደረገው ይህንን ነው፡፡[101]

[100] ዕብ. 2፡ 5-9

[101] መዝ. 2፡ 7-9; 8፡ 6; 109፡1



For more books www.amharicchristianbooks.com

ጥንት በታሪክም ሆነ ዛሬ በዘመናችን የምናየው የሰው መንግሥት በሙታን እጅ ያለ በመሆኑ በየጊዜው የሚነሳና የሚወድቅ፣ በክፉው ተጽእኖ የሚሠራ፣ ጽድቅና ፍትህ የጎደሉበት፣ ሙስናና የግብረገብ ዝቅጠት የሰፈነበት ስለ መሆኑ ብዙ ምርምር አያሻውም፡፡ ይህ በክርስቶስ በኩል የተገለጠው የአዲሱ ሰው መንግሥት ግን ጽድቅ የሰፈነበት፤ የማይናወጥና የማይለወጥ፤ ዘላለማዊ የእግዚአብሔር መንግሥት ነው፡፡ ስለዚህ በዚህ ታላቅ ኃይል እግዚአብሔር ክርስቶስን ከሙታን በማስነሳት፣ ከአለቅነትና ከስልጣን፣ ከኃይልና ከጌትነት ሁሉ በላይ በዚህ ዓለም ብቻ ሳይሆን ሊመጣ ባለው ዓለም ከሚጠሩ ስሞች ሁሉ በላይ በቀኙ በማስቀመጥና ሁሉን ከእግሩ በታች በማስገዛት ታላቁን ሥራ ጀምሯል፡፡ ሆኖም ይህ ሥራ ተጀመረ እንጂ ገና አልተፈፀመም፡፡ በመዝሙር 8፡6 እና 110፡1 በዳዊት አፍ በተነገረውና በአዲስ ኪዳን መጻሕፍት በብዙ ስፍራ በተጠቀሰው የትንቢት ቃል መሠረት እግዚአብሔር ጌታ ኢየሱስን በቀኙ ያስቀመጠው ጠላቶቹን ሁሉ የእግሩ መረገጫ ሊያደርግለት እንደ ሆኑ እሙን ነው፡፡ ይህም ተስፋ የመጨረሻው ጠላት የሆነው ሞት በሚሻርበት በቅዱሳን ትንሳኤ ወቅት ሙሉ በሙሉ ይፈፀማል፡፡ ይህም ሥራ በኢየሱስ ክርስቶስ ሞትና ትንሳኤ ይጀመር እንጂ ፍፃሜው ገና ወደፊት መሆኑን የዕብራውያን መልዕክት ፀሐፊ ፡- *"ሁሉን ከእርሱ በታች ባስገዛለት ጊዜ ያልተገዛለት ምንም አልተወምና፡፡ አሁን ግን ሁሉ እንደተገዛለት ገና አናይም ..."* (ዕብ. 2፣8) በማለት ይነግረናል፡፡

ይህም ሁሉን ከእግሩ በታች የማስገዛት ሂደት ከአንድ ዋና ነገር ጋር በጽኑ የተቆራኘ ነው፡፡ ይህንንም ሐዋርያው በመቀጠል የሚያነሳው ሲሆን ጉዳዩም የኤፌሶን መልዕክት ዐቢይ ርዕስ ነው፡፡

### *4. ". . . ከሁሉ በላይም ራስ እንዲሆን ለቤተክርስቲያን ሰጠው፡፡ እርስዋም አካሉና ሁሉን በሁሉ የሚሞላ የእርሱ ሙላቱ ናት፡፡"*

ሐዋርያው እግዚአብሔር የኃይሉን ታላቅነትና የብርታቱን ጉልበት ለመግለጥ በክርስቶስ የሠራውን ሥራ ሲዘረዝር የመላዕክትን ዓለም፣ የግዑዙን ፍጥረት ዓለምና የሰውን ልጆች በተለያየ ጎራ ጠቅሷል፡፡ ስለ መላዕክቱ ዓለም ሲጽፍ ሰው የሆነው የእግዚአብሔር ልጅ ከአለቅነት፣ ከሥልጣንም፣ ከኃይልም፣ ከጌትነትም ሁሉ በላይ እጅግ ከፍ ማለቱን አሳየን፣ ስለ ሌላውም ፍጥረት ሲጽፍ ሁሉን ከእግሩ በታች አስገዛለት አለን፣ አሁን ደግሞ በክርስቶስ ስለ ሆነው አዲስ ማኅበረሰብ ይጽፍልናል፡፡ ይህንንም አዲስ የሰው ዘር ለመግለጽ የተጠቀመበት ፍኖት "አካል" የሚል ነው፡፡ አብ ለክርስቶስ ከሰጠው ስጦታዎች ውስጥ የክርስቶስን ልብ



For more books www.amharicchristianbooks.com

በደስታ የሚመስጠው ከሁሉ በላይ በአብ ቀኝ መቀመጡ፣ ሁሉ ከእግሩ በታች መገዛቱ ሳይሆን በደሙ የተዋጀችው ሙሽራው ቤተ-ክርስቲያን አካሉና ሙላቱ ሆና ለእርሱ መሰጠቷ ይመስለኛል፡፡ ለዚህም ነው በዮሐንስ ወንጌል 17 ላይ ወደ አባቱ ሲፀልይ ሰባት ጊዜ “እነዚህን የሰጠኸኝን” እያለ ስለ ቤተ-ክርስቲያን የማለደው፡፡

ከዚህም በክርስቶስና በክርስቶስ ማኅበረሰብ መካከል ያለው ግንኙነት ከላይ እንዳየናቸው መንፈሳዊና ግዑዝ ፍጥረታት የገዢና የተገዢ፣ የበላይና የበታች ግንኙነት ሳይሆን ሕይወታዊ የሆነ የፍቅር ግንኙነት መሆኑን እንረዳለን፡፡ ራስና አካል አንድ ናቸው፤ እሷ ያለእርሱ መኖር አትችልም፣ እርሱም ያለ እርሷ አይገለጥም፡፡ እሷ እሱነቱ ናት፣ እሱም እሷነቷ ነው፡፡ አካሉ ስለሆነች ሞቱ ሞቷ ፣ ትንሳኤው ትንሳኤዋ፣ ከፍታው ከፍታዋ፣ መገለጡም መገለጧ ነው፡፡ ሲገዙም አብረው ይገዛሉ፡፡ እርሷ ለእርሱ የምትገዛው አብ በክርስቶስ ሆኖ ፈቃዱን በምድር ላይ እንደፈፀመ ሁሉ ክርስቶስም በእርሷ አድሮ ፈቃዱን እንዲፈፅምባትና እርሷም አብራው እንድትከብር እንጂ እንደሌሎቹ ባዕድ አካላት የሆነ መገዛት አይደለም፡፡[102] ይልቅ የዘላለም ርስት የሆነውን የሕይወት መንፈስ በጋራ እየተካፈሉ፣ በኃይልና በክብር ዕዝ ማዕከል ላይ ተቀምጠው ሁሉን እንዲገዙ፣ አብ ክርስቶስን ለቤተክርስቲያን ራስ አድርጎ ስለ ሰጠው ነው፡፡

እርሱ ሁሉን በሁሉ የሚሞላ ነው፡፡ በ4፡10 ላይ እንደተገለፀው ሁለንታን (ዩኒቨርስን) ማለትም ሰማይንና ምድርን፣ የሚታየውንና የማይታየውን ሁሉ ሊሞላ ተወስኗል፡፡ ቤተክርስቲያን ደግሞ ሙላቱ እንድትሆን ተመረጠች፡፡ ይህም ክርስቶስ አስቀድሞ እርሷን እንደሚሞላ በፍፃሜውም በእርሷ በኩል ሁሉን እንደሚጠቀልልና እንደሚሞላ ያሳየናል፡፡ እርሷም በወንጌል በማመን ከነገድ፣ ከቋንቋ፣ ከወገን፣ ከሕዝብ ሁሉ የተዋጁ ሰዎች ስብስብ ቅድስት ቤተ-ክርስቲያን ናት፡፡ ቤተ-ክርስቲያን በፍጥረቷ "ሁለንታዊ" ብትሆንም፣ በሌላ በኩል በየአካባቢው ባሉ የቅዱሳን ኅብረቶች በጸሎት፣ በአምልኮ፣ በትምህርት፣ እርስ በርስ በመደጋገፍና ላላመነው ማህበረሰብ የምሥራቹን በማድረስ የምትገለጥ "አጥቢያዊ" ናት፡፡

---

[102] ኤፌ. 5፡24



For more books www.amharicchristianbooks.com

# ምዕራፍ ፲

# ያኔና አሁን

ኤፌ. 2፡ 1 - 10

ጥቅጥቅ ባለ ደን የተሸፈኑት የኮሎምቢያ ተራሮች በሂሊኮፕተር ድምጽ ተረብሸዋል፡፡ ከላይ ሆኖ ለተመለከታቸው ከምድር አራዊትና ከሰማይ አዕዋፋት በስተቀር የሰው ዘር የማያልፍባቸው የሚመስሉት የአማዞን ደኖች በጫጫታ ተሞልተዋል፡፡ ግርማቸው በሚያስፈራ በነዚያ ተራሮች ለረዥም ዘመናት የሰፈሩት የፋርክ አማፅያን[103] ከኮሎምቢያ መንግስት ጋር የሚያካሂዱትን የሽምቅ ውጊያ የሚመሩት ተፈጥሮ በለገሳቸው ጎፈሬው እንዳማረ የአፋር ኮበሌ ጥቅጥቅ ባለ ደን በተሸፈኑ ተራሮች ተከልለው ነው፡፡ ሂሊኮፕተሩ በመዘውሩ አየሩን እየቀዘፈ ሽቅብ ይምዘገዘጋል፡፡ በውስጡ ያሉት የኮሎምቢያ ወታደሮች ድምፃቸውን ከፍ አድርገው በላቲን ቋንቋ ይዘምራሉ፡፡ ፊታቸው ላይ የድልና የደስታ ስሜት ይነበባል፡፡ አንዲት ሴት ግን አንገቷ የሚሰበር እስኪመስል ድረስ የኋሊት ታጥፋ ሂሊኮፕተሩ የተነሳበትን ስፍራ በትኩረት ትመለከታለች፡፡ ዕድሜዋ በአርባዎቹ መገባደጃ ላይ ቢሆንም የስድሳና የሰባ አመት አሮጊት የምትመስለው ሴት ዓይኖቿ ከወጣችበት ስፍራ አልተነቀሉም፡፡ ከስድስት ዓመት በፊት ለኮሎምቢያ የፕሬዘዳንትነት ውድድር ቅስቀሳ ስታደርግ በፋርክ አማጽያን የተጠለፈችው ኢንግላድ ቤታንኮርት ለስድስት ዓመት ተኩል በአማጽያኑ አሰቃቂ እገታ ውስጥ የመከራ ኑሮ ገፍታለች፣ አሁን ግን በአለም አቀፍ ማኅበረሰብ ጉትጎታና በኮሎምቢያ መንግስት ጥረት ከግዞት ተላቃ ወደ ነፃነት እያመራች ነው፡፡ አዎን ከፊት ለፊቷ የሚጠብቃት ብዙ ደስታ፣ ብዙ ክብር እንደ ሆነ ታውቃለች፡፡ የናፈቀቻቸውን ፈረንሳዊ ባሏና ልጆቿ ከብዙ አፍቃሪዋቿ ጋር በአየር ማረፊያ በጉጉት ይጠብቋታል፡፡ በመቀጠል በኮሎምቢያ ቤተመንግስት ፕሬዘዳንቱን ጨምሮ ታላላቅ ባለስልጣኖች ሊቀበሏት ተሰናድተዋል፡፡

ጉዳዩን በቅርበት የሚከታተሉት የፈረንሳዩ ፕሬዚዳንት ከወዲሁ የግብዣ ጥሪ አቅርበዋል፡፡ ወደዚህ ደስታና ክብር የምትገሰግሰው ቤታኮርት ግን አንገቷ የኋሊት ዞሮአል ዓይኖቿ ከርቀቱ የተነሳ እያነሰ የመጣውን ለዓመታት በግዞት የኖረችበትን አካባቢ በትኩረት ይመለከታሉ፡፡ ሰው አንገሽግሾት የወጣበትን የመከራ መንደር

[103] የኮሎንቢያ አብዮታዊ ታጣቂ ኃይል (FARC)



For more books www.amharicchristianbooks.com

ስለምን ወደ ኋላ ይመለከታል? ስለምን የትዝታና የትውስታ ማህደር በሕሊናው ይቀርፃል? እነዚያን መራራ ጊዜያት የሚተርኩ መጽሐፍትስ ስለ ምን ይፃፋሉ? በእውነት ነፃ ለወጡ ሰዎች የትናንት የግዞት ታሪካቸው ለዛሬው የሕይወት ጉዟቸው ያለው ፋይዳ በዋጋ ሊተመን አይችልም፡፡ ያ መራራ የኋላ ታሪክ፣ ዛሬ ወደ ክብር ለሚያደርጉት ጉዞ የማይነጥፍ ኃይል ነው፡፡ ያ የወጡበት የግዞት ታሪክ፣ ከኋላ ሲገፋቸው፣ ወደርሱ የሚገሰግሱለት የክብር ተስፋ ወደፊት ሲስባቸው ጉዞአቸው ይሰምራል፡፡ ሳይተጓጎል ይቀጥላል፡፡

ሐዋርያውም በትንሿ እስያ ላሉት ከጨለማው ሥልጣን ድነው ወደ እግዚአብሔር የፍቅር ልጅ መንግስት ለፈለሱት[104] አማንያን አሁን ወዳሉበት እረፍት ከመምጣታቸው በፊት የት እንደነበሩ በማሳየት የያኔውንና የአሁኑን ያነፃጽርላቸዋል፡፡ ራሱንም ከእነርሱ ጋር በመደመር እንደ ኮሎምቢያዋ ቤታኮርት የወጣበትን የባርነትና የግዞት ኑሮ የኋሊት ያያል፣ ያሳያል፡፡

ይህ ተግባሩ ብርቱ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ድጋፍ አለው፡፡ በቀደሙት ዘመናት እግዚአብሔር ለሕዝቡ ለእስራኤል አንድ መልዕክት ማስተላለፍ ሲፈልግ ንግግሩን የሚጀምረው *"ከግብጽ ምድር ከባርነት ቤት ያወጣሁህ እግዚአብሔር አምላክህ እኔ ነኝ"* (ዘፀ. 20፡2) በሚል የማስታወሻ ቃል ነበር፡፡ ምንም እንኳ ሕዝቡ ወደ ግብጽ እንዲመለሱ ፈጽሞ ባይሻም በግብጽ ምድር በባርነት ቤት የነበራቸውን ኑሮና እንዴት ባለ ሁኔታ እንዳወጣቸው እርሱንና ሥራውን እንዲረሱ አይፈልግም፡፡ እስራኤላውያን እንደ ሕዝብም፣ እንደ መንግስትም የዘወትር ውድቀታቸው እግዚአብሔር ለእስራኤል ያደረገውን መልካም ሥራ ከመርሳት ጋር በጽኑ የተቆራኘ ነበር፡፡[105] ይህ በሽታ ከግብጽ ከወጡበት ማግስት አንስቶ እንደተጠናወታቸው መጽሐፍት በግልፅ ይመሰክራሉ፡፡ ወደ ኋላ ዞር ብለው እግዚአብሔር በተዘረጋች ክንድ፣ በፀናችም እጅ እንዳወጣቸው፣ ንስር ለጫጩቶቿ እንደምታደርግ በክንፉ እንደተሸከማቸው፣ ማየት ባለመቻላቸው የተገረመው ሙሴ *"እኔ አመፃችሁንና የአንገታችሁን ድንዳኔ አውቃለሁና"* ብሏቸዋል፡፡ ዳሩ የናስ አንገት፣ የብረት ጅማት ያለው እንደምን ዞር ብሎ የኋላውን ማየት ይችላል?

እስራኤላውያኑስ የወጡት ከሥጋ ባርነት፣ በዓይን ከሚታይ ግዞት ነው፡፡ ስለዚህ እንዲህ አይነቱን ለማሰብም ሆነ ለማስታወስ ይቀላል፡፡ እኛ ግን የአዲስ ኪዳን አማኞች የወጣነው በመልክዐ ምድር ከሚገለጥ ግዑዝ ሥፍራ ሳይሆን፣ በዓይን

---

[104] ቆላ. 1፡13

[105] መሳ. 2፡ 6-10



For more books www.amharicchristianbooks.com

ከማይታይ መንፈሳዊ ግዛት በመሆኑ ለማስታወስ ሊያስቸግር ይችላል፡፡ ለዚህ ነው ደግሞ፣ ደጋግሞ ማስታወስ፣ ዞር ብሎ ወደ ኋላ መመልከት ግድ ይላል፡፡ ይህም የተሰጠንን ፀጋ፣ የተገለጠልንን ምህረትና ፍቅር እያሰብን ለእግዚአብሔር የሚገባውን ክብር እንድንሰጥ፣ ለተጠራንበትም መጠራት እንደሚገባ እንድንኖር ወደር የማይገኝለት መፍትሄ ነው፡፡

## ያኔ

ሐዋርያው የልብ ዓይኖቹ በርተው አሻግሮ ወደኋላ እያየ በደማቅ ቀለማት በብዕሩ የሚስልልን፣ ቀደም ሲል የኖርንበት መንፈሳዊ ግዛት ወድደን የከተምንበት፣ ዐልመን የሰፈርንበት ሳይሆን ተወልደን የገባንበት፣ ተገዝተን የኖርንበት የባርነት ቤት ነበር፡፡

"በበደላችሁና በኃጢአታችሁ ሙታን ነበራችሁ . . . ፡፡"

ምንም እንኳ ኑሮአችን የተፈጠርንበትን ዓላማ ስቶ በኃጢአት የተነከረ፣ የተሰመረልንን ገደብ ጥሶ በመተላለፍ የተሞላ፣ የበደል ኑሮ ቢሆንም፣ ጥንስሱ እኛው ጋ ተጥሎ፣ እኛው ጋ የተጠመቀ አልነበረም፡፡ ምንጭ አለው፡፡ ይህንንም ጸሐፊው *"እንደሌሎቹም ደግሞ ከፍጥረታችን የቁጣ ልጆች ነበርን"* ከሚለው መረዳት እንችላለን፡፡ ይህ "ፍጥረት" የመጀመሪያውን የሰው ልጅ አፈጣጠር የሚያሳይ ሳይሆን በኃጢአት ከወደቀው ከአዳም ዘር በመወለድ የወረስነውን ጥንተ-አበሳን የሚያመለክት ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ በሌሎች ክፍሎች የሚገኘውን የጳውሎስን አስተምህሮ ስንመለከት የመጀመሪያውንና በፈቃደኝነት የተፈፀመውን የኤደን ገነቱን የአዳምን ኃጢአትና በደል እኛ በሥጋ ከእርሱ ዘር የተወለድን ልጆቹ አይመለከተንም ልንል እንደማንችል ያሳየናል፡፡ በእርሱ ወገብ ነበርንና ወደድንም ጠላን በኃጢአቱም ሆነ ተከትሎት በመጣው ሞት ተካፍለናል፡፡ [106]

ስለዚህ በኃጢአታችንና በበደላችን ሙታን ነበርን፡፡ "ሙታን" ሲል መኖር ያቆምን በድን ነበርን ለማለት አይደለም፡፡ ከእግዚአብሔር ሕይወት ርቀን [107] በስጋ ምኞት ስለምንቅበዘበዝ ከእግዚአብሔር አንፃር ሙታን ነበርን፡፡ በበደልና በኃጢአት ጦር ተወግቶ በሞት ከእግዚአብሔር የተለየው መንፈሳችን በልዩ ልዩ ኃይላት ሥር ይገዛ ነበር፡፡ ሞት በመንፈሳችን ላይ ነግሦ፣ ነፍሳችንን ከሕይወት ጌታ ለይቶ፣ ሥጋችንን እያስረጀ ወደ ዘላለም ሞት ይጋልበን ነበር፡፡ ይህን የሞት ኑሮ የምንገፋው

[106] ሮሜ 5፡12-21
[107] ኤፌ. 2፡11-13; 4፡17-19



For more books www.amharicchristianbooks.com

ለብቻችን አልነበረም፡፡ ጳውሎስ በዕብራውያን የንግግር ለዛ *“ያለመታዘዝ ልጆች”* ከሚላቸው ብዙሃን ጋር እንጂ፡፡ "ያለመታዘዝ ልጆች" አመጽን እናቴ፣ መተላለፍን ወላጄ ብለው የሚጠሩ፣ ከዚህ ውጭ ሌላ ሕይወት የማይናፍቃቸው፣ እውነት ቢነገራቸው እንኳ በአመፃ የሚከለክሉ ማኅበረሰብ ናቸው፡፡ ከእነዚህ ጋር ተባብረን በዚህ ዓለም እንዳለው ኑሮ እንመላለስ ነበር፡፡ በዚህ ስፍራ ጸሐፊው "ዓለም" ሲል የምንኖርበትን ግዑዝ ሥፍራ ማለቱ ሳይሆን በዲያቢሎስ ቁጥጥር ስር ያለውን የአሁኑን ዘመን ለማሳየት ነው፡፡

ቀደም ሲል በ1፡21 ላይ “በዚህ ዓለም ብቻ ሳይሆን ነገር ግን ሊመጣ ባለው ዓለም . . . ፡፡” በማለት የጻፈውን ያስታውሰናል፡፡ በዚህ ዓለም ውስጥ የሚሠራ መንፈስ አለ፡፡ በእርግጥ ጳውሎስ “አሁን ለሚሠራው መንፈስ” ሲል ሰብዕና ስላለው ስለ አንድ ነጠላ መንፈስ ለመናገር ፈልጎ አይደለም፣ ይልቅስ ማኅበራዊ ኑሮን፣ ኃይማኖታዊ ፍልስፍናን፣ ኢኮኖሚያዊ ስሌትንና በሰው ልጆች ዘንድ ያለውን የማይበጠስ ሥነልቦናዊ ትስስር ተገን በማድረግ ሰውን ሁሉ ለዲያቢሎስ አገዛዝ የሚያመቻቸውን የሕይወት ሥርዓትና የኑሮ ዘይቤ ማለቱ እንደሆነ የቃሉ አገባብ ያመለክታል፡፡ ልክ በ1ኛ ቆሮንቶስ 2፡12 ላይ *“. . . የዓለምን መንፈስ አልተቀበልንም”* እንዳለው፡፡

በዚህ እግዚአብሔር አልባ በሆነ የአመጽ ሥርዓት ላይ ተንሰራፍቶ የሚገዛ አለቃ መኖሩንም ይነግረናል፡፡ ይህም አለቃ፣ ጳውሎስ ቆየት ብሎ በ4፡27 እና በ6፡11 ላይ የሚያነሳው ዲያቢሎስ ለመሆኑ ምንም ጥርጥር የለውም፡፡ የሚገርመው ሥልጣኑን የሚገልፀው በአየር ላይ መሆኑ ነው፡፡ በእርግጥ ጥንታዊ የአይሁድ መምህራን እግዚአብሔር ከቅዱሳን መላዕክቱ ጋር በሰማይ ሰማያት ሲኖር ምድርን የሸፈናት ከባቢ አየር የክፉ መናፍስት ማደሪያ እንደሆነ ያስተምሩ ነበር፡፡ ሆኖም ይህን አስተሳሰብ በቅዱሳት መፃሕፍት ስንፈትሸው ውድቅ ይሆናል፡፡ ሌላው ግሪካውያኑ መንፈስ የሚለውን ቃል የወሰዱት አየር ወይም ነፋስ ከሚለው ቃል ስለሆነ ነፋስ በዙሪያችን እንዳለ፣ ነገር ግን በዓይናችን ባናየውም በሥራው መኖሩን እንደምንገነዘብ ሁሉ፣ በዙሪያችንም የሚኖርና የሚሠራ መንፈሳዊ ዓለም ባይታይም አለ ይሉ ነበር፡፡ ይህ አስተሳሰብ የጳውሎስን አባባል ለመረዳት የተሻለ ፍንጭ ይሰጣል፡፡ ዛሬ ብዙዎች እንደሚያስቡት በዙሪያችን ያለው ከባቢ አየር ኦክስጅን፣ ካርቦንዳይ አክሳይድ ወ.ዘ.ተ በመሳሰሉት ንጥረ ነገሮች እንጂ በክፉ መናፍስት የተሞላ አይደለም፡፡ ነገር ግን ዲያቢሎስ በአየር ውስጥ ሳይሆን በአየር በተመሰለው በዙሪያችን በእንቅስቃሴ ላይ ባለው መንፈሳዊ ዓለም ላይ አለቃ ሆኖ ፈቃዱን ይፈጽማል፡፡



For more books www.amharicchristianbooks.com

የሚፈጽመውም ሥጋ የለበሱ ሰዎችን በመጠቀም ነው፡፡ ይህ አለቃ ያለ ሥጋ ለባሽ ሰው በግዑዙ ዓለም ውስጥ አንዳች ማድረግ አይችልም፡፡ በእግርጥ ያኔ እኛ ፍቃዱን ይፈጽምብን፣ አይፈጽምብን የምናውቀው ነገር አልነበረም፡፡ ነገር ግን እንመላለስ ነበር፡፡ “መመላለስ” የሚለው ቃል አይሁዳውያን የሰውን የምድር ኑሮ በጥቅሉ ለመግለጽ የሚጠቀሙበት ዘይቤያዊ አነጋገር ነው፡፡ ጳውሎስም ዕብራዊ እንደመሆኑ መጠን ይህን ቃል በዚህ መልዕክት ውስጥ ብቻ አምስት ጊዜ ያህል ተጠቅሞበታል፡፡[108]

ሐዋርያው “እናንተ” በማለት የሚጽፍላቸውን አሕዛብ የቀድሞ ኑሮ በመተረክ ይጀምርና ብዙም ሳይቆይ ራሱንና የሚወክላቸውን አይሁዳውያን በዚህ ውድቀት ውስጥ በማካተት “እኛ ሁላችን ደግሞ የሥጋችንንና የልቡናችንን ፈቃድ እያደረግን በሥጋችን ምኞት በፊት እንኖር ነበርን . . . ፡፡” ይላል፡፡ በእርግጥ ይህ አባባል ሕግ፣ ኪዳን፣ የአምልኮ ሥርዓት፣ ተስፋ ወ.ዘ.ተ በመቀበላችን ሕያዋን ነን ሙታን አይደለንም ብለው ለሚከራከሩት አይሁዳውያን የማይዋጥ ቢሆንም ሐዋርያው ግን ራሱንም ጨምሮ መላው የሰው ዘር በኃጢያት ምክንያት ሙት መሆኑን በድፍረት ይመሰክራል፡፡[109]

ያኔ በዓለም ስንኖር በአየር ላይ የሚሰራውን መንፈስ አለቃ ፈቃድ መፈጸማችንን አናውቅም ነበር፡፡ እኛ የምናውቀው ሥጋችንና ሃሳባችን የፈጠሩት የሚመስለንን ምኞት ማድረጋችንን ነበር፡፡ ነገር ግን ምኞታችን በክፉው መረብ ወጥመድ ውስጥ ወድቆ ኖሮ የክፉውን ሃሳብ ሲያገለግል ኖሯል፡፡ ወትሮም ምኞት በልቦናችን መቀስቀሱ ሰይጣን የእኛን አምሮት የማርካት ዓላማ ኖሮት ሳይሆን እኛ በማይገባን ረቂቅ ስልት የራሱን ፈቃድ የሚያስፈጽምበት ዘዴ ስለ ነበር ብቻ ነው፡፡

የዚህ አለቃ ገዢ ፈቃድ ምንድን ነው? ቢዘረዘር ቦታ ላይበቃው ይችል ይሆናል፡፡ በጥቅሉ ሲቀመጥ ግን ፈቃዱ አሳባችንን በጠላትነት በመሙላት፣ ብልቶቻችንን የአመፃ የጦር መሣሪያ በማድረግ የእግዚአብሔርን ጽድቅ መዋጋት ነው፡፡ ሆኖም ይህ መሆኑ ሰውን ከተጠያቂነት ሊያድነው አይችልም፡፡ ፈቃዳችን በዲያቢሎስ ፈቃድ ተጠልፎ የእግዚአብሔርን እውነት ለመዋጋት ቢውልም፣ እንደ ሰው ነፃ ፈቃድ ያለን ፍጡር ነንና በፍርድ መጠየቃችን አይቀሬ ነው፡፡ ለዚህ ነው ሐዋርያው “. . . እንደሌሎችም ደግሞ ከፍጥረታችን የቁጣ ልጆች ነበርን፡፡” በማለት ይህንን ክፉ ፈቃድ እየፈጸምንና እያስፈጸምን ከኖርነው የዐመጽ ኑሮ የተነሳ ወደፊት

[108] ኤፌ. 2፡2; 10; 4፡1; 17; 5፡2; 10; 15
[109] ሮሜ 3፡ 9 - 20



For more books www.amharicchristianbooks.com

የሚጠብቀን ዘላለማዊ ርስት የእግዚአብሔር ቁጣ ንዳድ እንደነበር የሚነግረን፡፡

ሐዋርያው በእነዚህ ሦስት ቁጥሮች ውስጥ በገጠገጣቸው ጠንካራ ቃላት የነበርንበት መንፈሳዊ ግዛት ምንኛ አሰቃቂ እንደነበር በጉልህ ተንፀባርቋል፡፡ በደልና ኃጥያት፣ መንፈሳዊ ሞት፣ የአመጽ የኑሮ ሥርዓት፣ የሥጋ ምኞት፣ የማያባራ ቁጣ፣ ጽኑ የዲያቢሎስ አገዛዝ ተጭነውን ራሳችንን ለማዳን ጣታችንን እንኳ ማንቀሳቀስ በማንችልበት ሞት ውስጥ ወድቀን እንደነበርን ያሳየናል፡፡

## አሁን

ጸሐፊው ምንም እንኳ ከላይ የያኔውን ጨለምተኛ ኑሯችንን ያለመቆጠብ ቢተርከም ብዙም ሳይቆይ "ነገር ግን" በሚል ኃይለ ቃል የላይኛውን እየሻረ አዲስ የምሥራች ያበስረናል፡-

> *"ነገር ግን እግዚአብሔር በምህረቱ ባለጠጋ ስለሆነ ከወደደንም ከትልቅ ፍቅሩ የተነሳ በበደላችን ሙታን እንኳ በሆንን ጊዜ ከክርስቶስ ጋር ሕይወትን ሰጠን፡፡" (ቁ.4)*

ቀደም ሲል በ2፡1 ላይ አዲሱን ዓረፍተ ነገር ሲጀምር *"በበደላችን . . . ሙታን"* እንደነበርን ነግሮናል፡፡ አሁን ግን ሞታችን በሕይወት ተለወጠ፡፡ መንፈሳችን ተነሳ፣ ሕያው ሆነ፡፡ ቀደም ሲል በ1፡19-23 የእግዚአብሔር የኃይሉ ታላቅነትና የብርታቱ ጉልበት የተገለጠበትን የኢየሱስ ክርስቶስን ትንሳኤና ክብር ጽፎልን ነበር፡፡ አሁን ግን ትንሳኤው የአንድ የእርሱ ብቻ ሳይሆን በእርሱ የሚሆነው አዲስ ፍጥረት ጭምር መሆኑን፣ እኛም በስሙ በማመናችን የትንሳኤው ተካፋይ ሆነን ከሞት ወደ ሕይወት መሻገራችንን የምሥራች ይነግረናል፡፡ የኢየሱስ ትንሳኤ አካላዊና ታሪካዊ ነው፡፡ የእኛ ትንሳኤ ግን በአካል የምንነሳበት ተራ እስኪደርስ፣ ተስፋ እስኪሞላ ድረስ መንፈሳዊ ነው፡፡ ስለዚህ በበደላችን ምክንያት በመንፈስ ሙት የነበርነውን፣ ኢየሱስን ከሙታን ያስነሳው የእግዚአብሔር መንፈስ ወደ ውስጣችን በመግባት ሕያው አደረገን፡፡ የማዳን ሥራው በዚህ አላበቃም፡፡ ልክ በኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ሆነው ሁሉ እኛንም *"በሰማያዊ ሥፍራ ከእርሱ ጋር አስቀመጠን፡፡"*

ይህ ታላቅ ለውጥ እንዴት ሊመጣ እንደቻለ ሲጽፍ በብቸኝነት የሚጠቅሰው የእግዚአብሔርን ምህረትና ፍቅር ነው፡፡ ቀደም ሲል የክብሩን ባለጠግነት፣ የኃይሉን ታላቅነት ነግሮናል (ቁ.19) አሁን ደግሞ የምህረቱን ባለጠግነትና የፍቅሩን ታላቅነት ይተርክልናል፡፡ የማረን ለምሕረት የሚያበቃ ተግባር ስለተገኘብን፣ ያፈቀረን ፍቅር ስለታየብን ሳይሆን እግዚአብሔር ራሱ በማንነቱ ፍቅር ስለሆነ፣



For more books www.amharicchristianbooks.com

ከእኛ ወገን ምክንያት አልባ በሆነ መንገድ አነሳሽና ቀስቃሽ በማይፈልግ በራሱ ፍቅር ወደደን በብዙ ምሕረትም ከለለን፡፡

ሐዋርያው ይህንን ድንቅ ተግባር የሚያበረክተው ለእግዚአብሔር ፀጋ ነው፡፡ *"በፀጋ ድናችኋልና… ፡፡"* (ቁ.5, 7, 8) በማለት፡፡ ፀጋ ነፃ ስጦታ ብቻ አይደለም፡፡ ነገር ግን ለማይገባው የሚሰጥ፣ ተቀባዩ የማይመጥነው፣ ሰጭውን የሚያከል፣ ነፃ ስጦታ ነው፡፡ ይህም ምሕረቱና ፍቅሩ ከሰው ዘንድ የሆነ አንዳች አነሳሽ እንደሌለው፣ የማዳኑ ተግባር ሙሉ በሙሉ በራሱ በጎነት የተከናወነ እንደሆነ ያረጋግጥልናል፡፡ እዚህ ጋ ለመዳናችን ያበረከትነው የእግዚአብሔር ፀጋ ላይ የምንደምረው አንዳች ሥራ አለመኖሩን ልብ ልንል ይገባል፡፡ ለነገሩ "ሙት" ምን ሊሠራ ይችላል? የዳንነው በእምነት ብቻ ነው፡፡ ነገር ግን እምነቱም ቢሆን የእኔ አበርክቶት ነው ብለን ልንመካበት አንችልም፡፡ ያመንነውም ከእርሱ የተነሳ ነውና፡፡ ማመናችን የማመን ጉልበት እንደነበረን ሳይሆን፣ የሰማነው የእምነት ቃል እምነትን የመፍጠር ጉልበት እንደነበረው የሚያመላክት ነው፡፡ *"እናንተም ደግሞ የእውነትን ቃል ይኸውም የመዳናችሁን ወንጌል ሰምታችሁ፣ ደግሞም በክርስቶስ አምናችሁ . . . ፡፡"* (1፡13) ይላልና፡፡ ዘር፣ አፈር ውስጥ ወድቆ አፈሩን ተመግቦ መብቀሉ በዘሩ ውስጥ ያለውን የሕይወት ኃይል እንጂ የአፈሩን ጉልበት እንደማያሳይ ሁሉ፣ የእኛም ማመን የሰማነው የሕይወት ቃል ፍሬ እንጂ የማንነታችን ውጤት አይደለም፡፡ ስለዚህ መዳናችንን በተመለከተ በእግዚአብሔር ፊት የምንመካበት አንዳች ነገር የለንም፡፡

እግዚአብሔር እያንዳንዳችንን በተናጠል አላስነሳንም ወይም እያንዳንዳችንን በሰማያዊ ስፍራ አላስቀመጠም፡፡ ኢየሱስን አንድ ጊዜ ከሙታን አስነስቷል፣ ከሁሉ በላይ በቀኙ አስቀምጦታል፡፡ ያ ከሙታን መነሳትና ያ በቀኙ መቀመጥ፣ በክርስቶስ ያሉትን ሁሉ የሚጠቀልል ነውና፣ ማንም በየትኛውም ዘመን በወንጌል ሲያምን፣ በዚያ መነሳት ይነሳል፣ በዚያው መቀመጥ ይቀመጣል፡፡ ይህንንም ሦስት ጊዜ *"ከእርሱ ጋር"* በማለት የተፃፈው ቃል ያረጋግጥልናል፡፡ *"ከእርሱ ጋር ሕይወትን ሰጠን፣ ከእርሱ ጋር አስነሳን፣ ከእርሱ ጋር አስቀመጠን፡፡"* ይላልና፡፡ ይህም ከእርሱ የተለየ ማንነትና ከእርሱ የተለየ ታሪክ እንደሌለን ያስረዳናል፡፡ የዘላለም ጌታ ዘላለማዊ ታሪክ፣ ታሪካችን ሆኖአልና፡፡

ይህ ክፍል እግዚአብሔር መዳናችንን እንዴት እንዳደረገው ብቻ ሳይሆን ለምን እንዳደረገውም ጭምር ይነግረናል፡፡ በ1፡6 ላይ *"በውድ ልጁም እንዲያው የሰጠን የፀጋው ክብር ይመሰገን ዘንድ ይህን አደረገ"* በማለት ምክንያቱ በፀጋ ለሰጠን ክብር ምስጋና መሻቱ መሆኑን እንደ ነገረን ሁሉ፣ አሁንም የማዳኑ ዓላማ *"በሚመጡት*



For more books www.amharicchristianbooks.com

*ዘመናትም በክርስቶስ ኢየሱስ ለእኛ ባለው ቸርነት ከሁሉ የሚበልጠውን የፀጋውን ባለጠግነት ያሳይ ዘንድ . . . ፡፡"* መሆኑን ይነግረናል፡፡

ይህም አገላለጽ በእግዚአብሔር የማዳን *ሥራ* ውስጥ በተለያዩ ጊዜያት በሚገለጡ የፀጋ ዓይነቶች መካከል የመጠንና የይዘት ልዩነት መኖሩን ሳይሸሽግ ይነግረናል፡፡ በወንጌል ባመንን ጊዜ ለመንፈሳችን ሕይወትን በመስጠት አዲስ ፍጥረት ሲያደርገን ፀጋ ተገልጧል፡፡ የመንፈስን በኩራት ካገኘንም በኋላ የነፍሳችንን መዳን እየፈፀምን ዕለት ዕለት በፊቱ ስንመላለስ ይህ ነው የማይባል ፀጋ በኑሯችን ይገለጣል፡፡ ነገር ግን በዘመን ፍፃሜ ሰውነታችንን በኃይል በሚያስነሳበት ጊዜ የሚገለጠው ፀጋ አቻ የሌለውና ከቀደሙት ሁለቱ የሚበልጥ መሆኑን የምንረዳው *"በሚመጡት ዘመናት በክርስቶስ ኢየሱስ ለእኛ ባለው ቸርነት* ***ከሁሉ የሚበልጠውን*** *የፀጋ ባለጠግነት ያሳይ ዘንድ . . . "* የሚለውን ስናነብ ነው፡፡ ይህን ከሁሉ የሚበልጥ ፀጋ በተመለከተ፣ ተስፋ ከማድረግና በናፍቆት ከመጠበቅ በቀር ምን ልንል እንችላለን!? ቃሉ እንደሚያስረዳን ይህ ፀጋ የምናየው ብቻ ሳይሆን የምንታይበት ነው፡፡ ባለጠግነትን ተመልካች ብቻ ሳይሆን መመልከቻ እንሆናለን፡፡ የሚገለጠው በእኛ ነውና፡፡ በዚያን ቀን ፍጥረት ሁሉ የእግዚአብሔርን የፀጋ ባለጠግነት በገሃድ የሚያይብን ዐውደ ርዕይ እንሆናለን፡፡

ቀደም ብዬ እንደገለጽኩት የዳንነው በፀጋ እንጂ በ*ሥራ* አይደለም፡፡ ነገር ግን ምንም እንኳ በ*ሥራ* ባንድንም ለ*ሥራ* እንደዳንን ሊታወቅ ይገባል፡፡ በ2፡8-10 ሐዋርያው ሦስት *ሥራ*ዎችን ያሳየናልና፡፡ አንደኛው እኛን ለማዳን እግዚአብሔር በክርስቶስ ኢየሱስ የሠራው *ሥራ* ነው፡፡ ይህም *ሥራ* ስጦታ ተደርጎ ተሰጥቶናል፡፡

"ፀጋው በእምነት አድኗችኋልና ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም፣ ማንም እንዳይመካ ከ*ሥራ* አይደለም፡፡" (ቁ.8) እንደሚል፡፡

ነገር ግን የፀጋው *ሥራ* በክርስቶስ የምትክነት ሞት *ሥራ*ችንን ሠርቶ፣ *ሥራ*ውንም ስጦታ አድርጎ በመስጠትና ያመንነውን ኃጢአተኞች በማጽደቅ የሚያከትም አይደለም፡፡ በመቀጠል *"እኛ የእጆቹ ሥራዎች ነንና"* ስለሚል፡፡ *ሥራ*ችንን የሠራልን ጌታ ካፀደቀንም በኋላ ብልሃተኛ እጆቹን ዘርግቶ እንደሚሠራን ይነግረናል፡፡ ይህ ቃል በግሪክ ቋንቋ፣ የአንድን ሰዓሊ ወይም ቀራጭ የ*ሥራ* ውጤት የሚያሳይ ትርጉም ያዘለ ነው፡፡ የሚሠራንም በከንቱ አይደለም *"እንመላለስበት ዘንድ አስቀድሞ ያዘጋጀውን መልካሙን ሥራ ለማድረግ . . . ፡፡"* አልሞ እንጂ (ቁ.10)፡፡ በቀድሞው የሙታን ኑሯችን በአየር ላይ ስልጣን እንዳለው አለቃ ፈቃድ ተመላልሰናል፡፡ (ቁ.2) አሁን ግን ዓለም ሳይፈጠር አስቀድሞ



For more books www.amharicchristianbooks.com

ያዘጋጀውን መልካም *ሥራ* እየሰራን እንድንመላለስ በክርስቶስ ኢየሱስ አዲስ ፍጥረት አደረገን፡፡ ይህ ከእኛ መፈጠርም ሆነ ዳግም መወለድ አስቀድሞ የተዘጋጀ መልካም *ሥራ* ገና በጠዋቱ በ 1፡4 ላይ እንዳየነው ". . . በፊቱ ቅዱሳንና ነውር የሌለን ሆነን በፍቅር . . . " መመላለስ ነው፡፡

ስለዚህ የተሠራው ለእኛ፣ የተሠራነውም እኛ፣ የሚሠራውም በእኛ በኩል መሆኑን ስንመለከት የሠራተኛውን የእግዚአብሔር ብርታት በግልፅ እያየን፣ "ሠራልን፣ እየሠራን ነው፣ ይሠራብናል" የሚል አዲስ ቅኔ እንቀኛለን፡፡

## የሁለት ዓለም ንጽጽር

ጳውሎስ በ 2፡1-10 ሰው ሁሉ በኃጢአት ምክንያት ከእግዚአብሔር መለየቱን እና በ 2፡11-22 አሕዛብ ከእግዚአብሔር ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔር ሕዝብ ከሆኑት ከእስራኤላውያን መለየታችንን ለመግለጽ የተጠቀመበት ስልት ንጽጽራዊ ነው፡፡ በ2፡11-22 ያለውን በራሱ ጊዜ ስለምናየው ላሁን 2፡1-10 የሰፈረውን በዝርዝር እንመልከት፡፡ ምንም እንኳ በግሪኩ ሰዋሰው 2፡1-10 ያለው አንድ ወጥ ዓረፍተ ነገር ቢሆንም፣ ንጽጽሩን በግልጽ ለማየት ሲባል ከቁጥር 1-3 ያለውንና ከቁጥር 4-10 ያለውን ለሁለት ከፍለን እናያለን፡፡

የመጀመሪያው ክፍል ከቁጥር 1 - 3 በተፈጥሮ ምን እንደነበርን ሲያሳይ፣ ከቁጥር 4 - 10 ያለው ደግሞ በፀጋ ማን እንደሆንንና ምን ልንሆን እንደምንችል ለማሳየት ይሞክራል፡፡ በእርግጥ ከሁሉ ከሚበልጠው ከፀጋው ባለጠግነት የተነሳ ወደፊት ልንሆነው ያለውን ይቅርና አሁን የሆነውን እንኳ ዘርዝሮ ለመረዳት ከመታወቅ የሚያልፍ መሆኑን መገመት አያስቸግርም፡፡

ወደ ንጽጽሩ ስንመለስ ከቁጥር 1 - 3 ባሉት ክፍሎች ውስጥ የተነሱት መሠረታዊ ችግሮች ሁሉ እግዚአብሔር በክርስቶስ ኢየሱስ ከሠራው *ሥራ* የተነሳ በቁጥር 4 - 10 ባሉት ክፍሎች የማያዳግምም መፍትሔ እንዳገኙ እንመለከታለን፡፡ ከእነዚህ ችግሮች የመጀመሪያው ሙታንነት ነበር፤ ሆኖም በቁጥር 4 ላይ "ከክርስቶስ ጋር ሕይወት ሰጠን፣ ከእርሱ ጋር አስነሳን" በማለት ችግሩ ፍፁም መፍትሄ ማግኘቱን ይጽፍልናል፡፡ በመቀጠል የሚያነሳው ተግዳሮት *"በአየር ላይ ስልጣን ባለው አለቃ ፈቃድ"* (ቁ.2) መገዛታችን ነበር፡፡ ይህ ችግር መፈታቱን በአንድ ቃል ሲገለጽ *"በክርስቶስ ኢየሱስም በሰማያዊ ስፍራ ከእርሱ ጋር አስቀመጠን፡፡"* ይላል፡፡ ቀድሞ በመንፈስ ሙታን በነበርን ጊዜ ከበላያችን ከፍ ብሎ ይገዛን የነበረው የመንፈስ አለቃ ፈጽሞ ሊያስበውና ሊረዳው በማይችል ረቂቅ አሠራር በብዙ ርቀት ከበላዩ



For more books www.amharicchristianbooks.com

ከፍ ብለን እንደተቀመጥን ይነግረናል፡፡ ይህ እንዴት ሊሆን ቻለ? ብሎ የሚጠይቅ ካለ 1፡19-21 ላይ የተፃፈውን ማንበብ ይኖርበታል፡፡

የሰው ልጅ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን ሲነሳና በሰማያዊ ስፍራ በአብ ቀኝ ሲቀመጥ ከአለቅነትና ከሥልጣንም ፣ከኃይልም ፣ከጌትነትም ሁሉ በላይ ከፍ ሲል፣ ብቻውን ሳይሆን የአዲሱ የሰው ዘር ራስ ሆኖ ነውና እኛም በእርሱ ውስጥ በሕይወት ከፍ ከፍ በማለታችን መገዛት ማከተሙን፣ መግዛት መጀመሩን የምሥራች ይለናል፡፡ ሌላው የያኔው መዘዝ በዲያቢሎስ ረቂቅ መረብ ውስጥ ከመጠመዳችን የተነሳ፣ የሥጋችንን ምኞት እየፈፀምን ሲመስለን ሳናውቅ በአየር ላይ ሥልጣን ባለው አለቃ ፈቃድ እንመላለስ እንደነበር በቁጥር 2 ላይ ነግሮናል፡፡ አሁን ግን በክርስቶስ ኢየሱስ በማመናችን የመጣውን ሥር ነቀል ለውጥ ሲነግረን "እኛ የእጆቹ ሥራዎች ነንና እንመላለስበት ዘንድ እግዚአብሔር አስቀድሞ ያዘጋጀውን መልካሙን ሥራ ለማድረግ በክርስቶስ ኢየሱስ ተፈጠርን፡፡" (ቁ.9፣10) ይለናል፡፡ ቀድሞ በሞት አገር በባርነት ቤት፣ በጥፋት ምድር እንመላለስበት የነበረው የኑሮ ዘይቤ፣ ከእባብ ምላስ ሥር የሚመነጭ ገዳይ መርዝ ነበር፡፡ አሁን ግን እግዚአብሔር አለም ሳይፈጠር አስቀድሞ እንመላለስበት ዘንድ ባዘጋጀው የኑሮ ስልት ለመመላለስ እንደገና ተፈጠርን፡፡ የመጣው ለውጥ የፀባይ፣ የአመለካከት፣ የግብረገብና የልማድ ብቻ ሳይሆን የተፈጥሮ ለውጥ መሆኑን ልብ ይሏል!

በመጨረሻም ከመዳናችን በፊት ለጠላት ጦር ተሰልፈን በአሳባችንም ሆነ በተግባራችን ከእግዚአብሔር ጋር በመዋጋታችን ተቀዋሚዎችን ሊበላ የተዘጋጀ የእሳት ፍርድ የተጠበቀልን የቁጣ ልጆች እንደነበርን በቁጥር 3 ላይ ነግሮናል፡፡ አሁን ግን በክርስቶስ ከማመናችን የተነሳ በዘመን መጨረሻ የሚጠብቀን የእግዚአብሔር ቁጣ መሆኑ ቀርቶ ለእኛ የሚገለጥ የፀጋው ባለጠግነት ሆነ፡፡ ". . . በሚመጡት ዘመናትም በክርስቶስ ኢየሱስ ለእኛ ባለው ቸርነት ከሁሉ የሚበልጠውን የፀጋውን ባለጠግነት ያሳይ ዘንድ" ተብሎ እንደተፃፈ (ቁጥር 6) ለጥፋት የተዘጋጀን የቁጣ ዕቃዎች ወደ ምሕረት ዕቃነት ተለወጥን፡፡[110]

[110] ሮሜ 9፡22-24



For more books www.amharicchristianbooks.com

# ምዕራፍ ፬
# አብሮ መግባት

ኤፌ. 2፡ 1 - 22

ቀኑ ሰኞ እ.ኤ.አ. ጁን 27/2011 ነው፡፡ በዋና ከተማዋ በኢየሩሳሌም የሚገኘውን የእስራኤልን ቤተ-ክኔሴት (ፓርላማ) ለመጎብኘት እድል ስላገኘሁ በማለዳ ከቴሌአቪቭ ወደ ኢየሩሣሌም አቀናሁ፡፡ ለረዥም ሰዓታት በፓርላማው ውስጥ ቆይቼ ከሰዓት በኋላ 10 ሰዓት ላይ ስወጣ ከፓርላማው ጎን ያለው መናፈሻ ጭንቀላታቸው ላይ ከዳንቴል የተሰራ ኮፍያ ባደረጉና ከላይ እስከ ታች ጥቁር በለበሱ ወግ አጥባቂ ኦርቶዶክስ አይሁዶች ተሞልቷል፡፡ የሰልፉን ምክንያት ለማወቅ ብቸገርም ጉዳዩ የተቃውሞ ሰልፍ እንደሆነ ለመረዳት ጊዜ አልፈጀብኝም፡፡ ትእይንቱ ትኩረቴን ስለ ሳበው የትራፊኩን ጭንቅንቅ እንደምንም አልፌ ወደ ማደሪያዬ ከገባሁ በኋላ የጉዳዩን የጀርባ ታሪክ ለማወቅ የዜና ማሰራጫዎችን ማሰሴን ተያያዝኩት፡፡ ነገሩ እንዲህ ነው፡- ከስድስት ወራት በፊት ይስሐቅ ሻፒራ የሚባል አይሁዳዊ ፀሐፊ አንድ መጽሐፍ አሳትሟል፡፡ የዚህ አከራካሪ መጽሐፍ ርዕስ በዕብራይስጥ “ቶራህ አሜሌክ” ወይም የንጉሡ ሕግ የሚል ነው፡፡ በአይሁዳውያን ዘንድ እጅግ ከተከበሩና ዝነኛ ከሆኑ የሃይማኖት መምህራን መካከል አንዱ የሆኑት በዌስት ባንክ አካባቢ የሚገኙት የቂርያት አርባና የሔብሮን ዋና ራቢ (መምህር) ዶቪ ሊኦር በዚህ መጽሐፍ መግቢያ ላይ የድጋፍ ቃላቸውን አስፍረዋል፡፡ የመጽሐፉ አጠቃላይ ይዘትና የዶቪ ሊኦር አስተያየት ያሳሰባቸው ፖለቲከኞች መምህሩ ፖሊስ ጣቢያ ቀርበው ቃላቸውን እንዲሰጡ ሲጠየቁ ስድስት ወራት ተቆጥረዋል፡፡ ሆኖም መምህሩ እንደ ጲላጦስ "የጻፍኩትን ጽፌያለሁ!" በሚል ቃላቸውን ለመስጠት አሻፈረኝ ብለው ከርመዋል፡፡ በዚህ ቀን ግን ፖሊስ በትልቅ አክብሮት የሚያሽከረክሩትን መኪና አስገድዶ በማጀብ ወደ ፖሊስ ጣቢያ ቃላቸውን ተቀብሎ ሊመልሳቸው ወሰዳቸው። ሆኖም ወደ ፖሊስ ጣቢያ መወሰዳቸው ሲወራ ደጋፊዎቻቸው ፓርላማውንና ከአጠገቡ ያለውን የአገር ውስጥ ሚኒስቴር ቢሮ በተቃውሞ አጥለቀለቁ፡፡

በመጽሐፉ የሰፍረው በርካታ አጥባቂ አይሁዶች የሚጋሩት የሊኦር አስተያየት ባጭሩ ፡-

> “የአይሁድ ነፍስና የአሕዛብ ነፍስ በእግዚአብሔር ፊት እኩል ዋጋ የላቸውም፡፡ በሕግ መጽሐፍ “አትግደል” በሚል የተሰጠው ትዕዛዝ



For more books www.amharicchristianbooks.com

> አይሁድ አይሁዳዊውን እንዳይገድል እንጂ አሕዛብን አይመለከትም፡፡ አድገው አይሁዳውያንን ሊያጠቁ የሚችሉ የእስራኤል ጠላት የሆኑ የአሕዛብን ሕፃናት ልጆች መግደል አግባብ ነው፡፡ እግዚአብሔር ለአይሁዳውያን ነፍስ እንጂ ለአሕዛብ ነፍስ ርህራሄ የለውም፡፡ ባጠቃላይ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ አሕዛብን መግደል የከፋት ዝንባሌያቸውን ከመግታት ባሻገር የህሊና ፀፀት ወይም የስነ ምግባር ተጠያቂነት የሚያመጣ ጉዳይ አይደለም፡፡[111]

የሚል ነው፡፡ እንዲህ በሚያስቡ ሰዎች መሃል በሥጋ አሕዛብ ሆኖ መመላለስ ምን ዓይነት ስሜት እንደሚፈጥር መገመት አያስቸግርም፡፡ ይህ እስከ ዛሬ በጉልህ የሚንፀባረቅ የአይሁድ መምህራን አመለካከት ዛሬ የተነሳ ድንገተኛ አመለካከት ሳይሆን፣ ዘመናትን ያስቆጠረና ስር የሰደደ መሆኑን ባርክሌይ የተባለ ፀሐፊ አይሁዳውያን አሕዛብ ላይ ያላቸውን የሰላ ጥላቻና ንቀት በብዕሩ እንዲህ በማለት ገልጾታል፡፡

> “እግዚአብሔር አሕዛብን የፈጠረው የሲዖል እሳት እንዳይጠፋ ማገዶ ይሆኑ ዘንድ ነው . . . አንዲት አሕዛብ ሴት ልትወልድ ደርሳ ምጥ ተይዛ ስትጨነቅ ብታገኛት በሰላም እንድትገላገል ልትረዳት አይገባም፡፡ ይህን በማድረግህ አንድ አሕዛብ ወደ ዓለም እንዲመጣ ትተባበራለህና፡፡ . . . አንድ አይሁዳዊ ወጣት ከአሕዛብ ወገን የሆነች ልጃገረድ ቢያገባ ወይም አይሁዳዊት ልጃገረድ አሕዛብ የሆነ ወጣት ብታገባ ዘመዶቻቸው የቀብር ሥነ ሥርዓታቸውን በሌሉበት ይፈጽማሉ፡፡ ምክንያቱም እንዲህ ዓይነቱ ትስስር በአይሁዳውያኑ ዘንድ የሞት እኩያ ተደርጎ ይቆጠራልና፡፡”[112]

የአዲስ ኪዳን መጻሕፍትም አይሁዳውያን አሕዛብን እንደ ድንጋይ፣[113] እንደ ውሻ፣[114] እንደ እርኩስ እንስሳ[115] ይመለከቷቸው እንደነበር ይመሰክርልናል፡፡ ይህም እንደሰው በኃጢያታችን ምክንያት ከእግዚአብሔር መለየታችን ሳያንስ፣ ከአሕዛብ ዘር በመወለዳችንና ሥጋችንን ባለመገረዛችን ምክንያት የእግዚአብሔር ሕዝብ ለመሆን ከተመረጡት ከእስራኤላውያን መለየታችን ሞታችንን የሞት ሞት ያደርገዋል፡፡

---

[111] ቶራት ሃሜሌክ “የንጉሡ ሕግ” የተሰኘው መጽሐፍ አከራካሪ ከመሆኑ የተነሳ መጽሐፉን ማግኘት አስቸጋሪ ስለሆነ ደግሞም የእንግሊዘኛ ቅጂ ስለሌለው የመጽሐፉን ሙሉ መረጃ ለማስቀመጥ አልተቻለም፡፡

[112] Barclay, p. 125.

[113] ማቴ. 3፡9

[114] ማቴ. 15፡ 26 - 28

[115] ሐዋ. 10፡10-17



For more books www.amharicchristianbooks.com

ቀደም ሲል በምዕራፍ 2፡ 1 – 10 ከእግዚአብሔር በሞት መለየት የአሕዛብ ብቻ ሳይሆን በአዳም ዘር ሁሉ ላይ የመጣ የሰው ልጅ ሁሉ ሞት መሆኑን ጳውሎስ ራሱንና አይሁዳውያንን ሁሉ ጨምሮ “. . . እኛ ሁላችን . . . ” ቁ. 3 በማለት ገልፆልናል፡፡ አሁን ግን ኃጢአተኛ በመሆናችን እንደ ማንኛውም ሰው ከእግዚአብሔር መለየታችን ሳያንስ አሕዛብ በመሆናችን የእግዚአብሔር ሕዝብ ከሆኑት ከእስራኤላውያንና እነርሱ ብቻ ከተቸሩት ወደ እግዚአብሔር የመቅረብ፣ የዘላለምን ሕይወት ተስፋ የመጠበቅ እድሎች መጉደላችንን በተመረጡ ቃላት ይነግረናል፡፡ የመጀመሪያው መለየት የማይታይና መንፈሳዊ ነው፡፡ ይኸኛው ግን የሚታይና አካላዊ ነው፡፡ ከእግዚአብሔር ጋር በኃጢአት፣ ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር በሕግና በሥርዓት ተለይተናል፡፡ ታዲያ ይህንን ጣምራ መለየት ሁለት ሞት ወይም የሞት ሞት ከማለት በቀር ምን ልንለው እንችላለን?

ጳውሎስ መራቃችንን፣ መለየታችንን፣ እንግዶች መሆናችንንና ተስፋ ማጣታችንን ለመግለጽ የተጠቀመባቸው ቃላት የራቅነው ወደን፣ ሸሽተን ሳይሆን ዕድሉን ባለማግኘታችን መሆኑን በጉልህ የሚያሳዩ ናቸው፡፡ ምንም እንኳን በዘመናት ውስጥ በእቅድ የሚሠራው እግዚአብሔር ይህንን የፈቀደው ወደፊት በክርስቶስ ሊያደርግ ያለውን እያሰበ በዓላማ ቢሆንም አይሁዳውያኑ ግን ይህንን ፈጽመው የተረዱ አይመስልም፡፡ ምንም እንኳን እለት እለት የሚያነቧቸው ቅዱሳት መጽሐፍት እግዚአብሔር አብርሃምን የጠራው ለራሱ ብቻ ሳይሆን ክርስቶስን ከእርሱ ዘር በማምጣት የምድር ነገዶችን ሁሉ ሊባርክ[116] እንደሆነ ቢናገሩም፣ አይሁዳውያኑ ግን ሊያደምጧቸው የሚፈልጉ አይመስሉም፡፡ ስለዚህ አሕዛብን እንደ አናሳ ፍጥረት ማየታቸውን ሥራዬ ብለው ተያይዘውታል፡፡

ለመሆኑ በዚያን ዘመን አይሁዳውያኑ የነበሯቸው እኛ ግን በሥጋ አሕዛብ ከመሆናችን የተነሳ ያጣናቸው መንፈሳዊ በረከቶች ምን ምን ነበሩ? ሐዋርያው በመቀጠል እንዲህ ያስቀምጣቸዋል፡፡ *“ከእስራኤል መንግስት ርቃችሁ . . . ”* የእስራኤል መንግሥት የሚለውን በርካታ የእንግሊዝኛ መፍሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች “የእስራኤል የጋራ ብልጽግና” ብለው ይተረጉሙታል፡፡ ከዚህ መንግስት መራቅ እንደ ጉዳት የተቆጠረው በዘመኑ በሌሎች አገሮች ታላላቅ መንግሥታት ስላልነበሩ ሳይሆን የእስራኤል መንግሥት በአለም ላይ እውነተኛው አምላክ በብቸኝነት የሚመለክበት በእግዚአብሔር ምድር፣ በእግዚአብሔር ሕግ፣ በእግዚአብሔር ሕዝብ የተዋቀረ ሊመጣ ላለው ለእግዚአብሔር መንግሥት ተምሳሌት ሆኖ የተመሰረተ መንግሥት በመሆኑ ነው፡፡

---

[116] ዘፍ. 12፡3; ኢሳ. 42፡1; 6 49፡6



For more books www.amharicchristianbooks.com

*“ለተስፋው ቃል ኪዳን እንግዶች ሆናችሁ በዚህ ዓለም ተስፋን አጥታችሁ . . . ፡፡”* ይህ የተስፋ ቃል እግዚአብሔር አስቀድሞ ከአብርሃም በኋላም ከዳዊት ጋር የገባው ቀጥሎም በነቢያት አፍና በቅዱሳት መጻሕፍት ያፀናው ስለ ክርስቶስ፤ በእርሱም በኩል ስለሚመጣው ሕይወት፣ ስለ ኃጢአት ሥርየት፣ ስለ ጽድቅ፣ ስለ ትንሳኤና ስለሚመጣው ክብር የተነገረ ክቡር ተስፋ ነው፡፡ ጳውሎስ ቀደም ሲል በ1፡11 ላይ አይሁዳውያን ተስፋውን በመስማትና በመጠበቅ አሕዛብን እንደሚቀድሙ በገለፀው መሠረት፣ አሕዛብ ወንጌል እስከ ታወጀበት ዘመን ድረስ ይህ ተስፋ ይኑር አይኑር አንዳች የማያውቁ ባይተዋርና እንግዶች መሆናቸውን ያሳያል፡፡

አይሁዳውያን ጽድቅን የሥጋ ትንሳኤንና የዘላለም ሕይወትን በተስፋ ይጠብቁ ነበር፡፡ በዚያን ዘመን የነበሩ አሕዛብ ግን በተለይ ግሪካውያንና ሮማውያን በፈላስፎቻቸው አማካይነት የሚንፀባረቀውና በሕዝቡ ውስጥ የሰረፀው አመለካከት ከዚህ ተስፋ እጅግ የራቀ ነበር፡፡ የፈላስፎቹ ትምህርት "ቁሳዊው ዓለም ክፉና አዳፋ ነው፡፡ ፈፅሞም ሊነፃና ሊቀደስ አይችልም፡፡ ሥጋችንም የዚህ ቁሳዊ አካል ክፍል እንደመሆኑ መጠን በክፋት የታሰረና ከክፉ ተግባሩ ሊገታ የማይችል ነው፡፡ ቅዱስ የሆነው በሥጋችን ውስጥ ያለው መንፈሳችን ብቻ ነው፡፡ አምላክ ለዚህ ለመንፈሳችን ብቻ እንጂ ለሥጋችን ግድ የለውም፡፡ ሥጋችን የፈለገውን ቢፈፅም ምኞቱን ለማርካት ነውና ከቁጥር አይፅፈውም፡፡ ከዚህ እስራት ነፃ የምንወጣው የመንፈሳችን እስር ቤት ከሆነው ከሥጋችን በሞት ስንፈታ ብቻ ነው" በማለት ሞትን እንደ ነፃ አውጪ ይጠባበቁ ነበር እንጂ በዚህ ዓለም አንዳች ተስፋ አልነበራቸውም፡፡ ይህንንም የሚያረጋግጥልን የዚህ ፍልስፍና አባት እንደሆነ የሚነገርለት ሶቅራጥስ ተከታዮቹ በተሰበሰቡበት የሞትን ነፃ አውጭነት ከሰበከ በኋላ ሁሉም እያዩት በብልቃጥ የያዘውን መርዝ በመጨለጥ እስከ ወዲያኛው ማሸለቡ ነው፡፡ ይህንን የእውነተኛ ተስፋ እጦት ክንውን እ.ኤ.አ የ 1787 ቱ ታዋቂ ሰዓሊ ጃክ ሉዊስ ዴቪድ በሸራ ላይ በዘይት ቀለም ፍንትው አድርጎ ስሎታል፡፡[117]

ወንጌል ለዓለም ሁሉ እስከታወጀበት ጊዜ ድረስ ከእስራኤላውያን ውጭ፣ ለተቀረው ዓለም እንግዳ የነበረው ይህ ተስፋ በመሢሁ ያመኑ የሰው ልጆች ሁሉ በአንድነት እንዲወርሱት[118] የተዘጋጀ ባለ ብዙ በረከት ታላቅ ተስፋ መሆኑን[119] ጳውሎስ በዚህ መልእክት ውስጥ በተለያዩ ክፍሎች በዝርዝር ጽፏል፡፡

*“ከእግዚአብሔር ተለይታችሁ . . . ”* ጳውሎስ በሥጋ አሕዛብ ለነበሩ ተደራሲያኑ

[117] www.bc.edu/bc_org/avp/cas/his/coreart/art/neocl_dav_soc.html
[118] ኤፌ. 3፡5
[119] ኤፌ. 4፡4



For more books www.amharicchristianbooks.com

ክርስቲያን ከመሆናቸው በፊት ስለ ነበሩበት ሁኔታ ከእግዚአብሔር ተለይታችሁ ትኖሩ ነበር ለማለት የደፈረው "በዚያን ዘመን" የሚያመልኳቸው፣ የሚከተሏቸው፣ የሚያገለግሏቸው አማልክት ስላልነበሯቸው አይደለም፡፡ ነገር ግን "በዚያን ዘመን" የሁሉ ፈጣሪና ባለቤት የሆነው እውነተኛ አምላክ የሚገኘው በእስራኤል ዘንድ ብቻ መሆኑንና አሕዛብ በሥፍራ ሁሉ የሚያመልኳቸው ሰው ሰራሽ "አማልክት" እንደነበሩ ለማስታወስ የተጠቀመበት ቃል ነው፡፡[120]

*"ያለ ክርስቶስ ነበራችሁ"*[121] ሐዋርያው የአይሁዳውያንን ጥቅምና አሕዛብ የጎደሉበትን በረከት የሚዘረዝረው ስለ አሁን ሳይሆን "በዚያን ዘመን" በሚል ከክርስቶስ በሥጋ መምጣት በፊት የነበረውን ዘመን ነው፡፡ ታዲያ ክርስቶስ የመጣው "በዚያን ዘመን" ሳይሆን በዚህ ዘመን ከሆነና ይህን በሥጋ የመጣውን ክርስቶስን አምነው አሕዛብ የክርስቶስን ማኅበረሰብ ከተቀላቀሉ እንዴት "ያለ ክርስቶስ" ሊሆኑ ይችላሉ? "በዚያን ዘመን" አይሁዳውያንስ "ያለ ክርስቶስ" አልነበሩምን? የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል፡፡

ጳውሎስ በ፲፡፲፩ ላይ እስራኤላውያን በሥጋ ከመምጣቱም አስቀድሞ "ክርስቶስ" በተስፋ ቃል እንደነበራቸው ነግሮናል፡፡ ዘመኑ ሲደርስ ያ ቃል ሥጋ ሆነ፡፡[122] "በዚያን ዘመን" በእስራኤላውያን ኑሮና አምልኮ ውስጥ ሲንፀባረቅ የምናየው ነገር ሁሉ የክርስቶስ ጥላና ምሳሌ ነበር፡፡[123] ክርስቶስ በሥጋ በእስራኤል አባቶች ወገብ ውስጥ ነበርና፡፡[124] ስለዚህም ክብራቸውና ድላቸው ብቻ ሳይሆን መከራቸውም እንኳ የክርስቶስ መከራ እንደነበር የአዲስ ኪዳን መጽሐፍት ይመሰክራሉ፡፡[125] ኢየሱስ ክርስቶስ ሲባል ስም ከነአባት የሚመስላቸው አንዳንድ አማኞች እንደሚኖሩ ጥያቄ የለውም፡፡ ይህም ክርስቶስ የሚለው ስም ኢየሱስ እንዲጠራበት የወጣለት ስም ሳይሆን ማንነቱንና ሥራውን የሚያሳይ ከጥንት ዘመን ጀምሮ የነበረ ማዕረጉ እንደሆነ ያሳየናል፡፡ እኛም የዳንነው የናዝሬቱ ኢየሱስ እርሱ ሲጠበቅ የኖረው ክርስቶስ እንደሆነ በማመናችን ነው፡፡ ይህም እስራኤላውያን ከነበራቸው "ክርስቶስ" በዚያን ዘመን አሕዛብ ጎድለው እንደነበር በጉልህ ያሳየናል፡፡

ባጠቃላይ ከላይ የተዘረዘሩትን ፍሬ አሳቦች ስንመለከት አሕዛብ ከአዳም ዘር

---

[120] ፲ቆሮ. 8፡5-6; ገላ. 4፡8; ፲ተሰ. 4፡5

[121] ይህ ሐረግ በግሪኩ መጽሐፍ ቅዱስ ከዝርዝሮቹ መጀመሪያ የሚመጣ ቢሆንም አቀማመጡ የሚያመጣው ለውጥ ስለሌለ የአማርኛውን መጽሐፍ ቅዱስ ቅደም ተከተል ተጠቅሜያለሁ፡፡

[122] ዮሐ. 1፡1; 14

[123] ቆላ. 2፡16; 17

[124] ሮሜ 4፡5

[125] ሮሜ 9፡4-5; ዕብ. ፲፡ 26



For more books www.amharicchristianbooks.com

በመወለዳቸውና ኃጢአትን በመውረሳቸው ከእግዚአብሔር ከመለየታቸው ባሻገር በሥጋ አሕዛብ በመሆናቸው ምክንያት “በዚያን ዘመን” እስራኤላውያኑ ይካፈሉት ከነበረው በረከት መጉደላቸው የሞት ሞት እንደሆነ መመልከት እንችላለን፡፡

## ሰላማችን ኢየሱስ

ጳውሎስ በእስራኤልና በአሕዛብ መካከል “በዚያን ዘመን” የነበረውን ልዩነት በደማቅ ቀለም ካሰመረ በኋላ ወዲያው በመቀጠል የምሥራቹን ያበስረናል፡፡ የምሥራቹም ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ መምጣቱና በእግዚአብሔርና በሰው መካከል እንዲሁም በእስራኤልና በአሕዛብ መካከል ያለውን ጥል በሞቱ በማስወገድ የማያዳግም እርቅ ማምጣቱ ነው፡፡ምንም እንኳ  በሌሎች ስፍራዎች ኢየሱስ ክርስቶስ በሰላም ላይ ስልጣን ያለው የሰላም አለቃ፣[126] ሰላምን የሚሰጥ የሰላም ባለቤት እንደሆነ[127] ቢፃፍም፣ ጳውሎስ ግን በዚህ ስፍራ ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ በሥጋ የተገለጠ “ሰላም” መሆኑን ያሳየናል፡፡ ሰላምነቱም ለአይሁድ ብቻ ሳይሆን ሥጋ ለለበሰ ሁሉ ነው፡፡ *“እርሱ ሰላማችን ነውና፡፡”* (ቁ.14) ለአይሁድም፣ ለአሕዛብም ይህ “ሰላም” የሆነ ጌታ፣ የሰላምን ሥራ ሰርቶ “ሰላምን” የምሥራች ብሎ ሰበከ፡፡ (ቁ.17)

“ሰላም” የሚለው ቃል በዕብራውያን ዘንድ “ሻሎም” በመባል የሚታወቅ ቃል ነው፡፡ ትርጉሙም ከጦርነት ከማረፍና በነፃነት ከመኖር ባሻገር፣ ዘላቂ ድነትን፣ ሁለንተናዊ ጤንነትን፣ ውስጣዊና ውጫዊ ብልፅግናን የሚያመለክት ሲሆን፣ በዘመን ፍፃሜ እግዚአብሔር ሁሉን ጠቅልሎና አዲስ አድርጎ ሲነግስ የሚሰፍነውን ፍፁም ሰላም የሚያሳይ እንደሆነ የቋንቋው ሊቃውንት ያስረዳሉ፡፡[128] በዚህም ክፍል በክርስቶስ ኢየሱስ የተፈጠረው ሰላም አይሁዳውያኑ በሚጠብቁት የመጨረሻው ዘመን ተስፋ አሕዛብ ከእስራኤል ሕዝብ ጋር በጽዮን ተራራ በአንድነት እግዚአብሔርን እንደሚያመልኩ በነቢያት መጽሐፍት ከተገለፀው ጋር ተዛማጅ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡[129] ከዚህም በመነሳት እግዚአብሔር በክርስቶስ የሰጠን የግንኙነት ሰላም ብቻ ሳይሆን ለዘላለም የሚኖር ሰብዕና ያለው ሰላም መሆኑን መመልከት እንችላለን፡፡ ይህም ሰላም በማንነቱ ብቻ ሳይሆን በመስቀል ላይ በሠራው ሥራ ፈፅሞ ልንቀርብ ወደማንችለው እንዳቀረበን “አሁን ግን እናንተ

---

[126] ኢሳ. 9፡6
[127] ዮሐ. 14፡27
[128] World Bible Commentary, Ephesians p. 140
[129] ኢሳ. 2፡2-4; ሚክ. 4፡1-4



For more books www.amharicchristianbooks.com

በፊት ርቃችሁ የነበራችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ ሆናችሁ በክርስቶስ ደም ቀርባችኋል፡፡" (ቁ.13) በማለት ይገልፃል፡፡

ከቁጥር 14 አንስቶ እስከ 19 የተዘረዘሩትን ክርስቶስ በአይሁድና በእስራኤል፣ በሰውና በእግዚአብሔር፣ መካከል ያመጣውን ሰላም የሚገልፁ ክፍሎች በአንድ ወጥ ትእይንት በጉልህ ልንመለከታቸው እንችላለን፡፡ ይህም ትእይንት ቀድሞ የእስራኤል የአምልኮ ማዕከል በሆነው በመቅደሱ ዙሪያ የሚያጠነጥን ነው፡፡ ምንም እንኳ ጳውሎስ የሚጽፍላቸው አሕዛብ በኢየሩሳሌም ያለውን መቅደስ ላያውቁ እንደሚችሉ ከመገመቱ የተነሳ መቅደሱን በተመለከተ ቃል በቃል ያነሳው ነገር ባይኖርም ይህንን ክፍል በሚጽፍበት ጊዜ በሕሊናው የነበረው ስዕል የመቅደሱ ሥርዓት ስለ መሆኑ እርግጠኛ መሆን እንችላለን፡፡ ጌታ ኢየሱስ በምድር በተመላለሰባቸው አመታት በኢየሩሳሌም ከተማ በሞሪያ ተራራ ላይ በግርማ ሞገስ ተሰይሞ የነበረውና በታላቁ ሄሮድስ እንደተገነባ የሚታመነው የኢየሩሣሌም ቤተመቅደስ ሁለት አደባባዮች እንደነበሩት ይነገራል፡፡ እነዚህም አደባባዮች አንደኛው በመቅደሱ ፊት ለፊት የሚገኘውና ውስጠኛ አደባባይ ተብሎ የሚጠራው የአይሁዳውያን አደባባይ ሲሆን ሌላኛው ከረዥም ግንብ በስተጀርባ የሚገኘው የአሕዛብ አደባባይ ነው፡፡ እነዚህ ሁለት አደባባዮች ከፍ ብሎ በተገነባ የግንብ አጥር የተከፈሉ ሲሆን በምንም ዓይነት መተያየትም ሆነ መደራረስ እንዳይችሉ ተደርጎ የታጠረ ነው፡፡[130]

በዚህ የግንብ አጥር ውጫዊ ክፍል ላይ ማለትም የእስራኤልን አምላክ ለማምለክ ከተለያየ የዓለም ክፍል የመጡ አሕዛብ በሚገኙበት አቅጣጫ በግሪክና በላቲን ቋንቋ ተጽፎ የተሰቀለ የማስጠንቀቂያ መልዕክት ነበረ፡፡ መልዕክቱ በዕብራይስጥ ያልተጻፈበት ምክንያት እንዲነበብ የተፈለገው ከእስራኤል ውጭ ባሉት አሕዛብ በመሆኑ ነው፡፡ ጽሁፉም "ይህን አጥር አልፎ በውስጠኛው ክፍል የሚገኝ ማንኛውም አሕዛብ በሞት ይቀጣል፡፡" ይላል፡፡ ይህ ጽሑፍ በ1987 በአንድ ፈረንሳዊ አርኪዎሎጂስት በቁፋሮ እንደተገኘና በአሁኑ ሰዓት በቱርክ የንግድ ከተማ በሆነችው በኢስታንቡል ባለ ቤተ መዘክር ውስጥ እንደሚገኝ መጽሐፍት ይመሰክራሉ፡፡[131] በግድግዳው ላይ የተፃፈውን እስከ አንድ ሜትር የሚጠጋ ርዝመት ያለውን ይህን ማስጠንቀቂያ መተላለፍ በአይሁዳውያኑ ዘንድ በቀላሉ የሚታለፍ ጉዳይ እንዳልነበር የሚያረጋግጥልን ሉቃስ በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ ያሰፈረልን የራሱ የጳውሎስ ገጠመኝ ነው፡፡ ቀደም ሲል ኢየሩሳሌም ከተማ

[130] Josephus, Ant. 15.11.5; J.W.5.5.2
[131] J.A Robinson, 59-60, 158



For more books www.amharicchristianbooks.com

ጳውሎስን ከኤፌሶኑ ጥሮፊሞስ ጋር ያዩት አይሁዳውያን በኋላ በመቅደሱ ውስጥና አደባባይ መስዋዕት ሲያቀርብ ሲያዩት አሕዛብ የሆነውን ጥሮፊሞስን ይዞ የገባ መስሏቸው ያስነሱት ሁከት ጳውሎስ ይህን መልዕክት ሲጽፍ ለሚገኝበት እስር ዋንኛ ምክንያት ነበር፡፡[132] ጳውሎስም “. . . በመካከል ያለው የጥል ግድግዳ . . . ” እያለ የሚጠራው ይህንኑ አጥር ነው፡፡ ሆኖም ይህ አጥር እንዲሁ ግዑዝ አጥር ብቻ አልነበረም፤ የሚወክለው አካል ነበረው፡፡ ያም አካል በመቀጠል “በአዋጅ የተነገሩት የትዕዛዛት ሕግ” እያለ የሚጠቅሰው የሲና ሕግ ነው፡፡ በእርግጥ ሕጉ አጥር ነበር፡፡ እስራኤልን ከተቀረው ዓለም የሚለይ ጽኑ አጥር፡፡ በጊዜው አጥሩ ያስፈለገበት ዐብይ ምክንያት ክርስቶስ በሥጋ የሚመጣበትን ዘር ለይቶ በንጽህና ለመጠበቅ ነበር፡፡ አሁን ግን ክርስቶስ በሥጋ መጥቷል የአጥሩም አስፈላጊነት አክትሟል፡፡[133] ይህንንም ክርስቶስ ራሱ በመስቀሉ ሥራ ሲያፈርሰው እናያለን፡፡ ጌታ ኢየሱስ በመስቀል ሞቱ ያፈረሰው መንፈሳዊውን እንጂ ግዑዙን አጥር አልነበረም፡፡ ቢሆንም መንፈሳዊው ገጽታ ከፈረሰ ከ40 ዓመታት በኋላ የሮማ ሠራዊት ግዑዙን አጥር አፍርሶታል፡፡

ይህ ክፍል ክርስቶስ በሥጋው ሞት *"በአዋጅ የተነገሩትን የትዕዛዛትን ሕግ"* እንደሻረ ይናገራል፡፡ ከዚህ መልዕክት ጋር አብሮ እንደተፃፈ የሚታመነው የቆላስያስ መልዕክትም በተመሳሳይ መልኩ *“በእኛ ላይ የነበረውን የሚቃወመንንም በትዕዛዛት የተፃፈውን የዕዳ ጽሕፈት ደመሰሰው እርሱንም በመስቀል ጠርቆ ከመንገድ አስወግዶታል . . . ፡፡ ”* (ቆላ. 2፡14) በማለት ይህንን ሃሳብ ያፀናልናል፡፡ ታዲያ ሕግ ተሽሯል ማለት ነው? እንዲህ ከሆነ ጌታ ኢየሱስ በወንጌል ውስጥ *“እኔ ሕግንና ነቢያትን ለመሻር የመጣሁ አይምሰላችሁ ልፈጽም እንጂ ለመሻር አልመጣሁም፡፡”* (ማቴ. 5፡17) ያለው ለምንድነው?

ለእስራኤል በሲና የተሰጠው ሕግ ሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ነበሩት፡፡ አንደኛው የግብረ ገብ ሕግ ሲሆን ሁለተኛው የመንፃት ሕግ ነው፡፡ ጌታ ኢየሱስ በሞቱ በመፈፀም የሻረውና ያስወገደው በሥጋ ሥርዓት የተሞላውን የመስዋዕትና የመንፃት ሕግ እንጂ የግብረ ገብን ሕግ አይደለም፡፡ ይህንን ሕግ በተመለከተ ሕጉ ከሚጠይቀው በላይ መፈፀም የምንችልበትን የሕይወት መንፈስ ሕግ ሰጥቶናል እንጂ ፈጽሞ አልሻረውም፡፡[134]

አይሁድንና አሕዛብን ለይቶ የነበረው የሥጋ ሥርዓት ሕግ በክርስቶስ ሞት

[132] ሐዋ. 21፡27-32
[133] ገላ. 3፡19-25
[134] ሮሜ 8፡2-3



For more books www.amharicchristianbooks.com

ፈርሷል፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ይህን የሚለይ አጥር በማፍረስ አይሁድንና አሕዛብን አዋህዷል፡፡ ሆኖም የተዋሃዱት በወንጌል ያመኑ አይሁድና አሕዛብ እንጂ የአይሁድ ሕዝብ ሁሉና አሕዛብ ሁሉ አይደሉም፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ በሞቱና በትንሳኤው ሁለቱን ያዋሃደው አይሁድም ያልሆነ፣ አሕዛብም ያልሆነ፤ ነገር ግን ከአይሁድም የሆነ ከአሕዛብም የሆነ *"አንድን አዲስን ሰው በራሱ በመፍጠር ሰላምን ያደርግ ዘንድ ነው፡፡"* (ቁ.15)

በመቅደሱ ስፍራ የምናየው፣ በአጥሩ ተምሳሌትነት የተገለጠው፣ የአይሁድና የአሕዛብ ልዩነት፣ የሁለቱ ልዩነት ብቻ አልነበረም፡፡ አይሁዳውያኑ ባሉበት በውስጠኛው አደባባይ ፊት ለፊት ከመሰዊያው ባሻገር ያለው መቅደስ ወደ ውስጡ ሲዘለቅ ሁለት ክፍሎች ነበሩት፡፡ የመጀመሪያው ካህናት ዕለት ዕለት እየገቡ የሚያገለግሉበት ቅድስት በመባል የሚጠራው ክፍል ሲሆን ሁለተኛው ሊቀ ካህኑ ብቻ በዓመት አንዴ ለራሱና ለሕዝቡ የሚሆን የኃጢአት ሥርየት ደም ይዞ፣ በብዙ ፍርሃትና ጥንቃቄ የሚገባበት ቅድስተ ቅዱሳን የሚባለው የውስጠኛው ክፍል ነው፡፡[135] ይህንንም ክፍል ከሌላው ክፍል የሚለይ ከሰማያዊ፣ ከሐምራዊና ከቀይ ግምጃ የተሠራና[136] ከ42 ጫማ[137] በላይ የሚረዝም መጋረጃ ነበረው፡፡ ይህም መጋረጃ በውጭ ያሉትን አይሁድና አሕዛብን ጨምሮ ሰውን ሁሉ ከእግዚአብሔር የሚለይ የጥል መገለጫ ተምሳሌት ነው፡፡

በመጋረጃዎቹም ላይ በልዩ ጥበብ የተጠለፈ የኪሩቤል ምስል ነበረበት፡፡ ይህም ያንን መጋረጃ የሚተላለፍ ሁሉ በሞት እንደሚቀጣ የሚያሳይ ሲሆን የአዳም ዘር የሆነ ሰው ሁሉ በኃጢያት ምክንያት የሕይወት ምንጭ ወደሆነው ወደ እግዚአብሔር እንዳይደርስ መባረሩንና ከውጭ መዘጋቱን ያሳያል፡፡[138] በዚህም መቅደሱ ጥልን በሚያንፀባርቁ የልዩነት መገለጫዎች እንደተሞላ መመልከት እንችላለን፡፡ ሰውን ከሰው የሚለየው አጥር በውጭ፣ ሰውን ከእግዚአብሔር የሚለየው መጋረጃ በውስጥ፡፡ አይሁድና አሕዛብ በሕግ አጥር፣ እግዚአብሔርና ሰው በሥጋ መጋረጃ[139] እንደተለያዩ እንመለከታለን፡፡ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ግን በመስቀሉ ሥራ የጥሉን ግድግዳ በማፍረስና መጋረጃውን በመቅደድ ሁለቱንም ጥሎች አስወገደ፡፡

---

[135] ዕብ. 9፡1-8
[136] ዘፀ. 26፡1-6
[137] 42 ጫማ ርዝመት የነበረው የሙሴ መገናኛ ድንኳን መጋረጃ ድንኳኑ ወደ ግዙፍ መቅደስነት ሲያድግ ርዝመቱ እንደሚጨምር ይገመታል፡፡
[138] ዘፍ. 3፡22-24
[139] ዕብ. 10፡ 19-20



For more books www.amharicchristianbooks.com

አስቀድሞ ያስወገደው መጋረጃውን ሳይሆን የጥል ግድግዳውን ነው፡፡ ከግድግዳው አስቀድሞ መጋረጃውን አስወግዶ ቢሆን ኖሮ የአይሁድና የአሕዛብ መዳን ልዩ ልዩ በሆነ ነበር፡፡ እነርሱ ከአሕዛብ ቀድመው ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ይገቡ ነበርና፣ መዳናቸውም ከአሕዛብ የተለየ ይሆን ነበር፡፡ እርሱ ግን ያደረገው እንዲህ ነው፤ ቀድሞ የጥሉን ግድግዳ በማፍረስ ሁለቱን አዋሃደ፣ ሁለቱን ካስታረቀና አንድ ካደረገ በኋላ ከአይሁድና ከአሕዛብ የሆነ፣ ነገር ግን አይሁድም አሕዛብም ያልሆነ አንድ አዲስ ሰው በትንሳኤው ፈጥሮ ሁለቱንም በአንድ አካል ከአብ ጋር ለማስታረቅ ጉዞውን ወደ ቅድስተ ቅዱሳን አቀና፡፡ የሕጉን አጥር በማፍረስና ሁለቱንም በአንድ አካል በማጣመር የጀመረውን ሥራ በመቅደሱ መግቢያ በር ላይ እንዳለው የመሠዊያ ሥርዓት ራሱን የኃጢአት መሥዋዕት አድርጎ በማቅረብ ደሙ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ሲገባ ሥጋው ግን ከሰፈር ውጪ መከራን ተቀበለ፡፡[140] በፍፃሜውም የእግዚአብሔርን የጽድቅ ጥማት በአንድ መስዋዕት በማርካት እግዚአብሔርንና ሰውን የሚለየውን መጋረጃ በሞቱ ቀዶ በአዲሱ ማንነት ሁለቱንም ወደ ቅድስተ ቅዱሳን አስገባ፡፡[141] ይህንን ነው ጳውሎስ *"በእርሱ ሥራ በአንድ መንፈስ ወደ አብ መግባት አለንና"* (ቁ.18) የሚለው፡፡

መግባት የሚለው ቃል የእስራኤል ልጆች ርስታቸው ወደ ሆነችው ወደተስፋይቱ ምድር ከመግባታቸውና ሊቀ ካህናቱ ሕዝቡን በመወከል በአመት አንዴ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ከመግባቱ ጋር አያይዘው የሚጠቀሙበት የተለመደ ቃል ነው፡፡ እኛም በክርስቶስ ሥራ፣ በእርሱም በማመን በተሰጠን በመንፈስ ቅዱስ የዘላለም ርስታችንና ማደሪያችን ወደ ሆነው ወደ አብ መግባት ሆነልን፡፡

የጥሉ ግድግዳ ከመፍረሱ አስቀድሞ አሕዛብ ከአጥር ውጭ ሳሉ ራሳቸውን ውጭ፣ እስራኤላውያኑን ደግሞ ውስጥ እንዳሉ ለማሰብ ይገደዱ ነበር፡፡ አይሁዳውያንም በተሰጣቸው ልዩ መብት በመመካት፣ ራሳቸውን ውስጥ፣ አሕዛብን ደግሞ ውጭ አድርገው ያስቡ ነበር፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ ግን በሰላ ብዕሩ *"መጥቶም ርቃችሁ ለነበራችሁ ለእናንተ (አሕዛብ) ሰላምን፣ ቀርበውም ለነበሩትም (አይሁድ) ሰላምን የምሥራች ብሎ ሰበከ . . . "* ቁ. 17 (አፅንኦት ከራሴ) በማለት "ውስጥ ነን" ለሚሉት አይሁዳውያን "ቀርባችሁ ነበር እንጂ ውስጥ አልነበራችሁም፣ መቅረብና መግባት ይለያያሉ፣ በአይሁድነታችሁ ብትቀርቡም መግባት የምትችሉት ግን በክርስቶስ ኢየሱስ ብቻ ነው" በማለት ከመጋረጃው ውጭ እንደነበሩ ያስታውሳቸዋል፡፡

[140] ዘፀ. 29፡14; ዘሌ. 4፡12

[141] ማቴ. 27፡50፡51



For more books www.amharicchristianbooks.com

ሌላው ዋና ጉዳይ፣ እስራኤላውያን የገቡበትን የከነዓን ርስት ወይም ሊቀ ካህናቱ በዓመት አንዴ የሚገባበትን ቅድስተ ቅዱሳን ስናስብ የሚመጣልን ግዑዝ ቦታ ነው፡፡ በዚህ ሥፍራ ግን በክርስቶስ ኢየሱስ ሥራ በአንዱ በመንፈስ ቅዱስ የገባነው ወደ ግዑዝ ሥፍራ ሳይሆን ወደ አብ እንደሆነ እናነባለን፡፡ የገባነውም ለዘለዓለም በሕይወት ልንኖር ነው፡፡ ይህም እግዚአብሔር ለዘላለም ኗሪ ብቻ ሳይሆን፣ ወደ እርሱ የገቡትን ለዘላለም የሚያኖር የሕይወት መንፈስ መሆኑን በጉልህ ያሳያል፡፡ እንዴት ወደ አብ ገባን? ብለን ስንጠይቅ የምናገኘው መልስ የናዝሬቱ ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ፣ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ስናምንና የሠራልንን ሥራ ስንቀበል መንፈስ ቅዱስ ወደ ውስጣችን ገባ፡፡ መንፈስ ቅዱስ ወደ ውስጣችን የገባው ከወጣበት ከምንጩ ከአብ ሳይለይ ስለሆነ፣ እርሱ እኛ ውስጥ ሲገባ እኛም በአብ ውስጥ ገባን፡፡ ይህም፣ ጳውሎስ በቈላስይስ መልእክት ውስጥ ከፃፈው አሳብ ጋር ይስማማል፡፡

> *“. . . ሞታችኋልና ሕይወታችሁም በእግዚአብሔር ከክርስቶስ ጋር ተሰውሮአል፡፡” ቆላ.3፡3*

ከፍ ብዬ እንደገለጽኩት የገባነው ቅድስተ ቅዱሳን ወደሚባል ሥፍራ ሳይሆን ወደ አብ ነው፡፡ እርሱም የሚገባበትና የሚወረስ የሕይወት ርስት ነው፡፡ በእርሱ ዘንድ ሞት የለም፣ መጥፋት የለም፣ ማርጀት የለም፣ መለወጥ የለም፡፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ሥራ፣ መንፈስ ቅዱስንም፣ በመካፈል የገባንበት አብ ቅድስተ ቅዱሳናችን ነው፡፡ የሰማያዊው ምሳሌ የሆነው ምድራዊ ቅዱስተ ቅዱሳን በውስጡ የተለያዩ ነገሮች ነበሩ፣ እነዚህም ነገሮች እርሱ ሕይወትን የሚሰጥ መንፈስ መሆኑንና ወደ እርሱ የገቡትን ያለ መለወጥ ለዘላለም በሕይወት የሚያኖር መሆኑን ለማሳየት ሆን ብለው የተቀመጡ አስገራሚ ተምሳሌቶች ናቸው፡፡ ከብዙዎቹም መካከል የሁለቱን ብቻ ብናነሳ በውስጣቸው ያዘሉትን አስገራሚ መልዕክት ማየት እንችላለን፡፡ እነዚህንም ነገሮች የዕብራውያን መልዕክት ጸሐፊ እንዲህ በማለት ይገልፃቸዋል፡፡

> *“. . . ከሁለተኛውም መጋረጃ ወዲያ ቅድስተ ቅዱሳን የምትባለው ድንኳን ነበረች፡፡ በዚያም ውስጥ . . . መና ያለባት የወርቅ መሶብና የበቀለች የአሮን በትር ነበሩ፡፡” ዕብ. 9፡3-4*

የእስራኤል ልጆች በምድረ በዳ ሳሉ ከሚወርደው መና አንድ ጎሞር (1 ሊትር) ወስዶ በቅድስተ ቅዱሳን እንዲያስቀምጥ እግዚአብሔር ለሙሴ አዞት ነበር፡፡[142] የመናውን ባሕሪ ስንመለከት ማለዳ ወርዶ ፀሐይ ሲወጣ ይቀልጥ ነበር፡፡ በዕለቱ ካልተበላ በቀር ሲያድር ይሸትና ይገማ ነበር፡፡ ነገር ግን ይህ ቀልጦ የሚጠፋና

[142] ዘፀ. 16፡32-33



For more books www.amharicchristianbooks.com

ሲያድር የሚሸት መና በቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ ሲቀመጥ ለዘመናት አልቀለጠም፣ ደግሞም አልሸተተም፡፡ ይህም የመናውን ተፈጥሮ ሳይሆን የገባበትን ሥፍራ ምንነት የሚያሳይ ነው፡፡ አስቀድማ ደረቅ የነበረችዋንና በኋላም የለመለመችውን የአሮንንም በትር ስንመለከት፣ እንደ ተፈጥሮዋ ከሆነ ተመልሳ መድረቅና መጠውለግ ነበረባት፡፡ ሆኖም የገባችበት ሕይወት የሚያለመልምና የሚያኖር ነውና ቁጥሩ ለማይታወቅ ረዥም ዘመን እንደ ለመለመች ኖረች፡፡ እኛም በፍጥረታችን የሞት፣ የማርጀት፣ የመበስበስ ብሎም የመጥፋት ባሕሪ ያለን ብንሆንም፣ ወደ አብ ስንገባ ተፈጥሮአችን ተለወጠ፡፡ አሁን የገባነው በመንፈስ ስለሆነ መንፈሳችን ሕያው ሆኖአል፣ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም በሚመጣበት በቤዛ ቀን ግን ሥጋችንም ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ስለሚገባ ውርደት፣ ማርጀት፣ ሞት፣ መበስበስ ተሽረው ሁለንተናችን ለዘላለም ሕያው ሆኖ ይኖራል፡፡

የሰማያዊው ምሳሌ ስለ ሆነው ስለ ምድራዊው ቅድስተ ቅዱሳን ስናስብ በኅሊናችን የሚሳለው ስፋቱ፣ ርዝመቱና ከፍታው ሁሉ አራት ሜትር በአራት ሜትር የሆነ አንድ ጠባብ ክፍል ነው፡፡ አሁን የገባንበት መለኮት የሆነ ሰማያዊውና እውነተኛው መቅደስ ግን የተለየ ባሕሪ አለው፡፡ ከውጭ ሲታይ መውጫ የሌለው አንድ ጠባብ ክፍል ይመስላል፡፡ ሲገባበት ግን ወደ አንድ አገር እንደሚያስገባ የድንበር ከተማ መተላለፊያ ወሰን፣ ማለቂያ ወደ ሌለው ርስት የሚያደርስ የሁለት ዓለማት ወሰን ነው፡፡ በሥጋ ሕይወትና በመንፈስ ሕይወት፣ በሰውና በእግዚአብሔር፣ በመንፈሳዊውና በግዑዙ ዓለም መካከል የሚለይ ድንበር ነው፡፡ ይህንንም የምንረዳው ሐዋርያው "ወደ አብ መግባታችንን" ከነገረን በኋላ ቅድስተ ቅዱሳን በሚባል አንድ ክፍል ተወስነን እንደምንቀመጥ ሳይሆን ትልቅና ሰፊ አገር እንደ ወረስን በሚገልጽልን አጻጻፉ ነው፡-

> *"እንግዲያስ ከእንግዲህ ወዲህ ከቅዱሳን ጋር ባለአገሮችና የእግዚአብሔር ቤተሰቦች ናችሁ እንጂ እንግዶችና መጻተኞች አይደላችሁም፡፡" ኤፌ. 2፡ 19*

ከእግዚአብሔር ጋር በእግዚአብሔር ውስጥ የምንኖር፣ እግዚአብሔር መኖሪያችን ማደሪያችን የሆነ ባለርስት ነን፡፡ ይህንንም ዘላለማዊ ርስት ከቅዱሳን ጋር በአንድነት እንካፈላለን፣ እንወርሳለን፡፡ አሁን አይሁድ፣ አሕዛብ የለም፤ ሴት፣ ወንድ የለም ባርያ፣ ጨዋ የለም፤ ሁላችን በክርስቶስ ኢየሱስ የተስፋው ወራሽ ሆነናል፡፡ ከክፍሉ እንደምንረዳው ይህ ርስት እንደ አገር የሰፋ ቢሆንም በሌላ በኩል ደግሞ እንደ ቤተሰብ የተቀራረበ ነው፡፡ ስለዚህ እኛም ከቅዱሳን ጋር ባለ አገሮች፣ የእግዚአብሔርም ቤተሰቦች ሆነናል፡፡



For more books www.amharicchristianbooks.com

እዚህ ጋ ቆም ብለን ልናስበው የሚገባ ክቡር እውነት፣ ራሳችንንም ልንጠይቀው የሚገባ ትልቅ ጥያቄ አለ፡፡ ሰውን ከሰው ለይቶ የነበረው ግንብ እንዲሁ በቀላሉ እንዳልፈረሰ፣ ነገር ግን ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ በመስቀል ላይ ለሰአታት በስቃይ መጮሁን ግድ እንዳለ ልብ እንላለን፡፡ ሆኖም በታላቅ ጭንቅና መከራ የፈረሰውን ይህን የጥል ግድግዳ ዛሬ ሰዎች በዘርና በቀለም ሲገነቡት እናያለን፡፡ ይህም አሳዛኝ ክስተት በማያምነው ማሕበረሰብ ዘንድ ብቻ ሳይሆን የጌታን ስም በሚጠሩ "አማኞች" ዘንድ ይከናወናል፡፡ በአሜሪካ ከዘረኝነት የመነጨው የጥቁርና የነጭ ልዩነት (ሰግሪጌሽን) ከብርቱ ትግል በኋላ ከረዥም ዓመታት በፊት በሕግ ተሸሯል፡፡ ነጭና ጥቁር በአንድ የሕዝብ ትራንስፖርት የማይሄዱበት፣ አንድ ምግብ ቤት የማይመገቡበት፣ አንድ ትምህርት ቤት የማይማሩበት ዘመን አክትሟል፡፡ ነገር ግን ዛሬም በሚገርም ሁኔታ በአሜሪካ ልብ ያልተባለ ልዩነት (ሰግሪጌሽን) አለ፡፡ የሳምንቱን ቀናት ሁሉ ነጭና ጥቁር አብረው ሲማሩ፣ አብረው ሲበሉ፣ አብረው ሲሰሩና አብረው ሲጓዙ ይከርሙና እሁድ ሲመጣ ልዩነቱ ይጀመራል፡፡ ልዩነቱ የሚከናወነውም "በቤተክርስቲያን" ውስጥ ነው፡፡ ነጮች፣ በነጮች ቤተክርስቲያናት፤ ጥቁሮችም በጥቁሮች ቤተክርስቲያናት በመሰብሰብ በሕግ የፈረሰውን የልዩነት (የሰግሪጌሽን) አጥር እንደ ገና ይገነቡታል፡፡

በዘር፣ በቀለም፣ በጎሳ ላይ ተመስርተን ቤተክርስቲያን ስንመሰርትና አንዱን ከአንዱ ስንለይ፣ ክርስቶስ በመስቀል ጣሩ ያፈረሰውን ግንብ እየገነባን መሆኑን ልናስተውል ይገባል፡፡ ይህም ትልቅ ፍርድ የሚያመጣ ክፉ ተግባር ነው፡፡ ኢያሱና የእስራኤል ሕዝብ ለሰባት ቀናት ከጮኹ በኋላ የፈረሰውን የእያሪኮ ግንብ ዳግመኛ ሊገነባ በሚነሳ ማንኛውም ሰው ላይ ኢያሱ *"ይህችን ከተማ ኢያሪኮን ለመሥራት የሚነሣ ሰው በእግዚአብሔር ፊት ርጉም ይሁን፤ መሠረትዋን ሲጀምር በኩር ልጁ ይጥፋ፣ በሯንም ሲያቆም ታናሽ ልጁ ይጥፋ . . . ፡፡"* (ኢያሱ 6፡26) በማለት እንደ ማለ እናነባለን፡፡ ከብዙ መቶ አመታት በኋላ በነገሥታት ዘመን የቤቴል ተወላጅ የሆነ አኪኤል የተባለ ሰው የኢያሪኮን ግንብ ሊሠራ ተነሣ፤ ሆኖም መሠረቱን ሲጥል ትልቁ ልጁ አቢሮን፤ በሩንም ሲያቆም ትንሹ ልጁ ሠጉብ እንደ ሞተ ተራ በተራ ሞቱ፡፡[143] ታዲያ የምድራዊው የኢያሱ ቃል እንዲህ ከደረሰ፣ የእርግማኑም ቃል ከፀና፤ ከሰማይ የመጣው የእግዚአብሔር ልጅ ቃል ምንኛ የፀና ይሆን!

ጳውሎስ በመቀጠል የሚነግረን በዚህ ሰማያዊ የሕይወት ርስት ላይ የሚገነባ መቅደስ መኖሩን ነው፡፡ ቀደም ሲል እግዚአብሔር መቅደሳችን የዘላለም

[143] ኢያሱ 6፡26; 1ነገሥት 16፡34



For more books www.amharicchristianbooks.com

ማደሪያችን እንደ ሆነ ጽፎልናል፡፡ አሁን ደግሞ እኛ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት በእርሱ ውስጥ እንደምንኖር ሁሉ እርሱም በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት በእኛ ውስጥ የሚያድርብን መቅደሱ መሆናችንን ይነግረናል፡፡[144] በሁለቱ መቅደሶች መካከል የምናየው አብይ ልዩነት፣ አንደኛው መሠራት የማያስፈልገው ዓለም ሳይፈጠር በፊት የተዘጋጀ[145] ሲሆን፣ ሁለተኛው ግን ገና የሚሠራ መሆኑ ነው፡፡[146] አንደኛው ራሱ እግዚአብሔር ሲሆን ሁለተኛው በክርስቶስ አምነው በዳኑና በመንፈስ ቅዱስ በተሞሉ አማኞች አንድነት የምትገነባ አዲሷ ማሕበረሰብ ቤተክርስቲያን ናት፡፡ ይህች የዘር፣ የቀለም፣ የጎሳ፣ የባሕል፣ የፆታ፣ የመደብ ልዩነት በሌለበት ሁኔታ ከተለያዩና ብዙ ሕብር ካላቸው ሕያዋን ድንጋዮች የምትሠራ ቅድስት ቤተ-መቅደስ ዋና አገልግሎቷ ለእግዚአብሔር መኖሪያ መሆን ነው፡፡ (ቁ.22) ይህም በግል ድነትን በማግኘት ብቻ የሚፈፀም[147] ሳይሆን በጋራ መሠራትን የሚጠይቅ የእውነተኛ መንፈሳዊ እድገት ዋነኛ መገለጫ ነው፡፡

ጳውሎስ በዚህ የቤተመቅደስ ግንባታ ውስጥ ትኩረት የሰጣቸው ሁለት የሕንፃው ክፍሎች አሉ፡፡ አንደኛ መሠረቱ ሲሆን ሁለተኛው የሕንፃው ክፍሎች ሁሉ የሚጋጠሙበት የማዕዘኑ ራስ ድንጋይ ነው፡፡ ከመሬት ወለል በታች የሚውለውና ከውጭ የማይታየው የሕንፃው መሠረት ክርስቶስ መሆኑ ምንም ጥያቄ የለውም፡፡ ጳውሎስ ራሱ በ1ቆሮ.3፡11 መሠረቱ ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን በግልፅ ጽፏል፡፡ ነገር ግን በዚህ ሥፍራ ሊጠራው የወደደው በመሠረቱ ስም ሳይሆን በመሠረት ጣዮቹ ስም ነው፡፡[148] "በሐዋርያትና በነቢያት መሠረት ላይ ታንፃችኋል (ቁ.20) ፡፡" በማለት ምንም እንኳ ክርስቶስ ወደ ላይ በወጣ ጊዜ ለቤተክርስቲያን የሰጣቸው የእርገት ስጦታዎች የሆኑ አገልግሎቶች ሐዋርያት፣ ነቢያት፣ ወንጌል ሰባኪዎች፣ እረኞችና አስተማሪዎች ቢሆኑም ጳውሎስ ግን መሠረት ከመጣል ጋር የሚያዛምዳቸው የመጀመሪያዎቹን ሁለቱን ማለትም ሐዋርያትንና ነቢያትን ብቻ ነው፡፡

ቀዳሚዎቹ ሐዋርያትና ነቢያት የውስጠኛው መሠረት (Sub-structure) ላይ ሲያተኩሩ፣ ቀጣዮቹ ወንጌል ሰባኪዎች፣ እረኞችና አስተማሪዎች ሕንፃው (Super-structure) ላይ እንደሚያተኩሩ መገመት እንችላለን፡፡ ጳውሎስም በዚህ ክፍል ትኩረቱ እንደ 1ቆሮ. 3፡1 መሠረቱ ላይ ሳይሆን ሕንፃው ላይ በመሆኑ መሠረቱን

144 ራዕ. 21፡22
145 ማቴ. 25፡34
146 1ጴጥ. 2፡4-5
147 ኤፌ. 2፡5፣8
148 ራዕ. 21፡14



For more books www.amharicchristianbooks.com

ከራሱ ከመሠረቱ ይልቅ በአናፂዎቹ ሰይሞ ያልፈዋል፡፡ ትኩረቱን ስለ ጣለበት ስለሚታየው የሕንፃው ውጪያዊ ክፍል ሲጽፍ እያንዳንዱን የሕንፃውን ክፍል የሚያገናኘውና የሚያጋጥመው *"የማዕዘን ራስ ድንጋይ"* ክርስቶስ ኢየሱስ መሆኑን በግልጽ ያስቀምጣል፡፡ በመጀመሪያው ምዕራፍ ላይ ቤተክርስቲያን አካሉ እንደሆነች ሲያሳይ ኢየሱስ ክርስቶስ የአካሉ ራስ እንደሆነ ነግሮናል፡፡[149] አሁን ደግሞ ቤተክርስቲያን ሕንፃ መሆኗን ሲስልልን ኢየሱስ ክርስቶስ የማዕዘን ራስ መሆኑን ይጽፍልናል፡፡ ይህም ኢየሱስ ክርስቶስ በቤተክርስቲያን በሚታይም ሆነ በማይታይ ማንነቷ ላይ ያለ ምንም ተቀናቃኝ ዋና የበላይ መሆኑን ያሳየናል፡፡ ሐዋርያ፣ ነቢይ፣ ወንጌል ሰባኪ፣ እረኛ ወይም አስተማሪ ብንባል ኃላፊነት የተሰጠን ባሮች እንጂ አንዳች እንዳልሆንን ያስገነዝበናል፡፡[150]

ሐዋርያትና ነቢያትም መሠረት የጣሉት በመንፈስ የተገለጠላቸውንና በቀደሙት ዘመናት ለሰው ልጆች ታውቆ የማያውቀውን ምሥጢር በመግለጽ ነው፡፡[151] እነዚህ ሐዋርያትና ነቢያት በየትኛውም ዘመን የማይደገመውን መሠረት ለአንዴና ለዘላለም በተግባርም በጽሑፍም ጥለው አልፈዋል፡፡ በየትኛውም ትውልድ የሚነሱ አገልጋዮች የእነዚህን ሐዋርያትና ነቢያት መሠረት በመረዳት ይሠራሉ እንጂ የራሳቸውን መገለጥ ሊያመጡ አይችሉም፡፡ ሊገለጥ የሚገባው ሁሉ ተገልጦ አልቋል፡፡ የሚያስፈልገን አብርሆት እንጂ አዲስ መገለጥ አይደለም፡፡

ሌላ ትኩረት ሰጥተን ልናየው የሚገባን "ነቢያት" የሚለው ቃል ነው፡፡ እነዚህ ነቢያት የብሉይ ኪዳን ነቢያት አይደሉም፡፡ ቢሆኑ ኖሮ የተገለጠላቸው ምሥጢር *"ለቅዱሳን ሐዋርያትና ለነቢያት በመንፈስ አሁን እንደ ተገለጠ በሌሎች ትውልዶች ዘንድ ለሰው ልጆች አልታወቀም፡፡"* (ኤፌ. 3፡ 6) ባልተባለም ነበር፡፡ እነዚህ የክርስቶስን መምጣት ከተናገሩት የብሉይ ኪዳን ነቢያት ተሰውሮ የኖረው ምስጢር በመንፈስ ተገልጦላቸው[152] ፣በትጋት የገለጡ የቤተክርስቲያን ነቢያት ስለመሆናቸው አንዳች ጥርጥር የለውም፡፡ እነዚህ ነቢያት በዘመናችን "የነቢያት አገልግሎት" ሲባል እንደምንሰማው "ይሄ ይሆንልሃል ... ይሄ ይሳካልሃል" በማለት ለሰዎች ምሪትን የሚሰጡ ሳይሆኑ[153]፣ በክርስቶስ ኢየሱስ የተፈፀመውን የእግዚአብሔርን ምክር በመንፈስ እየገለጡ በማስተማር ቤተክርስቲያንን የሚያንፁ አገልጋዮች ናቸው፡፡

---

[149] ኤፌ. 1፡22
[150] 1ቆሮ. 3፡ 5-8
[151] ኤፌ. 3፡6
[152] 1ጴጥ. 1፡10-12
[153] በአዲስ ኪዳን መጽሐፍት ውስጥ ነቢይ ተብሎ ተጠርቶ ምሪትን በመስጠት ማገልገሉ በሁለት ቦታዎች የተጠቀሰው አጋቦስ ብቻ ነው፡፡ ሐዋ. 11፡ 27-30; 21፡ 10-11



For more books www.amharicchristianbooks.com

በእርግጥ በአዲስ ኪዳን ቤተክርስቲያን ውስጥ ለማነጽ፣ ለመምከርና ለማፅናናት የሚመጡ ትንቢቶች ነበሩ አሁንም አሉ፡፡ እነዚህ ግን መንፈስ ቅዱስ እንደ ወደደ ለእያንዳንዱ አማኝ በማከፋፈል በቅዱሳን ማህበር የሚገልጣቸው የፀጋ ሥጦታዎች ናቸው እንጂ የሚገለጡባቸውን ሁሉ ነቢያት የሚያሰኙ የአገልግሎት መስኮች አይደሉም።



For more books www.amharicchristianbooks.com

# ምዕራፍ ፲

# የተገለጠ ምሥጢር

ኤፌ. 3፡ 1 - 21

በዚህ ክፍል ጳውሎስ ራሱንና የአሕዛብ ሐዋርያ እንዲሆን የተሰጠውን ታላቅ ኃላፊነት ይዘግባል፡፡ አገልግሎቱም ለዘመናትና ለትውልዶች ተሰውሮ የኖረን ምሥጢር ከመግለጥ ጋር በጽኑ የተቆራኘ መሆኑን ያስረዳል፡፡[154] ክፍሉንም የሚጀምረው በጸሎት መንፈስ በእንብርክክ ሆኖ ነው፡፡ የጸሎቱም ብቸኛ ርዕስ፣ ቀደም ባለው ምዕራፍ የተረከው በእርሱ በኩል ለአሕዛብ የተገለጠው አስደናቂ ምሥጢር ነው፡፡ አሕዛብ ወገኖች ይህ ምሥጢር እንዲገለጥላቸውና የእግዚአብሔርን ፀጋ በማወቅ እንዲፀኑ ምልጃውን በቁጥር 1 ላይ ይጀምርና በመሃል ራሱንና አገልግሎቱን ሲያስተዋውቅ ቆይቶ እንደገና በቁጥር 14 ላይ ይቀጥለዋል፡፡

ጳውሎስ ራሱን ማስተዋወቅ ያስፈለገው መልዕክቱን ከሚጽፍላቸው አማኞች ጋር በዓይነ ሥጋ ስላልተያዩና እርሱ ስለ እነርሱ ያለው፣ እነርሱም ስለ እርሱ ያላቸው እውቀት ከአገልጋዮቻቸው የሰሙት የሩቅ ለሩቅ መረጃ ብቻ ስለሆነ ነው፡፡[155] ሐዋርያው መልዕክቱን የሚያነቡት አሕዛብ ስለ እርሱና ስለ አገልግሎቱ እንዲገነዘቡ የፈለጋቸው ነገሮች አሉ፡፡ ከእነዚህም አንዱ የእስራቱን ምክንያት ግልፅ ማድረግ ነው፡፡

ጳውሎስ በመልዕክቱ በድፍረት እስረኛነቱን ይገልፃል፡፡[156] ይህን ድፍረት የሰጠውም የታሰረው እንደሌሎች በሌብነት፣ በነፍስ ገዳይነት ወይም በሰዎች ነገር በመግባት ሳይሆን፣ ስለ ወንጌል በመሆኑ ነው፡፡[157] በሌላ የእስር ቤት መልዕክቱ *“ነገር ግን ወንድሞች ሆይ ይህ የደረሰብኝ በእውነት ወንጌልን ለማስፋፋት እንደሆነ ታውቁ ዘንድ እወዳለሁ፡፡ ስለዚህም እስራቴ ስለ ክርስቶስ እንደሆነ በንጉስ ዘበኞች ሁሉና በሌሎች ሁሉ ዘንድ ተገልጧል . . . ፡፡”* (ፊሊ. 1፡12-14) በማለት መፃፉ ተደራስያኑ የእስራቱን ምክንያት በግልጽ እንዲያውቁ መፈለጉን ያሳያል፡፡ ይልቁንም በዚህ ስፍራ *“... አሕዛብ ስለ ሆናችሁ ስለ እናንተ የክርስቶስ ኢየሱስ እስር የሆንሁ እኔ ጳውሎስ . . . ፡፡”* (3፡1) በማለት የእስራቱ ምክንያት በቀጥታ አሕዛብ እንደሆኑና

---

[154] ሮሜ 16፡25፣26; ቆላ. 1፡27
[155] ኤፌ. 1፡15; 3፡2; ቆላ. 2፡1; 1፡7-8
[156] 3፡1፣ 4፡1፣ 6፡20
[157] 1ጴጥ. 4፡15፣16



For more books www.amharicchristianbooks.com

በእርሱ በታወጀው ወንጌል ያመኑ በቅርብም፣ በሩቅም ያሉ አሕዛብ የአገልግሎቱና የመከራው ባለ ዕዳ መሆናቸውን የሚገልጽ ስሜት ያንፀባርቃል፡፡

ወደ ኋላ ሄደን የዚህን እስራት ጅማሬ ስናጤን ታሪክ ጸሐፊውና ባለ መድሃኒቱ ሉቃስ በዘገበው የሐዋርያት ሥራ ውስጥ ይህ ምክንያት ቁልጭ ብሎ እናየዋለን፡፡ ጳውሎስ በኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ ሲያመልክ ሁከት ያስነሱት ከእስያ የመጡ አይሁድ ያቀረቡበት ክስ፡-

“የእስራኤል ሰዎች ሆይ እርዱን ሕዝብን፣ ሕግንም ይህንንም ስፍራ (መቅደሱን) ሲቃወም ሰውንም ሁሉ በየስፍራው የሚያስተምረው ሰው ይህ ነው፡፡” (ሐዋ. 21፡27) (በቅንፍ የገባው ማብራሪያ የራሴ ነው)

የሚል ነበር፡፡ እስራኤልን፣ እስራኤል የሚያሰኟትና ከሌሎች የዓለም ሕዝቦች የሚለዩአት ሦስቱ የአይሁድ እምነት ምሶሶዎች፡- 1. ሕዝቡ (አም እስራኤል) 2. ሕጉ (ቶራት) 3. ምድሩና መቅደሱ (ኤሬፅ እስራኤል) ናቸው፡፡ ከፍ ብለን ባየነው ክፍል ጳውሎስ እነዚህን ሦስቱንም የአይሁድነት መገለጫዎች ተቃውሞ እንዳስተማረ ክስ ቀርቦበታል፡፡ በእርግጥም ቀደም ሲል በ2፡11-22 የፃፈውን ስናነብ እግዚአብሔር ከላይ የተጠቀሱትን ሦስቱንም ምሰሶዎች ዞር በማድረግ በክርስቶስ ኢየሱስ ከአሕዛብም ከአይሁድም የሆነ አንድ አዲስ ሕዝብ መፍጠሩን፣ በፊደል ሳይሆን በመንፈስ፣ በድንጋይ ጽላት ላይ ሳይሆን በልብ ጽላት ላይ የሚጻፍ አዲስ የሕይወት ሕግ በማምጣት የቀደመውን የፊደል ሕግ መሻሩን፣ በመጨረሻም በሰው እጅ የተሠራውን ምድራዊ መቅደስ ትቶ ከአይሁድም፣ ከአሕዛብ በሆኑ ሕያዋን ድንጋዮች የሚገነባውን መንፈሳዊ መቅደስ መምረጡን ጽፏል፡፡እንግዲህ የእስሩ ምክንያት ይህ ነው፡፡ ምንም እንኳ እንደ አሥራ ሁለቱ ከመጀመሪያው ከኢየሱስ ጋር ያልነበረና በምድር አገልግሎቱ የተካፈለ ባይሆንም ከተሰጠው ፀጋ የተነሳ ከእነርሱ በተካከለ ፀጋ የአሕዛብ ሐዋርያ ሆኖአል፡፡[158]

ጳውሎስ የሚጽፍላቸው አሕዛብ እስሩ ስለ ወንጌል መሆኑን ብቻ ሳይሆን፣ ይህ ወንጌል ወደ እነርሱ የደረሰው ዋጋ ተከፍሎበት እንደሆነ እንዲያውቁና ከዚህም በመነሳት ይህን አዲስ እምነታቸውን እንዲያከብሩ ፈልጓል፡፡ ስለዚህ ነው፡- “. . . ስለ እናንተ ስላለ መከራዬ እንዳትታክቱ እለምናችኋለሁ ክብራችሁ ነውና፡፡” (ቁ.13) የሚላቸው፡፡ በሌላም ስፍራ አሕዛብ የእግዚአብሔር ሕይወት ወራሾች እንደሆኑ የሚያውጀውን የምስጢር መገለጥ ወደ አሕዛብ ለማድረስ ስለሚቀበለው መከራ ሲጽፍ ስለዚህ ሞቱ በእኛ ሕይወቱም በእናንተ ይሠራል፡፡” (2ቆሮ. 4፡12)

[158] ገላ. 2፡6-9



For more books www.amharicchristianbooks.com

ብሎአል፡፡

ሌላው እንዲታወቅለት የፈለገው ለዚህ መከራና እስራት ምክንያት የሆነው ለአሕዛብ የተሰጠው የወንጌልን ምሥጢር የመግለጥ አገልግሎቱ መሆኑን ነው፡፡ ይህንንም፡-

> *"ለእናንተ ስለ ተሰጠኝ ስለ እግዚአብሔር ፀጋ መጋቢነት በእርግጥ ሰምታችኋል አስቀድሜ በአጭሩ እንደፃፍኩ ይህንን ምስጢር በመግለጥ አስታወቀኝ. . . ፡፡"* (ቁ.2፣3)

በማለት ያብራራዋል፡፡ ጳውሎስ ፀጋውን የእኔ ብሎ አይጠራውም ይልቁንም *"ለእናንተ ስለተሰጠኝ"* በማለት አድራሽ መልዕክተኛ እንጂ ባለቤት አለመሆኑን ግልጽ ያደርጋል፡፡ ይልቅ "መጋቢነት" (ባለአደራነት) ተሰጠኝ በማለት የዚህን ፀጋ አስተዳዳሪነት በኃላፊነት መቀበሉንና በኋላም ተጠያቂ፣ ሥራውም ተመዝኖ ተሸላሚ መሆኑን በሚያሳይ መንገድ ይገልፀዋል፡፡

*". . . አስቀድሜ በአጭሩ እንደፃፍኩ . . ."* የሚለውም የዚህን ምስጢር ዋና እፍታ የያዘውን በ2፡11-22 የሚገኘውን ክፍል ለአንባቢያኑ ለማስታወስ ነው፡፡

## የምስጢሩ ምንነት

ጳውሎስ "ምስጢር" የሚለውን ቃል በዚህ መልዕክት ውስጥ ስድስት ጊዜ የተጠቀመ ሲሆን ከስድስቱ ሦስቱ የሚገኙት እያየን ባለነው በምዕራፍ ሦስት ውስጥ ነው፡፡ በዚህ እግዚአብሔርንና ሰውን፣ አይሁድንና አሕዛብን፣ ሰማይንና ምድርን በሚጠቀልለው ምስጢር[159] ውስጥ ሰፊውን ስፍራ ይዞ የምናየው የአይሁድና የአሕዛብ አብሮ ወራሽነት ነው፡፡ የዚህንም ምስጢር እምብርት የምናገኘው በቁጥር 5 ላይ ነው፡፡ በዚህ ስፍራ የአንዱን ምስጢር ምንነት በሦስት አቅጣጫ በመከፈል ያስቀምጥልናል፡፡

1. **አሕዛብ አብረው እንዲወርሱ፡-** ይህ አባባል አሕዛብ ከአይሁዳውያን ጋር አንድ በመሆን የእግዚአብሔር ወራሾች እንደሚሆኑ ያሳያል፤

2. **በአንድ አካልም አብረው እንዲሆኑ፡-** አይሁድና አሕዛብ አብረው የሚወርሱ ብቻ ሳይሆኑ አንድ ሕይወት በመካፈልና የአንድ አካል ክፍሎች በመሆን ሊወዳደሩ፣ ሊበላለጡ፣ ሊፎካከሩ፣ ሊደራደሩ፣

[159] ኤፌ. 5፡32፣ 3፡5፣ 1፡9፣10



For more books www.amharicchristianbooks.com

በማይችሉበት መጠን በአብና በወልድ መካከል እንዳለው አይነት አንድነት[160] ፍፁም አንድ እንዲሆኑ መደረጉን ያሳያል፤

3. **በወንጌልም መስበክ በክርስቶስ ኢየሱስ በሆነ የተስፋ ቃል አብረው እንዲካፈሉ፡-** ይህ ሐረግ አሕዛብ ከአይሁድ ጋር የሚካፈሉት በ2፡12 ላይ የተጠቀሰውን እስራኤላውያን ብቻ የነበራቸውን የቀደመ ተስፋ ሳይሆን፣ ተስፋው የምሥራች በሆነበት በወንጌል በክርስቶስ ኢየሱስ ትንሳኤ እውን መሆን በጀመረውና በዘመን ፍፃሜ ሁሉ በክርስቶስ ሲጠቀለል በክብር የሚፈፀመው ተስፋ ተካፋይ መሆናቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

እንግዲህ ሁሉን ጠቅልለን ምስጢሩ ምንድነው? ብለን ስንጠይቅ የምናገኘው መልስ አሕዛብ ከአይሁዳውያን ጋር አንድ አካል ሆነው በክርስቶስ ኢየሱስ በተፈፀመውና በወንጌል በታወጀው ተስፋ መሠረት የእግዚአብሔር ወራሾች መሆናቸው ነው፡፡ ሆኖም ሁልጊዜ "ወራሽ" የሚለውን ቃል ስናነሳ "ተወራሽ" የሚለውን ቃል በምላሹ ልናነብ ይገባል፡፡ ተስፋው እኛ በክርስቶስ እግዚአብሔርን እንደምንወርስ[161] ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔርም በክርስቶስ ኢየሱስ እኛን እንደሚወርሰን ይናገራልና፡፡

ጳውሎስ የምስጢሩን ምንነት በቁ. 5 ላይ ከዘረዘረ በኋላ ይህ ምስጢር *". . . ለቅዱሳን ሐዋርያትና ለነቢያት በመንፈስ አሁን እንደተገለጠ በሌሎች ትውልዶች ዘንድ ለሰው ልጆች አልታወቀም፡፡"* (ቁ.6) በማለት የዚህ ምስጢር መገለጥ ፍፁም አዲስ መሆኑን ይጽፋል፡፡ ሆኖም ይህ ዓረፍተ ነገር በብዙዎች ዘንድ በተለይም በአይሁዳውያን ዘንድ ጥያቄ ማስነሳቱ አልቀረም፡፡ እነዚህ ጠያቂዎች የሚያነሱት ሙግት ይህ ነው፡- አሕዛብ የእግዚአብሔር በረከት ተካፋይ እንደሚሆኑ በክርስቶስ እንደሚወርሱ፣ ከአይሁድ ጋር በእግዚአብሔር ተራራ በሚሆነው አምልኮ እንደሚካፈሉ ወ.ዘ.ተ. ከክርስቶስ መምጣት በፊት በነበሩ ነቢያት ተነግሮ የለምን?[162] ያዕቆብስ በኢየሩሳሌም ጉባዔ ሰለ አሕዛብ ያለ ሕግ መጽደቅ ክርክር በተነሳ ጊዜ ጉባዔውን ያረጋጋው ከነቢያት መጽሐፍ በመጥቀስ አይደለምን?[163] ይላሉ፡፡

እውነት ነው፡፡ መጋረጃው ተገፎለት፣ የዓይኑ ቅርፊት ወድቆለት፣ በአዲስ ኪዳን

160 ዮሐ. 17፡ 11፣21፣22
161 ሮሜ 8፡17፣ መዝ. 2፡8
162 ሐዋ. 15፡13-20፣ አሞጽ 9፡11፣12; 1ጴጥ. 1፡10-12
163 ሐዋ. 15፡ 13-20; አሞፅ 9፡ 11-12



For more books www.amharicchristianbooks.com

ብርሃን የቀደሙትን ቅዱሳት መጽሐፍት ለተመለከተ፣ ይህን ምስጢር በሚያፀኑ ትንቢቶችና የተስፋ ቃሎች የተሞላ እንደሆነ ለመረዳት አያስቸግርም፣ ሆኖም እነዚያ ነቢያት ፍሬ ነገሩን ቢናገሩትም እንኳ ተናገሩት እንጂ ልክ እንደ አሁኑ ፍንትው ብሎ አልተገለጠላቸውም ነበር፡፡[164] መናገር አንድ ነገር ሲሆን፣ የተናገሩትን ሙሉ በሙሉ መረዳት ደግሞ ሌላ ጉዳይ ነው፡፡ ለእነዚህ ነቢያት የተገለጠላቸው አንድ ነገር ቢኖር በተናገሩት ነገር እኛን እንጂ ራሳቸውን አለማገልገላቸው ነው፡፡ ስለዚህ ጳውሎስ ይህ ምስጢር ከሰማይ በተላከ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ቅዱሳን ለሚላቸው የአዲስ ኪዳን ሐዋርያትና ነቢያት ብቻ መገለጡን በድፍረት ይጽፋል፡፡ ሆኖም ለአሕዛብ ይህን ምስጢር የመግለጥ ጉዳይ ሲነሳ ጳውሎስ የአንበሳውን ድርሻ እንደሚወስድ በኢየሩሳሌም ሐዋርያት እንኳ የታወቀ ቢሆንም፣ እርሱ ግን "ቅዱሳን ሐዋርያትና ነቢያት" በማለት በብዙ ቁጥር እየጠራ መገለጡን ከሌሎች የወንጌል ሠራተኞች ጋር ይጋራል እንጂ የራሱ ብቻ ለማድረግ ሲሞክር አናይም፡፡[165]

## የመገለጥ ሠንሰለት

መቼም ምሥጢር ሲባል ለበቁ፣ ለነቁ እንጂ ለሁሉ የማይነገር እንደሆነ መገመታችን አይቀርም፡፡ ይህ ምሥጢር ግን ምንም እንኳ ለዘመናት ለትውልዶች ተሰውሮ የኖረ ቢሆንም፣ አሁን ግን ምሥጢር ሆኖ እንዲቀጥል የእግዚአብሔር ፈቃድ አይደለም፡፡ ዘመኑ የፀጋ፣ ኪዳኑም የመገለጥ ነውና በሁሉ ዘንድ ይልቁንም በአማኞች ዘንድ እንዲታወቅ የአምላካችን በጎ ፈቃድ ነው፡፡ ሆኖም በአንድ ጊዜ ለሁሉ ሊገለጥ አይችልም፡፡ ስለዚህ በሂደት ደረጃ በደረጃ ይገለጣል፡፡ ይህንንም ሂደት የመገለጥ ሠንሰለት ልንለው እንችላለን፡፡

> ጳውሎስ "... በመንፈስ አሁን እንደተገለጠ በሌሎች ትውልዶች ዘንድ ለሰው ልጆች አልታወቀም፡፡" (ቁ.6)

በማለት ሲጽፍ ይህ ምስጢር በአንድ ወቅት በእግዚአብሔር ዘንድ ብቻ የተሰወረና ከአብ፣ ከወልድና ከመንፈስ ቅዱስ በቀር የሚያውቀው አንዳች እንዳልነበር እንረዳለን፡፡[166] ሆኖም ዘመኑ በደረሰ ጊዜ ከቅዱሳን ሐዋርያቱ አንዱ ለሆነው

164 1ጴጥ. 1፡10-12
165 ገላ. 2፡ 6-9
166 ማቴ. 11፡25-27፣ 1ቆሮ. 2፡10፡11



For more books www.amharicchristianbooks.com

ለጳውሎስ እግዚአብሔር ይህን ምስጢር ገለጠለት፡፡[167] እግዚአብሔር ይህን ታላቅ ሚስጥር ለጳውሎስ የገለጠለት ጳውሎስን ለማስደነቅ አልነበረም፡፡ ነገር ግን ሐዋርያው የዚህን መገለጥ አደራ፣ ተቀብሎ ነፍሱን እንደማትከብር ከንቱ ነገር በመቁጠር ይህን መገለጥ አስቀድሞ ለአይሁዳውያን ከዚያም ለአሕዛብ ሁሉ እንዲያደርስ ነበር፡፡[168]

ጳውሎስም በውስጡ እንደሚሠራው የእግዚአብሔር ኃይልና እንደተሰጠው ፀጋ ስጦታ መጠን የወንጌል አገልጋይ ሆነ (ቁ.7) ፡፡ ፍለጋ የሌለውንም የክርስቶስን ባለጠግነት እንደሚወርሱ ለአሕዛብ የምሥራች ሰበከ (ቁ.8)፡፡ ሁሉን በፈጠረ በእግዚአብሔር ከዘላለም የተሰወረውን የምሥጢር ሥርዓት አይሁድ አሕዛብ ሳይል ለሰው ሁሉ ገለጠ፡፡(ቁ.9) በዚህም በእግዚአብሔር ዘንድ ብቻ የነበረው ምስጢር ለጳውሎስ፣ በጳውሎስ ዘንድ የነበረውም ምስጢር ለአሕዛብና ለአይሁድ፣ በቤተክርስቲያን ዘንድ ያለውም ምሥጢር በሰማያዊ ሥፍራ ላሉ አለቆችና ሥልጣናት መገለጡን እንመለከታለን፡፡ ሆኖም ጳውሎስ ይህ ታላቅ ምስጢር ቢገለጥለትና ቢገለጥበትም እንኳ ራሱን የሚያየው እንደ አንድ ታላቅ ሰው ሳይሆን “ከቅዱሳን ሁሉ ይልቅ እንደሚያንስ” (ቁ.9) ነው፡፡ ጳውሎስ ይህን የሚለው ለአጉል ትህትና ሳይሆን ሮማዊ ስሙ የሚገልጠውን ተፈጥሮውንና[169] ይህን ብርሃን ከማግኘቱ በፊት በክርስቶስ ቤተክርስቲያን ላይ ከፈፀመው በደል የተነሳ ነው፡፡[170]

ይህ ምስጢር የተገለጠላቸው አይሁድና አሕዛብ በወንጌል የታደሉትን የክርስቶስን ሕይወት በመካፈል አዲስ ማኅበረሰብ ሆኑ፡፡ ይህችም ማኅበረሰብ "ቤተክርስቲያን" (ኤክሌዥያ) ተብላ ተጠራች፡፡ የመገለጡ ሠንሰለት በርሷ አላከተመም፡፡ በአንድ መንፈስ የመጠቅለል ምስጢር የተገለጠላትና የተገለጠባት ቤተክርስቲያን ብዙና ልዩ ልዩ የሆነውን የእግዚአብሔርን ጥበብ በሰማያዊ ስፍራ ውስጥ ላሉት አለቆችና ስልጣናት መግለጡን ተያያዘችው(ቁ.10)፡፡

በእርግጥ ጳውሎስ ለቤተክርስቲያን ምስጢሩን ያሳወቀበት መንገድና ቤተክርስቲያን በሰማያዊ ስፍራ ላሉ አለቆችና ስልጣናት የምታሳውቅበት መንገድ ይለያያል፡፡ እርሱ ወንጌልን በመስበክ የገለጠው ሲሆን እርሷ ግን አይሁድና ግሪክ፣ ጨዋና ባርያ፣ ሴትና ወንድ፣ የተገረዘና ያልተገረዘ፤ አረማዊና እስኩቴስ ሳይለያዩ ክርስቶስን

[167] ቲቶ 1፡3
[168] ሐዋ. 20፣24; ሮሜ 1፡16
[169] በላቲን “ጳውሎስ” ማለት “ትንሽ” ማለት ሲሆን ሰውነቱም ይህን ያመለከተ እንደነበር እንዳንድ ጥንታዊ ጽሁፎች ያስረዳሉ፡፡
[170] 1ቆሮ. 15፣8-10፣ 1ጢሞ. 1፡12-16



For more books www.amharicchristianbooks.com

ለብሰው በመንፈስ አንድ ሆነውባት እግዚአብሔርን ሲያመልኩ የምትገልጠው ነው፡፡

እነዚህ አለቆችና *ሥልጣናት*፣ ቅዱሳን መላዕክት ይሁኑ የወደቁት መላዕክት፣ ጳውሎስ ግልጽ ያደረገልን ነገር የለም፡፡ ሆኖም በሰማያዊ ስፍራ የሚኖሩ መንፈሳዊ አካላት መሆናቸውን እርግጠኛ መሆን አንቸገርም፡፡ ጳውሎስ በ1፡20 ላይ እነዚህን አካላት በጥቅል ቢዘረዝራቸውም በ2፡2 እና 6፡12 ላይ የእግዚአብሔርና የሕዝቡ ጠላቶች የሆኑቱን በነቂስ ሲያወጣቸውና ማንነታቸውን ግልጽ ሲያደርግ እናያለን፡፡ በዚህ ስፍራ ግን ስለ እነዚህ አለቆችና *ሥልጣናት* ማንነት የፈታልን ነገር የለም፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ዝም ሲል አብሮ ዝም ማለትን የመሰለ ምን አለ? ሆኖም ስለ እነዚህ መንፈሳዊ አካላት (መላዕክት) በድፍረት ልንላቸው የምንችላቸው እውነቶች አሉ፡፡ እነዚህ መላዕክት በሰማያዊ ስፍራ ቢኖሩና ለዚህ ምስጢር በምድር ካለን ከሰው ልጆች ይልቅ ቅርብ ቢመስሉም እንኳ፣ እግዚአብሔር ምስጢሩን ሊገልጥላቸው የወደደው በእኛ በኩል መሆኑን በመገረም እናስባለን፡፡ እነዚህ መላዕክት፣ አይሁድና አሕዛብ በአንድነት የሚወርሱትን መዳን (ሕይወት) እንደማይወርሱ ብናውቅም[171] እኛ ወራሾቹ ተስፋውን በሙላት ለመያዝ ወደ ሰማያዊቱ ኢየሩሳሌም ስንገሰግስ እኛን ለመቀበል እዕላፋት ሆነውና በጽዮን ተራራ በደስታ ተሰብስበው እንደሚጠባበቁን የዕብራውያን መልእክት ፀሐፊ ይነግረናል፡፡[172] እነዚህን መላዕክት አናያቸውም፡፡ እነርሱ ግን እንደሚያዩንና ሕብረታችንን፣ ፍቅራችንን፣ አምልኮአችንን እየተመለከቱ የእግዚአብሔርን ጥበብ እንደሚያደንቁ እንረዳለን፡፡ የሚያደንቁትም ጥበብ፣ እርስ በርሳችን ያለንን የመንፈስ አንድነት ብቻ ሳይሆን፣ አንድ አካል ሆነን በአንድ መንፈስ በክርስቶስ *ሥራ* በመታመንና በድፍረት ወደ አብ መግባታችንን ነው፡፡ (ቁ.12) ይህንን እያዩ መደነቅና ለእግዚአብሔር ክብር መስጠት የእነርሱ ምርጫ ብቻ ሳይሆን፣ እግዚአብሔር *"በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን የፈፀመው የዘላለም አሳብ ነበር"* (ቁ.11) ጴጥሮስ በአንደኛው መልዕክቱ እንደጠቀመው መላዕክቱ ይህን የሚያዩት ተገደው ሳይሆን ሲመኙት የኖሩት የውስጥ ፍላጎታቸው ምላሽ ነው፡፡[173]

እንደ ቤተክርስቲያን ራሳችንን ስንመለከት ለመላዕክት ይቅርና ለመንገደኛ እንኳ ለመታየት የሚማርክ ምን ነገር አለን? ብለን ለመጠየቅ መገደዳችን አይቀሬ ነው፡፡ ነገር ግን ዓይናችን ተከፍቶ ከሚታየው ባሻገር ብንመለከት፣ እንደ ዮሴፍ በኅብረ-

[171] ዕብ. 1፡14
[172] ዕብ. 12፡22
[173] 1ጴጥ. 1፡12



For more books www.amharicchristianbooks.com

ቀለማት ያሸበረቀ የእግዚአብሔርን ጥበብ እንደለበስን ማየት እንችላለን፡፡[174] ይህም መላዕክት ብቻ ሳይሆኑ ጌታ ራሱ የሚናፍቀውና ሊቀርበው የሚፈልገው መንፈሳዊ ውበት ነው፡፡ (5፡27) ይህን ውበት ዛሬ ለመላዕክት ቢያሳይም በሚመጣው ዘመን ግን ለፍጥረቱ ሁሉ ሊያሳይ ቀጠሮ ሰጥቷል፡፡ (2፡6) እግዚአብሔር ክብሩን ለሰው ልጆች የገለጠው በአሮጌው ፍጥረት በዩኒቨርስ ነበር፡፡[175] አሁን ግን ለመላዕክት ክብሩን ሊገልጥ የወደደው በአዲሷ ፍጥረት በቤተክርስቲያን በኩል ሆነ፡፡[176]

ይህን የመገለጥና የመግለጥ ትዕይንት ጆን ማኬይ የተባለው ጸሐፊ በተውኔት ገቢር መስሎ ባሰፈረው ጽሑፍ ልቋጭ፡-

> "ታላቅ ተውኔት በመተወን ላይ ያለ ይመስላል፡፡ ዓለም መድረክ ሆና፣ ታሪክ ተውኔት ሆኖ በየሥፍራው ያሉ የቤተክርስቲያን አካላት ሁሉ መሪ ተዋንያን ሆነው ይጫወታሉ፡፡ እግዚአብሔር የተውኔቱ ፀሐፊ ሲሆን ደራሲና አዘጋጁም ራሱ ነው፡፡ ገቢር በገቢር፣ ትዕይንት በትዕይንት ታሪኩ እየተተነተነ ይቀጥላል፡፡ የልዕለ ዓለም ኃያላን በሰማያዊ ሥፍራ ያሉ አለቆችና ስልጣናት ተውኔቱን ለመመልከት ታድመዋል፡፡ የእግዚአብሔርን የማዳን ተውኔት በተመስጦ ይመለከታሉ፡፡ በዚህም ዓይነት የዘመናት የቤተክርስቲያናት ታሪክ ለመላዕክቱ የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት ሆኖላቸዋል፡፡"[177]

## ምልጃ

ፀሐፊው በታሰረበት የግዞት ቤት ውስጥ በታላቅ አክብሮትና መገዛት በጉልበቱ ተንበርክኳል፡፡ አባቶቹ ለፀሎት በእግዚአብሔር ፊት ሲቀርቡ ልማዳቸው መቆም ቢሆንም እንኳ እርሱ ግን ይህን ታላቅ ምልጃ ቆሞ ሊያቀርብ አልወደደም፡፡[178] ይልቅ የቀደሙት ነቢያት በታላቅ መነካትና የምልጃ መንፈስ ውስጥ ሲሰጥሙ እንደሚያደርጉት በጉልበቱ ተንበርክኮ ይማልዳል፡፡[179]

የልቡ ጩኸት፣ የሚጽፍላቸው አሕዛብ አማኞች በክርስቶስ የተሰጣቸውን በረከት በእምነት እንዲያዩ፣ አዕምሮአቸው ተከፍቶ እንዲያውቁና በመሢሁ ካመኑ

[174] ዘፍ. 37፡3
[175] መዝ.(19)፡1; ሮሜ 1፡19-20
[176] John Sttot, p. 124.
[177] Mackay, John p.84
[178] ማር. 11፡25; ሉቃ. 18፡11,13
[179] ዕዝራ 9፡5; ዳን. 6፡10



For more books www.amharicchristianbooks.com

አይሁዶች ጋር በአንድ መንፈስ በመተባበር ያዩትን እንዲወርሱ ነው፡፡ በ 3፡1 ላይ *"ስለዚህ አሕዛብ ስለሆናችሁ ስለ እናንተ የክርስቶስ ኢየሱስ እስር የሆንሁ እኔ ጳውሎስ ለእግዚአብሔር እንበረከካለሁ፡፡"* በማለት ጀምሮት የነበረውን የምልጃ ዘገባ በእርሱ በኩል ለአሕዛብ የተገለጠውን የምስጢር ሥርዓት መተረክ በመምረጡ ምክንያት ለጥቂት ጊዜ ገትቶት ይቆይና ከቁጥር 14 በመነሳት እስከ ቁጥር 19 ድረስ በሚያስገርምና በሌሎች መልዕክቶቹ አቻ በማይገኝለት መልኩ ምልጃውን ይቀጥላል፡፡ የፀሎቱ አቅጣጫ አማኞች በውስጣቸው ባደረው በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት የውስጥ ሰውነታቸው በኃይል እንዲጠነክርና ከዚህም የተነሳ ክርስቶስ በውስጣቸው እንደሚኖር ያላቸው እምነትና መረዳት እንዲጨምር ፤(3፡15-16) ክርስቶስ በውስጣቸው መኖሩን ከመለማመድ ባሻገር በሰው አዕምሮ ታውቆ ሊያልቅ የማይችለውን የዘላለማዊ ፍቅሩን ደርዝ ከቅዱሰን ሁሉ ጋር ለማወቅ በመትጋት (18) ወደ እግዚአብሔር ፍፁም ሙላት እንዲደርሱ ማገዝ ነው፡፡ (19) የዚህ ክፍል አፃፃፍ እምብዛም ያልተለመደ ከመሆኑ የተነሳ በቀላሉ ለመፍታት የሚያስቸግሩ ሁለት ስንኞች በውስጡ አዝሏል፡፡ (ቁ.14 እና 18) ሁለተኛውን (ቁ.18) በተራው የምንመጣበት ስለሚሆን ለአሁኑ ቁጥር አሥራ አራትን ወደ ማየት እንለፍ፡፡

ጳውሎስ ወደ ማን እንደሚማልድ ሲገልጽ፡- *". . . በሰማይና በምድር ያለ አባትነት ሁሉ ከሚሰየምበት ከአብ ፊት እንበረከካለሁ፡፡"* ብሎአል፡፡ ለመሆኑ ይህ በሰማይና በምድር ያለ አባትነት ምንድነው? ከአብ የሚመነጨው ስያሜስ ምንድነው? የኤፌሶን መልዕክት የአብን አባትነት በሚገባ አጉልቶ የሚያሳይ መልዕክት ነው፡፡ (1፡2፤3፤17 ፤ 2፡18፤ 4፡6፤ 5፡20፤ 6፡23) አብ የፍጥረት ሁሉ ወጣኝ፣ የሁሉ ፈጣሪ፣ የሁሉ መጋቢ፣ የሁሉ ዳኛና የሁሉ ባለቤት ነው፡፡ ነገር ግን ይህ የሁሉ አባትነቱን አያሳይም፡፡ «አባ» የአረማይክ ቃል ሲሆን ፍቺውም የሕይወት ምንጭነትን ያሳያል፡፡[180] የሕይወት ዝምድና የሌላቸው «አባ» ብለው ሊጠሩ አይችሉም፣ ቢጠሩም አያምርባቸውም፡፡ በአገራችንስ "ያልወለድኩት ልጄ አባ፣ አባ ቢለኝ፣ አፌን ዳባ፣ ዳባ አለኝ" ይባል የለ? ምንም እንኳ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ጥቂት ቦታ እግዚአብሔርን እንደ አባት ቢጠቅሱም በዋነኝነት በአይሁዳውያንም ሆነ በአሕዛብ ዘንድ አምላክን የሚፈራና የማይቀረብ መለኮት እንጂ አባት አድርጎ መመልከት ያልተለመደ ነው፡፡ ይህን ትምህርትና ልምምድ ለመጀመሪያ ጊዜ በጉልህ ያንፀባረቀው ራሱ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡

[180] Gerald F. Hawthorne, Ralph P. Martin, Daniel G. Reid; Dictionary of Paul and his Letters. P. 357



For more books www.amharicchristianbooks.com

የአዲስ ኪዳን ገፆች በግልፅነት እንደሚያሳዩን ከጥንት ከዘላለም እግዚአብሔር አብ "የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባት" ነው፡፡ (1፡3) ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስም "አንድያ ልጁ" ነው፡፡ (ዮሐ. 1፡18) ነገር ግን ከኢየሱስ ክርስቶስ የማዳን ሥራ የተነሳ አብ ልጆቹ አደረገን፣ በዚህም የወልድ ብቻ የነበረውን የልጅነት ክብር ተካፈልን ፤(ዮሐ. 17፡22) ስለዚህ አሁን አብ የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ አባት ብቻ ሣይሆን፣ የእኛም አባት ሆኖአል፡፡ (1፡2) ጌታም ብዙ ልጆች በመወለዳቸው ምክንያት አንድያ ልጅነቱ እንደ ተጠበቀ ሆኖ በወንድሞቹ መካከል በኩር ሆኖአል (ሮሜ 8፡29)፡፡ ሌላው ፍጥረት ግን በዚህ መልዕክት ውስጥ በተደጋጋሚ የተጠቀሱትን መላዕክት ጨምሮ (1፡21 ፣ 3፡10፣ 6፡12) ይህን ልጅነት አልተካፈሉም፡፡ (ዕብ. 1፡4፣5፣14) ሆኖም በዘመን መጨረሻ ሁሉ በክርስቶስ መንፈስ በሚጠቀለልበትና የእግዚአብሔርን ሕይወት በሚካፈልበት ጊዜ እግዚአብሔር የሁሉ አባት ይሆናል፡፡ (4፡6)

ስለዚህ አሁን የእግዚአብሔርን አባትነት ስናነሳ አባትነቱ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስና በእርሱ *ሥራ* መንፈሱን በተካፈሉት ዘንድ ብቻ የተወሰነ እንደሆነ ለማሰብ እንገደዳለን፡፡ በርግጥ በዚያን ዘመን የነበረው አባትነት በተለይም በጌቶችና በባለጠጎች ቤት ውስጥ የነበረውን ሥርዓት ስንመለከት፣ የተወለዱ ልጆች ብቻ ሣይሆኑ ወንዶችና ሴቶች ባሮች ከእነርሱም የሚወለዱ ልጆች እንደ ቤተሰብ ስለ ሚቆጠሩ በቤቱ አባ ወራ አባትነት ውስጥ መጠራታቸው የተለመደ ሁኔታ ነበር፡፡ ከዚህ በመነሳት መላዕክትም አገልጋይ እንደ መሆናቸው መጠን በእግዚአብሔር አባትነት ስም የሚጠሩ የአንድ ትልቅና ዘላለማዊ ቤተሰብ አባል መሆናቸው ሊካድ አይችልም፡፡ ነገር ግን የዚህ ክፍል አከራካሪነት በዚህ አይወሰንም፡፡ የቋንቋው ሊቃውንት "አባትነት" እና "ቤተ-ሰብ" የሚሉት ሁለት የግሪክ ቃላት ተመሳሳይነት ስላላቸው የትርጉም አሻሚነት ፈጥረዋል ይላሉ፡፡ በግሪክ ቋንቋ አባት "ፓተር" ሲሆን፣ ቤተሰብ ደግሞ "ፓትሪያ" ነው፡፡[181] ስለዚህም *"በዚህ ምክንያት በአብ ፊት እንበረከካለሁ፣ ከእርሱም በሰማይና በምድር ያለ ቤተሰብ ሁሉ ስያሜ ያገኛሉ፡፡"* (አፅንኦት ከራሴ) የሚለው የአዲሱ መደበኛ ትርጉም የተሻለ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

ይህ "በሰማይና በምድር ያለ ቤተሰብ ሁሉ" ምንድነው? የመልዕክቱ ዋና አሳብ እንደሚያስገነዝበን የሰው ልጅ በአፈጣጠር ደረጃ ከአዳም የተገኘ አንድ ቤተሰብ ቢሆንም፣ (ሐዋ. 3፡25)[182] ለዘመናት የእስራኤል ቤት እና የአሕዛብ ቤት በመባል ተለያይቶ ኖሮአል፡፡ አሁን ግን እግዚአብሔር በክርስቶስ ኢየሱስ ከሠራው ሥራና ከተገለጠው ምስጢር (3፡5) የተነሳ ከሁለቱ የተለያዩ ቤተሰቦች ውስጥ በወንጌል

[181] Sttot, John R W Ephesians p. 133
[182] ግሪኩ "የምድር ቤተሰቦች ሁሉ" ይለዋል፡፡ World Bible commentary p.202 p.2



For more books www.amharicchristianbooks.com

ያመኑት አንድ ቤተ ሰብ ሆኑ፡፡ (2፡19) ስለዚህ አይሁድ ቢሆን አሕዛብ፣ የተገረዘ ቢሆን ያልተገረዘ፣ አረማዊ ቢሆን እስኩቴስ፣ ባሪያ ቢሆን ጨዋ፣ በክርስቶስ አንድ ቤተሰብ ሆኖአል፡፡ (ቆላ. 3፡11) በሰማይና በምድር የሚለውም ጆን ስቶት አሳምረው እንደ ከሸኑት በምድር ያለችው "ወታደራዊቷ" ቤተክርስቲያንና በሰማይ በዕረፍት ያለችው "ድል ነሺዋ" ቤተክርስቲያን" በሥጋ ሞት ተለያይተው ነገር ግን በአንድ መንፈስ፣ አንድ ቤተ ሰብ ሆነው በአንድ አባት ስም መጠራታቸው ነው፡፡[183]

ስለዚህ የሐዋርያው የምልጃ ግብ በማያሻማ መልኩ ተቀምጧል፡፡ ቀደም ሲል በ1፡15-23 ያቀረበው ምልጃ ዋና ትኩረቱ እነዚህ ከአሕዛብ ወገን የሆኑ አማኞች በጥበብና በመገለጥ መንፈስ ተሞልተው፣ የልብ ዓይኖቻቸው በርተው፣ የተሠራላቸውን፣ የተሰጣቸውንና አሁን በእጃቸው ያለውን መንፈሳዊ እውነት እንዲያውቁ መለመን ነበር፡፡ በዚህ ክፍል ውስጥ አንባቢያኑ እንዲያውቁ የፈለገው እውነት በ 1፡15-23 ላይ ከሰፈረው ለየት የሚያደርጉት ሁለት ባሕሪያት አሉት፡፡ አንደኛው ቀደም ሲል ያተኮረው "ኃይል" ላይ ነበር፡፡ *". . . ለምናምንም ከሁሉ የሚበልጥ የኃይሉ ታላቅነት ምን እንደሆነ ታውቁ ዘንድ ነው፡፡"* (ቁ.19) በማለት፡፡ በዚህኛው የምልጃ ዘገባ ውስጥ ግን የማወቅ ትኩረቱ ከኃይል ወደ "ፍቅር" ሲሸጋገር እናያለን፡፡ ሌላው በዚህ ክፍል እንዲያውቁ፣ ለማወቅም እንዲበረቱ የተፈለገው የክርስቶስ ፍቅር ከመታወቅ የሚያልፍ መሆኑ ነው፡፡ ቀደም ሲል የክርስቶስን ባለጠግነት "ፍለጋ የሌለው"[184] "የማይመረመረው"[185] "ወሰን የሌለው"[186] "ጥልቅና ታላቅ የሆነውን"[187] በማለት እንደገለፀው ሁሉ በ3፡14 ፍቅሩን "ከመታወቅ የሚያልፍ" መሆኑን ለማሳየት ይጥራል፡፡ በዚህ ክፍል ስለ ኃይል አንስቷል ሆኖም ያነሳው እንደ ቀደመው ምልጃ ኃይሉ እንዲታወቅ ሳይሆን እንዲያሳውቅ ነው፡፡ *". . . ከመታወቅም የሚያልፈውን የክርስቶስን ፍቅር ለማወቅ ትበረቱ ዘንድ . . . "* ስለሚል፡፡ ይህም መንፈሳዊ ኃይል በመንፈሳዊ እውቀት ውስጥ ያለውን ሚና በጉልህ ያሳየናል፡፡ ለካ ለማወቅም ኃይል ያስፈልግ ኖሮአል?

ጳውሎስ በፊቱ የተንበረከከው "የክብር አባት" (1፡17) ለቅዱሳን አብያተ ክርስቲያናት "እንደ ክብሩ ባለጠግነት መጠን" እንዲሰጥ የሚለምነው ሁለት ተያያዥ ነገሮችን ነው፡-

[183] Sttot, John p. 133 p. 2
[184] የ1962 የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም
[185] የ2001 አዲሱ መደበኛ ትርጉም
[186] የ1988 ቀለል ያለ አማርኛ ትርጉም
[187] የ1985 ሕያው ቃል



For more books www.amharicchristianbooks.com

### 1. “በመንፈሱ በውስጥ ሰውነታችሁ በኃይል እንድትጠነከሩ ...”

በዚህ ስፍራ "የውስጥ ሰውነታችሁ" የተባለው፣ አስቀድሞ ሙት የነበረው (2፡1) በኋላም ከክርስቶስ ጋር ሕያው የሆነው (2፡5) እውነተኛ በሆነ ጽድቅና ቅድስና እንደገና በመፈጠር “አዲስ ሰው” የተባለው (4፡24) መንፈሳችን ነው፡፡ መንፈሳችን ሲወለድ በክርስቶስ ሕፃን ነው፡፡[188] ሕፃን ደግሞ ምንም አያውቅም፡፡ ነገር ግን ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በሚኖረው ኅብረት የሕይወትን ቃል እየተመገበ በኃይል ይጠነከራል፡፡ ጳውሎስም በአንደኛ ደረጃ የሚለምነው ይህንኑ ነው፡፡

### 2. “ክርስቶስ በልባችሁ በእምነት እንዲኖር”

የውስጥ ሰውነታችሁ የተባለው መንፈሳችን ሕይወት ከሆነው ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ያለው ኅብረት እየጠነከረ ሲሄድ፣ በጥቅሉ “ልብ” ብለን የምንጠራቸውን አሳባችንን፣ ስሜታችንን፣ ፈቃዳችንን እየተቆጣጠረ ይሄዳል፡፡ (4፡23) ያኔ ክርስቶስ በውስጣችን ስለ መኖሩ ያለን መረዳት ይጨምራል፡፡ መኖሩንም የምንረዳውም በእምነት ነው፡፡ እምነት የማናየውን የሚያስረዳ እንደ መሆኑ መጠን (ዕብ. 11፡1) የመንፈሳችን የስሜት ሕዋስ በሆነው በእምነት በኩል ክርስቶስ በልባችን እንደሚኖር ያለን እርግጠኛነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ ይሄዳል፡፡

በዚህ ክፍል ውስጥ በክርስቶስና በመንፈስ ቅዱስ መካከል ያለውን አንድነት መመልከት ግድ ይለናል፡፡ በርግጥ የጳውሎስ ጽሑፎች የሚታወቁት ክርስቶስን እና መንፈስ ቅዱስን በጣምራ በማየታቸው ነው፡፡[189] ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በሰማያት በአብ ቀኝ መሆኑን እናውቃለን፣ ነገር ግን በእርሱ ውስጥ ያለው፣ ከእርሱም የሚወጣው  መንፈስ በአማኞች ውስጥ ሲያድር የሕይወት መንፈስ እንደ መሆኑ መጠን በወጣበትና በገባበት መካከል የሕይወት ግንኙነት ይፈጥራል፡፡ ስለዚህ አንዱ በሁሉም ውስጥ፣ ሁሉም በአንዱ ውስጥ መኖር ይጀምራሉ፡፡[190] ይህም ኑሮ አካላዊ ሳይሆን ሕይወታዊ ነው፡፡ ስለዚህ መንፈሳችን በኃይል ሲጠነከር ክርስቶስ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት በልባችን እየኖረ እንደሆነ ከእምነት የሚገኝ እርግጠኝነታችን እየጨመረ ይሄዳል፡፡[191]

ይህ ጥንካሬና እምነት ለምን አስፈለገ? “ከቅዱሳን ሁሉ ጋር ስፋቱና ርዝመቱ

188 1ቆሮ. 3፡1፣ 4፡14
189 ሮሜ 8
190 ዮሐ. 15፡4-7
191 2ቆሮ. 5፡14-15



For more books www.amharicchristianbooks.com

ከፍታውም ጥልቀቱም ምን ያህል መሆኑን ለማስተዋል ከመታወቅ የሚያልፈውን የክርስቶስን ፍቅር ለማወቅ ትበረቱ ዘንድ ...።" (ቁ.18፣19) በማለት ይመልስልናል። ምክንያቱም ይህን ወሰን አልባና ባለብዙ ደርዝ ፍቅር፣ ለማወቅ ኃይልና ብርታት አስፈልጓል። ብዙዎቻችን ኃይልን ከድንቅና ከተዓምራት ጋር እንጂ ከ"ማወቅ" ጋር አዛምዶ ማየት አይመጣልን ይሆናል። ነገር ግን የምንጋደለው ሰውን በአለማወቅ ጨለማ ውስጥ ዘግተው ከሚገዙት ኃይላት ጋር በመሆኑ (6፡12) በሚበልጥ ኃይል ታግዘን ካላወቅን በስተቀር፣ በቀላሉ የሚታወቅ ነገር እንደሌለ ያስገነዝበናል። ለዚህ ነው፣ ከዚህ መልዕክት ጋር አብሮ በላከው የቈላስይስ መልዕክትጳውሎስ እንዲህ ያለው፡-[192]

> *". . . ለዚህም ነገር ደግሞ በእኔ በኃይል እንደሚሠራ እንደ አሠራሩ እየተጋደልሁ እደክማለሁ። . . . ስለ እናንተና በሎዶቅያ ስላሉት ፊቴንም በስጋ ስላላዩት ሁሉ እንዴት ያለ ትልቅ መጋደል እንዳለኝ ልታውቁ እወዳለሁና። ልባችሁ እንዲፅናና በፍቅርም ተባብረው በማስተዋል ወደሚገኝበት ወደ መረዳት ባለጠግነት ሁሉ እንዲደርሱ የእግዚአብሔርንም ምስጢር እርሱንም ክርስቶስን እንዲያውቁ እጋደላለሁ። የተሰወረው የጥበብና የዕውቀት መዝገብ ሁሉ በእርሱ ነውና።" ቆላ. 1፡29-2፡2*

በማለት፣ ሰዎች የእግዚአብሔር ምሳሌ የሆነው የኢየሱስ ክርስቶስ የክብሩ ወንጌል ብርሃን እንዳያበራላቸው ሃሳባቸውን አሳውሮ ከያዘው ከዚህ ዓለም አምላክ እጅ ነፃ ወጥተው በመገለጥ ብርሃን የክርስቶስን ፍቅር በጥልቀት እንዲያውቁ በኃይል እንደሚጋደል ይጽፋል።

የክርስቶስን ፍቅር ደርዝ ለመግለጽ የተጠቀመበት መንገድ፣ በዘመናት ውስጥ ለበርካታ የመጽሐፍ ቅዱስ ማብራሪያ ፀሐፍት አስቸጋሪ ሆኖ የኖረ አገላለፅ ነው። *"ስፋቱና ርዝመቱ፣ ከፍታውም፣ ጥልቅነቱም፣ ምን ያህል መሆኑን ለማስተዋል ከመታወቅ የሚያልፈውን . . . ።" (ቁ.18)*

ይህ አስደናቂ አገላለጽ ከጥበብ ጋር በተያያዘ በኢዮብ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኝ ከመሆኑ ውጭ፣ በሌላ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ውስጥ አቻ የለውም።[193] ምንም እንኳ በመካከለኛው ዘመን የነበሩ የኃይማኖት አባቶች ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል አራት አቅጣጫዎች ጋር በማያያዝ መስቀል ላይ የተገለጠው ፍቅር

[192] ኤፌ. 6፡22-22፣ ቆላ. 4፡7-9፣ 16
[193] ኢዮብ 11፡8-9



For more books www.amharicchristianbooks.com

ጥልቀቱ እስከ ሲኦል፣ ከፍታው እስከ ሰማይ፣ ስፋቱና ርዝመቱ ከምድር ዳር እስከ ምድር ዳር ፣ ሁሉን የሚደርስ፣ ሁሉን የሚያቅፍ መሆኑን የሚያሳይ ነው፤ ቢሉም ዘመናዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ተርጓሚዎች ደግሞ ጳውሎስ በጊዜው ሊል የፈለገው ይህን አይደለም በሚል ያጣጥሉታል፡፡ እነዚህ ዘመናዊ ተርጓሚዎች ሊሆኑ ይችላል ብለው የሚገምቱትን የተለያየ መላምት ቢጠቅሱም፣ ብዙዎቹ አንድ ድምዳሜ ላይ ስለማይደርሱ የሚሉትን መከተል አስቸጋሪ ይሆናል፡፡

በመሠረቱ ጳውሎስ *"የክርስቶስ ፍቅር ስፋትና ርዝመቱ ከፍታውና ጥልቀቱ . . . ከመታወቅ ያልፋል"* ሲል አውቆ ለመጨረስ ያስቸግራል ማለቱ እንጂ፣ ማወቅ አይቻልም እያለ አይደለም፡፡ እንዲያ ቢሆንማ *"ለማወቅ ትበረቱ ዘንድ"* ብሎ ባልማለደም ነበር፡፡ ይህ ፍቅር በአብ ልብ ውስጥ የሚፈልቅ[194] በወልድ ውስጥ በሥጋ ተገልጦ ለአለም የታየ፣[195] በአማኞች ልብ ውስጥ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት የሚፈስ[196] እርስ በርስ በሚኖራቸውም ጤናማ ግንኙነትና መልካም ሥራ የሚገለጥ የእግዚአብሔር ፍቅር ነው፡፡

በዘላለም ውስጥ ይህ የአብ ፍቅር የተንፀባረቀው በልጁ ላይ ብቻ ነበር፡፡[197] ልጁ ግን ሥጋ ለብሶ መጥቶ ስለ ሰው ልጆች ኃጢያት በመስቀል ላይ በመሞቱና ከሙታን በመነሳቱ ይህ ፍቅር ዳርቻው ሰፋ፡፡ አይሁድም፣ አሕዛብም እስከ ምድር ዳር ድረስ ያሉ ወገኖች ሁሉ የዚህ ፍቅር መዳረሻ ሆኑ፡፡ ይህ የፍቅር ወንዝ ከሰማይ ፈልቆ፣ ዓለምን አጥለቅልቆ በቅዱሳን ሁሉ ልብ አደረ፡፡[198] ስለዚህ ከሌሎች ቅዱሳን ሁሉ ጋር በመተባበር ካልሆነ በስተቀር ማንም በግሉ ይህንን ፍቅር አውቆ ሊጨርስ አይችልም፡፡

ማላጁ አሕዛብ ይህን ፍቅር እንዲያውቁ የሚማፀንበት ምክንያት አለው፡፡ ምክንያቱንም እንዲህ በማለት ገልጿል፡፡

1. **"የእናንተም ሥርና መሠረት በፍቅር ይፀና ዘንድ"**

*ሥርና መሠረት አንድ የጋራ ጠባይ አላቸው፣ ሁለቱም ከመሬት ወለል በታች የሚገኙ የማይታዩ ናቸው፡፡ ነገር ግን ሥርም ለዛፍ፣ መሠረትም ለሕንፃ የመቆም ምክንያት ናቸው፡፡ ሐዋርያው በዋነኛነት ትኩረት የሰጠው የሚጽፍላቸው አማኞች*

[194] 1ዮሐ. 4፡8
[195] 1ዮሐ. 4፡9፤ ሮሜ 8፡39
[196] ሮሜ 5፡5
[197] ዮሐ. 17፡24፤ ማቴ. 3፡17
[198] ሮሜ 5፡5



For more books www.amharicchristianbooks.com

ውጭያዊ ማንነት ሳይሆን፣ በሰው ፊት የማይታየው በሥርና በመሠረት የተመሰለው ውስጣዊ ማንነታቸው ነው፡፡[199]

ጳውሎስ ተግባራዊ ሕይወትን በሚዳስስበት በሚቀጥለው ክፍል (ከምዕራፍ 4 – 6) አማኞች በፍቅር እንዲመላለሱ ትዕዛዝ ሲሰጥ እንመለከታለን፡፡ ነገር ግን በሰው ፊት በግልጥ ስለሚታየው ኑሮአቸው ከመፃፉ በፊት፣ የሁሉ መሰረት የሆነው ውስጣዊ ሕይወታቸው በፍቅር እንዲፀና አስቀድሞ ያሳስባል፡፡ በውሥጣችን የሌለውን እናስመስል ይሆናል እንጂ በእውነት ልንኖረው አንችልም፡፡ ውስጣችን በፍቅር ሊፀና የሚችለው፣ ስፋቱና ርዝመቱ፣ ከፍታውም ጥልቅነቱም ምን ያህል መሆኑን ለማስተዋል ከመታወቅም የሚያልፈውን የክርስቶስን ፍቅር ስናውቅና ለማወቅም ስንበረታ ብቻ ነው፡፡ ይህ የሆነላቸው አማኞች በመልካም ቀን ብቻ ሳይሆን በብዙ መከራ ውስጥ ባለመናወጥ ፀንተው ይቆማሉ፡፡

## 2. “እስከ እግዚአብሔርም ፍፁም ሙላት ደርሳችሁ ትሞሉ ዘንድ” (ቁ.19)

የዚህ ምልጃ ዓላማ የክርስቶስን ፍቅር በማወቅ ማደግ ቢሆንም በዚህ ብቻ ተገድቦ አይቆምም፡፡ ግቡ እስከ እግዚአብሔር ፍፁም ሙላት ደርሶ መሞላት ነው፡፡ ይህ ሙላት በወንጌል ባመንን ጊዜ በተለማመድነው የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት የሚያከትም፣ የከዕለታት አንድ ቀን ጉዳይ ሳይሆን፣ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ በመሄድ ወደ ሙላት የሚያደርስ የዘወትር ልምምድ ነው፡፡[200] አስቀድሞ በእኔነት የተሞላን የራሳችን ሙላት ነበርን፤ አሁን ግን የእግዚአብሔር ሙላት፣ የክርስቶስ ሙላት፣ የመንፈስ ቅዱስ ሙላት እንድንሆን ተጠርተናል፡፡[201] ምክንያቱም በ 3፡19 "የእግዚአብሔር ሙላት"፣ በ 1፡23 "የክርስቶስ ሙላት"፣ በ 5፡18 ደግሞ የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ማደሪያ መሆናችን ተጠቅሷልና፡፡ አሁንም የክብር ጌታ የፍቅሩ መገለጫ እንሆን ዘንድ በመስቀሉ ሥራ እኔነታችንን እያስወገደ በእሱነቱ ይሙላን፡፡

ሙላት የኤፌሶንና የቈላስይስ መልዕክቶች ልዩ መገለጫ ነው፡፡[202] በ ኤፌ.1፡ 13 ላይ ያየነው የመንፈስ ቅዱስ መታተም የመዳናችን ወንጌል የሆነውን የእውነትን ቃል በሰማን ጊዜ የተከናወነ ነው፡፡ ይህም በርካታ አማኞች ስለ ሙላት ሲያስቡ ለአዲስ

---

[199] ቆላ. 2፡7

[200] 5፡18

[201] 3፡19፤ 1፡23

[202] ኤፌ. 1፡ 23; 3፡ 19; 4፡ 10; 13; 5፡ 18; ቆላ. 1፡ 19; 2፡ 9; 10; 3፡ 16



For more books www.amharicchristianbooks.com

ልደት የሆነውን የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ብቻ እንዲያስቡ አድርጓቸዋል፡፡ ነገር ግን በዚህም ሆነ በቆላስያስ መልዕክቱ ሙላትን በአላፊ ጊዜ በመጠቀም "ተሞልታችኋል" ያለው ጳውሎስ፣ በመቀጠል "ትሞሉ ዘንድ"[203] በማለት የጊዜ ግሡን ወደ አሁንና ወደ ወደ ፊት ይወስደዋል፡፡ በዳንን ጊዜ መንፈሳችን ከተካፈለው ሙላት ባሻገር፣ በሂደት የሚከናወን ቀጣይ ሙላት እንዳለ ይጠቁመናል፡፡ ይህም ሙላት እንደ መጀመሪያው ከመንፈሳችን ጋር ብቻ የተያያዘ ሳይሆን የነፍሳችን ዋነኛ መገለጫ ከሆነው ከአዕምሮአችን ጋር በጽኑ የተቆራኘ ነው፡፡ የአዕምሮአችን ዋና ሥራ ማወቅ ነው፡፡ አዕምሮአችን ከሥጋ ሕይወት እየተላቀቀ በመንፈስ ቅዱስ ሲወረስ፣በሰው አቅም ሊታወቅ የማይቻለውን የእግዚአብሔርን ምሥጢር እርሱም ክርስቶስን በማወቅ እየተሞላ ይሄዳል፡፡ ይህንንም የሚያረጋግጥልን ሐዋርያው *". . . ከመታወቅ የሚያልፈውን የክርስቶስን ፍቅር ለማወቅ ትበረቱ ዘንድ"* ካለ በኋላ ወዲያው በመቀጠል *"እስከ እግዚአብሔርም ፍፁም ሙላት ደርሳችሁ ትሞሉ ዘንድ"* ማለቱ ነው፡፡

ባመንን ጊዜ ያገኘነው ሙላት ፍፁም የሚሆነው ከመንፈሳችን ወደ አዕምሮአችን ተሻግሮ በዕውቀት ሲሞላን ነው፡፡ ስለዚህ በአዲስ ቋንቋ እንድንናገርና የተለያዩ ፀጋ ሥጦታዎችን እንድንለማመድ  በሚያደርገን በመጀመሪያው የመንፈስ ሙላት ላይ ቆመን ልንቀር አይገባንም፡፡ ይልቅ በጥበብና በመገለጥ መንፈስ እያደግን፣ በአዕምሮአችንም መታደስ እየተለወጥን፣ በክርስቶስ ዕውቀት ወደምንሞላበት የሕይወት ክልል ልናድግ ይገባል፡፡ ይህ ከዕለታት አንድ ቀን በመንፈሳችን የጀመረ ፣ አሁንም በነፍሳችን እየሰረፀ ያለ የእግዚአብሔር ሙላት፣ አንድ ቀን በሥጋችንም ይገለጣል፡፡ ሥጋችንም በመንፈስ ቅዱስ፣ በሕይወት ይሞላል፡፡ ያንንም ቀን ጳውሎስ የ "ቤዛ ቀን" በማለት ይጠራዋል፡፡[204] ይህም ቀን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፣ በአብ ክብር፣ በመላዕክት አለቃ ድምፅ፣ በብዙ ክብር ታጅቦ በምድር ላይ የሚገለጥበትና እኛም በሥጋ ከሙታን ተነስተን ወይም በቅፅበት አይን ተለውጠን ከእርሱ ጋር የምንከብርበት የሥጋችን ዳግም ልደት ቀን ነው፡፡

## ቡራኬ

ጳውሎስ ይህን በትምህርት (ዶክትሪን) ላይ የሚያተኩር ሰፊ ክፍል የሚደመድመው ለእግዚአብሔር ክብር በመስጠት ነው፡፡ ክብር የሚሰጠውም ከላይ የማለደውን ምልጃ ሰምቶ እንደሚመልስ በማመን ብቻ ሣይሆን

[203] ቆላ. 2፡ 9-10 እና ኤፌ. 4፡13 ን ያነፃፅሩ
[204] ኤፌ. 4፡ 30



For more books www.amharicchristianbooks.com

*"ከምንለምነው ወይም ከምናስበው ሁሉ ይልቅ እጅግ አብልጦ ሊያደርግ"* እንደሚቻለው በማወቅ ነው፡፡

ጳውሎስ ስለ እግዚአብሔር ኃይል ያለውን ጥልቅ መረዳትና ልምምድ ከፍ ብሎ ባሰፈራቸው እውነቶች መረዳት ይቻላል፡፡ ቀደም ሲል እግዚአብሔር ኢየሱስን ከሙታን ያስነሳበት፣ ከአለቅነት፣ ከስልጣንም፣ ከኃይልም፣ ከጌትነትም ሁሉ በላይ ከስምም ሁሉ በላይ ከፍ አድርጎ በቀኙ ያስቀመጠበት ኃይልና የብርታት ጉልበት ለምናምን ለእኛ እንደተሰጠንና በእኛም እንደሚሠራ ነግሮናል፡፡ (1፡19-21) በመቀጠልም ለተሰጠው ወንጌልን ለአሕዛብ የማድረስ ተልዕኮ ይህ ኃይል አብሮት እንደሚሠራ ተርኮልናል፡፡ (3፡7) በመጨረሻም ቅዱሳን በውስጥ ሰውነታቸው ጠንክረው የክርስቶስን ፍቅር ለማወቅ በሚያደርጉት ትጋት ፣ ይህ ኃይል በውስጣቸው እየሰራ ወደ እግዚአብሔር ፍፁም ሙላት እንደሚያደርሳቸው ጽፏል፡፡ (3፡16-19)

እንግዲህ ይህ መረዳት ነው *"በእኛ እንደሚሠራው ኃይል መጠን ከምንለምነው ወይም ከምናስበው ሁሉ ይልቅ እጅግ አብልጦ ሊያደርግ ለሚቻለው . . . ፡፡"* (ቁ.20) እንዲል ያስቻለው፡፡ እግዚአብሔር በቅዱሳኑ ሕይወት ውስጥ በሙሉ ኃይል በሥራ ላይ ነው፡፡ የማይሠራና ዝም ያለ በሚመስለን ጊዜ እንኳ ይሠራል፡፡ ኃይሉ የሚሠራው እርሱ የሚፈልገውን እንጂ እኛ የምንመኘውን ሁሉ ስላልሆነ እየሠራ ያለ ባይመስለን አይደንቅም፡፡ ነገር ግን በክርስቶስ ኢየሱስ አስቀድሞ የወሰነውን የዘላለም አሳብ እያከናወነ ነው (ቁ.11) የፈቃዱን ምክር እየፈፀመ ነው፡፡(1፡11) በሰማይና በምድር ያለውን ፍጥረት ሁሉ በአንድ ራስ ሥር የመጠቅለሉን ሥራ በትጋት እየሰራ ነው፡፡ ይህ ሥራ በምድር ላይ ጊዜውን ጠብቆ እንዲከናወንና ሁሉን ጠቅላ የምትገዛው መንግሥቱ ፈጥና ወደ ምድር እንድትመጣ ተግተን እንድንፀልይ ታዘናል፡፡[205] ሆኖም እግዚአብሔር የሚሠራውም በእኛ እንደሚሠራው ኃይሉ መጠን እንጂ፣ በእኛ አሳብና ልመና መጠን ተወስኖ እንዳልሆነ ልናውቅ ይገባናል፡፡ ሰው የሚለምነው ሊያስብ በሚችለው መጠን ነው፡፡ የሚያስበውም በሚያውቀው መጠን ነው፡፡ የእግዚአብሔር ሥራ ግን በራሱ የኃይል ችሎታ እንጂ ፣ በእኛ በማሰብ ብቃትም ሆነ፣ የመለመን ትጋት ላይ የተመሠረተ አይደለም፡፡ ለዚህ ነው ጸሐፊው ለዚህ ከሃሊ ኩሉ አምላክ "በቤተ ክርስቲያን በኩል፣ በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል እስከ ትውልዶች ሁሉ ድረስ ከዘላለም

[205] ማቴ. 6፡ 10



For more books www.amharicchristianbooks.com

እስከ ዘላለም ክብር ይሁን፡፡" (ቁ.21)[206] በማለት ቡራኬውን በ "አሜን" የሚዘጋው፡፡

ቤተክርስቲያን ከክርስቶስ ጋር ለእግዚአብሔር ክብር መገለጫነት መጠራቷ በእግዚአብሔር ዘላለማዊ ዕቅድ ውስጥ ምን ያህል ትልቅ ሥፍራ እንደተሰጣት ያሳያል፡፡ ይህም በቤተክርስቲያን የተገለጠ ክርስቶሳዊ ክብር በትውልዶች ሁሉና በዘላለም ውስጥ ሳይቋረጥ እየደመቀ እንደሚያበራ ለእግዚአብሔርም የሚገባውን ክብር እንደሚያመጣ ያሳየናል፡፡ በዚህም እግዚአብሔር ሁሉን ለክብሩ ምስጋና እንዳደረገ እርግጠኞች መሆን እንችላለን፡፡ (1፡6)

[206] ከቅደም ተከተል አኳያ ቤተክርስቲያንን ከክርስቶስ ቀድማ መፃፍዋ፣ ፀሐፊው እንዲህ ያሉ ነገሮችን ሲዘረዝር ከትንሽ ወደ ትልቅ የመሄድ ስልቱን የሚያሳይ ሊሆን ይችላል፡፡ (4፡4-6)



For more books www.amharicchristianbooks.com

# ክፍል ሁለት
# በርስት ላይ መመላለስ

ኤፌ. 4፥1 – 6፥9

## መግቢያ

> *“እንግዲህ በጌታ እስር የሆንሁ እኔ በተጠራችሁበት መጠራታችሁ እንደሚገባ ትመላለሱ ዘንድ እለምናችኋለሁ . . . ፡፡” 4፥1*

ጳውሎስ በአስተምሮ የተሞላውን የመልዕክቱን የመጀመሪያ ክፍል በ “አሜን” ዘግቶ ተግባራዊ ሕይወት ላይ የሚያጠነጥነውን አዲስ ክፍል በልመና፣ በብርቱ ማሳሰቢያና በመማፀኛ ቃል አሃዱ ይላል፡፡[207] ልመናውንም የሚጽፍላቸው ከአሕዛብ ወገን የሆኑ አማኞች፣ ለዘመናት ከተገዙለት የኑሮ ዘይቤ ወጥተው “ለተጠሩበት መጠራታቸው እንደሚገባ እንዲመላለሱ” ነው፡፡ ከዚህ አባባሉም ቀደም ሲል የፃፈውን ከምዕራፍ አንድ እስከ ምዕራፍ ሦስት ያለውን ክፍል፣ በአንድ ሐረግ ጨምቆ ማስቀመጡን እንረዳለን፡፡ ሐረጉም “የተጠራችሁበት መጠራት” የሚል ነው፡፡ የቀደሙት ምዕራፎች እግዚአብሔር አይሁድ፣ አሕዛብ ሳይል ሰውን ሁሉ መንፈሳዊ በረከት (1፥3) የክብር ባለጠግነት (1፥18) የኃይል ታላቅነት (1፥19) ወደሞላበት ዘላለማዊ ርስት (1፥ 11-13; 18) በፀጋው ብዛት፣ (1፥7) በቸርነቱ ስፋት (2፥7) በምህረቱ ባለጠግነትና በፍቅሩ ታላቅነት (2፥4) እንደጠራን (1፥17) የሚተርኩ ምዕራፎች ነበሩ፡፡ ዓላማቸውም ለጥሪው ምላሽ የሰጡ አማኞች ወደምን ዓይነት ርስት፣ በምን ዓይነት ተስፋ እንደተጠሩ ያውቁ ዘንድ ዓይናቸውን በመግለጥ ለጥሪው የሚመጥን ኑሮ እንዲኖሩ ማዘጋጀት ነው፡፡

በእነዚህ ክፍሎች የተተረከው ከፍ ያለው የእግዚአብሔር መጥራት ያልተገለጠለት ሰው፣ በሚቀጥሉት ክፍሎች የሰፈሩቱን በክርስቶስ ልክ የተዘጋጁትን የአዲሱ ፍጥረት የኑሮ ደረጃዎች ሊያሟላ አይችልም፡፡ ከዚህም የምንረዳው የክርስትና ሕይወት ከመታዘዝ በፊት ከእምነት፣ ከሥራ በፊት ከፀጋ፣ ከኑሮ በፊት ከማወቅ

---

[207] የአስተምህሮት መልዕክቱን ጨርሶ ወደ ተግባራዊ ክፍል ሲዘልቅ “እለምናችኋለሁ” በሚል የመማፀኛ ቃል መጀመሩ የተለመደ የጳውሎስ የአፃፃፍ ስልት ነው፡፡ ሮሜ 12፥1



For more books www.amharicchristianbooks.com

እንደሚጀምር ነው፡፡ “መጠራት” ሐዋርያው ጳውሎስ በሥጋ ለተገኘባቸው የእስራኤል ልጆች በደም ሥራቸው ውስጥ የሚሮጥ የሕይወት መዘወር እንጂ፣ ፈጽሞ እንግዳ ቃል አይደለም፡፡ እስራኤላዊነት የተመሠረተበት ንጣፍ ዓለት ከምድር ሕዝቦች ሁሉ ተለይተው መጠራታቸው ነው፡፡[208] ይህም መጠራታቸው ርስትን ከመውረስና በዚህ ርስት ላይ በእግዚአብሔር ሕግና ሥርዓት ከመመላለስ ጋር በጽኑ የተቆራኘ ነው፡፡

እግዚአብሔር አብርሃምን እንደ ግለሰብ ከከለዳውያን ዑር ሲጠራው፣ ያዕቆብን እንደ ቤተሰብ ከላባ ዘንድ ከሶሪያ ሲመልሰው፣ እስራኤልንም እንደ ሕዝብ ከግብጽ ምድር ሲጠራ፣ በቀጥታ የተናገራቸው ስለ ርስት ነበር፡፡[209] ለዚህ ነው እስራኤላውያን የወረሱት የከነዓን ምድር ለዘመናት “የተስፋው ምድር” እየተባለ ሲጠራ የኖረው፡፡

ጳውሎስ ግን ቀደም ሲል ባየናቸው ክፍሎች ጥላና ምሳሌ ስለ ሆነው የከነዓን ምድር ሳይሆን፣ እውነተኛ አካል ስለ ሆነው ከዘላለም ዘመናት በፊት በተስፋ ስለ ተሰጠው የክርስቶስ ሕይወት እየጻፈ ይህን ሕይወት ለመውረስ መጠራታችንን በስፋት ገልፆልናል፡፡ ይህም መጠራት በልጁ አማካይነት ከአብ ጋር በመንፈስ ወደሚሆን ሕብረት የመግባትና በክርስቶስ የምድር ኑሮ ወደ ተገለጠው የሕይወት ሙላት በመገስገስ የልጁን መልክ የመምሰል ጥሪ ነው፡፡[210] በእውነት ይህ ጥሪ ታላቅ ነው፡፡ የታወጀው ለታናናሾች ቢሆንም፣ ጥሪው ግን እጅግ ታላቅ ነው፡፡[211] ስለ ታላቅነቱ ለመግለጽ “ታላቅ” የሚለው ቃል በራሱ ምንኛ ያንስ ይሆን?!

የዚህ በረከት የሞላበት የሕይወት ጥሪ ተካፋይ መሆን በራሱ ወደር የሌለው ዕድል፣ ብጽዕናና መመረቅ ነው፡፡ ሆኖም ዕድል ብቻ ሳይሆን ታላቅ ኃላፊነትም መሆኑ ሊዘነጋ አይገባውም፡፡ ዓለም ሳይፈጠር አስቀድሞ በመንፈስ ቅዱስ የሚሆን የሕይወትን ርስት እንድንካፈል የመረጠን እግዚአብሔር፣ በዚህ ርስት ላይ የምንመላለስበትን የሕይወት ሥርዓት ያዘጋጀው ዓለም ሳይፈጠር በፊት ነው፡፡(1፡4; 2፡10) ከዚህ የኑሮ ሥርዓት ውጭ በዚህ ርስት ላይ መኖር የማይታሰብ ጉዳይ ነውና፡፡”

እግዚአብሔር የእስራኤልን ልጆች ከግብጽ ካወጣ በኋላ ለአባቶቻቸው እሰጣችኋለሁ ብሎ የማለላቸውን የተስፋይቱን ምድር ከማውረሱ በፊት በሲና

208 ዘፀ.19፡5-6
209 ዘፍ 15፡1; 28፡13-15; ዘፀ. 3፡7-8
210 1ቆሮ.1፡9; ሮሜ 8፡28-30
211 1ቆሮ.1፡28



For more books www.amharicchristianbooks.com

ተራራ ሕግን ሰጣቸው፡፡ የሕጉ ዓላማ ርስት አድርገው በሚገቡባት ምድር እንዴት እንደሚመላለሱ ማሳወቅ ነበር፡፡ ሕጉን ባይጠብቁ የሚገጥማቸው ፍርድ በግልጽ ተነግሯቸዋል *". . . በዚህ መጽሐፍ የተፃፉትን የዚህን ሕግ ቃሎች ሁሉ ታደርግ ዘንድ ባትጠብቅ . . . እግዚአብሔርም በጎ ያደርግላችሁ ዘንድ ያበዛችሁም ዘንድ ደስ ይለው እንደነበር እንዲሁ እግዚአብሔር ሲያጠፋችሁ ሲያፈርሳችሁም ደስ ይለዋል፡፡ ትወርሷት ዘንድ ከምትገቡባት ምድር ትነቀላላችሁ፡፡ እግዚአብሔር ከምድር ዳር እስከ ዳርቻዋ ድረስ ወዳሉ አሕዛብ ሁሉ ይበትንሃል፡፡" ዘዳ. 28፡58፣63*

ለእስራኤላውያን በረከት ማለት በተሰፋ በተሰጣቸው ርስት ላይ መመላለስ ሲሆን፣ ርግማን ደግሞ ባለመታዘዛቸው ጠንቅ ከርስታቸው ተነቅለው በአሕዛብ መካከል መበተን ነበር፡፡ ጳውሎስ የዚህ ምሣሌ እውነተኛነት ስለ ገባው በክርስቶስ አምነውና በመንፈስ ቅዱስ ታትመው የሰማያዊው ጥሪ ተካፋይ የሆኑትን አሕዛብ፤ እግዚአብሔር አስቀድሞ ባዘጋጀው የሕይወት ሥርዓት እንዲመላለሱ ይማፀናል፡፡

ርስትን ማወቅ ትልቅ በረከት ሲሆን በርስት ላይ መመላለስ ደግሞ እጅግ የላቀ በረከት ነው፡፡ ከዚህ ቀደም ለማየት እንደ ሞከርነው "መመላለስ" የሚለው ቃል በአይሁድ ኃይማኖታዊ ባሕል የተጠመቀ ቃል ሲሆን ፍቺውም፣ ለርስቱ የተመረጠው ሕዝብ በተቀደሰችው ምድር ላይ ሕግን እየጠበቀና እግዚአብሔርን እያመለከ የሚኖረውን የኑሮ ዘይቤ ያመለክታል፡፡ ጳውሎስም በክርስቶስ ኢየሱስ የሆነውን አዲሱን የመንፈስ ኑሮ ለመግለጽ ይህን ቃል መጠቀም መርጧል፡፡[212]

ተደራሲያኑ ከመዳናቸው በፊት በሞት አገር፣ በዲያቢሎስ የአገዛዝ ቀንበር ሥር፣ በሥጋ ምኞት የኖሩትን ኑሮ ". . . በዚህ ዓለም እንዳለው ኑሮ በማይታዘዙትም ልጆች ላይ አሁን ለሚሠራው መንፈስ አለቃ እንደ ሆነው በአየር ላይ ሥልጣን እንዳለው አለቃ ፈቃድ በፊት ተመላለሳችሁባቸው፡፡" 2፡2 በማለት ከገለጸ በኋላ በክርስቶስ ኢየሱስ ትንሳኤ ሕያዋን ሆነው፣ ከእርሱም ጋር በሰማያዊ ሥፍራ በመንፈስ ከከበሩ በኋላ ብርሃን በሞላበት በቅዱሳን ርስት እንዴት ሊኖሩ እንደሚገባ ሲያመለክት፡- "እኛ ፍጥረቱ (የእጆቹ ሥራዎች)[213] ነንና እንመላለስበት ዘንድ እግዚአብሔር አስቀድሞ ያዘጋጀውን መልካሙን ሥራ ለማድረግ በክርስቶስ ኢየሱስ ተፈጠርን፡፡" 2፡10 በማለት በዝግጅት ጥንታዊ፣ በመታወቅና በመተግበር

[212] 1ተሰ. 2፡12; 4፡1; 12; ገላ. 5፡16; ሮሜ 6፡4; 8፡4; 13፡13; 14፡15; 1ቆሮ.3፡3; 7፡17; 1ቆሮ.4፡2; 5፡7; 10፡2-3;12፡18; ፊሊ.. 3፡17;18; ቆላ.1፡10; 2፡6; 3፡7

[213] ኦርጂናሉ የግሪክ ቃልና ሁሉም የእንግሊዘኛ ትርጉሞች የቀድሞው አማርኛ "እኛ ፍጥረቱ ነንና" የሚለውን "የእጆቹ ሥራዎች ነንና" ይሉታል፡፡



For more books www.amharicchristianbooks.com

ግን አዲስ የሆነውን ለአዲሱ ፍጥረት የተመደበውን የመንፈስ ኑሮ መስፈርት አስቀድሞ ያሳያል፡፡ ይህንንም ብርሃን በምዕራፍ 2፡2 እና 10 በጥቂቱ ከፈነጠቀልን በኋላ አሁን በምናየው ከ 4፡1 እስከ 6፡9 ባለው ሰፊ ክፍል በሙላት ይዘረዝረዋል፡፡[214]

መንፈሳዊውን እውነታ ለማይረዱ ፍጥረታዊ ሰዎች ኑሯችን በአንድ አቅጣጫ ብቻ የሚታይ ነው፡፡ በሥጋ አካል በምድር ላይ የምንኖር ግኡዛን ነን፡፡ የልብ አይኖቻቸው ለበሩ ግን በሥጋ አካል በምድር ላይ መኖራችን እንዳለ ሆኖ በመንፈስ ዳግም ተወልደን በገባንበት በእግዚአብሔር መንግሥት የሕይወት ርስት ላይ የምንመላለስ ሰማያዊ ፍጥረታት ነን፡፡ የምንኖረውም በእግዚአብሔር ፊት ሲሆን(1፡4) በሰማያዊ ስፍራ ባሉት አለቆችና ስልጣናትም እንታያለን፡፡(3፡10) ኑሯችን ማንም የማያገባው የኛ የራሳችን ጉዳይ ሳይሆን፣ ከእግዚአብሔር ክብር ጋር በጽኑ የተቆራኘ የክርስቶስ ኑሮ ነው፡፡[215] ይህን ኑሮ እንደሚገባ ከኖርን ሽልማት[216]፣ ካልኖርን ደግሞ ፍርድና ቅጣት በፍጻሜ ይጠብቀናል፡፡[217] ምሳሌዎቻችን እስራኤላውያን ለተቀደሰችው ምድር በሚገባው በተቀደሰው ሥርአት ለመኖር እምቢ ባሉ ጊዜ ምድሪቱ እንደ ተፋቻቸው፣ እኛም ከሕይወት ርስት እንዳንተፋ በርስቱ ሥርዓት እንድንኖር እነሆ የሕይወት መንፈስ ሕግ ቀርቦልናል፡፡ ጳውሎስ በዚሁ ክፍል 5፡5 ላይ፡-

> *"ይህን እወቁ ሴሰኛም ቢሆን ወይም እርኩስ ወይም የሚመኝ እርሱም ጣዖትን የሚያመልክ በክርስቶስና በእግዚአብሔር መንግሥት ርስት የለውም"*

በማለት እንደ ጻፈው በሥርዓቱ ካልኖርን ከርስቱ እንነቀላለን፡፡ ርስቱን እንድናረክስና እንድናጎሳቁል እግዚአብሔር ፈፅሞ አይፈቅድም፡፡ ይህ ርስት እንደ ቀድሞው ምሳሌ መሬት ሳይሆን የዘላለም ህይወት የሆነው መንፈስ ቅዱስ ነው፡፡ እርሱም ለቤዛ ቀን የታተምንበት የርስታችን መያዣ ነው፡፡(1፡13; 4፡30) በእግዚአብሔር ዘንድ በመንፈስ ቅዱስ ቀልድ የለም፡፡[218] እግዚአብሔር ቀደም ሲል እንዳየነው የፀጋ፣ የቸርነትና የምህረት አምላክ ብቻ አይደለም ቀናተኛና የፍርድ አምላክ ነው፡፡[219] ርስታችን እንዲሆን የሰጠንን መንፈሱን እንድናሳዝን፣በማሳዘንም

[214] 4፡1;17; 5፡2;10;15
[215] ገላ.2፡20; 2ቆሮ5፡14;15
[216] 2ኛጢሞ4፡7
[217] 2ኛቆሮ5፡10
[218] ኢሳ. 63፡10-14
[219] ዘዳ. 4፡24; ዕብ10፡-26-29



For more books www.amharicchristianbooks.com

እንድንቀጥል አይፈቅድም፡፡ ይልቅ ለሕይወትና እግዚአብሔርን ለመምሰል የሚያስፈልገውን ሁሉ እንደ ሰጠን እያሰብን፣[220] በርስቱ ላይ ፍሬ እያፈራን፣ ከክብር ወደ ክብር እየተለወጥን፣ "ለተጠራንበት መጠራት እንደሚገባ"፣ "ለክርስቶስ ወንጌል እንደሚገባ"፣ "ለጌታ እንደሚገባ"፣ "ወደ መንግሥቱ ወደ ክብሩም ለጠራን ለእግዚአብሔር እንደሚገባ" ልንኖር ይጠብቅብናል፡፡[221]

ይህ ልመና ወይም ተማጽኖ የመጣው፣ ምቾት ካንደላቀቀው፣ ዝና ካሰከረው ወይም ስብከቱን ለማጣፈጥ ቃል ከሚመርጥ "አገልጋይ" ሳይሆን፣ የምሥራቹን ቃል ለአሕዛብ ለማድረስ ሲል በአይሁድ ተከሶ፣ ሠንሰለት ለብሶ፣ በሮም እሥር ቤት በመከራ ከሚጠበስ የሰማይ መልዕክተኛ ብዕር ነው፡፡ እነሆ! የመማፀኛ ጥሪው ይድረሰን!!

[220] 2ኛጴጥ1፡2

[221] ኤፌ. 4፡1; ፊሊ. 1፡27; 1ተሰ. 2፡11



For more books www.amharicchristianbooks.com

# ምዕራፍ ፺
# የመንፈስ አንድነትን መጠበቅ

ኤፌ. 4፡ 1 - 16

በቀደሙት ምዕራፎች (1-3) እግዚአብሔር ሁሉን ነገር ወደ አንድ ለማምጣት ያሰበውን አሳቡን፣ የመከረውን ምክሩን፣ እንዲሁም ለዘላለም እና ለዘመናት ምስጢር አድርጎ ይዞ የኖረውን ፈቃዱን ወደ ብርሃን የማውጣቱን ብሥራት ተመልክተናል፡፡ ይህንንም ተግባር ፈጽመው የተለያዩትን አይሁድንና አሕዛብን በአንድ አካል በማጣመር ጀምሮታል፡፡ ወዲያውም የአይሁድም የአሕዛብም ውቅር የሆነችውን ቤተክርስቲያን፤ ከሙታን ከተነሳውና በሰማያት ከከበረው ከክርስቶስ ጋር በማጣመር አዲስ የሰው ዘር ፈጥሮአል፡፡ (2፡11-22) ከዚያም አጽናፈ-ዓለሙን በሚያካትት መልኩ በሰማይና በምድር ያሉትን ሁሉ በአንድ አገዛዝ ሊጠቀልል ለዘመን ፍፃሜ ቀጠሮ ሰጥቷል፡፡ (1፡10) ከዚህም እርሱ ራሱ አንድ የሆነው እግዚአብሔር ሁሉን በአንድ ለመጠቅለል መነሳቱን በግልጽ እናያለን፡፡

ታዲያ ይህን ግዙፍ አሳብ ለመረዳት፣ ቀድሞ የእግዚአብሔር ብቻ የነበረውን፣ አሁን ወደኛም የዘለቀውን ዓላማ የራሳችን ለማድረግና ለዓላማው ለመኖር የምስጢሩ መፍቻ የሆነውን አንድ ቁልፍ ልናገኝ ይገባል፡፡ ቁልፉም ከአብና ከወልድ የሚመጣው፣ በወንጌል እውነት ባመኑ ሁሉ ውስጥ እንደ ወንዝ የሚፈሰው፣ በዘመን ፍፃሜም በአማኞች አካል በሙላት በመገለጥ የሚታየውንም የማይታየውንም ፍጥረት በሕይወት በማጥለቅለቅ ሁሉን አንድ የሚያደርገው፣ የአንድነት ምስጢር መንፈስ ቅዱስ ነው፡፡

መንፈስ ቅዱስ ራሱን የማያሳይ፣ አብንና ወልድን የሚያከብር፣ የሕይወትን ሚና የሚጫወት፣ ከወጣበት ሳይለይ የሚገባበት ውስጥ የሚያድር፣ አንድ ሆኖ ሁሉን አንድ የሚያደርግ ድንቅ የሥላሴ አካል ነው፡፡ የአብና የወልድ አንድነት ምስጢር፣ የአይሁድና የአሕዛብ አማኞች አንድነት ምስጢር፣ የክርስቶስና የቤተ ክርስቲያን አንድነት ምስጢር ወደፊትም በሰማይና በምድር ያሉ ሁሉ በአንድ የመጠቅለል ምስጢር፣ የማይታየው መሪ ተዋናይ መንፈስ ቅዱስ ነው፡፡ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ከምድር ወደ አብ ከመሄዱ አስቀድሞ ለመስቀል ሞቱ ሲዘጋጅ በደቀ መዛሙርቱ ፊት ወደ አብ የፀለየውን ፀሎት በጥሞና ብንመለከት ይህ ምስጢር ተገልጦ እናየዋለን፡፡ ሥጋ ለብሶ ወደ ምድር የመጣበት፣ በድካም የሚሞትበትና በኃይል የሚነሳበት፣ ክርስቶሳዊ ተልዕኮ የዘላለም ሕይወት የሆነውን መንፈስ ቅዱስን ሥጋ



For more books www.amharicchristianbooks.com

ለባሽ ለሆኑ ሰዎች መስጠት መሆኑን ከጠቀሰ በኋላ፣ እነዚህ መንፈስ ቅዱስን የሚቀበሉት አማኞች አብና ወልድ አንድ እንደ ሆኑ፣ አንድ እንዲሆኑ መለመኑ፣ በአማኞች ዘንድ እንዲኖር የተፈለገው አንድነት በመንፈስ ቅዱስ የሚሆን የአብና የወልድ (የሥላሴ) አንድነት እንደ ሆነና ያም አንድነት በሕይወት መንፈስ አማካይነት አንዱ በሌላው ውስጥ በመኖር የሚፈፀም መሆኑን በዮሐንስ 17 ውስጥ አስተምሮናል፡፡ ይህን አንድነት ለመረዳት የሕዝበ እስራኤል ታሪክ ጥሩ አብነት ሊሆነን ይችላል፡፡ የእስራኤል ልጆች ከ12 ነገዶች የተቀናጁ ናቸው፡፡ የወረሱትም የተስፋ ምድር እንደየነገዳቸው 12 ቦታ የተከፋፈለ ነው፡፡ ነገር ግን በአንድነት አንድ አምላክ ያመልካሉ፡፡ የሚያመልኩትም የሰላም መሠረት በሆነችው በኢየሩሳሌም[222] በዓመት ሦስት ጊዜ በመሰብሰብ ከየርስታቸው ያመጡትን ልዩ ልዩ በረከት በጋራ በመካፈል ነው፡፡[223] ይህም አንድነታቸው በእግዚአብሔር አንድነትና በርስቱ አንድነት ላይ የተመሠረተ መሆኑን ያስገነዝበናል፡፡ እኛም ልዩ ልዩ ብንሆንም ርስታችን የሆነው መንፈስ አንድ ነው፡፡ የመንፈስንም አንድነት መጠበቅ የርስታችን የሕይወት ሕግ ነው፡፡

አሁን ጳውሎስ ይህን ምስጢር መተረኩን ገትቶ ከተለያየ ዘር፣ ነገድ፣ ቋንቋ፣ ከተለያየ የኑሮና ማኅበራዊ መደብ የተሰበሰቡትን አማኞች በመንፈስ ቅዱስ ያገኙትን የሕይወት አንድነት እንዴት እንደሚጠብቁ ተግባራዊ ምክር መስጠቱን ይቀጥላል፡፡ በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተሰበሰቡትን ዓይነት ሰዎች፣ በዚያን ዘመን በየትኛውም መድረክ መሰብሰብ የማይቻል ነበር፡፡ በሃይማኖት ቢሆን በማኅበራዊ፣ በፖለቲካው ቢሆን በአገራዊ፣ በፍልስፍና ቢሆን በፆታዊ መድረክ፣ እንደ እነዚህ የተሰበጣጠረ ማንነት ያላቸውን ሰዎች በአንድነት ማስቀመጥ ፈጽሞ አይታሰብም፡፡ በቤተ ክርስቲያን ግን ተቻለ፡፡ ለዚህ ነው ጳውሎስ፡-

> *"በዚያም (በአዲሱ ሰው) የግሪክ ሰው፣ አይሁዳዊውም፣ የተገረዘም ያልተገረዘም አረማዊም፣ ባሪያም ጨዋ ሰውም መሆን አልተቻለም፡፡ ነገር ግን ክርስቶስ ሁሉ ነው በሁሉ ነው፡፡" ቆላ. 3፡11*

በማለት የፃፈው፡፡ ጳውሎስ በሰማያዊ ስፍራ ያሉት አለቆችና ስልጣናት ይመለከቱታል የሚለን ብዙና ልዩ ልዩ የእግዚአብሔር ጥበብ፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በቅዱሳን ኑሮ እየተገለጠ ያለው የመንፈስ አንድነት ነው፡፡ ይህም አንድነት ፈጽሞ ሊገናኙ የማይችሉ የኅብረተሰብ ክፍሎች በመንፈስ ሕይወት አንድ ሆነው፣

[222] «የሩሻላይም» የሚለው የዕብራይስጥ ቃል ትርጉም «የሰላም መሠረት» ማለት ነው፡፡
[223] ዘሌ. 23፡1-22;



For more books www.amharicchristianbooks.com

በልዩ ልዩ ፀጋ አሸብርቀው በአንድ ሃሳብ፣ በአንድ ንግግር፣ በአንድ ዓላማ ሲንቀሳቀሱ ማየት ነው፡፡ ይህም ትዕይንት፣ በዘመን ፍፃሜ በሰማይና በምድር ያሉትን ሁሉ በክርስቶስ በመጠቅለል አንድ ለማድረግ የታሰበው ሃሳብና የተጀመረው ሥራ በምንም ዓይነት የማይቀር መሆኑን ያስገነዝባቸዋል፡፡

ለዚህ ነው ጳውሎስ ቅዱሳን ይህን ኃላፊነታቸውን በመረዳት የመንፈስን አንድነት በመጠበቅ እንዲተጉ የሚያሳስባቸው፡፡ የመንፈስ አንድነትን እንዲፈጥሩ ሳይሆን እንዲጠብቁ፡፡ የመንፈስ አንድነት በክርስቶስ ኢየሱስ አምነን መንፈስ ቅዱስን ስንቀበል ተፈጥሯል እንጂ ወደ ፊት በእኛ ጥረት የሚፈጠር ጉዳይ አይደለም፡፡ ይህ አንድነት ሊጠበቅ የሚችለው በአማኞች መካከል ሰላም ሲኖር፣ ሰላማችን የሆነው ክርስቶስ በሞቱና በትንሳኤው ያመጣው ሰላም በመካከላችን ገዢና አለቃ ሲሆን ብቻ ነው፡፡ ይህንንም ጳውሎስ እንዲህ በማለት ይገልጻዋል፡-

> *"በአንድ አካልም የተጠራችሁለት ደግሞ የክርስቶስ ሰላም በልባችሁ ይግዛ . . . ፡፡" ቆላ. 3፡15*

ምንም እንኳ በሥጋ ብዙ ልዩነት ቢኖረንም በመንፈስ ግን በሕይወት ተሳስረናል፡፡ አንዳችን በሌላችን ውስጥ ሆነን እርስ በርሳችን እያንዳንዳችን የሌላው ብልቶች ሆነናል፡፡[224] ይህም የመንፈስ መተሳሰር የሚቋጠረው በሰላምና በፍቅር ነው፡፡ ሰላማችን ሲደፈርስ ማሰሪያው ላይ ውጥረት ይፈጥራል፣ ውጥረቱም በአንድ የገመደንን ቅዱሱን የእግዚአብሔርን መንፈስ ያሳዝናል፡፡ (4፡30) ስለዚህ በሰላም ማሰሪያ የመንፈስን አንድነት መጠበቅ ግድ ይላል፡፡ ይህም አንድነት ሊጠበቅ የሚችለው ከራሱ ከመንፈስ ቅዱስ በሚመነጭ፣ በአማኞች የዕለት ተዕለት ኑሮ ውስጥ በሚገለጥ የመንፈስ ፍሬ በሆኑ ባሕሪያት ነው፡፡

## የመንፈስን አንድነት መጠበቂያ ባሕሪያት

በደርግ ዘመን በኢትዮጵያ ውስጥ ከወታደሩ በቀር የትኛውም ሲቪል መሣሪያ እንዲታጠቅ አይፈቀድለትም ነበር፤ ነገር ግን አንዳንድ ባለ ሃብቶች "ንብረት መጠበቂያ" በሚል ርዕስ መሣሪያ እንዲታጠቁ የሚፈቅድ የሕግ ክፍተት ነበርና ከመንግሥት ፈቃድ አውጥተው የታጠቁ ባለ ሃብቶች እንደ ነበሩ አስታውሳለሁ፡፡ ይህን ያለፈ ታሪክ ማንሳት የፈለግሁት "ሃብት መጠበቂያ የሚለው" መሣሪያ የመታጠቂያ ምክንያት ትኩረቴን ስለሳበው ነው፡፡ ቤተ ክርስቲያን ሃብት አላት፡፡ ነገር ግን ሃብቷ በካዝና ያስቀመጠችው ገንዘብ ወይም የገነባችው ሕንፃ ሳይሆን

[224] ሮሜ 12፡4-5



For more books www.amharicchristianbooks.com

የመንፈስ አንድነቷ ነው፡፡ ሃብት ባለበት ደግሞ ሌባ ማንዣበቡ አይቀርምና ሃብት መጠበቂያ መሣሪያ መታጠቅ ግድ ይላል፡፡

### ትህትና

> *"በትህትና ሁሉና በየዋህነት በትዕግስትም እርስ በእርሳችሁ በፍቅር ታገሱ፡፡" (ቁ.2)*

በዘመኑ የግሪኮ-ሮማን ዓለም በንቀት የሚታየው የ "ትህትና" ባሕሪ ዛሬም በብዙ ሥፍራ ተመሳሳይ እጣ ይገጥመዋል፡ ትሁት መሆን ደካማ መሆን፣ በራስ አለመተማመንና፣ የራስን መብት ማስከበር ያለመቻል አቅመ-ቢስነት ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ በትክክል ለተረዳው ግን ትህትና አግባብ ባለው መንገድ ራስን የመረዳትና ለራስ ትክክለኛ ሥፍራ የመስጠት አመለካከት ነው፡፡ ይህም አመለካከት በእውነተኛ ብርሃን ራስን በመመርመር፣ የእግዚአብሔር ፀጋና የወንድሞችና የእህቶች ድጋፍ የሚያስፈልገን፣ በራሳችን ሙሉ ያልሆንን ደካሞች መሆናችንን የምናጤንበት የጠለቀ ስሜት ነው፡፡ ትህትና ከስሜትነትም ባለፈ፣ ስለ ራሳችንም ሆነ በዙሪያችን ስላሉ ሰዎች ካለን ጤነኛ ግምትና አስተሳሰብ የሚልቅ የአእምሮ ፍሬ ነው፡፡ ትህትና በትዕቢት ያበጠን ልብ ለመሸፈን በአንደበት የሚዠጎደጎድ ከግብዝነት የሚፈልቅ የቃላት ብዛት አይደለም፤ ይልቅስ የሆንነውን የሆንነው ከእግዚአብሔር ፀጋ የተነሳ እንደ ሆነ በመረዳት፣ አእምሮአችን የትዕቢትን ነገር እንዳያስብ እየከለከልን፣ ባልንጀሮቻችንን ከእኛ ይልቅ እንዲሻሉ እየቆጠርን፣ ከራሳችን በፊት ለእነርሱ የሚጠቅመውን በማሰብ የምንመራው ኑሮ ነው፡፡[225]

ይህ ባሕሪ በክርስቶስ ኢየሱስ የተገለጠ የእግዚአብሔር ባሕሪ ሲሆን በክርስትና ሕይወት ውስጥ እጅግ አስፈላጊና የመንፈስን አንድነት ለመጠበቅ የሚያገለግል መሣሪያ ነው፡፡ ዘር፣ ቋንቋ፣ ባህል፣ የኑሮ ደረጃ የሠሩትን አጥር አልፈን በመጠጋጋት በምንኖርበት የቅዱሳን ሕብረት ውስጥ መብትን፣ ጥቅምን፣ ዝናን፣ ስምን፣ የሚነኩ ጉዳዮች መከሰታቸው ሳይታለም የተፈታ ጉዳይ ነው፡፡ ታዲያ ያኔ ትህትና አሳባችንን፣ ስሜታችንና ፈቃዳችንን ካልገዛ በቀር፣ ጠላት የሰላም ማሰሪያን በመበጠስ የመንፈስን አንድነት ለማጥፋት መንገድ ያገኛል፡፡

**የዋህነት** (gentleness)፡ - የመንፈስን አንድነት ለመጠበቅ ሌላው አስፈላጊ ባሕሪ ነው፡፡ ይህም ባሕሪ ከግል ስምና ዝና ይልቅ የጋራ ጥቅምን በማስቀደም የራስን መብት በፈቃደኝነት የመተው ተግባር ነው፡፡ የዚህ ባሕሪ መፍለቂያ የሆነው ጌታ

[225] ፊሊ. 2፡1-5; ሮሜ 12፡3



For more books www.amharicchristianbooks.com

ኢየሱስ ክርስቶስ የዋህ፣ በልቡም ትሁት እንደሆነ እርሱ ራሱ ነግሮናል፡፡[226] እኛም ከእርሱ ጋር በሚኖረን የሕይወት ሕብረት ይህ ባሕሪ የመንፈስ ፍሬ ሆኖ ይገለጥብናል፡፡[227] የዋህነት ጠብን በማግታት ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ለመኖር የሚያግዘን ብርቱ መሣሪያ ነው፡፡ ይህ ባሕሪ ከተለያየ ሥፍራ በመጡ የተለያየ ልማድና ፍላጎት ባላቸው ሰዎች ለተገነባች ቤተክርስቲያን የመንፈስ አንድነት ለመጠበቅ እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡

***ትዕግሥት፡***- ቤተ ክርስቲያን ከሰፊው ማኅበረሰብ ተጠርተው በወጡ አማኞች የተገነባች አነስተኛ ማኅበረሰብ ናት፡፡ ማኅበራዊ ኑሮ በርካታ ነገሮችን በጋራ ለመካፈል ተጠጋግቶ የሚኖርበት የኑሮ ዘይቤ ነው፡፡ ዛሬ ዛሬ ይህ ዓይነቱ የጋርዮሽ ኑሮ ገና በማደግ ላይ ያሉ አገሮች ቤተክርስቲያናትን ካልሆኑ በቀር፣ የምዕራቡን ዓለም ቤተክርስቲያን ሲያልፍም አይነካው፡፡ የመጀመሪያው ክፍለ ዘመን ቤተ ክርስቲያን ግን ማኅበረሰባዊነትን በሚገባ እንዳስመሰከረች የአዲስ ኪዳን ገፆች ያሳያሉ፡፡ በእንደዚህ ዓይነት ማኅበረሰባዊ ኑሮ ውስጥ ያለ ትዕግሥትና ያለ ልበ ሰፊነት በአንድነት መኖር ፈፅሞ አይታሰብም፡፡

***በፍቅር መታገስ፡***- በመቻቻል ለመኖር ዋናው ነገር ትዕግሥት ነው፣ ነገር ግን የትዕግሥቱ ዓይነት ወሳኝ ነው፡፡ ጸሐፊው በዚህ ሥፍራ የትዕግሥቱን ዓይነት አብራርቶ ለመግለጽ የፈለገ ይመስላል፡፡ ሰው ቁጣውን እያመቀ፣ ንዴቱን እየገታ፣ ሐዘኑን እያጠራቀመ፣ የተበደለውን እየቆጠረና የሚበቀልበትን ቀን እየጠበቀ ሊታገስ ይችላል፡፡ ይሄ ግን የበቀል ፈንጂ ለማምረት መዘጋጀት እንጂ ትዕግስት አይደለም፡፡ እውነተኛ ትዕግስት ከመቻል ይልቅ መረዳት፣ በደል ከመቁጠር ይልቅ ይቅር ማለት ላይ የሚያዘነብል የፍቅር ትዕግሥት ነው፡፡

ጳውሎስ በሌላ ክፍል በክርስቶስ አዲስ ፍጥረት የሆኑት ቅዱሳን፣ እነዚህን ባሕሪያት እንደ ልብስ እንዲጎናፀፉአቸው እንዲህ በማለት ይመክራል፡-

> ". . . ምህረትን፣ ርህራሄን፣ ቸርነትን፣ ትህትናን፣ የዋህነትን፣ ትዕግስትን ልበሱ እርስ በርሳችሁ ትዕግስትን አድርጉ፡፡ ማንም በባልንጀራው ላይ የሚነቅፈው ነገር ካለው ይቅር ተባባሉ፡፡ ክርስቶስ ይቅር እንዳላችሁ እናንተ ደግሞ እንዲሁ አድርጉ፡፡ በእነዚህም ሁሉ ላይ የፍፃሜ ማሠሪያ የሆነውን ፍቅርን ልበሱት፡፡"

[226]ማቴ. 11፡29

[227] ገላ. 5፡22



For more books www.amharicchristianbooks.com

## "ፍፁም አንድነት" ፡ - ሰባቱ የአንድነት ምሰሶዎች

እስራኤላውያን የመጨረሻው ዘመን መድረስ፣ የመሲሁ መምጣትና የአዲሱ ዘመን ጅማሬ ብሥራት አድርገው ከሚወስዷቸው ትንቢቶች መሃል አንዱና ዋነኛው በኢሳይያስ ትንቢት አሥራ አንደኛ ምዕራፍ ላይ የሰፈረው የተስፋ ቃል ነው፡፡[228] ይህ ክርስቶስ ከዳዊት ዘር ስለ መምጣቱ፣ ስለ መቀባቱና ስለ አስተዳደሩ የሚናገር ትንቢት ክርስቶስ በሚገዛበት ወቅት ስለሚከሰተው አስደናቂ ሥርዓት እንዲህ በማለት በምሳሌ ያመለክታል፡፡

> *"ተኩላ ከበግ ጠቦት ጋር ይቀመጣል፣ነብርም ከፍየል ጠቦት ጋር ይተኛል፣ ጥጃና የአንበሳ ደቦል፣ ፍሪዳም በአንድነት ያርፋሉ፣ ታናሽም ልጅ ይመራቸዋል፡፡ ላምና ድብ አብረው ይሰማራሉ፣ ግልገሎቻቸውም በአንድነት ያርፋሉ፣ አንበሳም እንደ በሬ ገለባ ይበላል፡፡ የሚጠባውም ሕፃን በእባብ ጉድጓድ ላይ ይጫወታል፣ ጡት የጣለውም ሕፃን በእፉኝት ቤት ላይ እጁን ይጭናል፡፡ በተቀደሰው ተራራዬ ሁሉ ላይ አይጎዱም፣ አያጠፉምም፣ ውሃ ባሕርን እንደሚከድን ምድር እግዚአብሔርን በማወቅ ትሞላለች፡፡" ኢሳ. 11፡6-9 (ኢ.መ.ት)*

በክርስቶስ አገዛዝ ውስጥ የሚሆነውን ይህን ልዕለ ተፈጥሮአዊ ትዕይንት ስንመለከት የሚመጣውን ዘመን በጉጉት እንድንጠብቅ ልባችን ይነሳሳል፡፡ ነገር ግን ይህ ትንቢት የወደፊት ተፈፃሚነት እንዳለው ብናስብም፣ በዋነኝነት ግን እንደ ተፈጸመ እርግጠኛ መሆን እንችላለን፡፡ ይህ አስደናቂ ትዕይንት የሚከሰተው እግዚአብሔርን ከማወቅ የተነሳ እንደ ሆነ ነቢዩ በመደምደሚያው ላይ "*በተቀደሰው ተራራዬ ሁሉ ላይ አይጎዱም፣ አያጠፉምም፣ ውሃ ባሕርን እንደሚከድን ምድር እግዚአብሔርን በማወቅ ትሞላለች*" በማለት ተናግሯል፡፡ ታዲያ እርሱን በማወቅ የሚሞሉትና የተፈጥሮ ባህሪያቸው የሚለወጠው እንሰሳትና አራዊት ናቸው? ወይስ ሰዎች? ከላይ የተጠቀሱት እንስሳትና አራዊት በተፈጥሮአቸው አብረው መኖር የማይችሉ ጠላቶች፣ በይና ተበይ፣ አጥፊና ጠፊ ናቸው፡፡ ልክ እንዲሁ አይሁድና አሕዛብ፣ ጌቶችና ባሮች፣ የተገረዙና ያልተገረዙ፣ አረማውያንና እስኩቴሶች አብረው መኖር የማይችሉ ጠላቶች ነበሩ፡፡ ነገር ግን እነዚሁ ሰዎች በክርስቶስ አምነው፣ አዲስ ፍጥረት ሆነው፣ እግዚአብሔርን በማወቅ ተሞልተው፣ በሕብረት መኖርና አንዱን አምላክ ማምለክ ጀመሩ፡፡ ታዲያ ከዚህ በላይ የትንቢት መፈፀም የት አለ?

---

[228] ኢሳ. 11፡1-10



For more books www.amharicchristianbooks.com

ይህ ትንቢት ስለ እንስሳትና አራዊት ሳይሆን ስለ ሰዎች ይልቁንም አሕዛብ በክርስቶስ ኢየሱስ ከአይሁድ ጋር ስለሚኖራቸው ሕብረት እንደሚናገር የምንረዳው በትንቢቱ መጨረሻ ላይ ለምሳሌው የተሰጠውን ትርጓሜ ስናነብ ነው፡፡

> *"በዚያም ቀን እንዲህ ይሆናል፣ ለአህዛብ ምልክት ሊሆን የቆመውን የእሴይን ሥር አህዛብ ይፈልጉታል ማረፊያውም የተከበረ ይሆናል፡፡" ኢሳ 11፡10*

ክፍሉ ከእንስሳትና ከአራዊት ተምሳሌት ይወጣና በግልፅ "*ለአሕዛብ ምልክት ሊሆን የቆመውን የእሴይን ሥር አህዛብ ይፈልጉታል*" ይላል፡፡

ዮሐንስ በራእይ መጽሐፉ፡-

> *". . . ታርደሃልና በደምህም ለእግዚአብሔር ከነገድ ሁሉ፣ ከቋንቋም ሁሉ፣ ከወገንም ሁሉ፣ ከሕዝብም ሁሉ፣ ሰዎችንዋጅተህ ለአምላካችን መንግሥትና ካህናት ይሆኑ ዘንድ አደረግሃቸው . . . ፡፡"* ዮ. ራእይ 5፡9-10

በማለት ባማረ ቅኔ እንዳስቀመጠው፣ የክርስቶስ ማኅበር በሆነችው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ፈፅሞ ሊገናኝ ከማይችል የተለያየ ሁኔታ የመጡ፣ ሕልቈ መሣፍርት የሌለው ልዩነት ያነገቡ ሰዎች በአንድነት መሰብሰባቸውን እናያለን፡፡ ከእነዚህም ልዩነቶች መካከል ጎልተው የሚታዩት የዘር፣ የቋንቋ፣ የባህል፣ የኑሮ ደረጃና የኃይማኖት ልዩነቶች ናቸው፡፡ እነዚህም ልዩነቶች በአማኞች የዕለት ተለት ግንኙነቶች ውስጥ በአስተሳሰብ፣ በንግግር፣ በእሴት፣ በቅድሚያ አሰጣጥ፣ በአለባበስ፣ በአምልኮ ቅርጽ ወዘተ . . . ይንፀባረቃሉ፡፡ ማንኛውም ሰው የጀርባ ማንነቱ እስረኛ እንደ መሆኑ መጠን ካደገበትና ከኖረበት አስተሳሰብና ልማድ ተላቆ በክርስቶስ ኢየሱስ ያለውን የአዲሱን ሰው መልክ እስኪላበስ ድረስ አብሮአቸው ከሚያመልካቸው አማኞች ጋር ልዩነት እንደ አሸን ይፈላበታል፡፡ ይህን ስንመለከት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ፍፁም አንድነት ይመጣል ብሎ ማሰብ ዘበት ይሆናል፡፡ ነገር ግን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ቆይታው የመጨረሻ ሰዓት ወደ አባቱ የፀለየውንና ዮሐንስ በወንጌሉ የዘገበውን ፀሎት በጥንቃቄ ስንመለከት የፍፁም አንድነት ተስፋ ይፈነጥቅልናል፡፡

> *"እኛም አንድ እንደ ሆንን አንድ ይሆኑ ዘንድ እኔም በእነርሱ፣ አንተም በእኔ ስትሆን በአንድ ፍፁማን እንዲሆኑ የሰጠኸኝን ክብር እኔ ሰጥቻቸዋለሁ፡፡" ዮሐ. 17፡22*

ይህ አባባል ውጪያዊ ልዩነቶቻችን እንዳሉ ሆነው ከማንነታችን የተነሳ ሳይሆን



For more books www.amharicchristianbooks.com

ከአብና ከወልድ ጋር እንዲሁም ከአማኞች ሁሉ ጋር በአንድ ካስተሳሰረን ከመንፈስ ቅዱስ የተነሳ ፍፁም የሆነና ወደ ፍፁምነት የሚያደርስ አንድነት እንዳለን ያበስረናል፡፡

የአንድነታችን መሠረት የእግዚአብሔር አንድነት ነው፡፡ የእስራኤል ልጆች በነገድና በድንበር አሥራ ሁለት ቦታ የተለያዩ ሆነው ሳሉ አንድነታቸው ለረዥም ዘመናት ተጠብቆ የኖረው አንድ አምላክ ከማምለካቸው የተነሳ ነበር፡ አንድ አምላክ፣ አንድ ምድር፣ አንድ ሕግ ያላቸው ሕዝብ ነበሩ፡፡ እስራኤልን ለሁለት ለመክፈል ሌላ አምላክ (ጣኦት) መፍጠር፣ ሌላ መሠዊያ ማበጀት የግድ ነበር፡፡[229]

የእግዚአብሔር አንድነት የተለያዩ አካላት የሆኑት አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ መሆናቸው እንደሆነ ሁሉ፣ የአማኞችም አንድነት የተለያዩ ሰዎች በአንድ የሕይወት መንፈስ ተሳስረው አንድ አካል መሆናቸው ነው፡፡ ስለዚህ የእግዚአብሔር አንድነት የሕዝቡ አንድነት መሠረት፣ የሕዝቡም አንድነት የእግዚአብሔር አንድነት መንፀባርቅ፣ መሆኑን እንረዳለን፡፡

ከዚህ በመነሳት ጳውሎስ በውጭ የሚታዩ ብዙ ልዩነቶች የሞሉበትን የአማኞች አንድነት አጽንተው የሚይዙ፣ የማይታዩ ሰባት ምሰሶዎች መኖራቸውን ይዘረዝርልናል፡፡ ቁጥራቸው ሰባት መሆኑም የታሰበበት ይመስላል፡፡ 7 ቁጥር በመላው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የፍፁምነት መግለጫ ቁጥር ነውና፡፡ ሌላውን ሁሉ ትተን በዮሐንስ ራእይ ውስጥ ብቻ ብንመለከት 7 ቁጥር 31 ጊዜ ተጽፎ እናገኘዋለን፡፡ በዚህም ክፍል “አንድ” የሚለው ቃል ሰባት ጊዜ ተደጋግሞ ተጽፏል፡፡ ይህም የ«አንድ» ሰባት ጊዜ መደጋገም በክርስቶስ የመጣው አንድነት ፍፁም መሆኑን ያመለክታል፡፡

ይህ ማለት በአማኞች መካከል ምንም አይነት ልዩነት አይፈጠርም ማለት አይደለም፡፡ አንድነታችን ልዩነት በሞላበት የተፈጠረ ነውና፡፡ ነገር ግን በአማኞች መካከል ሊፈጠሩ የሚችሉትን ልዩነቶች በሁለት ከፍለን ልናያቸው እንችላለን፡፡ "የሚለዩ ልዩነቶች" እና "የማይለዩ ልዩነቶች" በሚል፡፡ ሊለዩን በማይገቡ ልዩነቶች በመለያየታችን ሆነ፣ ሊለዩን በሚገቡ ልዩነቶች ባለመለየታችን በሁለቱም አቅጣጫ ልንጎዳ እንችላለን፡፡ ለእነዚህ ለሁለቱ ምሣሌ መስጠት ቢያስፈልግ ጳውሎስ በገላትያና በሮሜ መልእክቱ ያነሳቸውን በአይሁድና በአሕዛብ አማኞች መከከል የተፈጠሩ ልዩነቶችን ማንሳት እንችላለን፡፡ በገላትያ የክርስቶስ አገልጋዮች ነን የሚሉ አይሁድ፣ አሕዛብ ይፀድቁ ዘንድ መገረዝና ሕግን መጠበቅ እንዳለባቸው

---

[229] 1ነገሥት 12፡25-33



For more books www.amharicchristianbooks.com

አስተማሩ፡፡ ጳውሎስ ተቆጣ፡፡ ከእምነት ወደ ሕግ መመለስ መለያየትን የሚያመጣ ጉዳይ ነበርና እንዲህ ካሉት አስተማሪዎች እንዲለዩ አዘዛቸው፡፡[230] በሌላ ጊዜ በሮም ያሉ አሕዛብ፣ ያመኑት አይሁድ ለምን ሕግን ይጠብቃሉ? ለምንስ ቀናትን ያከብራሉ? ለምንስ በምግብ ይጠነቀቃሉ? በማለት ላነሱት የተቃውሞ ጥያቄ ጉዳዩ የማይለይ መሆኑን እንዲህ በማለት ገልጧል፡-

> *"በእምነቱ ደካማ የሆነውን ሰው <u>አከራካሪ በሆኑ ጉዳዮች</u> ላይ በአቋሙ ሳትፈርዱበት ተቀበሉት፡፡" ሮሜ 14፡1* ኢ.መ.ት (አጽንኦት ከራሴ)

ይህን ያለበት ምክንያት ሕግ አልባ ሆነው ኖረው በክርስቶስ በማመን የሕይወት መንፈስ ሕግ ለተሰጣቸው አሕዛብና ከልጅነታቸው አንስቶ ሕግን በመጠበቅ ለኖሩ አይሁድ ሕግን የመጠበቅ ጉዳይ አንድ አይነት ስላልሆነ ነው፡፡ ለአሕ ዛብ ከእምነት ማፈግፈግ፣ ከፀጋ መውደቅ ሲሆን ለአይሁዳውያን ግን ልማድን መፈፀም ብቻ ነው፡፡

በሌላ በኩል ሐዋርያው ዮሐንስ በስህተት ትምህርት ለተናወጡት በትንሿ እስያ ለሚገኙ አማኞች በጻፈው መልዕክት የገጠማቸው መለየት አግባብ እንደ ነበር በድፍረት እንደ ገለፀላቸው እናነባለን፡-

> *"ከእኛ ዘንድ ወጡ ዳሩ ግን ከእኛ ወገን አልነበሩም፣ ከእኛ ወገንስ ቢሆኑ ከእኛ ጋር ፀንተው በኖሩ ነበር ነገር ግን ሁሉ ከእኛ ወገን እንዳልሆኑ ይገለጡ ዘንድ ወጡ፡፡" 1ዮሐ. 2፡19*

ጳውሎስም ስለ ቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን የጌታ ራት ሥርዓት ሲጽፍ፡-

> *"ከሁሉ አስቀድሞ በቤተ ክርስቲያን በምትሰበሰቡበት ጊዜ በመካከላችሁ መለያየት እንዳለ ሰምቻለሁ ይህም ሊሆን እንደሚችል በከፊል አምናለሁ፡፡ <u>ከእናንተ መካከል እውነተኞቹ ተለይተው ይታወቁ ዘንድ ይህ መለያየት በመካከላችሁ መኖሩ ግድ ነው</u>፡፡" 1ቆሮ. 11፡18-19* (አጽንኦት ከራሴ)

እንዲያው ለምልክት ያህል እነዚህን አነሳሁ እንጂ ከእምነት እና ከተግባር አንፃር አንድ ልንሆንና ልንለይባቸው የሚገቡን ጉዳዮች በርካታ ናቸው፡፡ ከዚህም በመነሳት አንድ ያደረጉንን በየመንገዱም አንድነታችንን ልንፈትሽባቸው የሚገቡንን ሰባት የአንድነት ምሰሶዎች አንድ በአንድ ለማየት እንሞክራለን፡፡

**አንድ ተስፋ፡-** በዝርዝሩ መጀመሪያ ላይ የምናገኘው ጳውሎስ *"በመጠራታችሁ በአንድ ተስፋ እንደ ተጠራችሁ . . . ፡፡"* ቁ.4 በማለት የሚጠቅሰው አንድ ተስፋ

[230] ገላ. 6፡11-12 የገላትያ መልዕክት ሙሉውን ይህን ሃሳብ የሚያቀነቅን ነው፡፡



For more books www.amharicchristianbooks.com

ነው፡፡ ቀደም ሲል በ1፡18 ላይ "የመጥራቱ ተስፋ ምን እንዲሆን . . . ታውቁ ዘንድ" በማለትም ጽፏል፡፡ ይህ የእስራኤል ልጆች አስቀድመው ሲጠብቁት፣ አሕዛብ ግን ርቀውና እንግዶች ሆነው የኖሩበት አሁን ግን በወንጌል በማመን በአንድነት የሚካፈሉት አንድ ተስፋ[231] በክርስቶስ ጌትነት በማመን፣ በመንፈስ ቅዱስ በመጠመቅና፣ አንድ አካል በመሆን ከሁሉ በላይ የሆነውን፣ በሁሉ የሚሠራውንና በሁሉ የሚኖረውን አንድ አምላክ በማምለክ፣ የሚመጣውን ክብር የመጠበቅ ተስፋ ነው፡፡ ጳውሎስ በመግቢያው ላይ በግልጽ እንደ ፃፈልን አሁን በከፊል በመያዣነት የተሰጠን፣ ወደፊት ግን በሙላት የምንወርሰው፣ ወንጌልን በማመን ስንድን የታተምንበት የተስፋው መንፈስ፣ እርሱም መንፈስ ቅዱስ የሁላችንም ተስፋ ነው፡፡ ይህ ተስፋ እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ አማኝ በግል የሚሠጠው ተስፋ ሳይሆን አማኞች ሁሉ በአንድነት የሚካፈሉት፣ የሚኖሩበትና የሚጠብቁት ሁሉን አንድ የሚያደርግ የጋራ ተስፋ ነው፡፡ ይህ ተስፋ በውስጡ የተፈፀሙና የተወረሱ ነገሮች ቢኖሩትም የሚበዛው ክፍል ግን ገና የሚጠበቅና በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ቀን በሙላት የሚገለጥ ነው፡፡[232] በዚህ ተስፋ አንድ ካልሆንን፣ አንድ አይደለንም፡፡ ያለዚህ ተስፋ አንድነት የለምና!

**አንድ አካል**፡- ክርስቶስ በመንፈሱ በውስጣቸው አድሮ ራስ የሆናቸውን፣ ከአይሁድም ከአሕዛብም ወገን የሆኑ አማኞች አንድነት የሚያሳይ ተምሳሌታዊ መግለጫ ሲሆን፣ በሥጋ ሰውነት የተለያዩ፣ ነገር ግን አንድ አካል ይሆኑ ዘንድ በአንድ መንፈስ የተጠመቁና አንዱን መንፈስ በመጠጣት አንዳቸው የሌላቸው ብልቶች የሆኑ፣ በጅማትና በደም ሥር የተያያዙ እስኪመስሉ ድረስ በሚኖሩበት አካባቢ የክርስቶስን ሕይወት የሚገልጡ፣ ቤተ ክርስቲያን በመባል የሚጠሩ የክርስቶስ ማኅበረሰብ ናቸው፡፡[233] ያለዚህ አካል አንድነት የለም!

**አንድ መንፈስ**፡- በሰማያዊ ሥፍራ የተባረክንበት፣ የርስታችን መያዣ እንዲሆን የታተምንበት፣ በሕይወት የእድገት ጉዞአችን ላይ የልብ አይኖቻችንን እያበራ የጠራንን አብንና የተጠራንበትን ተስፋ የሚያሳውቀን፣ ዘወትር ወደ አብ የምንገባበት፣ በውስጥ ሰውነታችን በኃይል የምንጠነክርበት፣ በመጨረሻም በቤዛ ቀን በክብር የምንገለጥበት መንፈስ ቅዱስ ነው፡፡ ያለ መንፈስ ቅዱስ አንድነት የለም!

**አንድ ጌታ**፡- ከሙታን የተነሳውን፣ ከአለቅነት፣ ከስልጣናት፣ ከኃይል፣ ከጌትነትም

[231] ኤፌ. 1፡12; 2፡12; 3፡5
[232] ሮሜ 8፡24፤25
[233] ኤፌ. 1፡23; 2፡16; 1ቆሮ 12፡13; ሮሜ 12፡5; 4፡16



For more books www.amharicchristianbooks.com

ሁሉ በላይና በዚህ አለም ብቻ ሳይሆን ሊመጣ ባለው ዓለም ከሚጠሩት ስሞች ሁሉ በላይ በሰማያዊ ሥፍራ የተቀመጠውን፣ ሁሉ ከእግሩ በታች የተገዛለትን የቤተ ክርስቲያን ራስ፣ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ የማዕዘን ራስ፣ የአለቅነትና የሥልጣን ራስ የሆነውን፣ የሁሉ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን የሚያመለክት ነው፡፡ እርሱ የአንድነታችን ማዕከል ነው፡፡ ያለርሱ አንድነት የለም!

**አንድ እምነት** (ሃይማኖት)፡- የእውነትን ቃል እርሱም የመዳናችንን ወንጌል ሰምተን የክርስቶስን ጌትነት የተቀበልንበት፣ ኢየሱስ ክርስቶስን ከሙታን ያስነሳው የኃይሉ ታላቅነትና የብርታቱ ጉልበት ዛሬ ለእኛ፣ በእኛ እንደሚሠራ የምናውቅበት፣ ከእግዚአብሔር ምህረትና ፍቅር የተነሳ የተገለጠውን የማዳን ፀጋ የተቀበልንበት፣ በመታመንና በድፍረት ወደ አብ የምንገባበት፣ ክርስቶስ በልባችን እንደሚኖር የምናውቅበት፣ የእግዚአብሔርን ልጅ በማወቅ ወደ አንድነት የምንደርስበት፣ ከክፉ ኃይላት የሚወረወሩብንን የሚንበለበሉትን ፍላፃዎች የምናጠፋበት፣ የመንፈሳችን የስሜት ሕዋስ ነው፡፡ እውነተኛ አንድነትና ሕብረት የእምነት (የኃይማኖት) አንድነት ነውና! በድፍረትም ያለዚህ እምነት አንድነት የለም! እንላለን፡፡

**አንዲት ጥምቀት** በማለት ከዝርዝሮቹ መሃል ነጥሎ በአንስት ፆታ[234] የሚጠራው ጥምቀት ምንም እንኳን በዚህ መልእክቱ ውስጥ ከዚህ ውጭ የተጠቀሰበት ሥፍራ ባይኖርም፣ ከዚህ መልእክት ጎን ለጎን በተፃፈው በቈላስይስ ውስጥ በስፋት የተጠቀሰ ዓብይ ጉዳይ ነው፡፡[235] ጥምቀትን በአማኞች የአንድነት መግለጫ ውስጥ እንደ ምሰሶ ማንሳቱ የሚገርም ቢመስልም፣ በውስጡ ያለውን እውነታ በጥሞና ስንመለከት ሊስተዋል የሚገባው የአንድነት ምስጢር እናገኝበታለን፡፡ ጥምቀት ማለት አንድ ነገር ሙሉ ለሙሉ በሌላው ውስጥ መግባቱን፣ መጥለቁን ወይም መስመጡን የሚያመለክት ቃል ነው፡፡[236] እኛ በኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝነትና ጌትነት ስናምን መንፈስ ቅዱስ ወደ ውስጣችን ገባ፡፡ በዚያ ቅጽበት እኛም በውስጡ ገባን፡፡ ይህን አሳብ ሁለት ክፍሎች በሚገባ ያብራሩታል፡፡ 1ቆሮ 12፡13 *“. . . እኛ ሁላችን በአንድ መንፈስ አንድ አካል እንድንሆን ተጠምቀናልና፡፡ ሁላችንም አንዱን መንፈስ ጠጥተናል፡፡”* ይላል፡፡ ልክ ልብስ ውሃ ውስጥ እንደሚገባ፣ እኛ ሁላችን አንዱ መንፈስ ውስጥ በመግባት አንድ አካል እንድንሆን ተጠምቀናል ይለንና በዚህ

[234] ምንም እንኳ አዲሱ መደበኛ ትርጉም ቢቀይረውም በቀደመው እ.አ.አ 1962 እትም በሴቴ ጾታ ተጠርቷል፡፡ የማቴ 20፡22 እና 21፡25 አጠራርም ከዚህ ጋር ይስማማል፡፡

[235] ቆላ. 2፡9-15

[236] አንዳንድ ወንጌላውያን አብያተ-ክርስቲያናት በውሃ ውስጥ ከማስጠም ይልቅ በመርጨትና በተለያዩ መንገዶች ጥምቀትን እንደሚፈፅሙ ይታወቃል፡፡



For more books www.amharicchristianbooks.com

ሳያበቃ ሁላችን አንዱን መንፈስ ጠጥተናል በማለት እኛ እንደልብስ በውስጡ የገባንበት ብቻ ሳይሆን፣ እርሱ እንደሚጠጣ ውሃ በውስጣችን የገባ መሆኑን ይነግረናል፡፡ ይህም በዮሐ. 14፡17 ላይ ጌታ *". . . ከእናንተ ዘንድ ስለሚኖር፣ በውስጣችሁም ስለሚሆን እናንተ ታውቃላችሁ፡፡"* ካለው ጋር ይመሳሰላል፡፡

ደህንነት ጥምቀት ነው፡፡ ሰው ሲያምን መንፈስ ወደ ውስጡ ይገባል፣ ከመንፈስ ይወለዳል፣ መንፈስ ቅዱስ እኛ ውስጥ በመግባቱ እኛም በእርሱ ውስጥ ገብተናል፣ በእርሱ ውስጥ ስንገባ ደግሞ እርሱ ባለበት ሁሉ ውስጥ ገብተናል በዚህ መልኩ በአብ ውስጥ ገብተናል፣ በወልድ ውስጥ ገብተናል በክርስቶስ አምነው በዳኑ አማኞች ሁሉ (በአካሉ) ውስጥ ገብተናል፡፡ ከገባንበትም ሁሉ ጋር አንድ ሆነናል፡፡ በተለይ በክርስቶስ ውስጥ ስንገባ በውስጡ በሕይወት በጥልቀት ከመግባታችን የተነሳ ዘላለማዊና ታሪካዊ ማንነቱ ውስጥ ገብተናል፡፡ ከዚህም የተነሳ በሌለንበት፣ ዓለም ሳይፈጠር ተመርጠናል፣ ሳንወለድ፣ የዛሬ 2000 ዓመት ለኃጢአት፣ ለዓለምና ለእኔነት ሞተናል፡፡ በአዲስ ሕይወት እንድንመላለስ ከእርሱ ጋር ከሙታን ተነስተናል፣ ከእርሱም ጋር በሰማያዊ ሥፍራ በአብ ቀኝ ተቀምጠናል፣ ከእርሱም ጋር ገና በክብር እንገለጣለን፡፡ ይህንንም በመንፈሳዊው ዓለም የተከናወነ እውነታ ባመንን ጊዜ በውሃ በመጠመቅ በገሃድ ገልፀነዋል፡፡ የውሃ ጥምቀት የዚህ መንፈሳዊ እውነት አካላዊና ውጫዊ መገለጫ ነው፡፡ በውሃ ጥምቀት ውስጥ ትልቁ ቁም ነገር ሰውነታችን ውሃ ውስጥ ገብቶ መውጣቱ ሳይሆን የልብና የሕሊና ተሃድሶ ማግኘቱ ነው፡፡[237]

የእስራኤልም ልጆች ከግብጽ ወጥተው ወደ ርስታቸው ለመግባት ሲጓዙ ሙሴን ይተባበሩ ዘንድ ውሃው ውስጥ ገብተዋል፣ በዚህም በደመናና በባሕር ተጠምቀዋል፡፡[238] ጥምቀቱ እነርሱ ውሃው ውስጥ በመግባታቸው አላከተመም፣ ይከተላቸው ከነበረው ዐለት የፈለቀውን ውሃ ሲጠጡ ውሃው ወደ እነርሱ ውስጥ ገብቷል፡፡ እነርሱ በውሃው ውስጥ፣ ውሃው በእነርሱ ውስጥ፡፡ ይህም በእኛ ሕይወት በመንፈሳዊው ዓለም ለተከናወነው ነገር ዓይነተኛ ምሳሌ ነው፡፡ ይህንንም መሠረት በማድረግ በውስጥ በእምነት የሚከናወን፣ በውጭም በገሃድ የሚመሰከር ጥምቀት ከሌለ አንድነት የለም! እንላለን፡፡

**አንድ አምላክ፡-** በመጨረሻም በዝርዝሩ ፍፃሜ ላይ "ከሁሉ በላይ የሚሆን፣ በሁሉም የሚሠራ፣ በሁሉም የሚኖር፣ አንድ አምላክ የሁሉ አባት" በማለት

---

[237] 1ጴጥ. 3፡21-22

[238] 1ቆሮ. 10፡1-5; 11



For more books www.amharicchristianbooks.com

የሚጠቅሰው የአንድነታችን ምሰሶ የሆነውን እግዚአብሔር አብን ነው፡፡ በአብ ዘላለማዊ ፈቃድ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ ሥራ፣ በመንፈስ ቅዱስ ሕይወትነት፣ ከአይሁድና ከአሕዛብ ውህደት የተፈጠረውን አዲሱን ማኅበረሰብ እንደ አንድ ቤተሰብ በመመልከት አብ የሁሉም የበላይ የሆነ፣ በሁሉም አማኞች ውስጥ የሚሠራ፣ በሁሉም አማኞች ውስጥ የሚኖር የሁሉ አምላክና አባት እንደሆነ፣ በዚህም አባት ዙሪያ በምድርም ሆነ በሰማይም ያለ ቤተሰብ በአንድነት እንደሚሰበሰብ ይጽፍልናል፡፡ ቀደም ሲል "የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባት እንደሆነ የነገረን "የክብር አባት" በክርስቶስ ሥራ የእኛም የሁላችን አባት መሆኑንና በሰማይና በምድር ያለ ቤተሰብ ሁሉ አባትነት ፍለጋ ከዙፋኑ ፊት እንደሚሰየም ጽፎልናል፡፡ (3፡14-15) ስለዚህ ይህ አባት፣ አባታችን፣ ይህም አምላክ አምላካችን ካልሆነ አንድነት ከየት ሊመጣ ይችላል?

ይህ ዝርዝር በውስጡ አብን፣ ወልድንና መንፈስ ቅዱስን በመጥቀሱ የአማኞች አንድነት መሠረቱ የሥላሴ አንድነት መሆኑን ያስተምራል፡፡ እንግዲህ በእነዚህ ፍፁም አንድነቶች አንድ ከሆንን ሌላ እልፍ ልዩነቶች ቢኖሩን እንኳ ሊለዩን አይችሉም፣ ሊለዩንም አይገባም፡፡ የተለያየን ቢመስለን እንኳ በርግጥ አንለያይም፡፡ አንድነታችን በየምክንያቱ የሚበጠስና የሚቋጠር አይደለምና፡፡ በርግጥ በአንዳንድ ምክንያቶች ሊለጠጥ ይችል ይሆናል፣ ሆኖም አይበጠስም፡፡ አንድነታችን የመንፈስ እንጂ የቦታ አይደለምና በተለያየ ቦታ መሰብሰባችንና ማምለካችን ሊያፈርሰው አይችልም፡፡ በዚህ የአንድነት ማዕቀፍ ውስጥ እስካለን ድረስ የአምልኮ ቅርጽ፣ የአስተዳደር ስልት፣ የመጠሪያ ስም ወ.ዘ.ተ አይለየንም፡፡

ሆኖም የዚህን ትምህርት ተግባራዊ ገፅታ ሳስብ በሃገር ውስጥም ሆነ በውጭ ባሉ የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ስመላለስ ያየሁትና ዘወትር የሚከነክነኝ አንድ ተግዳሮት በፊቴ ይደቀናል፡፡ ቀደም ሲል በኢሳይያስ ትንቢት ውስጥ ክርስቶስ በሞቱና በትንሳኤው በመሠረተው፣ በጽድቅና በቅንነት በሚመራው መንግሥቱ ውስጥ ከተፈጥሮአቸው ልዩነት የተነሣ በአንድነት ሊሰማሩ የማይችሉ ተኩላና የበግ ጠቦት፣ ነብርና የፍየል ጠቦት፣ ጥጃና የአንበሳ ደቦል፣ ላምና ድብ፣ በአንድነት መሠማራት እንደ ቻሉ በምሳሌነት አይተናል፡፡ ነገር ግን በእምነት አንቀፅም ሆነ በአምልኮ ሥርዓት አንዳች ልዩነት የሌለን አማኞች፣ በዚሁ በክርስቶስ መንግሥት ውስጥ እንኖራለን እያልን በአንድነት ማምለክ ስለምን ተሳነን? ስለምንስ በአንድ አካባቢ እየኖርን፣ ለሥራና ለገበያ በአንድ ቋንቋ እየተጠቀምን ለአምልኮ ሲሆን በዘርና በቋንቋ መለያየት ስለምን አስፈለገን? በአንድ ላይ እናመልክ የነበርን ሰዎች የፖለቲካ ድንበር ሲከፈል እኛም ስለምን ተከፋፈልን?



For more books www.amharicchristianbooks.com

ቋንቋ ወንጌልን ለማሰራጨት ዓይነተኛ መሳሪያ መሆኑ እሙን ነው፡፡ ሰዎች በተቻለ መጠን አፍ በፈቱበት ልሣን ወንጌል ቢሰሙ ይመረጣል፣ ነገር ግን ቋንቋ ሰዎችን በወንጌል ለመድረስ የተሰጠን የጽድቅ መሣሪያ ሆኖ ሳለ ስለምን የምንከፋፈልበት የአመፅ መሣሪያ አደረግነው? ሊለዩን በማይገቡ አናሳ ጉዳዮች ባንለያይ ኖሮ ፍሬያችን ምንያህል በጎመራ!

## በልዩነት አንድነት

አንድነት፣ አንድ ዓይነት መሆን አይደለም፡፡ እግዚአብሔር የብዙ ኅብር አምላክ እንጂ የአንድ ዓይነት አምላክ አይደለምና፡፡ የዚህን አባባል እውነትነት ተፈጥሮ ራሱ በታላቅ ድምጽ ያስተጋባል፡፡ በአዕላፋት የእግዚአብሔር የእጅ ሥራዎች ውስጥ ቁጥር፣ ስፍር የሌላቸው ልዩነቶች እናያለን፣ እነዚህም ልዩነቶች የፍጥረት ማራኪነትና አይጠገቤነት ዋነኛ ምክንያት ናቸው፡፡

ልዩነት ሁለት አይነት ነው፡፡ ገንቢ ልዩነቶች አሉ፤ ለምሳሌ፡- የቀለም፣ የዘር፣ የቋንቋ፣ የጾታ ወ.ዘ.ተ የመሳሰሉ ልዩነቶች አሉ፡፡ በእነዚህ ልዩነቶች ላይ ባለቤቱ ምንም አስተዋፅኦ ሊያደርግ አይችልም፡፡ ከእግዚአብሔር የተቸረውና በፀጋ ሊቀበለው የሚገባ ልዩነት ነው፡፡ አፍራሽ ልዩነቶች ደግሞ አሉ፡፡ የእምነት፣ የዓላማ፣ የግብ፣ የንፅረተ- ዓለም ልዩነቶች፡፡ ስለዚህ አፍራሽ ልዩነቶችን፣ ከገንቢ ልዩነቶች ልንለይ ይገባል፡፡

ገንቢ ልዩነትን የሚያስወግድ አንድነት እድሜው አጭር ነው፡፡ የሚያፈርሰው ከውጭ የመጣ ኃይል ሳይሆን ያ ያስወገደው ማንነት ነው፡፡ አንድነታችንን ለመገንባት ልንጠቀምበት ስንችል አውጥተን የጣልነው የልዩነት ድንጋይ ነገ አንድነታችንን በማፍረስ ተግባር ላይ እንደሚሰማራ ልንዘነጋ አይገባም፡፡ ሕንፃ ሲገነባ ጥቅም ላይ የሚውሉ ግብዓቶች በርካታ ናቸው፡፡ እነዚህ ልዩ ልዩ ቁሶች በአንድነት ተሰግስገው ሕንፃውን አፅንተው ያቆሙታል፣ በልዩነታቸውም ሕንፃው ያሸበርቃል፡፡ ሊጠቅመን እየቻለ ብናስወግደው ግን ሊጠቅመን በሚችልበት አቅሙ፣ ሊያፈርሰንም እንደሚችል ማሰብና ማስተዋል ነው፡፡ ራሱን ከራሱ መለየት የጀመረ ኃይል ማንነቱ እስኪጠፋ ድረስ መለየቱን ይቀጥላል እንጂ ማቆሚያ የለውም፡፡ ሽንኩርት ስንልጥ አላስፈላጊውን የላይኛ ቆዳ ከላጥን በኃላ መላጣችንን እናቆማለን፣ ካላቆምን ግን ስንልጥ እንውላለን፣ በመጨረሻም ለምግብ ያልነው ሽንኩርት ሁሉ ተልጦ ያልቃል፡፡ ይህንን አባባል ግልፅ የሚያደርግ ምሳሌ ልስጥ፡፡ በሌላ ሃገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን አማኞች «እኛ ኢትዮጵያውያን ነን» ብለው ራሳቸውን በመካከላቸው ከሚኖሩ ሌሎች አማኞች ከለዩ፣ የተጠናወታቸው



For more books www.amharicchristianbooks.com

የመለየት አባዜ እየባሰ ይሄዳል እንጂ መቆሚያ ድንበር አይኖረውም፡፡ አስቀድሞም ቋንቋን፣ ቀለምን፣ ብሔርን፣ ባሕልንና ዜግነትን መሠረት አድርገው የተለዩት ኢትዮጵያውያን ትንሽ ይቆዩና እኔ ትግሬ ነኝ፣ እኔ አማራ ነኝ፣ እኔ ኦሮሞ ነኝ ብለው ይለያያሉ፡፡ ይህ በስህተት የተጀመረ መለያየት ገደብ እንደሌለው የምናየው ትግሬው የራያ፣ የእንደርታ፣ የአሸአ (አክሱም፣ ሽረና አድዋ) እያለ፤ አማራውም የጎንደር፣ የጎጃም፣ የወሎ፣ የሸዋ እያለ፣ ኦሮሞውም የሐረር፣ የባሌ፣ የወለጋ፣ የአርሲ፣ . . . እያለ እስከ ጎሳና እስከ ቤተሰብ ቁልቁል ሲዘልቅ ነው፡፡ ታዲያ መፍትሄው ምንድን ነው? መፍትሄው ጎልቶ መሳፍርት የሌላቸውን ሥጋዊና ውጫዊ ልዩነቶች እንዳሉ ተቀብለን በመንፈስ ቅዱስ አንድነት በማተኮር በጽናት መቆም ነው፡፡

አንድነትን መጠበቅ ዋጋ ያስከፍላል፡፡ አሁን ያለን አንድነት ያለ መሥዋዕትነት አልመጣም፤ ሰማይንና ምድርን፣ አይሁድንና አሕዛብን፣ ሰውንና እግዚአብሔርን፣ አንድ ለማድረግ የእግዚአብሔር ልጅ በመስቀል ላይ ነፍሱን መስጠት ነበረበት፡፡ እኛ ግን ይህን በመሥዋዕትነት የመጣ አንድነት ለመጠበቅ ጥቂት ደስታችንን፣ ጥቂት ክብራችንን፣ ጥቂት ጥቅማችንን ለመሰዋት ምን ያህል ዝግጁ ነን?

የመንፈስ አንድነት የንግግር፣ የልብና የሃሳብ አንድነት እንጂ የውጪያዊ መልክና የቅርጽ አንድነት አይደለም፡፡ ሐዋርያው የማይታዩትንና ውስጣዊ የሆኑትን ሰባት አንድነቶች ከዘረዘረ በኋላ “ነገር ግን” የሚለውን አያያዥ በመጠቀም ወደ አዲስ አሳብ ይገባል፡፡ ቀደም ሲል ስለ አካል ሲጽፍ ነበር፣ አሁን ግን ትኩረቱን በማጥበብ የአንድ አካል ክፍሎች ወደሆኑት ብልቶች ዞር ይላል፡፡ አካል አንድ ነው፡፡ ብልቶች ግን ብዙና የተለያዩ ናቸው፡፡ ስማቸው፣ ቅርፃቸው፣ የሥራ ድርሻቸው የተለያየ ነው፡፡ ነገር ግን ይህ ልዩነታቸው አንድነታቸውን ያጠነክረዋል እንጂ አያጠፋውም፡፡

የአካል ብልቶችን ልዩ፣ ልዩ የሚያደርጋቸው ወደ ላይ በወጣው ጌታ አማካይነት ለእያንዳንዱ የተሰጠው ፀጋ ነው፡፡ ይህ ፀጋ በ2፡5 እና 8 ላይ እንዳየነው የመዳን ፀጋ ሳይሆን የአገልግሎት ፀጋ ነው፡፡ ቀደም ሲል በእነዚህ ክፍሎች ያየነው የመዳን ፀጋ በዋነኝነት እኛ ላይ ያተኮረ ሲሆን በዚህ ክፍል የምናየው ፀጋ ግን በክርስቶስ ማህበር መታነፅና በሌሎች መዳን ላይ የሚያተኩር ነው፡፡ ይህ ፀጋ የተሠጠን እንደ ክርስቶስ ስጦታ መጠን ነው፡፡ ከዚህ ቀደም እንዳልነው ፀጋ፣ ተቀባዩ የማይገባው ወይም የማይመጥነው፣ የሰጪውን ልግስና እንጂ የተቀባዩን ማንነትና ችሎታ ፈጽሞ የማያሳይ፣ ነፃ ስጦታ ነው፡፡ የክርስቶስ የአካል ክፍሎች ያለ አንዳች ልዩነት ፀጋን መቀበላቸው የአንድ እውነት መስተጋብር ነው፡፡ ያም ከሰማይ የወረደው ስጋ



For more books www.amharicchristianbooks.com

ለብሶ በምድር ላይ የተመላለሰውና ስለ ኃጢአታችን የሞተው ኢየሱስ ክርስቶስ፣ ድል በመንሳት ከሙታን መነሳቱንና ከሰማያት ሁሉ በላይ በመውጣት መክበሩን ያሳያል፡፡

ጳውሎስ ይህንን አጉልቶ ለማሳየት የተጠቀመበት የቅዱሳት መጻሕፍት ክፍል በእስራኤላውያን ዘንድ ብሔራዊ የድል መዝሙር በመባል የሚታወቀውን መዝሙር (68) ነው፡፡ ይህም አማኞች የትኛውንም ፀጋ ስጦታ ሲለማመዱ ስናይ ክርስቶስ ከሙታን መነሳቱን፣ ድል መንሳቱንና ከሁሉ በላይ ከፍ ማለቱን ያሳስበናል፡፡ ምድርን ሲገዙ የኖሩት የወደቁት መላእክት ዘመን እያከተመና የሚመጣውን ዓለም የሚገዛው የአዲሱ ሰው ዘመን እየቀረበ መሆኑን ያበስረናል፡፡[239]

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ስጦታ አድርጎ የሰጠው ፀጋን ብቻ ሳይሆን ሰዎችን ጭምር ነው፡፡ አዎን ሰዎችን ለሰዎች ሰጥቷል፡፡ እነዚህም ስጦታ የሆኑ ሰዎች ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ላይ ከፍ ከፍ ባለ ጊዜ ለምድር የሰጣቸው፣ እርሱ ብቻውን በሦስት ዓመት ተኩል ቆይታው ሲሠራው የነበረውን ሥራ ዳር የሚያደርሱ ሰዎች ናቸው፡፡ አብ ክርስቶስን ከሁሉ በላይ ራስ እንዲሆን ለቤተ ክርስቲያን ሲሰጠው፣ ክርስቶስ ደግሞ ሐዋርያትን፣ ነቢያትን፣ ወንጌል ሰባኪዎችን፣ እረኞችንና አስተማሪዎችን የሚሠሩ እጆች አድርጎ ሰጥቷል፡፡ እሱ በምድር አገልግሎቱ ከአብ ዘንድ የተላከ ብቸኛ ሐዋርያ ነበር፣ በቃልና በሥራ ብርቱ ነቢይ ነበር፣ ለድሆች ወንጌልን እሰብክ ዘንድ ቀብቶኛል ያለ ወንጌላዊም ነበር፣ መልካም እረኛ እኔ ነኝ የሚል እረኛም ነበር፣ በሕዝብ ሁሉ ዘንድ የተገለጠ መምህር ነበር፡፡[240] ባረገ ጊዜ ግን እነዚህን አገልግሎቶች ሁሉ ይዞ ወደ ሰማይ መሄድ አልፈለገም፡፡ ስጦታዎቹ የሚያስፈልጉት ሰማይ ሳይሆን እዚሁ ምድር ነውና፡፡ ራሱን በሌሎች ውስጥ ሊገልጥ ወደደ፡፡ ስለዚህ ለእነዚህ አገለግሎቶች የተጠሩት ሰዎች ሐዋርያት፣ ነቢያት፣ ወንጌል ሰባኪዎች፣ እረኞችና አስተማሪዎች የሆኑት ሐዋርያው፣ ነቢዩ፣ ወንጌል ሰባኪው፣ እረኛውና አስተማሪው ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ተገለጠባቸው እንጂ በራሳቸው አይደለም፡፡ ለዚህም እንደ ዋቢ ልንጠቅሰው የምንችለው ሰው ጳውሎስ ነው፡፡ በገላትያ መልዕክቱ ስለ ጥሪውና ስለ አገለግሎቱ ሲመሰክር *". . . በአሕዛብ መካከል ስለ እርሱ ወንጌልን እሰብክ ዘንድ ልጁን በእኔ ሁኔታ ሊገልጥ በወደደ ጊዜ . . . " ገላ. 1፡15-16* ብሏል፡፡ በሮሜ መልዕክቱም ስለ ሦስቱም የተልዕኮ ጉዞው ሲጽፍ *"አሕዛብ እንዲታዘዙ ክርስቶስ በቃልና በሥራ፣ በምልክትና በድንቅ ነገር ኃይል፣*

[239] ዕብ. 2፡5-8

[240] ዕብ.3፡1; ሉቃ.24፡19; 4፡17-19; ዮሐ.10፡11; 1፡39



For more books www.amharicchristianbooks.com

*በመንፈስ ቅዱስም ኃይል በእኔ አድርጎ ከሠራው በቀር ምንም ልናገር አልደፍርም. . ."* ሮሜ 15፡18 ማለቱ ክርስቶስ ፀጋ መስጠት ብቻ ሳይሆን በአገልጋዮቹ ውስጥ አድሮ ራሱ መስራቱን በግልፅ ያሳየናል፡፡

ጳውሎስ ስለ አሰጣጡ ሲነግረን አስቀድሞ ከመዝሙር 68፡18 ላይ በጠተቀሰው ክፍል ላይ በመመርኮዝ *"ወደ ምድር ታችኛ ክፍል ደግሞ ወረደ ማለት ካልሆነ ይህ ወጣ ማለትስ ምን ማለት ነው?"* በማለት ይጠይቅና ጥያቄውን ራሱ ሲመልስ *"ይህ የወረደው ሁሉን ይሞላ ዘንድ ከሰማያት ሁሉ በላይ የወጣው ደግሞ ያው ነው፡፡"* በማለት ሰዎችን ስጦታ አድርጎ መስጠቱን ይዘግባል፡፡ ከዚህ በመነሳት ከሰማያት ሁሉ በላይ የወጣው ኢየሱስ "ሁሉን" ማለትም ምድርን ሁሉ የሚሞላው፣ እነዚህ ስጦታ ተደርገው የተሰጡ ሠራተኞች ከስፍራ ስፍራ እየተዘዋወሩ የወንጌልን የምሥራች ለዓለም ሲሰብኩ፣ ባመኑትም ዘንድ የእግዚአብሔርን ምስጢር በመግለጥ መሠረት እየጣሉ፣ የተመሠረቱትንም እያነፁና እየገነቡ ወደ ክርስቶስ ሙላት ለማድረስ ሲሰሩ መሆኑን እንረዳለን፡፡ ይህም በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን እውን መሆን ችሎ ነበር፡፡ ለዚህም ማስረጃ የሚሆነን ሐዋርያው ጳውሎስ አብረውት ከሚሰሩ የክርስቶስ አገልጋዮች ጋር በኤፌሶን ተቀምጦ በሁለት ዓመት ጊዜ ብቻ በእስያ ለሚኖሩ አይሁድና አሕዛብ ሁሉ ወንጌልን ማሰማቱ ነው፡፡[241]

ይህ በእንዲህ እንዳለ፣ በዘመናት ውስጥ አማኞች እንዲያገለግሏቸው በተሰጧቸው የወንጌል ሠራተኞች ዙሪያ መለያየታቸው የሚያስገርም ነገር ግን ሊካድ የማይችል እውነታ ነው፡፡[242] ይህ ሕፀፅ ያኔም ነበር፣ አሁንም በስፋት ይናኛል፡፡ ነገር ግን መለያየቱ የተከሰተው፣ ጌታ የተለያየ ፀጋ ያላቸው አገልጋዮች በመስጠቱ ምክንያት ሳይሆን፣ አገልጋዮችም ሆኑ አማኞች የፀጋ ስጦታዎችን ዓላማ በቅጡ ባለመረዳታቸው ነው፡፡ እንዲህ ሲባል ግን አገልጋዩች ሁሉ የፀጋ ሥጦታዎችን ዓላማ አልተረዱም ማለት አይደለም፡፡ የአገልግሎት ሥጦታዎቹን ምንነት በመረዳትና በእውነተኛ መሰጠት የሚያገለግሉ እንዳሉ ሁሉ ባለማወቅም ይሁን በራስ ወዳድነት አገልግሎቶቹን ለዝናና ለግል ጥቅም የሚያውሉ መኖራቸውን ልብ ማለት ይገባል፡፡ ይህን ርዕሰ ጉዳይ በተመለከተ ያለውን ውዥንብር በሚቀጥለው ንዑስ ርዕስ በጥቂቱ እንመለከታለን፡፡

241 ሐዋ. ሥራ 19፡10

242 1ቆሮ. 1፡11-13



For more books www.amharicchristianbooks.com

## የአገልግሎት ሥጦታዎች

ኤፌሶን ምዕራፍ አራትን በተለይም ደግሞ ቁጥር አሥራ አንድን ስናስብ ፈጥኖ ወደ አዕምሮአችን የሚመጣው "አምስቱ የአገለግሎት ቢሮዎች" በመባል የሚታወቀው ዝነኛ ርዕስ ነው፡፡ እንዲያውም የኤፌሶን መልዕክት ባጠቃላይ ስለ አምስቱ ቢሮዎች እንደሚያወሳና ከዚያ ያለፈ ሌላ መልዕክት እንደሌለው የሚያስቡ አማኞች ቁጥር ጥቂት አይደለም፡፡

በእርግጥ ይህ ቁጥር (4፡11) ክርስቶስ ለቤተ-ክርስቲያን ሥጦታ አድርጎ ስለ ሰጣቸው አገልጋዮች ይናገራል፡፡ ሆኖም ቁጥራቸው አምስት ይሁን አራት እርግጠኛ መሆን አይቻልም፡፡ ምክንያቱም ጸሐፊው የመጀመሪያዎቹን አራቱን አገለግሎቶች ከመስተአምር (article) ጋር "አንዳንዶቹን" "ሌሎቹም . . . " በማለት ጠርቶ የመጨረሻዎቹን ሁለቱን *"ሌሎቹንም እረኞችና አስተማሪዎች እንዲሆኑ ሰጠ"* በማለት እረኝነትንና አስተማሪነትን በአንድ ይጠቀልላል፡፡ ይህም አንዳንድ የሥነ-ቋንቋ አጥኚዎች "አራት ናቸው እንጂ አምስት አይደሉም" ብለው እንዲከራከሩ አድርጓቸዋል፡፡[243] በእርግጥ እረኞች መንጋውን መመገብ ስላለባቸው ያስተምራሉ፤ ሆኖም ሁሉም እረኞች አስተማሪዎች፣ ሁሉም አስተማሪዎች እረኞች ናቸው ማለት ያስቸግራል፡፡ አንዳንዴ እረኞች ያልሆኑ አስተማሪዎች፣ አስተማሪዎች ያልሆኑ እረኞች ይኖራሉና፡፡

በሌላ በኩል አንዳንዶች፣ የመጀመሪያዎቹ ሁለት አገለግሎቶች ማለትም "ሐዋርያትና ነብያት" በዚያን ጊዜ እንጂ አሁን የሉም፤ ምክንያቱም መልዕክቱ በተጻፈበት ጊዜ የአዲስ ኪዳን መጽሐፍት ተጽፈው ስላልተጠናቀቁ አስፈላጊነታቸው የግድ ነበር፤ አሁን ግን በቅዱስ ቃሉ መሠረት ተጥሎ ስለ ተጠናቀቀ አገልግሎታቸው አክትሟል ይላሉ፡፡[244] ሌሎች ደግሞ በተቃራኒው ሥጦታው የተሰጠው ለቤተ-ክርስቲያን እንደ መሆኑ መጠን ቤተ-ክርስቲያን እስካለች ድረስ ሁሉም ሥጦታዎች ዛሬም አሉ ደግሞም ይሠራሉ በማለት ይከራከራሉ፡፡[245] ይህ ክርክር ዛሬም እንዳለ የቀጠለ ቢሆንም ይህ ማብራሪያ ሊያስተላልፈው ከሚፈልገው መልዕክት አንጻር ዋናው ጉዳይ የመጠሪያ ስም ሳይሆን የሥራና የተግባር ጉዳይ ስለሆነ ከሥያሜው ይልቅ ሕይወቱ ላይ በማተኮር

[243] Sttot, John R. W. the Message of Ephesians: 2n ed. 1989. P. 163, p. 3
[244] John F. Walvoord, Roy B. Zuck, the Bible Knowledge Commentary SP Publications, 1983. P. 634-635
[245] Wagner, C. Peter, Apostles of the City, 2000. David, Jonaathan, Apostolic Strategies Affecting Nations. Eckhardt, John, Moving in the Apostolic, 1999.



For more books www.amharicchristianbooks.com

እንቀጥላለን፡፡

በዚያም ላይ ጳውሎስ ይህንን ክፍል የጻፈልን ሐዋርያትና ነብያት አሁንም አሉ! የሉም! ሥጦታዎቹ አራት ናቸው! አምስት! ብለን እንድንከራከር ሳይሆን በክርስቶስ ሥራ፣ በመንፈስ ቅዱስም መሠጠት የተገኘውን አንድነት ለመዘከርና አገልጋዮች ለቤተ-ክርስቲያን የተሰጡበት ዋና አላማ ይህን በክቡር ዋጋ የተገዛ አንድነት እንዲጠብቁና እንዲያስጠብቁ ለማስገንዘብ ነው፡፡ ለነገሩማ ይህንን አንድ ቁጥር ከመላ መልዕክቱ ሃሳብ በማፋታትና በመለጠጥ የሚባለውና የሚተገበረው ለማመን የሚቸግር አይደል?!

በአንዳንድ ሥፍራዎች እነዚህ አገልገሎቶች፣ አገልግሎት ከመሆን ይልቅ የቤተክርስቲያን መዋቅር የዕድገት እርከን ተደርገው በመቆጠር፣ ወንጌላዊ በመባል የጀመረው ሰው ከጥቂት አመታት በኋላ ፀባዩን ካሳመረ የሥራ ዕድገት በማግኘት የእረኛ (መጋቢ ወይም ፓስተር) ማዕረግ የሚጎናፀፍበት መስከ ከሆነ ሰንብቷል፡፡ ከረዥም ቆይታ በኋላ ያገኘኝ ይህ ዕድገት የተሰጠው አንድ አገልጋይ "ያሬድ፤ አሁንም ድረስ ወንጌላዊ ትባላለህ? እስካሁን ፓስተር አልሆንክም?" በማለት በአግራሞትና በርህራሄ የጠየቀኝ መቼም አይረሳኝም፡፡ ይህ አገልጋይ፣ አንድ ሰው ተሳስቶ በልሙጥ ስሙ ወይም "ወንድም" ብሎ ቢጠራው ውስጡ እንደሚቆጣና "ለመሆኑ በደንብ ታውቀኛለህ/ሽ" ብሎ እንደሚጠይቅ መገመት አያስቸግርም፡፡ ታዲያ እኮ ይህ የማዕረግ ዕድገት ጉዳይ ተጠብቆ የሚገኘው በአንጋፋዎቹ ቤተ-ክርስቲያናት ውስጥ እንደሆን ነው እንጂ በቅርቦቹ ዘንድ ሌላው እስኪሾምና እስኪያፀና የሚጠብቅ ያለ አይመስለኝም፡፡ ማንም ከተሰማውና ከመሰለው ራሱን ፓስተር፣ ነብይ፣ ሐዋርያ ብሎ ከመሰየም ወደ ኋላ አይልምና፡፡ እውነቱ ግን ወንጌላዊነት ወደ ፓስተርነት የሚያድግ አናሳ አገለግሎት አለመሆኑ፣ እረኝነትም ሰንብቶ ወደ ሐዋርያነት የሚለወጥ የበታች ፀጋ አለመሆኑ ነው፡፡ መጠሪያነቱም ለራሳችን የምንቸረው ወይም እንደ ሌሎቹ የዓለም ማዕረጎች ከስማችን በፊት የምንዶለው ሳይሆን ሰዎች ተግባራችንን አይተው፣ ፍሬያችንን ተመልከተው የሚለዩን የተግባራችን መገለጫ ነው፡፡

ታሪካቸውን በአዲስ ኪዳን ገፆች የምናነበው የመጀመሪያው ክፍለ ዘመን ቤተክርስቲያን አገልጋዮች በማዕረግ ስም አልተጠሩም፡፡ ምክኒያታቸውም ግልፅ ነበር፤ የኖሩትና ያገለገሉት የራሳቸውን ስም ለማስጠራት ሳይሆን በእነርሱ ውስጥ



For more books www.amharicchristianbooks.com

የሚሠራውን የአንዱን እርሱም የሰማዩን ጌታ ስም ለማስጠራት ስለ ነበር ነው፡፡[246] እኛም የዛሬዎቹ ራሳችንን ዝቅ አድርገን በማገልገል ጌታን ገልጠን እንድናሳይና ለመንፈስ አንድነት ጉልህ ሥፍራ በመስጠት ቅዱሳንን ለአገለግሎት ሥራ እንድናዘጋጅ እግዚአብሔር ይርዳን፡፡

## የእውነተኛ አገልግሎት ፍሬ

አገልግሎት ስም ሳይሆን ክርስቶስ በእኛ ውስጥ ራሱን በመግለጥ ሰዎችን ለማዳንና አካሉን ለማነፅ በእኛ አድሮ የሚሠራው የፀጋ ሥራ መሆኑን በጥቂቱ አይተናል፡፡ ሁሉን ይሞላ ዘንድ ከሰማያት በላይ የወጣው ክርስቶስ ይህን ዓላማውን ለማሣካት የሚጠቀምባቸውን የወንጌል ሠራተኞች እንደሰጠም ተመልክተናል፡፡ ነገር ግን የእርሻው ባለቤት (የሰው ልጅ) እርሻው በሆነው በዓለም ላይ የወንጌል ሠራተኞች የሆኑትን የመንግሥት ልጆች ሲዘራ፣ ሲልክ፣ ሲያሰማራ፣ ጠላት ዝም ብሎ እንደማይመለከት ይልቁኑም የራሱ የሆኑትን የዲያቢሎስ ልጆች በአገልግሎት ስም በዓለም ላይ እንደሚዘራ፣ እንደሚልክና እንደሚያሰማራ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አስቀድሞ በእርሻው እንክርዳድ ምሳሌ አስተምሮአል፡፡[247] ስለዚህ ሠራተኞች ወደ ዓለም ሲወጡ በማን መንፈስ እንደሚገለጡ መመርመር የአማኞች ኃላፊነት ነው፡፡ እንዴት ይለያሉ የሚል ጥያቄ ቢነሳ መልሱ ቀላልና ግልጽ ነው፡፡ ጌታ እንዳስተማረው በፍሬያቸው እናውቃቸዋለን፡፡[248]

ፀሐፊው የሠራተኞች የሥራ መስክ የሆነችውን ቤተ ክርስቲያን በሁለት ተምሳሌት ይስላታል፣ አካልና ሕንፃ፡፡ እነዚህ ሁለት ተምሳሌቶች ቀደም ሲል በ1፡23 እና በ2፡20-22 ከተጻፉት መግለጫዎች ጋር ይስማማሉ፡፡ ሁለቱንም አንድ የሚያደርጋቸው ጉዳይ ቢኖር በአንድነት ተያይዘው ማደጋቸው ነው፡፡ አካልም ወደ ሙሉነት፣ ሕንፃም ወደ ፍፃሜ ያድጋሉ፡፡ ነገር ግን እርስ በርስ ተያይዘው እንጂ ተነጣጥለው አይደለም፡፡ ምንም እንኳ ማደግ ብንመኝ የሰውነታችን ክፍሎች ተነጣጥለው እንዲያድጉ አንሻም፡፡ አፍንጫችን ከሌላው የሰውነታችን ክፍል ተነጥሎ ቢያድግ፣ ቀኝ እጃችን ግራ እጃችንን ጥሎ ቢመነደግ፣ አንድ ባልንጀራዬ እንዳለው ሞላላ ሰላላ ሆንን እንጂ አላደግንም፤ ሕንፃም እንዲሁ እየተገጣጠመ፣

[246] ማቴ. 23፡8-12; ያዕቆብ ጴጥሮስን በኢየሩሳሌም ጉባኤ "ስምዖን"፣ ጳውሎስ ጴጥሮስን በአንፆኪያ ጉባኤ "ጴጥሮስ"፣ ጴጥሮስ በሁለተኛ መልዕክቱ ስለ ጳውሎስ ሲጽፍ "ወንድማችን ጳውሎስ" ተብለው በስማቸው ተጠሩሩ እንጂ ዛሬ እንደ ምንሰማው አንድም ቦታ በማዕረግ አልተጠራሩም፡፡

[247] ማቴ. 13፡24-30; 36-43

[248] 1ዮሐ. 4፡1; ማቴ 7፡15-20



For more books www.amharicchristianbooks.com

እርስ በርሱ እየተያያዘ ያድጋል፡፡ ስለዚህ የእውነተኛ የወንጌል ሠራተኞች መገለጫ ፍሬ፣ አማኞች በየአጥቢያቸው፣ በፍቅር ተያይዘው እንዲያድጉ መሠረት መጣልና ሁኔታዎችን ማመቻቸት ነው፡፡

እውነተኛ አንድነት፣ እንደ አሸዋ በሆነ ጊዜያዊ ስሜት ላይ የሚቆም ሳይሆን የአንድነት መሠረት የሆነውን የእግዚአብሔርን ልጅ በማመንና በማወቅ ጽኑ ዐለት ላይ የሚገነባ ሕንፃ ነው፡፡ ስለዚህ የወንጌል ሠራተኞች ከሁሉ በፊት አማኞች ያመኑትን የእግዚአብሔርን ልጅ እንዲያምኑ ብቻ ሳይሆን እንዲያውቁ ተግተው ሊሠሩ ይገባል፡፡

እውነተኛ የወንጌል ሠራተኞች በአንድ አጥቢያ ቆይታቸው አማኞችን ለአገልግሎት ሥራ ያዘጋጃሉ እንጂ የሁሉንም አባላት ተግባር ጠቅልለው ለማከናወን በመታገል ራሳቸውንም አይገድሉም፣ አንዳች ድርሻ የሌላቸው ጥገኛ ተከታዮችም አያፈሩም፡፡ አማኞች በሠራተኞቹ ላይ የአገልግሎት ጥገኛ፣ ሠራተኞቹ በአማኞቹ ላይ የገንዘብ ወይም የጥቅም ጥገኛ እንዲሆኑ አያደርጉም፡፡ ምንም እንኳ የሚያስተምረው ከሚማረው ጋር መልካምን ነገር ሁሉ ቢካፈልም፣ የጥገኝነት ስሜት እንዲፈጠር ግን አይፈቅዱም፡፡[249] ይህ የመጀመሪያው ክፍለ ዘመን የሐዋርያት ወግ አልነበረም፡፡ ይልቅ በአንድ ወቅት የጀመሩትን ሥራ ትተው ወደሌላ አዲስ የሥራ መስክ እንደሚሄዱ በማሰብ እነርሱ በማይኖሩበት ጊዜ አማኞች የራሳቸውን ድርሻ ተግተው እንዲወጡ አብነት በመሆን ያሳዩአቸዋል፡፡

አማኞችን ሁሉ ለቅዱሳን አገልግሎት ያዘጋጁቸዋል እንጂ፣ ሲያገለግሏቸው አይኖሩም፡፡ ይህም በአዲስ ኪዳን፣ አማኞች ሁሉ ካህናት መሆናቸውንና እርስ በርስ በመቀባበል የአጥቢያቸውን የሥራ ኃላፊነት ሊወጡ እንደሚገባቸው ያስገነዝባል፡፡ አካሉ ወደ ሙላት፣ ሕንፃውም ወደ ፍፁምነት እንዲደርስ የአማኞች ራስን በመቻል ማደግ ወሳኝ ነው፡፡ አንድነት ከሌለ ደግሞ ማደግ አይቻልም፡፡ እዚህ ጋ ስለ እውነተኞቹ ሠራተኞች ልብ ልንለው የሚገባን አንድ ቁም ነገር በእነርሱና በአካሉ በቤተ ክርስቲያን መካከል ያለው ግንኙነት የእናትና የልጅ ዓይነት መሆኑን ነው፡፡ እነዚህ ሠራተኞች በክርስቶስ ሞትና ትንሳኤ የተገኘችውን ቤተ ክርስቲያንን በራእይ ይፀንሳሉ፣ በፀሎት ያምጣሉ፣ ወንጌልን በመስበክ በብዙ መከራ ይወልዳሉ፣ ከዚያም ያሳድጋሉ በመጨረሻም ራስ ያስችላሉ፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥ የአማኞች የጥገኝነት ሁኔታ ደረጃው እየቀነሰ ይሄዳል እንጂ አይጨምርም፡፡ ጽንስ በማህፀን ሳለ መቶ በመቶ በእናቱ ላይ ጥገኛ ነው፣ ከተወለደ በኋላ

[249] ገላ. 6፡6-10; 1ቆሮ 9፡14; 1ጢሞ. 5፡17-18



For more books www.amharicchristianbooks.com

በጨቅላነቱ ጥገኝነቱ ቢቀጥልም፣ የጽንሱን ያህል አይሆንም፣ ሲያድግ ወደ ትምህርት ቤት መሄድ ሲጀምር እየቀነሰ፣ እየቀነሰ ይመጣና ኮሌጅ ሲገባ፣ ሚስት ሲያገባ፣ ልጆች ሲወልድ እየመነመነ ይሄዳል፤ በፍፃሜውም ያከትማል፡፡ ከዚያ በኋላ በጋራ ፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የፍቅር ግንኙነት ይቀጥላል እንጂ ጥገኝነት አይኖርም፡፡ ልክ እንዲሁ አካል ወደ ሙሉ ሰውነት ሲደርስ "ራሱን በፍቅር ለማነጽ አካሉን ያሳድጋል፡፡" ሕንፃውም ሲጠናቀቅ በመንፈስ ለእግዚአብሔር መኖሪያ በመሆን አገልግሎቱን ይቀጥላል፡፡ ቅዱሳን ሁሉ ከሕፃንነት ወደ ሠራተኝነት (ቢያንስ በአካባቢያቸው) ይሸጋገራሉ፡፡ ይህም የመንፈስ አንድነትን ለመጠበቅ የሚሠሩ የእውነተኛ አገልጋዮች የድካም ፍሬ ነው፡፡

ከፉዎች ሠራተኞች ግን ፈጽሞ እንደዚህ አያደርጉም፡፡ አማኞች ሁልጊዜ ሕፃናት ሆነው እንዲኖሩ ይፈልጋሉ፡፡ አለዚያ ለሽንገላና ለተንኮላቸው አይታለሉማ! እነዚህ ሠራተኞች ትምህርት አላቸው፣ ነገር ግን ትምህርታቸው መሠረት ሳይሆን እንደ ንፋስ የተመሠረተውን የሚያፈርስና የሚነጣጥል ነው፡፡ አማኞች መሪ እንደሌለው መርከብ በኮምፓስ ሳይሆን በነፋስ እንዲነዱ ይፈልጋሉ፡፡ አላማቸውም የመንፈስን አንድነት በማናጋት አማኞች ራስ ወደ ሆነው ወደ ክርስቶስ እንዳይደርሱ ማገድ ነው፡፡ ሐዋርያው ይህንን "አይገባንም" ይላል፡፡ (4፡14)

ይልቅ እውነተኞቹ ሠራተኞች የጣሉት መሠረት ላይ በወርቅ፣ በብርና በከበረ ድንጋይ እየገነባን፣ እርስ በርሳችን የሕይወትን ቃል እየተመጋገብን፣ እንደ ጤናማ አካል የሕይወት ራስ ወደ ሆነው ወደ ክርስቶስ ልናድግ ይገባል፡፡ ያን ጊዜ እያንዳንዱ አማኝ ልክ እንደ አካል በደም ሥር፣ በነርቭ ሥርዓት፣ በጅማት ትስስር ተያይዞ፣ እያንዳንዱ የተሰጠውን ልዩ ተግባር በብቃት እያከናወነ፣ በተዘረጋለት የሕይወት መስመር ከራስ የሚመጣለትን ምግብ ለሰውነት ክፍሎች ሁሉ እያዳረሰ ራሱ አውቆ ያድጋል፡፡ ይህም ተግባራዊ የሚሆነው ስለ ክርስቶስ የተገለጠልንን እውነት እርስ በርሳችን በፍቅር በመነጋገር መተናነጽ ስንችል ነው፡፡(4፡15)



For more books www.amharicchristianbooks.com

# ምዕራፍ ፺
# በአዲስነት መመላለስ

ኤፌ. 4፡17-5፡2

በአንድ አገር ውስጥ ለመኖር የአገሩን ሕግና የምድሩን ሥርዓት ማወቅና ማክበር ግድ ይላል፡፡ ጳውሎስ በሌላ መልእክቱ እንደ ጻፈልን አብ በቅዱሳን ርስት በብርሃን እንካፈል ዘንድ ከጨለማው ሥልጣን አድኖ የኃጢአታችን ሥርየት የሆነውን ቤዛነት ወዳገኘንበት ወደ ፍቅሩ ልጅ መንግሥት እንዳፈለሰን ነግሮናል፡፡[250] ነገር ግን ይህ ቤዛነትና ፍልሰት የመንፈስ እንጂ ገና የአካል ባለ መሆኑ በሥጋ የምንኖረው ቀድሞ በነበርንበት አገርና ማኅበረሰብ መካከል ነው፡፡ ሆኖም ይህንን ግዑዝ ምድር እንደ ጋራ ርስት ብንካፈልም፣ ከሕይወት አኳያ ፈጽሞ በተለያየ ዓለም የምንኖር የተለያየ አገር ዜጎች ነን፡፡ ልዩነታችን የሚገለፀው እንደ ቀድሞው የአይሁድና የአሕዛብ ልዩነት በሥጋ ግርዘትና ውጪያዊ የመንፃት ሥርዓቶችን በመጠበቅ ሳይሆን በአስተሳሰብ ተሃድሶና በአኗኗር ዘይቤ ነው።

በአሕዛብ አገር ተወልዶ ያደገውና የዘመኑን ዓለም ጠንቅቆ የሚያውቀው ጳውሎስ፣ የአሕዛብ ኑሮ በምኞት፣ በርኩሰትና ቅጥ በሌለው ብልግና የተሞላ እንደሆነ ይነግረናል፡፡ ሆኖም በዚህ አያበቃም፣ ይህ በርኩሰትና በሴሰኝነት ድንበር የጣሰ የልቅነት ኑሮ ከየት እንደሚፈልቅ ምንጩን ያሳየናል፡፡ ምንጩ በአእምሮ ከንቱነት መመላለስ ነው፡፡ ጠቢቡ ሰሎሞን *"ሰው እንደሚያስብ እንዲሁ ነው . . ."* እንዳለ የማንነታችን ሠገነት፣ የሁለንተናችን መዘውር የሆነውን አእምሮአችንን የተቆጣጠረ ነገር፣ ተግባራችንን ሁሉ ወደ ወደደው ሊመራው እንደሚችል ሳይታለም የተፈታ ነው፡፡ ለመሆኑ ከንቱ አእምሮ ምንድነው? የማያስብ፣ የማይመራመር፣ የማይጠበብ አእምሮ ነው? በፍፁም፡፡ ጳውሎስ በዚህ ስፍራ ስለ ከፉ ምግባራቸው የሚኮንናቸው አሕዛብ፣ በንግግር የላቁ፣ በጥበብ የመጠቁ፣ በሥራ የረቀቁ ፣ግሪካውያንና ሮማውያን ናቸው፡፡ አእምሮን ከንቱ የሚያሰኘው የተፈጠረበትን ዓላማ ማከናወን ሲሳነው ነው፡፡ ሰው የተፈጠረው የሚኖርበትን አካባቢ እንዲመረምርና እንዲያውቅ ብቻ ሳይሆን ፈጣሪውን እንዲያውቅ ጭምር ነው፡፡

እነዚህ አሕዛብ ግን ስለ እግዚአብሔር ሊታወቅ የሚችለው ግልጥ ሆኖ ሳለ

---

[250] ቆላ 1፡14



For more books www.amharicchristianbooks.com

እግዚአብሔርን ለማወቅ ስላልወደዱ አእምሮአቸው ከንቱ ሆነ፡፡[251] ችግራቸው አለማወቅ ብቻ ቢሆን ጉዳቱ ባልከፋ ነበር፡፡ በማወቅ ይፈወሳላ! ነገር ግን ይህ ጠንቅ እንዳይድን የልብ ደንዳንነት ተጨመረበት፡፡ በልባቸው ደንዳናነት ወደ እነርሱ የሚመጣውን የእግዚአብሔር ወንጌል ተቃወሙ፡፡ ከብርሃን ይልቅ ጨለማን ወደዱ፡፡  ላመኑትና ለዳኑት አሕዛብ የመጣው የርስት ጥሪ ለእነርሱም ደርሶ ነበር ግን ገፉት፡፡ ስለዚህ ያመኑት ሕይወትን ሲወርሱ እነዚህ ከእግዚአብሔር ሕይወት ራቁ፡፡

ቀደም ሲል "መራቅ" የሚለውን ቃል የተጠቀመው አሕዛብ ሁሉ የእስራኤል የጋራ ብልጽግና ከነበረው የርስት ተስፋ ቃል መራቃቸውን ለማሳየት ነበር፡፡(2፡11-17) አሁን ግን በወንጌል ያላመኑ ሰዎች ሁሉ (ያላመኑትን አይሁዳውያን ጨምሮ) የምሥራች ከሆነው ከእግዚአብሔር ሕይወት ራቁ፡፡ ከብርሃን በተራቀ ቁጥር ጨለማው ድቅድቅ እንደሚሆን ሁሉ እነዚህ ኢ-አማንያን  ከእግዚአብሔር ብርሃን በራቁ ቁጥር የሚሠሩትን ተግባር፣ የሚሄዱበትን አቅጣጫ፣ የሚኖሩበትን አላማ እየሳቱ፣ ቅጥ ላጣ ኑሮ ራሳቸውን አሳልፈው ሰጡ፡፡

ሐዋርያው የሚጽፍላቸውን ወገኖች ጥለውት ወደመጡት ወደ ቀድሞው የኑሮ ዘይቤ ተንሸራተው እንዳይወድቁ በብርቱ ያስጠነቅቃቸዋል፡፡ ባመኑ ጊዜ በአገልጋዮቻቸው የተማሩትን እውነትና እጅ በእጅ የተቀበሉትን ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር ያስታውሳቸዋል፡፡ እንደ ሌሎቹ አብያተ ክርስቲያናት ከራሱ ከጳውሎስ አንደበት ባይማሩም አብረውት ከሚሠሩት እንደ ኤጳፍራ ካሉ አገልጋዮች ተምረዋልና፡፡[252] የተማሩትም ሕይወት አልባ የሆኑ ኃይማኖታዊ ሥርዓቶች ሳይሆን አሃዳዊ የክርስትና ትምህርት የሆነውን ክርስቶስን ነው፡፡

ክርስቶስን፣ በክርስቶስ ውስጥ በመሆን ከክርስቶስ ተምረውታል፡፡(4፡20-21) እነዚህ ክርስቶስን በቃልም፣ በኑሮም፣ በሥራም፣ በንጽህናም ምሳሌ በመሆን ያስተማሯቸው መምህራን ሊበረዝ የማይችል፣ የማይሸቃቀጥ የሥነ ምግባር መርህ እንዳስተላለፉላቸው አያጠያይቅም፡፡ በዚህ ትምህርት ውስጥ፣ የገቡበትን በጽድቅና በቅድስና ያሸበረቀ የአዲስ ፍጥረት እውነታ በተግባር አይተዋል፡፡ ከውስጡ የወጡትን እያረጀ፣ እየሞተና እየበሰበሰ ብሎም እየጠፋ የሚሄደውን የአሮጌውን ሰው ማንነት ተረድተዋል፡፡ ነገር ግን መማርና መረዳት ብቻውን አንዳች ውጤት የለውም፡፡ የታወቀ ነገር ካልተተገበረ ባይታወቅ ይሻላልና፡፡ ማወቅ የሚፈተነው

[251] ሮሜ 1፡18-32

[252] ቆላ 1፡7



For more books www.amharicchristianbooks.com

በድርጊት ነው፡፡ እነዚህም አማኞች "ፊተኛ ኑሮአቸውን እያሰቡ እንደሚያታልል ምኞት የሚጠፋውን አሮጌውን ሰው እንዲያስወግዱ፣ በአእምሮአቸውም መንፈስ እንዲታደሱና ለእውነት በሚሆኑ ጽድቅና ቅድስና እንደ እግዚአብሔር ምሳሌ የተፈጠረውን አዲሱን ሰው እንዲለብሱ" ታዘዋል፡፡[253] (4፡22-24) በሚያምንና በማያምን መካከል ያለው ልዩነት እንዲህ በቀላል የሚገለጽ አይደለም፡፡

ክርስትና ሰዎች በባህሪ በጥቂቱ የሚሻሻሉበት ፀባይ ማረሚያ አይደለም፡፡ ልዩነቱ የአሮጌና የአዲስ ፍጥረት ልዩነት ነው፡፡ ለውጡም የለበጣ ሳይሆን ሥር ነቀል ነው፡፡ ስለዚህ በምኞት የረከሰውን፣ በመጨረሻም የሚጠፋውን፣ አሮጌውን የኑሮ ጠባይ እንደ ጨርቅ አውልቀን፣ በጽድቅና በቅድስና ያጌጠውን አዲሱን ሕይወት እንድንለብስ ታዘናል፡፡ ታዘናል የምለው ያለ ምክንያት አይደለም፡፡ እግዚአብሔር አሮጌውን እንዲያወልቅልንና አዲሱን እንዲያለብሰን ልንፀልይ አይገባንም፡፡ ይሄ ድርሻን ያለማወቅ አባዜ ነው፡፡ መለኮታዊ አነሳሽነትና ሰብዓዊ ኃላፊነት እጅ ለእጅ የሚቀባበሉ ተያያዥ ጉዳዮች ናቸው፡፡ እኛ ራሳችንን አዲስ ፍጥረት አላደረግንም፣ ከሃሌ-ኩሉ የሆነ እግዚአብሔር ራሱ አደረገን፡፡ ይህን ከተረዳን በዕለት ተለት ኑሮአችን አሮጌውን ማስወገድ፣ አዲሱን መልበስ፣ የእኛ ድርሻ መሆኑን መገንዘብ አያዳግተንም፡፡ የማይቻለው ሁሉ የእርሱ ድርሻ፣ የሚቻለው ሁሉ የእኛ ድርሻ ነውና፡፡ እኛ የእርሱን ድርሻ አልፈን መሥራት አንችልም፣ እርሱም የእኛን ድረሻ አልፎ መሥራት አይፈልግም፡፡

ሆኖም ይህንን ለመተግበር አንድ ወሳኝ ነገር ያስፈልገናል፡፡ አሕዛብ እንዲያ ቅጥ ያጣ ኑሮ እንዲኖሩ የዳረጋቸው ምን ነበር? በአእምሮአቸው ከንቱነት መመላለስ አይደል? እኛም አሮጌውን ሰው አስወግደን አዲሱን ሰው ለመልበስ በአእምሮአችን መንፈስ መታደስ ይኖርብናል፡፡ አእምሮ የሥጋም ይሁን የመንፈስ ሕይወት፣ የተቆጣጠረው ሁሉ የሚገለጥበት የማንነት ሰገነት ነው ብለናል፡፡ አሮጌው የሥጋ ሕይወት ሲቆጣጠረው ከክፉ መሻቱና ከምኞት ጋር ይገለጥበታል፣ አዲሱ የመንፈስ ሕይወት ከተቆጣጠረው ደግሞ ጽድቅና ቅድስና ይገለጥበታል፡፡ አእምሮአችን ሲታደስ በፍጥረት የተሰጠውን ነገር ግን በውድቀት ያጣውን መንፈሳዊ ሥራ መሥራት ይጀምራል፡፡ ያም የአእምሮ መንፈሳዊ ሥራ መልካሙንና ክፉውን የመለየት ሥራ ነው፡፡[254] ያኔ የመጣለትን አሳብ ሁሉ አያስተናግድም፡፡ ከሥጋ ይሁን ከመንፈስ፣ ከእግዚአብሔር ይሁን ከዓለም፣ ከጌታ ይሁን ከሰይጣን፣ ምንጩን መርምሮ ይለያል፣ አሮጌውን ያስወግዳል አዲሱን ይገልጣል፡፡ ያኔ አዲሱን

---

[253] በቆላስያስ መልእክት ይህ ተግባር በአላፊ ጊዜ (past tens) ተጽፎአል፡፡ ቆላ 3፡10
[254] ዕብ 5፡14 ሮሜ 12፡2



For more books www.amharicchristianbooks.com

ሰው ለበስን ማለት ነው፡፡

መልበስ ማለት ወደ አደባባይ ስንወጣና በሰዎች መሃል ስንመላለስ እንዲታይ የማንፈልገውን እርቃናችንን ሸፍነን፣ እንዲታይልን የምንሻውን ንፁሕና ያማረ ነገር መጎናፀፍ ማለት ነው፡፡ ስለዚህ የለበስነው ነገር በሰዎች ፊት ሊሸሸግ አይችልም፣ ይልቅ ፊት ለፊት ደምቆ ይታያል፡፡ የሚለብሰው ስለ ሌለው ፣ያረጀ፣ ያደፈና የተቀደደ ቡቱቶ የሚከናነብ ሰው፣ በድሃ አቅሙ ሊገዛው የማይችል አዲስ ልብስ ስጦታ ቢሰጠው ፈንድቆ አያባራም፡፡ ከዚያም አሮጌውን አውልቆ ጥሎ አዲሱን ይለብሳል እንጂ ቁም ሳጥን ውስጥ አይቆልፍበትም፡፡ አዲሱ ልብስ ቢኖረውም እንኳ ካልለበሰው እሱም አይደምቅበትም፣ ተመልካችም አያደንቀውም፡፡ እኛም አዲስና ሰማያዊ፣ ዋጋው በእግዚአብሔር ፊት እጅግ ውድ የሆነ፣ የማያረጅና የማይጠፋ፣ ለሥርክ፣ ለክት፣ ለሥልፍ፣ ለጌጥ ለሁሉ ሁኔታ የሚመች፣ ክረምት በጋ፣ ፀደይ፣ መፀው ሳይል ለሁሉ ወቅት የሚሆን፣ የሕይወት ልብስ እንድንጎናፀፍ ተሰጥቶናል፡፡ ሆኖም በምኞት ያደፈውንና የሚጠፋውን አሮጌውን ሕይወት አስወግደን አዲሱን ካልለበስን በስተቀረ ሰዎች በእኛ ላይ የክርስቶስን ውበት ሊያዩ አይችሉም፡፡

በመቀጠል ይህን የማውለቅና የመልበስ ሂደት እንዴት በተግባር እንደምንፈጽም ለማሳየት አምስት ርዕሰ ጉዳዮች ላይ መመሪያ ተሰጧል፡፡ በመመሪያው መሠረት ማውለቅና መልበስ እንለማመዳለን፡፡

## ከውሸት ወደ እውነት

> *"ስለዚህ ውሸት አስወግዳችሁ እርስ በርሳችን ብልቶች ሆነናልና እያንዳንዳችሁ ከባልንጀሮቻችሁ ጋር እውነትን ተነጋገሩ፡፡" 4፡25*

በዚህ ሥፍራ ውሸትን ለመግለፅ የገባው ቃል የእግዚአብሔርን እውነት ለመቃወም የሚነገርን ውሸት ወይም በሕግ ፊት ከመሃላ በታች የሚዋሽን ውሸት የሚያመለክት ቃል አይደለም፡፡ ነገር ግን ከባልንጀሮቻችን ጋር ዕለት ተለት በሚኖረን ግንኙነት የምንለዋወጣቸውን መረጃዎች ያመለክታል፡፡ መዋሸት ወይም እውነትን አለመናገር የአሮጌው ሰው መታወቂያ ነው፡፡ በክርስቶስ አምነን የአዲሱ ሰው አካል ብንሆንም፣ የኃጢአት ሥጋ የሆነው አሮጌው ሰዋችን የማንነታችንን ሠገነት እስከ ተቆጣጠረ ድረስ፣ የበላይነቱን ለማሳየት ከመታገል አይቦዝንም፡፡ ስለዚህ በንግግራችን ውስጥ ለክብር፣ ለዝና፣ ለጥቅም ወ.ዘ.ተ የቋጠርናቸውን ድብቅ የእኔነት አጀንዳዎች በመንተራስ የሰሉ ምክንያቶችን በመፍጠር በአንደበታችን ይተላለፉ ዘንድ የውሸት አሳቦችን እያመረተ ለአእምሮአችን ያቀብላል፡፡ ያኔ ከአሮጌው የሥጋ ሕይወት



For more books www.amharicchristianbooks.com

ተጽእኖ ተላቆ በአዲሱ የመንፈስ ሕይወት የሚመራ የታደሰ አእምሮ ካለን፣ የመጣለትን በምክንያት የተለበጠ የውሸት አሳብ በአንደበታችን ሳይተላለፍ በፊት መርምሮ ይለየውና አሽቀንጥሮ ይጥለዋል፤ ያስወግደዋል፡፡ አእምሮአችን ካልታደሰ ግን በተንኮል በተቀመሙት የሥጋ ምክንያቶች እየተረታ፣ በረቀቀ ስልቱ እየተታለለ የመጣለትን ሁሉ ያስተላልፋል፡፡ በዚህ ፍልሚያ ውስጥ የአማኙ ድርሻ ከፍተኛ ነው፡፡ በእውነተኛ ማንነት፣ እውነትን ለመመስከር የተፈጠረውን አዲሱን ማንነት አጥብቆ በመረዳት፣ በማንኛውም ጊዜና ሁኔታ እውነት መናገር የሚያስከፍለው ዋጋ ቢኖርም እንኳ ለመክፈል ፈቃደኛ በመሆን እውነትንና እውነትን ብቻ ለመናገር መጨከን የአማኙ ድርሻ ነው፡፡ ይህም በአንድ ጀንበር የሚገኝ ድል ሳይሆን፣ እግዚአብሔርን ለመምሰል የሚደረግ ያላሰለሰ ጥረት ውጤት ነው፡፡ ያኔ የክርስቶስ ማኅበረሰብ ያለመሃላ በቃሉ ብቻ የሚታመን የሐቅ መናሃሪያ ይሆናል፡፡[255]

ጳውሎስ እርስ በርሳችን እውነትን እንነጋገር ዘንድ ግድ እንዳለብን ምክንያት አድርጎ ያቀረበው እውነታ፣ የቤተ ክርስቲያን መሠረታዊ አስተምህሮ የሆነውን የአዲሱን ተፈጥሮአችንን አካላዊ ይዘት ነው፡፡

> *"እርስ በርሳችን ብልቶች ሆነናልና ከባልንጀሮቻችሁ ጋር እውነትን ተነጋገሩ"*

የቀድሞው አሮጌ ተፈጥሮ በእኔነትና በግለኝነት ላይ የተመሠረተ የተናጠል ሕይወት ስለ ነበርና በዚህ ሥርዓት ውስጥ እኔና እሱ፣ እኔና እሷ፣ የየራሳችንን ኑሮ የምንኖር የተለያየን ሰዎች ነንና ባልንጀራዬን ዋሽቼ ራሴን እጠቅማለሁ ብለን እናስብ ነበር፡፡ በአዲሱ የሕይወት ሥርዓት ውስጥ ግን ሁላችንም በአንድ መንፈስ የተሳሰርን የአንድ አካል ብልቶች ነንና ወንድምን ወይም እህትን መዋሸት ሌላ ሰው የመዋሸት ጉዳይ ሳይሆን ፣ራስን የማታለል ያህል ቂልነት ይሆናል፡፡ ማንም ሰው የአካል ክፍሉን ሊዋሽ አይችልምና፡፡

## ከቁጣ ወደ ይቅርታ

> *"ተቆጡ ኃጢአትንም አታድርጉ በቁጣችሁ ላይ ፀሐይ አይግባ ለዲያቢሎስም ፈንታ አትስጡት፡፡"*

ጳውሎስ ይህን ክፍል ሲጽፍ መዝሙር 4 በውስጡ መኖሩ ግልጽ ነው፡፡ ዳዊት በመዝሙሩ *"ተቆጡ ነገር ግን ኃጢአትን አታድርጉ፡፡"* በማለት አስቀድሞ ቃል በቃል ጠቅሶታልና፡፡ በዚህ ትዕዛዝ ውስጥ የሚያስገርመውና ትኩረት የሚሻው

[255] ማቴ 5፡33-37



For more books www.amharicchristianbooks.com

ጉዳይ ቁጣና ኃጢአት ተለያይተው መታየታቸው ነው፡፡ ይህም ሰው ተቆጥቶም ከኃጢአት ነፃ ሊሆን የሚችልበት ሁኔታ እንዳለ እናያለን፡፡ በክርስቶስ ኢየሱስ እንደ እግዚአብሔር ምሳሌ የተፈጠረ ሰው ዋሽቶ ከኃጢአት ነፃ ሊሆን አይችልም፡፡ በምሳሌው በተፈጠረው በእግዚአብሔር ዘንድ ውሸት የለምና፡፡ ነገር ግን በ5፡6 ላይ እንደ ተፃፈልን በእግዚአብሔር ዘንድ ቁጣ አለ፡፡ ሆኖም ይህ ቁጣ ከፍቅር፣ ከኃላፊነት፣ ሌላውን ከመታደግ ስሜት የሚመነጭ እንጂ ከእኔነት፣ ከጥላቻ፣ ከክፋት የሚፈልቅ የሥጋ ቁጣ አይደለም፡፡ በቅዱሳን ሕብረት ሆነ በቤተሰብ መካከል በተቀራረብን መጠን ሳንቆጣ መኖር አንችልም፡፡ እግዚአብሔርን የሚያስቆጡ ነገሮች ሲከሰቱ በነገሮች ላይ ልንቆጣ እንችላለን፤ ደግሞ ይገባል፡፡ ነገር ግን ቁጣችን የሰው ቁጣ ከሆነ የእግዚአብሔርን ጽድቅ ሊሠራ አይችልም፡፡ እኛንም በኃጢአታችን ይበክለናል ስለዚህ በመቆጣትና ባለመቆጣት መካከል ያለውን ሚዛን መጠበቅ ይኖርብናል፡፡ እግዚአብሔር በውስጣችን ሳይቆጣ የራሳችንን ቁጣ መቆጣት፣ እግዚአብሔር ሲቆጣ በይሉኝታ ታፍነን፣ ሰውን በመፍራት ታጅለን አለመቆጣት ሁለቱም ኃጢአት ይሆናሉ፡፡ ጽድቅ ያለበት ቁጣ ዋነኛ መገለጫው ይህ ነው፡፡

ትኩረታችን ሰውየው ወይም ሴትየዋ ላይ ከመሆን ይልቅ በእነርሱ በኩል የሚመጣ አሳብ ወይም የሚገለጠው ተግባር ላይ ይሆናል፡፡ ይህን መለየት አስቸጋሪ ቢመስልም፣ በመንፈስ ለታደሰ አእምሮ እምብዛም አስቸጋሪ አይሆንም፡፡ ከአዲሱ ሰው የሚፈልቅ የጽድቅ ቁጣ አሳቡና ተግባሩ ላይ ተቆጥቶ ሰውየውን ማቀፍ አይቸገርም፡፡ ቁጣውንም በፀሎት ለእግዚአብሔር በመንገር ያበርዳል እንጂ ሰውን ለመበቀል አይሞክርም፡፡ ለእግዚአብሔር በፀሎት ካሳሰበ በኋላ ከአእምሮው አውጥቶ በሰላም ይተኛል እንጂ ነገር ሲያጠነጥንና ሲብከነከን አያድርም፡፡ ለምሣሌ በልጆቻችን ላይ ክፉ ተግባር ስናይ እንቆጣለን፡፡ ባንቆጣ የወላጅነታችንን ኃላፊነት አልተወጣንምና በእግዚአብሔርም በሰውም ዘንድ ተጠያቂ ያደርገናል፡፡ ነገር ግን ተቆጥተን፣ ቀጥተን ስናበቃ ልጆቻችንን አይናችሁ ላፈር ብለን አንተዋቸውም፤ ወዲያው ተመልሰን እናቅፋቸዋለን፣ ፍቅራችንን እንገልጥላቸዋለን፣ የቀጣንበትንም ምክንያት ለይተን እናሳያቸዋለን፣ እነርሱም በእቅፋችን ውስጥ ይገባሉ፡፡ የበለጠም በአክብሮት ያፈቅሩናል፡፡

ጳውሎስ *"በቁጣችሁ ፀሐይ አይግባ"* ያለው ፀሐይ መጥለቋና አለመጥለቋ የሚያመጣው ምትሃታዊ ለውጥ ስላለ ሳይሆን፣ ከመኝታና ነገርን እያሰላሰሉ ከማደር ጋር አዛምዶ ለማሳየት ይመስላል፡፡ ቀን ከሌሎች ጋር ያሳለፍነው ነገር ሌት እንቅልፍ ነስቶ ካብሰለሰለን አሮጌ ሰዋችን በሥራ ላይ ነው፡፡ ዲያቢሎስም ይህን



For more books www.amharicchristianbooks.com

አጋጣሚ የመንፈስ አንድነት ለማጥፋት ዘመቻው ከመጠቀም አይቦዝንምና ቁጣን ፈጥነን ከራሳችንም ሆነ ከተቆጣንባቸው ሰዎች ውስጥ ማውጣት ይኖርብናል፡፡ ይህ ምልስነት፣ ቅንነት፣ ሰላም ናፋቂነት የአዲሱ ሰው ባሕሪ ነውና ልንጎናፀፈው ይገባል፡፡

## ከሥርቆት ወደ ማካፈል

*"የሰረቀ ከእንግዲህ ወዲህ አይስረቅ ነገር ግን በዚያ ፈንታ ለጎደለው የሚያካፍለው እንዲኖርለት በገዛ እጆቹ መልካምን እየሠራ ይድከም፡፡"*

ስርቆት የራስ ወዳድነት፣ የስስት፣ የከፉ ምኞት አስቀያሚ መገለጫ ነው፡፡ ያልደከምንበትን የሌላውን የድካም ፍሬ በመውሰድ እርሱ ሲያዝን እኛ ስንደሰት፣ እርሱ ሲያለቅስ እኛ ስንስቅ፣ እርሱ ሲያጣ እኛ ባለ ንብረት ለመሆን ማሰብ፣ የአሮጌው ሰው ዝቅጠት ዓይነተኛ ገፅታ ነው፡፡ ይህንን ነው እንደ እድፋም ልብስ አስወግዱ የሚለን፡፡ ነገር ግን ስርቆትን ማስወገዳችን ብቻውን አዲሱን ሰው መልበሳችንን አያሳይም፡፡ የአዲሱ ሰው ባሕሪ በፊት ይሰርቁ የነበሩ እጆች መስረቅ እንዲያቆሙ ብቻ ሳይሆን፣ መልካም እንዲሠሩ፣ ደክመው ያገኙትንም ለጎደላቸው እንዲያካፍሉ ያደርጋል፡፡ አዲሱን ሰው የለበሱ አማኞች ትጉሃን የሥራ ሰዎች ሊሆኑ ይገባል፡፡ ነገር ግን ሠርተው የሚያገኙትን ሁሉ የራሳቸውን ኑሮ ብቻ ለማሻሻል አያውሉትም፡፡ የሚሠሩት እንደ እነርሱ መሥራት ለማይችሉት ጭምር እንደሆነ ያምናሉ፡፡ ስለዚህ ለጎደለው ያካፍላሉ፡፡ ትላንት ያልደከሙበትን የሌላውን ሃብት ሲያራቁቱ የነበሩ ዛሬ የራሳቸውን የድካም ፍሬ ለሌላው ሲያካፍሉ ከማየት የበለጠ ለውጥ ምን አለ?

## ከከፉ ቃል ወደ በጎ ቃል

ፀሐፊው ከእጅ ተግባር ወደ አንደበት ተግባር ይሻገራል፡፡ ንግግር ትልቅ ፀጋ ነው፡፡ በእጁ የሞትና የሕይወት ኃይል እንዳለ ቅዱሳት መጽሐፍት ያስተምሩናል፡፡[256] በአሮጌው ህይወት ተጽእኖ ሥር የሚኖር ሰው ግን የአንደበትን ክቡርነት አያስተውልም፡፡ ወደ አእምሮው የመጣለትን ሁሉ ወደ ውጭ ያስተላልፋል፡፡ የሚያደርሰውም ጥፋት ልክ የለውም፡፡ በሰዎች መካከል የነገር ሰደድ ያስነሳል፣ የፍጥረትን ሩጫ ያቃጥላል፡፡  መንፈሳዊ ሰው ግን መናገር ትልቅ ፀጋ እንደሆነ ይረዳል፡፡ ጆን ስቶት ደህና አድርገው እንደገለጡት "መናገር በእግዚአብሔር ምሳሌ

[256] ምሳሌ 18፡21; 13፡2;21፡23; ማቴ 12፡37



For more books www.amharicchristianbooks.com

መፈጠራችንን የምናንፀባርቅበት በማንነታችን ውስጥ ያለ ብቃት ነው፡፡ እግዚአብሔር ይናገራል፣ እኛም በአምሳሉ ተፈጥረናልና እንደ እርሱ እንናገራለን፡፡ መናገር ከእንስሳት ዓለም የሚለየን አንድ አይነተኛ ነገር ነው፡፡ አዎን በሬ እምቧ፣ ውሻ ዋው! ዋው! አህያ ኢሃ! . .ኢሃ!፣ ዶሮ ኩኩሉ!፣ በግ በአአ! ይላሉ፡፡ አንበሳ ያገሳል፣ ወፎች ያፏጫሉ፣ ጦጣዎች ይንጫጫሉ፣ ሰው ግን ይናገራል፡፡ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው፡፡"[257]

እኛም ይህን ፀጋ ለልማት እንጂ ለጥፋት ልንጠቀምበት አይገባም፡፡ ሰው ለመናገር የዘገየ፣ ለቁጣም የዘገየ ይሁን[258] ተብሎ እንደተፃፈ ቃል ከአፋችን ከመውጣቱ በፊት በእግዚአብሔር ብርሃን ሊፈተሽ ይገባዋል፡፡ የአፍ ወለምታ . . . እንዲሉ ሊጠገን በማይችል መልኩ ከመስበሩም ሆነ ከመሰበሩ በፊት ገና ወደ አሳብ አለማችን ብቅ ሲል ተመርምሮ ክፉ ከሆነ እንደ በሰበሰና እንደ ተበላሸ ፍሬ ተሸንቀጥሮ መጣል አለበት፡፡ ነገር ግን ክፉ ቃል አለመናገር ብቻ በቂ አይደለም፡፡ ብዙ አማኞች ይህንን ማሰብ "ዝምታ ወርቅ ነው" ማለትን ይመርጣሉ፡፡ ሆኖም ዝም ማለት በራሱ ሰውን መንፈሳዊ አያደርገውም ይልቅ እግዚአብሔር በሰጠን ልዩ የመናገር ፀጋ የሚሰሙን ሰዎች ፀጋን አግኝተው የሚታነፁበትን የጊዜውን ቃል በመናገር ልንተጋ ይገባል፡፡ የሰው ማንነት ከሚመዘንባቸው መንገዶች ዋነኛው አንደበት ነውና በዙሪያችን ያሉ ቅዱሳን የሚመገቡት ጣፋጭ የከንፈር ፍሬ በማፍራት በእግዚአብሔር ምሳሌ የተፈጠረውን አዲሱን ሰው እንግለጥ፡፡

> *". . . ንግግራችሁ ሁልጊዜ በጨው እንደ ተቀመመ በፀጋ ይሁን." (ቆላ. 4፡6)*

ተብሎ እንደ ተፃፈ ንግግራችንን በእርጋታ እና በብልሃት እንቀምም፡፡

## <u>መንፈስ ቅዱስን አታሳዝኑ</u>

ከላይ የተጠቀሱት *ሥነ-ምግባሮች* ለምን አስፈለጉ? ብለን ብንጠይቅ የምናገኘው መልስ "ለቤዛ ቀን የታተማችሁበትን ቅዱሱን የእግዚአብሔርን መንፈስ አታሳዝኑ" የሚል ነው፡፡ "ለቤዛ ቀን የታተምንበት" ማለት ምን ማለት ነው? መንፈስ ቅዱስንስ እንዴት ማሳዘን እንችላለን? መንፈስ ቅዱስ እንደ አብና ወልድ ማንነትና አካል ያለው ሕላዌ ነው፡፡[259] አካል ደግሞ አሳብ፣ ስሜት፣ ፈቃድ አለው፡፡ ያዝናል

---

[257] Sttot, John R.W, Ephesians p. 188 par.3

[258] ያዕ. 1፡19

[259] አካል የሚለው ቃል በእንግሊዝኛው Person የሚለውን ሃሳብ ለመግለፅ የገባ ቃል ነው እንጂ ሰውነትን ወይም ስጋን የሚያሳይ አይደለም፡፡



For more books www.amharicchristianbooks.com

ይደሰታል፡፡ ለዚህ ነው በዚህ ስፍራ “. . . ቅዱሱን የእግዚአብሔርን መንፈስ አታሳዝኑ ተብሎ የተፃፈው፡፡ መንፈስ ቅዱስን እንድናስደስተው አልታዘዝንም፣ እርሱ የደስታ መንፈስ ነው፡፡ የእግዚአብሔር መንግሥት በመንፈስ ቅዱስ የሆነ ደስታ ናትና፡፡[260] እሱ ደስታ ይሰጠናል እንጂ እኛ ልንሰጠው አንችልም፡፡ እንዳናሳዝነው ግን ታዘናል፡፡ ምሣሌዎቻችን የእስራኤል ልጆች[261] ከባርነት ቤት ያወጣቸውን ወደ ዕረፍት የመራቸውን መንፈስ ቅዱስ እንዳሳዘኑት ኢሳይያስ ጽፎልናል[262] ይህም መንፈስ ቅዱስ የሚያዝን ማንነት እንዳለው ያሳየናል፡፡ ጌታ ኢየሱስ ሥጋ ለብሶ፣ ሰው ሆኖ ስለ መጣ ስድብን ታግሷል፣ መንፈስ ቅዱስ ግን ስስ ነው፣ ያዝናል፡፡ ሊያሳዝኑት የሚችሉትም ሊያድናቸው በመካከላቸው ያደረ፣ ሊያሳርፋቸው በውስጣቸው የኖረ የራሱ ሰዎች ናቸው፡፡ ማዘን ውስጣዊ፣ ቁጣ ግን ውጫዊ ነው፡፡ በውስጥ የጀመረ ሃዘን በውስጥ ተሰውሮ አይቀርም እያደር ቁጣ ሆኖ በውጭ ይገለጣል፡፡ የእስራኤል ልጆች በምድረ በዳ ልባቸውን እልከኛ ባደረጉ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ አዘነ፣ በእልከኝነታቸው ቀጥለው መንገዱን በተቃወሙ ጊዜ ተቆጣ፣ መጨረሻም ባላመኑትና ኃይሉን በካዱ "ወደ እረፍቴ አይገቡም" ብሎ በቁጣው ማለባቸው፡፡[263] ሆኖም በዚህ ሁሉ ውስጥ የምንማረው የትዕግሥቱን ብዛት ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስ ኢየሱስን ከሙታን ያስነሳ ከሁሉ የሚበልጥ ታላቅ ኃይል ሆኖ ሳለ ወደ ውጭ ከመቆጣት ይልቅ ወደ ውስጥ ያዝናል፡፡ ነገር ግን አብ የመንፈስ ቅዱስን ሃዘን ፍፁም በዝምታ አያልፈውም፡፡ ይህንንም ከፍ ብለን እንዳየነው በምድረ በዳ በወደቁት የእስራኤል ልጆች ላይ በግልፅ አሳይቷል፡፡ አሁንም በሥጋ ኑሮአችን መንፈስ ቅዱስን የምናሳዝን አማኞች በዚያን ቀን በክርስቶስ ፍርድ ወንበር ፊት መቅረባችንና ብድራታችንን ማግኘታችን አይቀርም፡፡[264]

መንፈስ ቅዱስ አይታይም፣ ስለዚህ ማንም ፊት ለፊት አግኝቶ ሊያሳዝነው አይችልም፡፡ ነገር ግን በቀላሉ በሰዎች ውስጥ ልናሳዝነው እንችላለን፡፡ የእስራኤል ልጆች ያሳዘኑት በሙሴ ውስጥ ነበር፡፡[265] ፈሪሳውያን የሰደቡት በኢየሱስ ውስጥ ነበር፡፡[266] ሐናኒያና ሰጲራ መንፈስቅዱስን የዋሹት በሐዋርያት ውስጥ ነበር፡፡[267]

[260] ሮሜ 14፡17
[261] 1ቆሮ. 10፡11
[262] ኢሳ. 63፡10፣ 14
[263] ዕብ 3፡7-12
[264] 2ቆሮ. 5፡10
[265] መዝ 106፡32፣33
[266]ማቴ 12፡22-37



For more books www.amharicchristianbooks.com

በአዲስ ኪዳን መንፈስ ቅዱስ በአማኞች ሁሉ ውስጥ አድሮአልና እርስ በርስ ያለን ግንኙነት ጤናማ ካልሆነ በቀላሉ ልናሳዝነው እንችላለን፡፡ በእምነት ቤተሰብ ውስጥ ስንመላለስ ፊት ለፊት የምንገናኘው ከሰዎች ጋር ብቻ ቢመስለንም፣ ከሚታየው ሰው ጀርባ ከማይታየው ጋር እንደምንገናኝ ይህ ክፍል አስቀድሞ ነግሮናል፡፡ ቀደም ሲል ከሰዎች ጋር ስላለን ግንኙነት ሲጽፍ "ለዲያቢሎስ ፈንታ አትስጡት" ብሎናል፡፡ አሁን ደግሞ ከዚሁ የእርስ በርስ ግኑኙነት ርዕስ ሳይለወጥ "ቅዱሱን የእግዚአብሔርን መንፈስ አታሳዝኑ" ይለናል፡፡ ሁለቱም ከሰዎች ጋር ለዚያውም ከአማኞች ጋር ስላለን ግንኙነቶች የሚናገሩ ናቸው፡፡ ስለዚህ ሰዎች ላይ በምንናገረው ክፉ ቃልም ሆነ በምንፈጽመው ክፉ ምግባር ከግለሰቦቹ ባሻገር መንፈስ ቅዱስን እናሳዝናለንና እንጠንቀቅ፡፡

እርሱ ለቤዛ ቀን የታተምንበት የርስታችን መያዣ ነው፡፡(1፡13) ቤዛ ማለት ዋጋ ከፍሎ መግዛት፣ ምትክ ሆኖ ማዳን ማለት ነው፡፡ በመስቀሉ ደም ከኃጢአት በመንፃት የዘላለምን ቤዛነት አግኝተናል፣ በዚህም መንፈሳችን ሕያው ሆኖአል፣ ሆኖም መዳናችን ገና አልተፈፀመም፡፡ በመንፈሳችን ሕያውነት የጀመረው፣ በነፍሳችን መታደስ የሚቀጥለው ቤዛነታችን የሚጠናቀቀው የሰውነታችን ቤዛ የሆነውን ልጅነት ስንጎናፀፍ ነው፡፡[268] ይህም በመጨረሻው ቀን በክርስቶስ መገለጥና በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በሚሆን የአካል ትንሳኤ ይፈፀማል፡፡ ለዚህ ነው በዚያን ቀን የኃይልና የክብር ልብስ ሆኖ በበጉና በአብ ፊት የሚያቆመንን መንፈስ ቅዱስን እንዳናሳዝን የሚመክረን፡፡

በጥንት ዘመንም ሆነ አሁን በሰም ማኅተም የታሸገ ደብዳቤ ቀኑ እስኪደርስ ድረስ አይከፈትም፡፡ በመንፈስ ቅዱስ በውስጣችን የተሰወረው የክርስቶስ ክብር የሚገለጥበት ቀን ተቀጥሮአል፡፡ እስከዚያን ቀን ድረስ ማንም ሊያየውም ሆነ ሊያውቀው አይችልም፡፡ ሆኖም እስከዚያው ቀን ድረስ የማን መሆናችን በላያችን በታተመው ማኅተም ይታወቃል፡፡ ማኅተሙ መንፈስ ቅዱስ፣ መገለጫውም የመንፈስ ፍሬ ነውና በግንኙነታችን ሁሉ የከንፈራችን ፍሬ ያማረ ይሁን፡፡

## <u>ከመራርነት ወደ ርህሩህነት</u>

*"መራርነትና ንዴት፣ ቁጣም ፣ጩኸትም መሳደብም ሁሉ፣ ከክፋት ሁሉ ጋር ከእናንተ ዘንድ ይወገድ፡፡ እርስ በርሳችሁም ቸሮችና ርህሩሆች ሁኑ፡፡*

[267] ሐዋ. ሥራ 5፡1-11

[268] ሮሜ 8፡23



For more books www.amharicchristianbooks.com

*እግዚአብሔርም በክርስቶስ ይቅር እንዳላችሁ ይቅር ተባባሉ፡፡"*

ጳውሎስ በሚያታልል ምኞት ወደ ጥፋት የሚመራውን የአሮጌውን ሰው ማንነት እየገፈፈና እያራቀተ ሲያስነበኘን ይቆይና በመጨረሻ የሆዱን ጉርጆ ሳይቀር አንጀቱን ዘርግፎ የሚያሳየን እስኪመስል ድረስ ውስጣዊ ገጽታውን ፊታችን ይደቅነዋል፡፡ በዚህ ሥፍራ የዘረዘራቸው ስድስት ባሕሪያት ከማናችንም የተሰወሩ አይደሉም፡፡ በአንድ ወቅት እጅና ጓንት ሆነን ተመላልሰንባቸዋል፡፡ የከት ሳይሆን የሰርክ ልብስ አድርገን ደርበናቸዋል፡፡

መራርነት እንደ ስሙ መራራ መንፈስንና ስሜትን የሚያሳይ ነው፡፡ መራርነት የተጠናወተው ሰው ለሕይወት ያለው እይታ ጨለምተኛ ነው፡፡ ዙሪያውን በከበቡት ስጦታዎች ውስጥ የእግዚአብሔርን መልካምነት በማየት ማመስገን አይችልም፡፡ መራራ ሰው አንዴ በደል ከደረሰበት እሱን ሲያኝክና ሲያመነዥግ ይኖራል እንጂ ለእርቅ በጄ አይልም፡፡ ከዚህ ዓይነት ሰው ውስጥ ንዴትና ቁጣ እንደ አሸን ይፈላሉ፡፡ በንግግር ወቅት ከሌሎች ጋር ረጋ ብሎ መወያየት አይችልም፡፡ የትዕግሥት ክሩ ፈጥኖ ይበጠሳል፣ ድምፁ ይነሳል፣ ይጮሃል፡፡ ይህ ሰው ከሚሳሳለትና ከሚዋጋለት እኔነቱ በቀር ለሰው አክብሮት የለውም፡፡ ፊት ለፊትም ሆነ ከጀርባ ስለ ሰው ሲናገር ሰዎችን ለማቃለል፣ ማንነታቸውን ለማብጠልጠልና ለማጣጣል፣ ድካማቸውን ለማጉላትና ለመኮነን ወደ ኋላ አይልም፡፡ ስለ ሰው ሲያነሳ አስተያየቱ በስድብ የተሞላ ነው፡፡ ይህ ሰው ክፋት ሁሉ የታመቀበት ነው፡፡ ለሰዎች ቀና አመለካከት የለውም፡፡ የማንንም በጎ አይሻም፣ ሰዎች የሚወድቁበትንና የሚሰናከሉበትን ወጥመድ ከመስራት አይመለስም፡፡ ሌሎች ካልተዋረዱ የከበረ፣ ሌሎች ካልደበዘዙ የደመቀ፣ ሌሎች ካልወደቁ የቆመ አይመስለውም፡፡ ይህ ሰው እገሌ ወይም እገሊት ሳይሆኑ በሁላችንም ዘንድ የነበረ አሮጌው ሰዋችን ነው፡፡[269]

ይህንን ሰው ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ጠርቆ ከመንገድ አስወግዶታል፡፡ የእርሱ የሆኑትም ከክፉ መሻቱና ከምኞቱ ጋር ሰቅለውታል፡፡ እኛም ከዚህ እውነት ጋር ተባብረን አውልቀን እንድንጥለው እየተመከርን ነው፡፡ በምትኩ በእግዚአብሔር ምሳሌ የተጠፈረውን የአዲሱን ሰው ጌጠኛ ልብስ እርሱም ቸርነትን፣ ርህራሄንና ይቅርታን ልንጎናፀፍ ይገባል፡፡ የተጠየቅነው ይቅርታ መስፈርቱ በሰባት ወይም በሰባት ጊዜ ሰባት የሚለካ ሰዋዊ ይቅርታ ሳይሆን፣ በአምሳሉ የተፈጠርነው የእግዚአብሔር ይቅርታ ነው፡፡ እግዚአብሔር በክርስቶስ ይቅር እንዳለንና

[269] ሮሜ 6፡6



For more books www.amharicchristianbooks.com

እንደታረቅን እኛም በዙሪያችን ያሉትን በክርስቶስ ይቅር ልንላቸውና ልንቀበላቸው ይገባናል፡፡

እርስ በርስ ልንገልጠው ስለሚገባ ቸርነት፣ ርኅራኄና ይቅርታ ሲነግረን በተለይ ይቅርታን የገለጠበት መንገድ ትኩረት የሚስብ ነው፡፡ እርስ በርሳችን ይቅር እንድንባባል የተጠየቅንበት ደረጃና መስፈርት በባሕሪው ሰዋዊ ሳይሆን መለኮታዊ ነው፡፡ "እግዚአብሔር ደግሞ በክርስቶስ ይቅር እንዳላችሁ ይቅር ተባባሉ" የሚል፡፡ ታዲያ የተሰጠን መለኮታዊ ትዕዛዝ ብቻ ሳይሆን መለኮታዊ ባሕሪ ጭምር ነውና ሲታይ የሚከብድ ቢመስልም ሊተገበር የማይችል አይደለም፡፡ አናሳ ከሆነው አሮጌ ፍጥረት ውስጥ ወጥተን እንደ እግዚአብሔር ምሣሌ በተፈጠረው አዲሱ ማንነት ውስጥ ከገባን እንደ ምሳሌው የተፈጠርነውን እግዚአብሔርን መምሰል የማይወጣ አቀበት ሊሆንብን አይገባም፡፡ ይልቅ ጉልቁ መሳፍርት የሌለውን ኃጢአታችንን ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ ይቅር ያለን የእግዚአብሔር ዓይኖች፣ እኛ እርሱን ከበደልነው ጋር ሲነፃፀር ኢምንት በደል የበደሉንን ባልንጀሮቻችንን እንዴት እንደምናስተናግድ በትኩረት እንደሚያዩ ማሰብ መልካም ነው፡፡[270]

ይቅርታና ምሕረት መፍለቂያ ምንጭ አላቸው፡፡ ምንጫቸው ፍቅር ነው፡፡ ቀደም ሲል የዳንበት የእግዚአብሔር የምሕረቱ ባለጠግነት እኛን ከወደደበት ከትልቅ ፍቅሩ እንደ መነጨ ተመልክተናል፡፡ (2፡4) እኛም ወንድሞቻችንና እህቶቻችንን ይቅር የምንልበት ምሕረት ከዚያው የፍቅር ወንዝ ይቀዳል፡፡ ከፍቅር የሚመነጭ ይቅርታ ለአስታራቂ ኮሚቴ ይሉኝታ ሲባል ለታይታ የሚደረግ ሥርዓት ሳይሆን በውስጣችን ያለው እግዚአብሔርን መምሰል የሚለካበት ሁነኛ መመዘኛ ነው፡፡

## <u>በፍቅር መመላለስ</u>

4፡32 እና 5፡1-2 ለንባብ ይመች ዘንድ በምዕራፍ የተከፈሉ ቢሆንም በሃሳብ ግን የተነጣጠሉ አይደሉም፡፡ ጸሐፊው "እንግዲህ" በማለት ከፍ ብሎ የጀመረውን ሃሳብ በማጽናት ይቀጥላል፡፡ በክርስቶስ ሥራ የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን ቀደም ሲል ነግሮናል፡፡(1፡5) አሁን ደግሞ የተወደድን ልጆች እንድንሆን ይመክረናል፡፡ በመጀመሪያ ልጆች ሳንሆን የተወደድን ልጆች ልንሆን አንችልም፡፡ ነገር ግን በእርሱ ሥራ ልጆች ከሆንን በኋላ፣ እርሱ በእኛ እንዲሠራ በመፍቀድ የተወደድን ልጆች ልንሆን እንደምንችል ይነግረናል፡፡ የተወደዱ ልጆች ወላጆቻቸውን የሚመስሉ ናቸው፡፡ ስለዚህ "እንደ ተወደዱ ልጆች እግዚአብሔርን የምትመስሉ ሁኑ"

[270] ማቴ 18፡21-35



For more books www.amharicchristianbooks.com

ይለናል፡፡ አስቀድሞ ለእውነት በሚሆኑ ጽድቅና ቅድስና እንደ እግዚአብሔር ምሳሌ እንደ ተፈጠርን ጽፎልናል፡፡(4፡24) አሁን ደግሞ ይህንን አዲስ ሰው በመጎናፀፍ፣ ባህሪውንም በማግለጥ እግዚአብሔርን እንድንመስል እየተነገረን ነው፡፡ እግዚአብሔር ምን ይመስላል? እግዚአብሔር ፍቅር ነውና ፍቅርን ይመስላል፡፡ እግዚአብሔር ምን እንደሚመስል አላውቅም እንዳንል በኢየሱስ ክርስቶስ የምድር ኑሮ በገሃድ ተተርኳልና ማምለጫ አይኖረንም፡፡ እግዚአብሔር ፍቅር ነው፣ የፍቅሩም አድማስ በጎልጎታ ተራራ በኢየሱስ ክርስቶስ መስዋእትነት ተገለጠ፡፡[271] ክርስቶስ በአባቱ ፍቅር ወደደን፡፡[272] ፍቅሩንም ከእግዚአብሔር ፊት የነጠለንን ክፉ ጠረናችንን በመልካም መአዛ ይለወጥ ዘንድ በመስዋዕትነት ገለፀው፡፡ ይህ ተግባር እንደምናስበው ቀላል አልነበረም፡፡ ትልቅ ዋጋ ጠይቋል፡፡ ዋጋ የማይከፈልበት ፍቅር ከቃላት ያለፈ ምንም ፋይዳ የለውም፣ ክርስቶስ ግን በመስዋእትነት ፍቅሩን ሊገልጥልን ወደደ፡፡ በብሉይ ኪዳን የአምልኮ ሥርዓት ለእግዚአብሔር ስለ ሰዎች የሚቀርብ ጣፋጭ ሽቱ የሚገኘው ከሚቃጠል መስዋእትነት ነበር፡፡ ኃጢያተኛው ወደ እግዚአብሔር ይቀርብ ዘንድ እንከን የሌለበት አውራ በግ ኃጢአቱን ተሸክሞ በመሰዊያ ላይ ይቃጠላል፡፡ እግዚአብሔርም ከመስዋዕቱ የሚወጣውን ጣፋጭ ሽታ ያሸትና ኃጢአተኛውን ይቀበለዋል፡፡ ክርስቶስ በእርሱ ወደ እግዚአብሔር የሚቀርቡትን ኃጢያተኞች ጠረን ወደ መልካም መዓዛ ለመለወጥ፣ የሁሉን ኃጢአት ተሸክሞ በቀራኒዮ መስቀል ላይ በፍርድ እሳት ተቃጠለ፡፡

እግዚአብሔር የጥፋትን ውሃ ያመጣ ዘንድ ግድ ያለው የክፋት ሽታ፣ በፍርድ ከተወገደ በኋላ፣ ኖህና ቤተሰቡ ከመርከብ ወጥተው የሚቃጠል መስዋዕት ባቀረቡ ጊዜ፣ እግዚአብሔም መልካሙን መዓዛ አሽትቶ "ምድርን ዳግመኛ ስለ ሰው አልረግምም . . . " እንዳለ፣ እርግማንና ቁጣን ከእኛ አስወግዶ ዘላለማዊ በረከት ሊያወርሰን ክርስቶስ ስለ እኛ፣ ለእግዚአብሔር የመዓዛ ሽታ የሚሆን መባና መስዋእት አድርጎ ራሱን አሳልፎ ሰጠ፡፡[273] ታዲያ ይህ ፍቅር የተተረከልን አድንቀን እንድንቀመጥ ሳይሆን፣ እኛም በዚህ ዓይነት፣ በዚህ ደረጃና መስፈርት ፍቅራችንን ለሌሎች እንድንገልጥ ነው፡፡ የገባንበት፣ ገናም የምንገባበት ርስት ለዘላለም ፀንቶ የሚኖር ፍቅር ነውና በመስዋእትነት በሚገለጥ ፍቅር ጣፋጭ ሽታዎች ሆነን እንመላለስ፡፡[274]

[271] 1ዮሐ. 4፡9

[272] ዮሐ. 15፡9

[273] ዘፍ. 6፡11፣ 12፡ 8፡21

[274] ሕዝ. 20፡41



For more books www.amharicchristianbooks.com

# ምዕራፍ ፳
# በቅድስናና በብርሃን መመላለስ

ኤፌ. 5፡3-14

ይህ መልእክት የሚፃፍላቸው አማኞች ከምን ዓይነት ማኅበረሰብ ውስጥ እንደወጡ፣ አሁንም ዙሪያቸውን የከበባቸው ኅብረተሰብ ምን እንደሚመስል ለመገመት ብዙ መድከም አያስፈልግም፡፡ ቀደም ሲል በተመለከትነው በ4፡19 ላይ የሰፈረው ቃል ከክርስቶስ ውጭ ያሉት አሕዛብ ምን ያህል በሴሰኝነት እንደዘቀጡ ቁልጭ አድርጎ ያሳያል፡፡

> *“. . . ደንዝዘውም በመመኘት ርኩሰትን ሁሉ ለማድረግ ራሳቸውን ወደ ሴሰኝነት አሳልፈው ሰጡ፡፡” 4፡19*

አሁንም አሕዛብን እንደ ደረቀ የዱር ዛፍ እያነደደ ያለው የሴሰኝነት፣ ሰደድ ወላፈኑ እንዳይነካቸው ለሚጽፍላቸው አማኞች ብርቱ ማስጠንቀቂያ ይሰጣል፡፡ “. . . ዝሙትና ርኩሰት ሁሉ ወይም መመኘት በእናንተ ዘንድ ከቶ አይሰማ" (ቁ.3) በማለት፡፡

“ከቶ አይሰማ!” ጠንካራ መልዕክት ያለው ቃል ነው፡፡ ጳውሎስ የሚኮንነው ድርጊቱን ብቻ አይደለም፡፡ “የሚያሳፍር ነገርም፣ የስንፍና ንግግርም ወይም ዋዛ የማይገቡ ናቸውና አይሁኑ . . . ፡፡” (ቁ.4) በማለት ዝሙት ነክ ወሬዎችን፣ ጫወታዎችንና ቀልዶችን በአማኞች መካከል እንዳይስተናገዱ ያዛል፡፡ ርኩሰትን የሚያነሳሱና ወደዚያ የሚመሩ ንግግሮች ላይ፣ ካለው ጠንካራ አቋም የተነሳ *“አሕዛብ በስውር የሚያደርጉትን መናገር እንኳ ነውር ነውና”* በማለት ይዘጋዋል፡፡ በምትኩ ከቅዱሳን ልብ ሊፈልቅ፣ ከአንደበታቸው ሊደመጥ የሚገባው አንድ ነገር ቢኖር “ምስጋና” ብቻ እንደሆነ ይነግረናል፡፡

“ከቶ አይሰማ!” “የማይገቡ ናቸውና አይሁኑ!” “እነርሱ በስውር ስለሚያደርጉት መናገር እንኳ ነውር ነውና” የሚሉትን፣ በየትኛውም መንገድ ለርኩሰት ፍንጭ የማይሰጡትንና ፈፅመው የማያፈናፍኑትን ቃላት ስንመለከት ሐዋርያው በዚህ አቅጣጫ ያነገበውን ጽኑ አቋም መመዘን አያስቸግረንም፡፡

> *“ለቅዱሳን እንደሚገባ ግን ዝሙትና ርኩሰት ሁሉ ወይም መመኘት በእናንተ ዘንድ ከቶ አይሰማ . . . ፡፡”*

ብዙ ጊዜ ስለ ቅድስና ከመድረክ የምንሰማቸውም ሆነ የምንሰጣቸው መልእክቶች



For more books www.amharicchristianbooks.com

"ተቀደሱ"፣ "ከዝሙት ራቁ" የሚሉ ናቸው፡፡ ስለዚህ ብዙ አማኞች ከዝሙት የሚርቁት ለመቀደስ ነው፡፡ ሐዋርያው ግን "ለቅዱሳን እንደሚገባ ግን፡፡" (ቁ.3) ይላቸዋል፡፡ ቅዱሳን ናችሁ፡፡ ቅዱሳን ስለ ሆናችሁና ይህ ለቅዱሳን ስለማይገባ፣ በእናንተ ዘንድ ከቶ አይሰማ! አይሁን! ይላቸዋል እንጂ ለመቀደስ እነዚህን አድርጉ አላለም፡፡ መቼም ለመሆን የሚደረግና፣ ስለሆንን የሚደረግ ነገር አንድ አይደለም፡፡ ከሆንን ለሆንነው ነገር የሚገባ፣ ስፍራው የሚጠይቀውን ኑሮ መኖር አያስቸግርም፡፡ ጥቁር አሜሪካዊ የሆኑት ባራክ ኦባማ የአሜሪካን ፕሬዘዳንት ከመሆናቸው ከስድስት ዓመታት በፊት በጣም የሚቀርቧቸውን ወዳጆቻቸውን ጨምሮ የአሜሪካ ፕሬዘዳንት ይሆናሉ ብሎ እንኳን በውኑ፣ በሕልሙ የሚታዥ ሰው አልነበረም፡፡ እሳቸውም አነስተኛ ገቢ ባለቸው ነዋሪዎች በተሞላው የቺካጎ ከተማ ደቡባዊ ክፍል በማኅበረሰብ አገልግሎት ተጠምደው ተፍ ተፍ ሲሉ ትርፍ ጊዜያቸውን ስለሚያሳልፉበት ቦታና ስለሚበሉበት ምግብ ቤት፣ ስለሚያገኟቸው ሰዎች እምብዛም ግድ የነበራቸው አይመስልም፡፡

ዛሬ ግን ያኔ የሚዝናኑበት ቦታ መዝናናት፣ ያኔ የሚበሉበት ቤት መመገብ፣ ያኔ የሚሄዱበት ቤተክርስቲያን መሄድ፣ ያኔ የሚኖሩበት ቤት ውስጥ መኖር አይችሉም፡፡ ባጭሩ ያላቸው ስልጣን ፕሮቶኮል አይፈቅድም፡፡ ያኔ ገና ፕሬዚደንት ሳይሆኑ በፊት፣ ለፕሬዚደንት እንደሚገባ ልኑር ቢሉ አስቸጋሪ ይሆን ነበር፡፡ አቅማቸውም አይፈቅድም፡፡ የግድ ቢልም የማስመሰል ተውኔት እንጂ እውን ሊሆን አይችልም፡፡ አሁን ግን ናቸውና ወደዱም ጠሉም ለሆኑት ማንነታቸው የሚገባ ኑሮ ይኖራሉ፤ እምቢ ቢሉ ግን ይዋረዳሉ፡፡ ስፍራቸውንም ያጣሉ፡፡ የሚገባንን እና የሚመጥነንን ከማይገባንና ከማይመጥነን ለይቶ ማወቅ እንዴት ያለ ብጽዕና ነው!!!

ወደ እኛ ወደ አማኞች ማንነት ስንመጣ በክርስቶስ ሥራ ቅዱሳን መሆናችንን የሚነግሩን ከ 10 የሚበልጡ ክፍሎች በዚሁ መልዕክት ውስጥ ሰፍረዋል፡፡ ምንም እንኳ የተቀደስነው በራሳችን ጥረት ሳይሆን በክርስቶስ ሥራ ቢሆንም ለቅዱሳን እንደሚገባ መኖር ግን ከሰማይ የምንጠብቀው ሳይሆን በቀጥታ የእኛ ድርሻ ነው፡፡ ከተሰጠን የቅዱስነት ማዕረግ እንዳንወርድ ከማይመጥኑንና ከማይገቡን ድርጊቶች ልንርቅ ይገባል፡፡ ዝሙት፣ ርኩሰት ሁሉ፣ ወይም መመኘት አይገባንም፣ አይመጥነንም!

ሐዋርያው ፣ ቅዱሳንን በተመለከተ በዝሙት፣ በርኩሰት ሁሉና በመመኘት እንዲሁም በማንኛውም ዓይነት ዝሙት ነክ ቀልዶችና ንግግሮች ላይ እንዲህ ጨክኖ የሚናገረው ለምን ይሆን? ሁለት አንኳር ምክንያቶችን ከሥር አስፍሯል፡፡ የመጀመሪያው "አመንዝራም ቢሆን ወይም ርኩስ ወይም የሚመኝ እርሱም ጣዖትን



For more books www.amharicchristianbooks.com

የሚያመልክ በክርስቶስና በእግዚአብሔር መንግሥት ርስት የለውም" (ቁ.5) የሚል አስደንጋጭ ምክንያት ነው፡፡

የተጠራነው ዘላለማዊ ርስት ለመውረስ ነው፡፡ ርስቱም መንግሥት አለው፤ መንግሥቱም ፅድቅና ሰላም በመንፈስ ቅዱስም የሆነ ደስታ ነው፡፡[275] ለቅዱሳን በዚህ የሕይወት መንግስት ውስጥ ርስት ከማጣት የሚብስ ምን አስደንጋጭ ነገር ሊኖር ይችላል?

ከላይ የተጠቀሱትን የኃጢአት ተግባሮች የኑሮ ዘይቤ አድርጎ ለመለማመድ ግለሰባዊ ዝንባሌ ብቻ ሳይሆን ተፈጥሮ ይጠይቃል፡፡ በተፈጥሮ ውሻ ካልሆኑ በቀር ሰው ሆኖ እንደ ውሻ መኖር አስቸጋሪ ብቻ ሳይሆን፤ የማይቻል ነው፡፡ ውሻ ባህሪው የሆነውን፣ ለእኛ ለሰው ልጆች ግን ለማድረግ ብቻ ሳይሆን ለማሰብ የሚቀፈንን ድርጊት ሲፈፅም ብናይ አንደነቅም፡፡ ተፈጥሮው ነዋ! ሰው ግን እንደዚህ ሆኖ ቢገኝ በእርግጥ ዜና ሊሆን ይገባዋል፡፡

ለእውነት በሚሆኑ ጽድቅና ቅድስና እንደ እግዚአብሔር ምሣሌ የተፈጠሩ ሰዎች፣ በፍጥረታቸው ያለመታዘዝና የቁጣ ልጆች እንደሆኑት ኢ-አማንያን ለመኖር ተፈጥሮአቸው አይፈቅድላቸውም፡፡ መኖር ከቻሉ ግን ቀድሞም የአዲሱ ሰው ተፈጥሮ አልነበራቸውም ወይም ከእልከኝነት ብዛት ከውስጣቸው ተሟጦ አልቋል እንጂ በእግዚአብሔር ሕይወት የእንስሳ ማንነት እየገለጡ መኖር ከቶ አይቻልም፡፡

ለአባቶቻቸው በገባው የተስፋ ቃል መሠረት ለእስራኤል ልጆች ርስትን የሰጠው ራሱ እግዚአብሔር ቢሆንም፣ በተለያዩ ጊዜያት ከርስታቸው የነቀላቸውና በባዕዳን ምድር የበተናቸው ራሱ እግዚአብሔር እንደ ነበር በቅዱሳት መጻሕፍት እናነባለን፡፡ ለምን? በቅድስና እንዲኖሩ የርስቱን ሕግ ሰጣቸው፡፡ "በዚህ ርስት ላይ እንዲህ አይኖርም፣ ከክፉ ሥራችሁ ተመለሱ!" ብሎ ነቢያቱን ቢልክባቸው አልሰሙም፤ ይልቅ መልዕክተኞቹን አንገላቷቸው፣ አሳደዷቸው አንዳንዶቹንም ገደሏቸው፡፡ ከብዙ ትዕግሥት በኋላ ወደ አሕዛብ ምድር በግዞት የሚያፈልሷቸውን ነገሥታት አስነሳ፡፡ ለምን? "በዚህ ቅዱስ ርስት ላይ መኖር የሚቻለው በዚህ መሠረት ነው ብዬ ሕግን ሰጥቻችሁ ነበር፡፡ እናንተ ግን አይ እንዲህ አይሆንም፣ በሕግ አንታሰርም፣ በግፍና በርኩሰት እንዳሻን እንኖራለን አላችሁ፡፡ እንግዲያስ ልክ እናንተ እንደምትኖሩት የሚኖሩ ሕዝቦች የሚኖሩበትም ርስት አለ፣ ስለዚህ የምትፈልጉትን አይነት ኑሮ እዚያ ሄዳችሁ ትኖሩ ዘንድ እሰዳችኋለሁ እንጂ በርስቴ ላይ እንዲህ በመኖር ልትቀጥሉ አትችሉም" ማለቱ ነዋ!

[275] ሮሜ 14፡17



For more books www.amharicchristianbooks.com

ዛሬም እግዚአብሔር አልተለወጠም፡፡ በምሕረቱ ወደ መንፈሳዊ ርስቱ ገብተው ፣ነገር ግን በተሰጣቸው የሕይወት መንፈስ ሕግ ለመኖር አሻፈረኝ ለሚሉ እግዚአብሔር ከብዙ ትዕግሥት በኋላ ከመንግሥቱ ርስት ያስወግዳቸዋል፡፡

ሁለተኛው ምክንያት “ከዚህ የተነሳ በማይታዘዙት ልጆች ላይ የእግዚአብሔር ቁጣ ይመጣልና ማንም በከንቱ ንግግር አያታላችሁ፡፡” (ቁ.6)

"ከዚህ የተነሳ" የሚለው ከላይ የዘረዘራቸውን የርኩሰት ተግባሮች ነው፡፡ በመቀጠልም የሚጽፍላቸውን ሰዎች ለማታለል የሚዳዳው “ከንቱ ንግግር” መኖሩን ይጠቁማል፡፡ በእነዚህ አማኞች ዙሪያ ያሉ አሕዛብ እነዚህን የርኩሰት ተግባራት በፍፁም ልቅነት ያለገደብ ይፈጽማሉ፡፡ ነገር ግን እስከአሁን የመጣባቸው ምንም ቁጣ የለም፡፡ እንዲያውም ተመቻችተው በድሎት ይኖራሉ፡፡ በዘመኑ በስፋት ተደማጭነት ያላቸው ፈላስፎቻቸውም "ፍትወት እንደ ምግብና መጠጥ ለሥጋ አስፈላጊ ነው፡፡ ሲርበን በልተን እንደምንጠግብ፣ ሲጠማን ጠጥተን እንደምንረካ ፍትወትም ባሰኘን ጊዜ ፈፅመን የምናረካው የሥጋ አፒታይት ነው፡፡ በውስጣችን ይህን ስሜት የሚቀሰቅሱና የሚያረኩ ነርቮችን የዘረጋ አምላክ ለምን ይህን አደረጋችሁ ብሎ አይወቀስንም፣ በዚህም ምክንያት የሚመጣ አንዳች ቁጣ የለም፣ ትክክልና ስህተት፣ ሰው በራሱ የፈጠራቸው የኃይማኖት አባዜዎች ናቸው እንጂ በራሱ ኃጢአት የሆነ ነገር የለም" በሚሉና ይህንን በመሳሰሉ አጋንንታዊ ትምህርቶች ብዙዎችን ያስታሉ፡፡ ለዚህ ነው ጳውሎስ “ማንም በከንቱ ንግግር አያታላችሁ” የሚለው፡፡ ይህ አይነቱ በውሸት እውቀት የተባለ ከንቱ ልፍለፋ ጥንት ያከተመ ጉዳይ ሳይሆን፣ ዛሬም በአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ በዓለም ዙሪያ እየናኘ ያለ ፣ብዙዎችንም የዋጠ ክፋት ነው፡፡

እግዚአብሔር ለቁጣ የዘገየ ምሕረቱ የበዛ አምላክ ነው፡፡ ነገር ግን ቁጣው ይዘገያል ማለት ይቀራል ማለት አይደለም፡፡ አምላካዊ ትዕግስቱ "የታል የምትፈርደው?" የሚለውን የሰውን የትዕግሥት አቅም መፈተኑ የማይቀር ቢሆንም በቀጠረው ቀን ቁጣው በማይታዘዙት ላይ መገለጡ አይቀሬ ነው፡፡

ስለዚህ በርኩሰት የሚኖሩ ሰዎች በክርስቶስና በእግዚአብሔር መንግሥት ርስት ስለሌላቸውና ከእነዚህ ነገሮች የተነሳ በዓለም ላይ የእግዚአብሔር ቁጣ ስለሚመጣ “ከእነርሱ ጋር ተካፋዮች አትሁኑ” (ቁ.7) ይለናል፡፡ ተካፋይነት አንድነትን፣ አብሮነትን፣ መስጠትና መቀበልን፣ አንድን ነገር በጋራ መጠቀምን፣ የተገለጠም ይሁን የተሰወረ ሕብረትን የሚገልጥ ቃል ነው፡፡ ከአሕዛብ ጋር በቀጥታ ማኅበርተኛ ሳንሆንና ፊት ለፊት ሳንገናኝ፣ በርኩሰታቸው ተካፋይ የምንሆንባቸው



For more books www.amharicchristianbooks.com

መንገዶች በርካታ ናቸው፡፡ በተለይ በምንኖርበት የመረጃ ዘመን የምንፈልገው ነገር ሁሉ በቅጽበት እጃችን መዳፍ ላይ ማረፍ ስለሚችል የተካፋይነቱን መጠን ይጨምረዋል፡፡ ዛሬ በዓለማችን ካሉ ከፍተኛ ገቢ ካላቸው የኢኮኖሚ መስኮች አንዱ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየመጠቀ የመጣው የወሲብ ኢንዱስትሪ እንደሆነ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ይህ መስክ እንዴት እንዲህ የሰባና የማይነጥፍ የገንዘብ ምንጭ ሊኖረው ቻለ? ሲባል መልሱ የኢንዱስትሪውን ምርት መጽሔት ይሁን፣ ፊልም፣ ድረገጽ ይሁን የብዙሃን መገናኛ ያለመታከት የሚሸምቱ በሴሰኝነት መረብ የተጠመዱ አእላፋት ታማኝ ደንበኞች በመኖራቸው ነው፡፡ ከእነዚህም መሃል ስንቶች አማኞች እንደሚገኙ ቤቱ ይቁጠረው፡፡ ከአምራቾቹ ጋር የፊት ለፊት ግንኙነት ባይኖረንም ምርቶቻቸውን ገዝተን መጠቀም በራሱ ተካፋይነት ነው፡፡

በሌላ መልኩ በኤፌሶንና በቆላስያስ መልእክት ስለ ተካፋይነት የተፃፈልን እውነት ፈጽሞ የተለየና የከበረ ነው፡፡ የተጠራነው "በቅዱሳን ርስት በብርሃን እንድንካፈል"(ቆላ.1፡12) "ከቅዱሳን ጋር በክርስቶስ ኢየሱስ የሆነውን የተስፋ ቃል በመካፈል አብረን ወራሾች እንድንሆን"(ኤፌ.3፡5) ተጽፎልናል፡፡

በዚህ ዓይነት አንድ የሕይወት ማዕድ ከአብና ከወልድ እንዲሁም ከቅዱሳን ሁሉ ጋር ዘወትር እንድንካፈል ተጠርተናል፡፡ ሆኖም ከሁለት ማዕድ ተካፋይ መሆን አንችልምና አንዱን መምረጥ ግድ ይላል፡፡ እዚህ ጋ ታዲያ ምን ይሻለኛል? የሚል ጥያቄ መጫሩ አይቀርም፡፡ ጳውሎስ "እንግዲህ በምድር ያሉትን ብልቶቻችሁን ግደሉ፡፡ እነዚህም ዝሙትና ርኩሰት ፍትወትም፣ ክፉ ምኞትም ጣዖትንም ማምለክ የሆነ መጎምጀት ነው . . . ፡፡" ይለናል፡፡ አዎን በራሳችን መግደል አንችልም፡፡ ነገር ግን ከፍ ብሎ "ሞታችኋልና ሕይወታችሁም በእግዚአብሔር ከክርስቶስ ጋር ተሰውሮአልና፡፡" የሚለው ከገባን የሞተን መግደል አይቸግረንም፡፡ (ቆላ. 3፡1-5) የሞተን ለመግደል መሳሪያው መሞቱን መቀበል፣ ማመን፣ መቁጠር፣ መናገር፣ መካድ ነው፡፡ ኃጢያት ባርያ አድርጎ ይገዛው የነበረን ማንነት፣ ጽድቅ ሲሰለጥንበት ስናይ የቀድሞው እንደ ሞተ ሌላ ማረጋገጫ ፍለጋ አያስኬደንም፡፡

ጳውሎስ ተካፋዮች አትሁኑ ካለ በኋላ ምክንያቱን ሲገልፅ ከቀድሞውና ከአሁኑ ማንነታቸው ጋር ያዛምደዋል፡፡ "ቀድሞ ጨለማ ነበራችሁና አሁን ግን በጌታ ብርሃን ናችሁ . . . ፡፡ (ቁ.8) በማለት፡፡

በብሉይ ኪዳን ቅዱሳት መፃሕፍት ውስጥ ብርሃን የእግዚአብሔርን ሕይወት የሚገልጥ፣ ከእግዚአብሔር ዘንድ የሚመጣን ማዳን የሚያሳይ ተምሳሌታዊ



For more books www.amharicchristianbooks.com

መግለጫ ነው፡፡[276] በአዲስ ኪዳንም በተለይም በዮሐንስ ጽሑፎች ውስጥ ይኸው አሳብ በጉልህ ተንፀባርቋል፡፡[277]

በክርስቶስ በማመናችን ያገኘነው ለውጥ ከምንገምተው በላይ ጥልቅ ነው፡፡ የእምነትና የፀባይ ለውጥ ብቻ ሳይሆን የማንነትና የተፈጥሮ ለውጥ ነው፡፡ የጨለማና የብርሃን ያህል ግልጽ ልዩነት ያለው ለውጥ በሕይወታችን መጥቷል፡፡ ውስጣችን ተለውጦ ብርሃን ከሆንን ልናደርግ የማንችለው አንድ ነገር ቢኖር ከጨለማ ጋር ኅብረት መፍጠር ነው፡፡ “ብርሃን ከጨለማ ጋር ምን ኅብረት አለው?” (2ቆሮ.6፡14) ተብሎ እንደ ተፃፈ፡፡ አዲሱ የብርሃን ማንነታችን፣ ከቀድሞው የጨለማ አኗኗራችን ጋር ሊተባበር አይችልም፡፡ እስከ ዛሬ በተፈጥሮ ተከስቶ ያላየነው የብርሃንና የጨለማ ትብብር እኛ ጋ ሊጀምር አይችልም፡፡ ግዑዙ የመንፈሳዊ ጥላ እንደ መሆኑ መጠን ይህ የሚታይ ምሣሌ የማይታየውን እውነታ አጥርቶ ያሳየናል፡፡ የእግዚአብሔር ሕይወት የብርሃን ሕይወት ነው፡፡ ብርሃኑም በጨለማ ይበራል፡፡ ጨለማም ሊይዘው አይችልም፡፡

በዚህ ክፍል የምናየው መሠረታዊ የብርሃንና የጨለማ ልዩነት፣ ብርሃን በፍሬ፣ ጨለማ በሥራ፣ መገለጣቸው ነው፡፡ ይህ ትኩረት የሚሻ አገላለጥ ነው፡፡ "ሥራ" አንድ ሰው በራሱ ተነሳሽነት፣ ምንም እገዛ ሳያስፈልገው ከራሱ፣ በራሱ አቅም፣ ለራሱ ጥቅም የሚፈጽመው ተግባር ነው፡፡ ፍሬ ግን ቅርንጫፍ ከግንዱ ጋር በመጣበቅ በሥሩ አማካይነት በሚካፈለው ሕይወት የዛፉን ውስጣዊ ማንነት የመግለጥ ሂደት ነው፡፡

አንድ ሰው ኃጢአት ለመሥራት በውስጡ ያለውን ምኞት በሥጋው መፈፀም እንጂ ሌላ ግንኙነት፣ ኅብረት፣ መጣበቅ አያስፈልገውም፡፡ ጽድቅን ለማድረግ ግን እርሱ ብቻ ጻድቅ የጽድቅም ሁሉ ምንጭ ከሆነው ከእግዚአብሔር ጋር በመንፈስ ኅብረት ማድረግ ይኖርብናል፡፡ የሚገልጠውም ከራሱ በራሱ የሆነ ጽድቅ ሳይሆን፣ ከክርስቶስ ኢየሱስ የሚገኝ የጽድቅ ፍሬ ይሆናል፡፡[278] ከሌላው ጋር ምንም ግንኙነትና ሕብረት ሳያስፈልገን በራሳችን የምናደርገው ሁሉ "ሥራ" ሲሆን ከራሳችን ውጭ ከሌላ ጋር ሕብረት አድርገን የምናገኘው ደግሞ "ፍሬ" ተብሎ ይጠራል፡፡ ለዚህ ምሳሌ የሚሆነን መጽሐፍ ቅዱስ ልጆችን የሚጠራበት መንገድ ነው፡፡ ልጆች የማሕፀን ፍሬ ወይም የሆድ ፍሬ እንደሆኑ ይናገራል፡፡ ፍሬ የተባሉት

276 መዝ. 27፡1 ፤ ኢሳ. 9፡2፤ 10፡17፤ 42፡6፤ 16፤ 49፡6፤ 51፡4፤ 60፡1

277 ዮሐ. 1፡4-5፤ 7-9፤ 3፡19-21፤ 8፡12፤ 9፡5፤ 12፡35፤36፤46፤ 1ዮሐ. 1፡5፤ 2-8

278 ፊሊ. 1፡9-11



For more books www.amharicchristianbooks.com

ወላድ እናት በራሷ የሠራቻቸው ሳይሆን ከወንድ ጋር ግንኙነት አድርጋ ያገኘቻቸው የግንኙነት ውጤት ስለሆኑ ነው፡፡

ለዚህ ነው ጳውሎስ “. . . የብርሃኑ ፍሬ በበጎነትና በጽድቅ በእውነትም ሁሉ ነውና ለጌታ ደስ የሚያሰኘውን እየመረመራችሁ እንደ ብርሃን ልጆች ተመላለሱ ፍሬም ከሌለው ከጨለማ ሥራ ጋር አትተባበሩ፡፡” (ቁ.8-11) የሚለው፡፡

የእኛ ብርሃንነት እንደ ፀሐይ በራሳችን የምናፈልቀው ሳይሆን፣ ጨረቃ ከፀሐይ ተቀብላ በጨለማ እንደምታበራ ከብርሃናት አባት የምናገኘውና የምንገልጠው ብርሃን ነው፡፡ ስለዚህ ብርሃናችን ፍሬ አለው፡፡ የሚታወቀውም በፍሬው ነው፡፡ ፍሬውም በጎነት፣ ጽድቅና እውነት ናቸው፡፡ ጨለማ ግን በመደረግ የሚጠፋ ከንቱ ሥራ እንጂ አንዳች ፍሬ የለውም፡፡ ለዚህ ነው በገላትያ 5፡19 እና 22 “የሥጋ ሥራ . . . የመንፈስ ፍሬ . . . ፡፡” እያለ የሚጽፈው፡፡

ብርሃን ምንጭ አለው፡፡ ምንጭ የሌለው ብርሃን የለም፡፡ ለዚህ ነው ስለ ብርሃን ስንናገር የፀሐይ ብርሃን፣ የኤሌክትሪክ ብርሃን፣ የሻማ ብርሃን የምንለው፡፡ ጨለማ ግን መገኛ ምንጭ የለውም፤ ስለዚህ የእንትን ጨለማ፣ የእንትን ጨለማ አንልም፡፡ ጨለማ ባጭሩ የብርሃን አልባነት ነው፡፡ ብርሃን የለቀቀውን ሥፍራ ሁሉ ጨለማ ይነግስበታል፡፡ ዝሙት፣ ርኩሰት፣ መመኘት፣ በሥጋ የሚገለጡ የጨለማ ሥራዎች ናቸው፡፡ እግዚአብሔርን ከማሳዘንና ቁጣውን ከማነሳሳት በቀር የሚፈይዱት አንዳች ነገር የለም፡፡

ስለዚህ በቅዱሳን ርስት በብርሃን እንድንካፈል ያበቃንን አብን እያመሰገንን በነገር ሁሉ እርሱን ደስ ልናሰኝ ለጌታ እንደሚገባ እንድንመላለስ ይለምነናል፡፡ በእርግጥ እኛ ከብርሃን የተወለድን የብርሃን ልጆች ነን እንጂ ባለማወቅ የምንመላለስ ከጨለማ የተገኘን የጨለማ ውጤት አይደለንምና ወደ እኛ የሚመጣውን ሁሉ በብርሃን እየፈተሸንና ለጌታ ደስ የሚያሰኘውን እየመረመርን፣ የጨለማን ሥራ ነቅሰን እያወጣን፣ እንደ ብርሃን ልጆች መመላለስ አይሳነንም፡፡

ብርሃን ይታያል፣ ያሳያል፡፡ ከጨለማ ወደ ድቅድቅ ጨለማ እየተመመ ባለው አለም ውስጥ በጎነትን፤ ጽድቅንና እውነትን እያፈራን በብርሃን ከተመላለስን አንዳች ቃል ሳንናገር የጨለማው ሥራ ይገለጣል፡፡ ብርሃናችን ወጥቶ ጨለማቸውን የሚገልጥባቸው ሰዎች ወይ ከእኛ ጋር ይተባበራሉ፤ ወይ አጥብቀው ይጠሉንና ይቃወሙናል፡፡ በሁለቱም መንገድ ብርሃናችን ተፅዕኖ ያመጣል፡፡ በተለይ ከርኩሰትና ከሴሰኝነት አንፃር በዙሪያችን ያሉ የጨለማ ሰዎች በስውር የሚያደርጉትን ለመግለፅ ማብራት እንጂ ማውራት አያስፈልገንም፡፡ ማውራቱ ራሱ



For more books www.amharicchristianbooks.com

ነውር ነውና፡፡ «ሁሉ ግን በብርሃን ሲገለጥ ይታያል፤ የሚታየው ሁሉ ብርሃን ነውና፡፡» (ቁ. 13)

ብርሃን ግልጽነትን ያመለክታል፡፡ ግልፅ ስንሆን ሁሉ ያየናል፤ ያውቀናል፡፡ ነገር ግን ግልጽ ለመሆን ድፍረትና መተማመን ይጠይቃል፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ በሁለተኛ የቆሮንቶስ መልዕክቱ «የሚያሳፍረውን ስውር ነገር ጥለናልና በተንኮል አንመላለስም» ብሏል፤ በመቀጠልም «ትምክህታችን . . . በእግዚአብሔር ቅድስናና ቅንነት በዚህ ዓለም ይልቁንም በእናንተ ዘንድ እንደ ኖርን የሕሊናችን ምሥክርነት ነው» ይላል፡፡ በዚህ ሳያበቃ «እንግዲህ የጌታን ፍርሃት አውቀን ሰዎችን እናስረዳለን ለእግዚአብሔር ግን የተገለጥን ነን፣ በሕሊናችሁ ደግሞ የተገለጥን እንደሆንን ተስፋ አደርጋለሁ፡፡» በማለት በእግዚአብሔርም ሆነ በሰው ዘንድ በፍፁም ግልጽነት እንደሚኖር ይጽፋል፡፡ ዳሩ ተከሶ በቀረበበት ሸንጎ በሊቀ ካህኑ ፊት «. . . እኔ እስከዚህች ቀን ድረስ በመልካም ኅሊና ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት ኖሬያለሁ፡፡» ብሎ የለ?[279] በሌላ በኩል ሰው የሚያሳፍር ነገር ሲኖረው ይሰወራል፤ መሰወር ሲሻ ደግሞ ጨለማን ይፈልጋል፤ ጨለማውም ቀስ በቀስ ይውጠዋል፡፡

ይህ አባባል ከጥቂት አመታት በፊት ያነበብኩትን አንድ ታሪክ አስታወሰኝ፡፡ ሰውየው ከሠላሳ ሚሊዮን በላይ አባላት ያሉት የአሜሪካ ወንጌላውያን ክርስቲያኖች ማህበር የወቅቱ ፕሬዚደንት ነበሩ፡፡ በዋነኝነትም በኮሎራዶ ስፕሪንግስ የሚገኘው አሥራ ሶስት ሺህ አባላት የነበሩት የአዲስ ሕይወት ቤተክርስቲያን መሥራችና ዋና መጋቢ ነበሩ፡፡ እኚህ በእግዚአብሔርም በሰውም ትልቅ አደራ የተጣለባቸው አገልጋይ ለካ ማንም ሰው የማያውቀው፣ ለዘመናት በውስጣቸው ሸሽገው የያዙት ጨለማ ኖሮ በከፉ ቀን በጨለማ የመዋጣቸው ዜና በታላላቅ የዜና አውታሮች በአለም ናኘ፡፡ ጉዳዩ እንዲህ ነው፡- እኚሁ «ታላቅ» መጋቢ ከሚኖሩበት ኮሎራዶ ስፕሪንግስ ጥቂት ርቆ ወደሚገኘው ዴንቨር ከተማ ጭምብል አጥልቀው፣ መልካቸውን ለውጠው ያቀኑና በስልክና በኢንተርኔት ከተገናኙት በወንድ አዳሪነት ሥራ የተሰማራ ሰዶማዊ ጋር በሆቴል ያሳልፋሉ፡፡ ደንበኛቸውን የተዋወቁት በንግድ ሥራ ላይ የተሰማራሁ ሰው ነኝ በሚል ነበር፡፡ ታዲያ አንድ ቀን በዋሽንግተን ዲ.ሲ ኋይት ሃውስ ውስጥ እሳቸው የሚመሩት ትልቅ ስብሰባ ነበር፡፡ የስብሰባው ርዕሰ ጉዳይ የአሜሪካ ወንጌላውያን አማኞች የሰዶማዊነትን መስፋፋት እንደሚቃወሙ ውሳኔ ያሳለፉበት ስብሰባ ነበር፡፡ በስብሰባው ማብቂያ ላይ የወቅቱ

---

[279] 2ቆሮ. 4፡2; 1፡12; 5፡11; ሐዋ.ሥራ 23፡1



For more books www.amharicchristianbooks.com

የማህበሩ ፕሬዚደንት እንደ መሆናቸው መጠን ፕሬዚደንት ጆርጅ ደብሊው ቡሽን ከጎናቸው አቁመው «ግብረ-ሰዶማዊነትን እንቃወማለን! እናወግዛለን!» በማለት መግለጫ ሰጡ፡፡ ታላላቅ መገናኛ ብዙሃን ዜናውን ዘገቡ፡፡ ያ በወንድ አዳሪነት የተሰማራው የዴንቨር ደንበኛቸው ዜናውን ተመለከተ፤ መግለጫውንም ሰማ፡፡ «እንዴ! ይህን ሰውዬ አውቀው የለ? ነጋዴ ነኝ አላለኝም? እዚያ ምን ይሰራል?» ብሎ ራሱን ጠየቀ፤ በሁኔታውም እጅግ ተናደደና ወዲያው የማጋለጡን ሥራ ተያያዘው፡፡

ሰውየው ገና ከኋይት ሃውስ ሳይሰናበቱ ማንነታቸውን የሚያብጠለጥለው ሌላ ዜና ዓለምን አዳረሰ፡፡ ደንበኛቸው ለምን እንዳጋለጣቸው ተጠይቆ ሲመልስ «ብዙ ደንበኞች አሉኝ አንዳቸውም ላይ እንዲህ አድርጌ አላውቅም፡፡ ይሄኛውን ግን እንዳጋልጠው ግድ ያለኝ ወደር የሌለው ግብዝነቱ ነው፡፡ ለእኔ ነጋዴ ነኝ ብሎ ይህን ተግባር እየፈፀመ፣ ኋይት ሃውስ ሰገነት ላይ ሌሎችን መኮነኑ አብግኖኛል፡፡» በማለት ተናግሯል፡፡ ሆኖም መጋቢው ውንጀላውን ወዲያው በጄ ብለው አልተቀበሉም፡፡ "ተቃዋሚዎች ስሜን ለማጥፋት ሆን ብለው የሚያናፍሱት ከንቱ አሉባልታ ነው" በማለት ሊያስተባብሉ ሞከሩ ሆኖም አልሰመረም፡፡ ነገሩ አገር ካወቀው፣ ፀሐይ ከሞቀው፣ ሰውየውም ከቤተ-ክርስቲያናቸውም ሆነ ከኃላፊነቶቻቸው ሁሉ ከተባረሩ ከጥቂት ጊዜያት በኋላ፣ በድረ-ገጻቸው ላይ እንዲህ የሚል ቃል ጽፈው አነበብኩ፡፡ «ከወጣትነቴ አንስቶ በሕይወቴ ጥግ ሸሽጌ የያዝኩት ጨለማ ነበር፣ ቀስ በቀስ አድጎ ዋጠኝ፡፡» የሚል፡፡

በተወሰነ መጠን ግላዊነት ሊኖረን ቢያስፈልግም፣ ግላዊነታችን ወደ ምስጢራዊነት እንዲሻገር መፍቀድ የለብንም፡፡ ሰዎች የማያውቁት እንዲያውቁትም የማንፈልገው ልምምድ ካለን በውስጣችን ጨለማ ሸሽገናል ማለት ነው፡፡

> *‹‹ክፉ የሚያደርግ ሁሉ ብርሃንን ይጠላልና፣ ሥራውም እንዳይገለጥ ወደ ብርሃን አይመጣም፡፡ እውነትን የሚያደርግ ግን ሥራው በእግዚአብሔር ተደርጎ እንደሆነ ይገለጥ ዘንድ ወደ ብርሃን ይመጣል፡፡›› (ዮሐ. 3፡ 20፣21)*

ተብሎ እንደተጻፈ የምናፍርበት፣ የምንሸማቀቅበት፣ ብርሃን (ገሃድ መውጣት) የሚያስጠላን፣ ጨለማን (ተሰውሮ መኖርን) የሚያስመርጠን ማንኛውም ልምምድ ካለን ፈጥነን አውጥተን እንጣለው፡፡ ስላለፈው ምሕረትን ለማግኘት ወደ እግዚአብሔር ዙፋን በንስሐ እንምጣ፣ ለወደፊቱ ፀጋን ለመቀበል ወደ ፀጋው ዙፋን



For more books www.amharicchristianbooks.com

በእምነት እንቅረብ፡፡[280]

አለዚያ ግን ብርሃን ቀስ በቀስ እየሸሸ ቀኑም እየመሸ ይሄዳል፣ ጨለማውም ቀስ በቀስ ያይላል፡፡ ብርሃን ሲሸሽ ጨለማን ተገን አድርገው አደጋ የሚጥሉ ዘራፊዎች ይበረክታሉ፣ ፍርሃትም ያይላል፣ ሰው ሁሉ በሩንና መስኮቱን ይከረችማል፤ ከዚያም ድካም እየበረታ፣ የእንቅልፍ ድባብ እየረበበ ይመጣና ፍጥረት ያሸልባል፡፡ ያ ሰዓት ሌባው በትጋት የሚሰራበት፣ ጸጋን የሚዘርፍበት ምቹ ሰዓት ነው፡፡ ለዚህ ነው ጳውሎስ በሚፅፍላቸው አማኞች መካከል ላሉ ፣ ጨለማው በርትቶባቸው ከሞት የማይተናነስ መንፈሳዊ እንቅልፍ ለሚጨልጡ አማኞች ፣ በዘመኗ ቤተ-ክርስቲያን በጥምቀት መዝሙርነቱ የሚታወቀውን ስንኝ በመጥቀስ፡-

> *«አንተ የምትተኛ ንቃ ከሙታንም ተነሳ ክርስቶስም ያበራልሃል» (ቁ. 14)* የሚለው፡፡

አንተ በርና መስኮትህን ጠርቅመህ ስለዘጋህ፣ ማንም እንዳያይህ ቀዳዳን ስለወታተፍህ፣ ራስህ በፈጠርከው ጨለማ ተውጠህ መላ ዓለሙ የጨለመ መሰለህ እንጂ ፀሐይ ወጥቷል፤ ሌቱ ነግቷል፣ ጊዜው ቀን ነው፡፡ የብርሃን ልጆች በብርሃን እየተመላለሱ ነው፡፡ አንተም ብትነቃ፣ ወደ ሞት ከሚወስድ ከዚህ ክፉ እንቅልፍ ብትባንን፣ የልብህንም በር በንስሐ ለጌታ ብትከፍት፣ ዳግም ከጨለማ ጋር ቃል ኪዳን ላትገባ ወስነህ ብትወጣ፣ ብርሃንህ ክርስቶስ እንደ ፀሐይ ያበራልሃል፣ ማለቱ ነው፡፡

[280] ዕብ. 4፡16



For more books www.amharicchristianbooks.com

# ምዕራፍ ፱
# በጥበብ መመላለስ

ኤፌ. 5፡ 15 - 20

«በአንድነት» «በአዲስነት» «በፍቅር» «በብርሃን» ተመላለሱ የሚለው ተግራባዊ ኑሮ ላይ ያማከለ የጳውሎስ መልዕክት ቀጥሏል፡፡ በዚህ ክፍል ትኩረቱን በጥበብ ላይ ያደረገና በመንፈስ የተሞላ ለመጨረሻው ዘመን የተገባ የጥበብ ኑሮ ምን እንደሚመስል ይገልፃል፡፡ ዕብራውያን እግዚአብሔር ርስት አድርጎ በሰጣቸው ምድር ሕጉን እየጠበቁ የሚኖሩትን ኑሮ የሚያሳየውን «መመላለስ» የሚለውን ቃል በዚህ ስፍራ ከዚህ ቀደም ከተጠቀመባቸው ዘጠኝ ስፍራዎች በመጠኑም ቢሆን በተለየ መንገድ ጥቅም ላይ አውሎታል፡፡ ልዩ የሚያደርገውም የተጨመረበት «በጥንቃቄ ተጠበቁ» የሚለው ገላጭ ቃል ነው፡፡

እንደ ተለመዱት የብሉይ ኪዳን የጥበብ መጻሕፍት ጳውሎስ ሰዎችን በሁለት ከፍሎ «ጥበበኞችና ጥበብ የሌላቸው» « አዋቂና ሞኝ» በማለት ይገልፃቸዋል፡፡ አንባቢዎቹንም ለአዲሱ የሰው ዘር በሚሆን ሰማያዊ ጥበብ እንዲመላለሱ ይመከራቸዋል፡፡

ጳውሎስ ጠቢብ የሚላቸው የዚህን ዓለም ጥበበኞች እንዳልሆነ ግልፅ ነው፡፡ በአንደኛ ቆርንቶስ መልዕክቱ «እግዚአብሔር ጥበበኞችን እንዲያሳፍር የዓለምን ሞኝ ነገር መረጠ» (፤ቆሮ.፤፡27 ) ብሎናልና፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔር ሞኞችን የመረጠው የሞኞች ማህበር ለማቋቋም አይደለም፡፡ ይልቅ የእግዚአብሔር ጥበብ የሆነውን ክርስቶስን ሊገልጥባቸው በዓለም ጠቢባን ፊት እንደ ሞኝ የሚቆጠሩትን ሰዎች በወንጌል ጠራ፡፡ ሞኝነት በጥበብ ፊት ያፍራል እንጂ ጥበብን ማሳፈር አይችልም፡፡ የእግዚአብሔር ዓላማ ግን ከንቱ የሆነውን የዓለምን ጥበብ ማሳፈር ነው፡፡ ይህንንም የሚያደርገው አስቀድሜ እንዳልኩት የጥበብ ራስ የሆነውን ክርስቶስን ጥበበኞች ነን በሚሉት ዘንድ እንደ ሞኝ በሚቆጠሩት አማኞች ውስጥ በመግለጥ ነው፡፡ ይህም ጥበብ እንደ ዓለም ሰዎች በንግግር ብዛትና በከንቱ ልፍለፋ የሚገለፅ ሳይሆን በጥንቃቄ በመመላለስ በተግባር የሚታይ ነው፡፡

ጳውሎስ ጥበብን ከጊዜ ጋር በማዛመድ «ቀኖቹ ክፉዎች ናቸውና ዘመኑን ዋጁ» ይለናል፡፡ ጊዜን ለመግለፅ የተጠቀመበት የግሪክ ቃል « ካይሮስ » የሚል ሲሆን ትርጓሜውም በጊዜ ውስጥ ከታወቀና በአግባቡ ጥቅም ላይ ሊውል ከሚገባው መልካም ዕድል ጋር የተቆራኘ ነው፡፡ ይህንኑ ቃል በገላትያ መልዕክቱ ላይ



For more books www.amharicchristianbooks.com

ሲጠቀምበት «እንግዲያስ ጊዜ ካገኘን ዘንድ ለሰው ሁሉ ይልቁንም ለኃይማኖት ቤተሰቦች መልካም እናድርግ» (ገላትያ 6፡10) በማለት በሚያልፍ ጊዜ የማያልፍ ሥራ ሊሰራ እንደሚቻል «በመንፈስ ግን የሚዘራው ከመንፈስ የዘላለምን ሕይወት ያጭዳል» (ገላትያ 6፡8) በማለት ጠቁሟል፡፡

የጥበብ መንፈስ ያደረባቸው ዳንኤልና ጓደኞቹ ናቡከደነፆር ጠቢባንን ለመግደል ትእዛዝ ባወጣ ጊዜ ያደረጉት ነገር ቢኖር ጊዜን በመግዛት የጌታን ፈቃድ መለመን ነበር፡፡ በዳዊት ሠራዊት ውስጥ የነበሩት እስራኤላውያን የሚገባውን ያደርግ ዘንድ ዘመኑን የሚያውቁ ጥበበኞቹ የይሳኮር ልጆች እንደ ነበሩ መጽሐፍ ይነግረናል፡፡[281]

የቀድሞው አማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ «ዘመን» ብሎ የተረጎመው «ካይሮስ» የተሰኘው የግሪክ ቃል «ጊዜ» ከሚለው የአማርኛ ቃል ጋር የሚቀራረብ ሲሆን ትርጓሜውም «ጊዜ ወርቅ ነው» ከሚለው ተለምዷዊ ብሂል ጋር የሚሄድና ጊዜ ማንኛውም ዋጋ ተከፍሎ ሊገዛ እንደሚገባው ውድ ሸቀጥ መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው፡፡ ሐዋርያው በመቀጠል «ዘመኑን ዋጁ» ይለናል፡፡ መዋጀት መቤዠት ከሚለው ቃል ጋር አንድ ዓይነት ሲሆን ሁለቱም አስቀድሞም የራስ የነበረን ንብረት ዋጋ ከፍሎ በመግዛት መልሶ የራስ ማድረግን የሚያሳዩ ቃላት ናቸው፡፡

እንግዲህ ጊዜን እንድንገዛ፣ እንድንዋጅ ወይም እንድንቤዥ ታዘናል ፡፡ ቀደም ሲል በ1፡7 እግዚአብሔር በውድ ልጁ ደም ከኃጢአት እንደተቤዠን ፅፎልናል፡፡በመቀጠልም በ1፡14 ላይ በደሙ የተቤዣቸውንና መንፈሳቸውን በቅዱስ መንፈሱ ሕያው ያደረገውን ሰዎች ሐሳባቸውን፣ ስሜታቸውን፣ ፈቃዳቸውን ባጠቃላይ ነፍሳቸውን በክርስቶስ የመጠቅለልና የመዋጀት ሥራ እየሰራ እንደሆነ ነግሮናል፡፡ ከዚያም በ4፡30 ላይ «ለቤዛም ቀን የታተማችሁበትን ቅዱሱን የእግዚአብሔርን መንፈስ አታሳዝኑ» በማለት ከፊት ለፊታችን እግዚአብሔር ሙታንን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በማስነሳት ሰውነታችንን እንደሚቤዥ አረጋግጦልናል፡፡ ከዚህም የእግዚአብሔር የማዳን ዕቅድ የሰውን ሁለንተና ማለትም መንፈስ፣ ነፍስ፣ ሥጋ በሂደት መዋጀት እንደ ሆነ መመልከት እንችላለን።

እግዚአብሔር መንፈሳችንን ከኃጢያት ዕዳ ከዋጀ (1፡7) ነፍሳችንን ከእኔነት፣ ከኃጢአተኝነትና ከዓለማዊነት እየዋጀ እንደሆነ (1፡14) ሥጋችንንም ከሞት ኃይል እንደሚዋጅ ፅኑ ተስፋ ከሰጠ (4፡30) በኋላ እኛ ደግሞ ጊዜን እድንዋጅ ትዕዛዝ ሰጥቶናል፡፡ እግዚአብሔር ሰውን እንጂ ጊዜን አይዋጅም፡፡ ነገር ግን ሰውን ይዋጅና የዋጀው ሰው ጊዜን እንዲዋጅ ትዕዛዝ ይሰጣል፡፡ በእርግጥም የተዋጀ ይዋጃል፡፡

281 ትን. ዳን. 2፡ 14-16; 1ዜና. 12፡ 32



For more books www.amharicchristianbooks.com

ጊዜ ለምን መዋጀት አስፈለገው? ጊዜ መዋጀት ያስፈለገው ቀኖቹ ክፉዎች ስለሆኑ ነው፡፡ ቀኖች በራሳቸው ክፋትም ሆነ መልካምነት የላቸውም፡፡ ነገር ግን በመንፈሳዊ ዓለም ክፋትን የሚያውጠነጥኑ የክፋት መንፈሳውያን ሠራዊት አሉ፡፡ እነዚህም አካል አልባ መናፍስት ያቀነቀኑትን ክፋት የሚገልጡባቸው የአመፅ ልጆች በየስፍራው ሞልተዋል፡፡ የሁለቱ ድምር ቀኑን ክፉ ያደርገዋል፡፡

በአይሁድም ሆነ በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን ክርስቲያኖች ዘንድ የቀን ክፋት ከመጨረሻው ዘመንና ከዓለም ፍፃሜ ጋር አያይዞ መግለፅ የተለመደ ጉዳይ ነበር፡፡ በእርግጥም ዘመኑ እያለቀ ሲሄድ ሰይጣንም ጥቂት ዘመን ብቻ እንዳለው አውቆ በቁጣ ሲወርድ ቁጣውን የሚገልጠው በቀን ውስጥ በሚኖሩ ሥጋ ለባሾች ውስጥ ስለ ሆነ ቀኑን ክፉ ያደርገዋል፡፡[282] ክፉው ክፉ ሰዎችን ተጠቅሞ ቀኑን ክፉ ማድረግ የቻለው የሚጠቀምባቸው ሰዎች በጊዜ ውስጥ ስለሚኖሩና ጊዜው በእጃቸው ስላለ ነው፡፡ ታዲያ ለክፉ ሰዎች መጠቀሚያ የሆነው ጊዜ ለአማኞችም ተሰጥቷል፡፡ ነገር ግን በጥበብ በመመላለስ፣ ጊዜውን መግዛትና መልካም ማድረግ የእኛ የአማኞች ሃላፊነት ነው።

በዙሪያችን ክፋት ሞልቷል፤ ቴሌቪዥናችንን ስንከፍት፣ ሬዲዮናችን ስንነገሩር፣ ጋዜጦችን ስናገላብጥ የምናየውና የምንሰማው ከዕለት ወደ ዕለት እየባሰ የሚሄድ ክፋት ነው፡፡ በእርግጥ ክፋትን ሁሉ እንድናስቆም አልታዘዝንም፡፡ የፈለገውን ያህል በፀሎት ብንተጋና በመቃወም ብንፀና ጊዜው ሳይደርስ ክፋት አይቆምም፡፡ ነገር ግን ክፋት በሞላበት ዓለም ውስጥ መልካም በማድረግ ዘመኑን ልንዋጅ እንችላለን፡፡ ይህ አባባል «መልካም ምንድነው?» ብለን እንድንጠይቅ ማነሳሳቱ አይቀርም። መልካም፣ አንድ እርሱም ጌታ ነው፤ ከእርሱም ውስጥ መልካም ፈቃድ ይፈልቃል፡፡ ለዚህም ነው ጳውሎስ «ስለዚህ የጌታ ፈቃድ ምን እንደሆነ አስተውሉ እንጂ ሞኞች አትሁኑ፡፡» (ቁ፡17) የሚለው፡፡ እነሆ ጥበብ በዚህ አለ፣ በራሳችን ዘንድ ጠቢባን ሆነን፣ በማስተዋላችን ተደግፈን፤ በዐይናችን ፊት መልካም መስሎ የታየንን ልናደርግ አይገባም፡፡ ነገር ግን ለዘመኑና ለጊዜው የሚሆነውን የጌታን ፈቃድ ለማወቅ ልንተጋ፣ በተገለጠልንም ጊዜ ያለማመንታት ልናደርገው ይገባናል፡፡ ለዚህም አውነተኛ አብነታችን ጌታ ራሱ ነው፡፡ በሕዝብ መካከል ባገለገለበት ሶስት ዓመት ተኩል ውስጥ «ቀን ሳለ የላከኝን ፈቃድ ላደርግ ሥራውንም ልፈፅም ይገባኛል፡፡» በማለት ሥራውን አከናወነ፡፡ በመጨረሻም በመስቀል ላይ የሚሰዋበት ጊዜ ሲደርስ በአባቱ ፊት ተደፍቶ « አባት ሆይ የአንተ ፈቃድ እንጂ

[282] ራዕይ 12፡12



For more books www.amharicchristianbooks.com

የእኔ ፈቃድ አይሁን» (ዮሐ 9፡) አለ፡፡ የአባቱንም ፈቃድ ለማወቅ በብርቱ ጩኸት ከእንባ ጋር ፀሎትንና ምልጃን አቀረበ፡፡ በመታዘዙም ሁላችንን አተረፈ፡፡ እኛም የታዘዝነው ይህንን ፈለግ እንድንከተል ነው፡፡

ታዲያ «የጌታን ፈቃድ እንዴት አውቃለሁ?» ብለን ልንጠይቅ እንችል ይሆናል፡፡ ፈቃዱን ለማወቅ የግድ ነቢይ ፍለጋ መሄድ ወይም ሕልምና ራዕይ ልናይ አያስፈልገንም፡፡ በእግዚአብሔር መንፈስና በእግዘአብሔር ቃል የታደሰ አዕምሮ ካለን፣ በጎውን፣ ፍፁሙንና ደስ የሚያሰኘውን የጌታ ፈቃድ ለይተን ማወቅ እንችላለን፡፡ (ሮሜ 12፡2)

ጳውሎስ ለቆላስያስ ወገኖች *«የፈቃዱ እውቀት መንፈሳዊ ጥበብና አዕምሮን ሁሉ እንዲሞላባችሁ እየለመንን ስለ እናንተ ፀሎትን አልተውንም . . . »* (ቆላ፡- 1፡9) እንደሚል፣ የፈቃዱ እውቀት መንፈሳዊ ጥበብንና ማስተዋልን ሁሉ እንዲሞላብን ልንማፀን ይገባል፡፡

ለአዲሱ ፍጥረት የሆነው መንፈሳዊ ጥበብ ይህ ነው፡፡ የጌታን ፈቃድ ማስተዋልና በማስተዋል የተረዳነውንም፣ ሁኔታው የሚጠይቀውን ዋጋ በመክፈል፣ ከክፉው ተናጥቀን በገዛነው ጊዜ ውስጥ በትጋት ማድረግ ነው፡፡

ጳውሎስ በመቀጠል *«መንፈስ ይሙላባችሁ እንጂ በወይን ጠጅ አትስከሩ»* በማለት ትዕዛዝ ይሰጥና በወይን ጠጅ መስከርን «ማባከን» በማለት ይኮንነዋል፡፡ በአማርኛ «ማባከን» ተብሎ የተተረጎመውን፣ ግሪኩ «አሶትያ» ይለዋል፡፡ ይህን ቃል በርካታ የእንግሊዘኛ ትርጉሞች «Debauchery» ብለው ተርጉመውታል፡፡ የኦክስፎርድ መዘገበ ቃላት ይህንን ቃል «ቅጥ ያጣ፣ መስመር የለቀቀ ወሲባዊ ተግባር» በማለት ይተረጉመዋል፡፡[283] ይህንንም የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አዋቂዎች በዘመኑ በስፋት ይመለክ ከነበረው «ዳዩኒሰስ» በመባል ከሚታወቀው የወይን ጠጅ አምላክ፣ የአምልኮ ስርዓት ጋር ያዛምዱታል፡፡ ጳውሎስ ይህን በሚፅፍበት ጊዜ ይህ ሃሳብ በውስጡ ይኑር አይኑር እርግጠኛ መሆን ባንችልም፣ በወይን ጠጅ መስከርን ከልቅ ወሲባዊ ልምምድ ጋር ማገናኘቱ፣ የመጀመሪያ ተደራሲያኑ በስፋት የሚያውቁትን የ«ዳዮኒሰስ» አምልኮ ጋር አያይዞ ማንሳቱ ሊሆን እንደሚችል ብዙዎች ይገምታሉ፡፡ የዚህ ጣኦት አምልኮ ተከታዮች የወይን ጠጅ አምላክ ለሚሉት ለዳዮኒሰስ ክብር ተሰብስበው ወይን ጠጅ ይጠጣሉ፣ ይሰክራሉ፣ ራሳቸውን ይስታሉ፣ በመጨረሻም ከሰውነት ክብር ወጥተው እንሰሳና አውሬ ይሆናሉ፡፡ በሰላም የጀመረው ጉባኤያቸው በረብሻ፣ በዝሙትና በጥፋት

[283] Oxford University Press 1974



For more books www.amharicchristianbooks.com

ይደመደማል፡፡ ከዚህ የተነሳ ራሱ በልቅነት የሚታማው የሮም መንግሥት በሚገዛቸው ሥፍራዎች ሁሉ የዳዮኒሰስ አምልኮ እንዳይካሄድ አውጆ እንደ ነበር መጻሕፍት ይመሰክራሉ፡፡[284]

ጳውሎስ ግን *«መንፈስ ይሙላባችሁ»* ይላል፡፡ አፃፃፉም ምክር አዘል ሳይሆን ትዕዛዝ ነው፡፡ በ1፡13 ላይ እንደ ተገለፀው የርስታችን መያዣ በሆነው በመንፈስ ቅዱስ ታትመናል፤ ይህም የአንድ ጊዜ ጉዳይ ነው፡፡ በመንፈስ መሞላት ግን የከዕለታት አንድ ቀን የመታሰቢያ ልምምድ ሳይሆን፣ የሁል ጊዜ ጉዳይ ሊሆን ይገባዋል፡፡ ጳውሎስ ጎን ለጎን በጠቀሳቸው ሁለት ተግባሮች ማለትም በመንፈስ በመሞላትና በወይን ጠጅ በመስከር ውስጥ ተወዳዳሪና ተነፃፃሪ ገፅታዎችን እናያለን፡፡ በበዓለ ሃምሳ ቀን መንፈስ ቅዱስ በአማኞች ላይ ሲወርድ የተመለከቱ ሰዎች *«ኢያሬዘባቸው ጉሽ የወይን ጠጅ ጠግበዋል አሉ፡፡»* በኋላም ጴጥሮስ ሲናገር *«ለእናንተ እንደመሰላችሁ እነዚህ የሰከሩ አይደሉም . . . »* በማለት ስለ መንፈስ ቅዱስ ተስፋ ሰበከላቸው፡፡ ይህም በመንፈስ ቅዱስ መሞላት ከወይን ጠጅ ስካር ጋር ተመሳስሎ እንደ ተወሰደ ያሳየናል፡፡

ወይን ጠጅ በሰው ውስጥ ሲሞላ ራሱን ያስተዋል! መንፈስ ቅዱስ ሲሞላብን ግን ራሳችንን እግዚአብሔር እንደሚያውቀን እንድናውቅና ራሳችንን እንድንገዛ ያደርገናል፡፡ በርግጥ ወይን ጠጅም፣ መንፈስ ቅዱስም፣ በሰው ውስጥ ሲሞላ ሰውየውን ይቆጣጠሩታል፡፡ ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ እንደ ስሙ ቅዱስ ነውና የሞላባቸው ሰዎች ራሳቸውን ከመግዛት ባሻገር ትርጉም ያለው'፣ ሰሚዎችንም ሆነ ተመልካቾችን የሚያንፅ ንግግር እንዲናገሩና መልካም ተግባር እንዲፈፅሙ ያግዛል፡፡

የዓለም ጥበብ ለእግዚአብሔርም ሆነ ለእኛ ሞኝነት ነው በምላሹም የእኛ ጥበብ ለአለም ሞኝነት ነው፡፡ ለእኛ በመንፈስ ቅዱስ መሞላት ጥበብ ነው፡፡ ዓለም ግን በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተን የምንሆነውን ሞኝነት አድርጋ ቆጥራ ልታፌዝበት ትችላለች፡፡ ሆኖም ይህ በየጊዜው በመንፈስ ቅዱስ ከመሞላት ሊከለክለን አይገባም፡፡

ለመሆኑ መንፈስ ቅዱስ ሲሞላብን ምን እናደርጋለን? ጳውሎስ አማኞች በመንፈስ ቅዱስ ሲሞሉ ምን እንዲሚያደርጉና የሙላቱ ውጤት ምን እንደሚመስል ሲፅፍ ፡- «በመዝሙርና በዝማሬ በመንፈሳዊም ቅኔ እርስ በርሳችሁ ተነጋገሩ ለጌታ በልባችሁ ተቀኙና ዘምሩ ሁልጊዜ ስለ ሁሉ በጌታችን በእየሱስ ክርስቶስ አምላካችንና

[284] Hared sayings of the bible



For more books www.amharicchristianbooks.com

አባታችንን ስለሁሉ አመስግኑ፡፡» (ቁ19፣20 ) ይላል፡፡ በዚህ ክፍል የተጠቀሱትን ዝማሬ ነክ ቃላት በሁለት ክፍለን ለመመልከት እንገደዳለን፡፡ « በመዝሙርና በዝማሬ በመንፈሳዊ ቅኔ እርስ በርሳችሁ ተነጋገሩ» የሚለው አንደኛው የእርስ በእርስ ሕብረትን ሲያመለክት፣ ሁለተኛው ደግሞ «ለጌታ በልባችሁ ተቀኙና ዘምሩ» የሚለው ደግሞ፣ በእኛና በጌታ መካከል ያለውን አምልኮ ያሳያል፡፡

እኛ ስለ መዝሙርና ዝማሬ ሲነሳ፣ በየስብሰባዎቻችን በአምልኮ መሪዎቻችን እየተመራን፣ በሙዚቃ መሳሪያ ታጅበን የምንዘምራቸውን፣ ነገር ግን የቃሎቻቸውን ፍሬ ሃሳብ እምብዛም ልብ የማንላቸው ኹነቶች ብቻ ልናስብ እንችል ይሆናል፡፡ ነገር ግን ክፍሉ በዚያን ዘመን የነበሩ አማኞች በማህበር ሲሰበሰቡ የሚዘምሯቸውን እንደ ፊሊ2፡6-11፣ ቆላ1፡15-20 እና 1ጢሞ 3፡16 ያሉ መሠረታዊና ጠንካራ የእምነት አንቀጾች ያዘሉ ዝማሪዎችን በመንፈሳዊ ቅኔ በመዘመርና በመነጋገር በጌታ ፊት ስለሚያሳልፉት ጊዜ የሚያወሳ ነው፡፡ እኛስ ዛሬ በመዝሙረ ዳዊት የተሰባሰቡትን የእነ ንጉሥ ዳዊትን፣ የእነ አሳፍን እና የቆሬ ልጆችን መዝሙሮች እየተማርንና እየተነጋገርን ጌታን እናመልክ የለ ?

በዚህ አቅጣጫ በጣምራ የተፃፉትን የኤፌሶንና የቆላስይስን ትይዩ ክፍሎች ስንመለከት አንድ የዘነጋነውን ነገር ያስታውሰናል፡፡ ኤፌ5፡18-20 እና ቆላ 3፡-16-17 ትይዩ ክፍሎች ናቸው፡፡ አንደኛው «መንፈስ ይሙላባችሁ» ሲል ሌላኛው «የእግዚአብሔር ቃል በሙላት ይኑርባቸሁ» ይላል፡፡ ከዚህም በእግዚአብሔር ቃል በመሞላትና በእግዚብሔር መንፈስ በመሞላት መካከል ልዩነት እንደሌለ፣ መንፈስ ሲሞላብን የእግዚአብሔር ቃል እንደሚሞላብን፣ የእግዚአብሔር ቃል ሲሞላብን መንፈስ ቅዱስ እንደሚሞላብን እንገነዘባለን፡፡ ቃሉ የመንፈስ ሰይፍ ስለሆነ ቃሉና መንፈሱ አይለያዩም፡፡

ታዲያ በመዝሙርና በዝማሬ፣ በመንፈሳዊም ቅኔ፣ እርስ በርሳችን በመነጋገር አናበቃም፣ ጊዜ ተወስዶ የበሰለና ያረጀ ወይን ጠጅ ሲጠጣ ቀስ በቀስ እየሞላና እእምሮን፣ ስሜትን፣ ፈቃድን፣ እየተቆጣጠረ እንደሚሄድ ሁሉ የቃሉም መንፈስ የልብ አይናችንን እያበራ፣ አዕምሮችንን እያስገረመ፣ ስሜታችንን እየኮረኮረ፣ በጎንዮሽ እርስ በእርስ ከሚሆን ንግግር ባሻገር በእኛና በጌታ መካከል ወደሚሆን ቋሚ አምልኮ ያሸጋግረናል፡፡ ይህንን ነው፡- « ለጌታ በልባችሁ ተቀኙና ዘምሩ . . .» (ቁ 19) የሚለው፡፡ ቅኔና ዝማሬያችንም የሚያተኩረው በማንነቱና በሥራው ላይ ሲሆን፣ በክርስቶስና በቤተ ክርስቲያን መካከል ያለው ሕብረት ትልቅ ሥፍራ ይይዛል፡፡ በእርግጥ በዙሪያችን የከበቡን እንድናዝን፣ እንድንመረር፣ ለምን? ብለን እንድንጠይቅ፣ ብሎም እድናጉረመርም ግድ የሚሉን በርካታ ነገሮች ሊኖሩ



For more books www.amharicchristianbooks.com

ይችላሉ፡፡ ቃሉ ግን «ሁል ጊዜ ስለ ሁሉ አመስግኑ . . . » (ቁ20) ይለናል፡፡ ሆኖም እንዲህ ሲል ስለ ክፋቱም፣ ስለዓመፁም ሁሉ እግዚአብሔርን አመስግኑ ለማለት ሳይሆን፣ በዚህ ሁሉ ውስጥ ጎልቶ ሊታይና ሁሉን ጥሶ ሊወጣ የሚገባው እግዚአብሔር በክርስቶስ አማካይነት ፍጥረተ- ዓለሙን ሁሉ ለመጠቅለል እየሰራ ስለ ሆነና የሁሉ ነገር ፍጻሜ ወደዚያ እንደሚያቀና ለእኛ ለምናምን ክፉ የሚመስለውን እንኳ እግዚአብሔር ለበጎ እንደሚለውጠው ለማሳሰብ ነው፡፡ ቀደም ሲል በ1፡6 ላይ «በውድ ልጁም እንዲያው የሰጠን የፀጋው ክብር ይመስገን ዘንድ ይህን አደረገ፡፡ » ብሎአልና፡፡

ሁሉ የተሰጠን በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል ነው፡፡ እኛም ሁልጊዜ ስለ ሁሉ አምላካችንንና አባታችንን የምናመሰግነው በኢየሱስ ክርስቶስ ስም መሆን አለበት፡፡



For more books www.amharicchristianbooks.com

# ምዕራፍ ፲
# ክርስቲያናዊ የቤተሰብ ግንኙነት

ኤፌ. 5፡21-6፡9

ይህ መልዕክት የተፃፈው በአንደኛው ክፍለ ዘመን ነው፡፡ እኛ የዛሬዎቹ አንባቢያን ደግሞ በሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን እንገኛለን፡፡ በእነርሱ (በጸሐፊውና በተደራስያኑ) እና በእኛ መካከል ያለው ርቀት የሃያ ክፍለ ዘመናት ነው፡፡ ስለዚህ መልዕክቱን ለመረዳት ከሥነ-ቋንቋ፣ ከሥነ-ታሪክና ከመልከዓ ምድራዊ ልዩነቶች ባሻገር ቢያንስ በዚያን ዘመን ስለ ነበረው አኗኗር፣ አስተሳሰብ፣ ሕግ፣ ልማድ፣ ባህልና ማህበራዊ መዋቅር በጥቂቱም ቢሆን መረጃ ማግኘት ይኖርብናል፡፡

የተባረክንበትን ሰማያዊ በረከት በማጤን በዚህ ምድር እንዴት ልንመላለስ እንደሚገባን ተግባራዊ ምክር ሲሰጥ የቆየው መልዕክት ከ5፡21 እስከ 6፡9 ባለው ክፍል በቤተሰባዊ ግንኙነት ላይ በማተኮር ተግባራዊ ትምህርቱን ይቀጥላል፡፡ አስቀድሞ በባልና ሚስት (5፡22-33) ፣ በመቀጠልም በወላጆችና በልጆች (6፡1-4)፣ በመጨረሻም በጌቶችና በባሮች (6፡5-9) መካከል ሊኖር ስለሚገባው በክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር የታነፀ ግንኙነት ይዘረዝራል፡፡

አማኞች በአለምና የክርስቶስ ማህበረሰብ በሆነችው በቤተ ክርስቲያን እንዴት ሊኖሩ እንደሚገባ ሲፅፍ የቆየው ጳውሎስ ወደ አማኞች ቤትና በውስጡም ወዳለው ቤተሰባዊ ግንኙነት ዞር እንዲል ምን ግድ አለው?

የአንደኛው ክፍለ ዘመን ማህበራዊ መዋቅር፣ በልዩነቶች የተሞላ ነበር፡፡ የጾታ፣ የዕድሜ፣ የኑሮ ደረጃ ወ.ዘ.ተ  የሚፈጥሯቸው ክፍተቶች አንዳች የማይሞላቸው ግዙፍ ሸለቆዎች ነበሩ፡፡ የዘመኑ ባሎች ስለ ሚስቶቻቸው የነበራቸውን ምልከታ ስንፈትሽ፣ ሕይወት እንዳለው ዕቃ በመቁጠር ለሰው የሚገባ ክብር ይነፍጓቸው እንደነበር ከታሪክ እንማራለን፡፡ የአይሁድ ወንዶችን እንደ ምሣሌ ብንወስድ፣ አንድ አይሁዳዊ ወንድ ዘወትር ለፀሎት «አምላኬ ሆይ! ሴት፣ አህዛብና ባሪያ ስላላደረከኝ አመሰግናለሁ» በማለት ሶስት የምስጋና ርዕሶችን ያቀርባል፡፡[285] በሰለጠኑት አሕዛብ ወንዶች ሳይቀር ለሴቶች ወይም ለሚስቶቻቸው የወሲብ አገልጋይ፣ የቤት ሠራተኛ፣ የልጆች ሞግዚት አድርጎ ከማየት ያለፈ ክብር አይሰጡም ነበር፡፡

ሌሎቹ የንቀት ጥቃት ሰለባዎች ልጆች ነበሩ፡፡ ልጆች፣ ወንዶችም ሆኑ ሴቶች፣

[285] Hard  Sayings of the bible P.642 p.2



For more books www.amharicchristianbooks.com

ለአቅመ አዳምና ለአቅመ ሔዋን እስኪደርሱ ድረስ እንደ ሰው አይቆጠሩም ነበር፡፡ ይህን ለመረዳት ሁለት ሺህ ዓመታት ወደ ኋላ ሄደን ታሪክ መመርመር የሚያስፈልገን አይመስለኝም፡፡ የእኛውን ሃገር የትናንት ትዝታና የዛሬ ተግባር በጥቅሉ ለልጆች ያለንን ምልከታ ብንዳስስ የምንለውን ነገር ፍንትው አድርጎ ያሳየናል፡፡ «የአንድን ሕዝብ አመለካከት ጠልቀህ ለማወቅ ከፈለግህ አስቀድመህ ተረቶቻቸውን አጥና!» በሚለው ብሂል መሠረት ስለ ልጆች የተረትናቸውን ተረቶች ዞር ብለን ብንቃኛቸው ልጆችን የሚያናንቁና የሚያጣጥሉ ናቸው፡፡ ከብዙ ጥቂቶቹን ብጠቅስ "ልጅና ፊት አይበርደውም!" "ከልጅ አትጫወት ይወጋሃል በአንጨት!" "ልጅ ደረሰ ቤት ፈረሰ!" "የልጅ ነገር ሁለት ፍሬ፣ አንዱ ብስል አንዱ ጥሬ!" "ልጅ ያቦካው ለራት አይበቃም!"፡፡ ታዲያ በእኛ ዘመን እንዲህ ከሆነ፣ ከሁለት ሺህ ዓመታት በፊትማ እንዴት ይሆን ነበር?

ወደ ባሮችና ጌቶች ግንኙነት ስንመጣ ለጎሊና የሚዘገንኑ እውነቶችን እናገኛለን፡፡ የሮም መንግሥት ኅልቁ መሣፍርት የሌላቸው ባሮች የሚኖሩበት ሥርዓተ ማህበር ነበር፡፡ ሰማንያ ሚሊዮን በሚጠጋው የያኔው የዓለም ሕዝብ ቁጥር መሃል የባሮች ቁጥር ስድሳ ሚሊዮን ይደርስ እንደ ነበረ ይገመታል፡፡[286] በዘመኑ ዓለም ፍልስፍና ላይ ግዙፍ ተፅዕኖ ያመጣው አርስቶትል እንኳ ስለ ባሮች በጻፈው ጽሁፉ «ባሮች ሕይወት ካለው መሣሪያ ያለፈ ማንነት የላቸውም»[287] «ባሮች ባሪያ የሆኑት በምርጫ ሳይሆን በተፈጥሮ ነው፡፡ ሴት ሴት፣ ወንድም ወንድ ሆኖ እንደሚወለድ ባሮችም ባሪያ፣ ጌቶችም ጌታ ሆነው ተወልደዋል»[288] ማለቱ በያኔው ዓለም ለባሮች የነበረውን አመለካከት ፍንትው አድርጎ ያሳያል፡፡

የባርያዎች ቁጥር ከመጠን በላይ ከፍተኛ ስለነበር፣ የሮም መንግሥት ሊመጣ የሚችለውን አመፅ ከመፍራቱ የተነሳ ባሮች በምንም ዓይነት ተመሳሳይ ልብስ ለብሰው በከተማ እንዳይታዩ ትዕዛዝ አውጥቶ ነበር፡፡ በተጨማሪም የባርያ አሳዳሪዎች በባሮቻቸው ላይ የፈለጉትን እርምጃ እንዲወስዱ በሕግ ሥልጣን ሰጥቷቸው ነበር፡፡ አንድ ጌታ አስቸገረኝ ያለውን ባርያ ከመግረፍ አልፎ ቢገድል፣ ባርያውን ለመግዛት ያወጣውን ገንዘብ ከመክሰሩ በቀር «ለምን እንዲህ አደረግህ?» ብሎ የሚጠይቀው አልነበረም፡፡[289]

[286] Gaebelein Frank Ely, The Expository's Bible Commentary, Ephesians, P.83
[287] Ibid (ዝኒ ከማሁ)
[288] Aristotle's theory of slavery, Book VII of the *Nicomachean Ethics*
[289] The slave system of Greek and Roman Antiquity by W.L Westermann 1955, PP. 75-76



For more books www.amharicchristianbooks.com

እንግዲህ እነዚህ ሁሉ (ሚስትና ባል፣ ልጆችና ወላጆች፣ እንዲሁም ባርያና ጌታ) ናቸው በክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በአንድነት የተሰበሰቡት፡፡ በዘመናችን ቤተ ክርስቲያን ስንል ፈጥኖ የሚመጣልን ከበላዩ የመስቀል አርማ የተሰቀለበት የተንጣለለ አዳራሽ ነው፡፡ በአንደኛው ክፍለ ዘመን ግን ክርስቲያኖች የሚሰበሰቡት በአማኞች ቤት ውስጥ ነበር፡፡[290] ስለዚህ ቤትና የሥራ ገበታ፣ ቤትና ቤተክርስቲያን፣ እምብዛም ልዩነት አልነበራቸውም፡፡ አብዛኞቹም የቤተክርስቲያን ስብሰባዎች የሚካሄዱት ሁሉን ሊሰበስብ የሚችል ቤት ባላቸው በጌቶችና በባሪያ አሳዳሪዎች መኖሪያ ነው፡፡ በዚህ ክፍል «ባሎች ሆይ . . . አባቶች ሆይ . . . ጌቶች ሆይ . . . » ተብለው ትዕዛዝ የተሰጣቸው እነዚሁ አባ ወራዎች ናቸው፡፡ ይህም የቤት ጉዳይ፣ የቤት ብቻ ሣይሆን የቤተክርስቲያንም እንደሆነ ያስገነዝበናል፡፡ ጳውሎስም ለቤተሰብ ጉዳይ ትልቅ ትኩረት ሰጥቶ በትጋት የሚፅፈው፣ የቤተሰብ ችግር የቤተ ክርስቲያን፣ የቤተ ክርስቲያንም ችግር የቤተሰብ ስለሆነና በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሸምግልና የሚያገለግሉት ወንድሞች በቤታቸው ባል፣ አባትና ጌቶች ስለሆኑ ነው፡፡ ለዚህም ነው ለጢሞቴዎስ ስለ ሽማግሌዎች ሲጽፍለት *«...ልጆቹን በጭምትነት ሁሉ እየገዛ የራሱን ቤት በመልካም የሚያስተዳድር፤ ሰው ግን የራሱን ቤት እንዲያስተዳድር ባያውቅ፣ የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን እንዴት ይጠብቃታል?»* (1ጢሞ 3፡4-5) በማለት የሚመክረው፡፡

በቤተሰብ ግንኙነት ላይ ያተኮሩት እነዚህ የጳውሎስ መልዕክቶች በየዘመናቱ ይልቁንም አሁን ባለንበት ዓለም ከክርክርና ከተቃውሞ አላመለጡም፡፡ ከክርክሮቹ ጥቂቶቹን ብንመለከት «ጳውሎስ፣ ሚስቶችን ለባሎቻችሁ ተገዙ፣ ልጆችን ለወላጆቻችሁ ታዘዙ፣ ባርያዎችን ለጌቶቻችሁ ተገዙ በማለት የዘመኑን ሥርዓት አጠናከረ እንጂ ምንም አዲስ ነገር አላመጣም ጳውሎስ ባጠቃላይ ሴቶች ላይ የአመለካከት ችግር ነበረው . . . እርሱ ራሱ የአይሁድ ባህልና የዘመኑ ኋላ ቀር አመለካከት ሰለባ ነበር፡፡» የሚሉ ናቸው፡፡ በእርግጥ ጳውሎስ የዘመኑን አመለካከት በመደገፍ አጠናከረ ወይስ ከዘመኑ የተለየ የአስተምህሮና የአስተሳሰብ ለውጥ አመጣ? ይህን ጥያቄ ለመመለስ ክፍሎቹን በጥንቃቄና በጥልቀት ማየት ይሻል፡፡ ብዙውን ጊዜ ይህን ክፍል ስናነብ ፈጥኖ ቀልባችንን የሚገዛው "ሚስቶች ሆይ ለባሎቻችሁ ተገዙ "(ቁ.)" ባሮች ሆይ ለጌቶቻችሁ ታዘዙ" (ቁ.) የሚሉት ነጠላ ክፍሎች ናቸው፡፡ ነገር ግን ትዕዛዙ ይህ ብቻ አይደለም፡፡ ይህንንም ተራ በተራ

[290] የአዲስ ኪዳን መጻህፍት በሙሉ የመጀመሪያዋ ክፍለ ዘመን ቤተ ክርስቲያን በአማኞች ቤት ውስጥ እንደ ነበረች የሚመሰክሩ ሲሆን ከታች የተዘረዘሩት ጥቂት ክፍሎች ያንን ለማሳየት ከየመጽሐፉ ተመርጠው የወጡ ናቸው፡፡ ሐዋ 2፡46; ሮሜ 16፡5; 1ቆሮ 16፡19; ቆላ 4፡15; 1ጢሞ 5፡13; ፊሊ 2.



For more books www.amharicchristianbooks.com

እንመለከታለን፡፡

ጸሐፊው በቤተሰባዊ ግንኙነት ላይ የሚያተኩረውን አንቀፅ የሚጀምረው፡

> *"ለክርስቶስ ካላችሁ አክብሮታዊ ፍርሃት የተነሳ አንዳችሁ ለአንዳችሁ ተገዙ፡፡ "(ቁ.21) /አ.መ.ት/ በማለት ነው፡፡*

የዚህ አባባል ጭብጥ ሚስቶች ለባሎች፣ ባሎችም ለሚስቶች፣ ልጆች ለወላጆች፣ ወላጆችም ለልጆች፣ ባሮች ለጌቶች ጌቶችም ለባሮች እንዲገዙ የሚጠይቅ ነው፡፡ እንግዲህ በዚያን ዘመን ከዚህ የበለጠ ሥር ነቀል ቋንቋ ከየት ሊመጣ ይችላል? አምላክ እጁን ታጥቦ የፈጠራቸው የሚባሉ፣ ሰማያዊ ደም እንዳላቸው የሚታሰቡ ጌቶች ከንብረቶቻቸው እንደ አንዱ ለሚቆጥሯቸው ባሮች ሊገዙ? እውነትም ኃያል የለውጥ መልዕክት!

ጳውሎስ መገዛትን የሚያየው ከማህበራዊ ግንኙነትና በህብረተሰብ ከሚሰጥ ሥፍራ አንፃር ሳይሆን በክርስቶስ አዲስ ከተገለጠው፣ በሚመጣውም ዓለም ገና በሙላት ከሚገለጠው ከእግዚአብሔር የሕይወት ሥርዓት አንፃር ነው፡፡

አንዳችሁ ለአንዳችሁ ተገዙ ሲል ባሎች የባልነታችሁን ሥፍራና ኀላፊነት ልቀቁ፣ ወላጆች የወላጅነት ድርሻችሁን አቁሙ፣ ጌቶች ጌትነታችሁን ጣሉና የባሪያዎቻችሁ ባሪያ ሁኑ፣ ማለቱ አይደለም፡፡ እንዲያ ቢሆንማ ኖሮ በመቀጠል ባሎች ሆይ . . . . አባቶች ሆይ . . . ጌቶች ሆይ . . . ብሎ ባልፃፈም ነበር፡፡ ነገር ግን ማምጣት የፈለገው የሥፍራና የስም ለውጥ ሳይሆን የአስተሳሰብና የተግባር ለውጥ ነው፡፡ አንዳቸው ለሌላቸው እንዲገዙ ያዘዘው፣ በቀድሞው ሥርዓት ከሚጠቀሙበት ተፈጥሮአዊና ማህበራዊ ማንነት የተነሳ ሳይሆን፣ ለክርስቶስ ካላቸው አክብሮታዊ ፍርሃት የተነሳ መሆን እንዳለበት ገልፆላቸዋል፡፡

ይህ በእርግጥ «አንዱ ለሌላው መገዛት» የሚለው ትምህርት ለዚያውም በዚያን ዘመን እንዴት ሊተገበር እንደሚችል ማሰብ በጣም ያስቸግራል፤ ሆኖም ዝቅ ብለን ለእያንዳንዱ የተሰጡትን መመሪያዎች ስንቃኝ ግልፅ ይሆናል፡፡ ሚስቶች ለባሎቻቸው ሲገዙ ለክርስቶስ ተገዝተዋል፣ ባሎች ሚስቶቻቸውን እንደ ራሳቸው አድርገው ሲወዱ፣ ተገዝተዋል፣ ልጆች ለወላጆቻቸው ሲታዘዙ፣ ተገዝተዋል፣ ባሮች ለጌቶቻቸው ሲታዘዙ ተገዝተዋል፣ ጌቶችም በሰማይ ያለውን ጌታ እያሰቡ ያለ አንዳች ዛቻ ለባሮቻቸው መልካም ሲያደርጉ ተገዝተዋል፡፡ በዚህ ሁኔታ አንዳቸው ለሌላቸው ተገዙ ማለት ነው፡፡ ይህም ክርስቶስን በማመን የመጣ ለዘመኑ እንግዳ አመለካከት ነው፡፡ ለዚህ ነው ትዕዛዞቹ "ክርስቶስ" እና "ጌታ" በሚሉ ሥነ-ክርስቶሳዊ ቃሎች የተሞሉት፡፡



For more books www.amharicchristianbooks.com

*"ዳሩ ግን ቤተ ክርስቲያን ለክርስቶስ እንደምትገዛ እንዲሁ ሚስቶች ደግሞ በሁሉ ለባሎቻቸው ይገዙ . . . ባሎች ሆይ ክርስቶስ ደግሞ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ወደዳት ሚስቶቻችሁን ውደዱ . . . ልጆች ሆይ ለወላጆቻችሁ በጌታ ታዘዙ . . . እናንተም አባቶች ሆይ ልጆቻችሁን በጌታ ምክርና በተግሣፅ አሳድጉአቸው እንጂ አታስቆጧቸው . . . ባሪያዎች ሆይ ለክርስቶስ እንደምትታዘዙ በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ በልባችሁ ቅንነት በሥጋ ጌቶቻችሁ ለሆኑ ታዘዙ. . . . እናንተም ጌቶች ሆይ ዛቻውን ትታችሁ እንዲሁ አድርጉላቸው፤ በእነርሱና በእናንተ ላይ የሚገዛው ጌታ በሰማይ እንዳለ ለሰው ፊትም እንዳያደላ ታውቃላችሁና፡፡"* 5፡24 25፡ 6፡1 4 5 9 (አፅንኦት ከራሴ)

በእርግጥ ጳውሎስ አንዳንድ የዘመናችን የፆታና የመደብ ተሟጋቾች እንደሚሹት፣ ሚስቶችን ለመብት፣ ባሮችን ለነፃነት እንዲታገሉ አልቀሰቀሰም፡፡ መቀስቀስም አይጠበቅበትም፡፡ ማናችንም ዛሬ ላይ ቆመን «ምናለ ጥቂት እንኳ የእኩልነትና የነፃነት ቃል በጻፈ» ልንል እንችል ይሆናል፡፡ ሆኖም የሐዋርያው ሰዎችን ከጨለማው አገዛዝ፣ ከኃጢአትና ከሞት ሥልጣን ነፃ የማውጣት እንጂ፣ የመደብ ትግል የማራመድ ተልዕኮ ወይም ባሮችን ለአመፅ የመቀስቀስ ተልዕኮ አልነበረውም፡፡ ለጳውሎስ ነፃነት፣ የሕይወት፣ የአስተሳሰብና የማንነት እንጂ የሥራ ድርሻ ጉዳይ አልነበረም፡፡ ይህንንም አመለካከቱን በአንደኛ ቆሮንቶስ መልዕክቱ ላይ በጉልህ አንፀባርቋል፡፡

*«. . . እያንዳንዱ በተጠራበት መጠራት እንደዚሁ ይኑር፡፡ ባሪያ ሆነህ ተጠርተህ እንደሆነ አይገድህም፤ አርነት ልትወጣ ቢቻልህ ግን አርነት ተቀበል፡፡ ባሪያ ሆኖ በጌታ የተጠራ የጌታ ነፃ ነውና፤ እንዲሁም ነፃ ሆኖ የተጠራ የክርስቶስ ባሪያ ነው፡፡ በዋጋ ተገዝታችኋል፤ የሰው ባሪያዎች አትሁኑ፡፡ ወንድሞች ሆይ እያንዳንዱ በተጠራበት እንደዚሁ ሆኖ በእግዚአብሔር ዘንድ ይኑር፡፡» 1ቆሮ. 7፡20-24*

በክርስቶስ በማመንና አዲሱን ማንነታቸውን በመረዳት በአስተሳሰባቸው የተለወጡ ባሮች በደሙ ለገዛቸው ለክርስቶስ እንጂ በብር ለገዟቸው ጌቶች ባሮች እንዳልሆኑ ያውቃሉ፡፡ በምድር ጌቶቻቸው ለሆኑት በሥጋ የሚታዘዙት፤ በሰማይ ያለውን የእነሱንም ሆነ የጌቶቻቸውን ጌታ ደስ ለማሰኘት እንጂ ለሰው ታይታ እንዳይሆን መክሯቸዋል፡፡ እውነተኛ ነፃነት በሥጋ መፈታት ሳይሆን በመንፈስ መፈታት እንደሆነ ከዚህ እንማራለን፡፡



For more books www.amharicchristianbooks.com

በእርግጥ ሚስቶች ለባሎች፣ ልጆች ለወላጆች የሚታዘዙበት መንገድና ባሮች ለጌቶች የሚታዘዙበት ሁኔታ በመጠኑም ቢሆን ተነጣጥሎ ሊታይ የሚገባው ነው፡፡ የባልና ሚስትም ሆነ የወላጆችና የልጆች ግንኙነት ተፈጥሯዊ ነው፡፡ ሴቶች ሴት የሆኑት፤ ወንዶችም ወንድ የሆኑት በምርጫና በግድ ሳይሆን በተፈጥሮ ነው፤ ባሮች ግን ባሮች የሆኑት አርስቶትል እንዳለው በተፈጥሮ አይደለም፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ይህንን አያስተምርም፡፡ ሰዎች በጦርነት በመሸነፍ፣ በዕዳ በመያዝ ወይም ከባሪያ ቤተሰብ በመወለድ ባሪያ ሊሆኑ ይችላሉ እንጂ ባርነት የተፈጥሮ ጉዳይ አይደለም፡፡ ይህንንም «*አርነት ልትወጣ ቢቻልህ ግን አርነት ተቀበል፡፡*» ከሚለው ከፍ ብለን ካነበብነው ከጳውሎስ ጽሑፍ መረዳት እችላለን፡፡ የዚህ አባባል የግሪኩ ፍቺ «ከባርነት ነፃ ለመውጣት ዕድሉን ካገኘህ ችላ አትበል፤ ዕድሉን ተጠቀምበት» የሚል ሃሳብ አዝሏል፡፡[291] ቤተሰብ እግዚአብሔር የሠራውና የደነገገው ተቋም ነው፡፡ ባርነት ግን የወደቀው የሰው ዘር በግፍና በዓመፅ ያመጣው እንጂ የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ሃሳብ አይደለም፡፡

ጳውሎስ ስለማህበራዊ ትስስር የጻፈውን አዲስ አመለካከት፣ በተለይ በያኔው ዓለም፣ በተግባር ለመተርጐም አስቸጋሪ ጉዳይ ነበር፡፡ ነገር ግን ለሚጽፍላቸው ወገኖች ቀላል የሚያደርገው፣ ይህንን ትዕዛዝ ከመስጠቱ አስቀድሞ ባሉት ክፍሎች(ከምዕራፍ 1 እስከ 3) ስለ እግዚአብሔር ሃሳብ፣ ስለ ክርስቶስ ጌትነት፣ በክርስቶስና በቤተ ክርስቲያን መካከል ስላለው ግንኙነትና እግዚአብሔር ሁሉን በአንድ ለመጠቅለል እየሰራ ስላለው *ሥራ* በጥልቀት አስተምሯል፡፡ ይህ ጥሪ የደረሳቸውና ይህም እውነት የተገለጣለቸው አማኞች ለጥሪው እንደሚገባ ከተመላለሱ እንዲህ መኖር አስቸጋሪ አይሆንባቸውም፡፡ ሸክሙንም ቀላል የሚያደርገው በሥጋ ብቃት ሳይሆን በመንፈስ ሙላት የሚኖር ስለሆነ ነው፡፡

ስለ ባልና ሚስት በፃፈው አንቀፅ ውስጥ ከዘፍጥረት መፅሐፍ ሁለት ክፍሎችን ጠቅሷል፡፡ ይህም ከሰው ውድቀት በፊት ለነበረው የእግዚአብሔር ሃሳብ የሰጠውን ሥፍራ ያሳያል፡፡ የነገሮችን ሁሉ መጀመሪያ በሚተርክልን በዘፍጥረት ምዕራፍ አንድ ላይ እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥር፣ በሰማይ የሚበሩትን አዕዋፍ፣ በምድር የሚነቀሳቀሱትን እንስሳትና በባሕር ያሉትን አሶች እንዲገዛ ሲያዘው፣ እንዲገዛ ያልፈቀደለት ነገር ቢኖር ራሱን ሰውን ብቻ ነው፡፡ ሰው ሰውን እንዲገዛ የእግዚአብሔር ፈቃድ አይደለም፡፡ ሰው መገዛት የሚገባው ለእግዚአብሔር ብቻ

[291] Gerald F. Hawthorne, et al, Dictionary of Paul and his Letters, p. 883



For more books www.amharicchristianbooks.com

ነው፡፡[292]

ጳውሎስ በትምህርቱ ለባሎችም ሆነ ለሚስቶች፣ ለወላጆችም ሆነ ለልጆች፣ ለጌቶችም ሆነ ለባሮች ምሳሌ አድርጎ የሚያቀርበው ክርስቶስን ነው፡፡ ክርስቶስ ለቤተ ክርስቲያን ያደረገው ነገር ለባሎች አቻ የሌለው ምሳሌ ነው፡፡ በሌላ መልኩ ደግሞ ወልድ አብን ራስ አድርጎ በአካል በምድር ላይ መመላለሱና ለአብ መገዛቱ፣ እንደ አካል ራሶቻቸው ለሆኑት ለባሎቻቸው እንዲገዙ ለተነገራቸው ለሚስቶች ምሣሌ ነው፡፡[293] ልጅ ሆኖ ለሥጋ ወላጆቹ በመታዘዝ፣ ለልጆች እውነተኛ ምሣሌ ነው፡፡ የባርያን መልክ ይዞ በመምጣት፣ እንደ ባርያ በመኖርና እንደ ባርያ በመሞት ለባሮች ፍቱን አርአያ ነው፣ [294] የሁሉ ጌታ በመሆን ለጌቶች አቻ የማይገኝለት አርአያ ነው፡፡[295] ከዚህ በመነሳት የክርስትና እምነት ቁጥር አንድ ጥሪ ሕይወቱን በመካፈል ክርስቶስን መምሰል እንደሆነ ማረጋገጥ እንችላለን፡፡

«ሣራ ለአብርሃም ጌታዬ ብላ እየጠራችው ታዘዘችለት» 1ጴጥ 3፡6 ይለናል፡፡ ነገር ግን በዘፍጥረት ውስጥ አንድም ቦታ አብርሃም በማለት ፈንታ ጌታ ብላ ስትጠራው አናይም፡፡ ይህ ሃሳብ የሚገኝበት ክፍል ሄደን ስንመለከት፣ አብርሃምና ሣራ ፈፅመው አርጅተው በነበረ ጊዜ፣ እግዚአብሔር መጥቶ ከፊታቸው በነበረው ዓመት ወንድ ልጅ እንደሚወልዱ ለአብርሃም ነገረው፤ በዚህ ጊዜ ከድንኳን ጀርባ የነበረችው ሣራ «ካረጀውና ጌታዬም ከደከመ በኋላ በዚህ ነገር መደሰት ይሆንልኛልን?» (ዘፍ 18፡12 አ.መ.ት.) ብላ እንደሳቀች የዘፍጥረት ፀሐፊ ይነግረናል፡፡ ታዲያ በዚህ የሣራ የልብ ሃሳብ ውስጥ አብርሃምን «ጌታዬ» ብላ እንደጠራችው መመልከት እንችላለን፡፡ ከዚህ በመነሳት ለሣራ አብርሃምን “ጌታ” በማለት መጥራቷ ቅፅል ወይም ተለዋጭ ስም መስጠቷ ሳይሆን፣ የልብ ሁኔታዋና የውስጣዊ አስተሳሰቧ መገለጫ እንደሆነ እንረዳለን፡፡ ጴጥሮስም የመጀመሪያው ክፍለ ዘመን አማኝ ሚስቶችን ሲመክር የሣራን ምሳሌነት የጠቀሰው፣ ስለ ቃል ማጣፈጫ የከንፈር ወዝ ለማውሳት ፈልጎ ሳይሆን፣ ስለ ልብ ሁኔታና አመለካከት ያለውን ግዙፍ ሥፍራ ለማሳየት ሽቶ እንደሆነ እርግጠኛ መሆን እንችላለን፡፡ ሣራ አመለካከቷ የተቀደሰ ስለ ነበር («ተስፋቸውን በእግዚአብሔር ላይ የጣሉ የቀድሞ ቅዱሳት ሴቶች . . . » 1ጴጥ.3፡5 ስለሚል) ኑሮዋ ከድንጋጤና ከፍርሃት የራቀ

[292] 1ቆሮ. 7፡23

[293] 1ቆሮ 11፡3

[294] ኢሳ 53; ፊሊ. 2፡5; 1ጴጥ 2፡18-25

[295] በአንደኛ ቆሮንቶስ መልዕክት ውስጥ ብቻ «ጌታ» የሚለው ቃል 66 ጊዜ መፃፉ የክርስቶስን ጌትነት አጉልቶ ለማሳየት የተደረገውን ጥረት ያመለክታል፡፡



For more books www.amharicchristianbooks.com

የመተማመን ኑሮ ነበር፡፡ ለዚህም ዋቢ የሚሆነን በአጋርና በእስማኤል ምክንያት ከባሏ ጋር የቁርጥ ቀን ፍጥጫ በገጠማት ጊዜ፣ ያለ አንዳች ፍርሃት አቋሟን መግለጥና ያመነችበትን ማስፈፀም መቻሏ ነው፡፡[296] ጴጥሮስም ይህንን መሠረት በማድረግ ለሚጽፍላቸው እህቶች «እናንተም ምንም ሳትፈሩ መልካም ብታደርጉ ልጆቿ ናችሁ» ፣ጴጥ. 3፡6 በማለት ይህ የተቀደሰ አመለካከት እንዲጋባባቸው ይመክራል፡፡

## ባልና ሚስት

በባልና ሚስት መካከል ሊኖር ስለሚገባ ግንኙነት በ12 ቁጥሮች ተከሽኖ የተቀመጠው ይህ ክፍል ጥልቀት የሞላበት ነው፡፡ በዚህ ጽሑፍ እያንዳንዱን ለመመልከት የሚያዳግት ቢሆንም ዋና ዋናዎቹን አይተን እንለፍ፡፡

ሚስቶች ለባሎች እንዲገዙ ታዘዋል፡፡ እንዴት? ለሚለው «. . . ለጌታ እንደምትገዙ . . . ቤተ ክርስቲያን ለክርስቶስ እንደምትገዛ» የሚል ንፅፅራዊ መግለጫ ተቀምጧል፡፡ ስለዚህ ሚስቶች ለባሎቻቸው ከመገዛታቸው በፊት ለጌታ መገዛት ምን እንደሆነ ሊያውቁ ይገባል፤ ይህ ትዕዛዝ የተፃፈው የአዲሱ ሕይወት ሥርዓት ለገባቸው አማኝ ሴቶች ነውና፡፡ ቤተ ክርስቲያን (የአማኞች ማህበር) ለጌታ የምትገዛው እንዴት ነው? የምትገዛውስ ለምንድነው? ክርስቶስ ስለወደዳት፣ ፍቅሩንም ራሱን የመዐዛ ሽታ የሚሆን መባና መሥዋዕት አድርጐ ለእግዚአብሔር ስላቀረበ፡፡ (5፡2) ስፋቱ ጥልቀቱ ከፍታውና ርዝመቱ ምን ያህል መሆኑ ከመታወቅ በሚያልፍ ፍቅር ቤተ-ክርስቲያንን ስለ ወደደ፡፡ (3፡18-19) በቃሉ አንፅቶ ስለ ቀደሳት፣ ስለሚመግባትና ስለሚንከባከባት (5፡25-26፣ 29-30) በፍቃዷ ወድዳ ትገዛለታለች፡፡ ይህ መገዛት በፍፁም ፈቃደኝነትና በፍቅር ላይ የተመሠረተ ነው እንጂ፣ በኃይልና በግዴታ የተገኘ አይደለም፡፡ ሁላችን የኢየሱስ ክርስቶስ ተከታዮች ለጌታ ለመገዛት ከዚህ የተለየ ምክንያት የለንም፣ ካለንም ጤናማ አይደለም፡፡

ጳውሎስ የሚፅፍላቸው ሚስቶች ለባሎቻቸው በመገዛት ላይ ያሉ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ሆኖም የሚገዙት በባህል ተፅዕኖ፣ በተፈጥሮ ግዴታ ሊቃወሙት የማይችሉት ባላንጣና ሊሰብሩት የማይችሉት ቀንበር አድርገው በመቁጠር ሊሆን ይችላል፡፡ አሁን ግን ሰማይንና ምድርን ሁሉ ሊጠቀልል ያለውን የአዲሱን ሕይወት ሥርዓት በመረዳት ለክርስቶስ በፈቃደኝነት እንደሚገዙ ሁሉ ለባሎቻቸው ይገዙ ዘንድ ይመክራቸዋል፡፡ ይህም አርነት የሚያወጣ እውነት ነው፡፡

[296] ዘፍ 21፡10



For more books www.amharicchristianbooks.com

«መገዛት» በትክክሉ ሲተረጎም ሁሉን «እሺ . . . እሺ» በማለት የሚገለጥ ሳይሆን፣ የውክልና ሥልጣን ለተሰጠው አካል ያየውን ሁሉ በማሳየት ድርሻን የመወጣት ወሳኝ ጉዳይ ነው፡፡ የሥልጣን ሁሉ ምንጭ አንዱ እግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡ እርሱ ደግሞ ሥልጣንን ሁሉ ይዞ እኔ ብቻ ካላስተዳደርኩ የሚል ሳይሆን፣ ሥልጣንን ከተጠያቂነት ጋር በውክልና በመስጠት የሚታወቅ ነው፡፡ ሆኖም ሥልጣን ሲሰጥ አብሮ ረዳት ይሰጣል፡፡ ቢሆንም ባለ ሥልጣኑ የረዳቱን ድምፅ መስማት የማይፈልግ ከሆነ ትልቅ ችግር ውስጥ መግባቱ አይቀርም፡፡ ስለዚህ የረዳት ድርሻ በቀላሉ የሚታይ አይደለም፡፡ ለምሳሌ ባልና ሚስት በአንድ ጉዳይ ሲነጋገሩ፣ ሚስት ባሏ ያልታየውን ወይም ማየት የተሳነውን (blind spot) ለማሳየት ብትጥር፣ ግትርና ተከራካሪ ተደርጋ ልትወሰድ አይገባትም፤ ድርጊቷ ለጋራ ጥቅም ሲባል ድርሻዋን የመወጣት ጉዳይ ነውና፡፡ እንዲያውም ችግር የሚሆነው እያየች ሁሉን በእሺታ ብታልፍ ነው፡፡ በእርግጥ የታያትንና ባሏ ግን ያያቸው ያልመሰላትን ጉዳዮች ሁሉ ካሳየችው በኋላ፣ እኔ ያልኩት ካልሆነ በሚል አምባጓሮ ከመፍጠር መሪነቱን ለእርሱ ብትተው፣ ካሳሰባትም ብትፀልይ መልካም ይሆናል፡፡ በእርግጥ ይህ ጉዳይ እንደምጽፈው ቀላል አይደለም፤ ቢሆንም መርሁ ከዚህ ሊወጣ አይችልም፡፡ ታዲያ ባልም ቢሆን፣ ምንም እንኳ የውክልና ሥልጣን ቢሰጠውም፣ ደካማና ውሱን መሆኑን ሊዘነጋው አይገባም፡፡ ፍፁም ቢሆንማ ረዳት ባላስፈለገው ነበር፡፡ በዚህ ክፍል የባልና ሚስት ግንኙነት የተመሰለው በባሪያና በጌታ ሳይሆን በራስና በአካል ነው፡፡ ራስ የሚለው የግሪክ ቃል መገኛ እና ምንጭ የሚለውን ሃሳብ እንጂ ገዥነትን አያመለክትም፡፡ ከዚህ የተነሳ ክርስቲያናዊ ትዳር የክርስቶስንና የቤተክርስቲያንን አንድነት ማሳያ መድረክ ሆኗል፡፡

መገዛት አንዳንዶች እንደሚያስቡት የማነስና የበታችነት ጉዳይ ሳይሆን፣ በሕይወት ተውኔት ውስጥ በተመደቡበት ስፍራ የተለያየ ገፀ ባህሪ ለብሶ የመተወን ጉዳይ ነው፡፡ እግዚአብሔር በከሃሊነቱ የመደበን ቦታ ላይ ፀንተን ድርሻችንን በሚገባ መጫወት፣ ዘላለማዊ ብድራት እንዳለው ማስተዋል ክብር እንጂ ውርደት አይደለም፡፡ ትዳር የቡድን ሥራ ነው፡፡ በቡድን ውስጥ ዋና እና ተራ የሚባል የለም፤ ሁሉም የራሱ ድርሻ አለውና፡፡ ቡድኑን ለድል የሚያበቃው ከባላጋራው ጋር ያለው ውድድር እንጂ የእርስ በርስ ፉክክር አይደለም፡፡ በአንድ ወቅት ባል ከሚስት እንደሚበልጥ በእርግጠኝነት ይነገር ነበር፡፡ የኋላ የኋላ ግን የሴቶች እኩልነት ታወጀና እኩል ናቸው ተባለ፡፡ ዛሬ ዛሬ ደግሞ፣ በተለይ በምዕራቡ አለም የደረጃው ምደባ ተቀያይጦ፣ መጀመሪያ ሴት፣ ቀጥሎ ሕፃናት፣ ከዚያም የቤት እንስሳት፣ በመጨረሻም ወንድ እስኪመስል ድረስ የሴቶች የበላይነት ገኗል፤ ሆኖም ክርስቶሳዊ አይደለም፡፡ በክርስቶስ የሕይወት ሥርዓት ውስጥ ባል ከሚስት



For more books www.amharicchristianbooks.com

አይበልጥም፤ ሚስትም ከባል አትበልጥም፤ ባልና ሚስት እኩልም አይደሉም፡፡ አንዳንዶች ይህን ሲያነቡ «ባል ከሚስት ካልበለጠ፣ ሚስትም ከባል ካልበለጠች ወይም ባልና ሚስት እኩል ካልሆኑ እውነቱ ምንድነው?» ብለው ሊጠይቁ ይችላሉ፡፡ ከላይ ባልና ሚስትን ለማወዳደር የተጠቀምንባቸውን ቃላት ልብ ብለናቸው ከሆነ፣ በሂሳብ ትምህርት ውስጥ «ይበልጣል ፣ ያንሳል እና እኩል ናቸው» በማለት ነገሮችን ለማወዳደር የምንጠቀምባቸው ቃላት ናቸው፡፡ ሆኖም እነዚህን የማወዳደሪያ ቃላት ወይም ምልክቶች ለመጠቀም ሁለት ተወዳዳሪ አካላት ያስፈልጉናል፤ አንድን ነገር ብቻውን ማወዳደር አይቻልምና፡፡ ባልና ሚስት ደግሞ በእግዚአብሔር ሥርዓት ውሰጥ አንድ ናቸው፡፡ አንድ ያደረጋቸውም ተፈጥሮ፣ ማህበራዊ ግዴታ፣ ባህል፣ ወይም የሰዎች ፍልስፍና ሳይሆን ራሱ እግዚአብሔር ነው፡፡[297] ስለዚህ አንድ ብቻውን ስለማይወዳደር ይበልጣል፣ ያንሣል እና እኩል ናቸው የሚሉትን ቃላት መጠቀም አንችልም፡፡ ባልና ሚስት አይተናነሱም፣ አይተካከሉም፣ አይበላለጡምም፤ ነገር ግን አንድ ናቸው፡፡ አንድ ደግሞ ይሞላላል እንጂ አይወዳደርም፡፡ ውድድር ከሌለ ፉክክር የለም፡፡ ይልቅ ሁሉ የየድርሻውን በደስታና በሰላም ይወጣል፡፡

በሌላ በኩል ሚስቶች ለባሎች እንዲገዙ ቢታዘዙም ባሎች ሚስቶችን እንዲገዙ ግን እንዳልታዘዙ እንመለከታለን፡፡ ባሎች የታዘዙት ሚስቶቻቸውን ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ወደደ እንዲወዱ ነው፡፡ ይህም ፍቅር ለመረዳት የሚያስቸግር ወይም ድብቅ አይደለም፡፡ በዚሁ መልዕክት በ 1፡4፣ 3፡14፣ 4፡2,15,16 እና 5:2 ላይ በሚገባ ተዘርዝሯል፡፡ ይህ መውደድ ሚስት ስላማረች፣ ስለ ተዋበች እና ስለ ተመቸች ብቻ የሚሆን ስሜታዊ መውደድ ሣይሆን፣ ባልሆነችበትም ጊዜ አንኳ ወደ መሆን ሊያመጣት በሚችል ራዕይና ለራዕይ በሚከፈል መስዋዕትነት የተሞላ መውደድ ነው፡፡ ይህ ዓይነቱ መለኮታዊ ፍቅር፣ የሌለ የሚመስለው እንዲኖርና የተሰወረው እንዲገለጥ የሚያደርግ ተዓምራታዊ አቅም አለው፡፡ በሁኔታ ላይ ያልተመሠረተ፣ ነገር ግን ከሁኔታ በላይ ሁኔታን የመፍጠር አቅም ያለው ፍቅር፣ በትዳር ውስጥ የማይሠራው ተአምር የለም፡፡ ይህ ፍቅር፣ ሚስት እግዚአብሔር በውስጧ ያስቀመጠው፣ ነገር ግን የተሰወረው መልካምነቷ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተገለጠ እንደሚያድግ ወይን እንድታድግ፣ እንደ ወይራ እንድትለመልም እና እንደ ዘንባባ እንድታፈራ የሚያደርጋት የሰማይ ጠልና የፀሐይ ብርሃን ነው፡፡ ይህም ከክርስቶስ የሚፈልቅ በባልም አማካይነት ወደ ሚስት የሚፈስና የሚያለመልም ንፁህ ወንዝ ነው፡፡ ፍቅር ስሜት ይኑረው እንጂ ስሜት አይደለም፡፡ ፍቅር ውሣኔ

[297] ዘፍ 2፡24; ማቴ 19፡4-5; ኤፌ 5፡31



For more books www.amharicchristianbooks.com

ነው፡፡ ውሣኔነቱም ለሞት ራስን አሳልፎ እስከ መስጠት ይደርሳል፡፡ ሆኖም ይህ መስዋዕትነት ለጊዜው ራስን ማጣት ቢመስልም ውጤቱ ግን ራስን ማብዛትና ራስን በክብር የማግኘት መንገድ ነው፡፡

ጳውሎስ ባሎች እንዲያስተውሉት የፈለገው ዋና ነጥብ፣ ክርስቶስና ቤተ ክርስቲያን በመንፈስ ሕይወት ተሳስረው አንድ እንደሆኑ ሁሉ፣ ባልና ሚስትም በደም ውስጥ በሚገኝ የሥጋ ሕይወት በመተሳሰር አንድ አካል መሆናቸውን ነው፡፡

ይህ በባልና ሚስት መካከል ያለ የሥጋ አንድነት በቃል ቢገባኝም ተግባራዊ ምስጢሩ ግን ተሰውሮብኝ ሳሰላስለው ብዙ ጊዜያት አሳልፌያለሁ፡፡ ነገር ግን እ.ኤ.አ በ 2009 ነሐሴ ወር በዳላስ የምትገኘው የኢትዮጵያ ባፕቲስት ወንጌላውያን ቤተ ክርስቲያን ባዘጋጀችው የባለ ትዳሮች ስብሰባ ላይ፣ የባልና የሚስት አንድነት የሕይወት ትስስር መሆኑን በኤፌ. 5፡25-33 ላይ ተመሥርቼ ሳስተምር፣ አንድ አይን ገላጭ ነገር ተከሰተልኝ፡፡ ነገሩ እንዲህ ነው፤ ለእረፍት ስንወጣ የማውቀው አንድ የሕክምና ባለሙያ የሆነ ሰው ወደ እኔ ቀረበና «ወንድም ያሬድ አሁን የተናገርከው የባልና ሚስት የሥጋ አንድነት ከሕይወት ጋር የተሳሰረ መሆኑ በሳይንስ የተደገፈ እንደሆነ ታውቃለህ?» በማለት ንግግሩን ጀመረ፡፡ እኔም «አዎን ባልና ሚስት አንድ አካል መሆናቸውን፣ ይህም አንድነት በግብረ ሥጋ ግንኙነት የሚፈጠር እንደሆነ በቃል ደረጃ አውቀዋለሁ፣ ነገር ግን የዚህ የአካላዊ አንድነት ውስጣዊ ምሥጢር ምን እንደሆነ አልተረዳሁም፡፡» አልኩት አዲስ ነገር ለመማር በሚጓጓ ስሜት፡፡ እርሱም ንግግሩን ቀጠለ፤ እኔም ሁለንተናዬ ጆሮ ሆኖ እስማው ዘንድ ያዝኩ፡፡ «እዚሁ አሜሪካ ውስጥ የሕክምና ትምህርት ስፔሻላይዜሽን ስሰራ አንድ ቀን ፕሮፌሰራችን በወሲብ ግንኙነት ወቅት በወንዱና በሴቷ መካከል እጅግ በጣም አነስተኛ በሆነ መጠን (በማይክሮ ሌቭል) የደምና የፈሳሽ ዝውውር እንደሚካሄድ በምስል አስደግፎ አስረዳን፡፡ ስለዚህ የሕይወት ትስስሩ ከደም ጋር የተያያዘ ነው» አለኝ፡፡ በመጀመሪያ የሰማሁትን ማመን አልቻልኩም ነበር፡፡ ስለዚህ አንድ ሁለት ጥያቄዎችን ሰነዘርኩ፡፡ እርሱም ከፈገግታ ጋር በቂ መልሶችን ሰጠኝ፡፡

ያኔ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ዘር ከመተካትና ስሜት ከማርካት ባሻገር፣ በአይን የማይታይ፣ ነገር ግን በሁለቱ መሃል አንድ አካል የሚያደርግድ የሕይወት መካፈል እንደሚፈጥር ለመጀመሪያ ጊዜ አስተዋልሁ፡፡ የሥጋ ሕይወት በደም ውስጥ ነውና ደም ከእርሱ ወደርሷ፣ ከእርስዋም ወደርሱ በመዘዋወሩ፣ እሱ በእሷ ውስጥ፣ እሷም በእሱ ውስጥ በመሆን አንድ ሥጋ ይሆናሉ፡፡[298] ለዚህ አይደል በደም ብቻ

[298] ዘሌ. 17፡11



For more books www.amharicchristianbooks.com

የሚተላለፉ የተለያዩ ቫይረሶች በግብረ *ሥጋ* ግንኙነት አማካይነት በዋነኝነት የሚተላለፉት?

ምንም እንኳ ይህ አባባል በቅድመ-ዘመናዊ የሕክምና ሳይንስ ሙሉ በሙሉ ያልተረጋገጠና ገና በክርክር ላይ ያለ ቢሆንም፣ በሚደግፉት ባለሙያዎች ዘንድ የሚቀርቡት ነጥቦች እውነትነቱን የማሳመን አቅማቸው ሚዛን የሚደፉ ነው፡፡ እውነቱ ይህ ከሆነ ደግሞ በተራክቦ ወቅት በሚካፈሉት የሥጋ ሕይወት እሱ በሷ፣ እሷም በእሱ ውስጥ በመሆን አንድ አካል ብሎም አንድ ሰው መሆናቸውን እርግጠኛ መሆን ይቻላል፡፡ ለዚህ አይደል ጳውሎስ «የገዛ ሚስቱን የሚወድ ራሱን ይወዳል . . . ፡፡» የሚለን? ባል ሚስቱን ሲወድ፣ የአቶ እገሌንና የወ/ሮ እገሊትን ልጅ፣ የማሙሽንና የሚሚን እናት እንደ ወደደ ሊያስብ ይችል ይሆናል፡፡ ይህ ሁሉ ሐቅ ቢሆንም እውነቱ ግን የወደደው ሌላ ሰው ሳይሆን ራሱን መሆኑን ላይገነዘብ ይችላል፡፡ ሚስቱም ለባሏ ስትገዛ ለራሷ መገዛቷን ረስታ ለሌላ ሰው እንደምትገዛ ልታስብ ትችላለች፡፡ እውነቱ ግን አንድ አካል በመሆናቸው እሷ እሱ፣ እሱም እሷን መሆኑ ነው፡፡ ይህም ከቅዱሳት መጽሐፍት አስተምህሮ ጋር ይስማማል፡ -

> *"እግዚአብሔር አዳምን በፈጠረ ቀን በእግዚአብሔር ምሣሌ አደረገው ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው፣ ባረካቸውም፡፡ ስማቸውንም በፈጠረበት ቀን አዳም ብሎ ጠራቸው፡፡" ዘፍ. 5፡2*

ስለዚህ እሷ የሥጋህ ቅጥያና ብዜትህ ናት፣ አካልህ ናት፣ አንተነትህን የተካፈለች ሙላትህ ናት፡፡ ስለዚህ ለገዛ *ሥጋህ* እንደምታደርገው ልታደርግላት ይገባል፡፡ *ሥጋህ* የቱንም ያህል ደካማ ነው ብለህ ብታስብ ልትጠላውና ልትጥለው እንደማትችል ሁሉ ሚስትህንም ልትጠላትም ሆነ ልትጥላት አይገባም፡፡ ባጠቃላይ የክፍሉ መልዕክት ለገዛ *ሥጋህ* የምታደርገውን ለሚስትህ አድርግ የሚል ነው፡፡ ያኔ እድፈትና የፊት መጨማደድ የሌለባት፣ ቅድስትና ያለ ነውር ሆና በክብር ወደ አንተ ትቀርባለች፡፡ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን የወደደው እንዲህ ነው፡፡

ክርስቲያን ባሎች ሚስቶቻቸውን ሊወዷቸው ብቻ ሣይሆን ሊያከብሯቸውም ይገባል፡፡ ምክንያቱም የሥጋን ሕይወት በመካፈል አንድ አካል ከመሆናቸው ባሻገር፣ በመንፈስ አንድ ሕይወት በመካፈል በእግዚአብሔር መንፈስ ለዘላለም አንድ ሆነዋል፡፡ ይህንንም ጴጥሮስ በመልዕክቱ እንዲህ በማለት ይገልፀዋል፤ *"እንዲሁም እናንተም ባሎች ሆይ . . . . አብረው ደግሞ የሕይወትን ፀጋ እንደሚወርሱ አድርጋችሁ አክብሯቸው፡"* ፩ ጴጥ 3፡7 ይህ ሃሳብ ከዚህ መፅሐፍ ርዕስ ጋር የሚዛመድ ግዙፍ ሃሳብ ነው፡፡ አብረን የምንወርሰው *ሥፍራን* ሳይሆን በፀጋ የተሰጠ ሕይወትን እንደሆነ ይናገራልና፡፡



For more books www.amharicchristianbooks.com

## ወላጆችና ልጆች

ትውልድ እንደ ዱላ ቅብብል ሩጫ ነው፡፡ አንዱ የተመደበለትን ዘመን ሮጦ ሲጨርስ የትውልድን አደራ ለተተኪው አስረክቦ ይሄዳል፡፡ ቀጣዩም ተቀብሎ ድርሻውን ይሮጣል፡፡ ታዲያ ቅብብሎሹ የሰመረ እንዲሆን ብዙ ጥንቃቄ ያስፈልገዋል፡፡ ተገቢው ጥንቃቄ ሳይደረግ ቀርቶ በቅብብሉ መሃል ዱላው ከወደቀ ሽንፈቱ የአንድ ወገን ሳይሆን የቡድን፣ ኪሳራውም የትውልድና የታሪክ ይሆናል፡፡

የኤፌሶን መልዕክት በተጻፈበት በአንደኛው ክፍለ ዘመን ይቅርና ከብዙ ዘመናት ባሻገር ርቀን በምንኖርበት በሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን እንኳ ለልጆች ተገቢውን ፍቅርና አክብሮት መስጠት እምብዛም የተለመደ አይደለም፡፡ "ነገርን ከሥሩ" እንዲሉ ሕዝብና ትውልድ ሊገራና ሊገነባ የሚገባው ገና በለጋነቱ ነው፡፡ ይህ ደግሞ እንደ ቤተሰብም ሆነ እንደ ሃገር ለልጆች ትልቅ ትኩረት እንድንሰጥ ያነቃናል፡፡

ጳውሎስ በመቀጠል ልጆች ለወላጆቻቸው በጌታ እንዲታዘዙ ይፅፋል፡፡ በዘመኑ የግሪክ እና የሮማውያን የፍልስፍና ጽሑፎች እንደ ተለመደው ትዕዛዝ የሚሰጠው ለልጆች ብቻ ሣይሆን ለወላጆች፣ ይልቁኑም ለአባቶች ጭምር ነው፡፡ ጤናማ ቤተሰብ የጤናማ ሕብረተሰብ መሠረት እንደመሆኑ መጠን በሁለቱ ማለትም በወላጆችና በልጆች መካከል ጤናማና ገንቢ ግንኙነት መኖሩ ለቤተክርስቲያንም ሆነ ለማሕበረሰብ ትልቅ ሚና አለው፡፡

ልጆች ለወላጆቻቸው መታዘዛቸው ተፈጥሮአዊ ግዴታ ቢሆንም፣ ጳውሎስ ግን “በጌታ ታዘዙ” በማለት ይህንን ከተፈጥሮ ባሻገር ለክርስቶስ ካላቸው አክብሮታዊ ፍርሃት የተነሳ እንዲያደረጉት ይመክራል፡፡ ለዚህም ሦስት ምክንያቶችን ያቀርባል፡፡

1. ***“የሚገባ ነውና”***

በዓለማችን ጨካኝ የተባሉ ሰዎች እንኳ ለልጆቻቸው በፍቅር ያስባሉ፡፡ «ዩሮ ኒውስ» የተሰኘው የአውሮፓ የቴሌቪዥን ስርጭት “ኖ ኮሜንት!” «ምንም አስተያየት አንሰጥም!» በተሰኘው መደቡ፣ አንድ በግለሰብ የተቀረፀ (አማተር) የቪዲዮ ፊልም ለዕይታ አብቅቶ ነበር፡፡ ፊልሙ ለ42 ዓመታት ሊቢያን በብረት በትር ሲገዟት የኖሩትና በቅርቡ በውርደት የሞቱት የቀድሞው የሊቢያ መሪ ሙአመር ጋዳፊን የሚያሳይ ነው፡፡ ሰውየው የስፖርት ቱታ ለብሰው በድንኳን ውስጥ ከልጅ ልጆቻቸው ጋር ሲጫወቱ ያሳያል፡፡ እጅግ ጨካኝ እንደሆኑ የሚነገርላቸው ሰው፣ ከልጅ ልጆቻቸው ጋር በልዩ እንክብካቤና ፍቅር ሲጫወቱ



For more books www.amharicchristianbooks.com

ማየት ትኩረትን የሚስብ ነበር፡፡ ይህም ወላጆች ለሌላው ክፉ ቢሆኑ እንኳ በተፈጥሮ ለልጆቻቸው መልካም እንደሚያስቡ ያሳያል፡፡ ስለዚህ ለወላጆች መታዘዝ የሚገባና የሚጠቅም ነው፡፡ ወላጆች ትዕዛዛቸው ብቻ ሣይሆን ቅጣታቸው እንኳ ለጥቅማችን እንደሆነ መጽሐፍ ሲናገር “እነርሱ መልካም ሆኖ እንደታያቸው ለጥቂት ቀን ይቀጡን ነበር . . . . “ ዕብ 12፡9-10 ይላል፡፡ እግዚአብሔር ወላጆች ባሉበት ቤት ውስጥ ልጆች እንዲወለዱ ያደረገው እርሱን የሚፈራ ዘር እንዲወጣ ስለሚፈልግ ነው፡፡[299] ይህም የሚሆነው ልጆች በልብ ፈቃድ ለወላጆቻቸው ሲታዘዙ ነው፡፡ ለዚህ ነው ጳውሎስ “ይህ የሚገባ ነውና” የሚለው፡፡

## 2. ፊተኛ ነውና

ጳውሎስ ይህን ክፍል የጠቀሰው ከዘፀ 20፡ 12 ላይ ከሰፈሩት አሥርቱ ትዕዛዛት አንዱን በመውሰድ ለመሆኑ ምንም ጥርጥር የለውም፡፡ ጳውሎስ ከአሥርቱ ትዕዘዛት መሃል የወሰደውን ይህን ሐረግ “ፊተኛ” ብሎታል፡፡ ከአሥርቱ ትዕዛዛት መካከል ላይ ተቀምጦ እንዴት ፊተኛ ወይም አንደኛ ሊሆን ይችላል? ብለን ልንጠይቅ እንችላለን፡፡ በተለያዩ ጽላት (ድንጋይ) ላይ የተፃፉት አሥርቱ ትዕዛዛት በሁለት የተከፈሉ ናቸው፡፡ የተከፈሉትም ከ1 እስከ 4 እና ከ5 እስከ 10 ነው፡፡ የመጀመሪያው ክፍል፣ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ግንኙነት የሚያሳይ ሲሆን፣ ሁለተኛው ክፍል ደግሞ ሰው ከሰው ጋር ያለውን ግንኙነት ያመለክታል፡፡ ስለዚህ ጳውሎስ አንደኛ ወይም ፊተኛ ትዕዛዝ ያለው ከአንደኛው ጽላት በመነሳት ቆጥሮት ሳይሆን የሁለተኛው ክፍል የመጀመሪያ ትዕዛዝ የሆነውን «አባትህንና እናትህን አክብር . . . » የሚለውን ሥርዓትና ፍርድ በመውሰድ ነው፡፡

ጳውሎስ ይህን መልዕክት የሚጽፍላቸው አማኞች በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉ የአዲስ ኪዳን አማኞች ሆነው ሳሉ ስለምን ሕግን ይጠቅስላቸዋል? ሊባል ይችል ይሆናል፡፡ ነገር ግን በእውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት ስንመላለስ፣ የሕግ ትዕዛዝ በብቃት ይፈፀማል እንጂ አይሻርም፡፡ ይህንንም ጳውሎስ በሌሎች ክፍሎች ከጻፋቸው መልዕክቶች መረዳት እንችላለን፡፡[300]

## 3. የተሰፋ ቃል ያላት ትዕዛዝ ስለሆነች

ሕግ በመደረግ የሚፈፀም ትዕዛዝ እንጂ የተሰፋ ቃል አይደለም፡፡ በሕግ ውስጥ

---

[299] ት.ሚል 2፡15 አዲሱ መደበኛ ትርጉም

[300] ሮሜ 3፡31; 8፡4



For more books www.amharicchristianbooks.com

ትዕዛዝ እንጂ የተስፋ ቃል የለም፡፡ ነገር ግን በሙሴ አማካይነት ለእስራኤል ልጆች ከተሰጡት ወደ 613 የሚጠጉ ትዕዛዛት መካከል፣ የተስፋ ቃል ካላቸው ጥቂቶች አንዱ፣ *"እናትህንና አባትህን አክብር"* የሚለው ነው፡፡ እግዚአብሔር ለዚህ ትዕዛዝ ትልቅ ትኩረት ከመስጠቱ የተነሳ *«እግዚአብሔር አምላክህ በሚሰጥህ ምድር ላይ ዕድሜህ እንዲረዝም መልካምም እንዲሆንልህ . . . »* የሚል ቀስቃሽና አጓጊ ተስፋ ሰጥቶታል፡፡

በእርግጥ ቃሉ በመጀመሪያ የተፃፈበት ዘፀአት 20ን ወይም ዘዳግም 5ን ስናነብ *"እግዚአብሔር አምላክህ <u>በሚሰጥህ ምድር</u> እድሜህ እንዲረዝም . . . "* የሚል ቃል እናገኛለን፡፡ ጳውሎስ ግን እግዚአብሔር አምላክ በሚሰጥህ ምድር የሚለውን አውጥቶታል፡፡ ለምን ይሆን? ሙሴ እግዚአብሔር አምላክ በሚሰጥህ ምድር የሚለው የተስፋይቱ ምድር የሆነችውን ከነዓንን ነው፡፡ የእግዚአብሔርና የሕዝቡ ርስት በመባል የምትታወቀው ይህች ምድር ምሳሌ እንደ ነበረች፣ አሁን ግን ምሣሌው በእውነተኛ አካል እንደ ተተካ፣ የተስፋው ርስት አብና ወልድ የሚኖሩበት፣ እኛም በአብና በወልድ የምንኖርበት የተስፋው መንፈስ፣ መንፈስ ቅዱስ እንደሆነ ተመልክተናል፡፡ ስለዚህ ጳውሎስ ከነዓንን መጥቀስ ያልፈለገ ይመስላል፤ ነገር ግን የዕድሜ መርዘም በ70 እና በ80 ወይም በ100 እና በ120 የሚለካው ሳይሆን፣ የዘላለም መሆኑን ለማሳየት በክርስቶስ ከተገለጠው ሕይወት ጋር አያይዞ ለመግለፅ የፈለገ ይመስላል፡፡ ይህንን መንፈሳዊ ትርጓሜ ብንተወውና ፊት ለፊት የሰፈረውን ብቻ እንኳ ብንወስድ በምድር ላይ በሰላምና በጤና ረዥም እድሜ መኖር በራሱ ትልቅ በረከት ነው፡፡ ይህም የሚገኘው በክርስቶስ ሆኖ እናትና አባትን በማክበር መሆኑን ያስተምረናል፡፡ በወጣትነት ይልቁኑም ልጆች ሁሉን የሚያውቁና ሁሉን የሚችሉ በሚመስላቸው በአሥራዎቹ የዕድሜ ክልሎች ለወላጆች መታዘዝ አስቸጋሪ ቢሆንም፣ ጥርስ ነክሶ መታዘዝ እንደሚበጅ ለክርስቲያን ወጣቶች ዓይነተኛ ማሳሰቢያ ይሰጣል፡፡

በባሕላችን ወጣትነትን ከጉርምስና፣ ከጥጋብና ከአስቸጋሪነት ጋር አያይዞ ማሰብ የተለመደ ጉዳይ ነው፡፡ ነገር ግን ወጣቶች አስቸጋሪ ሳይሆኑ ችግረኛ መሆናቸውን የሚረዱ፣ በውጭ የሚታየው ነውጥ፣ በውስጣቸው ከሚካሄደው ለውጥ እንደሆነ የሚገነዘቡ ጥቂቶች ናቸው፡፡ እንዲህ አይነት የባሕሪ ለውጦች የሚከሰቱት ወጣቶቹ ስለፈለጉ ብቻ ሳይሆን ከአዳጊ እድሜያቸው የተነሳ በውስጣቸው ከሚመነጨው ንጥረ ነገር (ሆርሞን) መሆኑን ተፈጥር ራሱ ያስተምረናል፡፡ ሰውን ካልተረዳነው በቀር ልንረዳው አንችልም፡፡ ወላጆችም በልጆች የባሕሪ ለውጥ ለመፍረድ ከመነሳታቸው በፊት ምንጬን ለመረዳት ቅድሚያ እንዲሰጡ ይህ ክፍል



For more books www.amharicchristianbooks.com

ያሳስባል፡፡ ማንም ወላጅ ልጁ እንዲያድግ ይመኛል፣ ይፀልያል፡፡ ነገር ግን ዕድገት ሂደት እንጂ ቅፅበታዊ ክስተት አይደለም፡፡ በሂደቱም አብረውት የሚመጡና በየፈርጁ የሚገለጡ በርካታ ነገሮች አሉት፡፡ እነዚህም የለውጥ ውጤቶች በፍቅር የሚያቀናቸው እንጂ የሚኮንናቸው አይፈልጉም፡፡ ሕፃኑን ከእጣቢው ውሃ ጋር ከመድፋት እግዚአብሔር ይጠብቀን!

እናትና አባትን ማክበር ልጆች በወላጅ ቁጥጥር ሥር ባሉበት የዕድሜ ክልል ብቻ የሚያከትም ሳይሆን፣ ወላጆች በሕይወት ባሉበት ዘመን ሁሉ የሚቀጥል ነው፡፡ በማቴዎስ ወንጌል፣ ጌታ ኢየሱስ የፈሪሳውያንን ግብዝነት ገልጦ ለማሳየት በተናገረው ክፍል ውስጥ፣ አዋቂ ሰው ወላጆቹን አለመጦሩና አለመንከባከቡ ይህን ፊተኛ ትዕዛዝ መሻሩ እንደሆነ ተናግሯል፡፡[301] ስለዚህ ልጆች ሳለን የተባልነውን በማድረግ ብቻ ሣይሆን፣ እኛ አድገን አምራች ስንሆን፣ በምትኩ ወላጆቻችንን አርጅተው ማምረት ሲያቆሙ፣ በሚያስፈልጋቸው ሁሉ በመርዳትና በመንከባከብ ይህን ትዕዛዝ ልንፈፅምና የተስፋውን ቃል ልንወርስ ይገባል፡፡ በልጅነታችንም ሆነ በጎልማሳነታችን አባትና እናታችንን ስናከብር ከእኛና ከወላጆቻችን ባሻገር ማህበረሰብም ሆነ አገር ያርፋል፡፡ ምክንያቱም ለወላጆቻቸው ባለመታዘዝ ከቤት ወጥተው ጐዳና የሚኖሩ ሕፃናት እና የሚጦሯቸው አጥተው በመንገድ የሚወድቁ አረጋውያን ቁጥራቸው ይቀንሳል፡፡

ጳውሎስ በምላሹ ወላጆች በተለይም አባቶች፣ ለልጆቻቸው ይልቁኑም ለቀሪው የሕይወት ዘመናቸው፣ በተለይም አዕምሮአቸው በሚቀረፅበት የልጅነታቸው ወራት ሊያደርጉላቸው ስለሚገባ ነገር ትዕዛዝ ሲሰጥ፡-

*"እናንተም አባቶች ሆይ ልጆቻችሁን በጌታ ምክርና በተግሳፅ አሳድጉአቸው እንጂ አታስቆጧቸው፡፡"* ይላል፡፡

በዘመናችን በትዳር ውስጥ ከሚነሱና ትዳርን አደጋ ላይ ከሚጥሉ ርዕሰ ጉዳዮች አንዱ ከልጆች ጋር የተያያዙ የባልና ሚስት ግጭቶች ናቸው፡፡ እናቶች ተፈጥሯቸው ሩህሩህና የልጆቻቸውን ገመና የሚደብቅ ስለሆነ አንዳች ችግር ሲፈጠር ባብዛኛው ቁጣ የሚበረታው በአባቶች ዘንድ ነው፡፡ ቁጣውም በልጆች ላይ ብቻ ሳይሆን "ልጆቹን አበላሸሻቸው" በሚል በሚስትም ላይ ይሆናል፡፡ በሚያሳዝን መልኩ አባት፣ የልጆቹ እናት እንደርሱ ቆፍጣና እንድትሆን ይፈልጋል፣ በሌላ በኩል ደግሞ እናት የልጆቿ አባት እንደርሷ ሩህሩህ እንዲሆን ትፈልጋለች፡፡ ሆኖም ያልተረዱት እውነት፣ በእናት ውስጥ ርህራሄን፣ በአባት ውስጥ ቆፍጣናነትን

[301] ማቴ 15፡3-6; 1ጢሞ 5፡8



For more books www.amharicchristianbooks.com

አስቀምጦ ልጆችን በተመጣጠነ መንገድ የሚያሳድገው እግዚአብሔር መሆኑን ነው፡፡ ልጆች ለማደግ የሚያስፈልጋቸውን ተመጣጣኝ ነገር የሚያገኙት እናትም አናት፣ አባትም አባት ሲሆን እንጂ ስፍራ ሲለዋወጡ አይደለም፡፡ ስለዚህ ክርስቲያን አባቶችም ሆኑ እናቶች ልጆቻቸውን እንዴት እንደሚያሳድጉ ሊመከሩና ሊማሩ ያስፈልጋቸዋል፡፡

በተለይ የባህልና የአስተሳሰብ ለውጥ በፈጠነበት በዚህ ዘመን፣ የትውልድን ክፍተት ለማጥበብ ወላጆች በተለይም አባቶች ከልጆቻቸው ጋር ለመናበብ ብዙ መስራት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ባለፉት 15 ዓመታት በስፋት በተዘዋወርኩባቸው በርካታ ኢትዮጵያውያን በሚኖሩባቸው ያደጉ ሃገሮች የታዘብኩትና የነገይቱ ቤተክርስቲያን ትልቅ ተግዳሮት ነው ያልኩት ነገር ከዚህ ሃሳብ ጋር ይዛመዳል፡፡ በእነዚህ ሃገሮች ያሉትን የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ቀጣይነት ጥያቄ ውስጥ የሚያስገባ ጉዳይ ከልጆች አስተዳደግ በተለይም በልጆችና በወላጆች መካከል ካለ ጤናማ ግንኙነት ጋር በጽኑ የተገመደ ነው፡፡ እነዚህ በውጭ የሚኖሩ ልጆች በቤት ውስጥ አበሻ፣ በደጅ ደግሞ ፈረንጅ ለመሆን ይገደዳሉ፡፡ በመጨረሻም "አበሻም፣ ፈረንጅም" መሆን ያቅታቸውና ለማንነት ቀውስ ይዳረጋሉ፡፡ ስለዚህ ወላጆች የባዕድን አገር ኑሮ ለመግፋት ካለባቸው ውጥረት ባሻገር የልጆቻቸውንም ጉዳይ ትልቅ ትኩረት ሊሰጡትና ገና ከጠዋቱ ሊሰሩበት ይገባል፡፡  ልጆችን እንደ ፈለጉ ይደጉ ብሎ መተው ኃላፊነትን መጣል ነው፤ በተቃራኒው ከመጠን በላይ ተቆጣጥሮ ማስጨነቅና ማስቆጣትም ምሬትን ማስፋፋት ነው፡፡ ስለዚህ ሚዛኑ ሊጠበቅ ይገባል፡፡ ሚዛኑም ይህ ነው፡፡ “በጌታ ምክርና በተግሣጽ ማሳደግ”፡፡ የምክር ክፍለ ጊዜያችንን በሚገባ ሳንፈፅም ወደ ተግሣፅ ልንዘምት አይገባም፡፡ ተግሣፃችንም ጥበብ የሞላበትና ዓላማው በትዕግሥት የማቅናት መሆን ይኖርበታል፡፡ በጌታ ምክርና በተግሣፅ ማሳደግ ማለት ጌታ እኛን በመንፈሳዊ ሕይወት ለማሳደግ የሚጠቀምባቸውን ስልቶች እኛም ልጆቻችን ላይ መተግበር ማለት ነው፡፡ እኛ ስንት ጊዜ አጥፍተናል? ስንት ጊዜስ ጌታን አሳዝነናል? ነገር ግን ባጠፉን ቁጥር ጌታ ቢጮህብንና በትር ቢያነሳ ኖሮ በጠፋን ነበር፡፡ እሱ ግን ትዕግሥቱ ብዙ ነው፡፡ እያጠፋን እንኳ በለሆሳስ ድምፅ በፍቅር ይመክረናል፣ ያስተምረናል፡፡ ነገር ግን እልከኞች ስንሆንና የያዝነው መንገድ የሚያጠፋን ሲሆን በሚገባን መንገድ ይገሥፀናል፡፡ እኛም ወላጆች ለልጆቻችን እንድናደርግ የታዘዝነው ይህንኑ ነው፡፡

ልጆች በተፈጥሮአቸው ክፉዎች አይደሉም፡፡ ነገር ግን ፍሬያማ ይሆኑ ዘንድ እንደ መልካም እርሻ መታረምና መኮትኮት ይፈልጋሉ፡፡ የሚያስፈልጋቸውም ጊዜ ሰጥቶ፣



For more books www.amharicchristianbooks.com

ዝንባሌያቸውን አጢኖ፣ መምከር፣ ማሠልጠን፣ ማበረታታትና ምሣሌ መሆን፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ደግሞ በቃል መገሠፅና፣ ሊገባቸው በሚችል መንገድ በአግባቡ መቅጣት ከቀጡም በኋላ ወደ እቅፍ አስጠግቶ ፍቅርን መግለፅ ነው፡፡

## ጌቶችና ባሮች (አሥሪና ሠራተኛ)

የመጀመሪያው ክፍለ ዘመን የባርያ ንግድ የጦፈበት ዘመን ነበር፡፡ በዕዳ፣ በጦር ምርኮኝነትና በዘር ወደ ባርነት የሚገቡ ሴቶችና ወንዶች ቁጥር የትየለሌ ነበር፡፡ በያኔው ዓለም ነፃ፣ ጨዋ፣ ጌታ ተብለው ከሚጠሩ ሰዎች ይልቅ የባሮች ቁጥር ብዙ ዕጥፍ ይበልጥ ነበር፡፡ የዓለም ሕዝበ ቁጥር እንደዛሬው ሳይጨምር፣ በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን በሮም ግዛት የሚኖሩት 80,000,000 /ሰማንያ ሚሊዮን/ ሕዝብ እንደነበሩና ከዚያም መሐል 60,000,000 /ስልሳ ሚሊዩን/ የሚጠጉት ባሮች እንደነበሩ አስቀድመን አይተናል፡፡ ጊዜው ባርያን መግዛት፣ መሸጥ፣ መለወጥ፣ መቅጣትና መግደል በጌታው ላይ የሕሊና ወቀሳ ወይም ተጠያቂነት የማያመጣበት፣ በባሪያ ላይ የሚደርስ ማንኛውም ግፍ በሕግ መብት ያገኘበት ዘመን ነበር፡፡ ባርያ ከጌታው ሲኮበልል ቢያዝ፣ ምንም ዕቃ ባይሰርቅ እንኳ ራሱን እንደሰረቀ ተቆጥሮ ሊገረፍ፣ ሊታሰር ወይም ሊገደል ይችላል፡፡

አንድ ጌታ እንደ ሃብቱ መጠን ቁጥራቸው በርከት ያሉ በተለያየ ሥራ ላይ የተሰማሩ ባሮች ሊኖሩት ይችላሉ፡፡ ሥራቸውም የጉልበት ብቻ ሣይሆን የንግድ፣ የማስተማር ወይም የተለያየ ሙያ ሊሆን ይችላል፡፡ ሆኖም ባሮች እነዚህን ሥራዎች የሚያከናውኑት እንደ ዘመናችን በተለየ የሥራ ቦታ ሣይሆን፣ በጌታቸው ቤት አብሮ በመኖር ስለሆነ ባርነት ከሥራነቱ ባሻገር የቤተሰብነትም ጉዳይ ነበር፡፡[302]

በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን አጋማሽ በጳውሎስና ለወንጌል ሥራ አብረውት በተጠመዱ አገልጋዮች አማካይነት የእግዚአብሔር መንግሥት በዓለም በታወጀ፣ ጊዜ የእምነት ምላሽ የሰጡት ጌቶች ብቻ ሣይሆኑ በርካታ ባሮችም እንደ ነበሩ ከመጽሐፍ ቅዱስም ሆነ ከታሪክ እንረዳለን፡፡ ሁሉም አንዱን ጌታ በመቀበል በአንድም መንፈስ በመሞላት የአዲሱ ሰው ዘር አካል ሆነዋል፡፡ ለዚህ ነው ጳውሎስ ለባሎች፣ ለሚስቶች እና ለልጆች ትዕዛዝ እንደፃፈ ሁሉ ለባሮችም ሊኖራቸው ስለ ሚገባ ክርስቲያናዊ ግብረገብ የሚፅፍላቸው፡፡ የክርስቶስ ወንጌል በጌቶችና በባሮች ግንኙነት ላይ ምን ያህል ተጽዕኖ እንዳመጣ ለመረዳት፣ ጳውሎስ

302 በአዲስ ኪዳን መጻህፍት ውስጥ ባሮች በጌታቸው ስም ተጠርተው የእገሌ ወይም የእገሊት ቤተሰብ የተባሉባቸው በርካታ ስፍራዎች ያሉ ሲሆን እነዚህን ክፍሎች እንደ ምሳሌ ልንወስዳቸው እንችላለን፡፡ 1ቆሮ 1፡11; 16፡15; ሮሜ 16፡11፣12



For more books www.amharicchristianbooks.com

በቈላስይስ ቤተክርስቲያን አገልጋይ ለሆነው፣ ብዙ ባሪያዎች ለነበሩት ፊሊሞና ስለ ባሪያው አናሲሞስ የፃፈውን መልዕክት መመልከት በቂ ይሆናል፡፡[303]

በእርግጥ በኖርንባቸውና ባቅራቢያችን በነበሩ ዘመናት "ባሪያ" ሲባል ከቀለም ጋር ብቻ ተሳስሮ ጥቁር ሰው እንደሚታሰብ የታወቀ ነው፡፡ ይህ አባዜ እስካሁን ያልለቀቃቸው እንደሚኖሩም ሳይታለም የተፈታ ነው፡፡ ሆኖም መጽሐፍ ቅዱስ ባሪያ ሲል ነጭም ሆነ ጥቁር ወይም ቢጫ የተወለደበትን ቤተሰብ፣ ያለበትን የኢኮኖሚ ሁኔታ ወይም በዕዳ የተዘፈቀበትን የኑሮ አይነት የሚያሳይ እንጂ በዋነኝነት ከቀለም ጋር የተያያዘ አለመሆኑን መገንዘብ ይጠቅማል፡፡

ጳውሎስ ለባሮችና ለጌቶች የጻፈውን ይህንን ክፍል (6፡5-9) ስናነብ፣ መልዕክቱ ምን ያህል በክርስቶስ እንደ ተሞላና ክርስቶስ ተኮር እንደሆነ መመልከት እንችላለን፡፡ ለባሮች ስለ ጌቶቻቸው ሲጽፍላቸው “ምድራዊ ጌቶቻችሁ” “በሥጋ ጌቶቻችሁ” የሚሉትን ሐረጋት ተጠቅሟል፡፡ ይህንንም የሚያደርገው እነዚህ ባሮች በወንጌል በማመናቸውና አዲስ ፍጥረት በመሆናቸው ምክንያት ከሰው ባርነት ነፃ ወጥተው ወደ ሰማያዊ ጌታና ወደ መንፈሳዊ ጌታ መሸጋገራቸውን ለማሳየት ነው፡፡ ስለዚህ «የክርስቶስ ባሪያዎች» በሚል የማዕረግ ስም ይጠራቸዋል፡፡ ጳውሎስ ነፃ ሰውና ሮማዊ ሆኖ ሳለ ዘወትር በመልዕክቶቹ መግቢያ ላይ ራሱን የሚጠራው “የክርስቶስ ባሪያ” በማለት ነው፡፡ ይህንኑ መጠሪያ ለባሮች ሲጠቀም እናያለን፡፡ ክርስቲያን ባሮች በጌታ በመሆናቸው ምክንያት ስማቸው አልተቀየረም፣ በማህበራዊ መዋቅር ውሰጥ ያላቸው ስፍራ አልተለወጠም፤ ነገር ግን ውስጣቸው ተቀይሯል፤ አመለካከታቸው ታድሷል፡፡ ጳውሎስም ከሁሉ በላይ የሚያሳስበው ይህ የልብ ነፃነት ነው፡፡ ቀድሞ እንደሚያደርጉት ጌቶቻቸውን በልባቸው እየናቁ፣ እየጠሉ፣ በሥራቸው እየለገሙ፣ ጌቶቻቸው ብቅ ሲሉ ብቻ ለታይታና ለይስሙላ የግብር ይውጣ ተፍ ተፍ እያሉ፣ ከአይናቸው ዞር ሲሉ ግን እያላገጡ ይፈፅሙት የነበረውን ስንፍና ወደ ኋላ እንዲጥሉና፣ በጌቶቻቸው ውስጥ የክርስቶስን ጌትነት እያዩና ለጌትነቱም ክብር እየሰጡ በአክብሮት፣ በፍርሃትና በልብ ቅንነት እንዲታዘዙ ያመለክታቸዋል፡፡ ክርስቲያን ባሮች በአመለካከታቸው ከሥጋ ባርነት ነፃ ወጥተው የክርስቶስ ባሮች እንደሆኑና ሥጋዊ ለሆኑ ጌቶቻቸው የሚታዘዙት በሥጋ ባርነት መንፈስ ሳይሆን የክርስቶስ ባርያዎች መሆናቸውን በማመንና በማወቅ እንዲሆን ያመለክታቸዋል፡፡

303 ይህንን ርዕሰ ጉዳይ በጥልቀት ለመረዳት አንድ ምዕራፍ በቻ የሆነውን የፊሊሞናን መልዕክት ማጥናት ይጠቅማል፡፡



For more books www.amharicchristianbooks.com

ባርነት የአስተሳሰብ ባርነት ጭምር እንጂ አካላዊ ብቻ አይደለም፡፡ በአካል ነፃ ወጥተው በአስተሳሰብ ባርነት የሚኖሩ ብዙዎች ናቸው፡፡ ስለዚህ *«የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንደሚያደርጉ እንደ ክርስቶስ ባሪያዎች እንጂ ለሰው ደስ እንደምታሰኙ ለታይታ የምትገዙ አትሁኑ፡፡»* በማለት ይመክራቸዋል፡፡

ማንም ሰው ለሚሰራው *ሥራ* ይነስም ይብዛ፣ ይመጥንም አይመጥን ደሞዝ ማግኘቱ አይቀርም፡፡ ደሞዝ መክፈል የአሠሪ ድርሻና ግዴታ ነው፡፡ እነዚህ ባሮች ደሞዝ የሚጠብቁት ከጌቶቻቸው ብቻ ነበር፡፡ አሁን የጌትነት ለውጥ ተካሂዷል፡፡ ጌታ ሲለወጥ ደሞዝ ከፋይም መለወጡ የግድ ነው፡፡ ምንም እንኳ አሁንም ከጌቶቻቸው ምድራዊ ምንዳ የሚቀበሉ ቢሆንም፣ ካዳናቸው ሰማያዊ ጌታ ዘንድ ዘላለማዊ ደሞዝ እንደሚጠብቃቸው ተጽፎላቸዋል፡፡ ደሞዝ የሚያገኙትም ባሪያዎች ብቻ ሳይሆኑ የኢየሱስ ክርስቶስን ጌትነት ተረድተው በመልካም ያስተዳደሩ ጌቶች ጭምር መሆናቸውን *«ባሪያ ቢሆን ወይም ጨዋ ሰው፣ እያንዳንዱ የሚያደርገውን መልካም ነገር ሁሉ ከጌታ በብድራት እንዲቀበለው ታውቃላችሁና፡፡»* በማለት ይገልፃል፡፡ ባሪያዎች በማመን ነፃ እንደ ሆኑ ሁሉ ጨዋዎቹም በማመን ባሪያዎች፤ አዎን ባሪያዎቹም የክርስቶስ ነፃ፣ ጨዋዎቹም የክርስቶስ ባሪያ ሆነዋል፡፡ ሽልማቱም ምን እንደሆነ በቆላስያስ መልዕክት (ቆላ. 3፡22-4፡1) በግልፅ ተቀምጧል፡፡

*"የምታደርጉትን ሁሉ ለሰው ሳይሆን ለጌታ እንደምታደርጉት ቆጥራችሁ ከልባችሁ አድርጉት፣ <u>ከጌታ ዘንድ እንደ ብድራት የምትቀበሉት ርስት</u> እንዳለ ታውቃላችሁና"* ቆላ. 3፡22፣24 አ.መ.ት (አፅንዖት ከራሴ)

ይህ ርስት በ1፡12,13,18; 3:6; 5:5 ላይ የተጠቀሰው አሁን የተሰጠን በዘመን ፍፃሜ በቤዛ ቀን የምንከብርበት በመንፈስ ቅዱስ ነው፡፡ ይህ ርስት እርሱም አንዱ የእግዚአብሔር መንፈስ ክርስቶስንና አማኞችን፣ አይሁድንና አሕዛብን አንድ እንዳደረገ፣ ወደፊትም በሰማይና በምድር ያሉትን አንድ እንደሚያደርግ ሁሉ በዚህ ስፍራ በማሕበራዊ ጉዳይ ውስጥ ገብቶ ጌታና ባሪያንም አንድ እንዳደረገ እንመለከታለን፡፡ ይህንንም ጳውሎስ የአዲሱ ሰው ማንነት በማህበረሰብ ውስጥ ሲገለጥ ምን እንደሚመስል ገልፆ በጻፈበት ክፍል ውስጥ በጉልህ እናየዋለን፡፡

> *"በዚያ (በአዲሱ ሰው) የግሪክ ሰው ወይም አይሁድ፣ የተገረዘ ወይም ያልተገረዘ፣ አረማዊ ወይም እስኩቴስ፣ ባሪያ ወይም ጌታ ብሎ ልዩነት የለም፤ ነገር ግን ክርስቶስ ሁሉም ነው፤ በሁሉም ነው፡፡"* ቆላ. 3፡11

ጳውሎስ በመቀጠል ለክርስቲያን ባሪያ አሳዳሪዎች ወይም ጌቶች ይጽፋል፡፡ በዚህ ስፍራ "እናንተም ጌቶች ሆይ" በማለት የሚጽፍላቸው ቀደም ሲል



For more books www.amharicchristianbooks.com

እንዳየነው “ባሎች ሆይ . . . ” እና “አባቶች ሆይ . . . ” በማለት የጻፈላቸው የቤት አባ ወራዎች ናቸው፡፡ በዘመኑ ልማድ ሚስትን የማስተዳዳር፣ ልጆችን የማሳደግና ባሮችን የመግዛት ኃላፊነት የቤተሰብ አባት (Pater Familia) ተብለው የሚጠሩት የአባ ወራዎች ነበር፡፡ ስለዚህ ከባሪያዎቻቸው ጋር ስለሚኖራቸው ግንኙነት ሲፅፍ ሦስት ዋና ዋና ነገሮችን በማንሳት ያሳስባቸዋል፡፡ አንደኛው *“እናንተም ጌቶች ሆይ . . . እንዲሁ አድርጉላቸው፡፡”* የሚል ነው፡፡ ይህ ቃል ግልፅነት የሚጐድለው ድፍን ትዕዛዝ ይመስላል፡፡ ነገር ግን ባሪያዎች ለጌቶቻቸው ሊያደርጉ የሚገባውን በዝርዝር ስለ ጻፈላቸው፣ ድግግሞሽን ለማስወገድ ሆን ብሎ ያደረገው ሳይሆን አይቀርም፡፡ ባሮች ጌቶቻቸውን በአክብሮት፣ በፍርሃት እና በልብ ቅንነት እንዲታዘዟቸው፣ ይህንንም ክርስቶስን በመመልከት የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማድረግ ካላቸው ተነሳሽነት እንዲያደርጉት ተነግሯቸዋል፡፡ ስለዚህ ጌቶችም በምላሹ ባሮቻቸውን ሊያከብሯቸው፣ በልብ ቅንነት መልካም ሊያደርጉላቸው እንደሚገባ እየተነገራቸው ነው፡፡ ይህ ድርጊት ለዘመኑ ልማድ ባዕድ ቢሆንም፣ በክርስቶስ አዲስ ፍጥረት ለሆኑትና የክርስቶስ ትምህርት ልቦናቸውን ለገዛ ክርስቲያን ጌቶች አስቸጋሪ አልነበረም፡፡

ሁለተኛው ትዕዛዝ «ዛቻውን ትታችሁ» የሚል ነው፡፡ ቀደም ሲል እንዳየነው የባሪያ አሳዳሪዎች በባሪያዎቻቸው ላይ የፈለጉትን እንዲያደርጉ ከሮም መንግሥት ነፃ ፈቃድ ተሰጥቷቸዋል፡፡ ስለዚህ ከባሪያዎቻቸው የሚፈልጉትን ለማግኘት ዋና መሳሪያቸው ዛቻ ነው፤ እገድልሃለሁ፣ እቆርጥሃለሁ፣ እፈልጥሃለሁ... የሚል ማስፈራሪያ፡፡ ሊገድለን እንደማይችል የምናውቀው ሰው «እገድልሃለሁ ብሎ» ቢዝት እምብዛም ላንፈራው እንችል ይሆናል፡፡ ነገር ግን እንዲገድለን ከመንግሥትም፣ ከሕግም፣ ከሕብረተሰብም ሙሉ ሥልጣን እንዳለው የምናውቀው ሰው «ዋ . . . እገድልሃለሁ» ብሎ ከዛተብን ነፍሳችንን ለማዳን በፍርሃት የተባልነውን ሁሉ ከማድረግ አንመለስም፡፡ አሁን ግን ዛቻን ፈፅሞ ለማስፈራሪያነት እንዳይጠቀሙበት እየታዘዙ ነው፡፡ የዚህ ሁሉ ምክንያት በሶስተኛውና በመጨረሻው ትዕዛዝ «የእነሱም የእናንተም ጌታ የሆነው በሰማይ እንዳለ የሰውንም ፊት አይቶ እንደማያዳላ ታውቃላችሁና፡፡» ተብሎ በግልፅ ተቀምጧል፡፡

አ! ወንጌል እንዴት የለውጥ ሃይል ነው?! እነዚህ ጌቶች ሲገቡ ሲወጡ ብድግ እየተባለላቸው፣ በውጭ በውስጥ እጅ እየተነሱና እየተሰገደላቸው የኖሩ ናቸው ፡፡ አሁን ግን ከባሪያዎቻቸው ጋር የሰማይና የምድር ጌታ የሆነው የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያዎች ሆነዋል፡፡ የቀድሞ ባሪያዎቻቸው፣ ወንድሞቻቸውና እህቶቻቸው ሆነዋል፡፡ በክርስቶስ ፍርሃት ጌቶች ለባሮቻቸው፣ ባሮችም ከፊት ይልቅ



For more books www.amharicchristianbooks.com

ለጌቶቻቸው እንዲገዙ ታዘዋል፡፡ ታዲያ ማንም ይህንን ቢያደርግ የርስት ብድራት ሽልማት እንደሚያገኝ ሁሉ፣ ባያደርግ ደግሞ ፍርድ እንደሚኖር በግልፅ ተጽፏል፡፡ ፈራጁም ጌታ የሚታወቅበት አንድ ባህሪ አለ፡፡ ፊፅሞ ለሰው ፊት አያደላም፡፡ በዚያን ዘመን በሪያዎች ጌቶቻቸውን የመክሰስ መብት ስላልነበራቸው ባሪያና ጌታ ተካሰው ፍርድ ቤት ሊቀርቡ አይችሉም ነበር፡፡ ቢቀርቡም ዳኛው ለማን እንደሚፈርድ ሳይታለም የተፈታ ነው፡፡ አሁን ግን በፊቱ የምንቀርበው ጻድቅ ፈራጅ የሆነ ጌታ፣ ለሰው ፊት አያደላምና ጌቶች እንዲጠነቀቁ ያሳስባቸዋል፡፡

በጥንቷ ሮም ወይም ከጥቂት ምዕተ ዓመታት በፊት በአውሮፓና በአሜሪካ፣ በጥቁር አፍሪካውያን ላይ ይተገበር የነበረው ዓይነት ባርነት ዛሬ በዘመናችን የለም፡፡ ነገር ግን በዘመናዊ መልክ ቢሆንም ዛሬም የአሠሪና የሠራተኛ ግንኙነት ቀጥሏል፡፡ እንደቀድሞ የባሪያ አሳዳሪ ሥርዓት አሠሪዎች በቤታቸው ባያሳድሩም፣ ዛሬም በድርጅታቸው እየቀጠሩ ያሰራሉ፡፡ እንደ ጥንቱ ሕግ የወደዱትን እንዲያደርጉ ባይተዋቸውም፣ ዛሬም ጥቂቶቹ ባለ ሃብቶች ወፈ-ሰማይ የሆነውን አምራች ይቀጥራሉ፣ ያስተዳድራሉ፡፡ ስለዚህ ሐኪም ብንሆን መሐንዲስ፣ የመንግሥት ሠራተኛ ብንሆን የግል፣ አለቃ ብንሆን ምንዝር፣ ሁላችንም አገልጋዮች ነን፡፡ በመንግሥት መሥሪያ ቤት በየትኛውም እርከን ላይ የሚገኙ ሠራተኞች «ሲቪል ሰርቫንት» ማለትም «ሕዝባዊ ባሪያ ወይም ሕዝባዊ አገልጋይ» ተብለው ይጠራሉ፡፡ ስለዚህ ሁላችንም ከበታቻችን ታዛዦች ያሉን «ጌቶች»፣ ከበላያችን አለቆች ያሉን «ባሮች» ነን፡፡ ታዲያ ይህ ክርስቶስን ማዕከል ያደረገ ትምህርት ምን ያህል ልቦናችንን ገዝቶት፣ አመለካከታችንን ቀይሮት ይሆን? ሠራተኞች ከአሠሪዎቻችን፣ አሠሪዎች ከሠራተኞቻችን ጋር ባለን ግንኙነት ይህንን የጥንት፣ ነገር ግን ዘመን የማይሽረው ክርስቶሳዊ መርህ ምን ያህል ተግባራዊ እናደርግ ይሆን? ለሥራ በተሰማራንባቸው ሥፍራዎች ሁሉ እኛን የክርስቶስ ተከታዮችን ከሌሎች ሠራተኞችም ሆነ አሰሪዎች የሚለየን ምን ይሆን? ለዚህ ሙሉ መልስ ልንሰጥ ይገባል፡፡



For more books www.amharicchristianbooks.com

# ምዕራፍ ፲፩
# መልካሙን የእምነት ገድል መጋደል

ኤፌ. 6፡ 10 - 11

## መግቢያ

ኢትዮጵያ በርካታ የጦርነት ታሪክ ያላት አገር ናት፡፡ ባሳለፍናቸው 150 ዓመታት ውስጥ ብቻ 92 ውጊያዎችን እንዳስተናገደች ይነገራል፡፡ ይህ መረጃ በአሃዝ ሲቀመጥ ቀላል ቢመስልም በተግባር ሲተመን ግን ለነፍስ የሚቆጠቁጥ ነው፡፡ በዚህ ሁሉ ጦርነት ውስጥ ስንት ሰው ወድቋል? ስንት ቤት ተፈቷል? ለልማት ሊውል የሚችል ስንት ሃብት ወድሟል? ግምት ከመሰንዘር ባሻገር ማንም በአሃዝ ሊያስቀምጠው የማይችል አስቸጋሪ ቀመር ነው፡፡ እነዚህ የጦርነት ታሪኮች ጥለውብን ያለፉት አሻራ ጉልህ ነው፡፡ የውጊያና የድል በዓላቶቻችን፣ ባለ ገድል ጀግኖቻችን፣ የፉከራና የሽለላ ዘፈኖቻችን፣ ሌሎችም በርካታ ክንውኖች ያለፉትን የጦርነት ታሪኮቻችንን መልሰን መላልሰን እንድናስብ ግድ ይሉናል፡፡ በሆነ አጋጣሚ ወደ ሰሜኑ የአገራችን ክፍል ስናቀና የምንሰማው ወንዳወንድ ስም፣ የምናየው ኮስታራ ግንባር፣ ከሩቅ የምናስተውላቸው ተራራን ተገን አድርገው የተገጠገጡ መንደሮች፣ ባጠቃላይ ዙሪያ ገባው የዘመናት ጦርነቶች ጥለውብን ያለፉትን አሻራ በደማቁ ያሳየናል፡፡

በአገር፣ በወገን፣ በቤተሰብ ላይ ጥፋት ሲቃጣና ሞት ሲታወጅ፣ አገር ከተት ብሎ ይወጣል፡፡ በዚህ ጊዜ ጦርነት ምንም ያህል ዋጋ የሚያስከፍልና መሥዋዕትነትን የሚጠይቅ ቢሆንም፣ መሳተፍ ግድ ይላል፡፡ ሰው አገሩን ሰጥቶ፣ ርስቱን ተነጥቆና ቤተሰቡን አጥቶ፣ የሚኖረው ሕይወት ከሞት አይሻልምና ሁሉን አጥቶ ነፍሱን ለማዳን ቢሸሽ፣ በቁሙ እንደሞተ ስለሚቆጠር ወገቡን ታጥቆና ድልን ሰንቆ ይዘምታል፡፡ በለስ ቢቀናው ድሉን ያጣጥማል፣ በፍልሚያው ላይ ቢወድቅም ስሙ በታሪክ መዝገብ በወርቅ ቀለም ይሰፍራልና እንደሞተ አይቆጠርም፡፡ ሰው ሊያሳስበውና ሊያስፈራው የሚገባው ሞት ሳይሆን የሚሞትለት ዓላማ መሆን ይኖርበታል፡፡ ዳሩ የሚሞቱለትን የሚያውቁ፣ የሚኖሩለቱን ያወቁ ብቻ ናቸው፡፡ ላንዱ ኖሮ፣ ለሌላው መሞት አይቻልምና፡፡

እንዲያው ብዕረ-መንገዴን የአገሬን የጦርነት ታሪክ አነሳሁ እንጂ፣ ትኩረቴስ የመንፈሳዊው ጦርነት ጉዳይ ነው፡፡ ባለፉት ሁለት ክፍሎች ከእግዚአብሔርና



For more books www.amharicchristianbooks.com

ከሰው ጋር እንዴት ልንኖር እንደሚገባ የመከረን ጳውሎስ፣ የድምፁን ቃና በመለወጥ ስለ መልካሙ ገድል መተረክ ጀምሯል፡፡ ይህ ጦርነት የጽድቅ ጦርነት ነው፤ የሚሳተፉበትም ብፁዓን ናቸው፡፡ ይህን ጦርነት ከሌሎች ጦርነቶች ሁሉ ልዩ ከሚያደርጉት ባሕርያት አንዱ ድሉ አስቀድሞ የታወቀ መሆኑ ነው፡፡ የሠራዊቱ ጠቅላይ አዛዥ የሆነው ጌታ ብቻውን ይህንን ጦርነት በቀራኒዮ ገጥሞ በትንሳኤው በድል ፈፅሞታል፡፡ ነገር ግን እኛም ድሉን፣ ከድሉም ባሻገር ያለውን የዘላለም ክብር እናጣጥም ዘንድ አስከትቶናል፡፡

ካስተዋልነው በዚህ ፍልሚያ ውስጥ እንደ ወታደር መሳተፋችን በራሱ ክብር ነው፡፡ ምክንያቱም በአንድ ወቅት በጨለማው ግዛት ውስጥ የዲያቢሎስን መንግሥት ለማቆም የአመፃ የጦር ዕቃ በነበሩት በብልቶቻችን የኃጢአትን ጡብ የምንጠፈጥፍ ባሮች ነበርን፡፡ ዛሬ ከባርነት ነፃ ወጥተን ትናንት ይገዛን የነበረውን መውጋት መቻላችን በራሱ ትልቅ ድል አይደል? ያኔ ባሮች የሆንነው ወድደንና መርጠን አልነበረም፡፡ በኃጢአት ከወደቀው ከአዳም ዘር ስንወለድ ራሳችንን ባሮች ሆነን አገኘነው፡፡ ለኃጢያትና ለልዩ ልዩ ተድላ ከመገዛት በቀር የሥጋ ምኞታችንን እንደ ጭምብል ለብሶ የሚመጣውን ጠላት እምቢ ማለት አልተሰራብንም ነበር፡፡ አሁን ግን ከእግዚአብሔር ዘር ስንወለድ ለሐሰትና ለርኩሰት እምቢ አሻፈረኝ የሚል አዲስ ተፈጥሮ ተላበስን፡፡ በኃጢያት ላይ አብየን ለጽድቅ ተገዛን፡፡ እንግዲህ የጦርነቱ መንስዔ ይህ ነው፡፡ ገና ሳንፈጠር ለጦርነት፣ ብሎም ለድልና ለክብር የተወሰንን ነንና «ተፈፀመ» ብለን ነፍሳችንን ለባለቤቷ እስክናስረክብ ድረስ፣ ለጽድቅ እንዋጋ ዘንድ እንደ ገና ተፈጥረናል፡፡

ጦርነት የሚመዘነው በዓላማው ነው፡፡ ይህ በዚህ ክፍል የምናየው መንፈሳዊ ጦርነት ሊኖርለት ብቻ ሳይሆን ሊሞትለት የሚገባ ክቡር ዓላማ ያነገበ ጦርነት ነው፡፡ ቀደም ባሉት ክፍሎች በተለይም በመጀመሪው ክፍል (1 – 3) የእግዚአብሔር ሃሳብ በጉልህ ተገልጦ አይተናል፡፡ ይህም ሃሳብ ከዘላለምና ከዘመናት ጀምሮ ተሰውሮ የኖረና ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን በመነሳቱ ወደ ብርሃን የወጣ ሃሳብ ነው፡፡ ይህ ሃሳብ እግዚአብሔር በመንፈሱ፣ ለቅዱሳን ሐዋርያቱና ለነቢያቱ እስከገለፀውና እነርሱም በዘመኑ አለም በቃልና በጽሑፍ እስካስተጋቡት ድረስ፣ በየትኛውም ዘመን ለሰው ልጆች ፈጽሞ ያልታወቀ ምሥጢር ነበር፡፡ ይህ ምሥጢር እንኳን በምድር ለሚኖሩ ሰዎች በሰማያዊ ስፍራ ላሉ አለቆችና ሥልጣናት እንኳ የተገለጠው በዚህ "በመጨረሻ" ዘመን እንደሆነ ቀደም ሲል ተመልክተናል፡፡ ይህ ሃሳብ እስራኤልና አሕዛብ በመባል ተለያይተው የኖሩትን የሰው ልጆች በክርስቶስ አንድ በማድረግ እውን መሆን የጀመረ ሲሆን፣



For more books www.amharicchristianbooks.com

በእግዚአብሔር መንፈስ ፍጥረትን ሁሉ በክርስቶስ ሥር በአንድ አስተዳደር በመጠቅለል የሚደመደም ሃሳብ ነው፡፡ ሆኖም ይህ ዕቅድ ሁሉን የሚያስደስትና ሁሉን አሜን የሚያሰኝ አይደለም፡፡ መዳንን ለምንወርስ ለሰው ልጆች የምሥራች የሆነው ይህ በክርስቶስ እየተፈፀመ ያለ የዘላለም ሃሳብ፣ ከእግዚአብሔር ተለይተው በዓመፅ ለሚኖሩት የወደቁ መላዕክት አስደንጋጭና ተስፋ አስቆራጭ መርዶ ሆኖባቸዋል፡፡ ስለዚህ እግዚአብሔር ከዘመናት አስቀድሞ ለክብራችን የወሰነውን ተሰውሮ ኖሮ አሁን የተገለጠውን ይህን ሃሳብ በፅናት ይቃወማሉ፡፡ ከዚህም የተነሳ የቀራቸውን ጥቂት ጊዜ ለመጠቀም በልዑሉ ቅዱሳን ላይ ጦርነት አውጀዋል፣ በቁጣ ወጥተዋል፡፡[304]

ይህ ጦርነት እነርሱ ቢያውጁትም አስቀድሞ የወሰነው ግን እግዚአብሔር ነው፡፡ አላማውም አለቆችና ሥልጣናት፣ የዚህ የጨለማው ዓለም ገዥዎችና በሰማያዊ ሥፍራ ያሉ የክፋት መንፈሳዊያን ሠራዊት በመባል የሚጠሩትን ስመ-ታላላቆች፣ በውጪያቸው እዚህ ግቡ በማይባሉ፣ ስምም ሆነ ታሪክ በሌላቸው ነገር ግን በውስጣቸው ካለው ክርስቶስ የተነሳ ኃይለኛ በሆኑ ሰዎች ስልጣናቸውን በመግፈፍ፣ ድል በመንሳትና፣ በማዋረድ ለስሙ ክብር ማምጣት ነው፡፡

ለትምህርታችን የተጻፉልን ቅዱሳት መጻሕፍት የሚተርኩልን በቀድሞ ዘመናት የተፈፀሙ የእግዚአብሔርና የሕዝቡ የጦር ሜዳ ውሎዎች ለዛሬው ገድላችን አይነተኛ ተምሳሌት ናቸው፡፡ እግዚአብሔር አብርሃምን እንደ ግለሰብ ከከለዳውያን ሃገር ከጠራ፣ ያዕቆብንና ሰባ ሁለት ነፍስ እንደ ቤተሰብ ወደ ግብፅ ካገባ፣ ከአራት መቶ ዓመታት በኋላ እስራኤልን እንደ ሕዝብ ከግብፅ ካወጣ፣ ጠላቶቻቸውን ከፊታቸው አጥፍቶ እንደ መንግሥት ርስትን ካወረሰበት ጊዜ አንስቶ፣ ቁጥር ስፍር የሌለው የጠላት ምክር፣ የጦር ድግስ፣ የሰልፍ ዓይነት ተካሂዷል፡፡ ከዚህ በመነሳት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት የጦርነት መጻሕፍት ናቸው ብንል ፈፅሞ ማጋነን አይሆንም፡፡ እስራኤል ጦርነቶች በታወጁባት ጊዜ ሁሉ ውጤቱ የሚወሰነው በጦር ኃይሏ ብርታት ሳይሆን ከእግዚአብሔር ጋር በሚኖራት ግንኙነት ነበር፤ ግንኙነቷ ሲሰምር ድል ትቀዳጃለች፣ ግንኙነቷ ሲበላሽ በውርደትና በሽንፈት ትመታለች፡፡ ምንም ያህል ብትመታና ብትሸነፍም፣ በፍፁም ልቧ ወደ አምላኳ ስትመለስ ትታደሳለች፣ በጠላቶቿም ፊት መፈራትና ድል ይሆንላታል፡፡ ይህም ለአዲስ ኪዳኖቹ ለእኛ ዓይነተኛ ምሳሌና ትምህርት ነው፡፡

በኤፌሶን መልዕክት ውስጥ የምናገኘው መንፈሳዊ ውጊያ ዓይነተኛ ሰበቡ ርስት

[304] ዮሐ. ራዕይ 12፡12



For more books www.amharicchristianbooks.com

ነው፡፡ እግዚአብሔር ርስትን ሰጠን፡፡ በልጁ ስናምን ፈፅሞ የማይገባንን፣ የማንመጥነውን ቅዱስ መንፈሱን ለዘላለም መኖሪያ ይሆነን ዘንድ እንዲያው በፀጋ ሰጠን፡፡ በእምነት በተቀበልነው ጊዜ መንፈሳችን ሕያው ሆነ፡፡ ሆኖም በዚህ አላበቃም፣ በሚመጣው ዘመን እንደ መንፈሳችን ሁሉ ሥጋችንም ሕያው እንደሚሆን ነግሮን የክብር ተስፋ አሰነቀን፡፡ ባላጋራዎቻችን ግን ይህ አልተመቻቸውም፣ ሊመቻቸውም አይችልም፡፡ እነርሱም ይህ ተፈፅሞ ከምናይ መጥፋት ይሻለናል ብለው ጦር መጎንጎንና ፍላፃ መሳል ከጀመሩ ዘመናት ተቆጥረዋል፡፡ ዛሬ በመንፈስ ከምንኖርበት ርስታችን ሊያፈናቅሉንና ለነገ የተሰጠንን ተስፋ ከእጃችን ሊያስጥሉ ዘምተዋል፡፡ እንግዲህ ለርስቱ የማይዋጋ ማን ነው!?

ይህን ክፍል «ርስትን መጠበቅ» ተብሎ ተሰይሟል፣ በሌላ በኩል ደግሞ ርስታችን እግዚአብሔር ነው፤ ቅዱስ መንፈሱን መኖሪያ አድርጎ ሰጥቶናል ብለናል፤ ታዲያ ርስታችን እግዚአብሔርን ነው ካልን፣ ርስታችንን የምንጠብቀው እንዴት ነው? እግዚአብሔር ይጠብቃል እንጂ እንዴት ይጠበቃል? የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል፡፡ ጥያቄውም አግባብነት ያለው ነው፡፡ እግዚአብሔር ይጠብቀናል እንጂ እንዴት እንጠብቀዋለን፡፡ እውነቱ ይህ ነው፤ የምንጠብቀው ርስቱ በጠላት እንዳይወሰድ ሳይሆን እኛ ከርስታችን እንዳንወሰድ ነው፡፡ ስለዚህ በሌላ አነጋገር የምንጠብቀው የሕይወታችን መዘውር የሆኑትን ፈቃዳችንን፣ ስሜታችንን እና ሃሳባችንን ወይም ራሳችንን ነው፡፡

በዘመናት ውስጥ እስራኤላውያን በጠላቶቻቸው ተማርከው የተወሰዱበትና ከርስታቸው የተፈናቀሉበትን ታሪክ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እናነባለን፡፡ ነገር ግን ይህ የሆነው በእግዚአብሔር ላይ ስላመፁ፣ በሕጉና በሥርዓቱ ለመሄድ አሻፈረኝ ስላሉ፣ ርስቱን ስላረከሱና ስላጎሰቆሉ እንጂ ጠላቶቻቸው ከእነርሱ ስለበረቱ አልነበረም፡፡ በቅዱስ ሕጉ በመመራት፣ ለቅዱስ ርስቱ እንደሚገባ፣ እንደ ቅዱስ ሕዝብ ሊኖሩ ስላልፈቀዱ እግዚአብሔር ለጠላቶቻቸው አሳልፎ ሰጣቸው፡፡ የኖሩበትን የጣዖት አምልኮ፣ የርኩሰትና የግፍ ኑሮ በርስቱ ላይ ከሚኖሩ ይልቅ የእነርሱን አይነት ኑሮ በመምራት ከሚመስሏቸው አሕዛብ ጋር በባዕድ ምድር እንዲኖሩ ለማረኳቸው አሕዛብ አሳልፎ ሰጣቸው፡፡ ለምድሪቱም ዕረፍትንና ሰንበትን ሰጣት፡፡ እንዲያርፉባት የተሰጠቻቸውን ምድር በክፉ ሥራቸው ስላስጨነቁ እነርሱ በባዕድ ምድር እንዲጨነቁ፣ ምድሪቱ ግን ለሰባ አመታት ከእነርሱ እንድታርፍ አደረገ፡፡

ሰባ አመቱ ሲፈፀምና እነርሱም በንስሐ ወደ እግዚአብሔር ሲመለሱ በምሕረትና



For more books www.amharicchristianbooks.com

በርህራሄ ወደ ርስታቸው መለሳቸው፡፡[305] ቀድሞም እነርሱ ከርስቱ በጠላት ተወሰዱ እንጂ ርስቱ በጠላት አልተወሰደም፡፡ ስለዚህ ርስትን መጠበቅ ስንል እኛ በጠላት ከርስቱ እንዳንወሰድ መጠበቅ እንጂ፣ ርስቱ በጠላት እንዳይወሰድ መጠበቅ አለመሆኑን ልብ ልንል ይገባል፡፡ ርስቱ ከተወሰደብንም የሚወስደው ራሱ እግዚአብሔር እንጂ ጠላት አይደለም፡፡ ይህንንም ንጉስ ዳዊት ኦሪዩንን አስገድሎ ሚስቱን ከጠቀለለ በኋላ ነቢዩ ናታን ወደ እርሱ መጥቶ ኃጢአቱን በገለጠ ጊዜ *«ከፊትህ አትጣለኝ፣ ቅዱስ መንፈስህንም ከእኔ ላይ አትውሰድብኝ፡፡»* (መዝ 51፡11) በማለት እግዚአብሔርን ከተማፀነበት ቃል መረዳት እንችላለን፡፡ ዳዊት መንፈስ ቅዱስ የሚሰጥም፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የሚወሰድም እንደሆነ ገብቶታል፡፡ ሆኖም ሊሰጥም ሆነ ሊወስድ የሚችለው ሰጪው ብቻ መሆኑን በትክክል ስለ ተረዳ *«...ቅዱስ መንፈስህንም ከእኔ ላይ አትውሰድብኝ፡፡»* በማለት እግዚአብሔርን ተማፀነ፡፡ ይህም በኃጢአት ከወደቀ በኋላ ያሳሰበው የመንግሥቱ፣ የሃብቱ እና የክብሩ ጉዳይ ሳይሆን የመንፈስ ቅዱስ ጉዳይ እንደነበር ያሳየናል፡፡

"የምንዋጋው ርስቱ እንዳይወሰድ ሳይሆን እኛ በጠላት ከርስቱ እንዳንወሰድ ነው" ማለታችን፣ ጠላቶቻችን እኛን ከርስታችን ለማፈናቀል ብቃትና ኃይል እንዳላቸው አያሳይም፡፡ ጌታ ራሱ «ከእጄም ማንም አይነጥቃቸውም . . . » ዮሐ. 10፡28 ብሏልና፡፡ ነገር ግን "ማንም ከእጄ አያወጣቸውም" ሲል የእኛን ነፃ ፈቃድ እንደማይጠቀልል ልብ ልንል ይገባል፡፡ ይህም እኛ ወደን ከእጁ ባንወጣም እንኳ፣ ተታለን ልንወጣ እንደምንችል በማስታወስ ያስጠነቅቀናል፡፡[306] ጠላታችን ኃይለኛ ሳይሆን ተንኮለኛ ነውና፡፡

በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት እግዚአብሔር የእኛ ርስት፣ እኛም የእርሱ ርስት እንደሆንን አስቀድመን አንስተናል፡፡ ስለዚህ ምክንያት መንፈስ ቅዱስ ከእኛ ቢወሰድ፣ እኛ በእግዚአሔር ውስጥ ያለንን ርስት እንደምናጣ ሁሉ፣ እግዚአብሔርም በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት በእኛ ውስጥ ያለውን ርስቱን እንደሚያጣ ግልፅ ነው፡፡ ስለዚህ እኛ በእርሱ ሆነን የምንዋጋው፣ እርሱም በእኛ አድሮ የሚዋጋው ለአንድ አላማ ነው፤ ርስትን መጠበቅ፡፡

## ቁጣ

በአሥራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን መባቻ የጀርመን ግዛት የነበረችው የፕሮይሰን

[305] ኤር. 29፡ 10 - 14

[306] ገላ. 4፡ 17



For more books www.amharicchristianbooks.com

የጦር ጄነራልና ተመራማሪ የነበረው ካርል ቮን ክላውስቪትስ ጦርነትን እንዲህ በማለት ተርጉሞት ነበር "ጦርነት ጠላታችን የእኛን ፈቃድ ያደርግ ዘንድ ኃይልን በመጠቀም ለማስገደድ የምንወስደው ርምጃ ነው፡፡"[307] በእርግጥም ጦርነት በሁለት ኃይሎች መሃል ሲካሄድ ሁለቱም ተቃራኒ ኃይላት ጠላት በሚሉት ተሸንፈው የፈቃዱ መፈፀሚያ ከመሆን እንዲተርፉና ባላጋራቸውን አሸንፈው ፈቃዳቸውን በኃይል ለማስፈፀም እንዲችሉ የሚያደርጉት የሞት ሽረት ግብ ግብ ነው፡፡

ጦርነት ሁለት ዓላማዎች አንግቦ ሊካሄድ ይችላል፡፡ አንደኛው የመስፋፋት ዓላማ ሲሆን፣ ሌላኛው ድንበር ጥሶ የመጣን ጠላት በመመከት ድንበርን የማስጠበቅ፣ ርስትን የማስከበር ዓላማ ነው፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ በዚህ ክፍል ክተት እያወጀበት ያለው መንፈሳዊ ጦርነት ብዙውን ጊዜ እንደሚታሰበው የመሄድ፣ የጠላትን ግዛት የመውረርና ድንበር የማስፋት ጦርነት አይደለም፡፡ ስለ እንዲህ አይነቱ ጦርነት የሚናገሩ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች እንዳሉ እሙን ነው። ይህ ክፍል ግን ስለ ሁለተኛው እንጂ ስለ አንደኛው አይነት ጦርነት አይናገርም፡፡ ይህንንም ፍንትው አድርገው የሚያሳዩን ሐዋርያው ሁለት ጊዜ በመደጋገም ያስቀመጣቸው ገላጭ ቃላት ናቸው፡፡ ". . . ስለዚህ በክፉ ቀን ለመቃወም ሁሉንም ፈፅማችሁ **ለመቆም** እንድትችሉ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ አንሱ . . . በሰላም ወንጌል በመዘጋጀት እግሮቻችሁ ተጫምተው **ቁሙ** . . . ፡፡" (ቁ. 13 እና 15) በዚህ ክፍል ላይ ያደመቅኋቸው ሁለት ቃላት ከርስታችን ሊያፈናቅሉን የሚመጡትን ጠላቶቻችንን ስፍራችንን ሳንለቅ ፀንተን በመቆም እስከ መጨረሻ መቃወም እንደሚገባን የሚያመለክቱ ቃላት ናቸው፡፡ መቆም የመውደቅ ወይም የመሸሽ ተቃራኒ ነው፡፡ በጠላቶቻችን ሽንገላ ሳንታለል፣ በዛቻቸውም ሳንበረግግ በሥፍራችን ፀንተን መቆማችን፣ ስለቆምንበት ርስት ያለንን መረዳት ያሳያል፡፡ ስለሚኖርበት ርስት ምንም መረዳት የሌለው ሕዝብ፣ እንኳን ጠላት መጥቶበት እንዲሁም ጥሎት ሊሰደድና ሊኮበልል ይችላል፡፡ ባደጉት ሃገራት በስደት የሚማቅቁ በርካታ የአፍሪካ ልጆች አንዳች ጠላት ሳይዘምትባቸው ገንዘብ ከፍለው ገንዘብ ፍለጋ የኮበለሉት፣ ይኖሩበት የነበረው አካባቢ ምን ሊያስገኝ እንደሚችል ባለመገንዘብ እንደሆነ መገመት አይከብድም፡፡[308] እነዚህ የአፍሪካ ልጆች ተወልደው ያደጉበት ምድር ምን ሊያስገኝ እንደሚችል ቢያውቁ፣ ተፈጥሮ የለገሳቸውን ጥሪት ወደ ሃብት መለወጥ

[307] Clausewitz, Carl von (1984) [1832]. Howard, Michael; Paret, Peter. eds. On War [Vom Krieg] (Indexed ed.). New Jersey: Princeton University Press. p. 75.
[308] ይህ አባባል የሚመለከተው የኢኮኖሚ ስደተኞችን ብቻ ነው፡፡



For more books www.amharicchristianbooks.com

የሚችሉበትን ዕውቀት ቢያካብቱ፣ በነፃነት ለመሥራትና ለመንቀሳቀስ የሚያግዛቸውን መልካም አስተዳደር ቢያገኙ ኖሮ፣ እንኳን በደላላ በጦር መሣሪያም አይኮበልሉም ነበር፡፡ ለዚህ ነው «ርስትን ማወቅ፣ ፀንቶ ለመቆም ወሳኝ ነው!» የምንለው፡፡

## በቀረውስ

በቀረውስ የሚለው ቃል ጸሐፊው ያገባደደውን ሃሳብ ተሰናብቶ አዲስ ወደ ጀመረው ሃሳብ ለመሸጋገር የተጠቀመበት ቃል እንጂ ራሱን የቻለ አንዳች ምሥጢራዊ መልዕክት የለውም፡፡ ይህን ቃል የ1886ቱ፣ 1962ቱ፣ የ1988ቱ የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች «በቀረውስ» በማለት የተረጎሙት ሲሆን አዲሱ መደበኛ ትርጉም «በተረፈ»፣ ሕያው ቃል ደግሞ «በመጨረሻ» ብሎታል፡፡

ሆኖም ቀጥታ ከቃሉ ባይሆንም እንኳ፣ ቃሉ ከተጠቀሰበት ቦታ በመነሳት ጠቃሚ ሃሳቦችን ማየት እንችላለን፡፡ አንዳንድ ሰዎች የክርስትና ሕይወት ተጀምሮ እስኪጨረስ የውጊያና የጦርነት ዐውድማ እንደሆነ ያስባሉ፡፡ ለእንዲህ አይነት ሰዎች የሌሊቱ ውጊያ በንጋት አያባራም፣ የቀኑ ሰልፍ በአመሻሽ አይበርድም፡፡ ሁሉን ነገር ከሰይጣን ጋር የሚያገናኙ፣ ከእያንዳንዱ ቁጥቋጦ ጀርባ ዲያቢሎስ የተደበቀ የሚመስላቸው፣ ከዚህም የተነሣ ተንበርክከው እስኪነሱ ተግሣፅ ከማዥጎድጎድ የማይቦዝኑ አማኞች ቁጥር ጥቂት አይደለም፡፡

የክርስትና እምነት በውስጡ መከራና ውጊያ አለ፡፡ ነገር ግን ምንም ያህል በውስጡ ውጊያ ቢኖርም፣ በውጊያ ጀምሮ በውጊያ የሚጨርስ የጭንቅና የሰልፍ ሕይወት ተደርጎ ሊቆጠር አይገባም፡፡ ክርስትና የሚጀምረው የእግዚአብሔርን ታላቅነትና ዘላለማዊ ሃሳቡን፤ በክርስቶስም የሠራልንን ታላቅ ሥራና በሞቱና በትንሳኤው ጠላቶቻችንን ድል ነስቶ ያስመዘገበልንን ድል ከመተረክ እንደሆነ ከኤፌሶን መልዕክት ውጪ ምሥክር አያሻም፡፡ በኤፌሶን መልዕክት ላይ በመንተራስ «መቀመጥ፣ መራመድና መቆም» በሚል ርዕስ በተፃፈ የዋች ማን ኒ መፅሐፍ ውስጥ ክርስትና ከጦርነት ሳይሆን በክርስቶስ ሥራ ከማረፍና በሰማያዊ ሥፍራ በአብ ቀኝ ከመቀመጥ እንደሚጀምር ተዘግቧል፡፡[309] ለዚህ ነው እኔም፣ በክርስትና ውስጥ ውጊያ «በመጀመሪያ» ሳይሆን «በቀረውስ» ነው የምለው፡፡

"በቀረውስ" የሚለው ቃል የሚያስታውሰን ሌላው ቁም ነገር እውነተኛ መንፈሳዊ ውጊያ ውስጥ የምንገባው በቅድሚያ የተሰጡንን ሰዋዊ ድርሻዎቻችንን ከተወጣን

---

[309] Nee, Watchman; Sit, Walk, Stand; Tyndal House © 1977



For more books www.amharicchristianbooks.com

በኋላ መሆኑን ነው፡፡ በመጀመሪያው ክፍል እግዚአብሔር ከምሕረቱ ባለጠግነት የተነሣ በትልቅ ፍቅሩ ወዶን ከሁሉ የሚበልጥ የኃይሉን ታላቅነት በመግለጥ፣ በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ሥራ ክብር የሞላበት ርስት እንደሰጠን መለኮታዊ ድርሻውን እንደተወጣ ተመልክተናል፡፡ በምላሹም በፀጋ ለተሰጠን ክብር የሚመጥን ምሥጋና እንድናቀርብ ተምረናል፡፡ በሁለተኛው ክፍል የመንፈስን አንድነት እየጠበቅን፣ በአዕምሮአችን መታደስ ተለውጠን፣ በብርሃንና በጥበብ እየተመላለስን ሰውን ሁሉ በመሥዋዕትነት ፍቅር እንድንወድ ተምረናል፡፡ እንግዲህ እነዚህን ቀዳሚ ድርሻዎቻችንን ከተወጣን በኋላ ነው ወደ ጦር አውድማው የምንዘልቀው፡፡ ሳያዛባና ሳያፋልስ ለእግዚአብሔር ምሥጋና፣ ለሰው ደግሞ ፍቅር መስጠት የቻለ አማኝ፣ ዲያቢሎስን መቃወም አይሳነውም፡፡ አለዚያ ግን የሠራልንንና የሰጠንን ሳናውቅ፣ በእግዚአብሔር ላይ ብናጉረመርም፣ በሕይወት መንፈስ ተሳስረን አንድ እንደሆንን ሳናውቅ፣ ከወገኖች ጋር በነገር ብንፋለም፣ እንስታለን፡፡ ያኔ የጦርነት አቅጣጫችን ይዛባል፡፡ ከሙሴ ጋር ሲነታረኩ፣ ከእግዚአብሔር ጋር ሲጣሉ ኖረው ጠላቶቻቸው ፊት ሲደርሱ «በፊታቸው አንበጣ ነን!» ብለው እንደ ሸሹት፣ በፍፃሜውም በእግዚአብሔር ቁጣ ተበልተው በምድረበዳ እንደ ወደቁት የእስራኤል ልጆች እንሆናለን፡፡ ለዚህ ነው «በቀረውስ» የሚለው ቃል፣ ስለ ውጊያ ከማውራታችን በፊት ድርሻችንን እንድንወጣ ያሳሰበናል ያልኩት፡፡ ሚስቱን እንደ ገዛ ሥጋው የመውደድ ድርሻውን ሳይወጣ ቀርቶ "ጠላት በሚስቴ ይዋጋኛል!" የሚል አባወራ፣ ለባሏ በአክብሮት የመገዛት ድርሻዋን ሳትወጣ "ጠላት በባሌ ይዋጋኛል!" የምትል እማ ወራ" ቢያጋጥሟችሁ ምን ትላላችሁ? ዳሩ የገዛ ድርሻቸውን ወደ ጎን ጥለው ሁሉን ነገር በዲያቢሎስ ማሳበብ የሚቀናቸው "ጠላት በልጆቼ ይዋጋኛል፣ በወላጆቼ ይዋጋኛል፣ በአሠሪዬ ይዋጋኛል፣ በሠራተኛዬ ይዋጋኛል!" የሚሉ አማኞች ስንት ይሆኑ? ቤቱ ይቁጠረው ከማለት ባሻገር መረጃ መጥቀስ የማይታሰብ ነው፡፡ ስለዚህ ወደ ውጊያው ዓለም ስንዘልቅ «በቀረውስ» የሚለውን ደማቅ መፈክር ከፍ አድርገን እናነሳለን፡፡

## . . . የበረታችሁ ሁኑ!

ሐዋርያው አዲሱን ክፍል የሚጀምረው በብርታት ቃል ነው፡፡ ዳሩ ለመንፈሳዊ ውጊያ ከሚዘጋጅ አማኝ በላይ ብርታት የሚያስፈልገው ማን አለ? ለሰልፍ የሚታጠቅ ሰው ድካም ቢኖረው እንኳ ሊነገረው የሚገባው ድካሙ ሳይሆን ልቡን ከፍ የሚያደርግ የብርታት ቃል ነው፡፡ ነቢዩ ኢሳያስ ፡ -



For more books www.amharicchristianbooks.com

> *«የደከሙትን እጆች አበርቱ፣ የላሉትንም ጉልበቶች አጽኑ፡፡ ፈሪ ልብ ላላቸው፡ - እነሆ አምላካችሁ በበቀል በእግዚአብሔርም ብድራት ይመጣልና፣ መጥቶም ያድናችኋልና በርቱ አትፍሩ፣ በሉአቸው፡፡» ኢሳ. 35፡3-4; ዕብ 12፡ 12*

እንዳለ፣ ባጠገባችን ያሉትን አማኞች «አይዞአችሁ፣ በርቱ፣ አትፍሩ . . . » ብለን ለእምነት ገድል እንድናጀግናቸው፣ እኛም እንድንጀግን ይመከረናል፡፡

በርግጥ፣ የምንገጥማቸው ጠላቶቻችን ማንነትና አሰላለፍ ሲጠራ ልብ ሊያርድ ይችል ይሆናል፡፡ ማንም ቢሆን «መጋደልህ ከአለቆችና ከሥልጣናት፣ ከዚህም ከጨለማ ዓለም ገዢዎች፣ በሰማያዊም ሥፍራ ካሉ መንፈሳውያን ሠራዊት ጋር ነው፡፡» ሲባል ቢፈራ አያስገርምም፡፡ ነገር ግን ለዚህ መፍትሄ ለመሻት ብዙ መድከም አያስፈልግም፡፡ ወደ ምዕራፍ አንድ ሄዶ ቀደም ሲል የተባለውን ዳግም በጥሞና ማየት ይበቃል፡፡ እነዚህ ኃይላት እነማን ናቸው? ብለን ስንጠይቅ የምናገኘው መልስ፣ በክርስቶስ ሞትና ትንሳኤ ድል የተነሱ፣ የተሸነፉ፣ የተገፈፉ፣ ከእግሩ በታች የተገዙ፣ ጠላቶች እንደሆኑ እናያለን፡፡ (ኤፌ. 1፡19-21; ቆላ. 2፡14-15)፡፡ ታዲያ ድልን ሰንቆ፣ ውጤትን አውቆ እንደ መዋጋት የሚያጀግን ምን አለ!

ጳውሎስ አንባቢያኑን እንዲያው በሜዳ ሳይሆን *« . . . በጌታና በኃይሉ ችሎት የበረታችሁ ሁኑ፡፡»* በማለት የሚበረቱበትን ኃይልና ችሎት በግልፅ ያሳያል፡፡ ከሙታን የተነሳው፤ ከሁሉ በላይ ከፍ ያለው፣ ክብርን ተጐናፅፎ በግርማው ቀኝ የተቀመጠው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የእኛ ነው፡፡ አካሉ እንሆን ዘንድ የሕይወት ራስ ሆኖ ተሰጥቶናል፡፡ ስለዚህ እርሱ በእኛ፣ እኛም በእርሱ ሆነናል፡፡ እርሱ የእኛ ከሆነ ደግሞ የእርሱ የሆነ ኃይል ሁሉ የእኛ ነው፡፡ ሐዋርያው ቀደም ባሉት ክፍሎች ክርስቶስ በዚህ ኃይል ከሙታን እንደተነሳና ከፍ ከፍ እንዳለ ነግሮናል (1፡19፣ 20)፣ በዚህ ኃይል ወንጌል በዓለም ሁሉ እንደተሰበከ ጽፎልናል (3፡ 7)፣ ክርስቶስ በልባችን በእምነት ይኖር ዘንድ በዚሁ ኃይል በውስጥ ሰውነታችን እንደምንጠነክር አስተምሮናል (3፡ 16)፤ በሁሉ አቅጣጫ እግዚአብሔር በዚህ ኃይል በእኛ እንደሚሠራ አስገንዝቦናል (3፡ 20)፡፡ ይህ ኃይል መኖሪያ ርስታችን ነው፤ የሕይወት ራስ ከሆነው ጌታ ዘንድ ለእኛ ያለማቋረጥ ይፈልቃል፡፡ ስለዚህ እኛ በራሳችን ልንበረታ አያስፈልገንም፤ ኃይለኛ እንድንሆን፣ ብርታት እንድናፈልቅ፣ ወይም የራሳችንን ድል እንድናስመዘግብ አይጠበቅብንም፡፡ ስለዚህ በድካማችን መመካት እንጂ ማዘንና ተስፋ መቁረጥ አይገባንም፡፡[310] የምንበረታው ጌታንና

---

[310] 2ቆሮ. 12፡9-10



For more books www.amharicchristianbooks.com

የትንሳኤውን ኃይል በማወቅና በማመን፣ በእርሱም በመደገፍ እንጂ በስሜት አይደለምና በዙሪያችን የሚታየንና በሥጋችን የሚሰማን ምንም ይሁን ምን አይናችንን በጌታ ላይ ልናደርግ ይገባናል፡፡ ይልቅ ከጌታ ጋር የማያቋርጥ የሕይወት ሕብረት በማድረግና የትንሳኤ ኃይል የሆነውን መንፈስ ቅዱስን ከሚያሳዝን፣ እግዚአብሔርንም ከሚያስቆጣ ከማናቸውም ነገር በመራቅ ኃይሉ በውስጣችን እንዲሠራ ልንፈቅድ ይገባናል፡፡ የእኛ ድርሻ ይህ ነው፤ ኃይል ማመንጨት ሳይሆን በተሰጠን ኃይል መበርታት፡፡

ይህም መበርታት ለርስታችን በሚጠብቀን የእግዚአብሔር ኃይል ላይ ያለንን መተማመንና እርግጠኝነት የሚያሳይ ነው፡፡[311] ጌታ እኛን ኃይለኞች አላደረገንም፣ ነገር ግን በእኛ ውስጥ ሆኖ ኃይላችን ሆነ፡፡ ያለ እርሱ ደካሞች ነን፣ ከእርሱ ጋር ግን ከሁሉ የምንበልጥ፣ ለምንም የማንበገር ኃይለኞች እንሆናለን፡፡ ይህም ኃይለኝነታችን ከእርሱ ጋር ካለን የማያቋርጥ ሕብረት የሚመነጭ እንጂ፣ አንዴ ተሰጥቶን ሁሌ የምንጠቀምበት የኃይል አስቤዛ አለመሆኑን ያስረዳናል፡፡ ለዚህ ነው ፀሐፊው «በጌታና በኃይሉ ችሎት የበረታችሁ ሁኑ» የሚለን፡፡ ፀሐፊው በዚህ ክፍል ኃይልን ለመግለጽ የተጠቀመበት «ክራቶስ» የተሰኘውና የግሪክ ቃል፣ በእንቅስቃሴና በሥራ ላይ ያለ ኃይልን የሚያመለክት ነው፡፡[312] እኛን ድል ለማቀዳጀት በቂ ኃይልና ችሎታ በጌታ ዘንድ አለ፡፡ ጌታ ኃይል ሰፍሮ ሰጥቶ ወደ ጦርነት አይሸኘንም፣ ነገር ግን እርሱ ራሱ ኃይላችን ሆኖ አብሮን ይወጣል፣ እኛም እርሱን ለብሰን እንዋጋለን፡፡ ያኔ የእኛ ድርሻ በኃይሉ መተማመን (1፡19)፣ መለመን (3፡20) መለማመድና (3፡16) መበርታት (6፡10) ብቻ ይሆናል፡፡

## ጠላትን ማወቅ

በየትኛውም የጦር አውድማ ላይ ድል ለመቀዳጀት ከፍልሚያው በፊት መፈፀም ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች አሉ፡፡ እኛም ወደ ውጊያው ከመግባታችን በፊት ጠላቶቻችን እነማን ናቸው? ምን አይነት የጦርነት ሥልት ይጠቀማሉ? የጦር መሣሪያዎቻቸው ምን አይነት ናቸው? የሚሉትን መሰለል ግድ ይለናል፡፡ ይህም ክፍል እነዚህን ለውጊያና ለድል ወሳኝ የሆኑ እውነቶች በዝርዝር አስቀምጦልናል፡፡

---

[311] 1ጴጥ. 1፡3-5

[312] Wuest S. Kenneth, Ephesians and Colossians in the Greek New Testament, Eerdmans publishing 1953. P. 140



For more books www.amharicchristianbooks.com

## ጦርነትና ውጊያ

አለማችን ውጊያ ያልተካሄደባቸውን ጦርነቶች ለበርካታ ጊዜያት አስተናግዳ ታውቃለች፡፡ ከእነዚህም መሃል በምሳሌነት የሚጠቀሰው «ቀዝቃዛው ጦርነት» በመባል የሚታወቀውና በቅርቡ በሸኘነው ክፍለ ዘመን በምሥራቁና በምዕራቡ፣ (በቀድሞዋ ሶቪየት ሕብረትና በአሜሪካ) መካከል የተካሄደው ጦርነት ነው፡፡ ይህ ጦርነት የባሩድ ጢስ ሰማዩን የሸፈነበት፣ ወታደሮች በሳንጃ የተሞሻለቁበት፣ መሬት ደም የጠገበችበት ውጊያ አልነበረውም፡፡ ነገር ግን ጦርነት ተብሎ ሲጠራ ኖሯል፡፡ ይህም በጦርነትና በውጊያ መሃል ያለውን ልዩነት በጉልህ ያሳየናል፡፡ ጦርነት የተኩስ ብቻ ሳይሆን የቃላት ጦርነት፣ የሥለላ ጦርነት፣ የሥነ-ልቦና ጦርነት፣ የኢኮኖሚ ጦርነት ወይም የዲፕሎማሲ ጦርነት ሊሆን ይችላል፡፡ ሃገሮችና መንግሥታት ጥይት ሳይታኮሱ ከላይ በተጠቀሱት መንገዶች ጦርነት ሊከፍቱ፣ በቃላት ሊጠዛጠዙ ይችላሉ፡፡ ስለዚህ እኛም የተገለጠ ውጊያ ላይ ባልሆንበትም ጊዜ እንኳን ከመንፈሳዊ ጠላቶቻችን ጋር ዘወትር ጦርነት ላይ እንደሆንን ልናስተውል ይገባል፡፡ ምክንያቱም እግዚአብሔር አስቀድሞ የደነገገውና የወሰነው ሊታረቅ የማይችል ጠላትነት በመካከላችን አለና፡፡[313]

መንፈሳዊ ጠላቶቻችን እኛን፣ ኃይልና ክብር ከሞላበት ከዘላለማዊ ርስታችን ለማፈናቀል ከሚጠቀሙባቸው ሁለት ሥልቶች መሃል አንደኛውና የመጀመሪያው "ቀዝቃዛው ጦርነት" ነው፡፡ ይህንን ነው ጳውሎስ "የዲያቢሎስ ሸንገላ" የሚለው፡፡ ሸንገላ የሚለውን ሃሳብ ለመግለፅ የተጠቀመበት «ሜቶዲያ» የሚለው የግሪክ ቃል ትኩረት የሚስብ ነው፡፡ "ሜተድ" በአማርኛ "ዘዴ" ወይም "ረቂቅ ሥልት" ለሚለው አቻ የሆነ የእንግሊዘኛ ቃል ሲሆን የተወረሰው «ሜቶዲያ» ከሚለው ሥርወ ቃል ነው፡፡ ሜቶዲዮ ለሚለው የግሪክ ቃል የምናገኝለት ሌላ አቻ «ስትራቴጂም» የሚለው ነው፡፡ እነዚህ ቃሎች ረቂቅ ተንኮልን፣ መሠሪነትን፣ በማባበልና በማታለል የሚፈፀም ክፋትን የሚያመለክቱ ናቸው፡፡[314]

ጠላቶቻችን ጦርነቱን በሸንገላ እንጂ በውጊያ አይጀምሩም፡፡ ጦርነቱም የሚጀመረው ሰላም በሚመስል፣ ነገር ግን ሰላም በራቀው የቀዝቃዛ ጦርነት የማንበርከኪያ ስልት ነው፡፡ ሸንገላው በዚሁ መልዕክት ውስጥ እንደምንመለከተው ጠላት የተለያዩ ሰዎችን በመጠቀም ወደ ቅዱሳን የሚያመጣው አታላይ የክፋት

[313] ዘፍ. 3፡15

[314] Wuest S. Kenneth, Ephesians and Colossians in the Greek New Testament, Eerdmans publishing 1953. P. 141



For more books www.amharicchristianbooks.com

ሃሳብ እንደሆነ መመልከት እንችላለን፡፡ ይህም በሁለት ይከፈላል፡፡ አንደኛው ቀደም ሲል በመሃከላችን ሾልከው ስለሚገቡ የስህተት አስተማሪዎች *«እንደ ስህተት ሽንገላ ባለ ተንኮል በሰዎችም ማታለል ምክንያት በትምህርት ነፋስ ሁሉ እየተፍገመገምን ወዲያና ወዲህም እየተንሳፈፍን . . . »* (4፡ 14) በማለት የጠቀሰው ሲሆን፣ ሁለተኛው ሽንገላ ደግሞ ኑሯችንን የሚበርዝ የዝሙትና የርኩሰት ሽንገላ መሆኑን *«ይህን እወቁ አመንዝራም ቢሆን ወይም ርኩስ ወይም የሚመኝ እርሱም ጣዖትን የሚያመልክ በክርስቶስና በእግዚአብሔር መንግሥት ርስት የለውም፡፡ ከዚህ የተነሳ በማይታዘዙት ልጆች ላይ የእግዚአብሔር ቁጣ ይመጣልና ማንም በከንቱ ንግግር አያታላችሁ፡፡»* (5፡ 6) በማለት ገልፆታል፡፡ እነዚህ ሁለት ሽንገላዎች አንደኛው የትምህርት፣ ሌላኛው ደግሞ የኑሮ መሆናቸውን ልብ ይሏል፡፡ እንዲህ የሆኑትም ያለ ምክንያት አይደለም፡፡ ትምህርት የኑሮ መሠረት ነው፡፡ ጤናማ ሥነ-መለኮት ከሌለ፣ ጤናማ ሥነ-ምግባር ከየትም ሊመጣ አይችልም፡፡ ስለዚህ ቀዝቃዛው ጦርነት የሚጀምረው ትምህርታችንንና ኑሮአችንን ከመበረዝና ከመመረዝ ነው፡፡

ለዚህ አልበገር ስንልና ፀንተን ስንቃወም ቅዝቃዜው ወደ ትኩሳት ይለወጣል፡፡ ጦርነቱ በውጊያ ይግላል፡፡ ጠላት በተቃውሞ የጥፋት ድግስ ይደግሳል፡፡ የሽንገላ ሥልቱ ቢሠራለትና ቢሰምርለት ኖሮ በቀላሉ አንበርክኮናልና ሌላ የጦር ሥልት መንደፍ ባላስፈለገው ነበር፡፡ አሁን ግን በማታለል ያልተሳካለትን በኃይል ለማግኘት ጦር ይሰብቃል፣ ቀስት ይገትራል፡፡ ጳውሎስ ይህን የውጊያ ወቅት «ክፉው ቀን» (6፡13) ብሎ ይጠራዋል፡፡ ይህ አጠራር (በተለይ በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን አማኞች ላይ) ስለ ክርስቶስ ስም ይደርስባቸው የነበረውና እንደ ሰደድ እሳት ከሥፍራ ሥፍራ ይቀጣጠል የነበረውን የተቀናጀ ስደት የሚያመለክት ነው፡፡ ይህም ስደት መልኩ ይለዋወጥ እንጂ እያለፈ በየዘመናቱ ያቆጠቁጣል፡፡ ዘመኑ እንጂ ጠላታችን መች ተለወጠና!



For more books www.amharicchristianbooks.com

# ምዕራፍ ፲፪
# የጦር ዕቃ

ኤፌ. 6፡ 11 - 17

## የእግዚአብሔር የጦር ዕቃ

በሸንገላውም ወቅት ሆነ ስደት በሚነሳበት በክፉ ቀን፣ ሁሉንም አሸንፈን በፅናት እንድንቆም የሚያስችለን የምንለብሰው የጦር ዕቃ ነው፡፡ *«የዲያቢሎስን ሽንገላ ትቃወሙ ዘንድ እንዲቻላችሁ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ልበሱ . . . ስለዚህ በክፉው ቀን ለመቃወም ሁሉንም ፈፅማችሁ ለመቆም እንድትችሉ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ አንሱ፡፡»* ይለናልና፡፡ ከዚህም በመነሳት በስውር ሽንገላው ወቅት የጦር ትጥቅ «መልበስ»፣ በፊት ለፊት ተቃውሞው ቀን ደግሞ የጦር ዕቃ «ማንሳት» እንደሚያስፈልግ እንመለከታለን፡፡ ይህም የጦር ዕቃው ሁሌም የሚለበሱና በውጊያ ቀን ብቻ የሚነሱ ሁለት ክፍሎች እንዳሉት ያሳየናል፡፡ የሐሰት ትምህርትን የምንቃወምበት የእውነት መታጠቂያ፣ የርኩሰትን ኑሮ አሻፈረኝ! የምንልበት የጽድቅ ጥሩር፣ ከተጠራንበት ከዋናው ጦርነት የሚያዘናጋንን የእርስ በርስ ጦርነትን እምቢ! የምንልበት የሰላም ጫማ፣ ሁል ጊዜ ከላያችን የማይወልቁ የሰርክ ትጥቆቻችን ሊሆኑ ይገባቸዋል፡፡ የእምነት ጋሻ፣ የመዳን ራስ ቁርና የመንፈስ ሰይፍ ግን ግልፅ ውጊያ በሚከፈትበት፣ ከውጭ ተቃውሞ በሚገነበት በሰልፍ ቀን ብቻ የምናነሳቸው የጦር ትጥቆቻችን ናቸው፡፡

የእግዚአብሔር የጦር ዕቃ ስሙ እንደሚገልጠው እግዚአብሔር ራሱ በጦርነት ቀን የሚለብሰው የጦር መሣሪያ ነው፡፡ "እግዚአብሔር የጦር ዕቃ ይለብሳል እንዴ?" ለሚል "እግዚአብሔር ተዋጊ ነው፣ ስሙም እግዚአብሔር ነው" የሚለውን ማንበብ ብቻ በቂ ይሆናል፡፡[315] በእርግጥ እግዚአብሔር የጦር ልብስ ይለብሳል፡፡ ይህንንም የትንቢተ ኢሳያስ ሁለት ክፍሎች በግልፅ ያሳዩናል፡፡ ኢሳይያስ ስለ ክርስቶስ በጻፈበት መሢሃዊ የትንቢት ክፍል ክርስቶስ ከእሴይ የዘር ግንድ እንደሚመጣ ከተናገረና የእግዚአብሔር መንፈስ እንደሚያርፍበት ከገለፀ በኋላ ፡-

> *"በአፉ በትር ምድርን ይመታል በከንፈሩም እስትንፋስ ክፉዎችን ይገድላል፡፡ የወገቡም መታጠቂያ ጽድቅ የጐኑም መቀነት ታማኝነት*

---

[315] ዘፀ. 15፡3



For more books www.amharicchristianbooks.com

*ይሆናል፡፡"* (ኢሳ. ፲፩:4፣5)

በማለት የጦርነትና የሰልፍ ቃላትን በመጠቀም ስለ መንፈሳዊ ውጊያ ይፅፋል፡፡ በመቀጠልም በምድር ላይ ፍርድ እንደሌለ፣ ወደርሱም የሚማልድ ሰው እንደሌለ ተመልክቶ እንዳዘነና በጠላቶቹ ላይ ሊዘምት እርሱ ራሱ የጦር ዕቃ ለብሶ ወደ ሰልፍ እንደገባ ሲገልፅ፡-

> *". . . ስለዚህ የገዛ ክንዱ መድኃኒት አመጣለት ጽድቁም አገዘው፣ ጽድቅንም እንደ ጥሩር ለበሰ፣ በራሱም ላይ የማዳንን ራስ ቁር አደረገ፣ የበቀልንም ልብስ ለበሰ፣ በቅንዓትም መጐናፀፊያ ተጐናፀፈ፡፡" ኢሳ. 59:16-17*

በማለት ለባላጋራዎቹ እንደ ሥራቸው መጠን ቁጣንና ፍዳን እንደከፈለ ይፅፍልናል፡፡ ስለዚህ ጌታ ራሱ በኢሳ. 59፡ 16-17 እና በኢሳ. ፲፩:4-5 ላይ የለበሰውን የጦር ዕቃ እኛም በዚህ የፍፃሜ ጦርነት ላይ እንድንለብስ እንደተሰጠን እንመለከታለን፡፡ ለመሆኑ የእውነት መታጠቂያ፣ የፅድቅ ጥሩር፣ የሰላም ጫማ፣ የእምነት ጋሻ፣ የመዳን ራስ ቁር፣ የመንፈስ ሰይፍ በሚል የተመሰለው ይህ ልብስ ምንድን ነው? ማን ነው? በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በልብስ የተመሰለውና እንድንጎናፀፈው የተሰጠን መንፈስ ቅዱስ ነው፡፡ ለምሳሌ ጌታ ኢየሱስ ወደ ሰማይ ከማረጉ ከጥቂት ጊዜያት በፊት ለደቀ መዛሙርቱ «እነሆም አባቴ የሰጠውን ተስፋ እኔ እልክላችኋለሁ፤ እናንተ ግን ከላይ ኃይልን እስክትለብሱ ድረስ በኢየሩሳሌም ከተማ ቆዩ፡፡» (ሉቃስ 24፡ 49) በማለት ከጥቂት ቀናት በኋላ የሚለብሱት ኃይል ፅድቅ፣ ሰላም፣ እምነት፣ መዳንና የመንፈስ ሰይፍ የሆነው የእግዚአብሔር ቃል ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ፣ በምድር ኑሮው በዕለት ተለት ገድሉ ውስጥ የለበሰው መንፈስ ቅዱስ እንደሆነ ይጠቁመናል፡፡ ጌታ የለበሰውን ስንለብስ የለበስነው ራሱ ጌታን እንጂ ሌላ ሊሆን አይችልም፡፡ ጌታና የጌታ መንፈስ አንድም ሁለትም ናቸውና፡፡ ጳውሎስ በሌላ መልዕክቱ *"እንግዲህ የጨለማውን ሥራ አውጥተን የብርሃንን ጋሻ ጦር እንልበስ፡፡ . . . ጌታን ኢየሱስ ክርስቶስን ልበሱት . . . .፡፡"* ሮሜ 13:12-14 በማለት ጽፏል፡፡ መቼም በአባቱ ቀኝ የከበረውን ጌታ ኢየሱስን በአካል ልንለብሰው እንደማንችል የታወቀ ነው፡፡ ልንለብሰው የምንችለው ከእርሱ በሚፈልቅ በእኛም ውስጥ በሚያድር በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ብቻ ነው፡፡ ከእግዚአብሔር ዘር በመንፈስ ስንወለድ እነዚህን የጦር ዕቃዎች ይዘን መወለዳችንን የምንረዳው « . . . ለእውነት በሚሆኑ ጽድቅና ቅድስና እንደ እግዚአብሔር ምሳሌ የተፈጠረውን አዲሱን ሰው ልበሱ» 4:24 የሚለውን ቃል ስናነብ ነው፡፡ ስለዚህ እውነት፣ ፅድቅና ቅድስና በሕይወት የተሰጡን ከላያችን የማይወልቁ ትጥቆቻችን ናቸው፡፡ ይህም ሕይወት መንፈስ ቅዱስ መሆኑን አስቀድመን አስረግጠናል፡፡ ከዚህ



For more books www.amharicchristianbooks.com

በመነሳት የምንለብሰውም ሆነ የምናነሳው የጦር መሣሪያችን ራሱ እግዚአብሔር እንደሆነ በድፍረት መናገር እንችላለን፡፡ ለዚህ አባባል እርግጠኛ ለመሆን ተጨማሪ መረጃ ካስፈለገ የጦር መሳሪያዎቹን ዝርዝር መመልከት በቂ ይሆናል፡፡ እውነታችን፣ ጽድቃችን፣ ሰላማችን፣ እምነታችን፣ መዳናችን ከጌታ በቀር ማን ሊሆን ይችላል? በዚህ ስፍራ የእምነትን ጋሻ እንድናነሳ ታዘናል፡፡ በሌላ ስፍራ ደግሞ እግዚአብሔር ለአብርሃም *« . . . እኔ ለአንተ ጋሻህ ነኝ . . . »* (ዘፍ. 15፡ 1) ሲለው እናያለን፡፡ ሙሴም እስራኤልን *"እስራኤል ሆይ ምስጉን ነህ! በእግዚአብሔር የዳነ ሕዝብ እንደ አንተ ማን ነው? እርሱ የረድኤትህ ጋሻ የከፍተኛነትህም ሰይፍ ነው፡፡ ጠላቶችህም ይገዙልሀል፣ አንተም ከፍተኛውን ትረግጣለህ፡፡"* ዘዳ 32፡29 በማለት እግዚአብሔር የሕዝቡ የጦር ልብስ እንደሆነ በግልፅ ጽፏል፡፡ ዳዊትም ሲዘምር «እግዚአብሔር ኃይሌና ጋሻዬ ነው . . . » መዝ. 28፡7 ብሏል፡፡ በብሉይ ኪዳን መጻህፍት ብቻ እግዚአብሔር ለሕዝቡ በጦርነት መሃል ጋሻና መከታ መሆኑን የሚገልፁ በርካታ ክፍሎች እናገኛለን፡፡[316] ለዚህ ነው በድፍረት "መንፈስ ቅዱስ የጦር፣ የኃይል፣ የክብርና የማዕረግ ልብሳችን ነው" የምንለው፡፡

ወታደር ለሰልፍ እንዲከት ሲታዘዝ ማቄን ጨርቄን ሳይል ራሱን ሰጥቶ ይወጣል፡፡ ወታደር ራሱን እንዲሰጥ እንጂ ራሱን እንዲያስታጥቅ አይጠበቅበትም፡፡ ይህ ኃላፊነት ለጦር ያስከተተው አካል ነው፡፡ እግዚአብሔርም የጦር ዕቃ እንድናመርት አልጠየቀንም፡፡ እነሆ መንፈሱን የጦር ዕቃ አድርጎ ሰጥቶናል፡፡ በእምነት መቀበል፣ በትጋት መልበስና በጽናት መዋጋት ግን የእኛ ድርሻ ነው፡፡

ይህንን መልዕክት ከሮም እስር ቤት የሚጽፍልን ጳውሎስ በዙሪያው ያሉትን የሮም ወታደሮች ትጥቅ በምሳሌነት በመጠቀም በጊዜውም አለጊዜውም ተዘጋጅተን በመያዣነት ከተሰጠን ርስት ሊያፈናቅሉን የሚመጡትን ጠላቶቻችንን እየተቃወምን በንቃት እንድንጠብቅ በዝርዝር ይጽፍልናል፡፡

የልብ ወገባችንን እንድንታጠቅበት የተነገረን እውነት አስቀድሞ በወንጌል የተሰበከነው፣ (1፡13) ከክርስቶስ የተማርነው፣ (4፡21) ከቅዱሳን ጋር በፍቅር እንድንነጋገረው የታዘዝነው፣ (4፡15) በብርሀን በመመላለስ በፍሬ እንድንገልፀው የተነገረን (5፡8)፣ ከእውነት መንፈስ የሚፈልቅ የእውነት ቃል ነው፡፡ ይህንን ነው ቀበቶ በሰው ወገብ እንደምትጣበቅ ከሕይወታችን ጋር እንድናጣብቀው የታዘዝነው፡፡ በዚህ ጦርነት ውስጥ እውነትን መታጠቅ ያስፈለገን ጠላቶቻችን

[316] መዝ 18፡2፣ 46-48; 35፡3; 37፡39፣ 40; 65፡5; 70፡4፣ 5; ኢሳ 33፡2፣ 6; 45፡17; 46፡13; 51፡5፣ 6; ኤር 31፡33



For more books www.amharicchristianbooks.com

ሐሰትን ታጥቀው ስለሚመጡ ነው፡፡ የአስራ ሰባተኛው ክፍለ ዘመን የፒዩሪታንስ አስተማሪ የነበረው ዊሊያም ገርኔል ስለ አማኞች የጦር ትጥቅ በጥልቀት በዘረዘረበት የዳጎሰ መጽሐፉ እውነትን በሁለት ከፍሎ ያየዋል፡፡ አንደኛው ከትምህርት (ዶክትሪን) አንፃር፣ ሁለተኛው ከልብ ቅንነት አንፃር፡፡[317] እነዚህ ሁለቱ ሊፋቱ የማይችሉ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገፅታዎች ናቸው፡፡

የተገለጠልንን እውነት በንፁህ ልብ ካልያዝነው ወገባችንን በሚገባ አልታጠቅንም ማለት ነው፡፡ «ሲሮጡ የታጠቁት ሲሮጡ ይፈታል» እንደሚለው ብሂል በሰልፍ መሃል ትጥቃችን እንዳይላላ በሁለቱም አቅጣጫ ወገባችንን ጠበቅ ልናደርግ ይገባናል፡፡ የሥጋ ወገቤን አጥርቼ አውቀዋለሁ፣ መንፈሳዊ ወገቤ ግን የቱ ጋ ነው? ብለን እንጠይቅ ይሆናል፡፡ ጴጥሮስ ለጥያቄያችን ፍቱን መልስ አለው፡፡ «ስለዚህ የልቦናችሁን ወገብ ታጥቃችሁ . . .» 1ጴጥ. 1፡ 13 ይለናል፡፡ ጴጥሮስ ይህንን አገላለፅ «ወገባችሁ የታጠቀ መብራታችሁም የበራ ይሁን . . . » ሉቃ. 12፡ 35 ከሚለው የጌታ ትምህርት የወሰደው ይመስላል፡፡ አማርኛው ልቦና የሚለውን፣ ሌሎች ትርጉሞች ሁሉ አዕምሮ ብለው ይተረጉሙታል፡፡ ዳሩ እውነትን የምንታጠቀው ከአዕምሮአችን ውጭ የት ሊሆን ይችላል?

ጥሩር ደረትን የሚሸፍን የመከላከያ መሣሪያ ነው፡፡ ደረት በውስጡ የያዛቸው ስስ ብልቶች በሕይወት ለመኖር እጅግ አስፈላጊዎቻችን ስለሆኑ በጎድን አጥንት ታጥረዋል፡፡ በዚህም ምን ያህል እንክብካቤ ልናደርግላቸው እንደሚገባ ተፈጥሮ ራሱ ያስተምረናል፡፡ ልክ እንዲሁ የሕይወት መውጫ የሆነውን ልባችንን እንድንጋርድበት ፅድቅ እንደ ጥሩር ተሰጥቶናል፡፡ ይህም ጽድቅ እንደ እግዚአብሔር ምሳሌ የተፈጠረው የአዲሱ ሰው ባህሪና (4፡24) ከብርሃናት አባት በመቀበል የምንገልጠው የብርሃን ፍሬ ነው(5፡9)። ይህንንም ጽድቅ በሁለት ከፍለን ልናየው እንችላለን፡፡ የፀጋ ጽድቅና የሥራ ጽድቅ በሚል፡፡ እነዚህን ሁለት የጽድቅ ገጽታዎች መነጣጠል አንችልም፡፡ አንደኛው ከሌለ ሌላኛው ሊኖር አይችልምና፡፡ ነገር ግን የፀጋን ጽድቅ በእምነት ሳንቀበል ዘለን ወደ ሕግ ጽድቅ በማምራት በወግ አጥባቂነትና በሕግ አክራሪነት ወጥመድ እንዳንወድቅ ልንጠነቀቅ ይገባናል፡፡ በሌላም ጽንፍ በጸጋ ጸድቀናል እያልን፣ ጸጋን የኃጢያት መንጃ ፈቃድ አድርገን ወደ ሞት ልንጋልብ አይገባም፡፡ ይልቅ በእምነት ዳግም በመወለድ ያገኘነውን የጽድቅ ባህሪ እለት ተለት በመለማመድና ኃጢያትን በማንኛውም መልኩ በመቃወም በጽድቅ እየተመላለስን፣ ሕይወታችንን ከአመፅ ጥቃት ልንከላከል ይገባናል፡፡

[317] William Gurnall, The Christian in Complete Armor, P.



For more books www.amharicchristianbooks.com

እንደ ጫማ እንድንጫማውና የአመፅ እሾህንና ቆንጥር እንድንረጋግጥበት የታዘዝነው የሰላም ወንጌል፡- ከአብ ፣ ከወልድ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ወደኛ የሚወርድ (1፡2) በክርስቶስ ሞትና ትንሳኤ ልዩነትን በማስወገድ፣ አይሁድንና አሕዛብን አንድ ያደረገ (2፡15)፣ እኛም በትህትና በየዋህነት በትዕግሥት በመመላለስ የምንጠብቀው (4፡3)፣ እርሱ ራሱ ክርስቶስ የሆነ የሰላም የምስራች ነው (2፡14)፡፡ ይህንንም የሰላም ወንጌል ተጫምተን በመዘጋጀት፣ በፅናት ስፍራችንን ሳንለቅ እንድንቆም ታዘናል፡፡ ሰላምን በአራት አቅጣጫዎች ከፍለን ልናየው እንችላለን፡፡ አንደኛው ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ሰላም ነው፡፡ ይህም ዕርቅን ያመለክታል፡፡ ሁለተኛው ከራሳችን ጋር ያለው ሰላም ነው፡፡ ይህም ንፁህ ሕሊናን ያመለክታል፡፡ ሦስተኛው በዙሪያችን ካሉ ሰዎች ጋር የሚኖረን ሰላም ነው፡፡ ይህም ፍቅርና አንድነትን ያመለክታል፡፡ የመጨረሻውና አራተኛው በዙሪያችን ካለው ፍጥረት ጋር የሚኖረን ሰላም ነው፡፡ ይህም ባለአደራነትንና መጋቢነትን ያመለክታል፡፡ ለእነዚህ ሁሉ የሰላም አቅጣጫዎች መሠረቱ ክርስቶስ ነው፡፡ ሆኖም በዚህ ክፍል እንደ ጦር ትጥቅ የተጠቀሰው ሰላም በዋነኝነት በዙሪያችን ካሉ ወገኖች ጋር የሚኖረንን ጤናማ ግንኙነት አጉልቶ የሚያሳይ ነው፡፡ በቀደሙት ክፍሎች ውስጥ እንዳየነው እግዚአብሔር የጠራንና በመንፈሱ አንድ ያደረገን ከተለያየ ነገድ፣ ቋንቋና ባህል ነው፡፡ ስለዚህ ጠላት ሰልፉን ለመበተን፣ እኛ እርስ በርሳችን በነገር ስንጠዛጠዝ፣ በረከታችንን ለመዝረፍ፣ የልዩነት ቀዳዳዎችን ተጠቅሞ መርዛማ ፍላፃዎቹን ይወነጭፋል፡፡ ታዲያ፣ እኛም የሰላምን ወንጌል በመጫማት በደረስንበት ሁሉ በወንጌል የተገኘውን ሰላም እያበሰርን ልንመላለስ ይገባናል፡፡

በክፉው ቀን እንድናነሳው የታዘዝነው የእምነት ጋሻ ጳውሎስ የሚፅፍላቸው ወገኖች በውስጣቸው እንዳለ ሰማሁ የሚለው (1፡15)፣ እኛም የእግዚአብሔርን የማዳን ፀጋ የተቀበልንበት (2፡8)፣ በክርስቶስ ሥራ ወደ አብ ለመግባት ድፍረት ያገኘንበት (3፡12)፣ ክርስቶስ በልባችን እንደሚኖር እርግጠኛ የምንሆንበት (3፡17)፣ ለቅዱሳን ሁሉ አንድ ጊዜ ፈጽሞ የተሰጠ (4፡5)፣ እምነት ነው፡፡ እምነት በሕይወት ለመኖር ዘወትር የሚያስፈልገን ቢሆንም እንኳ፣ ስደት በሚታወጅባቸው ሁሉ በእኛ ላይ በሚነሳበት፣ የተለያዩ ልብ-አርድ ወሬዎች ከየአቅጣጫው በሚወረወሩባቸው ክፉ ቀናት፣ እጅግ የሚያስፈልገን የመከላከያ መሳሪያ ነው፡፡ በእንዲህ አይነት ወቅት እግዚአብሔር በቃሉ የነገረን እንጂ በጠላቶቻችን የሚባለው ሁሉ እንደማይሆንብን እርግጠኛ እየሆንን፣ የሚንበለበሉትን የክፉውን ፍላፃዎች ለመመከት የየእምነትን ጋሻ እንድናነሳ ይጽፍልናል፡፡



For more books www.amharicchristianbooks.com

መዳን፣ ያኔ ወንጌል ሲሰብክልን የእውነትን ቃል በመስማት ያገኘነው (1፡13)፣ በእግዚአብሔር ምህረትና ባለጠግነት እንዲሁም ከትልቅ ፍቅሩ መንጭቶ ከሞት ወደ ሕይወት ያሻገረን፣ በጠላት ከመገዛት በቅዱስ ፍቃዱ ወደ መመላለስ ያመጣን፣ ለቁጣ ከመጠበቅ ወጥተን ብዙ ቸርነት እና ከሁሉም የሚበልጠውን የፀጋ ባለጠግነት ለመውረስ ተስፋ መሰነቅ የቻልንበት፣ የእግዚአብሔር ርህራሄ ውጤት ነው (2፡5፣8)። ይህ የመዳን ራስ ቁር በቀጥታ ምንን እንደሚያመለክት ለመረዳት ራሱ ጳውሎስ ስለ ጦር ትጥቅ በጻፈበት ሌላ መልዕክቱ የሰጠውን ትርጉም ማየት እንችላለን፡፡ *« . . . እኛ ግን ከቀን ስለሆንን የእምነትንና የፍቅርን ጥሩር፣ የመዳንንም ተስፋ እንደራስ ቁር እየለበስን በመጠን እንኑር. . . » 1ተሰሎ. 5፡8* በዚህ ክፍል ውስጥ የራስ ቁርን የመሰለው በመዳን ተስፋ ነው፡፡ አዲስ ኪዳን በጥቅሉ እንደሚያስተምረን ድነናል፣ እየዳንን ነው፤ እንድንማለን፡፡ ይህን ለመረዳት በመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ማውጫ ታግዘን በአዲስ ኪዳን ውስጥ ስለ መዳን የሚናገሩትን ክፍሎች ሁሉ ብናወጣና የጊዜ ግሳቸውን ብንመለከት ያላፈ፣ የአሁንና የወደፊት ጊዜ ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡ ከሁሉም የሚበዛው ግን የወደፊቱ ነው፡፡ ባመንን ጊዜ መንፈሳችን ዳግመኛ ተወልዷል፣ ከዳንን በኋላ ዕለት ዕለት በምንኖረው ኑሮ ውስጥ የነፍስ መዳን የሆነውን የአዕምሮ መታደስ እንቀበላለን፣ በመጨረሻም ጌታ በክብር ሲገለጥ ሥጋችንም ይከብርና መጨረሻ ላይ ከሚሻረው ጠላት፣ እርሱም ከሥጋ ሞት፣ ከመበስበስና ከውርደት እንድናለን፡፡

እንግዲህ ይህንን ማሰብ ነው፤ በማንኛውም ጊዜ ከጠላት ጥቃት የሚጠብቀን፡፡ የጠላት ሕልም አዕምሮአችንን በማናወጥ፣ ሀሳባችንን በዓለም ኮተት በመሙላት፣ የተካፈልነውንና፣ ገናም ወደፊት በሙላት የምንካፈለውን ታላቅ መዳን በናፍቆት እንዳንጠብቅ ማድረግ ነው፡፡ እኛ ግን ያለፈውን የመዳናችንን ታሪክና፣ የሚመጣውን የመዳናችንን ተስፋ፣ እንደ ራስ ቁር አጥልቀን ከተዋጋን፣ ጥረቱ ሁሉ ከንቱ ሆነ ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ጳውሎስ በሰልፍ መካከል በማንኛውም መከራና ፈተና ውስጥ ስናልፍ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ከሰማይ ሲገለፅ፣ በሥጋ ትንሳኤ በክብር የምንካፈለውን የመዳን ተስፋ ያለማቋረጥ በአእምሮአችን ልናስብና ልናሰላስል እንደሚገባን ይመክረናል፡፡ ዳሩ ከሙሴ ሞት በኋላ የእስራኤል መሪና የጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥ ሆኖ ለተሾመው፣ ሰባት አሕዛብ፣ ሠላሳ ነገሥታት፣ ከፊቱ ለተደቀኑት ለነዌ ልጅ ለኢያሱ እግዚአብሔር የሰጠው ብቸኛ ምክር፡- *«ባርያዬ ሙሴ ያዘዘህን ሕግ ሁሉ ጠብቅ፣ አድርገውም፣ በምትሄድበት ሁሉ እንዲከናወንልህ ወደ ቀኝም ወደ ግራም አትበል፡፡ የዚህ ሕግ መጽሐፍ ከአፍህ አይለይ፣ ነገር ግን የተፃፈበትን ሁሉ ትጠብቅና ታደርግ ዘንድ በቀንም በሌሊትም አስበው፣ የዚያን ጊዜም መንገድህ ይቀናልሃል ይከናወንልሃልም፡፡»* ኢያሱ 1፡7-8



For more books www.amharicchristianbooks.com

የሚል አልነበረምን?

የእግዚአብሔር ቃል፤ አምነን የዳንበት የምስራች (1፡13)፣ ሁሉን በእግዚአብሔር ሕይወት ስለመጠቅለል ለሐዋርያትና ለነቢያት የተገለጠ ምስጢር (3፡2-6)፣ ቤተ ክርስቲያን ከዕድፈትና ከፊት መጨማደድ ነፅታ እንደ ሙሽራ ቅድስትና ያለ ነውር ሆና ጌታዋን እንድትጠብቅ የሚያነፃት ምንጭ (5:26-28) ነው፡፡

የጠላቶቻችን ምኞት የእምነታችን መሰረት የሆነውን ጤናማ ትምህርት በማጣመም እውነትን በሀሰት መለወጥ ነው፡፡ እውነትን እንደ ወገብ መታጠቂያ ከታጠቅን ግን የጠላት ሙከራ ከሸፈ ማለት ነው፡፡ ምኞቱ በጽድቅ፣ በእውነትና በቅድስና የተሞላውን ኑሮአችንን በኃጢያትና በርኩሰት መንደፍ ነው፡፡ ጽድቅን እንደ ጥሩር ካጠለቅን፣ ድካሙ ከንቱ ሆነ ማለት ነው፡፡ የልቡ ናፍቆት፣ በክርስቶስ የመስቀል ሥራ የፈረሰውን የጥል ግድግዳ እንደ ገና በመገንባት በዓለም ታሪክ፣ ወንጌል ብቻ ሊያመጣው የቻለውን በመንፈስ አንድነት ላይ የተመሰረተ ሰላም ማናጋት ነው፡፡ የሰላምን ወንጌል በማመን፣ በማወቅ እና በመተግበር ተጫምተን ከተመላለስን ግን ጠላት ተሸነፈ ማለት ነው፡፡ እነዚህ የጦር ዕቃዎች በሰርክ የምንለብሳቸው፣ የዲያቢሎስን ሽንገላ ለመቃወም የሚረዱን፣ መከላከል ላይ ያተኮሩ ትጥቆች ናቸው፡፡ ቀጥለው የተዘረዘሩት ደግሞ በውጊያ ቀን ብቻ የሚነሱ ናቸው፡፡ ጸሐፊውም ይህንን ግልፅ ለማድረግ ነው ስለሚለበሱት የጦር ዕቃዎች ከዘረዘረ በኋላ *«በሁሉም ላይ ጨምራችሁ . . . »* በማለት ወደሚነሱት የጦር ዕቃዎች የዘለቀው፡፡ ትጥቆቹ የሚለበሱና የሚነሱ መሆናቸውን ልብ ይሏል፡፡ በውጊያ ቀን የሚነሱት፣ ጋሻ፣ የራስ ቁር እና ሰይፍ ናቸው፡፡

ጠላት ያለ የሌለ ኃይሉን አስተባብሮ ለውጊያ በሚወጣበት በክፉው ቀን ለማጥቃት የሚጠቀምበት አንድ መሣሪያ አለው፡፡ ይህንንም ጸሐፊው «የሚንበለበሉትን የክፉውን ፍላፃዎች» በማለት ይጠራዋል፡፡(ቁ 16) ፍላፃ የሚወረወር ቀስት ሲሆን በዚያን ጊዜ ሥልጣኔ ከዘመናችን ጥይት ጋር የሚመሳሰል የማጥቂያ መሳሪያ ነዉ፡፡ የቀስቱ ጫፍ ተቀጣጣይ መርዝ ውስጥ ይነከርና እሳት ተለኩሶ ይወረወራል፡፡ ቤቶችን ምሽጎችን ብሎም የተወረወረበትን ሰው ያቃጥላል፡፡ እነዚህ ፍላፃዎች በስደት ወቅት ጠላት የራሱን ሰዎች አንደበት በመጠቀም የሚያዘንበው የዛቻና የማስፈራራት ወሬ ነው፡፡ ነገር ግን አማኞች ያለ ፍርሃትና ያለ መናወጥ በእግዚአብሔር ላይ ያለንን ፅኑ እምነት እንደ ጋሻ ካነሳን ድካሙ ሁሉ ከንቱ ይሆናል፡፡

የሮም ወታደሮች በጦር አውድማ ላይ የሚያነግቱት ጋሻ ከእንጨት የተሰራና ፊት



For more books www.amharicchristianbooks.com

ለፊቱ በወፍራም ቆዳ የተለበጠ፣ ቁመቱ 1.2 ሜትር፣ የጐን ስፋቱ ደግሞ 0.8 ሜትር፣ ባጭሩ መለስተኛ በር የሚያክል የጦር ትጥቅ ነው፡፡ ታዲያ ከጠላት ሰፈር የሚዘንበውን በእሳት የተለኮሰ ቀስት መከላከል እንዲችል ከጦርነት በፊት በውሃ ተዘፍዝፎ ያድራል፡፡ የሚንበለበለው ፍላፃ በረጠበው ቆዳ ላይ በሚያርፍበት ጊዜ ወዲያውኑ ይጠፋል፡፡ ይህንን ጋሻ ይዞ በጽናት የቆመ ወታደር የጠላት ፍላፃ እንደ ዝናብ ቢወርድም ከርዝመቱና ከስፋቱ የተነሳ የትኛውንም የሰውነት ክፍሉን ሊያገኘው አይችልም፡፡ የጦር ዕቃዎቹን በአግባቡ የለበሰና ያነገበ ወታደር ለጥቃት የሚጋለጥ ምንም ክፍተት አይኖረውም፡፡[318]

በመቀጠልም የተጠቀሱት የጦር ዕቃዎች ከእምነት ጋሻ ጋር የሚነሱት የራስ ቁርና የመንፈስ ሰይፍ ናቸው፡፡ የጦር መሳሪያዎቹ የሚደረጉት በተጋዳዩ ስስ ብልቶች ላይ መሆኑን ልብ ልንል ያስፈልጋል፡፡ ለደረት ጥሩር፣ ለእግር ጫማ ፣ ለወገብ መታጠቂያ፣ ለራስ ከነሃስ የሚሠራ ቁር በምሳሌነት ሲታዘዝ እናያለን፡፡

ከጦር መሣሪያዎቻችን መሃል በመጨረሻ የተጠቀሰው የመንፈስ ሰይፍ ነው፡፡ አሁን ጸሐፊው ከመከላከል ወደ ማጥቃት፣ ለግራ ከሚሆን የጦር ዕቃ (ጋሻ) ለቀኝ ወደሚሆን የጦር ዕቃ (ሰይፍ) ዘወር እንዳለ እንመለከታለን፡፡[319] በዚህ የእምነት ገድል ውስጥ ብቸኛ ማጥቂያችን የመንፈስ ሰይፍ ነው፡፡ ትርጓሜውም «የእግዚአብሔር ቃል ነው» የእግዚአብሔር ቃል መንፈስ ነው (ዮሐ. 6፡63)፤ ሥራውም ቅልጥምንና ጅማትን፣ መንፈስንና ነፍስን በመለየት የተሰወረውን ሁሉ መግለጥ ነው፡፡ (ዕብ 4፡ 12፣13) ይህን ሰይፍ አስቀድሞ የምናየው ከጌታ ኢየሱስ አፍ ሲወጣና ጠላቶቹን ሁሉ ሲያጠፋ ነው (ኢሳ 11፡4; ራዕይ 1፡16)። አሁን ደግሞ በእኛ እጅ ተገኝቷል፡፡ ከሰገባው የተመዘዘ ሰይፍ የተገለጠ ቃልን ያመለክታል፤ በሥራ ላይ ሲውል መንፈስ የሆኑትን ጠላቶች ይቆራርጣል፡፡ ጌታ ኢየሱስ አገልግሎቱን ከመጀመሩ አስቀድሞ በምድረ በዳ በዲያቢሎስ ሲፈተን ድል የነሳው የማይታይ የመንፈስ ሰይፍ የሆነውን የእግዚአብሔርን ቃል በመምዘዝ ነበር፡፡ ለእኛም በዚህ ገድል ቀዳሚ የሆነው የጦር አዝማቻችን ከተጠቀመበት ውጭ ሌላ የማጥቂያ መሣሪያ ሊኖረን አይችልም፡፡

ሠይፍ የሩቅ ሳይሆን የቅርብ፣ የፊሪ ሳይሆን የጀግና መሣሪያ ነው፡፡ ፍላፃ የሚወረውር ምሽግ ይዞ ተደብቆ ሊወረውር ይችላል፣ ሰይፍ የታጠቀ ግን ከሩቅ ሆኖ አንዳች ሊያደርግ አይችልምና ራሱን በጦር ልብሶቹ ከልሎ በድፍረት ወደ

[318] (Keener, 1993) page 554
[319] 2ቆሮ 6፡7



For more books www.amharicchristianbooks.com

ጠላቱ ምሽግ ይተማል፡፡ በእግዚአብሔርም ቃል ምሽግ ያፈርሳል፤ ጠላቱንም ይበቀላል፡፡ ጳውሎስም ይህንኑ የእግዚአብሔር ቃል ነው እያቆለጳጰሰ *«በሰው ልማድ ምንም እንኳ የምንመላለስ ብንሆን በሰው ልማድ አንዋጋም የጦር ዕቃችን ሥጋዊ አይደለምና ምሽግን ለመስበር ግን በእግዚአብሔር ፊት ብርቱ ነው፡፡ የሰውን ሃሳብ በእግዚአብሔርም ዕውቀት ላይ የሚነሳውን ከፍ ያለውን ነገር ሁሉ እናፈርሳለን ለክርስቶስ ለመታዘዝ አዕምሮን ሁሉ እንማርካለን . . . »* (2ቆሮ 10፡ 3-6) የሚለው፡፡ መንፈስ ቅዱስ በጊዜው የሚሰጠን የእግዚአብሔር ቃል በአንድ ጊዜ ሁለት ሥራዎችን ይሠራል፣ በእምነት ስንናገረው መንፈስ የሆኑትን ጠላቶቻችንን ከመጣሉ ባሻገር፣ የሚሰሙትን ሰዎች ልብ ያቀልጣል፣ በውስጣቸውም የተሰወረውን በመግለጥ ወደ ንስሐ ያመጣቸዋል፡፡ የዚህ ጦርነት ዓላማ የጠላትን ጥቃት መከቶ በጽናት በመቆም በርስታችን ላይ ያለንን መብት ማስከበር ብቻ ሳይሆን፣ በጠላት ወጥመድ ተይዘው በሙሃሪያነት ሲያገለግሉ የነበሩትን ነፃ በማውጣት ምርኮ መበዝበዝ ነው፡፡

## ጠላትን መቃወም

የእግዚአብሔርን የጦር ዕቃ እንድንለብስ ተምረናል፡፡ ነገር ግን የጦር ዕቃው ምን እንደሆነ ማወቁ ብቻውን የጦር ዝግጅታችንን ሙሉ አያደርገውም፡፡ ለምን እንድንለብሰው እንደተፈለገ ዓላማውን ማወቅ ግድ ይላል፡፡ ጳውሎስ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር የምንለብስበትን ዓላማ ሲጽፍ *"የዲያቢሎስን ሽንገላ **ትቃወሙ** ዘንድ እንዲቻላችሁ . . . በክፉ ቀን **ለመቃወም** ሁሉንም ፈፅማችሁ ለመቆም እንድትችሉ . . . "* በማለት በማያሻማ ሁኔታ በግልፅ አስቀምጦታል፡፡ ባጭር ቃል የጦር ልብሱ ዓላማ "ጠላትን መቃወም" ነው፡፡ ታዲያ የዲያቢሎስን ሽንገላና ማስፈራራት የምንቃወመው እንዴት ነው? በድምፅ? በጩኸት? በኃይል በመገሰፅ? አይደለም! ክፍሉ "በመልበስ" እንደ ሆነ ይነግረናል፡፡ ይህ ርዕሰ ጉዳይ በመንፈሳዊ ውጊያ ስኬታማ ለመሆን የምንናፍቅ ሁላችን እንደገና በጥሞና ልናየውና በድፍረት ልንወያይበት የሚገባ ጉዳይ ይመስለኛል፡፡

እንደ ጳውሎስ አፃፃፍ ዲያቢሎስን የምንቃወመው የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር በመልበስና በማንሳት እንጂ በሚያስገመግም ድምፅ ያለማቋረጥ በመገሰፅ አይደለም፡፡ ዳሩ ዲያቢሎስ ለእኛ ድምፅ ምን ቁብ አለውና! የምንጠራው የጌታ ስም ቢሆንም፣ የሚሰራው ከሕይወታችን ጋር በተያያዘ እንጂ በከንቱ ደጋግመን



For more books www.amharicchristianbooks.com

በመጥራታችን አይደለም፡፡[320] በጳውሎስም ሆነ በተቀሩት የአዲስ ኪዳን መልዕክቶች ውስጥ "መቃወም" የሚለውን ቃል ስናጠና የምናገኘው አንድ እውነት ነው፡፡ እንድንቃወም የታዘዝነው በራሳችንም ሆነ በሌሎች ውስጥ በሥጋ አድሮ የሚገለጠውን የክፉውን ሃሳብ እንጂ፣ አይኑ በርበሬ፣ ፀጉሩ ጨበሬ የሆነ ጭራቅ አይደለም፡፡[321] የጠላት መሳሪያ "ሐሳብ" ከሆነ ሐሳብን የምንቃወመው በሐሳብ እንጂ በድምፅ ሊሆን አይችልም፡፡ የልብ አይናችን በርቶ ብናስተውል የምንቃወመው ነገር ያለው አየር ላይ ሳይሆን በሥጋዊ አዕምሮ ውስጥ የተመሸገ የጠላት ሃሳብ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡[322]

ለምሳሌ የጌታ ወንድም ያዕቆብ በመልዕክቱ ውስጥ "እንግዲህ ለእግዚአብሔር ተገዙ ዲያቢሎስን ግን ተቃወሙ . . . " ያዕ.4፡7 ብሎ ጽፏል፡፡ የአሁን ዘመን አንባቢ ይህን ጥቅስ ሲያነብ ፈጥኖ ወደ አዕምሮው የሚመጣው በብርቱ ድምፅ መገሰፅ ነው፡፡ በመንፈስ አፍ የፈታበትና ጡት የጣለበት ልምምድ ሊሆን ስለሚችል እንዲህ ማሰቡ አያስደንቅም፡፡ ነገር ግን ክፍሉን በጥሞና በማንበብ መልዕክቱ የሚጻፍላቸው ወገኖች ዲያቢሎስን መቃወም ለምን አስፈለጋቸው? ብለን አንጠይቅም፡፡ መቃወም ያስፈለጋቸው ዲያቢሎስ ስለ ቀረባቸው ነው፣ ለእግዚአብሔር መገዛት ያስፈለጋቸው እግዚአብሔር ስለ ራቃቸው ነው፡፡ የራቃቸው እግዚአብሔር ይቀርባቸው ዘንድ፣ የቀረባቸውም ዲያቢሎስ ይርቃቸው ዘንድ ለእግዚአብሔር መገዛት፣ ዲያቢሎስንም መቃወም አስፈልጓቸዋል፡፡ ይህ እንዴት ሊሆን ቻለ ብንል፣ ክፍሉ ራሱ መልሱን ይቸረናል፡፡ ያዕቆብ "በእናንተ መካከል ያለው ጦርነትና ጠብ ከየት የመጣ ነው?" በማለት ይጠይቅና "በውስጣችሁ ከሚዋጉት ምኞቶቻችሁ አይደለምን?" በማለት በምፀት ይመልሰዋል፡፡ (ያዕ. 4፡1 አ.መ.ት) ይህ በምኞት፣ ዓለምን በመውደድና በመንፈሳዊ ምንዝርነት የመጣ አባዜ ያጣላቸው እርስ በርስ ብቻ ሳይሆን፣ ከእግዚአብሔርም ጋር ነበር፡፡ ይህንንም *"አመንዝሮች ሆይ፣ ዓለምን መውደድ ለእግዚአብሔር ጥል እንዲሆን አታውቁምን? እንግዲህ የዓለም ወዳጅ ሊሆን የሚፈቅድ ሁሉ የእግዚአብሔር ጠላት ሆኖአል፡፡"* ያዕ 4፡4 በማለት የወጠረውን ያጠብቀዋል፡፡ ይህንን የሚለው፣ በመንፈስ አንድ የሆነው ከአማኞች ጋር ብቻ ሳይሆን፣ ከክርስቶስም ጋር በመሆኑ ከአንዱ ተጣልተን፣ ከሌላው ተፋቅረን መኖር እንደማንችል ለማሳየት ነው፡፡

---

[320] ዘፀ. 20፡ 7; ሐዋ.ሥራ 19፡ 11 - 16

[321] ማቴ. 4፡ 1 – 11; ሮሜ 16፡ 17 – 20; ያዕ. 4፡ 1 - 10

[322] 2ቆሮ. 10፡ 3 - 6



For more books www.amharicchristianbooks.com

ታዲያ በምኞት ተነድፈው ከወገኖች ጋር ጦር የተማዘዙ፣ ከእግዚአብሔርም ጋር ጠላትነትን ያወጁ ሰዎች፣ እንዴት አድርገው ነው ዲያቢሎስን የሚቃወሙት? በዚህ ሁኔታስ ውስጥ ምን ያህል ቢገሰፅ ነው ዲያቢሎስ የሚወድቀው? በዚህ ክፍል ውስጥ ዲያቢሎስን መቃወም ተብሎ የሰፈረው፣ እኛ "ሰይጣን" ብለን የምንስለውን ሃሳባዊ ምስል መቃወም ሳይሆን፣ ዲያቢሎስ እኛን ከወገኖችና ከእግዚአብሔር ጋር ለማጣላት የተጠቀመበትን በእኛ ውስጥ ያለውን ዓለማዊ ምኞት ነው፡፡ ዲያቢሎስ በዓይን አምሮትና በኑሮ ትምክህት በሥጋችን የሰነቀረውን ምኞት ስንቃወም፣ ከወገኖች ጋር ጤናማ ግንኙነት ለመመስረት እጃችንን ስናነፃ፣ ከእግዚአብሔር ጋር ሕብረታችን እንዲሰምር ልባችንን ስናጠራ፣ ያን ጊዜ ዲያቢሎስ ሃሳቡ እንደ ፈረሰ በመረዳት ምርኮውን ጥሎ፣ የዘረፈውን እየበተነ ይሸሻል፡፡(ያዕ4፡7-10)

ነገር ግን በሚያሳዝን መልኩ በልምምዳችን የሚስተዋለው ከዚህ የራቀ ነው፡፡ በእርግጥ ነጋ ጠባ ተንበርክከን በድምፅ የምንቃወመው ዲያቢሎስ ቢሆንና በዚያ መልኩ መቃወማችን በትክክል የሚሰራ ቢሆን ኖሮ፣ አጋንንቶች ሁሉ ተጠቃለው ወደ ጥልቅ በገቡና ምድር ነፃ በሆነች ነበር፡፡ አዎን፣ ጌታ በመገለጡ ዲያቢሎስን የሚሽርበት፣ በአፉም እስትንፋስ የዓመፅን ልጅ  የሚያጠፋበት ቀን ተቀጥሯል፡፡ ሆኖም ያ ቀን እስኪመጣ ድረስ ሃሳቡንና ሥራውን እንጂ ዲያቢሎስን ልናጠፋ አንችልም፤ እንድናጠፋም አይጠብቅብንምም፡፡ ጌታም ቢሆን በመጀመሪያ መገለጡ የዲያቢሎስን ሥራ ያፈረሰው ለአባቱ ፈቃድ በመታዘዝ እንጂ ከዲያቢሎስ ጋራ በመነታረክ አልነበረም፡፡ እኛም ዛሬ በአስተሳሰባችን፣ በኑሮአችንና በተግባራችን ዲያቢሎስን ካልተቃወምን በቀር፣ በድምፅ ስናጉተመትም ብንውል ጠብ የሚል ነገር አይኖርም፡፡[323]

የፓለቲካ ሥርዓታቸው በተወካዮች ምክር ቤት ወይም በሕግ መወሰኛ ምክር ቤት የሚመሩ አገሮች የመንግሥት ስብሰባዎቻቸው ስለ ተቃዋሚዎችንም ያካተተ መሆኑ ስለምንነጋገረው ጉዳይ ዓይነተኛ ምሳሌ የሚሆን ይመስለኛል፡፡ በፓርላማ ስብሰባ ወቅት የሚታደሙት የገዢው ፓርቲ ተወካዮች ብቻ ሳይሆኑ፣ የምርጫ ድምፅ አግኝተው ወደ ፓርላማ የመግባት ዕድል ያገኙ የተቃዋሚ ፓርቲ ተወካዮች ጭምር ናቸውና፡፡ ታዲያ እነዚህ ስማቸው ራሱ "ተቃዋሚ" ተብሎ የሚጠሩ

---

[323] በመንፈስ ተመርተን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ወይም የእግዚአብሔርን ቃል እየተናገርን ጠላትን የምንቃወምባቸው ጊዚያት እንዳሉ በፅኑ አምናለሁ፡፡ ነገር ግን በጠላት እንደ ተከበበ ከሚያስብ አዕምሮ በመነጨ ፍርሃት ለጸሎት በተንበረከክን ቁጥር ልማድ ሆኖብን ልንገስፅ እንደማይገባም አስባለሁ፡፡



For more books www.amharicchristianbooks.com

ወገኖች፣ የገዢው ፓርቲ ተወካዮች ሲናገሩ ተቃውሟቸውን የሚያሰሙት ተነስተው በመርገም፣ በማውገዝና በመገሰፅ አይደለም፡፡ ይልቅ ገዢው የሚያነሳቸውን ሃሳቦች በጥንቃቄ ይመረምሩና ተራ ሲሰጣቸው በሰላ አንደበት ሃሳቡን በሃሳብ ይቃወማሉ፡፡[324] መጽሐፍ ቅዱስም ዲያቢሎስን እንድንቃወም የሚያስተምረን ከዚህ በተለየ መንገድ አይደለም፡፡ በእኛም ይሁን በሌሎች በኩል የሚመጣውን ሃሳብ ከሥጋ ይሁን ከመንፈስ፣ ከዲያቢሎስ ይሁን ከእግዚአብሔር፣ ከሰማይ ይሁን ከምድር መርምረን ስንለይና ለእግዚአብሔር ሃሳብ ስንገዛ፣ የከፉውንም ሃሳብ ስንቃወም፣ ውጊያውን በአግባቡ አካሂደናል ማለት ነው፡፡

አንዳንዶች እንደሚያስቡት ጠላት የሚቃወመን ውደቁ፣ ድቀቁ ብሎ በመርገም አይደለም፤ ሲረግም ቢውል ጠብ የሚልለት ነገር እንደሌለ አበክሮ ያውቀዋልና፡፡ የሚቃወመን፣ ሲቃወመንም በሚያሳዝን መልኩ የሚሰምርለት በሽንገላ ነው፡፡ ለዚህም በምድረበዳ ወደ ተስፋይቱ ምድር የሚጓዙት የእስራኤል ልጆችና የበለዓም ሁኔታ ዓይነተኛ ምሳሌ የሚሆነን ይመስለኛል፡፡ ሟርተኛው በለዓም በንጉስ ባላቅ ተገዝቶ በሰባቱ የሞዓብ ተራሮች መሠዊያ እየሰራ እሥራኤልን ሊረግም በሞከረ ጊዜ ፈፅሞ አልተሳካለትም ነበር፡፡ ያልተሳካለት እሥራኤላውያን ሲቃወሙ ስለዋሉ ሳይሆን፣ የማይተኛና የማያንቀላፋ የእሥራኤል ጠባቂ ስለተዋጋላቸው ነበር፡፡

ነገር ግን በእርግማን ያልሰመረለት በለዓም፣ በሽንገላ እንደሚሳካለት አጥርቶ ያውቅ ነበርና፣ የሞዓብን ልጃገረዶች ወደ እስራኤል ሰፈር እንዲልክ፣ እነርሱም ብኤልፌጎር የተሰኘውን የሞዓብ ጣኦት ያመልኩ ዘንድ የእስራኤልን ወንዶች እንዲያማልሉ ባላቅን አስተማረው፡፡[325] እንደ ታሰበውም የእሥራኤል ልጆች ሴሰኑ ፤ጣኦትንም አመለኩ፤ የእግዚአብሔርም ቁጣ ነደደ፤ በአንድ ቀን ሃያ ሶስት ሺህ ሰዎች በቁጣው እሳት ተበልተው ሞቱ፡፡ በሞዓብ ሜዳ ሰፍረው፣ በየድንኳናቸው ተጋድመው ሳሉ በጀርባቸው ምን እየተካሄደ እንዳለ ሳይውቁ፣ የተሞከረው የእርግማን ሴራ፣ ራስ ምታት እንኳ ያላመጣባቸው የእሥራኤል ልጆች የበለዓም ሽንገላና ረቂቅ ተንኮል በምድረ በዳ እንዲረግፉ ዳርጋቸው፡፡ የጠላትን ሽንገላ መቃወም ባለ መቻላቸው በጠላት እጅ ሳይሆን፣ ሊረግማቸው መሠዊያ የሚቀያይረውን ሟርተኛ ርግማን ወደ በረከት እየቀየረ በተዋጋላቸው፣ በእግዚአብሔር እጅ እንዲጠፉ አድርጓቸዋል፡፡

ጠላት ከኤደን ገነት አንስቶ የሚቃወመን በረቂቅ ተንኮል ነው፡፡ ተቃውሞውም

[324] ይህ ምሳሌ የሕንድን ዓይነት ፓርላማዎችን ውሎ አይወክልም፡፡ ምክንያቱም እነዚህ ፓርላማዎች አንዳንዴ ቡጢና ወንበር መወራወር ያካትታሉና፡፡
[325] ዮሓንስ ራዕይ 2፡14



For more books www.amharicchristianbooks.com

የሚመጣው ከሩቅ ሳይሆን ከቅርብ ሊሆን ይችላል፡፡ ከዙፋን ሳይሆን ከመድረክ ሊሆን ይችላል፡፡ ለነገሩ መጽሐፍ ቅዱስ ለመጀመሪያ ጊዜ ሰይጣንን የሚያስተዋውቀን እንደ አንደበተ ርቱዕ ሰባኪ አድርጎ አይደል? የስብከቱም ርዕስ "በውኑ እግዚአብሔር . . . " የሚል ነበር፡፡ ያ የቀድሞ እባብ ዛሬ ዘንዶ ሆኖ ብዙዎችን በትምህርት ሸንገላ ይውጣል፡፡[326] ልንቃወመው የምንችለው እግዚአብሔርን ወደ መምሰል የሚመራንን ጤናማውን የክርስቶስ ትምህርት በሚገባ ያወቅን እንደሆነ ብቻ ነው፡፡ ያኔ ከፍርሃት የተነሳ ያለ ኢላማ እንደሚተኩስ ዝንጉ ወታደር ነፋስን የምንጎስም አንሆንም፤ ይልቅ እውነትን ታጥቀን ሃሰትን፣ ጽድቅን አጥልቀን ኃጢያትን፣ የሰላምን ወንጌል ተጫምተን መለያየትን፣ የእምነትን ጋሻ አንስተን ፍርሃትን፣ የመዳንን ራስ ቁር ደፍተን ዓለማዊነትን፣ የመንፈስ ሰይፍ የሆነውን የእግዚአብሔርን ቃል መዝዘን የእግዚአብሔር መንፈስ በሌለባቸው ሥጋውያን ሰዎች አማካይነት የሚመጣውን የዲያቢሎስን ትምህርት የምንቃወም የእምነት ጀግኖች እንሆናለን፡፡ የምንቃወመውም ለሽንገላው "እምቢ" በማለት ነው፡፡ "እምቢ" በጩኸት ተነገረም በለሆሳስ ያው "እምቢ" ነው፡፡ "እምቢ" በራሱ ትልቅ ኃይል አለው፡፡ ኃይሉም የሚመነጨው ከሚነገርበት ድምፅ ሳይሆን፣ ከሚፈልቅበት ለእውነትና ለጽድቅ ከጨከነ ልብ ይመነጫል፡፡

## የዲያቢሎስ የጦር ልብስ

ቀደም ሲል ለውጊያ ስለሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎች ስንነጋገር ካነሳናቸው ነገሮች አንዱና ዋነኛው ከሁሉ አስቀድሞ የጠላትን ስልት፣ የጦር ትጥቅና አሰላለፍ መሰለል ነው፡፡ ቀደም ባሉት ክፍሎች ስለ መንፈሳዊ ጠላቶቻችን ስልትና አሰላለፍ በጥቂቱ አይተናል፡፡ ነገር ግን እኛ ስለምንለብሰው እንጂ ስለ ጠላቶቻችን የጦር ዕቃ አንዳች የተነሳ ነገር የለም፡፡ በርግጥ በዚህ ክፍል ውስጥ ለአማኞች ስለተሰጠው የጦር ዕቃ እንጂ ጠላቶቻችን ስለሚለብሱት የጦር ዕቃ የሚናገር ሃሳብ ያለ አይመስልም፡፡ ነገር ግን ልብ ብለን ከተመለከትነው በግልፅ ባይሆንም በስውር ተቀምጧል፡፡ ጳውሎስ መጋደላችን ከአለቆችና ከሥልጣናት ጋር፣ ከዚህም ከጨለማው ዓለም ገዥዎች ጋር፣ በሰማያዊም ስፍራ ካለ ከክፋት መንፈሳውያን ሠራዊት ጋር መሆኑን ከመንገሩ አስቀድሞ *«መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለምና»* በማለት አዎንታዊውን አዘግይቶ ከአሉታዊው ይጀምራል፡፡ የሆነውን ከመንገሩ በፊት ስለ ምን ያልሆነውን አስቀደመ? አንድን ሰው «እንዲህ ነው!» ብለን ስንነግር አዲስ ነገር እያስተማርን እንደሆነ ይገባናል፡፡ ነገር ግን ትምህርታችንን «እንዲህ አይደለም!»

[326] ዝኒ ከማሁ (ልክ እንደዚሁ) 12፡9



For more books www.amharicchristianbooks.com

በማለት ከጀመርን ሰውዬው አስቀድሞ የተማረው ወይም የመሰለው የተሳሳተ መረጃ እንዳለ አውቀናል ማለት ነው፤ «እንዲህ አይደለም» ብለን የምንነግረው ግለሰቡ ነገሩ የሆነ ሲመስለው ብቻ ነው፡፡

ጳውሎስ የሚፅፍላቸው ሰዎች መጋደላቸው ከሥጋና ከደም ጋር መስሏቸዋል፡፡ ባይመስላቸው ኖሮ «አይደለም!» ብሎ ማረም ባላስፈለገው ነበር፡፡ ተደራሲያኑ መጋደላቸው ከሥጋና ከደም ጋር ቢመስላቸውም ፈፅሞ አያስደንቅም፤ ምክንያቱም በስህተት ትምህርት ሲሸነግሏቸው የነበሩት ሥጋ የለበሱ ሰዎች ነበሩ (4፡14)። በርኩሰት ሊያጠምዷቸውና በከንቱ ንግግር ሊያታልሏቸው፣ ሲታገሉ የነበሩት ሥጋ የለበሱ ሰዎች ነበሩ፡፡ ከዚህም በላይ ይባስ ብሎ በአዋጅ ሊያሳድዷቸውና ሊያንገላቷቸው እየገሰገሱ የነበሩት ሥጋና ደም የሆኑ ሰዎች ነበሩ፡፡ ታዲያ መጋደላቸው ከሥጋና ከደም ጋር እንደሆነ ቢያስቡ ምን ያስደንቃል?

መጋደላችን ከሥጋና ከደም ጋር ካልሆነ ታዲያ ከማን ጋር ነው? ጠላቶቻችን እንደሁ መንፈሳውያን ናቸው፤ የሚኖሩትም በሰማያዊ ሥፍራ ነው፤ ታዲያ እንዴት ነው የሚዋጉን? እኛስ እንዴት ነው የምንለያቸው? ጳውሎስ በ 2፡1 ላይ ስለ ዲያቢሎስ አሠራር ሲፅፍ « . . . በዚህ ዓለም እንዳለው ኑሮ በማይታዘዙትም ልጆች ላይ አሁን ለሚሠራው መንፈስ አለቃ . . . " በማለት መንፈሱ በሰው በኩል እንደሚሠራ ገልፆልናል፡፡ ስለዚህ ጠላት በቤተ ክርስቲያን ላይ የሚዘምተው በስሜታቸው፣ በሃሳባቸውና በፈቃዳቸው በሚሠራ ሥጋና ደም በሆኑ ሰዎች በኩል መሆኑ አንዳች ጥርጥር የለውም፡፡ ይህ መልዕክት የሚጻፍላቸው ቅዱሳን ሆኑ በዘመናት ውስጥ በስደት ውስጥ ያለፉ አማኞች፣ በክፉው ቀን ሆ! ብለው ሲወጡባቸው፣ በቁጣ ሲተሙባቸው የሚያዩት ሥጋና ደም የሆኑ ሰዎችን በመሆኑ ያለ ምንም ማቅማማት ውጊያቸው ከሰዎቹ ጋር እንደሆነ ለማሰብ ይገደዳሉ፡፡ ለዚህ ነው ፀሐፊው "መጋደላችን ከሥጋና ከደም ጋር አይደለምና . . . ፡፡" (ቁ.12) በማለት የሆነውን ካልሆነው ለይተውና አጥርተው እንዲያዩ የሚያመለክታቸው፡፡ ሆኖም የማይታዩትን መንፈሳዊ ጠላቶቻችንን ፊት ለፊት ከምናያቸው ሰዎች የመለየቱን ሥራ ከባድና ውስብስብ የሚያደርገው፣ የክፋት ኃይላቱ ለወንጌል የማይታዘዙትን የሰው ልጆች እንደ ጦር ዕቃ ስለሚለብሷቸው ነው፡፡ እዚህ ጋ ለስህተት የዳረገን፣ ጳውሎስ በ 2፡2 ላይ « . . . በአየር ላይ ሥልጣን እንዳለው አለቃ ፈቃድ በፊት ተመላለሳችሁባቸው፡፡» ሲል አየር የሚለው የምንተነፍሰውን ከባቢ አየር ሳይሆን፣ በዙሪያችን ያለውን መንፈሳዊ ዓለም ማለቱ እንደሆነ አለመረዳታችን ነው፡፡ በዚያው ምዕራፍ ላይ ዝቅ ብሎ ሲፅፍ፣ እኛ በክርስቶስ በማመን ከዚያ መንፈሳዊ ህዋ ወይም ከበብ መውጣታችንን « . . . ከእርሱ ጋር



For more books www.amharicchristianbooks.com

*አስነሳን በክርስቶስ ኢየሱስም በሰማያዊ ሥፍራ ከእርሱ ጋር አስቀመጠን፡፡»* በማለት ጽፎልናል፡፡ ታዲያ እኛ በማመናችን መንፈሳዊ አየር እንጂ ግዑዝ አየር አልቀየርንም፡፡ ከመንፈሳዊው ህዋ ወጣን እንጂ፣ በሥጋ አካል ከምንኖርበት ከባቢ አየር አልወጣንም፡፡

የማያምኑ ሰዎች የሚኖሩበትን መንፈሳዊ ህዋ (ዓለም) የተቆጣጠሩት መናፍስት፣ ግዑዝ አካል ስለሌላቸው ወደ ምድር መግባትና የወደዱትን ማድረግ አይችሉም፡፡ ነገር ግን ፈቃዳቸውን ለመፈፀም በግዛታቸው ሥር ያሉትን ሰዎች እንደ ጦር ዕቃ ይለብሷቸዋል፡፡ ታዲያ ያን ጊዜ ነው መደናገሩ የሚመጣው፡፡ ጠላትን ከልብሱ መለየት ግር ይላል፡፡ ለዚህ ነው ጳውሎስ «እኛ የምንዋጋው ከጠላቶቻችን ጋር እንጂ ከጦር ዕቃዎቻቸው ጋር አይደለም፡፡ በዚህ ውጊያ ጠላቶቻችንን እናፈርሳለን፣ የጦር ዕቃዎቻቸውን ግን እንማርካለን፡፡»[327] በሚል ቃና የሚፅፈው፡፡ ስደት በሚበረታበት በክፉ ቀን መንፈሳዊ ጠላቶቻችን አፋሽ አጎንባሹን እንደ ልብስ ያጠልቁታል፡፡ መንፈሳዊ አለቆችና ሥልጣናቱ፣ ምድራዊ አለቆችና ሥልጣናቱን ይለብሳሉ፤ ተራ መናፍስቱ ደግሞ ተራ ሰዎችን እንደ አሰላለፋቸው ይለብሳሉ፡፡

ታዲያ ስደት እንደ ሰደድ እሳት ግር ብሎ በሚመጣበት ቀን እኛ ፊት ለፊት የምናየው እውነተኛ ጠላቶቻችን የሆኑትን መንፈሳዊ ኃይላት ሳይሆን የለበሱአቸው ሥጋና ደም የሆኑ ሰዎችን ነው፡፡ ይህም ማደናገሪያ ስልት ነው፡፡ ልንወዳቸው፣ ልንማልድላቸውና የምሥራቹን ቃል ልንነግራቸው የሚገባንን ሰዎች እንድንጠላና እንድንቃወም የተወጠነ ሥልት ነው፡፡ እኛ ግን እንደ ተመከርነው እውነተኛ ጠላቶቻችንን፣ ጠላቶቻችን ከሚመስሉት፣ ነገር ግን ፈፅሞ ካልሆኑት ለይተን እንድናይ ወታደራዊ መመሪያ ተሰጥቶናል፡፡ ምሳሌያችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ከኃጢአት ጋር ሲጋደል ሁሉን ከፍ ብሎና አጥርቶ ያይ ነበርና፣ ጠላቶቹን ከለበሷቸው የጦር ዕቃዎች ለይቶ ማየት አልተሳነውም፡፡ ስለዚህ በመስቀሉ ሥራ *«አለቅነትንና ሥልጣናትን ገፎ ድል በመንሳት በእርሱ እያዞራቸው በግልጥ አሳያቸው፡፡»* (ቆላ. 2፡15) በጠላቶቹ እንደ ጦር ልብስ ተለብሰው በእጃቸው ለሚያሰቃዩት ሰዎች ግን *«የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው»* (ሉቃስ 23፡ 34) ብሎ ማለደ፡፡

ጳውሎስ በሮሜ መልዕክቱ የቀድሞ ኑሯችንን እያስታወሰ ሲመክር ". . . ብልቶቻችሁንም የዓመፃ የጦር ዕቃ አድርጋችሁ ለኃያጢአት አታቅርቡ . . . » ሮሜ 6፡13 ይላል፡፡ ይህም አባባሉ ያኔ ብልቶቻችን (ሥጋና ደም) የአመፅ የጦር ዕቃ

[327] 2ቆሮ 10፡4-6



For more books www.amharicchristianbooks.com

እንደ ነበሩ ይነግረናል፡፡ የጦር ዕቃ መኖሩ፣ ለብሶ የሚዋጋ ጦረኛ መኖሩን ያረጋግጣል፡፡ ዲያቢሎስም በግዛቱ ያሉትን ሰዎች እንደ ጋሻ ጦር ለብሶ ይዋጋል፡፡

ቀደም ሲል በሽንገላውም ሆነ በተቃውሞ ቀን እንለብሰው ዘንድ የእግዚአብሔር የጦር ዕቃ እንደ ተሰጠን፣ ይህም የጦር ዕቃ ራሱ እግዚአብሔር እንደ ሆነ ተመልክተናል፡፡ እኛ እግዚአብሔርን ለብሰን ለሰልፍ እንወጣለን፣ ጠላት ግን ሰዎችን (ሥጋና ደም) ለብሶ ለውጊያ ይወጣል፡፡ እኛ ላይ የሚወረወረውን ጥቃት የሚመክተው እግዚአብሔር ነው፤ ለብሰነዋላ! ጠላት ላይ የሚወረወረው ጥቃት ግን የሚያርፈው ሥጋና ደም የሆኑ ሰዎች ላይ ነው፤ ለብሰዋቸዋላ! ይህ ደግሞ በእግዚአብሔር ዘንድ ይቅርና በሰው ዘንድ እንኳ ይቅር የማይባል ወንጀል ነው፤ በጦርነት ላይ ያልታጠቁ ሲቪል ሰዎችን ተከልሎ መዋጋት (Human Shield) ዓለም አቀፍ የጦር ወንጀል መሆኑን የተባበሩት መንግስታት ደንብ በግልፅ ያስቀምጠዋልና ነው፡፡[328] ስለዚህ እኛም ከሥጋና ደም ጀርባ ያለውን ጠላት በማስተዋል ሥራውን ልናፈርስ፣ ለሚጠቀምባቸው የጦር ዕቃዎች ግን ልንራራና ልንማልድ፣ የምሥራቹንም ቃል ልናውጅ እንደሚገባን ከዚህ እንማራለን፡፡

[328] Third Geneva Convention, Article 23, first paragraph (cited in Vol. II, Ch. 32, § 2251); Fourth Geneva Convention, Article28 (ibid § 2252); Additional Protocol I, Article 51(7) (adopted by consensus) (ibid., § 2254).



For more books www.amharicchristianbooks.com

# ምዕራፍ ፲፫
# ጸሎት

ኤፌ. 6፡ 18 - 20

ጸሎት ምንም እንኳ ከጦር ዕቃዎች ዝርዝር በቀጣይነት ቢጠቀስም፣ በጦር አውድማ ላይ ከምንጠቀምባቸው የጦር መሣሪያዎች አንዱ አይደለም፡፡ ስለ ጸሎት ስናነሳ ልብ ልንለው የሚገባ አንድ ትልቅ ቁም ነገር አለ፡፡ ስንፀልይ የምንገባው የት ነው? የምንቀርበውስ በማን ፊት ነው? የምንሰራውስ ምንድነው? እነዚህ ጥያቄዎች ተገቢ መልስ ሊያገኙ ይገባቸዋል፡፡ ቀደም ብለን የኤፌሶን መልዕክት የጸሎት መጽሐፍ ነው ብለናል፡፡ ጳውሎስ ለተደራሲያኑ በተደጋጋሚ ይጸልያል፣ ሲጸልይም በማን ፊት እንደሚቀርብና ምን እንደሚሰራ በግልፅ አስቀምጧል፡፡ በማን ፊት እንደሚቀርብ ሲገልፅ «. . . እኔ ጳውሎስ ለእግዚአብሔር እንበረከካለሁ . . . በሰማይና በምድር ያለ አባትነት ሁሉ ከሚሰየምበት ከአብ ፊት እንበረከካለሁ፡፡» (3፡1፣14) በማለት ነው፡፡

ጸሎት በአብ ፊት የምንቀርብበት መንገድ እንጂ ለውጊያ ጠላቶቻችንን የምንገጥምበት አይደለም፡፡ ጠላቶቻችን ሰዎችን ለብሰው የሚዋጉ ከሆነ፣ ከጠላቶቻችን ጋር ፊት ለፊት የምንገናኘውና ውጊያውን የምናካሂደው በጸሎት ሥፍራ ሳይሆን፣ ከሰዎች ጋር በምንገናኝበት በሰው ገበያ ነው፡፡ በሥራ ይሁን በቤት፣ በሰፈር ይሁን በውጭ፣ ከሰዎች ጋር የምንገናኝበት ሥፍራ ሁሉ የጦር ልብሳችንን ለብሰን በጥንቃቄ ልንመላለስ የሚገባን ስፍራ ነው፡፡ እውነትን መታጠቅና ማወጅ የሚያስፈልገን ሐሰት በገነነበት ዓለም ነው፡፡ ጽድቅን መታጠቅና መግለጥ የሚያስፈልገን አመፅ በሞላበት በሰዎች ዓለም ነው፡፡ በወንጌል የታወጀውን ሰላም መጫማትና የመንፈስን አንድነት በመጠበቅ መመላለስ የሚያስፈልገን ልዩነት በሰፈነበት ጠብና ጦርነት በተንሰራፋበት፣ የዘር፣ የመደብና ዘርፈ-ብዙ ልዩነቶች በነገሱበት በሰዎች መሀል ነው፡፡

የጸሎት ሥፍራችን ግን፣ የተቀደሰ የክህነት ልብሳችንን ለብሰን በማክበርና በፍርሃት የምንገባበት የዙፋን ክፍል እንጂ የጦር ሜዳ አይደለም፡፡ አለዚያማ ሜዳውም ጦርነት፣ መቅደሱም ጦርነት ይሆናል፡፡ ጦርነት ድንበርን አልፎ የአምልኮ ማዕከል ከሆነው መቅደስ ከደረሰ እንኪያስ የት ሊታረፍ ነው? የጸሎት ሥፍራ የምንዋጋበት ሳይሆን፣ በሚያስፈልገን ጊዜ የሚረዳንን ፀጋና ኃይል የምንቀበልበት፣ አዝማቻችንና ሊቀ ካህናችን በሆነው በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ አቅራቢነት በአብ ዙፋን ፊት



For more books www.amharicchristianbooks.com

በመቅረብ ለክፉ ቀን የሚያስፈልገንን ትጥቅና ስንቅ የምንቀበልበት ብቸኛ መንገድ ነው፡፡[329]

ጌታ ኢየሱስ ራሱ ጸሎት እንዲያስተምራቸው ከደቀመዛሙርቱ ለቀረበለት ጥያቄ ምላሽ ሲሰጥ *"አባታችን ሆይ . . . "* ሉቃስ 11፡1-4 በማለት በአብ ፊት መቅረብን አስተማራቸው እንጂ፣ በፀሎት ከዲያቢሎስ ጋር ጦርነት ስለ መግጠም አልነገራቸውም፡፡ እርሱም ራሱ አገልግሎቱን ሲጀምር ፊት ለፊት በዲያቢሎስ ከተፈተነው በቀር፣ በቀሪ የአገልግሎቱ ዘመን ከክፉ መናፍስት  ጋር ግብ ግብ ሲገጥም አንመለከትም፡፡ ይህም ቢሆን በመንፈስ ቅዱስ ምሪት የተፈፀመ፣ አርባ ቀንና አርባ ሌሊት በጾም ወደ አባቱ  ከጸለየ በኋላ የተከናወነ ውሱን ትዕይንት እንጂ የዘወትር ልምምድ አልነበረም፡፡ በዚያን ጊዜም ጌታ፣ የእግዚአብሔር ሃሳብ የሆነውን ቅዱስ ቃል እየጠቀሰ ወደ አዕምሮው የሚወረወረውን የክፉውን ሃሳብ ተቃወመ እንጂ የተለየ ሥልት እንዳልተጠቀመ መገመት አያስቸግርም፡፡ ከዚያ በኋላ በቀረው የአገለግሎቱ ዘመን፣ እስከ ስቅለቱ ድረስ ዲያቢሎስን በሥጋና በደም ውስጥ እንጂ ፊት ለፊት ሲፋለመው አንመለከትም፡፡ ይልቅ በሰዎች መሀል ሲያስተምር፣ ሲሰብክ፣ ሲፈውስ፣ በአጋንንት የታሰሩትን ሲፈታ፣ አንዳንዴም ከፈሪሳውያን፣ ከጸሐፍት፣ ከካህናትና ከአይሁድ አለቆች መርዘኛ ጥያቄ ጋር ሲፋለም ይውልና ከደቀ-መዛሙርቱ ሳይቀር ተለይቶ ብቻውን ወደ ምድረ-በዳ ወይም ወደ ተራራ በመሄድ በጸሎት ከአባቱ ጋር ሲነጋገር ያድር ነበር፡፡

ከዚያም በሚቀጥለው ቀን መንፈሱ ታድሶ ለሌላ ፍልሚያ ተዘጋጅቶ ይመለስ፣ ተልዕኮውንም ይፈፅም ነበር፡፡ በመጨረሻም ሰዓት ከደቀ-መዛሙርቱ ጋር ራት በበላበት ደርብ ቤት ስለ ተከታዮቹ ሲማልድ፣ በኋላም በጌቴሴማኔ ከሞት ሊያድነው ወደሚችል በብርቱ ጩኸት ከእንባ ጋር ጸሎትና ምልጃን ሲያቀርብ፣ በቀጥታ በአባቱ ፊት ልቡን አፈሰሰ እንጂ እንደምናስበው ከዲያቢሎስ ጋር በጸሎት ግብ ግብ አልገጠመም፡፡ ግብ ግቡ በሰው መሃል እንጂ በጸሎት ስፍራው አልነበረም፡፡[330] ምንም እንኳ በቤት ውስጥ ጸሎቱ ስለ ደቀ መዛሙርቱ ሲማልድ *"ከክፉ እንድትጠብቃቸው እንጂ ከዓለም እንድታወጣቸው አልለምንም . . . ፡፡"* ዮሐ. 17፡15 በማለት ስለ ክፉው ቢጠቅስም፤ የክፉውን ስም ያነሳው አብ ከክፉው እንዲጠብቃቸው ለመለመን ብቻ እንደ ነበር እንመለከታለን፡፡

---

[329] ክፉ መንፈስ ከሰው ውስጥ በምናወጣበት ጊዜ መናፍስቱን በኃይልና በሥልጣን እያዘዝን ሰዎችን ነፃ በማውጣት ተግባር ላይ ስለሆንን ይህ እንደ አገለግሎት እንጂ እንደ ፀሎት ሊታይ አይገባውም፡፡

[330] ማቴ. 4፡1 – 11; 16፡ 23; 8፡ 28-34; ዮሐ. 8፡ 44



For more books www.amharicchristianbooks.com

ጸሎት ከእግዚአብሔር ጋር ፊት ለፊት የምንገናኝበት የንስሐ፣ የምሥጋና፣ የምልጃና የልመና ሥፍራ ነው፡፡ ይህንንም እውነት ለማፅናት ከዘፍጥረት እስከ ራዕይ ስለ ፀሎት የተጻፉትን ክፍሎች አንድ በአንድ መጥቀስ ከብዛቱ የተነሳ ቢያዳግተንም በኤፌሶን መልዕክት ውስጥ ብቻ ከምናገኛቸው የጳውሎስ የጸሎት ዘገባዎች በመነሳት ጸሎት ምን እንደሆነና ምን እንዳልሆነ መረዳት እንችላለን፡፡

> *". . . ስለ እናንተ **እያመሰገንሁ** ስጸልይ ስለ እናንተ **ማሳሰብን** አልተውም . . . **እለምናለሁ**፡፡" ኤፌ. 1፡16-17*
>
> *" ስለዚህ አሕዛብ ስለሆናችሁ ስለ እናንተ የክርስቶስ ኢየሱስ እስር የሆንሁ እኔ ጳውሎስ **ለእግዚአብሔር እንበረከካለሁ**፡፡" ኤፌ. 3፡1*
>
> *" **ከአብ ፊት እንበረከካለሁ** . . . እንደ ክብሩ ባለጠግነት መጠን **ይስጣችሁ** . . . **ከምንለምነው** ወይም **ከምናስበው** ሁሉ ይልቅ እጅግ አብልጦ ሊያደርግ ለሚቻለው . . . **ክብር** ይሁን አሜን፡፡" ኤፌ. 3፡14-21*
>
> *"በመዝሙርና በዝማሬ በመንፈሳዊም ቅኔ እርስ በርሳችሁ ተነጋገሩ ለጌታ ከልባችሁ ተቀኙና ዘምሩ፣ ሁልጊዜ ስለ ሁሉ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አምላካችንንና አባታችንን ስለ ሁሉ **አመስግኑ**፡፡" ኤፌ. 5፡19-20*

ሲል ይቆይና አሁን ደግሞ በመደምደሚያው ላይ፡ -

> *"በጸሎትና በልመና ሁሉ ዘወትር በመንፈስ ጸልዩ በዚህም ሃሳብ ስለ ቅዱሳን ሁሉ እየለመናችሁ በመፅናት ሁሉ ትጉ . . . ስለ እኔ ለምኑ . . . ስለ እርሱ በግልጥ እናገር ዘንድ ለምኑ፡፡" ኤፌ. 6፡18-20 ይላቸዋል፡፡*

ከዚህ በመነሳት ጸሎት በእግዚአብሔር ፊት የሚደረግ የምሥጋና፣ የልመናና የምልጃ ሥራ እንጂ ከጠላት ጋር አንገት ለአንገት ተናንቀን የምንዋደቅበት የጦርነት ሥፍራ እንዳልሆነ እንመለከታለን፡፡ በእርግጥ እንዳንጸልይ ጠላት በተለያየ መንገድ ሊያዘገየን ይችል ይሆናል፡፡ ነገር ግን ክልከላውን ሁሉ አልፈን ለጸሎት ከተንበረከክን ድል ነስተናል ማለት ነው፡፡ ከዚያ በኋላ ጉዳዩ ከእግዚአብሔር ጋር እንጂ ከጠላት ጋር አይደለም፡፡

ምናልባት አንዳንድ አንባቢያን በሌሎች የጳውሎስ መልዕክቶች ውስጥ ስለ "መጋደል" የተጻፉትን ቃላት፣ በተለይም በቆላስያስ 4፡12 ላይ ስለ ኤጳፍራ በጸሎት መጋደል የተጻፈውን ቃል ሲመለከቱ በዘመናችን የምናያቸውን ልምምዶች የሚያፀኑ ክፍሎች ሊመስሏቸው ይችላል፡፡ ሆኖም መፍትሄው ክፍሎቹን በጥልቀት



For more books www.amharicchristianbooks.com

ማየት ብቻ ነው፡፡ ሐዋርያስ ጳውሎስ በቆላ. 1፡ 29 እና 2፡1–2 ላይ "እጋደላለሁ" የሚለው፣ በክርስቶስ ኢየሱስ ለሰው ልጆች ሁሉ የተገለጠውን ምሥጢር ያውቁ ዘንድ ወንጌልን ለአሕዛብ እንዳይነግራቸው ከአይሁድ የሚደርስበትን ፅኑ መከራና እርሱም ለዚህ መከራ ባለመበገር የሚያደርገውን ቀጣይ ትግል የሚያሳይ ክፍል ነው፡፡ በርግጥ የቆላ. 4፡12 በቀጥታ ከጸሎት ጋር የተያያዘ በመሆኑ ጥያቄውን ከፍ ሊያደርገው ይችላል፡፡ ሆኖም ጳውሎስ ስለ ኤጳፍራ ጸሎት ሲዘግብ ". . . በእግዚአብሔር ፈቃድ ሁሉ ተረድታችሁና ፍፁማን ሆናችሁ እንድትቆሙ ስለ እናንተ ሁል ጊዜ በጸሎቱ ይጋደላል፡፡" ስለሚል ርዕሰ ጉዳዩ በቀጥታ ከእግዚአብሔር ጋር እንጂ ከሰይጣን ጋር እንደማይገናኝ መረዳት አያስቸግርም፡፡ ይልቅ ለተደራሲያኑ፤ የግሪክ አትሌት በጨዋታ ስፍራ በፅናት እንደሚጋደል፣ ኤጳፍራም ለሥጋው ድካም ሳይበገር "ሁል ጊዜ!" በጸሎት እንደሚጋደል ለማሳየት የተጠቀመበት ቃል ነው፡፡

ጳውሎስ ወደ ሮሜ ሰዎች በላከው መልዕክቱ መጨረሻ ላይ፡-

> *"ወንድሞች ሆይ፣ ስለ እኔ ወደ እግዚአብሔር እየጸለያችሁ ከእኔ ጋር ትጋደሉ ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስና በመንፈስ ፍቅር እለምናችኋለሁ . . . " ሮሜ 15፡30*

እንዳለው፤ በጸሎት መጋደሉ በእግዚአብሔር ፊት እንደሚሆን ከራሱ ከክፍሉ እንረዳለን፡፡ ሰው በጸሎት ከእግዚአብሔር ጋር እንደሚጋደል ወይም እንደሚታገል የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትም ይመሰክሩልናል፡፡ እስራኤል የተባለው ያዕቆብ፣ ከአጎቱ ከላባ አገር ተመልሶ ወደ ከነዓን ሲመጣ፣ ጵንኤል በተባለው ሥፍራ ሌሊቱን ሲጸልይ የሆነውን የዘፍጥረት ጸሐፊ እንዲህ በማለት ተርኮልናል፡፡

> *" ... አለውም፡- ከእንግዲህ ወዲህ ስምህ እሥራኤል ይባል እንጂ ያዕቆብ አይባል፣ **ከእግዚአብሔር ከሰውም ጋር ታግለህ አሸንፈሃልና፡፡**" ዘፍ. 32፡26-28፡፡*

በሌላም ስፍራ የያዕቆብ ትግል ከእግዚአብሔር ጋር እንደነበርና ያሸነፈውም በመሸነፍ እንደነበር ሲያስታውስ እንዲህ ይላል

> *"በማህፀን ውስጥ ወንድሙን በተረከዙ ያዘው፤ በጎልማሳነቱም ጊዜ ከአምላክ ጋር ታገለ፤ ከመላዕኩም ጋር ታግሎ አሸነፈ፤ አልቅሶም ለመነው፡፡ በቤቴልም አገኘው፣ በዚያም ከእኛ ጋር ተነጋገረ፡፡ እርሱም የሠራዊት አምላክ እግዚአብሔር ነው፤ የመታሰቢያው ስም እግዚአብሔር ነው፡፡" ሆሴዕ 11፡4-5*

ሆኖም የብዙዎቻችንን ልምምድ ስንመለከት ጸሎት በዋነኝነት ከጠላት ጋር ሳንጃ



For more books www.amharicchristianbooks.com

የምንሞሻለቅበት፣ ጉሮሮ ለጉሮሮ የምንተናነቅበት የጨበጣ ውጊያ አውድማ እንደሆነ አድርገን እንወስዳለን፡፡ ነገር ግን ይህንን አስተሳሰብም ሆነ ልምምድ ከየት እንዳመጣነው ማስረጃም ሆነ መረጃ ከቅዱስ ቃሉ ማቅረብ የምንቸገር ይመስለኛል፡፡ ምክንያቱም በብሉይ ኪዳንም ሆነ በአዲስ ኪዳን መጻሕፍት የምናነባቸው በጽሑፍ የሰፈሩ ጸሎቶች በእግዚአብሔር ፊት በመቅረብ ታላቅነቱን፣ ሁሉን ቻይነቱን፣ ክብሩን . . . ወዘተ በማወጅ የሚጀምሩና በልመና የሚቀጥሉ በመጨረሻም በምስጋና የሚቋጩ እንጂ ከጠላት ጋር የትንቅንቅ ስፍራዎች እንደሆኑ አናይም፡፡ ልመናዎቹም በዘፈቀደ የሚንበለበሉ ሳይሆን እግዚአብሔር በቅዱስ ቃሉ የሰጣቸውን የተስፋ ቃሎች በመጥቀስ የሚቀርቡ እንደ ነበሩ እንመለከታለን፡፡[331] ለዚህም፣ በከፍተኛ የስደት ወቅት በኢየሩሳሌም የነበሩ ሐዋርያትና አማኞች ከአለቆችና ከሊቀካህናት ተቃውሞና መከራ ከገጠማቸው በኋላ በአንድነት የጸለዩት ጸሎት ድንቅ አብነት ይሆነናል፡፡[332]

ጳውሎስ ከፊታቸው ብርቱ ስደትና መከራ ለተደቀነ፣ በትንሿ እስያ ለሚገኙ አማኞች "በፀሎትና በልመና ሁሉ ዘወትር በመንፈስ እንዲጸልዩ" ይመክራቸዋል፡፡ ዘወትር የሚለው ቃል በማንኛውም ሁኔታ የሚል ትርጉም ያዘለ ነው፡፡ ዘወትር መፀለይ እንዴት ይቻላል? እንል ይሆናል፡፡ ነገር ግን ፀሎቱ ደካማ በሆነው ሥጋ ሳይሆን ሁል ጊዜ ሊያግዘን ዝግጁ በሆነው በመንፈስ ቅዱስ የሚካሄድ ነውና በመንፈስ ለተሞሉ አማኞች አስቸጋሪ አይሆንም፡፡ በተለይም ከፊት ለፊታችን መከራና ስደት ሲኖር መንፈስ ቅዱስ ራሱ በልዩ ፀጋ የጸሎት ጉልበት ይሰጠናል፡ ዘማሪ ተስፋዬ ጋቢሶ በደርግ ዘመን ከተቀጣጠለው መከራ ቀደም ብሎ ፡-

አስቀድሞ ኃይል ይሰጣል ያለብሳል፣
ለኛ የማይቻለውን እርሱ ይችላል፣
የማይታለፈውን ያሳልፋል፣
ኢየሱስ ኃይል ይሰጣል፣ ያለብሳል፡፡

ብሎ እንደ ዘመረው በስደት ወቅት የሚበዛውን አስገራሚ የፀሎት ጉልበት አልፈውበት የተለማመዱት በሚገባ ያውቁታል፡፡

በመንፈስ መፀለይ ማለት የፀሎት ርዕሱም ሆነ ብርታቱ ከመንፈስ ቅዱስ የሚመነጭ ሆኖ፣ በውስጥ ስውነታችን በመቃተት የምንፀልየው ፀሎት ነው፡፡ ይህ መቃተት ብዙውን ጊዜ ከውስጣችን ፈንቅሎ በመውጣት በእግዚአብሔር ፊት

[331] 1ሳሙ 2፡ 1-10; 1ነገሥ 8፡ 22-61; 1ዜና 29፡ 10-19; 2ዜና 6፡12-42; ነህ.1፡ 4-11; 9፡ 5-38; ኢሳ 37፡ 15-20; ዳን 2፡ 17-23; ዕን 3፡ 1-19
[332] ሐዋ. ሥራ 4፡24-31



For more books www.amharicchristianbooks.com

ልባችን የምናፈስበት ልዩ ልሳን ነው፡፡ ጳውሎስ ራሱ በመንፈስ መፀለይንና በልሳን መፀለይን አዛምዶ ይፅፋል፡፡[333] ሆኖም ልሳን ከእግዚአብሔር ጋር በመንፈስ ምሥጢር የምንነጋገርበት የመንፈስ ቋንቋ እንጂ ከአጋንንቶች ጋራ አተካራ የምንገጥምበት ተደርጎ ሊቆጠር አይገባም፡፡[334] «. . . የሚያስተውለው የለምና . . . » ሲል አጋንንትንም ይጨምራልና፡፡

ፀሎት በርካታ ነገራትን የሚያካትት አጠቃላይ ቃል ሲሆን፣ ልመና የሚለው ግን ውሱን የሆነና በአንድ አላማ ላይ ያነጣጠረ ቃል ነው፡፡ ስለዚህ ልመና ሰፊ ማዕቀፍ በሆነው ፀሎት ውስጥ የሚካተት ይሆናል፡፡ ፀሎት በብዙ መልክና በብዙ ዓይነት መንገድ የሚቀርብ ስለሆነ ጳውሎስ «በፀሎትና በልመና ሁሉ» በማለት ይገልፀዋል፡፡ በዚህ ክፍል ውስጥ በአንድ ቁጥር ውስጥ ብቻ (ቁ. 18) "ሁሉ" የሚለው ቃል ሦስት ጊዜ እንደተደጋገመ እናያለን፡፡ የመጀመሪያው ስለ ፀሎት ዓይነት ለመግለፅ "በጸሎትና በልመና ሁሉ" የሚል ሲሆን ሁለተኛው ስለፀሎቱ ይዘትና ስለምንፀልይላቸው ሰዎች "ስለ ቅዱሳን ሁሉ" በማለት ይገልፃል፡፡ በመጨረሻም ሦስተኛው በጊዜውም አለጊዜውም ባለማቋረጥ እንድንፀልይ እየመከረ "በመፅናት ሁሉ ትጉ" ይለናል፡፡ በዚህ ክፍል በጥቂት ቃል ስለ ጸሎት ሰፊ ነገር እንደተገለፀ እንመለከታለን፡፡

የመጸለያን ጊዜ በተመለከተ በብሉይ ኪዳኗ እሥራኤል በቀን ሦስት ጊዜ በማለዳ፣ በቀትር፣ በሠርክ፣ ይቀርብ የነበረው በሰዓት የተገደበ ጸሎት፣ በአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን ያለ ምንም የጊዜ ገደብ ሁል ጊዜ በጸሎት በመትጋት፣ በጸሎት በመፅናት፣ ቀንና ሌሊት ሳያቋርጡ በመጸለይ እንደ ተተካ እንመለከታለን፡፡[335]

ጳውሎስ *«በዚህም ሃሳብ ስለ ቅዱሳን ሁሉ እየለመናችሁ በፀሎት ሁሉ ትጉ»* ማለቱ በምድር ኑሯችን ሰለሚገጥመን ልዩ ልዩ ውጊያ በአብ ፊት ስንጸልይ፣ በተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ የሚያልፉትን ሌሎች ቅዱሳንን ማሰብ ግድ መሆኑን ያሳየናል፡፡ በመሠረቱ የመንግሥት ወይም የሕዝብ እንጂ የግል ጦርነት የለም፡፡ በተለይ የእኛ ጦርነት ፈፅሞ የግል አይደለም፡፡ ጦርነቱ የእግዚአብሔር መንግሥትና የጨለማው መንግሥት እንደ ሆነ የታወቀ ነው፡፡ ስለዚህ በምንም ዓይነት አንዱ አማኝ ጦርነት ላይ ሆኖ ሌላው ዕረፍት ላይ ሊሆን አይችልም፡፡ በእርግጥ አንዳንድ አማኞች

[333] 1ቆሮ. 14፡ 13 – 19; ይህንን ክፍል ከሮሜ 8፡26 – 27 እንዲሁም ይሁዳ 20 – 21 ጋር ያስተያዩ፡፡
[334] 1ቆሮ 14፡3
[335] ዳን. 6፡10 መዝ. 55፡17; ሉቃ. 21፡36 ሐዋ.2፡42 ሮሜ 12.12 ፊሊ. 4፡6 ቆላ. 4፡2 1ተሰ. 5፡17 2ጢሞ 1፡3



For more books www.amharicchristianbooks.com

ጦርነቱ እነርሱ ላይ ብቻ ያነጣጠረ የግል ጦርነት ሊመስላቸው ይችላል፡፡ ሆኖም ይህ አመለካከት ጤነኛ አለመሆኑን ለማሳየት አንድ ምሳሌ ልጠቀም፡፡ አንድ ሰው ወደ እናንተ መጥቶ «የሱዳን መንግሥት ሊወጋኝ ይፈልጋልና ፀልዩልኝ» ቢላችሁ ምን ትመልሱለታላችሁ? ይህ ሰው እንደ ተሳሳተ ብቻ ሳይሆን "ንክ" እንደሆነ እንደምታስቡ አልጠራጠርም፡፡ «ለመሆኑ የሱዳን መንግሥት አንተ ላይ ጦርነት የሚያውጀው አንተ ማን ነህ?» ልትሉት ትችላላችሁ፡፡ ምክንያቱም መንግሥት በመንግሥት፣ ሕዝብ በሕዝብ ላይ እንጂ፣ መንግሥት ግለሰብ ላይ ጦርነት አይከፍትምና ነው፡፡ ልክ እንዲሁ በእነዚህ አማኞች ላይ የታወጀው የስደት ጦርነት እንዳቸውን ሳይሆን ሁሉን የሚመለከት ስለ ሆነ፣ ሐዋርያው አንዳቸው ለሌላቸው እንዲፀልዩ ይመክራል፡፡ ምንም እንኳ አንዳቸው ጋ የደረሰው ገና ሌሎቹ ጋ ባይከሰትም፣ እንደ ሰደድ እሳት እየተቀጣጠለ መድረሱ አይቀርምና አንዱ ስለ ሌላው መፀለዩ ይበጃል፡፡

ማንም ሰው ስለ ራሱ ቢጸልይ ምንም ክፋት የለውም፣ ነገር ግን በእግዚአብሔር መንግሥት ለራሳችን ከምንፀልይ ይልቅ ሌሎች ለእኛ፣ እኛም ለሌሎች ብንጸልይ የተመረጠ ነው፡፡ ጳውሎስ ለሚጽፍላቸው ከአሕዛብ ወገን ለሆኑ ቅዱሳን እንደሚጸለይላቸው ደጋግሞ ተናግሯል፡፡ ስለ ራሱ ግን ራሱ ከመጸለይ ይልቅ እነርሱ እንዲጸልዩለት በትህትና ይጠይቃል፡፡ የሚጠይቀውም ለሥጋ የሚያስፈልጉትን ነገሮች እንዲያገኝ፣ ከእሥር ቶሎ እንዲፈታ ወይም መከራው እንዲቀልለት ሳይሆን ከእግዚአብሔር ዘንድ አደራ ስለ ተቀበለው ስለ ወንጌል ነው፡፡

በመንፈስ ቅዱስ የሚሆን እውነተኛ ጸሎት በግል ፍላጐት ላይ ያተኮረ የስጠኝና የአድርግልኝ ዝርዝር አይደለም፡፡ እውነተኛ ጸሎት በዋነኛነት ለሌሎች እንደ ራስ የሚማልድ ነው፡፡ ስናየው የቆየነውም መንፈሳዊ ውጊያ የመንግሥት ውጊያ እንጂ የግለሰብ መቆራቆስ አይደለም፡፡ ሰይጣን ሊያጠቃ የሚነሳው ግለሰቦችን ቢመስልም ጠላትነቱ ግን ግለሰብ ሳይሆን የመንግሥት ነው፡፡ እኛም መዋጋት ያለብን እንደ መንግሥት ነው፡፡ በጊዜው ከተከሰተው መከራ እኛ ነፃ ብንሆን እንኳ፣ መከራን ከሚቀበሉት ቅዱሳን ጋር በሥጋ እንዳለን ሆነን ልንማልድ ይገባናል፡፡

የአገራችን ሰዎች ሲተርቱ “ቤት ሲቃጠል፣ ላይ ያለው ሸረሪት፣ ታች ባለው አይስቅም» ይላሉ፡፡ ይህንን የሚሉት ሸረሪቶቹ በድር ስለ ተያያዙና ስለ ተሳሰሩ ታች ያለውን ያገኘው እሳት ላይ ያለውንም እንደሚያገኘው ለመግለፅ ነው፡፡ እኛም ከድር በሚበልጥ ሕይወት ተሳስረናልና የሌሎችን መከራ እንደ ራሳችን ቆጥረን ልንማልድ ይገባናል፡፡ በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ እነርሱና እኛ የሚባል



For more books www.amharicchristianbooks.com

ነገር የለምና፡፡ ለዚህም ነው፤ *“በዚህም ሃሳብ* (*መንፈሳዊ ውጊያ*) *ስለ ቅዱሳን ሁሉ እየለመናችሁ በመፅናት ሁሉ ትጉ”* 6፡18 የሚለው፡፡ «ስለ ቅዱሳን ሁሉ» ሲልም፣ አይሁድም፣ አሕዛብም ባርያም፣ ጨዋም ወ.ዘ.ተ . . . . ማለቱ ነው፤ ዛሬስ ለኛ ምን ይሆን?

ስለወንጌል እውነት በሮም እስር ቤት በግዞት ያለው ጳውሎስ ራሱን የሚጠራው መልዕክተኛ እያለ ነው፡፡ በእግዚአብሔር ፈቃድ የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያ (መልዕክተኛ ወይም አምባሳደር) እንደሆነ በመግቢያው ላይ አስቀድሞ ጽፎልናል (1፡1) ፡፡ ነገር ግን መልዕክተኝነቱ እንደ ዘመኑ የሮም አምባሳደሮች በአንገትና በእጅ ላይ በሚደረጉ የወርቅ ጌጣጌጦች ያሸበረቀ[336] ሳይሆን እንደ ወንጀለኛ የብረት ሰንሰለት የለበሰ አምባሳደር ነበር፡፡[337]

መልዕክተኛው በሚሰብከው ወንጌል ሰዎች ከኃጢያትና ከሰይጣን እሥራት እየተፈቱ ነው፡፡ እርሱ ግን በሰንሰለት ታስሯል፡፡ ልመናው ሰንሰለቱ እንዲበጠስ አይደለም፤ ሰዎች ከዘላለም እስራት ይፈቱ ዘንድ ወንጌልን በፍፁም ግልፅነትና ድፍረት እንዲናገር እንጂ፣ እርሱ እንዲፈታ ሳይሆን ቃሉ እንዲፈታ ይጸልዩለት ዘንድ በትህትና ይጠይቃል፡፡[338] ጳውሎስ የነበረበት ሥፍራና የከበበው ሁኔታ የፍርሃት ድባብ የሚጥል ነበር፡፡ የ የቄሣር ደህንነት ጠባቂዎች በአቅራቢያው አሉ፡፡ የተከሰሰው በሕግ አዋቂዎቹና በነገረ ፈጆቹ አይሁዳውያን ነው፡፡ ይግባኝ ያለውም ለቄሣር ነው፡፡ ከዚህም የተነሳ ምክንያት የሚፈልጉበት የተከፈቱ አይኖች በፊቱ ተደቅነዋል፡፡ በወቅቱ የኢየሱስን ጌትነት ማወጅ አገር እንደ መክዳት፣ የንጉሱን ሥልጣን እንደ መጋፋት ተቆጥሮ ሊያስገድል የሚችል ወንጀል ነበር፡፡

ስለዚህ በትህትና ለተደራሲያኑ የጸሎት ርዕስ ያቀርባል፡፡ ጥያቄዎቹ ሁለት መሠረታዊ ነገሮች ላይ የሚያጠነጥኑ ናቸው፣ አንደኛው «ግልፅነት» ሲሆን ሁለተኛው «ድፍረት» ነው፡፡ የወንጌልን ምሥጢር በግልፅ ለመናገር የሚያስፈልገው ከእግዚአብሔር ዘንድ የሚሰጥ ገላጭ ቃል ሲሆን፣ በሚያስፈራ ሁኔታና በሚያስፈራሩ ሰዎች ፊት ገልጦ ለመናገር የሚያስፈልገው ደግሞ ከጌታ ዘንድ የሆነ ድፍረት ነው፡፡ ዛሬም የምሥራቹን ቃል ለምንሰብክ ሁሉ እግዚአብሔር

---

[336] Markus Barth እንደጻፈው፣ ሠንሰለት የሚለው የግሪክ ቃል ባለጠጋ ሴቶችና የመንግስት ተወካይ አምባሳደሮች የላካቸውን መንግስት ክብርና ባለጠግነት ለማሳየት በአንገታቸው ከሚያጠልቁትና በእጃቸው ላይ ከሚያስሩት ጌጣ ጌጥ ጋር ተዛማጅነት እንዳለው ይገልፃል፡፡ Stott, John R. W.The Message of Ephesians: God’s new society 2nd ed. P. 287

[337] ሐዋ. ሥራ 26፡ 29 (አዲሱ መደበኛ ትርጉም)

[338] 2ጢሞ 2፡8-9



For more books www.amharicchristianbooks.com

ግልፅነትንና ድፍረትን ያብዛልን! አሜን!

ይህም መልዕክት የደረሳቸው ወገኖች እንደ ጸለዩለት፣ ጸሎታቸውም እንደ ተሰማና እንደ ተመለሰ እርግጠኛ መሆን የምንችለው ሉቃስ የሐዋርያት ሥራ ትረካውን ሲደመድም ስለ ጳውሎስ የሮም የግዞት ቆይታ ካሰፈረልን ዘገባ ነው፡፡

> *"ጳውሎስም በተከራየው ቤት ሁለት ዓመት ሙሉ ተቀመጠ፣ ወደ እርሱም የሚመጡትን ሁሉ ይቀበል ነበር፡፡ ማንም ሳይከለክለው የእግዚአብሔርን መንግሥት እየሰበከ ስለ ጌታ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ እጅግ ገልጦ ያስተምር ነበር፡፡"* ሐዋ 28፡ 30-31

## ስንብት

ጳውሎስ የፀሎት ጥያቄውን ካቀረበ በኋላ በቀጥታ የዘለቀው ወደ መጨረሻ ስንበት ነው (6፡ 21 – 24)፡፡ በስንብቱም በሥጋ ከእርሱ ርቀው በትንሿ እስያ ያሉት አማኞች ከመልዕክቱ በሻገር ያለበትን ዝርዝር ሁኔታ እንዲያውቁ ፈልጓል፡፡ ከእነርሱ ዘንድ በመጡ አገልጋዮች ስለ ሁኔታቸው ዝርዝር ነገር እንደ ሰማ አስቀድመን አንብበናል (1፡15; ቆላ. 1፡ 3-9)፡፡ አሁን ደግሞ በተራው ከእርሱ ዘንድ ወደ እነርሱ በሚልካቸው አገልጋዮች ስለእርሱ ሁኔታ እንዲረዱ በመናፈቅ ይፅፍላቸዋል፡፡ የእስር ቤት ሁኔታውን እንዲያውቁ የፈለገው መረጃው ከመረጃነት ባሻገር ልባቸውን እንደሚያፅናናው ያውቅ ስለ ነበር ነው፡፡ በዚህም ሐዋርያው በሥጋ ፊት ለፊት ባያውቁትም እንኳ፣ የሐዋርያዊ ተልዕኮው ተካፋይ የሆኑ ወገኖች ስለእርሱ ሁኔታ ያለ ምንም ሽፍንፍን እንዲያውቁ በማድረግ ግልፅነትንና ትይዩነትን ለማጐልበት ያላሰለሰ ጥረት እንደሚያደርግ እንረዳለን፡፡

ጳውሎስ ይህንንና ምናልባትም የቈላስይስን መልዕክት በአንድነት አስይዞ የላከው የተወደደ ወንድምና በጌታ የታመነ አገልጋይ መሆኑ በተመሰከረለት በቲኪቆስ እጅ ነው፡፡ ጸሐፊው ቲኪቆስን ለመግለጥ የተጠቀመባቸው ቃላት ትኩረት የሚሰቡ ናቸው፡፡ ቲኪቆስ ለጳውሎስ የተወደደ ወንድም፣ ለጌታ ደግሞ የታመነ አገልጋይ ነበር፡፡[339] የተወደደ ወንድም ሳይሆኑ የታመነ አገልጋይ መሆን አስቸጋሪ ነው፡፡ ስለዚህ እነዚህ ሁለት ባሕሪያት ሊነጣጠሉ የማይገባቸው የአንድ ሳንቲም ሁለት ገፅታዎች ናቸው፡፡

በመጨረሻም እንደ አጀማመሩ ሁሉ (1፡2) ከእግዚአብሔር አብና ከጌታ ከኢየሱስ

---

[339] ኤፌ. 6፡21-22; ቆላ. 4፡7-9



For more books www.amharicchristianbooks.com

ክርስቶስ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት የሚፈስ ሰላምና ፍቅር ከእምነት ጋር ለወንድሞች እንዲሆን ያለውን ልባዊ ምኞት ከገለፀ በኋላ፣ አንድ አስገራሚ የቡራኬ ቃል በመጻፍ መልዕክቱን ይደመድማል፡፡ ቃሉም *«ጌታችንን ኢየሱስ ክርስቶስን ባለመጥፋት ከሚወዱ ሁሉ ጋር ፀጋ ይሁን»* ኤፌ. 6፡24 የሚል ነው፡፡ ይህን ቃል አንዳንድ ትርጉሞች «በማይጠፋ ፍቅር ከሚወዱ» በማለት ተርጉመውታል፤ ነገር ግን ከመላ መልዕክቱ አንፃር ትኩረት ልንሰጠው የሚገባው «አለመጥፋት» (አፐታርዚያ) የሚለው የግሪክ ቃል ነው፡፡ ይህንን የግሪክ ቃል በሚገባ ለመረዳት ቃሉ በቀጥታ የሰፈረባቸውን የአዲስ ኪዳን ክፍሎች መመልከት ይጠቅማል፡፡[340] ጳውሎስ ራሱ በሮሜ 2፡7 ላይ ". . . በበጎ ሥራ በመጽናት ምስጋናንና ክብርን የማይጠፋንም ሕይወት ለሚፈልጉ የዘላለምን ሕይወት ይሰጣቸዋል . . . " ይላል፡፡ የተሰመረበት ቃል የግሪክ ፍቺው እንደ ኤፌ. 6፡24ቱ "አፐታርዚያ" የሚል ነው፡፡ በ2ኛ ጢሞ. 1፡10 ላይ ይህንኑ ቃል በድጋሚ እናገኛለን "እርሱ ሞትን ሽሯልና . . . ሕይወትንና አለመጥፋትን ወደ ብርሃን አውጥቷል" ይላል፡፡

ከዚህም በመነሳት ባለመጥፋት ወይም በማይጠፋ ፍቅር ክርስቶስን መውደድ ማለት፣ በመንፈስ ቅዱስ በሆነ የሕይወት ልምምድ እውነተኛውን የክርስቶስን ፍቅር ማወቅና፣ ለዚህ ፍቅር ተግባራዊ ምላሽ በመስጠት፣ በመከራ ሳይበገሩ አስፈላጊም ሆኖ ሲገኝ ለሞት ነፍስን እስከ መስጠት ድረስ መታመንን የሚያሳይ ነው፡፡ ይህም ጳውሎስ በሌሎች መልዕክቶቹ ውስጥ እንዳሰፈረው በክርስቶስ ኢየሱስ የተገለጠውን፣ የማይሞትና የማይጠፋ ሕይወት ያመለክታል፡፡ ይህም ሕይወት ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን በመነሳቱ ምክንያት ሁለተኛ በመወለድ የገባንበት ሕያው ተስፋ ያለው፣ የማይጠፋና እድፈት የሌለበት የማያልፍ ርስት ነው፡፡[341]

ጳውሎስ "አሜን" የሚለውን ቃል በዚህ መልዕክት ውስጥ ሁለት ጊዜ ተጠቅሟል፡፡ መጀመሪያ በማወቅ ላይ ያተኮረውን ከምዕራፍ 1 - 3 ያለውን ትምህርታዊ ክፍል ሲዘጋ "አሜን!" ብሎ ነበር (3፡21)፡፡ አሁን ደግሞ ተግባራዊ ኑሮ ላይ ያጠነጠነውን ሁለተኛ ክፍል ሲዘጋ "አሜን" ይላል፡፡ «አሜን!» ማለት ይሁን፣ ይደረግ፣ ይበል፣ ይስመር፣ የሚል የመስማማት ቃል ነው፡፡ ለእኛም ለትውልዳችንም ሁሉ በዚህ መልዕክት ውስጥ የተጻፈው የእግዚአብሔር ፈቃድ "አሜን!" ይሁንልን፡፡ ■

[340] ሮሜ 2፡7; 1ቆሮ፡ 15፡53; 2ጢሞ. 1፡10; ቲቶ 2፡7

[341] 1ጴጥ. 1፡3-5



For more books www.amharicchristianbooks.com

# ዋቢ መጽሐፍት/Bibiliography/


1. Aristotle's theory of slavery, Book VII of the *Nicomachean Ethics*
2. A. S. Hornby; Oxford Advanced Learner's Dictionary of Current Englishe; Oxford University Press, 1974.
3. Bible Society of Ethiopia, ቀለል ባለ አማርኛ የተተረጎመ መጽሐፍ ቅዱስ፣ 1988.
4. Craig A. Evans, Stanley E. Porter; Dictionary of New Testament background; 2000.
5. David, Jonaathan, Apostolic Strategies Affecting Nations.
6. Eckhardt, John, Moving in the Apostolic, 1999.
7. F. F. Bruce in the Epistles to the Colossians, To Philemon, and To the Ephesians (Grand Rapids, William B. Eerdmans Publishing Company, 1984).
8. Gaebelein Frank Ely, The Expository's Bible Commentary Vol. 11; Zondervan Publishing House, 1978.
9. Gerald F. Hawthorne, Ralph P. Martin, Daniel G. Reid; Dictionary of Paul and his Letters; 1993.
10. International Bible Society; አዲሱ መደበኛ ትርጉም; 2001.
11. International Bible Society; ሕያው ቃል የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም፤ 1985.
12. John F. Walvoord, Roy B. Zuck; the Bible Knowledge Commentary SPPublications, 1983
13. Keener, C. S. (1993). *The IVP Bible background commentary: New Testament.* Inter Varsity Press.
14. Leslau, Wolf. English-Amharic Context Dictionary; 1972.




For more books www.amharicchristianbooks.com

15. Lewis, C. S. Mere Christianity; 1952 New York.
16. Lincoln, Andrew T. World Biblical Commentary Vol. 42 Ephesians, Thomas Nelson Publishers Inc. 1990.
17. Nee, Watchman; Sit, Walk, Stand; Tyndal House © 1977.
18. መሠረት ስብሃት ለአብ፣ ሥላሴ በተዋህዶ፣ መካነ የሱስ ሴሚናሪ 1996.
19. Stern, David H. Jewish New Testament Commnentary; 1989.
20. Sttot, John R W; the Messege of Ephesians; Inter-varsity Press 1979.
21. *The Holy Bible in Amharic.* Bible Society; Reprinted from the Edition of 1886.
22. United Bible Societies; የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም; 1962.
23. Wagner, C. Peter, Apostles of the City, 2000
24. Walter C. Kaiser Jr. Peter H. Davids, F.F. Bruce, Manfred T. Brache; Hared sayings of the bible; Inter Varsity Press 1996.
25. William Hendriksen, Exposition of Ephesians (Grand Rapids: Baker Book House, 1967).
26. William Whiston, Paul L. Maier; the New Complete Work of Josephus; Kregel.
27. William Gurnall, The Christian in Complete Armour, First published in 3 Volums during 1662- 65 and republished by Rev. J.C Ryle in 1995 by the Baner of Truth Trust.
28. W.L Westermann; The slave system of Greek and Roman Antiquity 1955.
29. Wuest, Kenneth S. Ephesians and Colossians in the Greek New Testament, Eerdmans Publishing Co. 1953.



For more books www.amharicchristianbooks.com